# የትግራይ ጦርነት

## በዝሆኖች ፍልሚያ የተረገጠው ሳር








ዶር. ዮሃንስ አበራ

# የትግራይ ጦርነት

## በዝሆኖች ፍልሚያ የተረገጠው ሳር

ዶር. ዮሃንስ አበራ

አዲስ አበባ 2016

# መታሰቢያነቱ

የልሂቃንን ህልም እውን ለማድረግ በስብከታቸው ተታላችሁ በማይመለከታችሁ ጉዳይ ስራችሁን፤ ትዳራችሁን፤ ልጆቻችሁን፤ ወላጆቻችሁን ትታችሁ ከማታውቋችውና ካልተጣላችኋቸው ሰዎች በማታውቁት ጦር ሜዳ ስትዋጉ ለወደቃችሁትና ለተጎዳችሁት ሁሉ!

**በዚህ መጽሃፍ ለተካተቱት ዜና ሪፖርቶች አስተዋጻኦ ያደረጉ**
**የአለም የዜና ምንጮችና ማሰራጫዎች በሪፖርቶች ብዛት የደረጃ ሰንጠረዥ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሮይተርስ | 12 | ቮይስ ኦፍ አሜሪካ | 23 | አል ዓራቢያ ኢንግሊሽ |
| 2 | አልጀዚራ እንግሊዝኛ | 13 | አዲስ ስታንዳርድ | 24 | ኢትዮጵያን ነውስ |
| 3 | ኢ.ኢ.ፒኤ.-ሆርን | 14 | አዣንስ ፍራንስ-ፕሬስ | 25 | ፋና ብሮድካስቲንግ. |
| 4 | ቢቢሲ ኒውስ | 15 | ኤቢሲ ኒውስ | 26 | ቲ.አር.ቲ.ወርልድ |
| 5 | አሶሴየትድ ፕሬስ | 16 | ትግሃት | 27 | ቤሊንግ ካት |
| 6 | ፍራንስ 24 | 17 | ብሉምበርግ | 28 | ኢትዮጵያ ኦብዘርቨር |
| 7 | ዘ ጋርድያን | 18 | ሲ.ኤን.ኤን. | 29 | ኦቨርት ዲፈንስ |
| 8 | ኤሪትርያ ሃብ | 19 | ስካይ ኒውስ | 30 | ዘ ሪፖርተር ኢትዮጵያ |
| 9 | ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ | 20 | ሱዳን ትሪቡን | 31 | ዋሽንግተን ፖስት |
| 10 | ዶይቸ ቬለ | 21 | ያሁ ኒውስ | 32 | ቫይስ ኒውስ |
| 11 | ዴይሊ ቴሌግራፍ | 22 | አፍሪካ ኒውስ | 33 | ሺንዋ |

| የይዘት ሰንጠረዥ | | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ፩ | ትግራይ በኢትዮጵያ፡- የዘመናት ቅራኔ | 1 |
| ምዕራፍ ፪ | በትግራይ የዝሆኖች ፍልሚያ ቀደምት ታሪክ | 23 |
| ምዕራፍ ፫ | የወያኔ አመጽ፤ የጎራ ግብግብ፤ የህወሓት ትግልና ድል | 46 |
| ምዕራፍ ፬ | የትግራይ ጦርነት መንስኤዎች | 63 |
| ምዕራፍ ፭ | የጦርነቱ ተዋናዮች፤ ደጋፊዎችና አጋጋዮች | 86 |
| ምዕራፍ ፮ | የጦርነቱ ዋዜማና የመጀመሪያው ምእራፍ | 113 |
| ምዕራፍ ፯ | ጅምላ ግድያ በትግራይ ጦርነት | 130 |
| ምዕራፍ ፰ | ማህበረ-ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጥፋቶች | 153 |
| ምዕራፍ ፱ | ሁለተኛው የትግራይ ወረራና የፕሪቶሪያው ስምምነት | 175 |
| ምዕራፍ ፲ | የድህረ-ፕሪቶሪያ የሃይል አሰላለፍ ለውጥ | 201 |
| ምዕራፍ ፲፩ | ኮምፓሱ የጠፋበት የትግራይ ድህረ-ጦርነት ፖለቲካ | 215 |

# ምዕራፍ ፩

# ትግራይ በኢትዮጵያ፡- የዘመናት ቅራኔ

## 1.1. መግቢያ

ነጋድራስ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ "አጼ ሚኒሊክ በአንድ ነገር መወቀስ አለባቸው፤ የትግራይን ህዝብ እንደ ራሳቸው ህዝብ አልቆጠሩትም" ያሉት ከምን ተነስተው ነበር? ከአጼ ዮሃንስ ህልፈት በኋላ የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት እርስ በርስና ከሸዋ ገዢዎች ጋር በስልጣን ፉክክር ተጠምደው ለግማሽ ምእተ አመት ህዝቡን እርስ በርስ ሲያፋጁት፤ እርሻውን ባለማረሱና ድርቅና አንበጣ ታክሎበትም በረሃብና ቸነፈር ሲሰቃይ አጼ ሚኒሊክ የሚቀናቀኗቸው የትግራይ መሳፍንት ይዳከሙልኛል በሚል አጭር እይታ ሊያገኙ ይችሉ የነበሩትን የትግራይን ህዝብ ፍቅር ማጣቸውን አስመልክቶ የተነገረ ቁጭት ነው፡፡

በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶቻቸው የትግራዩ አይነት ሁኔታ ቢከሰት አጼ ሚኒሊክና የሸዋ ገዢ መደብ ተመሳሳይ ዝምታን ይመርጡ ነበር ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ሊሆን የሚችለው የሚፋለም ዝሆን በሌለበት የሚረገጥ ሳር አይኖርም ነው፡፡ "አሳውን ለመግደል ባህሩን ማንጠፍ" ብሎ መሳይ መኮንን በኢሳት ያወጀው ፍጅት ለአሁኑ ዘመን ይሁን እንጂ በአጼ ሚኒሊክም በአጼ ሃይለሰላሴም ዘመናት የትግራይን "አሳነባሪዎች" ለማጥመድ የጉልበታቸው ዋና ምንጭ የሆነውን የድሃ ገበሬ "ባህር" በረሃብና በወረርሺኝ እንዲደርቅ መተው ያልተጻፈ ወታደራዊ ፖሊሲ ኖሮ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም፡፡ ለዚህ ህያው ማረጋገጫ የሚሆነው ከአጼ ሚኒሊክ በኋላም ወረራዎች፤ ያስተዳደር በደሎች፤ በመከራ ጊዜ ችላ መባሎች እየተደጋገሙ ለምእተ አመት መቀጠላቸው ነው፡፡

ከአጭር ጊዜው የሶማሊያ ወረራ ውጪ የኢትዮጵያ የጦር ሃይል የተገነባውና የውጊያ ልምድም ያካበተው ከውጭና በውስጥ በትግራይ ላይ በተደረጉ የወረራና የመከላከል ጦርነቶች ነው፡፡ በአኹሱም ዙሪያ የሰፈረው ከስድስት ሚልዮን በላይ የሆነ ህዝብ "ሶስት ሺ አመታት የኖረ የኢትዮጵያ ስረ-መሰረት ነው" እየተባለ ለመላ አለም በተነገርበት አንደበት "ከሰይጣን የባሰ በመሆኑ ከታሪክ ሳይቀር መፋቅ አለበት" የሚባልበት እንቆቅልሽ ለፈቺው ግራ ነው፡፡ ማን ከማን ታሪክ

ማንን ይፍቃል የሚለው ደግሞ የሚልዮን ዶላር ጥያቄ ነው! ከትግራይ ውጪ ባለው ቀሪው ኢትዮጵያ በትግራይ ህዝብ ላይ ያለው በጎ ያልሆነ አመለካከት ስር የሰደደ ከመሆኑ የተነሳ አሁን የበረደ የሚመስለው እሳት ተዳፍኖ ይሆናል እንጂ አልጠፋም ብሎ መገመት ይህን ያህል ከፍ ያለ የፖለቲካ ሊቅነት የሚሻ አይደለም፡፡ ትግራይን ከቀሩት የኢትዮጵያ ግዛቶች በእጅጉ የሚለዩ በርካታ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲጋራቸውና ለመፍትሄአቸውም አብሮ እንዲተጋ የሚጠበቅ ነበረ፤ ያፈጠጠው እውነታ ግን ይህ አይደለም፡፡

ከመተሳሰብና ከመደጋገፍ ይልቅ የትግራይ ህዝብ ወገኔ ነው ብሎ ከሚተማመንበት የኢትዮጵያ ህዝብ ሲሰነዘርበት የኖረው ስድብና ውርደት፤ በረሃብም ሆነ በጥይት እንዲጠፋ መመኘትና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይህንን ምኞት መተግብር ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ የሚሰቃይበት የድህነት አዘቅት ራሱ አርግዞ አምጦ የወለደው ሳይሆን ከአብራኩ በወጡ የስልጣን ሱስና የሃብት ስስት ያሳበዳቸው ልጆቹና ከነሱ አንጻር ተሰለፈው ለአገሪቱ ዙፋን ከሚገዳደሩት ኢትዮጵያ-በቀል አረሞች በኩል በሚወርድበት በደል ነው፡፡ ትግራይ የሺዎች አመታት የስልጣኔ ቆይታ ያስከተለው የመሬት መጎዳት፤ የእጸዋት መመናመንና መጥፋት፤ የምድራችን የበርሃማነት መስፋፋት በትግራይ በኩል ሰፊ ግንባር የከፈተ በመሆኑና አውዳሚ የሆነ ድርቅ በአጭር በአጭር የሚመላለስበት መሆኑ፤ ለምእተ አመታት የኢትዮጵያ ጠላቶች መግቢያ በር በትግራይ በኩል በመሆኑ የጦር አውድማ ሆኖ ያፈራትን ምርት፤ ያጠራቀማትን ጥሪት ሲገብር መኖሩ፤ መሪ አይውጣልህ ተብሎ የተረገመ በሚመስል ሁኔታ የትግራይ ህዝብ የሚጠቀሙበት እንጂ የሚጠቅሙት ፖለቲከኞችና አስተዳዳሪዎች ማጣቱ!

እንዳለመታደል ሆኖ ይህ ሁሉ በትግራይ ህዝብ ላይ የደረሰውና እየደረሰ ያለው መከራ የኢትዮጵያን ህዝብ አንጀት በልቶ ለድጋፍ የሚጋብዘው አልሆነም፡፡ በተቃራኒው "አለትህን ጋጥ፤ ቾክ አትገዛም፤ ባንተ ምክንያት ርሃብተኞች ተባልን፤ ብትገነጠል ግልግል ነው፤ የሃገር ፍቅር የለህም፤ ኢትዮጵያን ልታፈርሳት ነው፤ ዘረኛ ነህ፤ ካንሰር ነህ፤ ጅብ ነህ፤ ሰይጣን ነህ፤ ጸጉረ ልውጥ ነህ፤ እንደ ታስማኒያ አንድ ሰው እስከትቀር መጥፋት አለብህ" እየተባለ ከሌላ ፕላኔት እንደመጣ ባእድ ፍጡር ተቆጥሮ በደቦ ተቀጥቅጧል። ፍቅር ሲደጋገም "ለምን?" ብሎ መጠየቅ አያስፈልግም፡፡ ጸላኤ ሰናይ ካልሆነ በስተቀር ፍቅርን በችሎት አይጠይቅም፡፡

ጸብ ሲደጋገምና ዘመናት አልሽረው ሲሉ ግን ለአምላክ፤ ለህዝብና ለህሊና ፍርድ ማቅረብ የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ ከትናንት ወዲያ ነበረ፤ ትናንት ነበረ፤ ዛሬም አለ፤ ነገም ላለመቀጠሉ ዋስትና የለም፡፡ ባለፉት ዘመናት ከነበሩበት መከራዎች ልቆ የአሁኑ ጦርነት ለመግለጽ ቃላት በሚያጥሩበት ሁኔታ የትግራይን ህዝብ ስላወደመው ትግራይ ከቀሪው ኢትዮጵያ ጋር ስላላት ዝምድና ምንነቱን፤ ለምንነቱንና ወዴትነቱን አክርሮ መጠየቅ የተጀመረበት አጋጣሚ ተፈጥሯል፡፡

ከዚህ በፊት ትግራይ ላይ ከተፈጸሙት ወረራዎችና ውድመቶች የአሁኑን ጦርነት ልዩ የሚያደርገው ሚልዮን ህዝብ ያለቀበት፤ ሚልዮኖች የተሰደዱበት፤ መቶ ሺዎች የተደፈሩበት፤ በዚህ ዘመን ይተካል የማይባል የንብረትና መሰረተ ልማት ዝርፊያና ውድመት የደረሰበት በመሆኑ ብቻ አይደለም፤ የሃገሪቱ ህጎች ሁሉ ፈራርሰው ክልል ክልልን እንዲወር መፈቀዱና የሃገር ሉአላዊነትን የሚጠብቁ እሴቶች ሁሉ ተሽረው ወገን ላይ የባእድ ጦር መታዘዙም ጭምር እንጂ፡፡ በዚህ ከፍተኛ የአገር ከህደት ወንጀል የኢትዮጵያ ህዝብም እንደ ህዝብ አውቆም ይሁን ሳያውቅ፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እጁን ሰዶበታል፡፡ እዚህ ላይ በርካታ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች መጠየቅ ተገቢ ነው፡- ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ ይህን ያህል የከፋ ልዩነት ሳይኖረው የትግራይን ህዝብ “ጥቁር በግ” አድርጎ የሚያይበት አይኑ የተሰራው ከምንድነው? ከመቼስ ጅምሮ ነው? ትግራይን ለማጥቃት ሲሆን ጨርቄን ማቄን ሳይል በፍጥነት የሚሰለፍበት ሚስጥሩስ ምንድነው? የማይወዳቸው፤ የማያከብራቸው፤ የማያዳምጣቸው መሪዎቹም ቢሆኑ “ወደ ትግራይ ዝመት” ያሉት ቀን ገዥ-አናዛዦቹ መሆናቸው ተረስቶ ጀግኖቹ ሆነው የሚገኙበትና የሚወደሱብትስ እንቆቅልሽ?

ቀደምት የሰሩትን ጥፋት በመሰወር፤ አመቺና ተቃራኒ በሆነ ትርክት የአሁኑንና መጪውን ትውልድ በማደናገር “ትግራይ ኢትዮጵያን ወደብ አሳጣች” የሚለው “የአባየን ለእማየ” የሆነ የተንጋደደ ውንጀላ፤ “መለስ ባንዴራውን ጨርቅ ነው አለው” በማለት የማንም አገር ባንዴራ ከጨርቅ እንዳልተሰራ ሁሉ የህዝብን ስሜት የማደፍረስ መናኛ ፖለቲካ፤ ለዘመናት ሲሰራበት የኖረውን ወገናዊነት ወያኔ ያመጣው አዲስ ነገር ይመስል “መከላከያው የኢትዮጵያ ሳይሆን የትግራይ ነው” የሚለው የአመጽ ማነሳሻ፤ “ሲሾም ያልበላ...” እያለ ስርቆትን የሚቀድሰውና የሚያወድሰው የባህል ባለቤት ሙስናና የዘመድ ስራ በተጋሩ የተጀመረ አስመስሎ ህዝብን ለጥቃት ማጋለጥ የትግራይና የቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ

ግንኙነት ችግር በዘላቂነት ሊፈታ አይችልም፡፡ እነዚህ የእለት እርካታ የሚያስገኙ፤ ከጓሮ የማይርቁ ደካማ ትርክቶች ውለው አድረው ትርፋቸው የኃራ ኪሳራ ነው፡፡ በጥላቻና በውሸት ትርክት የተገነባ ህንጻ የባቢሎን ግንብ ነው፡፡


ቀደም ብለው የተነሱትን ጥያቄዎች በተሟላ ሁኔታ መመለስ ባይቻልም የትግራይና የቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ግንኙነት ከየት ተነስቶ እዚህ እንደደረሰ በመተረክ የችግሮችን ምንጮች ማወቅ ለሚፈልጉና አውቀውም ችግሮቹን ለመፍታት ለሚጥሩ ቅን-ልቦች ብርሃን መስጠት ይቻላል የሚል እምነት አለ፡፡ የትግራይ ህዝብ የአክሱምንና የቀይ ባህርን ታሪክ፤ የአድዋን የድል ምድር ባለቤትነትን ከእጁ ፈልቅቆ በመውሰድና የታሪኩ ባለቤትንም በአካል በማጥፋት የሚከናነቡት በቅሚያ የተገኘ የታሪክ ጃኖ እራቁትነትን የባሰ ያጋልጣል እንጂ የሚያስገኘው ግርማ ሞገስ የለም፤ የቱሪስቶችን ገንዘብ ከማፈስ በስተቀር፡፡

## 1.2. አኹሱም ወደ አገው፡- "የዱላ ቅብብሎሹ" ጅማሮ

የትግራይን አመጣጥና ምንነት፤ ከኢትዮጵያ ጋር ያገናኛትን የታሪክ ሂደት ጠንቅቆ ለመገንዘብ ትረካውን ከአኹሱም መጀመር የግድ ይላል፡፡ ታላቁ የአኹሱም ስልጣኔ ቀደም ካለው የዳአማት የመንግስት ጅማሮ ቀጥሎ እስከ ቀይ ባህር ዙሪያ ክልል የተሰንራፋ አጼያዊ መንግስት ነበር፡፡ በመጀመሪያው መቶ ዓ.ም የተከሰተው የአኹሱም ስልጣኔ ለአንድ ሺህ አመታት ያህል ገናና ሆኖ ቆይቷል፡፡ አኹሱም ከፋርስ፣ ከሮምና ከቻይና ጎን በጥንቶቹ የዓለም አራት ታላላቅ ኃያላን መንግስታት ምድብ ውስጥ ትገኝ ነበር፡፡ የአኹሱም መንግስት በቀይ ባህር ተፋሰስ፤ በሜዲትራኒያን ባህር ተፋሰስ፣ በደቡብ አረቢያ፤ እስከ ህንድና ቻይና ድረስ ገበያዎችን ያገናኙ አለም አቀፍ የንግድ አውታሮች ማዕከል ነበረ፡፡ የአኹሱም የላቀ ዓለም አቀፍ ንግድ የወርቅና የብር ሳንቲሞችንም ይጠቀም ነበር፣ በቀይ ባህርና በዙሪያው ለአንድ ሺህ አመታት የሰፈነው በአኹሱም የሚመራ የንግድና የፖለቲካ ዝምድና በሸቀጥና በወርቅ ሳንቲሞች ልውውጥ ብቻ ተወስኖ የቀረ አልነበረም፡፡ ሰፊ የሆነ የባህል መወራረስ ዳብሮ አኹሱምን ያካተተ አንድ የባህል ክልል ሆኖ እንደነበር ሙንሮ ሃይ ይተርካል፡፡

አኹሱም አሁን ካለችበትና በኋላኛው ዘመን አቢሲንያ/ኢትዮጵያ ከተባለው ኩታገጠም ደቡባዊ ክፈለ አህጉር ጋር ከዱር አራዊት ውጤቶች ግዢና ድንበር አካባቢ ከነበረው የክርስትና ሃይማኖት ስርጭት ያለፈ ግንኙነት አልነበራትም፡፡

በአኹሱም የመጀመሪያዎቹ ምእት አመታት ከቀሪው የቀይ ባህር ክልል ጋር የምትጋራው ሃይማኖት “ባእድ አምልኮ” የሚባለው ስለነበረ የሃይማኖት ልዩነትን መሰረት ያደረገ የውስጥ ውጥረት አልነበረም፡፡ አኹሱም ክርስትናን ከተቀበለች በኋላ ግን ከራሷ አካባቢ ርቃ እስከ ሂምያር (የመን) ድረስ በመሄድ ሃይማኖቱን ማስፋፋት ስለሞከረች ውጥረቶችና ግጭቶች መፈጠር ጀምረው ነበር፡፡




የአኹሱም ሃያልነት ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረበት ዘመን እስልምና ሃይማኖት በቀይ ባህር ዙሪያ እየተስፋፋ ነበር፡፡ ምንም እንኳ አኹሱም ለእስልምና ሃይማኖት መወለድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ብታደርግም፤ ነብዩ መሃመድም አኹሱምን “ካልነካቻችሁ አትንኳት” በማለት አደራ ቢሉም አኹሱም እንደ ክርስቲያን መንግስትና ህብረተሰብ ከአረብያ ተነስቶ በቀይ ባህር ክልል ወስጥ በፍጥነት ሲስፋፋ ከነበረው የእስልምና ሃይማኖት ጋር ተመሳስላ በቀይ ባህር የባህል ከልል አባልነቷን መቀጠል አልቻለችም፡፡ የቀይ ባህር ባህልና የእስልምና ሃይማኖት በተገጣጣሙበት የክልሉ አዲስ ሁኔታ አኹሱም በባህል ቀይ ባህር በሃይማኖት ክርስትያን ሆና የህብረቱ አባል ሆና መቀጠል አይቻላትም ነበር፡፡

ስለዚህ አኹሱም ለዘላለም ስቃይ የዳረጋትን ሁለት ባላ ለመርገጥ ተገዳለች፡- በባህል ወደ ሰሜን፤ በሃይማኖት ወደ ደቡብ! አኹሱምን ከደቡብ ጋር ያገናኘው የሃይማኖት ገመድ የባህል ውህደትን የማምጣት አቅም አልነበረውም፡፡ ለዚህ ምክንያት ሊሆን የቻለው የአክሱማዊ ስልጣኔ ወራሾች የበላይነት ስሜት የወለደው መሽካከር ነው፡፡

በጊዜ ሂደት አኹሱም ከቀይ ባህር መነጠሏን ተከትሎ የመጣባት ችግር የውስጥ ኢኮኖሚዋ መድቀቅ፤ የንግስት ዮዲት ጥፋትና የቤጃ ጎሳዎች ስርገትና ጥቃት ነበር፡፡ አኹሱም አቅጣጫ መጠቆሚያ ሳይኖራት ባህር ላይ እንደምትንሳፈፍ ጀልባ ሆነች፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች ነበር አኹሱም በደቡብ ድንበሯ ኩታ-ገጠም በነበረውና ከአኹሱም ክርስትናን በተቀበለው የአገው ህብረተሰብና መንግስት የተጠለፈችው፡፡ የአኹሱምን መዳከም ተከትሎ የተከሰተው አኹሱም ፊቷን ወደ ደቡብ ያዞረችበት ታሪካዊ ሂደት ተወልዳ ካደገችበት የቀይ ባህር ዙሪያ የባህል አውድ ነጥሎ ከማታውቀው ሌላ የባህል ከልል ጋር ስላገናኛት የባህል አለመገጣጠም ፈጥሮ በባእድነት እንዳስፈረጃት መገመት አይዳግትም፡፡ ከዚህ የተነሳ አክሱማዊት ትግራይና ቀሪው አቢሲንያ/ ኢትዮጵያ የኖሩት ውሃና ወተት ሳይሆን ዉሃና ዘይት ሆነው ነው፡፡

ይህ ያልተመቻቸ መገጣጠም የነበረበትን የባህል ሰፊ ክፍተት በሃይማኖት ስስ ሽፋን ማልበስ ቢቻልም ልዩነቱን አዳፈነው እንጂ አላጠፋውም፡፡ የቅርቡ የትግራይ ጦርነት ያረጋገጠውም ይህንኑን ሃቅ ነው፡፡ የሃይማኖት አንድነት በትግራይ ህዝብ ላይ ግፍ ከመሰራት ሊያግድ የሚችል አቅምም ፍላጎትም አልነበረውም፡፡ ሃይማኖቱ ለሁለት የተገመሰውም ማሰሪያ ገመዱ በጣም ቀጭንና የነተብ በመኖሩ ነው፡፡ አኹሱም እስካሁን የዘለቀውንና አለመግባባትና ግጭት የወረሰውን ከአቢሲንያ-ኢትዮጵያ ጋር ያደረገችው ውህደት የጀመረው ከጎረቤት የአገው ህብረተሰብ ጋር ነው፡፡ ዘአግዌ የሚባል አዲስ ስርወ መንግስት የጀመረው የላስታ-አገው መንግስት የአኹሱምን ማእከልነት ወደ ላስታ አዛወረ፡፡

አኹሱም ወደ አገው ያደረገችው ሽግግር ስምንት መቶ አመታት የፈጀ "የዱላ ቅብብሎሽን" አስጀምሯል፡- ከላስታ ወደ ወሎ፤ ከዛ ወደ ጎንደር፤ ቀጥሎ ወደ ሸዋ፡፡ ትግራይ ወደ ደቡብ፤ ምእራብና ምስራቅ በተደረገው መስፋፋት እጇን አላስገባችም፡፡ ከዚህም የተነሳ በነዚህ አዲስ የተካተቱ ሰፋፊ የሃጼ ግዛቶች ውስጥ

ምንነቷ አይታወቅም ነበር፡፡ ስለትግራይ የሚያውቁት ነገር ቢኖር ወደ ግዛቶቻቸው ባካተቷቸው ገዢዎች የተዛባ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ እነዚህ በአጼ ሚኒሊክ ዘመን ወደ አቢሲንያ-ኢትዮጵያ የተጠቃለሉት የምእራብ፤ የምስራቅና የደቡብ ግዛቶች ከትግራይ ጋር የተዋወቁት ከመቶ አመት የማእከላዊ መንግስት ጭቆናና የአድልዎ አገዛዝ አውጥቶ የራሳቸውን እድል በራሳቸው እንዲወስኑ የከፍተኛ መስዋእትነት ውጤት የሆነውን የራስ አስተዳደር ያቀዳጃቸው ትግል የተካሄደው እጅግ ከራቀው ትግራይ ውስጥ ስለነበር ነው፡፡ ሆኖም ይህ የሺዎች ደም ተገብሮበት የተገኘው የታላቅ ህዝብ የነጻነት ስጦታ ከጠቃሚዎቹ ለትግራይ የተሰጥው ምላሽ ሺ-ኪሎሜትር ተጉዞ ትግራይን ማጥፋት ሆነ፡፡ ለዘመናትና ለትውልዶች ትግራይን በአእምሯቸው የቀረጿት “የገዢየ ጠላት ናትና ጠላቴ ናት” የሚል በማያውቁትና ባልነካቸው ብቻ ሳይሆን ሞቶ ደህይቶ ነጻ ባወጣቸው ህዝብ ላይ ባደረ የተውሶ ጥላቻ ነው፡፡ አንድ ህዝብ ታላቅ ህዝብ ሊሆን የሚችለው ራሱን ችሎ ማሰብ ሲጅምር ብቻ ነው፡፡

## 1.3. ከአክሱማዊነት ወደ ትግራዋይነት

በዚህ “የዱላ ቅብብሎሽ” ሂደት አኹሱም በአኹሱምነቷ አልዘለቀችም፡፡ አኹሱም አንድ ወጥ ባልሆነና በየዘመኑ ስማቸው፤ መጠናቸውና ድንበራቸው የሚለዋወጥ የአስተዳደር ክፍልፋዮች ያሉት ትግሬ/ትግራይ በሚል የሚታወቅ የግዛት ክልል ተተከታለች፡፡ ለውጡ አዝጋሚ ሂደት ከመኖሩ የተነሳ አኹሱም ከመባል ትግሬ/ትግራይ ተብላ መጠራት የጀመረችው በየትኛው ዘመን እንደሆነ፤ ለውጡን ማን እንዳደረገውና በምን ምክንያት እንደተደረገ ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ የሚነገር ነገር ቢኖር ትግራይና ተጋሩ የአኹሱምና የአክሱማውያን ቀጣይ ትውልድ እንደሆኑ ነው፡፡ ሙንሮ ሄይ ተጋሩ እንደ ህዝብ ተከስተው መኖር የጀመሩበት ዘመን ከአኹሱም በፊት ወደነበረው 2000 አመተ አለም ይመልሰዋል፡፡ ኡሎንዶርፍ ግን የአሁኑ ዘመን ተጋሩ የጥንታዊት አኹሱም ወራሾች ናቸው ይላል፡፡

እርግጥ ነው፤ የአኹሱም መንግስት ማእከል የነበረችው አኹሱም ከተማ አሁን በካርታ ላይ ባለችውና ከ95 ከመቶ በላይ ትግርኛ ተናጋሪ ህዝብ ካለባት የትግራይ ክልል ውስጥ የምትገኝ መሆኗ ተጨባጭ ማረጋገጫ ሊሆን ይችላል፡፡ አኹሱም ከውድቀቷ በፊት የነበራትን ሰፊ ግዛት ይዛ አልቀጠለችም፡፡

አኹሱም/ትግራይ ይዛ የቀረችው የአሁኑ ትግራይና የኤሪትርያ ደጋማ ቦታዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ትግራይ እስከ አጼ ዮሃንስ ንግስና ድረስ የውስጥ ሃያላን የሚቀሟሟት ግን አቅም ያልተለያት ነበረች፡፡ ኩታ-ገጠም በሆኑት መስፍናዊ ግዛቶች ላይም የበላይነትን ታንጸባርቅ ነበር፡- በራስ ሚካኤልና በራስ ወልደስላሴ፡፡ ነገር ግን እነዚህ የውጪው አለም በአድናቆት የሚያነሳቸው በአገር ውስጥም  ሞገስ ያተረፉት ርእሳነ-መሳፍንት በማንነታቸው እንደባዳ ይታዩ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል፡፡

በስያሜ ደረጃ አክሱም ወደ ትግራይ ያደረገቺው ሽግግር በተመለከተ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ የአሁኗ ትግራይ በዘውዳዊው ስርአት ዘመናት "ትግሬ ጠቅላይ ግዛት" የሚል ስያሜ ነበራት፡፡ ይህ ስያሜ "ትግራይ" ወደሚል የተቀየረው በህዝብ ድምጽ አይደለም በመንግስት አዋጅም አይደለም፡፡ የኢትዮጵያው ወታደራዊ መንግስት ስልጣን ለመያዝ ዝግጅት በሚያደርግበት የለውጥ ነውጥ ጊዜ በግላቸው የተሰባሰቡ ሰዎች "ትግሬ" የሚለውን ስያሜ "ትግራይ" ወደሚል እንዲቀይር ደርግን ወጥረው ያዙት፡፡ ተቀባይነት ለማግኘት ሲጓጓ የነበረው ደርግ ጥያቄውን ተቀብሎ ቅያሬው በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት እንዲተገበር ፈቀደ፡፡ ይህ የስም ለውጥ የማን ፍላጎት ነው? የፊተኛው ስምስ ምን ችግር ነበረበት? እነዚህ ጥያቄዎች ቀላል ጥያቄዎች አልነበሩም፡፡ ለህዝብ ወይይት ሳይቀርቡና መልስ ሳይገኙ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የፖለቲካ ማእበል ተነሳ በትግራይም የህወሓት የትጥቅ ትግል ተጀመረ፡፡ የህይወት ዋስትና ባልነበረበት ዘመን ስለስያሜ ለውጥ ጥያቄ ማንሳት ቅንጦት ሆኖ ቀረ፡፡

የስያሜው ለውጥ ከህወሓት ምስረታ ጋር የተያያዘና የአዲሲቱን የፖለቲካ ድርጅት ማህበራዊ መሰረት የሚጠቁም ነበር፡፡ በዛ የቀወሰ ዘመን በቀረበለት ጀልባ ተሳፍሮ ወደሞቀበት መንሳፈፍ እንጂ ቆም ብሎ የሚታሰብበት ጊዜ ስላልነበረ በህወሓት የትጥቅ ትግል የመጀመሪያዎቹ አመታት የታየው መፈረካከስ፤ በደርግ ጊዜ ትግራይ ውስጥ የነበረው ሁለት እርስ በርሱ የሚጠፋፋ የፖለቲካ ጎራ፤ በህወሓት የሰላሳ አመታት የአስተዳደር ዘመንና አሁንም ቢሆን ውስጥ ለውስጥ እየጋመ ነገር ግን በይፋ የማይነገረው "አካባቢያዊነት" የፈጠረው ችግር ነው፡፡ "አካባቢያዊነት" ለ"አውራጃዊነት" የወጣለት የማለሳለሻ ቃል ነው፡፡ "በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አያገኝም"፡፡ የእንደርታ ፓርቲ፤ የተምቤን ፓርቲ፤ የራያ ፓርቲ እየተባለ ብቅ ጥልቅ የሚለው የትግራይ የተቃውሞ ፖለቲካ

ብልጽግና ህወሓትን ለማዳከም እየተጠቀመበት ነው ቢባልም ራሱ የፈጠረው ልዩነት አይደለም፤ መፍትሄ ያጣውን ችግር በእጁ አስገባው እንጂ፡፡ ችግሩ ይፋ ወጥቶ፤ ህዝብ ተወያይቶበት፤ የሚወቀስም ተወቅሶ፤ የሚቀጣም ተቀጥቶ ያበጠው ተንፍሶ መህትሄ እንዳያገኝ ከጅምሩ ጀምሮ ህወሓት ይህን የኖረ የዘመናት ችግር "ባንዳ፤ ከፋፋይ፤ የህዝብ ጠላት" በሚሉ አዋራጅ ቅጽሎች ልትሸፍነው ትሞክራለች፡፡ "ጁንታ፤ የቀን ጅብ" የሚሉት የስድብ ቃላት ህወሓትን ማጥፋት አልቻሉም፤ የሚሻለው ውይይት ነበር ከውድመት ይልቅ፡፡

የተማሩም ያልተማሩም የአድዋ ሰዎች አንዳንዴ በኩራት ስሜት ውስጥ ራሳቸውን ሲያገኙት "ትግራይ እኮ የአድዋ አካባቢ ስም ነው" በማለት ያበጠውን ያፈነዱታል፤ ይህ ሁሉ የህወሓት ስኬት የአድዋ ስኬት ነው ለማለት፡፡ እርግጥ ነው ከደርግ በፊት ከአድዋ ውጪ ያሉት እናቶች ለልጆቻቸው ሲነግሩ የኖሩት "ትግራይ" የሚባለው አድዋ መሆኑን ነው፤ ሰፋ ሲልም አኹሱምና ሽረን ያካትታል፤ 'አሽዓ' እንዲሉ፡፡ ከ"ትግሬ" ወደ "ትግራይ" የተደረገው የስያሜ ለውጥ በስም ለውጥ ብቻ ቢቀር ኖሮ ጸጉር አይነጭ ስጋ አይቦጭቅ፡፡ ችግሩ ለዘላቂ የአንድ የተወሰነ አካባቢ የፖለቲካ የበላይነት እንደ ስነ-አእምሯዊ ድልዳል ሆኖ ማገልገሉ ነው፡፡ ይህ ችግር ህዝብን ያበሳጩ በእንደርታና በራያ ላይ ሰፊ አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ እንደምታዎች ነበሩት ያሉትም ነው፡፡ ኪዳነ አመነ የመስቀል እለት 2007 ዓ.ም. መቐለ ፖስት በተባለ የፌስቡክ ገጽ ላይ ያወጡት "ትግሬ" ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ርእስ ያለው አጭር ጽሁፍ ይኸው፡-

ብዙ ጊዜ ትግረኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን "ትግሬ" ተብለን ስንጠራ ደስ አይለንም (እኔም ጭምር)፡፡ ለምን ቢባል ቋንቋችን ትግርኛ ነው፤ የክልላችን መጠሪያም "ትግራይ" ነው፤ እኛ ሰዎቹ ስንጠራም "ተጋሩ" ወይም "ትግራዮች" ተብለን መጠራት አለብን እንጂ "ትግሬ" መባል የለበትም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ አንዳንዴም "ትግሬ" እንደስድብ የሚቆጥሩት ሰዎች አሉ ("ትግሬ" አንኮበራውያን የሰጡን ቃል ነው ተብሎ ስለሚታመን ይመስለኛል-የህወሓት ተጽዕኖም ተጨምሮበት)፡፡ "ትግሬ" የሚባል ቃል ግን ግሬክ ነው፡፡ ትርጉሙም ነብር ማለት ነው፡፡ እኛ ተጋሩ /ትግራዮች/ ይህ ስም (ትግሬ) የሚል የተሰጠን ያለምክንያት ሳይሆን ታሪካዊ መሠረት አለው፡፡ በአንድ ወቅት የግሪክ ንጉሥ እስክንድር በጣም ሀይለኛ ነበር፤ መላ ዓለምን ያንቀጠቅጥ ነበር፤ ግዛቱም እስከ ምስሪ (ግብፅ) ከደረሰ በኋላ ኢትዮጵያን ለመያዝ ስለፈለገም እስከ ሀማሴን (ኤርትራ) ድረስ ጀነራሎቹን ይዞ ለስለላ እንደመጣ የታሪክ መዛግብት ያሳያል (ክሮኒክልስ ኦፍ ጆን ቢሾፕ ኦፍኒኮ) በሚል መጽሐፍ ተገልጧል፡፡ አገራችን ላይ ከደረሰ በኋላም እንዲህ ብሎ ፎከረ፡- "ቶካች ደከማሪስ" ትርጉሙ ኢትዮጵያን በ10 ቀን እቆጣጠራታለሁ ለማለት

ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን (ያኔ ብሔረ አጋእዚያን፣ መንበረ መንግስታቸውም አክሱም ላይ የነበሩ) አሸነፉትና እንዲህ አለ፡- "አፍቶሰኢነ ትግሬ" ብሎ ተናገረ ትርጉሙም እነዚህ (ተጋሩ) እንደ ነብር ተወርዋሪና ሀይለኛ ናቸው እንደ ማለት ነው (መስፍን ዘርአ ብሩክ መንገሻ፡ ካብ ኤርትራ ክሳብ ኢትዮጵያ፡ ገጽ 5) በሚል መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡ "ስሙ ይመርሆ ለግብሩ" ይላል ግእዝ፡፡ ያኔም ብሄረ አግኣዚያን ስማቸውና ግብራቸው እኩል ይራመድ ነበር፡፡ ስለሆነም "ትግሬ" አንኮበራዊያን ያወጡልን ስም ሳይሆን የግሪክ ቃል ሆኖ ትርጉሙ ደግሞ ነብር ማለት ነው፤ ትግሬ ተብለን ስንጠራም ቅር ልንሰኝ አይገባም፡፡ ማሳሰቢያ፦ ነብር ነን ተብሎ ደግሞ ለትምክህት እንዳትጠቀሙበት አደራ እላለሁ"

የኪዳነ አመነ ጽሁፍ ሙሉውን የቀረበው ለማሳጠር ስለሚከብድና መልእክቱም እንዳይዛባ በመስጋት ነው፡፡ ጽሁፉ የሚጠቁመው አንድ አቢይ ቁምነገር አለ፡፡ ይሄውም "ትግሬ" መቀየር ያልነበረበት መልካም ስያሜ እንደነበረ ነው፡፡ የቦታ ስሞች ይቀየራሉ፡፡ አንዳንድ ስሞች ለአሁኑ ትውልድ አስጸያፊ ስሞች ሆነው ሲገኙ ይቀየራሉ፡፡ ለምሳሌ ወደ "ማይ ነብሪ"፤ ወደ "ፍረወይኒ"፡፡ ሌላውም ገዢዎች በራሳቸው ቋንቋ የቦታ ስም ቀየሩብን እያሉ፡ "አዳማ"፤ ቢሾፍቱ፤ ጭሮ፤ ፊንፊኔ" እያሉ ቀይረዋል፡፡ በግሪክ "ትግሬ" ማለት ነብር ለማለት ቢሆን ለታሪኩ የሚመጥን ትርጉም የሰጡት ግን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በአማርኛ መዝገበ ቃላታቸው ውስጥ ነው፡- "ትግሬ ማለት ነጋዴ ማለት ነው" ይላሉ፡፡ አክሱም ገናና የነበረችው በግብርና ሳይሆን በአለም አቀፍ ንግድ ነበር፡፡ ታዲያ ተጋሩ የአክሱም ስልጣኔ ወራሾች ናቸው ከተባለ ይህ ስያሜ ትክክል አይሆንም? አሁን የትግራይ ስያሜ ወደ "ትግሬ" ይመለስ ብሎ መከራከሩ ፋይዳ የለውም፤ ተጠቃሚው ማን ይሁን ምን ስያሜው በመላ አለም የሚታወቅ ሆኗል፡፡

የስም ለውጥ ሲደረግ የተሰጠው ምክንያት ግን ልብ የሚሰብር የማጭበርበር ስራ ነበር፡፡ እንዲህ አሉ የስም ቅያሪውን ያስፈጸሙ ግለሰቦች፡- ሸዋ 'ትግሬ" ብሎ የጠራን "ተ-እግሬ" ለማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ "ከእግሬ ስር" ማለት ነው! ትግሬ ለሸዋ የሚያስፈራ ተቀናቃኝ እንጂ ከእግሩ ስር አልነበረም፡፡ ለትግራይ መሳፍንትና መኳንንት ልጆቻቸውን ሲድሩ የነበሩት የሸዋ ነገስታት ይህን ያህል ሲንቋቸው ስለነበር ነውን? "አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ" ነው እንጂ ነገሩ፡፡ በትግራይ የዘመነ መሳፍንቱ ቅሪት ከአሁኑ ዘመን ፖለቲካ ጋር አልላቀቅ እስካለ ድረስ፤ የአድዋው ደጃዝማች ገብረሰላሴ በእንደርታው ራስ ስዩም ላይ የነበራቸው ደመኝነት መንፈሱ አሁንም ሸው ሸው ማለቱ ከቀጠለ ትግራይን ገዝግዞ ይጥላታል፡፡ ህዝብ

ከልቡ አንድ የሚሆነው በእርግጫና በግልምጫ አይደለም፤ ወይም “ትግራይን ልታፈርሱ” በሚለው በበሽታው ላይ ሳይሆን በበሽታው ምልክት ላይ አትኩሮ ህዝብን በመፈረጅ አይደለም፡፡ የዛም ይሁን የዚህ ለሚኖርበት ክልል መልካሙን የሚመኘው የጥቅሙም የችግሩም እኩል ተጋሪ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት የአስተዳደር፤ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊና ህጋዊ መብቶቹ በእኩልነት ሲከበሩ፡፡ አንዱ መሬት ወራሪ ሌላው ተወራሪና ጾም አዳሪ፤ አንዱ አስተዳዳሪ ሌላው በገዛ ቀየው የበይ ተመልካች፤ አንዱ በቋንቋ ዘየ አሿፊ ሌላው በቋንቋው አፋሪ፤ አንዱ እንደልቡ ተሳዳቢ ሌላው ማን አለኝ ብሎ ዝም ባይ!

## 1.4. የአክሱማዊት-ትግራይ ወደ ቀይ ባህር መመለስ

ምንም እንኳ ትግራይ በአገውና በትልቁ የአቢሲኒንያ/ኢትዮጵያ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወት ውስጥ የውሃ ላይ ኩበት ሆና በርካታ መቶ አመታት ብታሳልፍም በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ የመጣባት ለውጥ ግን የወደፊት እጣዋን የሚወስን ሆኖ ቀረ፡፡ የአኹሱም ውድቀትና ከዛ የቀጠለው የደቡባዊ ውህደት ውስብስብ ታሪካዊ ጉዞ የጀመረው በእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ምክንያት ቀይ ባህር ለክርስቲያኗ አኹሱም ዝግ በመሆኑ ነበር፡፡ አሁን ግን ተዘግቶባት የነበረው ቀይ ባህር ተከፈተላት ሳይሆን ተከፈተባት! ቀይ ባህር የተከፈተው ለአውሮፓ ቅኝ ገዢ ሃያላን መንግስታት መመላለሻና ግዛት ማስፋፊያ እንጂ ትግራይ እንደ አኹሱም ቅድመ አያቶቿ በኢዛና ወርቅ ሳንቲም ከአለም ጋር ንግዷን የምታጧጡፍበት አዲስ እድል የከፈተ አልነበረም፡፡

በቀይ ባህርና ዙሪያው የተከሰተው ስር-ነቀል ጂኦፖለቲካዊ ለውጥ ለትግራይ እጅግ የሚያስደምም መገጣጠም ነበር፡፡ ቀይ ባህር የተዘጋው ንግስናው አኹሱም ላይ በነበረበት ዘመን ሲሆን የተከፈተውም ከስምንት መቶ አመታት በኋላ ከትግራይ የተነሳ መስፍን የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት በሆነበት ታሪካዊ አጋጣሚ ነው፡፡ ከአኹሱም በኋላ የመጀመሪያ የሆነው የትግራዋይ የኢትዮጵያ ንግስና ግን እዳና ፍዳ እንጂ የሚዘመርለት ፍስሃ ወሰላም አልነበረም፡፡ በእስልምና መስፋፍትና በሜዲተራንያንና በቀይ ባህር ክልሎች የተንሰራፋው የኦቶማን ቱርኮች ሺህ አመታት ያስቆጠረ አገዛዝ አውሮፓ ወደ እስያ የምታደርገውን የንግድ ልውውጥ መስመር ዘግቶባት ስለቆየ በደቡብ አፍሪካ በኩል ረዥም ጉዞ ማድረግ ተገዳ ነበር፡፡ ኦቶማን ቱርኮች ተዳክመው አካባቢውን ሲለቁ

አውሮፓውያን ሜዲተራንያንና ቀይ ባህርን የሚያገናኝ የስዌዝ ቦይን ቀደዱ፡፡ አሁን ከአውሮፓ ወደ እስያ ቅኝ ግዛቶች የሚደረገው ጉዞ ቀይ ባህርን አቋርጦ በመሆኑ በቀይ ባህር ዳርቻና አቅራቢያ ላይ ያሉ ህዝቦችና መንግስታት ትኩረት የሚስቡ ሆነው ተገኙ፤ እነሱን መቆጣጠርም የአውሮፓውያን ዋና ፖሊሲ ሆነ፡፡





ግራኝን ለመፋለምና የካቶሊክ ሃይማኖትን ለማስፋፋት ከመጡት የፖርቱጋል ወታደሮችና የጀዝዊት ቄሶች በስተቀር አቢሲኒያ/ኢትዮጵያ በአለም ተረስታ በመቆየቷ ከውጪ ጠላት ስትከላከል ሳይሆን እርስ በርስ ስትተራመስና አብያተ ከርስትያናትንና ገዳማትን ስትገነባ ለእምተ አመታት ኖረች፡፡ በቀይ ባህር ዳርቻና አቅራቢያ እንግሊዝ ግብጽን፤ ሱዳንን፤ የመንን በቅኝ ያዘች፡ ፈረንሳይ ጂቡቲ ላይ መሸገች፤ ዘግይታ ባለቀበት የደረሰችው “የቅኝ አገዛዝ ውሻ” ኢጣሊያ ደግሞ እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ያልደፈሩትን የምስራቅ አፍሪካው ተራራማ ምድርን በሃይል ለመግዛት “በምድሪ ባህሪ” በኩል ብቅ ጥልቅ ማለት ጀመረች፡፡ አስቸጋሪውን ክልል እንድትሸፍንላቸው እንግሊዞች ያበረታቷትና ድጋፍ የሰጧት ኢጣሊያ አሰብን ከአገሩ ባላባት እንደሸቀጥ ገዝታ በምጽዋ በኩል ወደ ሃማሴን ከፍታዎች ለመውጣት ጥረት ጀመረች፡፡

ይህ የኢጣሊያ ሃይል ስርሰራ ከቀይ ባህር ከቅርብ ርቀት ላይ ለነበረው ለትግራይና ከትግራይ ለተገኘው የኢትዮጵያ ንጉስ እንጂ በቀሪው አቢሲንያ/ኢትዮጵያ ለነበሩት ነገስታት፤ መሳፍንትና መኳንንት የሚያስጨንቅ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ይህ ለዘመናት እንደራሳቸው አካል ያላዩት ትግራይ የውጭ ወራሪ መጣበት ብለው፤ ጦር ሰብቀውና ጋሻ ወድረው ውድ ህይወታቸውን ጦር

ሜዳ ላይ የሚጥሉበት ምክንያት አልታያቸውም፡፡ በአጉል ጊዜ የነገሱትና ቤተመንግስት ሰርተው ያልኖሩበት አጼ ዮሃንስ በራስ ሲያቅት በጠላት እጅ ህይወታቸው መጥፋቱ እርግማን መስሎ እንደ ምርቃት ይቆጠር ነበር፡፡ ይህ ምኞት መተማ ላይ እውን ሆኗል፡፡ ትግራይንና መሪዎቿን አቅም ባለው የውጭ ሃይል ማስጠቃት በቀርቡ የተፈጸመ ድርጊትም ሆኗል፡፡

አጼ ዮሃንስና የትግራይ ተወላጅ የጦር አበጋዞቻቸው ከግብጽና ከኢጣሊያ በተደጋጋሚ ውጊያ በተጠመዱባቸው አመታት በቀሪው አቢሲንያ/ኢትዮጵያ የነበሩት ነገስታት፤ መሳፍንትና መኳንንት  የተፈጥሮ ሃብት ወደ ታደለው ምስራቅ፤ ምእራብና ደቡብ  ግዛቶቻቸውን እያስፋፉ በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚና በወታደራዊ አቅም እየተደራጁ ነበር፡፡ ለስሙ ብሄራዊ ጦር ይባል እንጂ በማያባራ የአገር መከላከል ውጊያ ሲዋከብ የኖረው የአጼ ዮሃንስ ሰራዊት ትግራይ-በቀል ነበረ፡፡ ስለዚህ ግብጽና ኢጣሊያ ብቅ ባሉ ቁጥር የምታለቅሰው የትግራይ እንጂ የሸዋና የጎንደር እናት አልነበረችም፡፡ ችግሩ “እናንተ ተወጡት እኛጋ እስኪደርስ ድረስ” የሚለው ዝምታ ብቻ አልነበረም፤ አጼ ዮሃንስ ከሚዋጓቸው የውጭ ጠላቶች ጋር መመሳጠርም ጭምር እንጂ፡፡

በሁለተኛው የኢጣሊያ ወረራ በሰሜን የመጣውን የፋሺሽት ጦር ለብዙ ወራት ትግራይ ውስጥ የተፋለመው በራስ ስዮም የተመራው የትግራይ ህዝብ ሰራዊት ነበር፡፡ የአጼ ሃይለስላሴ ጦር የደረሰው የኢጣሊያ ጦር መላ ትግራይን ተቆጣጥሮ ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ማይጨው ላይ ከደረሰ በኋላ ነው፡፡ በአድዋ ጦርነት የሆነውም የዚህ ተመሳሳይ ነው፡፡ የኢጣሊያ ጦር ትግራይን በሙሉ ተቆጣጥሮ እምባ አላጀ እስኪደርስ ድረስ ከቀሪው ኢትዮጵያ የአጼ ሚኒሊክ ጦር አልደረሰም ነበር፡፡ የኢጣሊያን ጦር ለመግፋት ጦርነት የተጀመረው በትግራይ ደቡባዊ ጫፍ ኋላም በመቐለ ነበር፡፡ አድዋ ላይ ጦርነት የተካሄደው የትግራይ ህዝብ ያለ ረዳት በኢጣሊያ ጦር እልቂትና ውድመት ከደረሰበት በኋላ ነው፡፡ ይህ በድህረ-አጼ ዮሃንስ የትግራይን ህዝብ የማዳከም ፖሊሲ አንዱ አካል ነበር፤ በጠላት እጅ!

በመሃል አገሩ አመራር አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ድንበር አላጀና ማይጨው ነበር ወይስ መረብ? የትግራዩ ጦርነት ለሶስተኛ ጊዜ ያመለከተው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያና የኢጣሊያ/ኢሪትርያ ድንበር መረብ ሳይሆን አላጀና ማይጨው መሆኑ ነው፡፡ ኢጣሊያ ከአላጀ ወደ አዲስ አበባ ለማለፍ ባትሞክር ኖሮ

ትግራይም እንደ ኤሪትርያ በኢጣሊያ እጅ እንድትሆን ይፈቀድ ነበረን? በኋላ እንዲህ ሊከዳ ይህ ትግራይን አሳልፎ የመስጠት ሴራ ሁለት ጊዜ የከሸፈው የትግራይ ህዝብ ፍላጎት ስላልነበረው ነው፡፡ አሁንስ? "ድንጋይ ሆይ! ሶስተኛ ካደናቀፍከኝ ድንጋዩ እኔ እንጂ አንተ አይደለህም!" የኢጣሊያ በኤሪትርያ መኖር የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት ለትግራይ ህዝብ ዘላቂ ጥቅም ሳይሆን ለእርስ በርስ የስልጣን ግድድር ተጠቅመውበታል፡፡

የኢጣሊያ ቀንደኛ ጠላት የነበሩት የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጆች ኤሪትርያ ውስጥ ከነበሩት ጣልያኖች ጋር መልካም ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ይህን ያደረጉት "የአጼ ዮሃንስንና የራስ አሉላን የኢትዮጵያ ፍቅር ያየህ ተቀጣ!" በማለት ይሆናል፡፡ በየዋህነት እንደባዳ ለምትቆጥራቸው አገር ነጻነት ተቆርቁረው እንጂ አጼ ዮሃንስም ሆነ ራስ አሉላ ከኢጣሊያ ጋር የግል ቂም አልነበራቸውም፡፡ ኢትዮጵያን ለጣሊያን አሳልፈው ቢሰጡ ኖሮ በግላቸው የተሻለ ጥቅም ያገኙ ነበር እንጂ አይጎዱም፡፡ አያቶቻችንን አስገድለው ማርያ ተሬዛ ብር ያፈሱት ባንዶች "ከነጻነት" በኋላ በወንጀል ሳይጠይቁ የተከበሩ ነጋዴዎች ሆነው ከኖሩ በኋላ ለልጆቻቸው ሃብትን አውርሰዋል፡፡ ባንዳ ይጠላል፤ መረዳት ግን ይገባል፡- "የፊት ወዳጅኽን በምን ቀበርከው በሻሽ፤ የኋለኛው እንድይሸሽ"፡- በላይ ዘለቀ!

## 1.5. "የገና-ዳቦ"፡- ትግራይ-ገዳይ ጂኦፖለቲካ

የሸዋው ንጉስ ሚኒሊክ የተዋጣላቸው ማክያቬሊያዊ ፖለቲከኛ ነበሩ፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ የዳጎሰ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ አቅም እያላቸው በቀይ ባህሩ ጦርነት የተጠመዱትን አጼ ዮሃንስን ወግተው የንግስና ሙከራ ማድረግ አያቃታቸውም ነበር፡፡ ወተቱ ሳይረጋ መናጥ በቂ ቅቤ እንደማያስገኝ የመረዳት ችሎታ ነበራቸው፡፡ ለቀጣይ ንግስናቸው ለመደራጀት ሲሉ በአጼ ዮሃንስ ጀርባ አልፈው ከጣልያኖች ጋር የነበራቸው ወዳጅነት፤ ከነገሱም በኋላ የትግራይን መተንፈሻ (ምድሪ ባሕሪ) ለጣሊያን በስጦታ ማስረከባቸው በአገር መውደድ እሴቶች ላይ ማክያቬሊ ማክያቬሊ ሲጫወቱ ስለነበር እንጂ ጣልያን ጊዜ ጠብቆ እንደማይለቃቸው አጥተውት አልነበረም፡-  የዓድዋ ጦርነትና የጣልያን ወረራ!

የአጼ ዮሃንስ ወራሾች ዙፋኑን ከሚኒሊክ ለመንጠቅ ያደረጓቸው ሙከራዎችን ለማከሸፍ መውጫ በራቸውን ለጣልያን አስረክቦ መዝጋትም ራሱ በቂ አልነበረም፤ የትግራይ መሳፍንት ኤሪትርያ ውስጥ ከሰፈሩት ጣሊያኖች ጋር ነጻ

የሆነ ግንኙነት ያደርጉ ስለነበር፡፡ አጼ ሚኒሊክ ባህር ዳርቻውን ካስረከቡ በኋላ ለኢጣሊያ ጠቃሚ ሆነው አልተገኙም፡፡ የጣልያኖች ዋና አላማ መላ ኢትዮጵያን መቆጣጠር ስለነበር በፍቅርና በምክር ካልሆነ ወደ ኢትዮጵያ አያሳልፉንም ብለው ከፈሯቸው የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት ጋር ተወዳጁ፡፡ "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባበታል"፡፡ አገር አንዱ ሲያፈርሳት በሌላኛው አትቆምም፡፡

በዛ ዘመን ለሰፈነው ፊዩዳላዊ የኢኮኖሚ ስርአት ለትግራይም ለሚኒሊኳ አቢሲኒያ/ኢትዮጵያም የባህር በር ባለቤትነት ብዙም የሚያጓጓና መስዋእትነት የሚሻ ነገር አልነበረም፤ ከእውቀት አቅማቸው በላይ በመሆን ራቅ አድርገው የወደፊቱን ትውልድ ለምን አላስተዋሉትም የሚል የአሁኑ ዘመን ቁጭት ካልሆነ በስተቀር፡፡ አጼ ሚኒሊክ የጂቡቲ የባህር በርንም ቢሆን በእጃቸው ማቆየት አላስፈለጋቸውም፡፡ የባህር በሮች አግልግሎት እርስ በርስ ለሚፋጁ ነገስታት፤ መሳፍንትና መኳንንት የጦር መሳሪያ ማስገቢያ ስለነበሩ ለአጼ ሚኒሊክ እርምጃው የትግራይ የዘውድ ተቀናቃኞችን ለማዳከም ለጊዜውም ቢሆን ውጤታማ ሆኖላቸው ነበር፡፡ "በሬ ሆይ የፊቱን ሳር አይተህ የኋላው ገደል ሳታይ"፡፡ በያኔው ፖለቲካ አጼ ሚኒሊክ የባህር በሩን አሳልፈው መስጠታቸው ብዙ ላያስገርም ይችላል፤ የሚያስገርመው ነገር ቢኖር ከመቶ አመታት በኋላ አጼ ሚኒሊክ ያኔ ያላሰቡትን "ከአጸደ ገነት" የሚያናግር ቴክኖሎጂ መፈብረኩ ነው፡፡

**የውጫሌ ውል አንቀጽ 3**.

*ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ሉዓላዊ መብቶችን የሚጠቀሙባቸውን ግዛቶች ወሰን በተመለከተ ያለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ሁለት ልዑካንና ሁለት ኢትዮጵያውያንን ያቀፈ ልዩ ኮሚሽን <u>በጣሊያን ምድር ላይ</u> ልዩ ምልክቶችን በመያዝ ምሽጎቹ ከዚህ በታች የተቀመጡበት <u>ቋሚ የድንበር መስመር</u> ይዘጋጃል፡፡*
*ሀ) የደጋው መስመር የኢትዮጵያ-ጣሊያንን ድንበር ያመለክታል*
*ለ) ከክልሉ አራፋሊ ሃላ፣ ሳጋንና አስመራ በጣሊያን ድንበር ውስጥ ያሉ መንደሮች ናቸው*
*ሐ) አዲ እና አዲ ነፋስ ጆአንስ ቦጎስ ከጣሊያን ድንበር ጎን ይሆናሉ*
*መ) በአዲ ጆአንስ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የተዘረጋው ቀጥተኛ መስመር በጣሊያን እና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ድንበር ያመለክታል*

በኢትዮጵያ የባህር በር ህዝባዊ አጀንዳ መሆን የጀመረው ከሁለተኛ የአለም ጦርነት በኋላ በነበረው አለም አቀፍ የኢኮኖሚ መነቃቃት ነው፡፡ ስለዚህ የድሮ ውሳኔ ሰጪዎች በድሮ በሬ እያረሱ በወሰዷቸው እርምጃዎች በዘመኑ ልኬት ላይ

እያስቀመጥን መገመገሙ ፋይዳ ቢስ ነው፡፡ ጣሊያን በአጼ ሚኒሊክ ስጦታ የምስራቅ አፍሪካ ህልሟን እውን ለማድረግ ጥንስሱን በነጻነት የምትጠነስስበት ቅርብ፤ ሰፊና አመቺ ግዛት አገኘች፡፡ አብሮ ሲጠነሰስ የነበረውም አስቸጋሪው የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ነበር፡፡ ኤሪትርያ ተብሎ በተሰየመው የቀይ ባህር ዳርቻ ግዛት ትግራይን ለዘለቄታ ቅርቃር ውስጥ የሚያስገባ የፖለቲካ ጂኦግራፊያዊ አሃድ ይፈጠራል ብሎ የተነበየ አልነበረም፡፡

የኋላ ዘመኗ ኢትዮጵያም የትግራይን መሳፍንት ለማዳከም በሚል አጭር እይታ እንደዋዛ ያጣችውን የባህር በር መልሳ ለማግኘት ለግማሽ ምእተ አመት በጦርነት ስሜት ውስጥ ሆና የአፍሪካ ቀንድ ሰላምዊ ኑሮን ምስቅለቀል ታወጣለች የሚል ቅዠት እያየ ሌሊቶችን ያሳለፈ የለም፡፡ “ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው አያወርዱት”፡፡ አጼ ዮሃንስ ተሰዉ፤ ሚኒሊክም አለፉ፤ ጣሊያን አገሯ ገባች የተቦካው ጂኦፖለቲካ ግን ለትግራይና ለኢትዮጵያ በቀላሉ የማይወጡት ከባድ እዳ ወስጥ አስገብቷቸው ቀረ፡፡ ምድሪ ባህሪ ኤሪትርያ ሆና ከቆይችባቸው ስድሳ የጣሊያን አመታት ሳጥን ውስጥ እንዳኖሩት አቃ የጥንቷ ምድሪ ባህሪ እንደሆነች አልተመለሰችም፡፡ በወሳኙ የቀይ ባህር ዳርቻ ጣሊያን ለኢትዮጵያና ለትግራይ ትታላቸው የሄደችው ቁርጥ ጣሊያንን የመሰለች፤ የጥንታዊ አኹሱም ወርቃማ እሴቶቿን ያጣች፤ የቅኝ አገዛዝ ታሪኳን እንደቡራኬ የምትቆጥር፤ አቅጣጫ የጠፋት ነገር ግን በባዶ የበላይነት ስሜት የተወጠረች ኤሪትርያን ነው፡፡

ትግራይ እንደ “ገና-ዳቦ” የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ያስተዋወቁት ታላቁ ኢትዮጵያዊው ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ነበሩ፡፡ በትግራይ ጦርነት ዋዜማ ባሳተሙት ምናልባትም የመጨረሻ ትንተናቸው ትግራይ በሰሜን የኤሪትርያ እሳት በደቡብ የኢትዮጵያ እሳት መካከል በተጣደ “የገና-ዳቦ” እንደምትመሰል የገለጹበት ትንቢት እውን ሲሆን አላዩም፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ትግራይ “ገና-ዳቦ” የሆነችበትን ምክንያት ሲያብራሩ ሸክሙን ያራገፉት በ“ወያኔ” ላይ ነበር፡- “ወያኔ ትግራይን ከኤሪትርያና ከኢትዮጵያ ጋር ከፉኛ አነካክሷታል”፡፡ በኤሪትርያና በኢትዮጵያ በኩል በትግራይ ላይ ያለው አመለካከት በጎ አለመሆኑ የወያኔ ዘመን የወለደው ክስተት አይደለም፤ አባብሶት እንደሆነ እንጂ፡፡ በአንድ ወገን፤ በኢትዮጵያ ውስጥ የባህል እሴት የመሆን ያህል ከየኢኮኖሚያዊው፤ ከየፖለቲካዊውና ከየማህበራዊው ድር ጋር አብሮ የተገመደው የትግራይ ጥላቻ በሌላኛው ወገን ደግሞ በጥንታዊቷ ምድሪ ባሕሪ ቅኝ አገዛዝ ያጣመመው

በትግራይ ላይ ያለው አመለካከት በንቀት ላይ የተመሰረተ መሆኑ፡፡ ረዥም ዘመን የተጣደው የ“ገና-ዳቦ” በስሎ ያረረው ግን በዚህ በያዝነው ትውልድ ነው፡፡

ትግራይ ባልፈለገችውና ከአቅሟ በላይ በሆነ የታሪክ አስገዳጅ ሂደት በተፈጠረችው ኤሪትርያ የኢትዮጵያ የባህር መውጫዋ ሲዘጋባት ጅራፏን ያነሳችው በትግራይ ላይ ነው፡፡ “ደምድም በገደለ አጎት ተሰቀለ”፡፡ በኢትዮጵያ ላይ የኢጣሊያ ወረራ ያበቃ ቢሆንም ለአስር አመታት ያህል እንግሊዝ ኤሪትርያን “በአደራ” ይዛ ቆይታለች፡፡ ከብዙ ዲፕሎማሲያዊ ውጣ ውረድ በኋላና በአሜሪካ ድጋፍ ኤሪትርያ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቀለች፡፡ ብዙም ሳይቆይ ከቀደምቶቹ ስህተት ያልተማሩት አጼ ሃይለሰላሴ ከኢትዮጵያው ኋላቀር ፊዩዳላዊ ሰርአተ-ማህበር በእጅጉ የተሻለ የካፒታሊስት ኢኮኖሚና የብዝሃ-ፓርቲ ፓርላማዊ ስርአት የነበራትን ኤሪትርያን ውሉን አፍርሰው ከፌደራል አቻነት ወደ አንድ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛትነት አወረዷት፡፡ ኢትዮጵያ ዳግም በሰራችው የአጭር እይታ ስህተት ለሰላሳ አመታት የማያባራ የኤሪትርያ የነጻነት ትግል ውስጥ ተነከረች፡፡ “አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” ሆነና ኢትዮጵያ ላፈረሰችው ፌዴሬሽን ኤሪትርያውያን ትግራይን ተጠያቂ አድርገው “ዓጋመ” የሚል ስድብ አከል ቅጽል ለጥፈው በተገኙበት ሁሉ የትግራይ ተወላጆችን ማንቋሸሽና ማሳነስ ተያያዙት፡፡ ይህ ኤሪትርያውያን በተጋሩ ላይ የነበራቸውን ቃር ከህወሓት ምስረታ በኋላና የትግራይ ህዝብ በህወሓት ሰራዊት በኩል ለኤሪትርያ የነጻነት ትግል እስከ ህይወት መስዋእትነት ድረስ ድጋፍ ቢደረግም ሊያለዝበው አልቻለም፡፡ በትግሉ ጊዜ ጥላቻው ጥግ የደረሰው የትግራይን ረሃብተኛ ህዝብ ወደ ሱዳን ተጉዞ እርዳታ እንዳያገኝ “ህዝባዊ” የሚል ቅጽል ስም የነበራቸው የኤሪትርያ ታጋዮች መንገድ ዘግተው ህዝብ እንዲያልቅ ምክንያት ሆነዋል፡፡

ኤሪትርያውያን ቁንጽል “ዘመናዊነትን” ከኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ የጭቆናና የአሽከርነት አመታት ተቀብለው ትግርኛ ቋንቋቸውን የጣሊያንኛ ጉራማይሌ ስላደረጉት በትግራይ ህዝብ ያልተከለሰ ነባር ቋንቋ እየቀለዱ ጤፍ ሊያሳክሉት ይምክራሉ፡፡ ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማሩና አስመራ ላይ ከጣሊያኖች እንዳይደርሱ ድካማ በሆኑ የአፓርታይድ መንደሮች ለመኖር ተገደው የነበሩት ኤሪትርያውያን በበታችነት ስሜት ያዳበሩትን “የበላይነት” በትግራይ ላይ ሲያራግፉት ኖረዋል፡፡ ኤሪትርያ ነጻነቷን እስካወጀችበት ድረስ የነበሩት አርባ ያህል አመታት በኤሪትርያም በኢትዮጵያም በኩል የነበረው የኢትዮጵያ

መንግስት ስለነበር ለትግራይ እሳቱ አንድ እንጂ ሁለት አልነበረም፡፡ የትግራይ "የገና-ዳቦ"ነት በሙሉ አቅሙ የተከሰተው የደርግ ውድቀትን ተከትሎ ኤሪትርያ ነጻነቷን ካወጀች ወዲህ ነው፡፡ ትግራይ በራሷ ላይ ሁለተኛውን እሳት ለማቀጣጠል ማገዶ ያቀበለችው ከአፍንጫው አሻግሮ ማየት ያልቻለ አመራር ስለነበራት ነው፡፡ የቀይ ባህር ወደቦች ከማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው ለትግራይ እንደሆነ የኢትዮጵያን ካርታ በጨረፍታም ቢሆን ያየ ሰው የሚስተው አይደለም፡፡

## 1.6. የተቃራኒዎች አንድነት በትግራይ ላይ

ማርክሳዊው ዲያሌክቲካል ማቴሪያሊዝም እድገት የሚመጣው በተቃራኒዎች አንድነት ነው ይላል፡፡ በትግራይ ግን የተቃራኒዎች አንድነት ያመጣው ውድመትን ነው፡፡ በተቃራኒ ምክንያቶች ትግራይን የጠምዱት ሃይሎች አብረው ትግራይን ካጠፉ በኋላ በፍቅር የምታኖራቸው ቅንጣት ታክል ነገር አልነበራቸውም፡፡ ለዚህ ሁሉ ያበቃው ታሪክ ምን እንደሆነ ቀጥሎ እናነባለን፡፡ ኤሪትርያ ምንም እንኳ የምትጀነንበት አንድ ሺህ ኪሎሜትር የባህር ዳርቻ ቢኖራትም "እብድ የያዘው መልክ አይበረክትም" እንደሚባለው ሆኖ ሰላሳ አመታት በታገሉለትና የትግራይ መሪዎች ባመቻቹላቸው ነጻነት ተጠቅመው በራሳቸው አቅም ለመልማትና ህዝባቸውን ለማበልጸግ ከመሞከር ይልቅ ከኢትዮጵያ አንቀልባ መውረድ አልፈለጉም፡፡ የኤሪትርያ ነጻ አውጪዎች የነደፉትና ሌላ መጠባበቂያ ያልያዙለት ብቸኛ ፍኖተ-ካርታ፡- "ኤሪትርያ የኢኮኖሚ ሃያልነት የምትገነባው በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት፤ በኢትዮጵያ ሰፊ የሸቀጣ ሸቅጥ ገበያና በኤሪትርያ የኢንዱስትሪ እድገት ነው" የሚል ፈገግ የሚያሰኝ ከቀድሞ ቅኝ ተገዥ የመነጨ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እቅድ ነው፡፡

ፍኖተ-ካርታቸውን አቤት ወዴት ብሎ የሚያስፈጽም ሃይል ህወሓት አመራር ውስጥ በቂ በሆነ ቁጥርና የፖለቲካ አቅም አለ የሚል እምነት ነበራቸው፤ ኤሪትርያውያን ፖለቲከኞች፡፡ እርግጥ ነው፤ ያሳመኑትም፤ ያስፈራሩትም፤ የከፈሉትም፤ ያሰረጉትም አቅም ያካበተ ሃይል ነበራቸው፡፡ ሆኖም ህወሓት ውስጥ ለኤሪትርያው ፍኖተ-ካርታ እኩል አቅም የነበራቸው የድጋፍና የተቃውሞ ድምጾች በመኖራቸው በሁለት ረድፍ ተሰልፈው ለህወሓት መንኮታኮት ከፍተኛ አስተዋጻኦ አደረጉ፡፡ በኢሳያስ አፈወርቂ የተመራው የኤሪትርያ የነጻነት ትግል

በቅድመ ሁኔታ የተከበበ እንደነበር እየተጋለጠ የመጣው እጅግ ቆይቶ ነው፡፡ በህወሓት መስራች መሪዎች አንደበት የተነገረውና በኢሳያስ አፈወርቂ ቃለ መጠይቅ እንደዋዛ የተጠቆመው የኤሪትርያ ትግል እንደሁኔታው በነጻነትም በውህደትም ሊጠናቀቅ እንደሚችል ነው፡፡ በትግሉ ወቅት ይህ መንታ መንገድ ለሌሎች የሻዕቢያ መሪዎች ስውር እንዳልነበረና በፍርሃትና በለዘብተኝነት ይሁን ለእቅዱ ድጋፍ በመስጠት ተዳፍኖ አልፏል፡፡ ፍኖተ-ካርታውን ተግባራዊ ለማድረግ ኢሳያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት መሆን ከቻሉ የሰላሳ አመታት ትግል ውሃ በልቶት ይቀርና ኤሪትርያውያን የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን ጨብጠው ያሻቸውን ይሰራሉ፡፡ አለዚያ "ኤሪትርያ በግላችን፤ ኢትዮጵያ በጋራችን" የሚለው መርሆ ይተገበራል፡፡

ሁለቱን ቀጥተኛውንና የእጅ አዙሩን የኤሪትርያ የቀኝ አገዛዝ እቅድ ሳይጠበቅ ከጨዋታ ውጭ ያደረገው ህወሓት-መሩ የኢትዮጵያ መንግስት ነበር፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላ በወያኔ ታዝሎና ታንክና መድፉን ወድሮ አዲስ አበባ የገባው ሻዕቢያ ከአስመራ ይልቅ አዲስ አበባን ነጻ አውጥቶ የተቀመጠ ይመስል ነበር፡፡ በፍኖተ-ካርታው "እቅድ-ለ" መሰረት ሻዕቢያ (ህግደፍ) የኢትዮጵያን ፖለቲካ ላልተረጋጋው ኢህአዴግ ትቶ ልምድ ባካበቱ የደህንነት አባላቱ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በህገ-ወጥ ገበያ መበዝበዙን ተያያዘው፡፡ ኢትዮጵያ ኢህአዴግ ያስተዋወቀውን አዲሱን የአስተዳደር ዘይቤ ያልተቀበሉት፤ ህወሓት ለኤሪትራያ የሙሉ ነጻነት ድጋፍ ሰጥታ ባህር በር አሳጣችን ብለው በከሃዲነት በፈረጇት ሰፊ የህዝብ ድጋፍ በነበራቸው ተቃዋሚዎች ስትዋከብ ለህግደፍ መንግስታዊ "ፓይሬቶች" ተመቻቸች፡፡ ህወሓት ውስጥ የነበሩት አፍቃሬ-ህግደፍ አመራሮች ለሻዕቢያ ድርጊት አንድ አይናቸውን ስለጨፈኑም ጉዳዩ ወደ ቀውስ አምርቶ "በባድመ ግጭት" ጦር እስኪያማዝዝ ድረስ ቆየ፡፡

ህግደፍ በባድመ አሳቦ ፍኖተ-ካርታው በደረሰበት ኪሳራ ምክንያት ጦርነት ሲጭር የህወሓት ጀርባ ባዶ ነው የሚል እምነት ነበረው፡፡ በዚህ ጦርነት ከኢትዮጵያ ህዝብ "የተጣላችውን" ትግራይን አምብርክኮ ደካማዋን ኢትዮጵያ እንደልብ ለመግዛት ያሰላው "መሶብ ሰርቼ ላጤ አበርክቼ" በተገላቢጦሹ በኤሪትርያ መገንጠል ቆሽቱ ያረረው የኢትዮጵያ ህዝብ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ኤሪትርያን ለመመለስ ሆ! ብሎ ከህወሓት ጎን ተሰለፈ፡፡ ከሚያስተዳድሯት ኢትዮጵያ ይልቅ ህግደፍን ይፈሩ ወይም ይወዱ የነበሩት የህወሃት መሪዎች

ኢትዮጵያውያን በባድመ ጦርነት ሰበብ ሊያገኙ ያሰቡት የባህር በር እድል ተጨናገፈ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ከማንኛውም ጊዜ በላቀ ህወሓትን አንቅሮ የተፋት በዚህ ዳግም የማይገኝ ታሪካዊ አጋጣሚ መክሸፍ የተነሳ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ጦር ህግደፍን አሸንፎ በባህር በር ጉዳይ ላይ የመጨረሻ መፍትሄ ለመስጠት ሲገሰግስ የህወሓቱ የበላይና የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የኢትዮጵያ ሰራዊት “አለም አቀፍ ህግን ተከትሎ” ወደ ድንበሩ እንዲመለስ አዘዙ፡፡ ህግደፍም ተስፋ ከቆረጠበት አንሰራራ፤ ሆኖም ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተነጥሎ ኤሪትርያን የሚያለማበት ዘዴውና ብልሃቱ ስለጠፋው መላ ኤሪትርያን የድህነትና የውትድርና ካምፕ አድርጓት ሃያ መራራ አመታትን አሳለፈ፡፡ በሁለት አስርት አመታት ለድህነቱ ዋና መንስኤ ነው ተብሎ በኤሪትርያ ህዝብ ጆሮ ሲንቆረቆር የኖረውና ወጣቱን የኤሪትርያ ሰራዊት ወደ አውሬነት የቀየረው “ህወሓትና የትግራይ ህዝብ የኤሪትርያን ህዝብ ዘግተው እያደኸዩት ነው” የሚል ነው፡፡

በጎረቤት አደገኛ የሚልዮኖች ምሬትና ጥላቻ እየተንቀለቀለ በነበረባችው በርካታ አመታት በህወሓት በኩል መርፌ ወድቆ የጠፋም አይመስልም ነበር፡፡ ህግደፍ ኤሪትርያን አድቅቆ መግዛት የራሱ ፍላጎት ቢሆንም “ያለ ሰላም፤ ያለ ጦርነት” እያለች ህወሓት በሰጠችው የዝምታ እድል ጣቱን ወደ ትግራይ “ልማት” እየቀሰረ የኤሪትርያን ህዝብ ጸጥ አድርጎ አቤት-ወዬት ብሎ እንዲገዛለት አድርጎታል፡፡ የወላጅ ፍቅር እንደማይለየው ግን ደግሞ ከሰፈር ጎረቤት ጋር እንደሚናከስ ክፉ ልጅ ከውስጥም ከውጪም ያለው የኤሪትርያ ህዝብ ለህግደፍ (ለወዲ አፎም) ያልተቆጠበ ድጋፍ እየሰጠ ዘልቋል፡፡

በህወሓት የውስጠ-ፓርቲ ውዝግብ በነገሰበት፤ ነገን ባላስተዋለ ሃብት ማካበትና የቅንጦት ኑሮ ጣፋጭ እንቅልፍ በተተኛበት፤ ባእድ የሆኑ ፋብሪካዎችና ህንጻዎች በትግራይ ከተሞች ቢገተሩም አብዛኛው የትግራይ ህዝብ ከድህነቱ ፈቀቅ ማለት ባልቻለበት፤ ህወሓትን ወደ ታች የሚጎትታት የአሸዋ አዙሪት ሊታወቃት አልቻለም፡፡ ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞ እንደ ቀልድ የሚነገር ጨዋታ አለ፡፡ የማለዳ የአዲስ አበባ ተእይንት፡- “የህወሓት አመራሮች ሲጠጡ አድረው ተድጋግፈው ወደ ቤታቸው ሲሄዱ፤ የኦህዴድ አመራሮች ጂም ይገባሉ”፡፡ መጪው ጊዜ የማን ሊሆን እንደሚችል ከዚህ ቁምነገር አዘል ዋዛ መረዳት ይቻላል፡፡ “አካሄዱን አይተው አረማመዱን፤ ሸክሙን ይቀሙታል

ያዘዘመመውን"፡፡ ህወሓት ላይ በውግንናም ትግራይ ህዝብ ላይ ያፈጠጡና አመቺ ጊዜ የሚጠብቁ ተቃራኒ አላማ ያላቸው አይኖች ነበሩ፡- ኤሪትርያን ያስቀማቻት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያን ያስቀማቻት ኤሪትርያ! የገና-ዳቦው ሲጣድ፡፡

ህወሓት ለኢትዮጵያ የቀይ ባህር ወደቦችን ለማስገኘት ጥረት ማድረግ ያልፈለገችበት ምክንያት ምንድነው ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አጼ ሚኒሊክ የባህር በሩን ለጣሊያን አሳልፈው ከሰጡበት ምክንያት ጋር የሚያመሳስለው ነገር አለ፡፡ ከሁለቱም የኤሪትርያ ወደቦች ምጽዋ የበለጠ ጠቃሚነት ያለው ለትግራይ ነው፤ አሰብም ቢሆን በጣም ሩቅ አይደለም፡፡ ወሳኙ ነገር ህወሓት ቅድሚያ ስትሰጥ የነበረችው በጦርነት ለተጎሳቆለችው ትግራይ እድገት ነበር ወይስ ዋና ዋናዎቹ የህወሓት አመራሮች አዲስ አበባ መሽገው በድሎት በተቀመጡበት ቅድሚያ የሰጡት ለትልቁ ገበታ ነበር? ምርጫው ግልጽ ነበር፡- ለአጼ ሚኒሊክ ለሰሜኑ ተቀናቃኝ ግዛትና ህዝብ ከመቸገር ከሰፋፊና ለም የኢትዮጵያ ግዛቶች መጠቀም፡፡ ለህወሓትም ለሰሜን ከመታገል የመሃል አገር ጸጋን መቋደስ!




የኢትዮጵያን የደለበ የተፈጥሮ ሃብትና ሰፊ የገበያ አቅምን ለመቆጣጠር ሲገዳደሩ የነበሩት የ"ነጻዋ" ኤሪትርያ የህግደፍ ቡድንና ህወሓት-መር የፖለቲካና የቢዝነስ ልሂቃን አንዱ ሌላኛውን ለማደናቀፍ የማይገለብጡት ድንጋይ አልነበረም፡፡ የህወሓት አመራርና የተዛመዱ ቢዝነሶች ከዚህ ወሳኝ ውድድር ኤሪትርያን ለማስወገድ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ለኢትዮጵያም ለትግራይም ከፍተኛ ጉዳት ቢሆንም ኤሪትርያን ከነወደቦቿ በጸበል እንድትርቅ ማድረግ ሆነ፡፡ ይህን በማድረግ የህወሓት ወገን የሆኑ የፖለቲካና የቢዝነስ ልሂቃን ኢትዮጵያንና ትግራይን "የአብራሃም በግ" አድርገው በየዋህነት ዘላቂ መስሎ ለታያቸው ጥቅም ቆሙ፡፡ ሁለቱም አሸናፊ ሊሆኑ ባልቻሉበት ግድድር ሁለቱም ከሳሪዎች ሆኑ፡፡

የሁለቱም ጥቅመኛ ሃይሎች ኪሳራ በነሱ ላይ ብቻ ተወስኖ አልቀረም፤ ኢትዮጵያና ትግራይን ህልውናቸውን ወደሚፈታተን ጥልቅ አዘቅት ከተቷቸው፡፡

የህወሓት ኪሳራ እጅግ የሚዘገንን ሆነ፤ ለኤሪትርያ ግን ለጊዜውም ቢሆን በብልጽግና የኢትዮጵያ ስልጣን መቆጣጠር ከሰማይ ህብስተ-መና ወረደላት፡፡ ህወሓት አጋፋሪ ያልሆነችበት የኢትዮጵያ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ለጉልበታሟ ኤሪትርያ ነጻ ሰፊ ግጦሽ ሆነላት፡፡ ደካማ የሆነ የኢትዮጵያ መንግስትና ኤሪትርያን እንደመሲህ የቆጠረው የአማራ የፖለቲካ ሃይል በኢትዮጵያ ላይ ለኤሪትርያ የሰጧት ገደብ የለሽ ሙብት ጨርሶ ያላለሙችው ነበር፡፡ የኢኮኖሚና ወታደራዊ ጓዳ ጎድጓዳቸውን ለኤሪትርያ ባለስልጣናት ሲያስፈትሹ የኢትዮጵያ ፓርላማ አባላትን የሚያስጎበኙ ይመስሉ ነበር፡፡ የኢትዮጵያና የአማራ ባለሰልጣናት ኤሪትርያ የራሷ የሆነ ብሄራዊ ጥቅም ለማሳደድ ስትል ሰላሳ ሁለት ጥርሶቿን እንደምታሳያቸው ያልተገነዘቡት ጸረ-ማክያቬሊ ፖለቲከኞች በእንጭጭነት “ጠላታቸው” የሆነችውን ህውሓትን ለማጥፋት ልትረዳቸው የመጣች “ቅዱስ ሚካኤል” መሰለቻቸው፡፡ ኤሪትርያ ህወሓትን ለመበቀል ተጠቅማባቸዋለች፡፡

የኤሪትርያው ህግደፍ ህወሓት ለፈረደችበት የሃያ አመት ዝግ የኢትዮጵያና የአማራን ሃይሎችን በመጠቀም መበቀል ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም አዲስ አበባ ላይ ወደ ስልጣን ተመልሳ በኢትዮጵያ ላይ ያገኘውን መልካም አጋጣሚ እንዳታሰናክልበት ከነደጋፊ ህዝቧ ወድቃ እንዳትነሳ ማድረግን አላማው አደረገ፡፡ ኢሳያስ አፈወርቂ በወደብ ጥም ተቃጥለው አርቀው ማየት የተሳናቸውን ኢትዮጵያውያንን የሚያማልለው በውሸት ፍልቅልቅ ፈገግታ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ወያነን ስላላጠፋችና እንዲያውም የባህር በር አክርራ መጠየቅ በመጀመሯ ያ የኢሳያስ አፈወርቂ ፍልቅልቅ ፈገግታ ደብዛው ጠፍቶ በተጨማደደ ፊትና በእረኛ ስድብ ተተካ፡፡ ቅዱስ ጋብቻ እንጂ የአመቺነት ጋብቻ ያስተሳሰረው ግንኙነት የማይዘልቅ መሆኑ የምርመር ውጤት አይደለም የተራው ሰው እውቀት ነው፡፡

ኢትዮጵያ የባህር በር ያስፈልጋታል፤ ይገባታልም፡፡ ሶስት ሚሊዮን የኤሪትርያ ህዝብ አንድ ሺ ኪሎ ሜትር የባህር ዳርቻ ታቅፎ ያለምንም ስራ ሲያባክነው ከማየት የከፋ ፍትህ ማጣት ሊኖር አይችልም፡፡ መቶ ሃያ ሚልዮን ህዝብ ግዙፍ ኢኮኖሚ ይዞ በር ይሁን መስኮት በሌለበት ቤት ወስጥ የሚታፈንበት የትኛው የሞራል እሴት ነው? አለም ለኢትዮጵያ የባህር በር የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

# ምዕራፍ ፪

# በትግራይ የዝሆኖች ፍልሚያ ቀደምት ታሪክ ፲ ፬ ፭ ፺፯ ፹

## 2.1 መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ያለው መረጃ ከሃጎስ ገብረ ዮሃንስ የማስተርስ ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ ተጨምቆና በርካታ ትንተናዎች ታክለውበት የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ መረጃ በዚህ መጽሃፍ እንዲካተት የተፈለገበት አቢይ ምክንያት ያለፈውን የህዝብ ቁስል ለመቅረፍና ለማድማት ሳይሆን ቁስሉ ስላልደረቀና በየዘመኑ እያመረቀዘ የህዝቡ ስቃይ አላባራ በማለቱ ነው፡፡ ስለዚህ ማወቅ ማለቅ ሳይሆን መጠንቀቅ ነው፤ በሽታውን የደበቀ መድሃኒት አይገኝለትምና፡፡ ይህ የትግራይ የፖለቲካ መሪዎች ዘመን የማይሽረው ሽኩቻና መበላላት የማይመለከተውን ምስኪን ህዝብ እየፈጀና እያስፈጀ በመሳፍንቱ ጊዜ አልፏል ሲባል በህወሓት በርካታ ሕንፍሽፍሾች ቀጥሎ እስከ የአሁኑ ጦርነትና ደህረ-ጦርነት ምስቅልቅል ድረስ ዘልቋል፡፡ የትግራይ የመሳፍንት የርስ በርስ ፍልሚያ ታላቁን ጀግና ራስ አሉላንም በልቷል፡፡

የድሮ መሳፍንት እነሱ በተጣሉ ቁጥር እርስ በርስ ስላፋጁት፤ የዘመኑ ፖለቲከኞች ደግሞ ህዝቡን በጎጥ ማለያየት ብቻ ሳይሆን በድህነትና በጥገኝነትም ስላደነዘዙት የነሱን ሽኩታ ተቆጣጥሮ አገሩን በራሱ ማህበራዊ ስርአት ሰላም ያደርጋል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ የመሪዎቹ መራኮት ካቅሙ በላይ ይሆንበትና "ቤቶች ይፈርሳሉ፤ ወጣቶች ያልቃሉ፡ እናቶች ያለቅሳሉ"፡፡ ተስፋ ያጣ ህዝብ "በሃጥያታችን ምክንያት ከላይ የተፈረደብን ነው" እያለ ይህን ሰው ሰራሽ በሽታ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያሸጋግራል፡፡ እንደ አዝማሪውና የውሃ ሙላት ተረት "የሰማው ይሄዳል፤ ያልሰማው ይመጣል"፡፡

## 2.2 ከአጼ ዮሃንስ ህልፈት እስከ አጼ ሚኒሊክ

ከአፄ ዮሃንስ ህልፈት በኋላ ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ሰራዊቱን መርተው ወደ ትግራይ ሲመለሱ የሞቱን ዜና ተከትሎ የህዝብ ትርምስና የመሳፍንቱ የስልጣን ሽኩቻ ተጀመረ፡፡ መተማ ላይ የተዋደቀው አርበኛ ሰራዊትም ብትንትኑ ወጣ፡፡ የራስ መንገሻ የዙፋን ወራሽነት ላይም ስምምነት ጠፋ፡፡ ራስ አልባ የአፄ ዮሃንስ

አስከሬን በክብር በከተማቸው ሳይቀበር፤ ማህዲስቶች ማርከው የወሰዱት የንጉሰ ነገስቱ ራስ ቅልም የት እንደገባ ሳይጠይቁ ነበር ትርምስ የጀመሩት፡፡ በዚህ አዝማሚያቸው ዙፋን ቢወርሱስ ኢትዮጵያን በአግባቡ ያስተዳድሩ ነበረን? ጦር መጣ ሲሉት የሚከንፍ ሰላም ሲሉት የሚተራመስ የማህበረሰብ ስርአት እንኳንና ለሌላው ለራሱም ቢሆን አይበጅም፡፡

በዚህ መልካም አጋጣሚ ንጉስ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን ቻሉ፡፡ ብዙ አመታት በትእግስት የጠበቁት የሸዋ መሳፍንት እርስ በርስ ሳይባሉ ሚኒሊክን አነገሱ፤ ኢትዮጵያንም ባምሳያቸው ቀረጿት፡፡ ከትግራይ መሳፍንት ሽኩቻ ጋር ተደራርቦ ወረርሺኝና ረሃብም ሰፈነ፤ አጼ ሚኒሊክም ዝምታን መረጡ፡፡ “ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ” አይደል የሚባለው? ሚኒሊክ የዋህ ፖለቲከኛ ሆነው ተቀናቃኞቻቸውን በማረጋጋት ሰራ ላይ ይጠመዳሉ ተብሎ አይታሰብም፤ ከማንም ለስልጣኑ ቀናኢ የሆነ የሰው ፍጡር እንደሚጠበቀው እሳቱ ላይ ጋዝ ያርከፈክፋሉ እንጂ፡፡ አልጋው ከመቐለ ተነስቶ አራት ኪሎ ለመዘርጋቱ ግንባር ቀደሞቹ ተጠያቂዎች የትግራይ መሳፍንት ናቸው፡፡



በዚህ ዘመን ትግራይ ሙሉ በሙሉ ነበር የወደመቺው፡፡ አብዛኛዎቹ መንደሮች ከነበሩበት የሉም፤ አገሩን ሽፍታና ወንበዴ ተቆጣጥሮታል፡፡ መሳፍንቱም ራሳቸውን ከመጠበቅና ሲጣሉ ህዝቡን በየጎራቸው እያሰለፉ ከማፋጀት በስተቀር ሽፍታና ወንበዴን የሚቆጣጠሩበት አቅሙም ፍላጎቱም አልነበራቸውም፡፡ የገበሬውን ህይወትና ሃብት የሚቀራመቱት መሳፍንቱም ሽፍቶቹም ነበሩ፡፡ የትግራይ ህዝብ ግን ከአብራኩ የወጡትን የራሱን ጉዶች ትቶ በአጼ ሚኒሊክ ላይ ጣቱን ሲቀስር ነበር፡- “መሳፍንቱን እያጣሉና ይቅር በሉኝ ያለውን ህዝብ የበደለ ሽፍታን ሁሉ እየሾሙና እየሸለሙ” እያለ፡፡ ምኒሊክ “ከጳጳሱ የላቁ ቄሱ” ነበሩን?

አጼ ሚኒሊክ ከትግራይ መሳፍንት በስተቀር ከፍተኛ ስጋት ፈጥሮ የሚቀናቀናቸው አልነበረም፡፡ በደቡብ፤ በምእራብና በምስራቅ የተቆጣጠሩት እጅግ የሰፋ ለም ግዛት ስልጣናቸውን የሚያደረጅ የኢኮኖሚ አቅም ሰጥቷቸው ነበር፡፡ የትግራይ የሚኒሊክ ተቀናቃኞች ድግምት የዞረባቸው ይመስል አቅማቸውን በእርስ በርስ ፍጅትና ቁብ ባልሰጡት ድህነት ሲያዳክሙ አጼ ሚኒሊክ ተረጋግተው በትግራይ ላይ የፖለቲካ ጨዋታቸውን ቀጠሉ፡፡ አጼ ሚኒሊክ በትግራይ ላይ ክንዳቸውን የበለጠ ለማፈርጠም እንዲረዳቸው የወሰዷቸው እርምጃዎች እንደሚከተለው ነበሩ፡-

መጀመሪያ ላይ አጼ ሚኒሊክ የራሳቸው ባለሟል የሆኑትን ደጃች ስዩም ገብረ ኪዳንን የትግራይ የበላይ አስተዳዳሪ አድርገው ሾሙ፡፡ ጊዜ ሳያጠፉ ደጃች ስዩም ገብረ ኪዳን ከሹም ዓጋመ ስብሓት ጋር ህብረት ፈጠሩ፡፡ ሹም ዓጋመ ስብሓት ራስ መንገሻ ዮሃንስን የወጉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ለሚኒሊኩ አዲስ ሹመኛ ሹም ዓጋመ ስብሓት ራስ መንገሻ ዮሃንስን (የዘውድ ተገዳዳሪ) ለማዳከም ጠቃሚ ነበሩ፡፡ ራስ መንገሻ ዮሃንስ የደጃች ስዩምን በትግራይ ላይ መሾምና የደጃች ስዩም ከሹም ዓጋመ ስብሓት ጋር ህብረት መፍጠርን ሰምተው ስጋት ስላደረባቸው ለአጼ ሚኒሊክ እጃቸውን ሰጡና የመላ ትግራይ ነጉስነት ዘውድ ይጭኑልኛል ብለው ተስፋ ሰነቁ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የትግራይ ንጉስ እንዲያደርጓቸው ኤሪትርያ ካሉት ጣልያኖች (የአባታቸው ጠላቶች) ጋርም ሲለሳለሱ ነበር ይባላል፡፡

አጼ ሚኒሊክ ራስ መንገሻ ዮሃንስን ጭራሽ ስላላመኗቸው የትግራይ ንጉስ ሊያደርጓቸው ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ እንዲያውም ራስ መንገሻን በግዞት አንኮበር ላኳቸውና እስከ እለተ ሞታቸው እዛው ቆዩ፡፡ እንዲያው እንደ ትዝብት ለሸዋው ሚኒሊክና ለጎጃሙ ተክለሃይማኖት አምነው ንጉስነት የሰጡት ግን የፖለቲካው በግ የራስ መንገሻ አባት አጼ ዮሃንስ ነበሩ፡፡ “አጼ ዮሃንስ ሞኝ ናቸው፤ እኛም ሁላችን ናቅናቸው፤ ንጉስ ሁኑ ቢሏቸው በመሃሉ ድንበር ጠባቂ ልሁን አሉ”፡፡

ቀጥሎ አጼ ሚኒሊክ ራስ መኮነንን የትግራይ አስተዳዳሪ አድርገው ሾሙ፡፡ በቋፍ ያሉትን የትግራይን መሳፍንት የበለጠ ለማናከስ ራስ መኮነን ዳጃች ገብረሴላሴን በሰሜን-ምእራብ ትግራይ (ዓድዋ፤ አኹሱም፤ ሽሬ) ላይ ሾሙ፤ ዳጃች ገብረስላሴ በራስ መንገሻ ላይ አምጸው የቆዩ ስለሆኑ፡፡ በተጨማሪም ራስ መኮንን ደጃች ተድላ ዋሂድን የወርዒና አምባ አላጀ ጊዜያዊ ምስለኔ፤ ደጃች ሓጎስ ተፈሪን

በዓጋመና በክልተ-አውላዕሎ፤ እንዲሁም ደጃች ተድላ አባጉበንን በእንደርታ፤ በዓዘቦና በአርሆ ላይ ሾሙ፡፡ ቀሪዎቹ የትግራይ መኳንንት ለአዲስ ተሿሚዎች እንዲታዘዙ፤ አለበለዚያ እንደ ወንበዴ እንደሚቆጠሩ የሚያስጠነቅቅ በራስ መኮነን አዋጅ ወጣ፡፡ ይህ በንዲህ እያለ የራያ ዓዘቦ ገዢ ደጃች ጉግሳ አርአያ እንዲሁም የተምቤን ገዢ ደጃች ስዮም መንገሻ አማጽያን ሆነው ነበር፡፡ ራስ መኮነንም በሁለቱ አማጽያን መካከል ጸብ እንዲፈጠር ይጥሩ ነበር፡፡

በኋላ አጼ ሚኒሊክ ራስ ወሌ ብጡልን (ጎንደሬው የእቴጌ ጣይቱ ወንድም) የትግራይ አጠቃላይ አስተዳዳሪ አድርገው ሾሙ፤ ነገር ግን ራስ ወሌ በተሰጣቸው ሹመት ላይ ብዙ አልቆዩም፡፡ አጼ ሚኒሊክ ከራስ ወሌ በኋላ ትግራይን በሶስት ከፈሏት፡- በወርዒ ወንዝና በመረብ ወንዝ መካከል (ዓድዋ፣ አኹሱምና ሽሬ) ለደጃች ገብረስላሴ፤ ተምቤን፣ ኢንደርታ፣ ክልተ-አውላዕሎ፣ ራያ-አዝቦ ለደጃች አብርሃ አርአያ፤ እንዲሁም ዓጋመን ለሹም ዓጋመ ደስታ፡፡ ደጃች ጉግሳ አርአያና ደጃች ስዮም መንገሻ (ሁለቱም የአጼ ዮሃንስ ዙፋን ወራሾች) በአዲሱ ሹመት ተበሳጩ፡፡ ሁለቱም መቐለ ድረስ ሄደው ከደጃች አብራሃ ጋር ገጠሙ፡፡ ደጃች ጉግሳ አርአያ ሲሸነፉ ደጃች ስዮም ሸሽተው ተምቤን ገቡ፡፡ ትግራይን በሙሉ ለመጠቅለል ደጃች ስዮም በየወሩ ነጋሪት እየተጎሰመ ህዝቡን በክተት እያነሳሱ በሶስቱም የሚኒሊክ ሹመኞች ላይ ይዘምቱ ነበር፡፡

የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጆች የሆኑት ደጃች ጉግሳ አርአያና ደጃች ስዮም መንገሻ ደጃች ገብረስላሴን የንግስና ዘር የሌለው ሰርጎ ገብ አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር፤ በተለይ ለደጃች ስዮም መንገሻ ደጃች ገብረስላሴ የመረረ ጠላት ነበሩ፡፡ ደጃች ገብረስላሴ አዲስ አበባ በሄዱበት አጋጣሚ ደጃች ጉግሳና ደጃች ስዮም ወደ ደጃች ገብረስላሴ ግዛት ገብተው ዓድዋን ዘርፈዋት ተመለሱ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ደጃች አብርሃ ሓጎስና ደጃች ሓጎስ ታፈረ ከአመጸኞቹ ጋር የተቀላቀሉት ዓጋመ ለምን ለሹም ዓጋመ ደስታ ተሰጠ ብለው ነበር፡፡ አጼ ሚኒሊክ ለደጃች ገብረስላሴ ብዙ ሺ ሰራዊት ሰጥተው ወደ ትግራይ ላኳቸው፡፡ ደጃች ገብረስላሴም በደጃች ጉግሳ አርአያና በደጃች ስዮም መንገሻ ወደ ተዘረፈው ዓድዋ ከተማቸው ያለ ምንም ችግር ገቡና ከአማፂያኑ ጋር የሰላም ድርድር ጀመሩ፡፡

ደጃች ስዩም ከደጃች ገብረስላሴ ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ ሄደው ለአጼ ምኒሊክ ታማኝነታቸውን ገለጹ፡፡ በለውጡ አጼ ምኒሊክ ለደጃች ስዩም የክልተ-

አውላዕሎ ገዢነት ሰጧቸው፤ ተምቤንና አበርገለንም ከደጃች አብርሃ ነጥቀው ጨመሩላቸው፡፡ ደጃች አብርሃ እንደርታንና እንዳ-መኾኒን ብቻ ይዘው ቀሩ፡፡ አጼ ምኒሊክ ገረዓልታን ለራስ ጉግሳ በርስትነት ሰጧቸው፡፡ አባታቸው አንኮበር በእስር ላይ እያሉ ቢሞቱባቸውም ደጃች ስዩም እስከ መጨረሻው ለአዲስ አበባው ማእከላዊ መንግስት ታማኝ አገልጋይ ሆነው ቀሩ፡፡ ደጃች ስዩም ለማእከላዊ መንግስት በማደራቸውም የደጃች ጉግሳ አርአያን ቁጣ ጋበዘ፡፡ ከዛ ወዲህ የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑት የደጃች ስዩምና የደጃች ጉግሳ ፉክክር ለቀጣዮቹ ብዙ አመታት ትግራይን ሲያምስ ኖረ፡፡

የአጼ ዮሃንስ አልጋ ወራሽ ራስ መንገሻ ዮሃንስ አንኮበር በእስር ላይ እያሉ ከሞቱ በኋላ በትግራይ ጎልተው የወጡት ተቀናቃኞች የሚከተሉት ነበሩ፡- ደጃች ገብረስላሴ ባርያጋብር፤ ራስ ስብሓት አረጋዊ፤ ደጃች ጉግሳ አርአያ፤ ደጃች አብርሃ አርአያና ደጃች ስዩም መንገሻ፡፡ አምስቱም የትግራይ የበላይ አስተዳዳሪ ሆነው እንዲሾሙ ማእከላዊ መንግስትን ለማሳመን ከፍተኛ ፉክክር ውስጥ ገቡ፡፡ ከአምስቱ ተቀናቃኞች መካከል ደጃች ገብረስላሴ ከአጼ ሚኒሊክ ጋር ጥብቅና ዘላቂ የሆነ ግንኙነት ፈጠሩና ከአጼ ሚኒሊክ የታመኑ ሹመኞች አንዱ ሆኑ፡፡ አጼ ሚኒሊክ ለደጃች ገብረስላሴ የነበራቸውን ቀረቤታ ለመግለጽ የእህታቸውን ልጅ ድረው በሰሜን ትግራይ ውስጥ ርስተ-ጉልት ሰጧቸው፡፡ ደጃች ገብረስላሴ የጣልያንኛን ቋንቋ አሳምረው የሚችሉና በጣልያኖችም በሚኒሊክም የሚወደዱ ስለነበሩ የትግራይ መሳፍንት (በተለይ ደጃች ጉግሳና ደጃች ሰዩም) ይቀኑባቸው ነበር፡፡ ደጃች ጉግሳ አርአያ በደጃች ስዩም መንገሻ ወደ ሚኒሊክ መከዳት ቢበሳጩም አመጻቸውን ግን ለጊዜውም ቢሆን ገታ አድርገውት ነበር፡፡

ደጃች ጉግሳ ከደጃች ገብረስላሴ ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ ሄደው ከአጼ ሚኒሊክ ጋር ሰላም ፈጠሩ ተብሎ ይነገራል፡፡ ሆኖም አጼ ሚኒሊክ ደጃች ጉግሳን በራስ ደምስ ስር ሆነው አውራጃ እንዲያስተዳድሩ ወደ ወሎ የግዞት ያህል ላኳቸው፡፡ ከብዙ አመታት በኋላ የተመለሱትም በእንጀራ እናታቸው በንግስት ዘውዲቱ ነበር፡፡ ንግስት ዘውዲቱ ደጃች ጉግሳን በራያ ዓዘቦና ቦራ ስላዋ ላይ ሾመው የራስነት መአርግ ሰጧቸው፡፡ ከዛ ጊዜ ጀምሮ ደጃች ጉግሳ የንግስት ዘውዲቱ ታማኝ አገልጋይ ሆነው ዘለቁ፡፡ ልጅ እያሱን ይዘው በማስረከባቸውም የላቀ ታማኝነት አግኝተው የልኡልነት መአርግ ተደረበላቸው፡- ልኡል ራስ ጉግሳ!

ደጃች አብርሃ ለአጼ ሚኒሊክ አድረው በተምቤን፤ በእንደርታና በእንዳ መኾኒ ላይ ከተሾሙ በኋላ ደጃች ሰዩምንና ደጃች ጉግሳን ሲያሳድዱ ነበር፡፡ ደጃች ሰዩምንና ደጃች ጉግሳን ከማሳደድ አልፈው በህዝብ ላይ ቀጥተኛ የሆነ በደል መፈጸም ጀመሩ፡፡ እርስ በርሳቸው በተጣሉ ቁጥር ህዝቡ በማይመለከተው እርስ በርሱ ሲተላለቅ የነበረበት ግፍ ሳያንስ ደጃች አብርሃ "የላም ጅራት" የሚባል በያንዳንዱ ላም የሚከፈል ቀረጥ ደነገጉ፡፡ ከታክሱ የሚገኘው ገቢ መቐለ ውስጥ ትልቅ ቤተመንግስት ለማስገንባት የሚውል ነበር፡፡ ትግሃት እንደተረከው ለዚህ ቤተመንግስት ግንባታ ህብረተሰቡ በግዳጅ የጉልበት ሥራ በመስራትና የግንባታ ቁሳቁሶችን በማዋጣት፤ በተለይም ቤተ መንግሥቱ የቆመበት ከፍ ያለ ቦታ በሕዝብ ጉልበት የተስተካከል ነው፡፡ ለጣሪያውና ለበሮች የሚሆን የወይራ እንጨትም ከዴሴኣ ጫካ በእግር ለሁለት ሳምንታት ያህል ተጓጉዟል፡፡

የዓጋመና ክልተ አውላዕሎ ህዝብ የደጃች አብርሃ "የላም ጅራት" ታክስን አንከፍልም አሉ፡፡ ደጃች አብርሃ የአጽቢ ደራን ህዝብ (ክልተ አውላዕሎ) ከባድ የሆነ የገንዘብና የአካል ቅጣት ጣሉበት፡፡ ይህን የሰሙት አጼ ሚኒሊክ በደጃች አብርሃ ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ቅጣት ጣሉ፡፡ አጼ ሚኒሊክ በደጃች አብርሃ ድርጊት ከመቆጣታቸው የተነሳ ከስልጣናቸው ያነሏቸዋል ተብሎ ስለተሰጋ እንደርታ ውስጥ የሚኖሩ የደጃች አብርሃ ደጋፊዎች በአጼ ሚኒሊክ ላይ እንዲያምጹ በሙግሳ ግጥሞች ያደፋፍሯቸው ነበር፦ ከደግ ባዳ የራስ ገዳይ፤ አጼ ሚኒሊክ ግራ ገባቸው፡፡ ህዝቡን ሲረሱ ወቀሳ ህዝቡን ሲይስታውሱም አመጽ!

አጼ ሚኒሊክ በሞት አፋፍ ላይ በነበሩበት ጊዜ እቴጌ ጣይቱ የፈለጉት እንዳሻቸው የሚዘውሯትን ዘውዲቱን እንዲያነግሱላቸው ነበር፤ አጼ ሚኒሊክ ደግሞ በተቃራኒው የወሰኑት ልጅ እያሱ እንዲወርሳቸው ነበር፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል በተፈጠረው የስልጣን ግድድር እቴጌ ጣይቱ ልቀው ሲታዩ የነበር ቢሆንም መንግስትን በአግባቡ የሚመራ አንድ ጠንካራ ሰው አልነበረም፡፡ ይህ ሁኔታ ለትግራይ መሳፍንት ዙፋኑን መልሰው ለመውሰድ አመቺ ነበረ፡፡ ሆኖም አጼ ሚኒሊክ ቀድመው የትግራይን መሳፍንት ሽባ አድርገዋቸው ነበር፡፡ እስከ እለተ ሞታቸውም የማዳከሙን ሰራ ቀጠሉበት፡፡ ለምሳሌ፤ አጼ ሚኒሊክ ባደረጉት የመጨረሻው ሹምሽር ደጃች አባተ ቧያለው ዋግ ሹም ሆነው የትግራይ ጠቅላይ ገዥም እንዲሆኑ ሾሙ፡፡

ራስ ስብሓት ከሃረር አስር አመት እስር ተለቀው በእቴጌ ጣይቱ ዓጋመ ላይ ተሾሙ፡፡ አሁን ትግራይ በደጃች አባተ ስር በሆኑ በደጃች አብርሃ፤ በደጃች ገብረሰላሴና በራስ ስብሓት ምክትል ገዢነት ተከፋፈለች፡፡ ቀጥሎ ሁሉም የትግራይ ገዢዎች፤ ደጃች ስዩምን ጨምሮ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው አልጋ ወራሽ ማን እንደሆነ ከአጼ ሚኒሊክ ተነገራቸው፡፡ ደጃች አብርሃ ብቻ ተቃውሞ አቀረቡ፡፡ ያቀረቡት ተቃውሞ ግን ስለ ዙፋኑ ሳይሆን የደጃች አባተ በትግራይ ላይ መሾም ነበር፡፡ እንዲህ የሚሉት በአጽቢ ደራ ህዝብ ላይ የፈጸሙትን ግፍ አጼ ሚኒሊክ የረሱት ወይም ይቀር ያሏቸው ስለመሰላቸው ይመስላል፡፡ ደጃች ገብረስላሴ አዲስ አበባ ሲቀሩ ደጃች አብርሃ ለደጃች አባተ ትግራይ ላይ አቀባበል አዘጋጃለሁ ብለው ወደ መቐለ ተመለሱ፡፡ ደጃች ስዩምም ቀጥለው ወደ ትግራይ (ተምቤን) ተመለሱ፡፡ ደጃች አብርሃ ወደ ትግራይ የተመለሱት ግን ለደጃች አባተ አቀባበል ለማድረግ ሳይሆን ደጃች አባተ ወደ ትግራይ እንዳይገቡ ለመከልከል ነበር፡፡ ደጃች አብርሃ ከራስ መንገሻ ዮሃንስ ሞት በኋላ የአጼ ዮሃንስ ቅርብ ወራሽ ያለሁት እኔ ነኝ በሚል የትግራይ ጠቅላይ ገዢ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ አሉ፡፡

አጼ ዮሃንስ ግን የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት እንጂ የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ሆነው አይውቁም ነበር፡፡ ደጃች አብርሃ ደጃች አባተ ላይ "ትግራይ ዋግን ትገዛለች እንጂ ዋግ እንዴት ትግራይን ትገዛለች" እያሉ ይዘባበቱ ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ ደጃች አብርሃ ደጃች አባተ የሳቸውን ቦታ መያዝ እንደሌለባቸው ወስነው ከራሳቸውም ወገን በቂ ድጋፍ ሳያገኙ ኮረም ላይ ዘግተው ውጊያ ከፈቱ፡፡ ቀሪዎቹ የትግራይ መኳንንት ምንም እንኳ በደጃች አባተ ውክልና በትግራይ ላይ የሸዋ አገዛዝን አምርረው ቢጠሉም ከደጃች አብርሃ ጋር ሆኖ ደጃች አባተን መውጋት የተቀበሉት ጉዳይ አልነበረም፡፡ ህዝቡም በደጃች አብርሃ ታክስና ቅጣት ቂም ስላደረበት ወደዚህ ውግያ ሊከተላቸው ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ይህ በትግራይ አገር-በቀል ገዢዎች ላይ ብዙም ያልተለመደ ህዝባዊ እምቢተኝነት ነበር፡፡

በኮረሙ ፍጅት የበዛበት ውጊያ ራስ ስብሓት ከደጃች አባተ ወገን ሆነው ነበር፡፡ ደጃች ስዩም ከተምቤን ደጃች አባተን እንዲያግዙ ቢታዘዙምንና ምንም እንኳ ደጃች አብርሃ ከዚህ ቀደም ስላሸነፏቸው ቂም ቢቋጥሩም ወደ ውጊይው ሳይገቡ አሸናፊው እስኪለይ ድረስ እየጠበቁ ነበር፡፡ ደጃች አባተ አሸነፉ፤ ደጃች አብርሃ ተማርከው ታሰሩ፡፡ ደጃች ስዩም ከደጃች አባተ ጋር ተገናኙ፡፡ ደጃች ስዩም ከደጃች አባተ ጎን ሆነው ባይዋጉም የደጃች አብርሃ ግዛት የበረው እንደርታ

በተጨማሪነት ተሰጣቸው፡፡ ራስ ስብሓት ከደጃች አባተ ጎን ሆነው ስለተዋጉና ደጃች አብርሃን ማርከው ስላስረከቡ የዓጋመ ሹመታቸው ጸድቆ እንዲቀጥሉ ተፈቀደላቸው፡፡ የደጃች አባተ የኮረም ድል ሰልጣኑን የተቆጣጠሩት እቴጌ ጣይቱን አስገንግጦ ነበር፡፡ ደጃች አባተ የአጼ ሚኒሊክ ታማኝና በሸዋ መኳንንት ዘንድም ተወዳጅ ነበሩ፡፡ ንግስቲቱ የትግራይ ጠቅላይ ገዥ እንዲሆኑ የፈለጉት ከፍተኛ አቅም የነበራቸውና የሚፈሯቸው ደጃች አባተን ሳይሆን ወንድማቸው ራስ ወሌ ብጡል በድጋሚ የትግራይ ጠቅላይ ገዥ እንዲሆኑ ነበር፡፡ የሚኒስትሮች ምክርቤቱንም በማባበል ደጃች አባተን ሽረው ራስ ወሌ የትግራይ ገዥ እንዲሆኑ አስወሰኑ፡፡

ራስ ወሌ ግን ሹመቱን አልተቀበሉም፤ የፊተኛው ሹመታቸው ችግር ፈጥሮባቸው ስለነበረ፡፡ በተጨማሪም ደጃች ገብረስላሴ ከሰሜን ትግራይ ግዛቶች እንዲሻሩ በመደረጉ ሁለቱም ተሻሪዎች ህብረት ፈጠሩ፡፡ ደጃች አባተ የሆነውን ነግረው ለሸዋ መኳንንት አቤቱታ በማቅረባቸው የሸዋ መኳንንትና የእቴጌ ጣይቱ የስልጣን ሽኩቻ ተባባሰ፡፡ አጼ ሚኒሊክ የሚፈለጉት አልጋ ወራሽ ልጅ እያሱ፤ የሱ ሞግዚት ሆነው የተመደቡት ራስ ተሰማ፤ የትግራዩ ደጃች ገብረስላሴ፤ ከሸዋ መኳንንት ጋር በአንድ ወገን፤ ሰልጣኑን በጉልበት ጠቅልለው የያዙት እቴጌ ጣይቱ በተቃራኒ ወገን፡፡ እቴጌ ጣይቱ ዙፋኑን ወደ ጎንደር ለመውሰድ ዘመዶቻቸውን በሹም ሽር እያጠናከሩ ነበር፡፡ እቴጌ ጣይቱን ያስፈራቸው “ከትግራይ የመጣ ሰው የሚኒሊክን ዙፋን ይወርሳል” የሚል ውስጥ ለውስጥ የሚናፈስ ትንቢት መኖሩ ነበር፡፡ በዚህም የጠረጠሩት ደጃች ገብረስላሴን ስለነበር ጠምደው ያዟቸው፡፡

በዚህም ሰበብ እቴጌ ጣይቱ ደጃች ገብረስላሴን ከሁሉም የትግራይ ግዛቶቻቸው አንስተው ዓድዋ ላይ የወልቃይቱን ደጃች ኪዳነ ማርያምን ሾሙ፡፡ ደጃች ገብረሰላሴ የሸዋን መኳንንት (ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ፤ ራስ ደምሴ) የሚኒሊክ ቃል እየተሻረ ነው በሚል በቴጌ ጣይቱ ላይ አነሳሱ፡፡ ሹም ሽር የልጅ እይሱ ስልጣን እንጂ የእቴጌ ጣይቱ አይደለም፤ የእቴጌይቱ ዋና ተግባር አጼ ሚኒሊክን ማስታመም ነው ተባለ፡፡ ይህ ሲነገራቸው እቴጌ ጣይቱ ከደጃች ገብረስላሴ ጋር ስድድብ ገጠሙ፡፡ እቴጌ ጣይቱ ለደጃች ገብረስላሴ፡- “ሸዋ አይደለህም አንተ ምን አግብቶህ ነው?”፤ ደጃች ገብረስላሴ ለእቴጌ ጣይቱ፡- “አዲስ አበባ የተወለደ የለም፡፡ ሁላችንም ሚኒሊክ ናቸው ያመጡን”፤ እቴጌ ጣይቱ ለደጃች

ገብረስላሴ፡- 'እረኛ ነህ!" አሏቸው፤ ደጃች ገብረስላሴ ለእቴጌ ጣይቱ፡- "ሚኒሊክ ባያመጡን ሁላችንም እረኞች ነበርን"፡፡

በሸዋና በትግራይ መኳንንት በተቀነባበረ መፈንቅል እቴጌ ጣይቱ ከመንግስት ስራ ተወግደው አጼ ሚኒሊክን የመንከባከብ ስራ ብቻ እንዲሰሩ ተደረገ፡፡ የመንግስት ስራ የልጅ እያሱና የሞግዚቱ ራስ ተሰማ ሃላፊነት ሆነ፡፡ ከዛ ቀጥሎ የትግራይ ሁኔታ እንደሚከተለው ሆነ፡- ራስ ወልደጊዮጊስ በበጌምድርና በትግራይ ላይ ተሾሙ፡፡ ከራስ ወልደጊዮርጊስ ስር፡- ራስ ስብሓት (የዓጋመ ገዥ)፤ ደጃች ገብረስላሴ (የዓድዋ፤ ሽሬ፤ ተምቤን፤ ሓራማት፤ እንደርታ፤ ክልተ አውላዕሎ፤ ገረዓልታ ገዥ)፤ ደጃች ጉግሳ (የአበርገለ፤ ቦራ ስላዋ ገዥ)፤ ደጃች አበራ ተድላ (የእንዳ መኾኒ፤ ወጀራት፤ ዓዘቦ ገዥ)፤ ከኮረም ጦርነት በኋላ ደጃች ጉግሳና ደጃች ሰዩም በትግራይ ላይ ሁለት ዋና ሃይሎች ሆነዋል፡፡ ራስ ስብሓት ከሞቱና ደጃች ገብረስላሴ ከተሸነፉ በኋላ ደጃች ስዩም ለጊዜውም ቢሆን በትግራይ ላይ ብቸኛ ገዢ ሆነው ቆዩ፡፡

ልጅ እያሱ ለዘውድ መድፋት ስነስርአት ሁሉም ወደ ደሴ እንዲመጡ በመጋበዛቸው ደጃች ስዩምም ተገኝተዋል፡፡ ደጃች ገብረስላሴና ራስ ስብሓት በዓጋመ ግዛት ላይ መገፋፋታቸውን ቀጠሉ፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ከሌሎቹም ጋር በነበራቸው ጸብ ከወዳጆቻቸው (አስመራ ከነበሩት ጣልያኖች) ብዙ ሺ መሳሪያ እንደተቀበሉ ተነግሯል፡፡ ተቀናቃኞቻቸውም ይህን አደገኛ ደርጊት ነው እያሉ ለማእከላዊ መንግስት ይከሷቸው ነበር፡፡ ጣልያኖች ራስ ስብሓትን እንደጠላት ይቆጥሯቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ለጣሊያኖች ደጃች ገብረስላሴን በራስ ስብሃት ላይ ማስነሳት ጠቃሚ ነበር፡፡ ደጃች ገብረስላሴ በዓድዋው ጦርነት የጣሊያን ወታደር ሆነው ኢትዮጵያን ወግተዋል፡፡ ከድል በኋላም ለአጭር ጊዜ ታስረው ወደ ሹመት ተመልሰዋል፡፡ በርግጥ ልጅ እያሱም ቢሆን የጣሊያኑን ተወካይ ትግራይን እንዲያረጋጋላቸው ለምነውታል ይባላል፡፡

### 2.3 ከአጼ ሚኒሊክ ህልፈት እስከ አጼ ሃይለሰላሴ

አጼ ሚኒሊክ ካረፉ በኋላ ልጅ እያሱ አባቱ ራስ ሚካኤልን የትግራይ የበላይ ገዢ ለማድረግ እንዳሰበ ደጃች ገብረሰላሴ ሰሙ፡፡ ይህንንም መረጃ ለራስ ስብሓትና ለደጃች ስዩም ነገሯቸው፡፡ ደጃች ገብረሰላሴ ከራስ ስብሓትና ከደጃች ስዩም ጋር በመሃላ ህብረት ፈጠሩ፡፡ ህብረቱን የፈጠሩት ከትግራይ ውጪ ሌላ ጠቅላይ ገዢ

እንዳይመጣባቸው ብቻ ሳይሆን የአጼ ዮሃንስን ዙፋን ለመመለስም ያቀደ ነበር፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ደጃች ስዩም የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ሆነው ሁለቱ (ራስ ስብሓትና ደጃች ገብረስላሴ) ከበታች እንዲሆኑ ሃሳብ አቅርበው አሳመኑ፡፡ ለዚህ ማስፈጸሚያም ደጃች ገብረስላሴ ከጣልያኖች መሳሪያ እንደሚያመጡ ቃል ገቡ፡፡ ውሉና መሃላው እንዳለ ሆኖ ራስ ስብሃት ግን ሲያሰሉ የነበሩት በምን ዘዴ ደጃች ገብረስላሴን እንደሚጎዱ ነበር፡፡ ህብረት የፈጠሩበትን ጉዳይ በሚመለከት ደጃች ገብረሰላሴ ለራስ ስብሓት የላኩላቸውን ደብዳቤ ራስ ስብሓት ወደ ማእከላዊ መንግስት በመላካቸው ራስ ሚካኤል ስለአመጹ ሰሙ፤ ሚስጢሩም ይፋ ሆነ፡፡ ራስ ስብሓት የደጃች ገብረስላሴን ደብዳቤ ለማእከል መላካቸው የተጋለጠው አንድ የደጃች ገብረስላሴ ወዳጅ የሆነ ሰው ደብዳቤውን ከጥያቄ ጋር መልሶ ለደጃች ገብረስላሴ ስለላከላቸው ነው፡፡

ከዛ ቀደም ሁለቱም አዲስ አበባ እያሉ ራስ ስብሓት በደጃች ገብረስላሴ ላይ ጥቃቶች ፈጽመዋል፡- ራስ ስብሓት ደጃች ገብረስላሴን፡- "ካንተና ከኔ መኮነንነት የማን እንድሚበልጥ ትግራይ ላይ ይለያል"፤ ራስ ስብሓት ለራስ ሚካኤል፡- "ደጃች ገብረሰላሴ የሚዎድዎት ቢሆን ኖሮ ልጅን ያገባ ነበር፤ ደጅች ገብረስላሴ ኤሪትርያ ምድር ውስጥ ከጣልያኖች ጋር ተገናኝቷል፤ ደጃች ገብረስላሴ ለኔ (ራስ ስብሓት) እና ለደጃች ስዩም "አጼ ሚኒሊክ ከሞቱ በኋላ ሸዋ ሊገዛን አይገባም" ብሎናል፤ ለደጃች ስዩምም የፈለግኸውን ያህል ጠመንጃ እሰጥሃለሁ ብሏቸዋል"

ደጃች ገብረስላሴ ለደጃች ስዩም እንዲህ አሏቸው፡ "እኔ በምእራብ ትግራይ ራስ ወልደጊዮርጊስን እወጋለሁ፤ አንተ ደግሞ በደቡብ ትግራይ፤ ከሁለታችን በህይወት የተረፈ ይነግሳል"፡፡ ደጃች ስዩም በጉዳዩ ላይ ከራስ ስብሓት ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ደጃች ገብረስላሴን ብቻቸውን አስቀሯቸው፡፡ ራስ ሚካኤል የሶስቱም የትግራይ ገዢዎች ስምምነት እንደሰሙ ለደጃች ስዩም ደብዳቤ ላኩ፡- "ሁለታችንም የአጼ ዮሃንስ ልጆች ነንና የኔን የወሎና የትግራይ ጠቅላይ ገዢነትን ተቀበል፤ ለዚህም ልጄን እሰጥሃለሁ"፡፡ ደጃች ስዩምም ይህን ተቀብለው ከራስ ስብሓት ጋር በመነጋገር በደጃች ገብረስላሴ ላይ ውግዘትን አስተላለፉ፡፡ ደጃች ገብረሰላሴ ለልጅ እያሱና ለራስ ሚካኤል ያላቸውን ታማኝነት አረጋግጠው በተከሰሱበት ጉዳይ ላይ ማብራሪያ ለመስጠት አዲስ አበባ እንዲመጡ ጠየቁ፡፡

በጠየቁት መሰረት ልጅ እያሱ እንዲመጡ አዘዟቸው፡፡ በጎን ራስ ሚካኤል ለራስ ስብሓት ልከው “ደጃች ገብረስላሴ አዲስ አበባ የሚሄደው እኔን ለመውጋት ነውና እንዳታሳልፈው” ብለው አዘዙ፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ይህን ሲሰሙ መቅረት ወሰኑና “ራስ ስብሓት በሌለሁበት ግዛቴን ይቀማል” የሚል ምክንያት ሰጡ፡፡ በተጨማሪም ጣሊያንን የመሳሪያ እርዳታ ጠየቁ፡፡ ልጅ እያሱ የጣልያኑን ተወካይ ደጃች ገብረስላሴ አዲስ አበባ እንዲመጡ እንዲያሳምንላቸው ጠይቀው ነበር፡፡ ደጃች ገብረስላሴ አዲስ አበባ የመሄድ ጫናው ሲበዛባቸው መንገድ ጀመሩ፡፡ ሆኖም ድጃች ስዩም፤ ራስ ስብሓት፤ ደጃች አበራ፤ ፊታውራሪ ግርማይ፤ ሹም ተምቤን ማሩ የደጃች ማሩ ግዛት የሆነውን ሓውዜንን ወረሩና ዓድዋም ድረስ እንደሚሄዱ አስፈራሩ፡፡

ደጃች ገብረስላሴ ግዛታቸውን ሊጠብቁ ቢመለሱ ከማእከል ጋር የበለጠ ተካረሩ፤ ከአዲስ አበባ ወደ ደጃች ገብረስላሴ ቴሌግራም ሲላክ በመቆረጡ ራስ ስብሓት “ደጃች ገብረስላኤ ነው የቆረጠው” በሚል ለውንጅላ ተጠቀሙበትና ደጃች ገብረስላሴ በይፋ እንደ አመጻኛ ተቆጠሩ፡፡ ማእከላይ መንግስት ደጃች ስዩም፤ ራስ ስብሓት፤ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ (የጎንደር ገዢና የደጃች ገብረስላሴ ሚስት አባት) ደጃች ገብረሰላሴን አስገድደው አዲስ አበባ እንዲሰዱ ታዘዙ፡፡ ደጃች ገብረስላሴም “ከነኩኝ ትግራይ ትገላባበጣለች” ብለው ፎከሩ፡፡ ጫና ሲበዛባቸው ደጃች ገብረስላሴ በጣሊያኑ ተወካይ ሽምጋይነት ወደ አዲስ አበባ መንገድ ሲጅምሩ ራስ ስብሓት ማንም ሳይፈቅድላቸው በራሳቸው ውሳኔ የደጃች ገብረስላሴን ግዛት ሲወሩ ደጃች ገብረስላሴ ራስ ስብሓትን በውጊያ ገደሏቸው፡፡

ቀጥሎ ደጃች ስዩም ደጃች ገብረስላሴን በውጊያ አሸነፏቸው፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ስላልተያዙ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከጎንደር ሄደው እንዲይዟቸው ታዘዙ፡፡ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ዓድዋ ሲገቡ ደጃች ገብረስላሴ መረብ ተሻግረው ኤሪትርያ ከጣልያኖች ዘንድ ተደበቁ፡፡ ደጃች ስዩም ደጃች ገብረስላሴን በማሸነፋቸው ለማእከላዊ መንግስት እፎይታን ፈጠሩ፡፡ በለውጡም የራስ ስብሓትና የደጃች ገብረሰላሴ ግዛቶች እንዲሰጣቸው ተስፋ ሰነቁ፡፡ ደጃች ስዩም ከማእከላዊ መንግስት ጋር ከመጣላት ይልቅ አብሮ በመስራት እንደሚጠቀሙ ስለተረዱ ግንኑነታቸውን አጠናከሩ፡፡ ማእከላይ መንግስት የራስ ወልደ ጊዮርጊስ የትግራይ ቆይታ የወደደው አይመስልም፤ የልጅ እያሱን ዙፋን ይቀናቀናሉ የሚል ስጋት ስለነበር፡፡ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከዓድዋ ወጡ፤ ራስ ሚካኤል የወሎ፤ የትግራይና

የቤጌምድር ንጉስ ሆኑ፡፡ ንጉስ ሚካኤል ደጃች ስዩምን የራስነት መአርግ ሰጥተው ከስራቸው የትግራይ ገዥ አደረጓቸው፡፡ ራስ ስዩምም በበኩላቸው ሹመቶችን ሰጡ፡- ደጃች ካሳ ስዩም አባ ይላቅ (ልጃቸው) ዓድዋ፤ ደጃች ግርማይ መንገሻ (ወንድማቸው) ተምቤን፤ ደጃች ካሳ ስብሓት ዓጋመ፡፡

ልጅ እያሱ ከዙፋን ተወግደው፤ ነጉስ ሚካኤልም ተሸንፈው ዘውዲቱ በራስ ተፈሪ ሞግዚትነት ነግሱ፡፡ ልጅ እያሱ ሸፍተው ያሉበት አልታወቀም፡፡ ራስ ስዩም ከንጉስ ሚካኤልና ከልጅ እያሱ ጋር ቤተሰብ ስለነበሩ ከልጅ እያሱ ጋር ይወግናሉ ተብለው ስለተጠረጠሩ የእቴጌ ዘውዲቱ አማካሪዎች ደጃች ገብረስላሴን ከተደበቁበት ኤሪትርያ ወደ አዲስ አበባ አስመጧቸው፡፡ ይህን ያደረጉት በራስ ሰዩም ምትክ የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ሊያደርጓቸው ስላሰቡ ነበር፡፡ ራስ ስዩም ይህን ሲሰሙ አዲስ አበባ ድረስ ሄደው ለንግስት ዘውዲቱ ታማኝነታቸውን ገለጹ፡፡ አዲስ አበባ ላይ በራስ ሰዩም፤ ደጃች ገብረስላሴና ደጃች ካሳ ስብሓት ላይ እርቅ ወርዶ ተስማሙ፡፡ ለደጃች ገብረስላሴ በትግራይ የቀድሞ ግዛታቸው ሲመለስላቸው አዲስ አበባ ተቀምጠው ጣልያን አገር በተማረ ልጃቸው በውክልና ያስተዳድሩት ነበር፡፡ ለሳቸው ሲያደርግ እንደነበረው ለልጃቸውም ድጋፍ እንዲያደርግ የጣልያን መንግስትን ተማጸኑ፡፡

ደጃች ግርማይ መንገሻ፤ ሹም ዓጋመ ካሳና ብላታ ወልደሚካኤል (ቴሌግራም ኦፐሬተር) የደጃች ገብረስላሴ ወደ ሹመት መመለስና የልጃቸውን ውክልና አልተቀበሉትም፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ዓድዋ ለነበሩት ታማኞቻቸው ፊታውራሪ ተድላና ደጃች ሃይሉ መልእት እየላኩ ስለሁኔታው ይጠይቁ ነበር፡፡ ደጃች ተክለሃይማኖት ዓድዋ ደርሰው የአባታቸውን ታማኝ ሹሞች አግኝተው ስልጣናቸውን ለማደላደል እንደሚረዷቸው ቃል ገቡላቸው፡፡ ራስ ጉግሳና ደጃች ግርማይ ባይቀበሉትም ሹም ዓጋመ ካሳ ከደጃች ገብረሰላሴ ጋር እርቅ ፈጥረው ነበር፡፡ የደጃች ገብረስላሴ ወዳጅ ደጃች አበራ በማእከላዊ መንግስት አማካይነት የአዘቦ እንዳመኾኒ ሹመታቸውን አስመለሱ፡፡ ይህ ድርጊት ራስ ጉግሳን አስቆጣ፤ ከግዛታቸው ስለተቆረሰ፡፡ ደጃች ተክለሃይማኖት በመሞታቸው ደጃች ገብረሰላሴ ራሳቸው ወደ ዓድዋ ግዛታቸው ሄዱ፡፡ ከራስ ስዩም ጋርም በጋብቻ ተሳሰሩ፡፡ በራስ ጉግሳ እየተመሩ ደጃች ተክሉ፤ ደጃች ግርማይና ሹም ተምቤን ገብረመድህን ደጃች ገብረስላሴን በበርካታ የማእከላዊ መንግስት ከህደቶች ይከሷቸው ነበር፡፡ ከክሶቹ መሳሪያ ከጣሊያን መቀበል አንዱ ነበር፡፡

ደጃች ገብረስላሴ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ወደ ጎጃም በግዞት ተላኩ፡፡ ከተለቀቁ በኋላም በሞት ተለዩ፡፡ ልጅ እያሱ ከዙፋን ተወግደው ብዙ ቦታ ከዞሩና ከተዋጉ በኋላ ከእህታቸው ባል ከራስ ስዩም ዘንድ ሄደው ተደበቁ፡፡ ራስ ስዩምም በሚስታቸው ወንድምና በማእከላዊ መንግስት መሃል አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ፡፡ የራስ ስዩም ተቀናቃኞች ራስ ጉግሳና ደጃች ገብረስላሴ በራስ ስዩምና በልጅ እያሱ ላይ እርመጃ እንዲወሰድ ወተወቱ፡፡ የራስ ስዩም ጠላት የነበረችው ጣልያንም በራስ ስዩምና በልጅ እያሱ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ገፋፋች፡፡ ደጃች ገብረስላሴ በራስ ስዩም ላይ የተነሱት በትግራይ ላይ የራስ ስዩምን የትግራይ ገዢነት ሹመት ለመቀማት ነበር፡፡ ደጃች ገብረስላሴ ማእከላዊውን መንግስት ሳያስፈቅዱ በጣሊያን (አስመራ) በኩል መልእክተኞች ልከው የትግራይ ህዝብ በራስ ስዩም ላይ አምጾ ከራስ ተፈሪ ጋር እንዲወገን ጥሪ አቀረቡ፡፡

ልጅ እያሱ ራስ ስዩም ይደራደሩብኛል ብለው ስለፈሩ የራስ ስዩምን ግዛት ለቀው ወደ ራስ ጉግሳው ቦራ ስላዋ ሄደው ተደበቁ፡፡ ራስ ጉግሳ ልጅ እያሱን ይዘው ለራስ ተፈሪ ለማስረከብ ፈለጉ፤ የራስ ስዩምን ስልጣን ለራሳቸው እንዲሰጣቸው፤ ለራስ ጉግሳ ከአዲስ አበባ ተጨማሪ ሃይል ሲላክላቸው ልጅ እያሱን አስረው አስረከቡ፡፡ በአዲስ አበባም ፈንጠዝያ ሆነ፡፡ ራስ ተፈሪ አሁንም ልጅ እያሱን ሊያስፈቱ ይሞክራሉ ብለው ራስ ስዩምን ስለፈሯቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት አሰልፈው አሳዩ፡፡ የራስ ሰዩምን የትግራይ ሹመታቸውን ገፈው አዲስ አበባ ወስጥ ለአመታት አቆዩአቸው፡፡ ራስ ተፈሪ ከራስ ሰዩም ግዛቶች (እንደርታ) ቀምተው ለራስ ጉግሳ ሰጡ፡፡

ደጃች ካሳ ሰዩም (አባ ይላቅ) የራስ ሰዩም ልጅ ትግራይ ውስጥ አመጽ ቀሰቀሱ፡፡ ለአመጹ የተለያየ ምክንያት ተሰጥቶበታል፡- በትግራይ ላይ የሸዋን የበላይነት አልቀበልም ስላሉ፤ የአጼ ዮሃንስን ዙፋን ካልመለስኩ ብለው፤ ልጅነት አጥቅቷቸው፤ ብስጩ ስለሆኑ፤ ወዘተ፡፡ ደጃች ካሳ ደጃች ሃይለማርያምንና ፊታውራሪ ቢተውን ተዋግተው አሸነፉ፤ ደጃች ግርማይንም (አጎታቸው) አጥቅተው ተምቤንን ተቆጣጠሩ፡፡ ደጃች ካሳ መቐለን ለመያዝ ሲሄዱ የአባታቸው የራስ ሰዩም ተወካይ (ደጃች ተካ) ከተማው እንዳይፈርስ ብለው ጥለውላቸው ወጡ፡፡ ለዚህም የውዳሴ ግጥም ተገጠመላቸው፡፡ ደጃች ካሳ በራስ ጉግሳ ላይ በራያ የግዛት ቅሬታ ስለነበረበት እንዳይጎዳው ተብሎ የመቐለ ሰዎች የራስ ጉግሳን ልጅ ሃይለሰላሴ ጉግሳን ወደ ቦራ አሸሸተውታል፡፡

የደጃች ካሳ ደጋፊዎች ዓድዋ፤ አኹሱምና ሽረ ነበሩ፡፡ የአባቱ ሰዎች ደጃች ካሳን መከተል አሻፈረን ብለው ነበር፡፡ የራስ ስዩም ከአዲስ አበባ መመለስንም ሲጠባበቁ ነበር፡፡ ደጃች ካሳ ሹምሽር አካሂዶ ደጃች መስፍንን፤ ደጃች አሰፋንና ደጃች ሃይሉን አንስቶ ሌላ ሾመባቸው፡፡ ራስ ስዩም ወደ መቐለ ሲመለሱ ደጃች ካሳ ወደ ዓድዋ ሄደው አባታቸውን ሊውጉ መዘጋጀት ጀመሩ፡፡ ራስ ስዩምም ደጃች ካሳ ወንበዴ ነው ብለው አዋጅ አወጡና ለዓድዋ ተከታዮቹ ማእከላዊ መንግስትን እንዲቀበሉና ደጃች ካሳን እንዳይከተሉ አስጠነቀቁ፡፡ የጨርጨሩ ፊታውራሪ አርአያ ከድጃች ካሳ ጎን መቆማቸውን አረጋገጡ፡፡ ራስ ሰዩም ደጃች ካሳን ሊውጉ አኹሱም ቢሄዱ አመለጣቸውና ጣልያኖችን ኤሪትርያ ውስጥ እንዲያስጠጉት ጠየቀ፡፡ ጣልያኖች በዚህ ስላልተስማሙ ደጃች ካሳ ለአባቱ እጁን ሰጠና ከተጣላቸው ሌሎች መኳንንትም ጋር እርቅ ፈጠረ፡፡

ደጃች ካሳ አባቱ ወደ አዲስ አበባ በኤሪትርያና ጂቡቲ አድርገው ሲጓዙ ደጃች ካሳ እንደገና አመጸና ራስ ስዩም ወደ ትግራይ ተመለሱ፡፡ የአዲስ አበባው መንግስት ራስ ስዩም ከልጃቸው ጋር በውስጥ ስምምነት አላቸው የሚል ጥርጣሬ አድሮበታል፡፡ ነገር ግን ራስ ስዩም ደጃች ካሳን ለመያዝ ውጊያ በገጠሙበት ጊዜ ደጃች ካሳ አባቱን ለማስገደል አስተኩሶ ስቷቸዋል፡፡ ደጃች ካሳ ተሸንፎ ወደ ሽረ ቢሸሽም ደጃች ማሩ ተከትለው ሄደው ከወጉት በኋላ ወደ ሽምግልና ገቡ፡፡ ደጃች ካሳ አባቱን ይቅርታ ቢጠይቅም ጅራፍ አስገረፉት፡፡ ራስ ስዩም ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ትልቅ እንቅፋት የሆነባቸው ልጃቸውን በሰንሰለት አስረው አዲስ አበባ ላኩት፡፡

ኋላም ከታሰረበት ሊያመልጥ ሲል ተገደለ ተብሏል፡፡ ማስመለጡ ላይ ለማስገደል ሆን ብሎ የተሸረበ ተንኮል ነበር፡፡ ራስ ስዩም ልጃቸውን አስረው በማስረከባቸው የጠበቁትን እምነት አላገኙም፡፡ ማእከላዊ መንግስትን ለመውጋት እንደ ዘዴ ተቆጠረባቸው፡፡ ሃይላቸው ለሁለት እንዳይከፈል ልጅ አስረከበው ከተደራጁ በኋላ የልጅ እያሱን መንግስት ለመመለስ ጥረት ያደርጋሉ ተብለው ተጠረጠሩ፡፡ እውነቱ ግን ራስ ስዩም ታማኝነት ለማግኘነት ብቻ ያደረጉት ነው፡፡ ራስ ሰዩም ልጃቸውን አስረው በማስረከባቸው ትግራይ ውስጥ ብዙ ተነቅፈዋል፡፡ ብዙ የውግዘት ግጥሞችም ተገጥሞባቸዋል፡፡ ዳጃች ካሳ ብዙ አድናቂዎች ነበሯቸው፡፡ አዲስ አበባ ላይ እንደ አደገኛ የሸዋ ጠላት ተቆጥረው ነበር፡፡ በዘዴ የተገደሉትም ለዛ ይሆናል፡፡

እቴጌ ዘውዲቱ ሞተው ራስ ተፈሪ ከነገሱ በኋላ በርካታ ለውጦች አደረጉ፡- የየግዛቶችን ገዢዎች አቅም አዳክመው ስልጣንን ማእከላዊ አደረጉ፡- አንድ ብሄራዊ ሰራዊት፡ አንድ የገንዘብ ስርአት፤ ዘመናዊ አስተዳደር በዘር ሳይሆን በችሎታ፤ የክልል ንጉሶች ለመሆን ሲጠባበቁ የነበሩት ራስ ሰዩም፤ ራስ ጉግሳ አርአያ፤ ራስ ካሳ፤ ራስ ጉግሳ ወሌ የነበራቸው የወሳኝነት ስልጣን ተነጥቀው የአጼ ሃይለሰላሴ የጠቅላይ ግዛታቸው ተወካዮች ብቻ ሆኑ፡፡ ህገ መንግስት አጽድቀው አጼ ሃይለስላሴ ሴኔቱን ራሳቸው ሾሙ (ትልልቆቹን መርጠው አይናቸው ስር አዲስ አበባ አስቀመጧቸው) ህግ አውጪዎችን በህዝብ አስመረጡ፡፡ ከስራቸው ነጉስ በሌለበት አጼ ሆነው ተሰየሙ፡፡

ከትግራይ የአጼ ዮሃንስ ዞፋን ብሎ የሚነሳ እንዳይኖር ራስ ስዩምንና ራስ ጉግሳን ከፋፍለው በጋብቻ አሳስረው፤ ተከፋይ ባለስልጣኖችን ከማእከል ልከው እንዳይላውሱ አድርገው ያዟቸው፡፡ ቀድሞም ቢሆን ተከፋፍለው ሲዋጉ ራሳቸውን ስላዳከሙ ለአጼ ሃይለሰላሴ ስራው ቀሎላቸው ነበር፡፡ የጎንደሩ ራስ ጉግሳ ወሌ ሰላመጹ ተገደሉ፡፡ ከዛ ራስ ጉግሳ አርአያና ራስ ስዩም የአጼ ሃይለሰላሴ ታማኞች ሆነው ቀጠሉ፡፡ ራስ ስዩም የንጉሱ የለውጥ ሃሳብ ለአገሪቱ ጠቃሚ ነው ብለው አምነው ተቀበሉ፡፡ ራስ ሰዩም፤ ሹም ተምቤን ገብረመድህን፤ ድጃች ካሳ ስብሓት የሴኔት አባላት ሆነው ተመደቡ፡፡ ትግራይ ላይ ያለውን ቁጥጥር ለማጥበቅ አጼ ሃይለሰላሴ በንጉሱ የአስመራ ቆንስል አማካይነት የትግራይን የጉምሩክ ስርአት ተቆጣጥሩ፡፡ የአኹሱም አስተዳደርም ከራስ ጉግሳ ተወሰዶ ለዚህ ቆንስሉ ተሰጠው፡፡

በትግራይ አቡነ ይሳቅ የሚባሉ የአማራ ተወላጅ ጳጳስ ተሾሙ፡፡ ራስ ጉግሳ ወደ ትግራይ እንዲመለሱ ተፈቀደላቸውና በአስመራ በኩል ሲመለሱ ከጣልያኖች ጋር ጓደኝነት ፈጠሩ፡፡ ከዛ ቀደም ጸረ ኢጣሊያ ቢኖሩም የአጼ ሃይለሰላሴን ማእከላዊ አስተዳደር አልተቀበሉትም፡፡ ራስ ስዩም ከራስ ጉግሳ ጋር ሁል ጊዜ እንደተናከሱ ነበር የሚኖሩት፡፡ ሁለቱም በአጼ ሃይለስላሴ ዘንድ ታማኝነት ለማግኘትና የትግራይ የበላይ ለመሆን ያላቋረጠ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ራስ ስዩም ለንጉሱ ሙገሳ እያጻፉ በጋዜጣ እንዲታተምላቸው ያደርጉ ነበር፡፡ የሁለቱም ምኞት የንጉሱ ሎሌ እንደሆኑ በትግራይ ላይ የበላይ መሆናቸው ብቻ ነበር፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ሁለቱንም የአጼ ዮሃንስ ወራሾች አላመኗቸውም፡፡ ጸባቸውም ይመቻቸው ነበር፡፡

አጼ ሃይለሰላሴ ለራስ ጉግሳና ለራስ ስዩም ትግራይን ምእራብና ምስራቅ ብለው ለሁለት አከፋፈሏቸው፡፡ ከዛ ቀጥሎ ወደ ትግራይ እንዲሄዱ አዘዟቸው፡፡ ሁለቱም ወደ ትግራይ እንዲሄዱ የታዘዙት የጣልያን ንጉስ አስመራ ሊጎበኝ ስለነበር አጼ ሃይለሰላሴን ወክለው ኤሪትርያ ድንበር ላይ ሆነው አቀባበል እንዲያደርጉለትና ጣልያንን ለማስፈራራት ብዙ ሺ ጦር ይዘው እንዲታዩ ነበር፡፡ ሁለቱም የትግራይ መሳፍንት በገዛ እጃቸው የነጉሱ መጫወቻ ሆኑ! የሁለቱም ወንድ ልጆች የአጼ ሃይለሰላሴን ሴት ልጆች አግብተዋል፡፡ ከዚህ በፊት ራስ ስዩም እህታቸውን ስላገቡ የልጅ እያሱ ወገን ሆነው ብዙ መከራን አሳልፈዋል፡፡ አሁንም ራስ ስዩም በልጃቸው ጋብቻ በረጅም ገመድ ታስረዋል፡፡

## 2.4 ጋብቻና የትግራይ መሳፍንት ፖለቲካ

በጊዜና በቦታ ድንበር ማስመር በማይቻልበት ሁኔታ የትግራይና የሸዋ መሳፍንትና መኳንንት በውስጣቸውና በመካከላቸው አንዴ ሲታረቁ አንዴ ሲጣሉ፤ ሌላ ጊዜ ሲጋቡ ጎራ ሲቀይሩ መጥፎ አጋጣሚ ተፈጥሮ ካልሆነ በስተቀር ህይወት መጠፋፋት አይፈልጉም፡፡ እንደ ቸዝ ጨዋታ ጠጠሩን እያስፈጁ ትልልቆቹ መማረክ፤ በምኞት መታሰርና አደጋ ከሌለው መፈታት የጌቶችና የጌቶች ልጆች እድል ነበር፡፡ የክተት አዋጅ እያወጁ ከየማሳውና ከየቤቱ እየቀሰቀሱ የሚያዋጉት ገበሬ ግን ሳያውቀውና ሳይጣላው ከተጋደለው ጋር እርቅ አያደርግ፤ ልጁንም አይድረለት፡፡ መደዴው የተፈጠረው ሙት ሲባል ለመሞት ነበር፤ አሁንም ድረስ ያው ነው፡፡ ሞቱ የዘላለም ለቅሶ የሚሆንለትና አንድ ቀን የሚያድር ትዝታም የማይቸረው አብረው ይዘምታሉ፡፡ ልጆቻቸውንና ራሳቸውን ከ"ጠላቶቻቸው" ጋር እያጋቡ የሚወልዷቸው ልጆችና የልጅ ልጆች የሚያፈሩት ነገስታት፤ መሳፍንትና መኳንንት ጸባቸው ከቆዳ ጥልቀት አይርቅም፡፡

የትግራይና የሸዋ የስልጣን ግድድር በተመለከተ ላለመሰባበር መተሳሰር የሚል አላማ የነበራቸው ጋብቻዎች በርካታ ነበሩ፡- ሚኒሊክ ልጃቸው ዘውዲቱን ለአጼ ዮሃንስ ልጅ አርአያ ስላሴ ዳሩ፤ የራስ ወሌ ልጅ የእቴጌ ጣይቱ ቤተሰብ ለራስ መንገሻ ዮሃንስ፤ አጼ ሚኒሊክ የእህታቸውን ልጅ ከባል አፋተው ትግራይን ለመቆጣጠር ይጠቅሙኛል ብለው ላመኑባቸው ለደጃች ገብረሰላሴ ዳሩ፤ ደጃች አብርሃ አርአያ አስራ አንድ አመት እድሜ የነበራትን የራስ ሚካኤል የእህት ልጅን አግብተዋል፤ ልጅ እያሱ የስድስት አመት ልጅ የነበረችውን የራስ መንገሻ ዮሃንስ

ልጅ አገቡ፡፡ እምቢ ብሎ አመጸ እንጂ ራስ ስዩም ለልጃቸው ደጃች ካሳ የራስ ተፈሪን ልጅ ለጋብቻ ለምነውለት ነበር፤ ራስ ጉግሳ አርአያ የሳምረ ተወላጅ ሚስታቸውን ፈተው የራስ መኮነን የልጅ ልጅ አገቡ (ልጅ ስላልወለዱ ፈቷቸው)፤ የተፈለገው የሸዋ ዘር ነበረና፡፡

ራስ ስዩም መንገሻ የራስ ሚካኤልን ልጅ አገቡ፤ ራስ ስዩም መንገሻ ሚስታቸው የራስ ሚካኤል ልጅ ሲሞቱ የንጉስ ሳህለስላሴ (ሸዋ) የልጅ ልጅ ልጅ የነበሩትን አገቡ፤ ራስ ስዩም ልጃቸውን ለአልጋ ወራሽ አስፋወሰን (የአጼ ሃይለስላሴ ልጅ) ዳሩ፤  ይህን ያደረጉት ከአጼ ሃይለስላሴ ጋር የትግራይ ንጉስ የሚሆን የልጅ ልጅ ለመጋራት ነበር (ልጅ ባለመወለዱ ተፋቱ)፡፡ ራስ ስዩም ወንድ ልጃቸውን (መንገሻ ስዩም ከአባቱ ሞት በኋላ የትግራይ ጠቅላይ ገዥ የሆነው) ለአጼ ሃይለስላሴ የልጅ ልጅ ዳሩ፡፡ የራስ ስዩም ተቀናቃኝ ራስ ጉግሳ በዚህ ጋብቻ ቀንተው ሌላዋን የአጼ ሃይለሰላሴ ልጅ ለልጃቸው ለደጃች ሃይለስላሴ ጉግሳ እንዲድሩላቸው ጠየቁ፡፡ የትግራይ መሳፍንት ጉድ የመጣው እዚህ ላይ ነበር፡፡

አጼ ሃይለስላሴ ሌላኛዋ ልጃቸውን ለዓጋመው ደጃች ካሳ ስብሓት ሊድሯት ቃል ገብተው ስለነበር ራስ ጉግሳ የጠየቁትን ማግኘት አልቻሉም፡፡ ስለዚህም ራስ ጉግሳ አንድ ተንኮል ሰሩ፡፡ ራስ ጉግሳ ደጃች ካሳን አታለው የራሳቸውን ልጅ ለጋብቻ ካስፈረሟቸው በኋላ ፊርማውን ለአጼ ሃይለሰላሴ አሳይተው ጋብቻውን ገልብጠው ለልጃቸው አስደረጉ፡፡ የሰላሳ ሁለቱ አመቱ ደጃች ሃይለስላሴ ጉግሳ የአስራ አራት አመቷን የአጼ ሃይለስላሴ ልጅ አገባ፤ ህጻናትን ለፖለቲካ ጨዋታ! የደጃች ሃይለስላሴ ጉግሳና የአጼ ሃይለሰላሴ ልጅ ጋብቻ ሰላም አልነበረውም፤ ከአጼ ሃይለስላሴ ጋር የነበረውም ግንኙነት መልካም አልነበረም፡፡ የአጼ ሃይለሰላሴ ልጅም መቐለ ሄደው ሞቱ፡፡ የጋብቻው ገመድ የትግራይን መሳፍንት ለማሰር በቂ አልሆነም፡፡

## 2.5 የትግራይ መሳፍንት፤ ጣሊያንና አጼ ሃይለስላሴ

ደጃች ሃይለስላሴ ወደ ጣልያኖች ማዘንበል ጀመሩ፡፡ ራስ ስዩም አስመራ ለነበረው የኢጣሊያ ተወካይ የትንሳኤ ድግስ የሚደግሱበትን ብር እንዲልክላቸው በደብዳቤ ጠይቀዋል፡፡ ራስ ስዩም በዚህ አላቆሙም አጼ ሃይለሰላሴ ትግራይ ውስጥ ተጨማሪ ግዛት ሰጥተውኛል ብለው የደስደስ መልእክት ለኢጣልያው ተወካይም ጽፈዋል፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ለድጃች ሃይለስላሴ ጉግሳ ወታደራዊ ልብስ

ሲልኩላቸው የመለሱት፡ “ዩኒፎርሙ ሲደርሰኝ በምስጋና አስር ጊዜ መሬት ሳምኩኝ፤ ወዲያውም ለበስኩት፡፡ ኮፍያው እስኪመጣ እየጠበቅሁ ያዘዙኝን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ”፡፡ ይህ ሁሉ ቁልምጫ የትግራይ ነጉስ ለመሆን ነበር፡፡

የኢጣሊያ ተቃራኒ የኢትዮጵያ ፖሊሲ፦ “የሸዋ ፖሊሲ” የተባለው የአጼ ሃይለስላሴን ማእከላዊነት ማገዝ (ኋላ የተተወ)፡፡ ምክንያቱም የሃይለስላሴ መጠናከር ለኢጣሊያ ስለማይበጅ፡፡ “የትግራይ ፖሊሲ” የተባለው የትግራይና የሸዋን ፉክክር ማጋጋል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጣሊያን ራስ ስዩምንና ራስ ጉግሳን አስማምታ ንጉሱን እንዲያዳክሙ ልትጠቀምባቸው ወሰነች፡፡ ጣሊያን የትግራይ መኳንንት ወደ ኢትዮጵያ እንድትዘልቅ እንዲያግዟት አግባባች፡፡ በኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ቆንስላዎች በማቋቋም ክልሎች ከአጼ ሃይለስላሴ ጋር በኢጣሊያ ላይ እንዳይተባበሩ ይሰብኳቸው ነበር፡፡ ጣልያኖች በተለይ ራስ ጉግሳን በጣም አቀረቧቸው፡፡ ታመው እስከሞቱ ድረስ በጣሊያን ዶክተሮች እንክብካቤ ተደረገላቸው፤ ራስ ጉግሳም የጣልያንን “ዉለታ” እያደነቁ ከዚህ አለም ተለዩ፡፡ የራስ ጉግሳ ልጅ ደጃች ሃይለሰላሴ ከአጼ ሃይለሰላሴ ጋር ብዙም የሚግባቡ አልነበረም፤ ከራስ ስዩምም ጋር ያባታቸውን ፉክክር አስቀጠሉ፡፡

ራስ ስዩም ትግራይን ለማግኘት ደጃች ሃይለስላሴ ደግሞ የአባታቸውን ግዛት ለማግኘት ታገሉ፡፡ ደጃች ሃይለሰላሴ አጼ ሃይለሰላሴ የራስነት መአርግ ስላልፈቀዱላችው ያባታቸውም ግዛቶች ስላልሰጧቸው የባሰ አኩርፈው ነበር፡፡ የአጼ ሃይለስላሴ አማካሪዎች ራስ ስዩምንና ራስ ጉግሳን አዳክመው ትግራይ ላይ ዘመናዊ አስተዳደር እንዲያዋቀሩ ሃሳብ ቢያቀርቡላቸውም ንጉሱ እንዲህ አሉ፦ “ትግራይ ውስጥ የሚሰራው ባህላዊ አስተዳደር ብቻ ነው”፡፡ ይህ የአጼ ሃይለስላሴ መልስ ውስጠ ወይራ ነበር፦ “የትግራይ ህዝብ የሚወደው ከሌላ አካባቢ የሄዱ መልካም አስተዳዳሪዎችን ሳይሆን ከአብራኩ የወጡ ገዢዎቹን ነው”፡፡ አጼ ሃይለሰላሴ ወደ ራስ ስዩም ቢያደሉም ሙሉ እምነት አልነበራቸውም፤ ያሰልሏቸውም ነበር፡፡ አጼ ሃይለሰላሴ ራስ ስዩም ከጣሊያን ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚሰልል፤ የህዝቡን ቅሬታ የሚሰማና የሚያስተላልፍ፤ የራስ ስዩም ጠላት የሆነ የራሳቸው ሰው ዓድዋ ላይ አስቀመጡ፡፡

ራስ ስዩምና ራስ ጉግሳ እርስ በርስ ስም እይተጠፋፉ ቀጠሉ፡፡ ይህን እያደረጉም ሁለቱም አጼ ሃይለስላሴን እያቆላመጡ እያሞገሱ እያጋነኑ ጣሊያንን እንደሚጠሉ

እየማሉ እየተገዘቱ ለማታለል ይሞክሩ ነበር፡፡ ደጃች ሃይለስላሴ በአንድ በኩል ንጉሱን እያታለሉ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ አበባ ተቀምጠው አስመራ ላይ በሚስጥር መኖሪያ ቤት ገዙ፡፡ አጼ ሃይለሰላሴ ቀጥለው የወሰዱት እርምጃ፡- ራስ ስዩምን የትግራይ ወታደራዊ አዛዥ አድርገው ሾሙ፤ ለራስ ስዩም ከደጃች ሃይለስላሴ የበለጠ ግዛት ሰጥተውም ደጃች ሃይለስላሴ በራስ ስዩም ስር እንዲሆኑ አደረጓቸው፡፡ ደጃች ሃይለሰላሴ አጼ ሃይለሰላሴ ለራስ ስዩም ባደረጉላቸው ነገር በመቀየማቸው ከጣሊያን ጋር ለመተባበር ወሰኑ፡፡ ለዚህ ድርጊታቸው የሰጡት ምክንያት፡- “ሁለታችንም አዋግተው ትግራይ ሲረበሽ የሸዋ ሰው ልከው ትግራይ ላይ ጠቅላይ ገዢ ሊያደርጉ ያስባሉ” ብለው ነው፡፡

ደጃች ሃይለስላሴ በተደጋጋሚ አዲስ አበባ እየሄዱ የተወሰደባቸውን የአባታቸው ግዛቶች እንዲሰጣቸው አጼ ሃይለስላሴን ጠይቀው አልቀናቸውም፡፡ ለጣሊያኖች ፕሮፓጋንዳ ደጃች ሃይለስላሴ እጅግ ጠቃሚ ነበሩ፡፡ አንደኛ የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጅ ልጅ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የአጼ ሃይለስላሴ አማች፡፡ ጣልያኖች ደጃች ሃይለስላሴን በጃቸው አስገቡ፡፡ ሆኖም ትውልድ እንጂ አቅም እንደሌላቸው ሲያዩ “ኢትዮጵያን መውረር እስክንጀምር ድረስ ጸጥ በል” ብለው አስጠነቀቋቸው፡፡ ራስ ስዩምም በአጼ ሃይለስላሴና በጣልያኖች መካከል ሆነው ሲያወላውሉ ቆዩ፡፡ ጣልያኖች ካሸነፉ ትግራይን ለደጃች ሃይለስላሴ ይሰጧታል ብለው የሰጉ ይመስላል፡፡ ጣልያኖችም የራስ ስዩም ማወላወል ተገንዝበውት ነበር፡፡ ራስ ስዩም ከጣሊያን ጋር አብረው ኢትዮጵያን ቢወጉ የኢትዮጲያ ንጉስ እንደሚያደርጓቸው ቃል ገቡላቸው፤ የጣሊያን አሻንጉሊት ማለት ነው፡፡

አጼ ሃይለሰላሴ ከትግራይ ስለ ደጃች ሃይለስላሴ ከጣሊያኖች ጋር መስማማት የመጣላቸውን የባንክ ማስረጃ አልተቀበሉም፡፡ የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጅ ከጣሊያኖች ጋር ያብራል ብለው ማመን አልቻሉም፡፡ እንዲያውም ማስረጃውን ያመጡላቸውን ሰዎች ተጠራጠሯቸው፡፡ ጣሊያኖች ወረራ ሲጅምሩ ደጃች ሃይለስላሴ መቐለ ላይ ራስ ስዩም ደግሞ ወደ ሰሜን ሄደው እንዲከላከሉ የወጣው እቅድ ሁለቱም አንድ ላይ እንዲከላከሉ ሆኖ ተቀየረ፡፡ ደጃች ሃይለስላሴ ሲያሰሉ የነበረው ግን ሌላ ነገር ነበር፡- በዚህ ጦርነት አጋጣሚ ራስ ስዩም ቢሞቱላቸው የትግራይ ጠቅላይ ገዥ የመሆን ህልም! ደጃች ሃይለስላሴ ወደ

ጣሊያን ሲከዱ ተከታዮቻቸውንን ለማሳመን የሞከሩት “ከጣሊያኖች ጋር ሆነን በትግራይ የሸዋን አገዛዝ እናስወግድ” የሚል ነበር'፡፡ የደጃች ሃይለስላሴ መክዳት ጣልያኖች ያለ ውግያ ወደ አርበኛው ንጉሰ ነገስት ዋና ከተማ (መቐለ) ሰተት ብለው እንዲገቡ ረዳቸው፡፡ የጣሊያን ሰራዊት መቐለ ሲገባ የከተማው ህዝብ ውግንና ለሁለት ተከፍሎ ነበር፡- በተምቤን በጣሊያኖች ቢሸነፍም በራያ ከራስ ሥዩም ጋር ሆኖ ትግሉን የቀጠለው አርበኛ በአንድ ወገን፤ ደጃች ሃይለስላሴ ቅድመ-አያታቸውን ክደው የጣሊያንን ሰራዊት መርተው ወደ መቐለ አጼ ዮሃንስ ቤተመንግስት ሲገቡ አቀባበል ያደረገላቸው ታጣቂና ሲቪል ህዝብ በሌላ ወገን፡፡



ጥርቡሹን አጥልቀህ ስትመላለስ
እንዴት ትታዘብህ ዕዳጋ ሓሙስ
ምንኛ ይርገሙህ አጼ ዮሃንስ
የጽላተ-ሙሴን ስርአት ስታፈርስ

በዚህ ጎራ የለየ ትርምስ የራስ ስዩም ወገን ናችሁ ተብለው በህዝብ ጥቆማ በጣሊያን ሰራዊት የተገደሉ  ነበሩ፡፡ ከነዚህ አንዱ የደራሲው አያት አሰላፊ ደስታ ነበሩ፡፡ አሰላፊ ደስታ ከራስ መንገሻ ዮሃንስ ጀምሮ የአጼ ዮሃንስ ቤተመንግስት የአስተዳደር ሃላፊነት የነበራቸው የራስ ስዩም የቅርብ ረዳት ነበሩ፡፡ በተምቤን ጦርነት ጊዜ የስንቅና ትጥቅ አቅርቦት ሃላፊ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው በእድሜ ምክንያት ራስ ስዩምን ተከትለው ወደ ራያ ግንባር ሳይሄዱ መቐለ ከራስ ስዩም ሌላ መኖርያ ቤት ማንነታቸውን ደብቀው ቆዩ፡፡ ጣሊያን መቐለ ሲገባ ራስ ስዩምን ሲቃረኑ በነበሩ ጎረቤቶቻቸው ለጣሊያን ጥቆማ ተደረገባቸው፡፡ ጣሊያንም ባገኘው መረጃ መሰረት አሰላፊ ደስታን ከነወንድ ልጃቸው የፊጥኝ አስሮ፤ ቤታቸውን አቃጥሎ፤ ከብቶቻቸውን አርዶ፤ ወንዝ ዳር ወስዶ በመትረየስ ጨፈጨፋቸው፡፡ የደራሲው እናትና ሴት አያት በሚቃጠለው ቤታቸው ፊት ለፊት ደንዝዘው ቀሩ፡፡ ፊልም ይመስላል! ከነጻነት በኋላ ራስ ስዩም ተመልሰው በህይወት የቀሩትን ያጽናኗቸው ቢሆንም ራስ ስዩም ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ሮም ሄደው ከሙሶሎኒ ጋር ተገናኝተው ስለነበር የአሳላፊ ደስታ መስዋእትነት ያተረፈው ነገር ቢኖር የቀሪ ቤተሰባቸው በጣሊያን ባንዳዎች መንገላታት ነበር፡፡

## 2.6 የጣሊያን ወረራና ድህረ-ወረራ

ራስ ስዩም በኢጣሊያ ወረራ ዋዜማ በኢትዮጵያ ሰራዊት የትግራይ ጦር ሃይል አዛዥ ሆነው በአጼ ሃይለስላሴ ተሹመው ስለነበር በትግራይ በኩል የመጣውን ዋናውን የጣሊያን ሃይል የትግራይ ሰራዊት ብቻ ይዘው ተምቤን ላይ ለሰባት ወራት ያህል የተጋፈጡት ብቻቸውን ነበር፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ረዳት ጦር የላኩላቸው የጣሊያን ጦር ድል እያደረገ መቐለን አልፎ ማይጨው ሊደርስ ሲል ነበር፡፡ የመላ ኢትዮጵያን ከውጭ ወራሪ የመከላከል ውጊያ ለትግራዩ መስፍንና ለትግራይ የገበሬ ሰራዊት መተዉ እጅግ የሚዘገንን ክህደት ነበር፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ማይጨው ላይ በአካል ተግኝተው ውጊያውን መራሁ ቢሉም ጦራቸው ከሽንፈት አልዳነም፡፡ አዲስ አበባ በሽብር እየተተራመሰ በነበረበትም ንጉሱ በጅቡቲ አድረገው ካገር ወጡ፡፡




በስልጣን ጥም ምክንያት ክህደት ፈጽመው የጣሊያንን ጦር እየመሩ ወደ ትግራይ ያስገቡት ደጃች ሃይለስላሴ ጉግሳ ጣሊያን የራስነት መአርግ ሸለማቸው፡፡ ወደ ሮም ተጋብዘውም የጀርመኑ ሂትለር ኢጣሊያን ሲጎበኝ አቀባበል ስነ ስርአት ላይ ተግኝተው ነበር፡፡ ኢትዮጵያን ከኢጣሊያ ወረራ ለማዳን ያለ ረዳት ለብዙ ወራት የተከላከሉት ራስ ስዩም መንገሻ በምርኮ ሮም ተወስደው ከቆዩ በኋላ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡ የጎጃሙ የንጉስ ተክለሃይማኖት ልጅ ራስ ሃይሉም ለኢጣሊያ አድረው ነበር፡፡ ሶስቱም የኢትዮጵያ ታላላቅ መሳፍንት አገራቸውን ለኢጣሊያ አስረክበው አገልጋዮች ሆነው ተቀመጡ፡፡ ሌሎች ግን በአርበኝነት በዱር በገደሉ እየተዋደቁ ነበር፡፡ ለጎጃሙ ራስ ሃይሉ በድርጊታቸው የሚያስቆጫቸው ነገር አይኖርም ነበር አርበኛው በላይ ዘለቀ በኢጣሊያ ሳይሆን በራሱ መሪዎች ሲሰቀል ቢያዩ፡፡

ለአገራቸው ነጻነት የታገሉት ራስ ስዩምንና ራስ አበበ አርጋይንስ የገደሏቸው የኢትዮጵያ ወታደሮች አልነበሩምን? መንግስቱ ሃይለማሪያም ቀሪዎቹን አርበኞች በመትረየስ አጨዳቸው፡፡ በየአመቱ እየተቅራራ የሚዘከረው ግን የጣሊያን ግድያ ብቻ ነው፡፡ ኢጣሊያ በእንግሊዝና በአርበኞች ሃይል ከኢትዮጵያ ተገፍታ ከወጣች በኋላ እንግሊዞች በነበራቸው የበላይነት ራስ ኃይለስላሴ ጉግሳን በትግራይ ጊዜያዊ ስልጣን ሰጥተዋቸው ነበር፡፡ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለይቶ ከኤሪትርያ ጋር በመቀላቀል ትግራይ/ትግሪኚ የሚባል አዲስ አገር ለመፍጠር በማሰብ ራስ ሃይለሰላሴ ጉግሳን የምስራቅ ትግራይ ግዛት አዛዥ አድርገው ሾሙ፡፡

ይህን እቅድ በርካታ እንግሊዛውያን ቢደግፉትም የማይቀበሉት ይበዙ ነበር፡፡ ራስ ሰዩምም ቢሆን በሃሳቡ ባለመስማማታቸው ቀይ ባህር ላይ ስር ነቀል የሆነ የጂኦፖለቲካ ለውጥ ሊያመጣ የነበረው እቅድ ከሸፈ፡፡ ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆይ ራስ ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ከጣሊያኖች ጋር ሲጻጻፉ ተያዙ በሚል ምክንያት እንግሊዞች አስመራና ቀጥሎም ሲሸልስ ውስጥ አሰሯቸው፡፡ አጼ ሃይለስላሴ ራስ ሃይለስላሴ ወንጀለኛ ስለሆኑ አስልፋ እንድትሰጣቸው እንግሊዝን ጠየቁ፡፡ ራስ ሃይለሰላሴ ለኢትዮጵያ ተላልፈው ከተሰጡ በኋላ እድሜ ልክ ተፈረደባቸው፤ የራስነት መአርጉም ተገፈፉ፡፡ ራስ ስዩም በብዙ ሺ የሚቆጠር የትግራይ ሰራዊት መርተው የኢጣሊያን ጦር ከሰሜን በማስወጣት ከፍተኛ ትግል መርተዋል፡፡ ለዚህም ማንም ተቀናቃኝ በሌለበት የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ሆነው በአጼ ሃይለስላሴ ተሹመዋል፤ የዘውድ ምክር ቤት አባልም ነበሩ፡፡

ምንም እንኳን በራሳቸው ፍላጎትና የአጼ ሃይለሰላሴን ትእዛዝ በማክበር ለኢትዮጵያ ነጻነትና አንድነት ብዙ የደከሙ ቢሆንም ራስ ስዩም የወያኔ አመጽ ሲነሳ በተባባሪነት ተጠርጥረው አዲስ አበባ ከተጠሩ በኋላ ከሸዋ ሌሎች መኳንንትና ጄነራሎች በምትካቸው ወደ ትግራይ ተልከዋል፡፡ ራስ ስዩም አዲስ አበባ ላይ በአመጸኛ ወታደሮች ተረሸነው ልጃቸው ራስ መንገሻ ስዩም በምትካቸው የትግራይ ጠቅላይ ገዥ ሆኑ፡፡ እኒህ መስፍን ከቀደምቶቹ ለየት ያለ ባህርይና የአስተዳደር ዘይቤ ነበራቸው፡፡ ከዛ ቀደም ሃዋሳ ከተማን በማልማትና የኢትዮጵያን አየር መንገድ በማደራጀት እውቅና ያገኙ ነበሩ፡፡ እሳቸውም ሆኑ ልጆቻቸው ከ"ተራው" ህዝብ ጋር ለመቀላቀልና አብሮ ለመስራት ችግር አልነበረባቸውም፡፡ ትግራይ ውስጥ መንገዶችን በመስራትና የተወሰኑ ፋብሪካዎችን በመገንባት ከበፊቶቹ መሳፍንት ለየት ያሉ መሆናቸውን ለማሳየት

ሞክረዋል፡፡ የልማት ድርጅቶች (ታይድል፤ ቲዲአ) የሚባሉትን በመመስረትም ለእድገት ተቋማዊ ድጋፍ ለመስጠት ጥረዋል፡፡ ሆኖም የግብር መብዛት፤ የልማት መወጮ አያያዝ ችግር፤ በጤናና ትምህርት  ዘርፍ የነበረው የአቅርቦት ችግር ህዝባዊ ቅሬታዎችን እየቀሰቀሰ ነበር፡፡ የአብዮቱ ንፋስ መንፈስ ሲጅምር “አሁን ይሻላል ወይ አቀርቅሮ ማልቀስ፤ ይሻል አልነበረ ግብርን መቀነስ” ተባሉ፡፡

የኢትዮጵያ አብዮት እንደፈነዳ ራስ መንገሻ ስዩም የነበራቸው አንጻራዊ የሆነ የህዝብ ፍቅር ጠቀማቸውና በወታደራዊ መንግስት ሳይታሰሩ ቀርተው እስካሁንም በህይወት ያሉት ከፍተኛ የቀድሞ መሳፍንት ዘር እሳቸው ብቻ ናቸው፡፡ በወታደራዊው መፈንቅለ መንግስት ዋዜማ መላ የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት እንደ በግ እየተጎተቱ፤ በራሳቸውም ፈቃድ እጅ እየሰጡ ሲታሰሩ ‘በህዝብ እርዳታ’ ወደ ስደት ተሸኝተዋል፡፡ ራስ መንገሻ ስዩም በወታደራዊው መንግስት ዘመን የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት የሚባል ሊበራል ፓርቲ መስርተው ትግራይ ላይ የትጥቅ ትግል ቢሞክሩም ከህወሓት ጋር የፖለቲካ አላማ ልዩነትና ምናልባትም የቀድሞው የትግራይ መሳፍንት የግጭት ርዝራዥ አስተሳሰብ የተነሳ ከመተባበር ይልቅ ብዙ ደም ያፋሰሰ ውጊያን አካሂደዋል፡፡

የግማሽ ምእተ አመቱ የትግራይ “ዘመነ መሳፍንት” በኢጣሊያ ወረራ ተቋርጦ ለአርባ አመታት ከቆየ በኋላ በርእዮተ አለም ልዩነት ተመስሎ “ጠራናፊት” በተሰኘችው የራስ መንገሻ ስዩም ድርጅትና “ተሓህት” ስትባል በነበረችው ቀደምቷ ህወሓት መካከል ለሁለት አመታት ያህል አውዳሚ ውጊያ ተካሄደ፡፡ ህወሓት አንዲት የትግራይ ድርጅትን በቁም እንደዋጠችና ኢህአፓንም በነፍጠኞች ተወካይነት ፈርጃ ከትግራይ እንዳሰወግደች ይነገራል፡፡ ያለፈው የትግራይ ታሪክ ይህን ይመስላል፡- “አብረው ድንኳን አይተከሉም”!

ይህ ታሪክ አሁን ተቀይሯል? በፍጹም፤ እጅግ ረቂቅ በሆነ ስልት በሳይበር ቴክኖሎጂ ተደግፎ ቀጥሏል፡- “ለትግራይ ጦርነት ባህላዊ ጨዋታ ነው” የሚሉ አሉ ጦረኛነት ጌጥ የመሰላቸው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ስር ነቀል የባህል አብዮት የሚያስፈልገው እዚህ ላይ መሆን አለበት፡፡ የትግራይ ተቃዋሚ ድርጅቶች “ስርነቀል ለውጥ ለማምጣት” ብለው ግንባር ፈጥረዋል፡፡ ለውጡ ግን ህወሓትን ከስልጣን በማስወገድ የሚጀምር ነው፡፡ የፖለቲካ ባህሉ ጨርሶ እስካልጸዳ ድረስ ህወሓት የምትተካው በሌላ ህወሓት ነው፡፡ ሁሉም የልዩነት ቫይረስ ተሸካሚ ነው፡፡

# ምዕራፍ ፫

# የወያነ አመጽ፤ የጎራ ግብግብ፤ የህወሓት ትግልና ድል

## 3.1 መግቢያ

ከአምስቱ አመታት የኢጣሊያ ወረራ በኋላ አጼ ሃይለሰላሴ ከለንደን የስደት ቆይታ በእንግሊዝ ሰራዊት ድጋፍ አዲስ አበባ ገብተው ዙፋናቸው ላይ ከተቀመጡ ጀምሮ የክልል ገዢዎችን አቅም አዳክመው ማእከላዊ አስተዳደርን ለማስፈን በርካታ እርምጃዎች ወስደዋል፡፡ ይህ ከኢጣሊያ ወረራ በፊት የጀመሩት ስር ነቀል ለውጥ "ነጻነት" ከተመለሰ በኋላም አጠናክረው ቀጠሉ፡፡ በዚህ ለውጥ መሰረት በትግራይ በእርስ በርስ ውጊያ በግብታዊነት ሲሰፉና ሲጠቡ የነበሩት በርካታ የመሳፍንቱ ግዛቶችና ርስተ-ጉልቶች እየተጠቃለሉ ስምንት አውራጃ ግዛቶች ተፈጠሩ፡- ራያ-ዓዘቦ፤ እንደርታ፤ ተምቤን፤ ክልተ-አውላዕሎ፤ ዓጋመ፤ ዓድዋ፤ አኹሱም፤ ሽረ፡፡ የማእከላዊ አስተዳደር መጠናከር በስመ ዘመናዊ አስተዳደር የሸዋ የበላይ አገዛዝን ለማጠናከር የታለመ ነው ብለው የተረጎሙት ባመዛኙ ትግራይን ሲገዙ የነበሩት መሳፍንትና መኳንንት ናቸው፡፡

መልካም አስተዳደር የሚባለው የራስ ጥቅም ከመስመር ሳይወጣ ህዝብን በአግባቡ ማገልገል ማለት ከሆነ በማእከለም ይሁን በክልል ቢተገበር ብዙም ልዩነት አይኖረውም፡፡ የአስተዳደር ስልጣን ከማእከል ወደ ክልልና ከዛ በታች ቢወርድ ለህዝብ ጠቃሚ የሚሆነው ከቅርብ ርቀት ሆኖ፤ የአካባቢ ባህልንና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ያገናዘበ የአስተዳደር አገልግሎት የሚያስገኝ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የሩቅ ሰው ጭቆናና ብዝበዛ ከማእከል ከሚወርድ ጭቆናና ብዝበዛ ከቅርብ ሰው በክልል ቢሆን ይሻላል ከሆነ ምርጫው ከማዶ አገር ጅብ እየመጣ ከሚበላኝ የጓሮየ ጅብ ቢቆረጥመኝ እመርጣለሁ እንደማለት ነው፡፡

የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት በቀረጥ ብዛት፤ በተዋጊነትም እያሰለፉ ህዝቡን ለረሃብና ለችጋር አጋልጠው የሸዋ አገዛዝን እንቃውማለን ማለት ከስልጣን ጥም እንጂ ከፍትሃዊነት የመነጨ ተቃውሞ አይደለም፡፡ ሸዋ ከሚገዛን እናንተ ብትገዙን ይሻላል የሚል ህዝብ ካለ ከእውቀት ነጻ የተደረገ ወይንም ከባዶ ኩራት ያለፈ ምንም ቁሳዊም ሆነ ማህበራዊ ፋይዳ በሌለው አጉል የአካባቢ ስሜት

ተሰብኮ የደንዘዘ መሆን አለበት፡፡ የእንደርታ ገዢ የነበሩት ደጃች አብርሃ የእንደርታን ህዝብ አፈር እያሸከሙ ለቤተ መንግስት መስሪያ ከፍታ ኮረብታ ሲያስደለድሉ፤ ከአምሳ በላይ ኪሎሜትር ርቀት ግንድ እያሸከሙ ጣሪያና በር ሲያሰሩ፤ የቤተመንግስት ማሰሪያ ቀረጥ አንከፍልም ያለውን ህዝብ ክፉኛ ሲቀጡ ቆዩ፡፡ አጼ ሚኒልክ ደጃች አብርሃ በህዝብ ላይ በፈጸሙት የጭካኔ ስራ ቀጥተው ከሹመታቸው ሊሽሯቸው ባሰቡበት ወቅት ደጃች አብርሃ በአጼ ሚኒሊክ ላይ እንዲያምጹ ህዝብ በዘፈን የገፋፋበት ድርጊት ከድንዛዜ በስተቀር ምን ሌላ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል? ጠላትነትና ወዳጅነት የሚለየው በአብሮ አደግነት?

በማእከላዊ አስተዳደር ላይ አመጽ ማካሄድ ፍትሃዊ የሚሆነው የክልል አስተዳደሩ ፈትሃዊ ሆኖ እያለ ከማእከል የማዳከምና የማሰናከል ተግባር የሚፈጸምበት ከሆነ ነው፡፡ አለበለዚያ የማእከሉም የክልሉም ጨቋኞች በሆኑበት ሁኔታ አመጽ መካሄድ ያለበት በሁለት አቅጣጫ ሁለቱም ላይ ነው፡፡ ኢጣሊያ ከኢትዮጵያ ለቃ የአጼ ሃይለሰላሴ አገዛዝ ከተመለሰ ሁለት አመት ሳይሞላው በትግራይ “ወያኔ” የሚባል አመጽ ተቀሰቀሰ፡፡

### 3.2 የወያነ አመጽ

ጀራርድ ፕሩኔር የወያኔ አመጽ የመደብ ትግልና የክልል የራስ አስተዳደር አላማ ነበረው ይላል፡፡ ለዚህም ነበር ተመሳሳይ ጥምር የመደብና የክልል አላማ ነበረው ከሚለው የህወሓት የትጥቅ ትግል ጋር “ቀዳማይ”ና “ዳግማይ” ብሎ ቅደም ተከተል መስጠት ተገቢ ነው ብሎ የተቀበለው፡፡ እዚህ ላይ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ የሚሆነው የመደብ ትግልና የክልል የራስ አስተዳደር ጥያቄ እኩል አብረው ሊራመዱ ይችላሉ ወይ? ነው፡፡ በመደብ ትግል ውስጥ የክልልም ይሁኑ የማእከል ገዢዎች የትግሉ ኢላማዎች እንጂ አጋሮች አይደሉም፡፡ በክልል የራስ አስተዳደር ጥያቄ ግን የክልል ገዢዎች የትግል አጋሮች እንጂ ኢላማዎች አይደሉም፡፡ የሁለቱም የወያኔ አመጾችን አፈጣጠርና አካሄድ በመመርመር ብዥታውን ማጥራት ያስፈልጋል፡፡

የመጀመሪያው ወያኔ በመክሸፉ ድል ቢያገኝ ኖሮ የሃይል አሰላለፉ ምን ሊመስል ይችል እንደነበረ መገመት ባይቻልም በድል የተጠናቀቀው የሁለተኛ ወያኔውን ግን በግልጽ ማየት ተችሏል፡፡ ከድል በኋላ ሰልጣኑን የያዘው ማን ነበር? የኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሆነውስ? “ለለውጥ ያጎፈረው ሰልጣን ላይ ሲወጣ፤ አዲስ

ነጉስ እንጂ ለውጥ መች መጣ"፡፡ ይህ የዘፈን ግጥም የዘር ጥላቻን ተንተርሶ የተደረሰ ነው በሚል ሲወገዝ የኖረ ነው፡፡ የግጥሙ ውስጠ ወይራ ቀና ይሁን ጠማማ ለደራሲው በመተው ከህወሓት ድል ማግስት የሆነውን ከወገናዊነት ነጻ በመሆን ቢገመገም ግን የአባባሉ እውነትነት የሚካድ አይሆንም፡፡ ከአስራ ሰባት አመት የብዙ ሺ ህዝብ እልቂት ያስከተለ የትጥቅ ትግል በኋላ የተፈጠረው በክልል የራስ አስተዳደር መብት ተሸፍኖ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ክንዱን ያፈረጠመው አዲስና ዘመናዊ የገዢ መደብ ነው፡፡

የመጀመሪያው ወያኔ አላማዎችና የመሪዎቹን ማንነት መመርመር ተገቢ ነው፡፡ ወያኔ የሚከተሉት አላማዎች ነበሩት፡- በኢትዮጵያ ባንዴራና አንድነት ስር የሆነ የራስ የክልል አስተዳደር፤ ከሸዋ የገዢ መደብ አገዛዝ ነጻ ሆኖ በትግራይ ባህላዊ ህጎችና በራሱ መሪ የሚተዳደር፤ ሌቦችና ሽፍቶች የጠፉበትና ካቅም በላይ የሆነ ግብር የማይከፈልበት የአስተዳደር ስርአት ማስፈን፡፡ እነዚህ የአመጹ አላማዎች የሸዋው የገዢ መደብን መታገል እንጂ የትግራይን የገዢ መደብ በተመሳሳይ የማስወገድ አላማ አልተካተተበትም፡፡ "በራሱ መሪ የሚተዳደር" የሚለው አላማም በራሱ ደሃ ነው ወይስ በራሱ ጌታ ነው የሚተዳደረው ለሚል ወሳኝ ጥያቄ መልስ አይሰጥም፡፡ የወያኔ መሪዎች ማንነት የሚያሳየው ደግሞ አመጹን የመሩት እነ "አበጀ በለው" እንዳልሆኑ ነው፡፡

ራስ ስዩም በአመጹ ደጋፊነት ተጠርጥረው አዲስ አበባ ውስጥ መታገታቸው የሚሰጠው ፍንጭ አለ፡፡ "በራሱ መሪ" የሚለው አንዱ አላማ ወደ ራስ ስዩም ያመራ ነበረን? የእንደርታ ልሂቃን "የላማችን ልጅ" የሚሏቸው የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጅን "የራስ መሪ" ካልተባሉ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? ከአራቱ የወያኔ የበላይ መሪዎች ሁለቱ የፊታውራሪና የደጃዝማችነት መአርግ የነበራቸው የገዢው መደብ አባላት ነበሩ፡፡ ቀሪዎቹም ዝቅ ያለ ይሁን እንጂ የመኳንንትነት መአርግ ነበራቸው፡፡ እርግጥ ነው በመደብ ትግል ሂደት "መደባቸውን የካዱ" ተሰኝተው ትግሉን የሚቀላቀሉ ብቻ ሳይሆን የሚመሩም የገዢው መደብ አባላት ነበሩ፡፡ ወያኔ በገዢዎች ላይ የነበረው ምሬት የወለደው የሰፊው ህዝብ የመደብ ትግል ነበረ የሚባል ከሆነ ይህን የሚያመለክት ጠንከር ያለ ነገር አልነበረም፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ግብር አንከፍልም ማለት ገዢዎቻችን ከጫንቃችን ወረዱና በተራው ህዝብ አስተዳደር ይተካ ማለት አይደለም፡፡

ከአፄ ዮሃንስ ህልፈት ጀምሮ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ የነበረው የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት የግዛት መቀማማት ትልልቆቹ አልቀው በልጆቻቸው ተተኩ፡፡ ትግራይ ውስጥ የነበረው የግዛት መቀማማቱ ስርአት በአፄ ሃይለስላሴ ማእከላዊ አስተዳደር ቢዳከምም የአስተሳሰብ ቅሪቱ ግን ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ ህዝቡ የገዢዎቹን ስሜት ተከትሎ በግዛቶች የኔነት ስሜት እርስ በርሱ ሲጠላላና ሲጣላ ኖሯል፡፡ መሳፍንቱና መኳንንቱ በተጣሉ ቁጥር በውጊያ ሲያልቅ የነበረው የማይመለከተው ተራው ህዝብ ስለሆነ የተለያዩ የትግራይ ንኡስ-ግዛቶች ውስጥ የነበረው ህዝብ እርስ በርሱ ተኳርፎና ተቀያይሞ ቀርቷል፡፡ መሳፍንቱና መኳንንቱ ህዝቡን ካጫረሱና ካጣሉ በኋላ በጋብቻም በእርቅም መልሰው ሲተሳሰሩ ነበር፡፡

ጸበኞች ሆነው ነገር ግን በጋብቻ የተሳሰሩት የደጃች ገብረስላሴና የራስ ሰዩም ፍልሚያ እስከ አሁን ድረስ የዘለቀ በዓድዋና በእንደርታ ህዝብ መካከል ጥላቻን ተክሎ ያለፈ ነገር ሆኗል፡፡ ይህ የክፍለ-ግዛቶቻቸውን ወሰን ተከትሎ ወደ ህዝብ እንዲሰርጽ ያደረጉት የጥላቻ ስሜት በወያኔ አመጽና በህወሓት ትግልም በአስከፊ ሁኔታ ተንጸባርቋል፡፡ አራቱም የወያኔ የበላይ መሪዎች የእንደርታ "ባላባቶች" ነበሩ፡፡ እንደርታ የራስ ስዩምና የራስ ጉግሳ የዘር ሃረግ የሚመዘዝበት በመሆኑ ከዓድዋው የደጃች ገብረሰላሴ ጎራ በጎ አመለካከት ይቸረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የወያኔን አመጽ ለማክሸፍ ምንም እንኳ የእንግሊዝ አውሮፕላኖችና የጦር ስልት አዋቂዎች፤ የአፄ ሃይለስላሴ ከፍተኛ የጦር አዛዦች የተሳተፉበት የግፍ ዶፍ የወረደ ቢሆንም የዓድዋው ደጃች ገብረ ህይወት ከንጉሱ ጎን መሰለፍ ያስከተለው ስነአእምሯዊ ጫና ቀላል አልነበረም፡፡ ማእከላዊ መንግስት እንደ በፊቱ የትግራይን መሳፍንት ልዩነት ተጠቅሞ ተሳክቶለታል፡፡

"ዳግማይ" ወያኔ ነው ተብሎ የተነገረለት የተሓህት/ህወሓት የትጥቅ ትግል ማእከሉ ያደረገው የመጀመሪያው ወያኔ በተካሄደበት የራስ ስዩም ግዛት በነበረው መቐለና በዙሪያው በነበሩ አምስት አውራጃ ግዛቶች ሳይሆን የደጃች ገብረስላሴ ግዛት በነበረው ሰሜን ምእራብ ትግራይ (አኹሱም፤ ዓድዋና፤ ሽሬ) ነበር፡፡ የህወሓት መስራችና ዘላቂ አመራሩም በዋናነት ከዓድዋ ተወላጆች እጅ አልወጣም ነበር፡፡ በትግሉ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት በተደረገው ከፍተኛና አሳማኝ ቅስቀሳ ወጣቱ አውራጃ ሳይለይ ከመላው ትግራይ ለትግል ወደ ሜዳ ጎርፏል፡፡ በውስን የአካባቢ ስሌት የተዋቀረው የህወሓት አመራር ከመላ ትግራይ

በመጡና የላቀ የመምራት አቅም በነበራቸው ታጋዮች ከባድ ፈተና ገጠመው፡፡ የአመራር ስነመህዳሩ እጅግ ከመጥበቡ የተነሳ በምክክር ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ቀላሉን ግን አደገኛው መንገድ ተመረጠ፡፡ "ህወሓትን ለማፍረስ ከደርግ የተላኩ" በሚል ውንጅላ ድርጅቷ ልትበተን ካፋፍ ደረሰች፡፡ ተዳፍኖ ሲግም የኖረው መሳፍንቱ የተከሉት የአውራጃ ልዩነትም አይኑን አፍጥጦ መጣ፡፡

በርከት ያሉት የህወሓትን የትጥቅ ትግል የጀመሩት አንኳር አመራሮች የትግራይ መኳንንት ልጆችና የልጅ ልጆች ነበሩ፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ማርክሳዊ ርእዮተ አለምን ተቀብለው "ጸረ-ፊዩዳልና ጸረ-ካፒታሊስት" በመሆናቸው የአባት አያቶቻቸውን ፈለግ ተከትለው የትግራይን ህዝብ በአዲስ አይነት የአገዛዝ ስርአት ስር ይጥሉታል ተብሎ አልታሰበም፡፡ እነዚህ የወጣትነት እድሜያቸውን በዱር በገደሉ ሲንከራተቱ የፈጁት ሰዎች በስተርጅና በትግራይ ህዝብ ላይ ከብረው ስልታዊ በሆነ የአግዛዝ ስርአት ተብትበው ያስሩታል ብሎ ህልም ያየ የለም፡፡

**3.3 የትግራይዋ ህወሓትና የትግራዮቹ ካድሬዎች**

ከአጼ ሚኒሊክ ጀምሮ የአዲስ አበባው አገዛዝ የተገነዘበው ነገር ቢኖር ትግራይን በውስጥ ሰይጣን እንጂ በውጭ መልአክ ማስተዳደር እንደማይቻል ነው፡፡ በህወሓቱ የትግል ዘመን በትግራዩ የደርግ የግድያ ክንፍ በነበረው "የህዝብ ድርጅት" ዋና ጽ/ቤትና የመላ ትግራይ የአውራጃና የወረዳ ቅርንጫፎች ውስጥ ከተጋሩ ውጪ የማንም ሌላ ብሄረሰብ አባል አልነበረም፡፡ በጽ/ቤቱ ስር የተደራጁት ነፍሰ በላዎች በህወሓት አባልነት የተጠረጠሩትን ዘመዶቻቸው ሳይቀር የግፍ አገዳደል ሲገድሉ በዛች በትግራይ ምድር የዘር ሃረግ መዘው የተፈጠሩ አይመስሉም ነበር፡፡ የደራሲውን ታላቅ ወንድምና አብሮ አደግ ጓደኛ በጥይት ደብድበው ሜዳ ላይ ለአሞራ ቀለብነት የሰጡ አረመኔዎች ነበሩ፡፡

ህወሓት ዓድዋን ማእከል ያደረገ የስሜን ምእራብ ትግራይ ትግል ነው ብለው የደመደሙት የራያና የእንደርታ ወጣቶች "ዘንዶ-ሰራዊት" እና "አዞ-ሰራዊት" የሚባሉ የታጠቁ "ጸረ-ሽብር" ቡድኖችን ፈጥረው ከህወሓት ጋር ሲያደርጉ የነበረው ውጊያ የትግራይን ህዝብ ግራ ያጋባ ነበር፡፡ ህዝቡ ህወሓትን ሲያስጠጋ ሌሎቹ ይመጡበትና ያንገላቱታል፤ ሌሎችን ሲስጠጋ ደግሞ የህወሓትን ቁጣ የሚሸከምበት አቅም አልነበረውም፡፡ ልጆቻቸውን ገድለው ከጣሉ በኋላ እናቶችን ከበሮ አስይዘው እንዲጨፍሩ ያስገድዱ ነበር የተባሉት የእፉኝት ልጆች

በስተመጨረሻ ውለታቸውን ሳይቆጥር የበላቸው ለግድያ ያሰማራቸው ወታደራዊ መንግስት ነበር፡፡ በመላ ትግራይ እንደተምች ተሰራጭተው የነበሩት ካድሬዎችና አስተዳዳሪዎች በወረንጦ ተለቅመው በማእከላዊ ምርመራ ድርጅት ማጎርያ ቤት ወስጥ የመርማሪዎች "የወፌ-ላላ" ድግስ ሆኑ፡፡ በአመራር ላይ የነበሩት ደስታ ታደሰና በላይ በርሄ ተረሸኑ፡፡ ከዚህ የሚማር ግን የለም፦ "አሉታ ኮቲኑዋ!"፡፡

## 3.4 ህወሓትና የኤሪትርያ የነጻነት ትግል እስከ ድል

ወያነ የከሸፈው ወደ ሁለተኛ አመቱ ሳይሸጋገር ነው፡፡ ለህወሓት ምስረታ በምክንያትነት የተሰጠው የወያነ አመጽ የከሸፈው "መሪ ፓርቲ ስላልነበረው" ነው የሚል ነበር፡፡ በአስራ ሰባት አመታት ቆይታ ሞትና ጉዳት ከበረከተበት ትግል በኋላ ድል የተገኘው መሪ ፖርቲ ስለነበረው ነው? በአላማው ትክክለኛነት ህዝባዊ ተቀባይነት ሰላገኘ ነው? የኤሪትርያ ትግል የወታደራዊውን መንግስት አቅም በመበታተኑ የህወሓትን ትግል ነጥሎ ማዳከም ስለተሳነው? ወይስ በውስጥ አለመረጋጋትና ለሶሻሊስቱ ወታደራዊ መንግስት የማይመች አለም አቀፋዊ ለውጥ ተጽእኖ ስር በመውደቁ? ትክክለኛ መልሱ፦ "ሁሉም መልስ ነው"፡፡ መጠየቅ ያለበት ግን የትኛው ምክንያት ሚዛን እንደሚደፋ ነው፡፡

ህወሓት ከድል በኋላ መተግበር የቀጠለችው ከመነሻ አላማዎቿ የትኞቹን ነበር? መጀመሪያ የትግሉ መነሻ የነበረውን "የመደብ ትግልን እንደ ግብ፤ ብሄረተኛነትን እንደ ትግል ስልት" የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የህወሓት ትግል የጀመረው ወታደራዊው መንግስት የዘውድ(ፊዩዳል) ስርአት ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረት ድምጥማጡን ባጠፋበት አመት ነበር፡፡ ይህ እርምጃ የህወሓት አመራሮች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ሲጮሁለት የነበረው የትግል አላማ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ የሚታሰብ የመደብ ትግል ማን በማን ላይ እንደሚካሄድ እንቆቅልሽ ሆነ፡፡ ህውሓት ትግል ስትጅምር የመደብ ትግሉ ተጠናቆ ነበር፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ የመደቦች ልዩነት ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ መሰረቱ መሬት ስለነበረ፡፡ ከዛ በተጨማሪም እንደ ህወሓት ሁሉ ወታደራዊ መንግስትም የሶሻሊስት ርእዮተ አለም ተከታይ ስለነበረ ለትብብር እንጂ ለግድድር የሚጋብዝ ነገር አልነበረም፤ የኔ ሶሻሊዝም ካንተው ይበልጣል ካልሆነ! አንዱ ሰብአዊ ሌላኛው ኢሰብአዊ ነበር ብሎ በመፈራረጅ የመጣ ልዩነት አለ ከተባለም ከሁለቱም ወገን ለስልጣኑ ቀናኢ የሆነው ሁሉ ከግድያ አልቦዘነም፡፡

እስከ ህወሓት ምስረታና መጠናከር ድረስ በነበሩት የዘውዳዊው ስርአት አመታት የኤሪትርያ ነጻነት ትግል እጅግ ደካማና የጎላ የኤሪትርያ ህዝብ ድጋፍም ያልነበረው ነበር፡፡ ለዚህም የሚሰጠው ምክንያት አጼ ሃይላስላሴ ፌዴሬሽኑን ቢያፈርሱም ከወታደራዊ ዘመቻ ይልቅ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ አያያዛቸው ለኤሪትርያ ህዝብ የተወሰነ መረጋጋት ፈጥሮ በኢኮኖሚው ረገድ ጠንክሮ ሲሰራ ስለነበር ነው የኤሪትርያ ህዝብ የነጻነት ትግሉን ብዙም ያላዳመጠው፡፡

ወታደራዊው መንግስት ስልት ባጣ ጉልበተኝነት የኤሪትርያ ህዝብ የሚያከብራቸውንና ለሰላማዊ መፍትሄ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበሩትን የኢትዮጵያ ጀግና ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን በመግደሉ፤ በተጭማሪም አሜሪአካውያንን፤ ጣሊያኖችን፤ አረቦችን በማባረር የኤሪትርያን የኢኮኖሚ መሰረት በመናዱ፤ ዘመናዊነት ኑሮና ቅንጦት ወዳድ የነበሩትን የኤሪትርያ ወጣቶች በከተማ ሽብር መድረሻ በማሳጣቱ የነጻነት ትግሉ ከስራና ከኑሮ በተፈናቀሉ ተስፋቢሶች ተሞላ፡፡ ወታደራዊው መንግስት የኤሪትርያን ትግል በወታደራዊ ሃይል አምበረክካለሁ ብሎ ስለቆረጠ ከሶማልያ ጦርነት መልስ "ሁሉም ነገር ወደ ሰሜን ጦር ግንባር" ብሎ ነበር የሁለት አስርት አመታቱን አውዳሚ ጦርነት የቀጠለው፡፡ ወታደራዊው መንግስት ትግራይ ነጻ ሆኖለት ቢሆን ኖሮ በኤሪትርያ ታጋዮቸ ላይ ያካሄደው ጦርነት በስኬት ይጠናቀቀ ነበረን?

ምንም እንኳ ኤሪትርያውያን የትግራይን ሰዎች በኤሪትርያ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል ሲወነጅሉ ቢቆዩም የህወሓት አመራሮች ከጅምሩ ለኤሪትርያ የነጻነት ትግል ድጋፍ እንደነበራቸው ይታወቃል፡፡ የዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ትግልም የኤሪትርያ ነጻነት ታጋዮች መዳፍ ውስጥ እንደነበረ ይጠረጠር ነበር፡፡ ጉዳዩን ከጥንታዊት አኹሱም ጋር በማገናኘት ይሁን ህዝብን ከጭቆና የማላቀቅ መርህ ተከትለው፤ ወይም ከአዲስ አበባ መንግስታት ጋር በነበራቸው አለመምቻቸት የህወሓት መሪዎች ሳሕል ድረስ በመሄድ ወታደራዊ ስልጠና መውሰዳቸው ለኤሪትርያ የነጻነት ትግል የነበራቸውን ድጋፍ የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ ኤሪትርያ ምድር ውስጥ ገብተው ተሰወሩ እየተባለ ከቀድሞ የህወሓት አመራሮች የሚነገረው አስገራሚ ታሪክ፤ ስለ ትግራይ ሳይሆን ስለ ኤሪትርያ ትግል መጽሃፍ ጽፈው ከጳጳሱ የበለጡ ካቶሊክ የሆኑበት አጠያያቂ ነገር ህወሓት የተሰራው ለትግራይ ወይስ ለኤሪትርያ ብሎ መጠየቅ የሚያስደነግጥ አይሆንም፡፡

የትግራይን ህዝብ እንደ አገዳ መጦ መጣሉ ደንታ የማይሰጠው የትግራይ ልሂቅ ለኤሪትርያ ነጻነት የትግራይን ህዝብ ደም መገበሩ የሚያስደንቅ አይሆንም።

የኤሪትርያ ታጋዮች ግንኙነት ከህወሓት ጋር ብቻ አልነበረም። ከራስ መንገሻ ስዩሙ ኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት፤ ከኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ሰራዊት ጋርም በጋራ ወታደራዊ ኦፐሬሽን እስከማካሄድ የሚደርስ ግንኙነት ነበራቸው። የኤሪትርያ ታጋዮች ፍላጎት ከማንም ጋር ተባብረው የኢትዮጵያን ጦር ማሸነፍ እንጂ ስለትግራይ የወደፊት እጣ የሚጨነቁበት ነገር አልነበረም። ህወሓት የትግራይ ሪፑብሊክ ብላ የነጻ ሃገር አጀንዳ በከተበችበት ወቅት የኤሪትርያ ታጋዮች ድጋፍ እንዳልነበራት እሙን ነው። በኢትዮጵያና በኤሪትርያ መካከል ነጻ አገር መኖር ለኤሪትርያ የኢትዮጵያ ህልም የሚበጅ አልነበረም። ይልቁንም የኤሪትርያ ታጋዮች ህወሓትን ሲገፉፉ የነበሩት ከኢትዮጵያ ደርጅቶች ጋር ህብረት እንድትፈጥር ነበር። ማየት የፈለጉት የኢትዮጵያ አንገት አንድ እንዲሆንላቸውና በአንድ እንደልባቸው የሚያሽከረከሩት የፖለቲካ ሃይል እጅ እንዲሆንላቸው ነበር፤ በአንድ ምት ለመቀንጠስ እንዲመቻቸው!

ህወሓት የኤሪትርያ ታጋዮች በተጫኑት ቁጥር የማኩረፍ አቅም አልነበረውም፤ በአንዳንድ ስብሰባዎች ሻዕቢያን በአድሃሪነት ከማማት በስተቀር። ሁለቱም መጣላታቸውን በአይነ ቁራኛ ለሚጠብቀው የኢትዮጵያ ጦር ሰርግና ምላሽ እንዲሆን አልፈለጉም። የኤሪትርያ ታጋዮች ትግራይ ውስጥ እንደልብ መንቀሳቀስ በመቻላቸው የኢትዮጵያን ጦር እንቅስቃሴ ገና ወደ ኤሪትርያ ምድር ሳይገባ ያሰናክሉት ነበር። ድሮውም ትግራይ የተፈለገው ለዚህ ነበር። በራዛ ዘመቻ ወደ ኤሪትርያ የጎረፈው ሚሊሺያ የተረፈረፈው ትግራይ ውስጥ ነበር፤ የኢትዮጵያ ሜካናይዝድ ጦርም በህወሓትና ሻዕቢያ ትግራይ ውስጥ እንክትክቱ ወጥቷል። የሽሬው ወሳኝ የመጨረሻ የትግራይ ውስጥ ውጊያ ሻዕቢያም እንደተሳተፈበት ይነገራል። ሳሕል ሄደው የተሰዉት የህወሓት ታጋዮች ሻዕቢያ ሳይሆን ቤታቸው ይቁጠራቸው። ከዚህ ሁሉ ውለታ በኋላ ሻዕቢያ ትግራይን እንደዚህ ማውደሙ ማክያቬሊን የሚያስንቅ ቀዝቃዛ ፖለቲከኛ እንደሆነ ህያው ማረጋገጫ ነው።

ህወሓትና ሻዕቢያ እከክልኝ ልከክልህ እየተባባሉ ለድል በቁ ቢባልም ለህውሓት አዲስ አበባ መግባት ወሳኝ ሚና የተጫወተው የአማራ ህዝብ ትብብር ነበር። መንግስቱ ሃይለማሪያም የኢትዮጵያም ሆነ የኤሪትርያን የፖለቲካ አያያዝ

አላውቅብት ብሎ ግፍ በማብዛቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ከደርግ የተሻለ እንጂ የባሰ አይኖርም በሚል እምነት ለህወሓት የአዲስ አበባ ጉዞ የከረረ ተቃውሞ አልነበረውም፡፡ የነበረው የአማራ ህዝብ ድጋፍ ሚምቶ መንገዱን ጨርቅ ሳይሆን እሾህ ያደረገባት አሜሪካ ውስጥ በሾለከ አንድ ከባድ ምስጢር ነበር፡፡ ለነገሩ ምስጢሩ በከፍተኛ የህዝብ ንቀትና ማናለብኝነት ስሜት አደባባይ ላይ የተለቀቀ ነበር፡፡ አንድ የህወሓት አመራር አባል በስብሰባ ላይ "አዲስ አበባ እንደገባን የኤሪትርያ ነጻነቷን እናጸድቅላታለን" ብሎ እንደዋዛ የወረወረው ቃል ህዝቡ የመርዶ ያህል ነበር የሰማው፡፡ ህወሓት ወደ አዲስ አበባ በገሰገሰባቸው ጎዳናዎች ላይ የነበረው የአማራ ህዝብ "እነዚህ የአጼ ዮሃንስ ልጆች በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ላይ አይደራደሩም" የሚል ሙሉ እምነት ነበረው፡፡

## 3.5 የህወሓት ወስጠ-ፓርቲ ህይወት፤ የትግራይና ኢትዮጵያ አስተዳደር

ሽኩቻውና መጠፋፋቱ እንዳለ ሆኖ በትግሉ ወቅት የነበረው ዲሲፕሊን የጾታ ግንኙነት እንኳ በሞት የሚያስቀጣ ነበር፡፡ በጊዜ ሂደት የትግሉ አቅም በመፈርጠሙና የድል ተስፋ በመስፈኑ የትግል ሜዳው ወደ "እንሰሳት እርሻ"ነት ተቀየረ፡፡ ባልተጻፈ ህግ መሰዋት ያለበትና መሰዋት የሌለበት ለየ፡፡ ሚስት አግብቶ የሚወልድ መኖሪያ ቤት ያለውና እናቱ የልጅ ልጅ ሳታይ የሚሰዋው "መደዴ" ሰሌዳ ያለው ያህል የሚታወቅ ሆነ፡፡ ወይ የመደብ ትግል! ወይ የጸረ-ጭቋኖች ትግል! ብዙ ናፖልዮኖች፤ ብዙ ስኲለሮች፡ ብዙ በጎች፤ ብዙ ታማኝ ቦክሰሮች፤ ብዙ ጠባቂ ሶሎግ ውሾች፡፡ መጀመሪያ "ማንም ታጋይ የጾታ ግንኙነት ማድረግ አይችልም"፤ ቀጠሎ "የጾታ ግንኙነት እንጂ ማግባት አይቻልም"፤ ከዛ "ማግባት ይቻላል፤ ልጅ መውለድ አይቻልም"፤ ወዘተ፡፡ በአለም ላይ የመደብ ልዩነትን አጠፋለሁ የሚል ሁሉ ሲፈትል የሚያድረው የመደብ ልዩነትን ነው፡፡

ህወሓት ትግራይን ተቆጣጥራ ወደ አማራ መገስገስ ስትጀምር ሲነገራቸው ከነበረው የትግሉ አላማ አኳያ ነገሩ አልገባቸው ያለ በሺዎች የሚቆጠሩ ታጋዮች ወሎና ጎንደር ሄደው የሚሞቱበት ምክንያቱ አልተገለጠላቸውም ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ ታጋዮች የተነገራቸውም የሚገባቸውም የድርጅቱ ስያሜ በግልጽ እንደሚያመለክተው የአስራ ሰባት አመት መራራ ትግልና መስዋእትነት ትግራይን ነጻ ለማውጣት እንጂ የህወሓትን መሪዎች አዲስ አበባ ደረስ ሸኝቶና ለአገራዊ ስልጣን አብቅቶ እንደጉም መበተን አልነበረም፡፡ ብዛት ያላቸው ታጋዮች ወደ

ትግራይ መመለስ ሲጀምሩ በተለመደው የጓይላ ምትሃትና ሆድ የሚያባባ ስብከት ተመልሰው ረኸሙን ውጊያ ተያያዙት፡፡ አዲስ አበባ ላይ ከመላ ኢትዮጵያ ከመጡ የፖለቲካ ቡድኖች ጋር ስልጣን ለመጋራት፤ የጦር ሃይሉንም የብሄር ተዋጽኦ ለማስተካከል ሲባል በሺዎች የሚቆጠሩ “ማስቲካዎች” ተቀንሰው የትም ወድቀው ቀሩ፡፡ ቤቱ ተቀምጦ ስልጣን የዘነበለት የብሄር ፓርቲዎች አመራርም ለምስጋና ጊዜ አልነበረውም፤ የሙስናው በር ወለል ብሎ ተከፍቶ ነበርና፡፡ ይህ ሁሉ የሁለት አስርት አመት መከራ እንደ አጼ ሃይለስላሴ፤ እንደ ራስ ስዩም፤ እንደ ደጃች ገብረስላሴ አራት ኪሎ ተቀምጦ ትግራይን ከሩቅ መቆጣጠር ሆነ፡፡ ለህወሓትና ለሁሉም የብሄር ፓርቲዎች አመቺ የሆነው የፌደራል ህገ መንግስት ከአማራው በኩል ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡

የህወሓት አመራር በኢትዮጵያዊነት አራማጅ ሃይሎች አይንህ ላፈር የተባለው በተለይ በህገ መንግስቱ ውስጥ በሰፈረው አንድ አንቀጽ ነው፡፡ አንቀጽ 39 የብሄር ክልሎች እስከ መገንጠል ሊደርስ የሚችል የራስ እድል በራስ የመወሰን መብት ያቀዳጃል፡፡ ይህ በየትም ሌላ አገር ያልተሰጠ መብት ነው፡፡ የህዝብ እውነተኛ ፍላጎትና ድምጽ በአግባቡ በማይሰማበት በኢኮኖሚ ወደኋላ በቀረው አለም፤ ግለሰቦችና የፖለቲካ ቡድኖች ያሻቸውን ውሳኔ ማስወሰንና መተግበር በሚችሉበት አገር ይህ አንቀጽ ባለበት ኢትዮጵያ ያለመበታተን ዋስትና ይኖራታል ማለት ቅዠት ነው፡፡ ይህ አንቀጽ ለኤሪትርያ ተለክቶ የተሰፋ እንደሆነም መጠርጠር ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያን ሊበትን የሚችል ህጋዊ መብት የተነደፈው አጼ ሚኒሊክ ከመቶ አመት በፊት ወደ አቢሲኒያ በቀላቀሏቸው ህዝቦች ቢሆን መረዳት ይቻል ኖሮ ይሆናል፡፡ ይህ አንቀጽ በስንት ሙግት ያካተቱት የፖለቲካ ሃይሎች ግን የኢትዮጵያ መሰረት ነው በሚባለው ክልል የተፈጠሩ ፖለቲከኞች ናቸው፡፡

ለኢትዮጵያውያን ይህ እንቆቅልሽ ነበር የሆነባቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የኤሪትርያን መገንጠልና ኢትዮጵይያን የባህር በር የማሳጣቱ ቅንብር የተከወነውም ከትግራይ በተገኙ የህወሓት አመራሮች ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን አንድ ለየት ያለ ባህርይ አላቸው፡፡ ማንም ይምራቸው ማንም የኢትዮጵያን ጥቅም ለሚያስጠብቅ ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ እየተራቡም ቢሆን ስለኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ከመጨነቅ አይቦዝኑም፡፡ ህወሓት የደፈረችው ስሜት ይህን ነበር፡፡ ህወሓት ስለኤሪትርያ መገንጠል የምትሰጠው ማሳመኛ ኤሪትርያውያን

ለነጻነታቸው ስለታገሉ “እንደ ነጻነት ወዳጅ” ይህን የመከልከል ፍላጎትም አቅምም እንደሌላት ነው፡፡ ይህ በዴሞክራሲ መርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በእውነታው የአገር አስተዳደር አለም ግን እንዲህ አይነት “ቅዱስነት” ህዝብ የሚቀበለው አይደለም፡፡ የአለም ታላቋ ዴሞክራሲ አሜሪካ ብሄራዊ ጥቅሟን በሚመለከት ሉአላዊ ሃገራትን በቦምብ ከማጋየት ወደ ኋላ አትልም፡፡ ኤሪትርያ መገንጠል ሲፈቀድላት ኢትዮጵያን ገድላ መሆን የለበትም፡፡ ሁለቱም አሸናፊ የሚሆኑበት እንጂ አንዱ በሌላው መከራ ነጻ የሚሆንበት ድርጊት ፍትሃዊ አይደለም፡፡ ኤሪትርያ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ወታደራዊው መንግስት ሚዛን ለመጠበቅ የወሰደው ጂኦፖለቲካዊ እርምጃ ነበር፡፡ ይህም አሰብ አውራጃ የአውሳ ታሪካዊ አካል ናት በሚል የ”አሰብ ራስ ገዝ” አስተዳደር የሚባል ከልል ፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

እዚህ ላይ ጠንቅቆ መገንዘብ የሚያስፈልገው የኤሪትርያ ትግል “ጸረ-ኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ” ነበር የሚለው በይፋ የተነገረ እንጂ በሚስጥር የተጠበቀ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ የኤሪትርያ ቅኝ ገዢ ነበረችን የሚለው ክርክር ወደ ጎን ትተን በተመረጠው የጨዋታ ህግ መጫወት አማራጭ የለውም፡፡ የጨዋታው ህግ የአፍሪካ አንድነት የደንበሮች ውሳኔ ነው፡- “አገሮች የቅኝ ግዛት ድንበሮችን ህጋዊ ያድረጉ” የሚል፡፡ በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ “እንደ ቅኝ ገዢ” የመጨረሻ የሰራችው የውስጥ አስተዳደር ካርታ ለድንበር ማካለሉ መነሻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ኤሪትርያ ነጻ መውጣት የነበረባት “የኤሪትርያ ራስ ገዝ” ሆና እንጂ አሰብን ጨምራ አልነበረም፡፡ የህወሓት አመራር ኢትዮጵያን በፍቅር ለማስተዳደር ኢትዮጵያን የማፍቀር ግዴታ አለበት፡፡ የኔ ናት የማይላትን አገር የሚያስተዳድር መሪ ሊሆን የሚችለው ቅኝ ገዢ ብቻ ነው፡፡ ጥያቄው ህወሓት ኢትዮጵያን ያስተዳደረቺው በአገር ልጅነት ነው በቅኝ ገዢነት? ማንኛውም ዋጋ ከፍሎ የአገርን ብሄራዊ ጥቅም መጠበቅ የአገር አስተዳደር ፎርሙላ ነው፡፡

አንድ ተንታኝ የተናገሩትን በዚህ አውድ ውስጥ ማንጸባረቅ ተገቢ ይሆናል፡- “ህውሓት የኢትዮጵያን ህዝብ የባህር በር አሳጥታ ካሳፈነች በኋላ የትምህርት ተቋማትን ብታስገነባ፤ የጤና አገልግሎትን ብታስፋፋ ማካካሻ አይሆንም”፡፡ እውነት ነው ልማት በማንኛውም አገር ቅድሚያ የሚሰጠውና ህዝብን የሚያስደስት ቢሆንም አፍንጫውን ይዞ ሰውን በአፉ ምግብ ማጉረስ መግደል እንጂ ማኖር ሊሆን አይችልም፡፡ ህዝብ መተኪያ በሌላት አገሩ ጉዳይ ላይ ደረጃ

የሚያወጣበት ባህል አለው፡፡ ምንም ቢሆን ከባህር በር ሆዱን አያስቀድምም፤ ላገሩ ነጻነት ብሎ ምትክ የሌላትን ህይወቱን የሚሰዋ ህዝብ፡፡ ይህ ጉዳይ የአሁን ሳይሆን ስለሚወልዳቸው የልጅ ልጆቹ ኑሮም ስለሚያስብ ነው፡፡ አያቶቻችን ቅኝ አገዛዝን ያልተቀበሉት ለራሳቸው መስሎ ማደር ስላቃታቸው ሳይሆን የልጅ ልጆቻቸው አሽከሮች ሆነው እንዳይቀሩ በመስጋት ነበር፡፡

ህውሓት የራሷ አስተሳሰብ ሳይንሳዊ የሌላው አስተሳሰብ አድሃሪና ጥንታዊ አድርጋ የምታስብ ደካማ ድርጅት ናት፡፡ ለዚህም ነው አሰብን በሚመለከት በሚነሳው ጉዳይ ላይ የምታንጸባርቀው አስተሳሰብ ሃላፊነት የጎደለው ነው፡፡ መለስ ዜናዊ “አሰብን አንጠይቅም፤ ለኤሪትርያም ቢሆን አይጠቅማትም፤ የግመል ውሃ መጠጫ ልታደርገው ካልሆነ” ብሎ የተሰጠው መልስ በኢትዮጵያውያን ቁስል ላይ ጨው እንደማርከፈከፍ ነው፡፡ ትእቢትና ማናለብኝነት የመሪዎች የፖለቲካ መሳሪያ ነው፤ መጥፊያቸውም እሱ ነው፡፡ አሰብ የተቃጠለ የደንከል በርሃ ነው፡፡ የሚጠጣ የገጸ-ምድር ዉሃ የለም ራቅ ያለ የከርሰ ምድር እንጂ፡፡ ግመል ከባህሩ ጨዋማ ዉሃ ይጠጣል ለማለት ከሆነ በከባድ ቁምነገር ላይ ማላገጥ ይሆናል፡፡ ከመለስ ዜናዊ የሚጠበቀው መልስ እንደ መሪ ወደ ኢትዮጵያ ያጋደለ እንጂ የውጪ ሰው የሚያስመስል አስተያየት አይደለም፡፡ መለስ ዜናዊ ማለት የነበረባቸው ቢያንስ፡- “እንደ ኢትዮጵያዊ መሪም እንደ ኢትዮጵያዊም የኢትዮጵያ ፍላጎት የኔም ፍላጎት ነው፤ አዎ የራሳችን ወደብ ያስፈልገናል”፡፡

ከህወሓት ጋር ከፍተኛ አተካራ የገጠመው የአርበኝነት የፖለቲካ ሃይል በውጪም በአገር ውስጥም ህውሓትን ለማሽመድመድ ከፍተኛ አቅም የነበረው ነበር፡፡ ህወሓት ይህን የፖለቲካ ሃይል በዱላ ሳይሆን በካሮት ብዛት ማለስለስ ተመራጭ መሆኑን ተገነዘበች፡፡ ሃቅ የያዘ አይፈራም አይለማመጥም፤ አዲስ አበባ የሰፈረው የህወሓት አመራርና የቢስነስ ልሂቅ ግን “ምን ያለበት ምን አይችልም” እንደሚባለው በከፍተኛ ሃብት የማካበት ተግባር በተሰማራበት ተቀናቃኞችን በሙስና ውስጥ እጃቸውን እየነከረ አልፈሰፈሳቸው፡፡ በዚህ ሂደት ትግራይ መረሳቷን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ እውነት ነው ትግራይ በፋብሪካዎችና በሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ተጨናንቃለች፤ በሃብት ብዛት “ልትሰምጥ” ነውም ተብላለች፡፡ ይህ በጥቂቶች የስልጣንና የዝምድና መረብ እጅ የተያዘ ሃብት እንጂ በሚልዮን የሚቆጠር ህዝብ በህወሓት የእርዳታ ጥገኝነት ስር እንደሚማቅቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙም የሚገነዘበው ነገር አልነበረም፡፡

“ትግራይ ከኢትዮጵያ በተዘረፈ ሃብት ከብራለች” ሲባል የህወሓት መሪዎች የሚያበረታቱት መልካም ዜና ነበር፡፡ በትግራይ ቴሌቪዥን ጣቢያዎችና በአዲስ አበባው የትግርኛ ስርጭቶች የሚቀርቡት የትግራይ ኑሮ ምርጥ ምርጦቹ እየተለዩ ስለነበር በትግራይ ላይ ላሳደረው የተዛባ አመለካከት የኢትዮጵያን ህዝብ ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም፡፡ በህወሓት ሰፈር የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ህዝብ መጠላት የህልውና ዋስትና ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ህዝብ ሁሉም ሲጠላውና ወገን ሲያጣ ለስራም ለሞትም ታዛዥ ይሆናል፡-“…ቢጭኑት አህያ፤ ቢለጉሙት ፈረስ”!

የህወሓት አመራር የስራና የመኖሪያ ቦታ ለሁለት ተከፍሎ ነበር፡- “የመቐለ አመራር” እና “የአዲስ አበባ” አመራር፡፡ “ምርጥ ምርጡ” አዲስ አበባ ሲመደብ “ግርድ ግርዱ” መቐለ ተቀምጦ ስለአዲስ አበባ ያዛጋል፡፡ አዲስ አበባ ያለው በፌደራል ስም ትግራይ ባሉት የማይገመገም ሲሆን ትግራይ ያሉት ግን የራሳቸውን የአይን ውስጥ ምሰሶ በማያዩት የህወሓት ፌደራሎች ቆዳቸው እስኪፋቅ ይተቻሉ፡፡ ትችቱ “አመድ በዱቄት እንደመሳቅ” ያለ ነው፡፡ የህወሓት ዋና ጽ/ቤት ትግራይ ውስጥ ሆኖ እያለ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባዎች አዲስ አበባ የሚካሄዱበት ምስጢር ምን ነበር? በታገሉበት ምድር ላይ ምቾት እንዳያጡ? የኋላ ኋላ ግን ትግራይ ያሉትና ከአዲስ አበባ የሚሄዱት ከህዝቡ ነጠሎ የራሳቸው አለም የፈጠረላቸው ፕላኔት ሆቴልና አፓርታይድ ሰፈርን ፈጥረዋል፡፡ የከፋ ቀን ሲመጣ ግን ከተጸየፉት ጋር አጎዛ አንጥፈው ገበሬ ቤት መድብ ላይ ተኙ፡፡ “ልምድ ሁለተኛ ተፈጥሮ ነው” እንደሚሉት እንግሊዞች ከ”መኸተ” መልስ ወደ ነበረበት ተመልሶ አንድነአትችን ይጠበቅ ሳይሆን “ርቀታችን ይጠበቅ” ሆነ፡፡

ህወሓት በጦር ሃይል አዲስ አበባ ገብታ እንደተደላደለች በሃይል የተገኘውን የአዲስ አበባ ቆይታ ወደ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ መረጋጋት ለመቀየር በርካታና ውስብስብ የፖለቲካ ጨዋታዎች ተጫውታለች፡፡ የኢህአዴግ ምስረታ፤ በክልል የአጋር ድርጅቶች በጥቅም መታሰርና ታዛዥነት፤ ህዝብን የሚያማልሉ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትና የድህነት ቅነሳ እርምጃዎች፤ አስደናቂ የሆነ አለም አቀፋዊና አፍሪካዊ ዲፕሎማሲ፤ በመሰረታዊ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ላይ እንደማተኮር የህወሓትን ስልጣን በህዝብ የሙቶ ስሌት የዘር ጥላቻ ፖለቲካ ሲያራምዱ የነበሩትን አቅመ ቢስ ተቃዋሚዎችን ሽባ በማድረግ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ላልተወሰነ ጊዜ ለመቆጣጠር አመቺ ሁኔታን ፈጥሮላት ነበር፡፡

ይህ መረጋጋትና ያልተገደበ የስልጣን ቆይታ በህወሓት አመራርና አባላት ዘንድ የፈጠረው ብዥታ ነበር፡፡ ብዙዎቹ ቀበቷቸውን አላልተው ትራሳቸውን ዝቅ አድርገው አንቀላፍተው ነበር፤ ከህወሓት ስልጣን መቀማት የሚችል ጠንካራ ሃይል የለም በሚል በየዋህነት ስሜት፡፡ በልጅነት ያነበቡት የዳዊትና የጎልያድ የመጽሓፍ ቅዱስ ታሪክ ዘንግተውት ይሆናል፡፡ ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና በአንድ ወቅት "ህውሓቶች ከስልጣን ቢወርዱ እንደ ድሮ በርሃ መሄድ አይችሉም፤ ወፍረዋል" ብሎ የህውሓት አመራርና አባላት መዘናጋትን በጥሩ ቋንቋ ገለጾታል፡፡



ሆኖም የከሳ ህዝብ ስለነበራቸው ውፍረታቸው በርሃ ከመግባት አላገዳቸውም፡፡ እንደ ሙሽራ ሄደው፤ እንደ ሙሽራ ቆይተው፤ እንደ ሙሽራ ተመልሰዋል፡፡ ድሮውንም የተማመኑት በህዝቡ ምርጫ አልባነት ነበር፡፡ እነሱ ሲያንሰራሩ ህዝቡ ግን እንደከሳ ቀርቷል፤ ምናልባት ለሌላ የበርሃ ቆይታ! በርሃ እያሉ መደብ ላይ እያስተኛ ጠባቂው ህዝብ ነበር፤ ከተማ ሲገቡ ግን ጠባቂው ሲያዩት የሚያስፈራ ቦዲ-ጋርድ ሆነ! መጠበቅ ከማን? ከጠበቀው ህዝብ? የበፊቱ ገዳይ ወዳጅ ሆኖ በሚላላሱበት? የህወሓት አመራርና አባላት ብቻ ሳይሆኑ ቀሪውም የትግራይ ልሂቅ የሚፈልገው ህዝብ "ደረጃውን" ጠብቆ እንዲያገለግል እንጂ እኩል ሆኖ እንዲገለገል አይደለም፡፡ ህወሓት ለህዝቡ ልክ እንደናት አንዲት ብቻ እንድትሆን በስፋትና በጥልቀት ሰርታለች፡፡ የኢኮኖሚ አቅሚም ድሃ ተቃዋሚን ካጠገብ የሚያስደርስ አልነበረም፦ የህወሓትና የትግራይ ልሂቅ ፕሉቶክራሲ፡፡

ህወሓት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሆዳቸው እስከሞላ ድረስ ስልጣኗን የመቀማት ፍላጎት የላቸውም የሚል መተማምን ነበራት፡፡ እርግጥ ነው፤ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሆኑ አባላት በህወሓት ቦታ ሆነው የፖለቲካ ወላፈኑ እንዲለበልባቸው አይፈልጉም፤ በህወሓት ተከልለው ሃብት ማጋበስን ይመርጣሉ እንጂ፡፡ ህወሓትን ከስልጣን አንስተው የገቡበት እዳ ሲታይ ቁጭት የሚመልሰው አልሆነም፡- “ከበሮ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ይደናገር”፡፡ የክልል አጋር ድርጅቶችም ቢሆኑ ሶፍትዌር ከተገጠመለት ሮቦት የተለዩ አልነበሩም፤ ከመተንፈሳቸው በስተቀር፡፡ ባትከበርበትም ህወሓት የምትፈራበት ነገር ቢኖራት አንድነቷ ነበር፡፡ ነገር ግን ህወሓት ብትበታተንም የማትደፈር ይመስላት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ አዚም ደገምኩበት ብላ አስባ ኖሮ ይሆን?

ህወሓት ጥንካሬዋን የሚፈትኑ በርካታ የፖለቲካ የውስጥ ውዝግቦችን አይታለች፤ እንደ ድህረ-ባድመ ሕንፍሽፍሽ ግን ከሞት አፋፍ ያደረሳት አልነበረም፡፡ የህወሓት አመራሮች በቃላት “ዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት”ን እንደ መርሆ እንጠቀማለን ይበሉ እንጂ የየራሳቸው አጀብ የነበራቸው የፓርቲ መኳንንትን በአንድ አስተሳሰብ እንዲገዙ ማድረግ የሚችል አሰራር አልነበረም፡፡ ከህወሓት ምስረታ ጀምሮ መሪዎች በስልጣን እየተሻኮቱ አንዱ አንዱን ሲተካ፤ አንዱ አንዱን ሲገለብጥ ከቀደምቶቹ መሳፍንት ያልተለየ የፖለቲካ ባህል ሰፍኖ ቆይቷል፡፡ በሆነው ባልሆነው ሲራኮቱ እሳቱን የሚያራግብ እንጂ ውሃ የሚደፉ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ ስርአት የለም፡፡ ብዙ ሰው “ልዩነትን ማብረድ ሳይሆን ማጋጋል የትግራይ ህዝብ የፖለቲካ ባህል ነው” ብሎ መናገር ያስጨንቀዋል፡፡ እስከ ትግራዩ ጦርነት ማግስት ድረስ እየታየ ያለው ሃቅ ግን ይኸው ነው፡፡

በሃበሻ የአመት አቆጣጠር በ1993 ዓ.ም የኢትዮ-ኤሪትርያ ጦርነት ውጤቶችን መሰረት አድርጎ በህወሓት አመራር ውስጥ በተፈጠረው ውዝግብ በሁለቱም በኩል “የፖለቲካ ዝሆኖች” የነበሩበት ሁለት ህወሓት ተፈጠረ፡- በሰየ አብርሃ የሚመራውና በመለስ ዜናዊ የሚመራው፡፡ ሁለቱም ዘመዳሞች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸውም ጓደኞች፤ አብረው አስራ ሰባት አመታት በመከራ ያሳለፉበትም ህይወት ሲታሰብ የፖለቲካ ስልጣን አይን፤ ጆሮና የሚያስብም ጭንቅላት እንደሌለው ያሳያል፡፡ ሁለቱም የአንጃ መሪዎች ማንን ተማምነው ላታቸውን ከውጭ እንዳሳደሩ ለራሳቸውም የገባቸው አይመስልም፤ እንደባሉን የተነፋው አቅማቸው ባንዲት መርፌ ሊተነፍስ እንድሚችልም

አልተረዱም፡፡ ጥቃት እንደተሰነዘረበት የጎሽ መንጋ የኋላቸውን ገጥመውና ቀለበት ሰርተው ቀንዶቻቸውን ወደፊት እንደመወደር በተቃራኒው ቀንዶቻቸውን ወደ እርስ በርስ አዞሩ፡፡

የ1993 የህወሓት ክፍፍል በውስጣቸው አፍነው ይህ የሚሆንበትን እድለኛ ቀን እጅግ በራቀ ተስፋ ሲጠባበቁ የነበሩት የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ባልታሰበ ጊዜ ያላሰቡት መና አወረደላቸው፡፡ ተቃዋሚዎቹም ቢሆኑ አጋጣሚው ሰርግና ምላሽ ሆኖላቸው ነበር፡፡ መለስ ዜናዊ በብአዴን ስየ አብርሃ ደግሞ በተቃዋሚዎች መጠለያ ውስጥ ገቡ፡፡ ተቃዋሚዎች ገብሩ አስራትን በአደባባይ ይቅርታ አስጠየቁ፡፡ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች ተሻሩ፤ የሃገሪቱ የደህንነት መሪም እንደዋዛ በወገን ጥይት ወደቁ፡፡ ስየ አብርሃ ታሰሩ፤ ከተፈቱ በኋላም የትምህርት እድል ሰጡኝ ብለው ህወሓትን አወገዙና ተቃዋሚ "ፓርቲያቸው"ን አደነቁ፡፡ ጋዜጦችና የኤሌክትሮኒክ ሚድያው በጉዳዩ ላይ ሲዘግቡና ሲተነትኑ ሌሎች የኢትዮጵያ አንገብጋቢ ጉዳዮች እስከመዘንጋት ደርሰው ነበር፡፡ የሰላሳ አመት ትግልና መስዋእትነት "አሞራው በረረ ቅሉ ተሰበረ፤ ጨዋታው ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" ሆኖ አረፈው፡፡

ህወሓት ከዚህ ከባድ ቁስል ማገገም አልቻለችም፡፡ በ1997 ዓ.ም ምርጫና በኋላ ህወሓት ማንም የሚደፍራት የሚያስፈራ ቅርጽ እንጂ የዳጎሰ ይዘት የሌላት የፖለቲካ ቅል ሆነች፡፡ "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" ሆነና የመለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት መለየት ለህወሓት የመጨረሻዋ መጀመሪያ ሆነ፡፡ በእቅድ ይሁን በአጋጣሚ መለስ ዜናዊ ቦሪስ የልሲንን ሆነው ለህወሓት ቭላድሚር ፑቲንን አልተዉላትም፡፡ የስላቅ ያህል መለስ ዜናዊ ይተኩኛል ብለው የሾሚቸው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ከእጅ የማይሻል ዶማ ሆነው የህወሓትን ውድቀት አፋጠኑት፡፡ ህወሓቶች ነገን ሳያዩ፤ መለስ ዜናዊን ዘላለም እንደሚኖር የብረት ምሶሶ አድርገው በመቁጠር በሱ ተከልለው በድግስ፤ በመጠጥ፤ በሙስናና ሃብት ማካበት ላይ ተጠምደው ቆይተዋል፡፡ ለስልጣኑም ብኩርና እንዳላቸው አሰቡ፡፡

የድህረ-መለስ የህወሓት አመራሮች የኢትዮጵያን የፖለቲካ የመውጫና መግቢያ በር ቁልፍ ሳይሰጣቸው ስላለፈ መላቅጡ ጠፍቷቸው ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች "ህወሓት በመለስ የሙት መንፈስ ኢትዮጵያን እየመራች ነው" ተብሎ እስኪነገር ድረስ በመለስ ጥቅሶች አገር የሚተዳደር መስሎ የታያቸው ይመስሉ ነበር፡፡

በአዲስ አበባ የማስተር ፕላን ሰበብ ኦሮሚያን ሲመራ የነበረው የኢህአዴግ አባል ድርጅት ኦህዴድ የወጣቶችን አመጽ ተጠቅሞ በኢትዮጵያ የህወሓትን ፈጻሜ አረጋገጠ፡፡ ህወሓትን ከስልጣን ያስወገዱት ህወሓት እሽሩሩ ብላ፤ በአንቀልባ ጀርባዋ ላይ አዝላ፤ ምርጥ ምርጡን እያጎረሰች፤ ከላይ ከላይ እየሾመች ያሳደገቻቸው ብልጥ ፖለቲከኞች ነበሩ፡- "ባመጣው ጠመንጃ ባመጣው እርሳስ፤ ተፈጠመ ጣሊያን ካበሻ እንዳይደርስ"፡፡



ህወሓት በነበራት ወታደራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉልበት ልቦናዋ ተደፍኖ ስለነበር በነዚህ ረዥም የስልጣን አመታት ብቻዋን እንደነበረች አልተረዳችም፡፡ "ጸጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል"፡፡ የሃገሪቱ ከፍተኛ ስልጣን ወደ ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አመራሮች ቢዛወርም በህወሓት ፖለቲካ ሆነ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረው የጎላ ለውጥ አይኖርም የሚል እምነት ያሳደረች ትመስል ነበር፡፡ በህንፍሽፍሹ ከፍተኛ የፖለቲካ አቅምና ተሰሚነት የነበራቸው የህወሓት አመራር-ነበር ከጨዋታ ውጪ ሆነው ስለነበር የቀሩት "አናሳ-አሳዎች" የመጣባቸውን የፖለቲካ ጎርፍ ቦይ ቀደው የሚያስተነፍሱበት አቅም አልነበራቸውም፡፡ ከዚህም የተነሳ የህወሓት አመራሮች የፖለቲካ እድላቸውን ለእድል አስረክበው በተበታትነ ሁኔታ ከፖለቲካ ውጪ ሆኑ፡፡ ህወሓት እንዲህ በቀላሉ ትዳከማለች ብለው ያላሰቡት የድሮ "አሽከሮች" የአሁን "ጌቶች" ህወሓት ከወደቀች በኋላም ከልክ ያለፈ ዶፍ አዝንበውባታል፡፡ ኦህዴድና ብአዴን በህወሓት ላይ በሚወስዱት እርምጃ ካሰቡት በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ድጋፍ ስላገኙ ህወሓትን እንደ አውሬ ቀረጿት፤ እንደ አውሬም ቀጠቀጧት፡፡

# ምዕራፍ ፬

# የትግራይ ጦርነት መንስኤዎች

## 4.1 መግቢያ

የትግራይ ጦርነት በመባል የሚታወቀው ለሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን በባህርዩ ልዩና እጅግ አውዳሚ የነበረው ጦርነት ከ23 ጥቅምት 2013 እስከ 23 ጥቅምት 2015 በሰሜን ኢትዮጵያይቱ ትግራይ የተካሄደ ነው፡፡ የአማራ ክልል መንግስት፤ የአማራ መደበኛ ያልሆኑ ታጣቂዎች፤ ወደ ውጊያው የተጋበዘው የኤሪትርያ መንግስት ጦር፤ የኢትዮጵያ የፌደራል ጦር ሰራዊት፤ የየክልሎቹ ልዩ ሃይሎች፤ እንዲሁም የአረብ ኢሚሬትስ አይር ሃይል በአንድ ወገን፤ የትግራይ ክልላዊ መንግስት ልዩ ሃይልና ሚሊሽያ በተቃራኒው ወገን፡፡ ጦርነቱ በፖለቲካ አቅም የዝሆኖች በወታደራዊ ዝግጅት ግን የዝሆንና ጥንቸል ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ጦርነት “በፕሪቶሪያ ስምምነት” መሰረት አፈሙዞች የቦዘኑ ቢሆንም ከስምምነቱ አፈጻጸም መጓተት የተነሳ የተሟላ ሰላም አልሰፈነም፡፡ ህዝቡ በጥይት መሞት ሲቀርለት በባሰው ገዳይ በረሃብ እያለቀ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መሪዎች ሳሩን ተመኝተው ገደሉን ሳያዩ ከዚች ድሃ አገር አቅም በላይ የሆነ መጠነ ሰፊ ጦርነት አካሄዱ፡፡ በሚስቱ አፍንጫ ላይ ያረፈችውን ተርብ እገድላለሁ ብሎ በዘነዘና አፍንጫዋን ገምሶ ለሞት ያበቃት ባል ተርቧን ለመክላት የሚስቱን ህይወት የማይጎዳ ዘዴ መፈልግ አቅም ስላነሰው ነበር፡፡ የፕሪቶሪያ ስምምነት ተፈርሞ ስለአተገባበሩ ጭንቀት ቢነግስም ኢትዮጵያ ራሷ በጦርነትና በኢኮኖሚ ድቀት የወደፊት እጣዋ አልታወቅ ባለበት ሁኔታ የትግራይ ችግር ልዩ ትኩረት ያገኛል ማለት ዘበት ነው፡፡ አሁን በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ውስጥ አውዳሚ ጦርነት እየተካሄደ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አመራርም ከበፊቶቹ የትግራይ ጦርነት ሽሪኮቹ ጋር ግብግብ ገጥሟል፡፡ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው ሆኖ ኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጋ በማትወጣው የዲፕሎማቲክ ምስቀለቀል ውስጥ ገብታለች፡፡ ኢትዮጵያ ከዚህ ማእበል ብትተርፍ በሰማዩ ጌታ ልዩ ተአምር እንደሚሆን የማይስማማ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ አምላክ መደበኛ ስራው ኢትዮጵያን መጠበቅ ብቻ ይመስል ከገባችበት ማጥ ተጋግዞ እንደማውጣት ተስፋን በልቶ ተስፋን እየጠጣ ተያይዞ እንጦሮጦስ ይወረዳል፡፡

## 4.2 የጦርነቱ መንስኤዎች

ጥቅምት 23/ 2013 ዓ.ም. ሌሊት ላይ የሰሜን እዝ በትግራይ ልዩ ሃይል ጥቃት ስለተከፈተበት ጦርነት ተጅምሯል የሚል መግለጫ ለኢትዮጵያና ለአለም ህዝብ ቀረበ፡፡ ምንም እንኳ አንዲት አገር በሰራዊቷ ላይ ከውጭ ይሁን በውስጥ ጥቃት ቢፈጸም እርምጃ የመውሰድ ግዴታ ቢኖርባትም ይህ ሰበብ እንጂ ምክንያት አልነበረም፡፡ አንደኛው የአለም ጦርነት የተጀመረው አንድ ሰርቢያዊ ወጣት የአውስትሪያዊውን መስፍን ፈርዲናንድ ሳራየቦ ላይ ተኩሶ ስለገደለው አይደለም፡፡ በቅኝ ግዛቶች ሽሚያ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ታላላቅ የአውሮፓ መንግስታት ሰራዊት ገንብተው ለጦርነት በእግሮቻቸው ጣቶች ላይ ቆመው ስለነበር ነው፡፡ በመስፍኑ ላይ ቃታ ሲሳብ ጥይት አጉርሶ ሲጠብቅ የነበረው የአውሮፓ የጦርነት ቃታም ተሳበ፡፡

ሲጠብቅ የነበረው ኢትዮጵያውያንንና አለምን በትግራይ ላይ የሚያበሳጭ አጋጣሚ እንዲፈጠር ነበር፡፡ ሶስት አመት ሙሉ ሲደረግ የነበረው የጦርነት ዝግጅት በጥላቻ አይኑን የጨፈነና ጆሮውን የደፈነ ካልሆነ በስተቀር ግልጽና ጸሃይ ላይ የተሰጣ ነበር፡፡ የኤሪትርያው መሪ የአገር ምስጢር የሆነውን የአየር ሃይል መደብ ፍርጥርጡን አውጥተው የጎበኙት ከሰሜን እዝ መጠቃት በኋላ ቢሆን ኖሮ ትግራይ ላይ ለመፍረድ ቀላል ይሆን ነበር፡፡ የሰሜን እዙ ጥቃት ጦርነት ለኮሰ ተባለ እንጂ ከወራት በፊት በትግራይ ላይ ምርጫ ሊካሄድ በመታቀዱ የተቆጡት የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር “ወጣቶች ይሞታሉ፤ እናቶች ያለቅሳሉ” ብለው ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ የቃላቶቻቸው እንድምታ የሚያደናግር አልነበረም፡፡ የሰሜን እዝ መጠቃት፤ በትግራይ መርጫ ማካሄድ፤ የህወሓት ወደ ብልጽግና ፓርቲ አለመቀላቀል ጸብን ያከረሩ እንጂ የጸቡ መሰረታዊ መንስኤዎች አልነበሩም፡፡

ሶስቱም ሃይሎች በትግራይ ላይ ጦርነት ያካሄዱበት ምክንያት ለየቅል ነበር፤ “የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” በማለት ነው እንጂ፡፡ በቀደሙት ምእራፎች እንደተተነተነው ኤሪትርያ ህወሓትን በኤሪትርያ ህዝብ የከፋ ኑሮ ትወነጅልና “የኤሪትርያ ህዝብ እንዲድን ከተፈለገ ህወሓት ከምድረ ገጽ መፋቅ አለባት” ትላለች፡፡ የኤሪትርያ ህዝብ ህይወት የከፋ የሆነው ህወሓት (የትግራይ ህዝብ) ኤሪትርያን “ወደ ኢትዮጵያ ሃብትና ገበያ አላሳልፋት ስላለች” ነበር፡፡ ፌደራል መንግስትን የሚመሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ኢትዮጵያን ለረዥም ጊዜ የመምራት ቁርጠኛነት አላቸው፤ በዚህ መንገዳቸው ላይ የሚገተር ማንኛውም ሃይል መደራደር ሳይሆን መወገድ እንዳለበት ወስነዋል፡፡ መንገዳቸው ላይ ቆሟል ብለው ያሰቡት ሃይል ደግሞ ህወሓት ናት፡፡ ኢህአዴግን በማፍረስ በብልጽግና መርሆ ላይ የተመሰረተ ፓርቲ መስርተዋል፡፡ ይህ ፓርቲ የኢህአዴግን አባላት በሙሉ እንዲሁም የክልል አጋር ፓርቲዎችንም ያጠቃለለ ስለሆነ

በሚልዮኖች የሚቆጠሩ አባላት ያሉት በአገሪቱ ግዙፉ ፓርቲ ነው፡፡ የአማራ ልሂቃን ደግሞ “ኢትዮጵያን ለመበተን የተተገበረው ህገ መንግስት የህወሓት እጅስራ ስለሆነ እነዛ እጆች ተቆርጠው ህገመንግስቱ እንዲቀየር” የሚል ቁርጠኛ አላማ አንግበዋል፡፡

የአማራ ልሂቃን ህገ-መንግስቱን ለምን ይህን ያህል ጠሉት? የመገንጠል መብት የሚሰጥ ህገ-መንግስት ለኢትዮጵያ አንድነት አደጋ ነው የሚለው ክርክር ውሃ ሊያነሳ ይችላል፡፡ ለአገር አንድነት ከመቆርቆር ብቻ ሆኖ ቢሆን ኖሮና አደጋው ተጭባጭ ከሆነ ሁሉም አማራ የመሆን ግዴታ ይኖርበታል፦ “እኔም አማራ ነኝ!”፡፡ ነገር ግን የአማራ ልሂቃን የህወሓት ጥላቻ ለኢትዮጵያ ከሌሎች ሚልዮኖች የበለጠ ፍቅርና ሃላፊነት ስላላቸው አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ህልውና ማንም “ከጳጳሱ ቄሱ” የሆነ ግለሰብ፤ ቡድንም ይሁን ህብረተሰብ ሊኖር አይችልም፤ ካለም ከጀርባው ሌላ መሸፋፈን ያለበት አላማ ይኖራል፡፡ የአማራ ልሂቃን በተለይ የጎንደሮቹ ወልቃይትና ሑመራ ከጎንደር ተወስደው ወደ ትግራይ አስተዳደር መጠቃለላቸው በህገ-መንግስቱ መሰረት የተተገበረ ነው በሚል ነው በሰነዱና ሰነዱን ባረቀቀው ላይ የተነሱት፡፡ በወሎ በኩልም የአላማጣና ኮረም ወደ ትግራይ አስተዳደር ስለተጠቃለለ ተመሳሳይ ተቃውሞ ነበረ፤ የወልቃይት ያህል የከረረ አይደለም እንጂ፡፡ የአማራ ሃይል ህጉን ወደ እጁ በማስገባት ወልቃይትና ራያን ወረረ፡፡

ሶስቱም ሃይሎች የተሳተፉበት ትግራይ ላይ የተካሄደው ሁለት አመታት የፈጀ አውዳሚ ጦርነት በኋላ ሶስቱም ሃይሎች ምን ያህል አላማቸውን አሳክተዋል ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከጦርነቱ የባሰ ውስብስብ ነው፡፡ የኤሪትርያ መሪዎች የፈጸሙት ውድመት፤ ዝርፊያና የህዝብ ፍጅት ከዳር ሳያደርሱ “ፕሪቶሪያ አላማችንን አሰናከለብን” ብለው ምድር የማትሸከመው ግፍ ተናገሩ፡፡ የፌደራል መንግስት ጦርም “ህወሓት/ ትግራይን ለማዳከም ከራሳቸው (ህወሓት/ ትግራይ) የሚበልጥ ሃይል ሊኖረን አይችልም፤ ስለዚህ ከሩቅ ሆኖ ህወሓትና ትግራይ “ባህላዊ” በሆነው ሽኩቻና ትርምስ በራሳቸው ጊዜ ይከስማሉ፤ ማድረግ ያለብን እሳቱ ላይ ጋዝ ማርከፍከፍ ነው” የሚል በጥበብ የተደገፈ ፖለቲካን መርጧል፡፡ የትግራይ የፖለቲካ ልሂቃን እንኳንና ሌላው ከደረሰበት ችግር ከራሳቸው ታሪክም መማር ያቃታቸው የፖለቲካ መናጢ ድሆች ናቸው፡፡

በዚህ መጽሃፍ ምእራፍ ሁለት የትግራይ መሳፍንትና መኳንንት እርስ በርስ ሲራኮቱ ትግራይን መቀመቅ ከተው በሳል ፖለቲካ የሰሩትን የአጼ ሚኒሊክን ዙፋን እንዳጠናከሩ አይተናል፡፡ ፖለቲካ ነውና ሚኒሊክ ልክ ነበሩ፡፡ በፖለቲካ አለም “ጨው ለራስህ ስትል ጥፍጥ ነው”፡፡ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እንደ አሸን በፈሉበት ትግራይ ከዘጠና አመታት በኋላ የትግራይ መሳፍንት ታሪክ ሳይበረዝ ሳይከለስ እየተደገመ ነው፡፡ ልዩነቱ መሳፍንቱ አዝማሪ ቀጥረው መሰዳደብ እንጂ ጥቅስ አይጠቅሱ፤ ቲዮሪና ፓራዲም አይተነትኑ፡፡ የአሁኖቹ በሳይንስ የድሮዎቹ በእምነት ሲገሰግሱ መድረሻቸው ግን አንድ!

**4.3 የወልቃይት ጉዳይና ከጀርባው ያዘለው ኢኮኖሚና ጂኦ-ፖለቲካ**

“ወልቃይት የአማራ ነው!”፤ አይደለም “ወልቃይት የትግራይ ነው!” አንድ ወልቃይት እንጂ ሁለት ወልቃይት ስለሌለ ግዛቱን ካልተቋረሱት በስተቀር ሊሆን የሚችለው ለአንዳቸው ብቻ ነው፡፡ አማራ የታሪክ ባለቤትነትን እያስታወሰ የወልቃይት ኗሪዎችም አማሮች ናቸው ይላል፤ ትግራይ ደግሞ ከአማራ በፊት የኔ ነበር አሁን ደግሞ በህገ መንግስት መልሼ አገኘሁት፤ የወልቃይት ኗሪዎችም ተጋሩ ናቸው ይላል፡፡ ከታሪክ ይልቅ ህገመንግስት የህግ ጉልበት ስላለው የአማራ አቋም የመሸነፍ እጣ ገጥሞት ጉዳዩ በትግራይ አሸናፊነት ሊያልቅ ይችላል፡፡ ይህ ግን የሚሳካ አልሆነም፡፡ አማራ ህገ መንግስቱን አልቀበልም ስለሚል የመስማሚያ ወይም የማሸነፊያ ሰነድ ሊሆን አልቻለም፡፡

በክልሎች መካከል የግዛትና የድንበር ይገባኛል ክርክር ሲነሳ ህገ መንግስቱ በፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲታይ ይደነግጋል እንጂ በጉልበት ግዛት መነጣጠቅን ወይም ድንበር መገፋፋትን አይፈቅድም፡፡ ይህ ከተደረገም ፌደራል መንግስቱ የህገ-መንግስቱ ጠባቂ እንደመሆኑ አጥፊውን ቀጥቶ ነገሮችን ወደ ነበሩበት ከመለሰ በኋላ ሁለቱን ወገኖች አከራክሮ ፍትህን ያሰፍናል፡፡ ይህ ግን ቲዮሪ እንጂ ተግባር አልሆነም፡፡ ቀጥሎም በህገመንግስቱ ላይ የማይታሰብ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በፌደራል መንግስቱና በኤሪትርያ መንግስት ድጋፍ አማራ ወልቃይትን ወሮ ያዘ፡፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተጋሩ ለስደት ተዳረጉ፤ ፍጅትና ጾታዊ አመጽም ህጋዊ ሆነ፡፡ ጥምር ሃይሉ ወልቃይትን ብቻ ሳይሆን መላ ትግራይን በመቆጣጠሩ አጠቃላይ ጦርነት ሆኖ ለሁለት አመታት ቆየ፡፡ በፕሪቶሪያ ስምምነትም አሸናፊ ያልነበረው መተላለቅ በክፊልና ለጊዜው እረጭ አለ፡፡

የፕሪቶሪያው ስምምነት ወልቃይትን ወሮ የያዘው የአማራ ሃይልን አላካተተም፡፡ እንደ ክልል ሃይል በፌደራል መንግስቱ ይወከላል እንጂ ራሱን ችሎ መቅረብ አይችልም ነበር፡፡ ትግራይ ክልል ቢሆንም ተቃራኒ ተዋጊ ሃይል በመኖሩ ለፕሪቶሪያ በቅቷል፡፡ በፌደራል መንግስት የአገር ክህደት ፈቃድ ሉአላዊነትን ጥሶ የኢትዮጲያን ግዛት የወረረው የኤሪትርያ መንግስት የአገር ውስጥ ጉዳይ በሆነው በፕሪቶሪያው ስምምነት ውስጥ እንዲካተት የሚፈቅድ የዲፕሎማሲ ፕሮቶኮል የለም፡፡ የኤሪትርያ መንግስት መሳተፍ የሚችልበት ህግና ደንብ ቢኖርም እንኳ በጦርነቱ የነበረው ሚና በዲፕሎማቲክ አለም ኢትዮጵያን የሚያሳፍር ስለሆነ ፌደራል መንግስት የኤሪትርያ ስም ሰነዱ ውስጥ በግልጽ እንዳይጠቀስ አስደርጓል፡፡

ከተኩስ አቁም በስተቀር አንድ አመት አልፎት እስካሁን ያልተተገበረው የፕሪቶሪያ ስምምነት በህገመንግስቱ መሰረት የአማራ ሃይል ከወልቃይት እንዲለቅና ለትግራይ እንዲያስረክብ የተወሰነው ውሳኔ አማራው ብቻ ሳይሆን ስምምነቱን የፈረመው ፌደራል መንግስትም ዳተኛ ሆኖበታል፡፡ አማራና ትግራይ በወልቃይት ላይ ያላቸው የይገባኛል ክርክር ሁለቱም በቀጥታ የሚፎካከሩበት ሳይሆን ትግራይ ለብቻ አማራ ደግሞ በፌደራል መንግስት ሞግዚትነት ነው፡፡ ሁለቱንም ክልሎች እኩል አይቶ መዳኘት የሚገባው ፌደራል መንግስት ላንዱ ተወካይ ሆኖ በሌላው ላይ ክንዱን ማንሳቱ በአገር አስተዳደር አለም እንቆቅልሽ ሆኗል፡፡ ወልቃይት ከ"አማራ ቀይ መስመርነትና የህልውና ማእከልነት" አልፎ "ወልቃይት ከአማራ እጅ ከወጣ ኢትዮጵያ ትፈርሳለች"፤ ስለዚህ "ወልቃይት የአማራ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያውያን የሃገር ህልውና አጅንዳ ነው" የሚል ጣራ ነክቷል፡፡ በጋለ ስሜት ታጅቦ የአለምን ጆሮ ታምቡር ያርገበገበው የወልቃይቱ አተካራ!

## 1. "ድሮ የኔ ነበር"፦ ታሪክ ላይ የተመሰረተ የይገባኛል ክርክር

ለዘመናት ሽራሮ፤ ወልቃይት፤ ሑመራ፤ ጸለምቲ፤ አድያቦ፤ ተከዜ ሽለቆ፤ ቋራ፤ መተማና አብደራፊ ደጋ ወይና ደጋ ላይ መሬት በመጣበቡ ከወባና ከሽፍታ ጋር እየታገለ ሰው ሰፈረባቸው እንጂ አዳኝና መናኒ ብቻ የሚደፍራችው ባዶ የአውሬ መፈንጫዎች ሆነው ኖረዋል፡፡ የደጋ ወይና ደጋው የአማራና የትግራይ መሳፍንት ከአለፋ ጣቁሳ፤ ከደምቢያ፤ ከአርማጭሆ፤ ክስሜን፤ ከወገራና ከሽሬ እየተነሱ ኩታ ገጠም የሆኑላቸውን ከላይ የተዘረዘሩትን በርሃማ ስፍራዎች ወደ ምእራብ ዘምተው ወደየ ግዛቶቻቸው ጠቀለሏችው፡፡ ግዛቶቹ "ከጥንት ጅምሮ የኔ ነበሩ" የሚባባሉትበት ጉንጭ አልፋ ክርክር ተረት ተረት ከመሆን አያልፍም፡፡ ጥያቄው ከየት የመጣው መስፍን ወይም ንጉስ የትኛውን ግዛት ቀድሞ ያዘ ነው፡፡

የኢትዮጲያ የ19ኛው እና የ20ኛው ክፍለ ዘመናት የግዛት ማስፋፋት ካርታ እንደሚያሳየው የሰሜን-ምእራባዊ ቆላማ ቦታዎች (ቋራ፤ መተማ፤ አብደራፊና ሑመራ) ከደጋው በተነሱ መሳፍንት የተያዙት እኤአ ከ1895 እስከ 1900 ባሉት አምስት አመታት ውስጥ ነው፡፡ ይህም በዓድዋ ጦርነት ማግስት መሆኑ ነው፡፡ ለካርታው ይህን ሊንክ ይከተሉ፦ http://www.eritrea.be/old/ethiopia.jpg የአለም አገሮች የውጪም የውስጥም ድንበርና ወሰናቸውን ቋሚና ህጋዊ ያደረጉት ከሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ከቅኝ አገዛዝ መክሰም ጋር

ተያይዞ እንጂ ከዛ በፊት የጎሳ ሆነ የብሄረሰብ ወሰንን ሳይከተሉ የታክስ ገቢያቸውን ለማደለብ ብቻ ግዛት ሲቀማሙ፤ ግዛቶች ሲጠቡና ሲሰፉ ነው የኖሩት፡፡ በየግዛቶቹና ንኡስ-ግዛቶቹ ውስጥ ሲኖር የነበረው ህዝብም ቋንቋውና ባህሉ ከቁጥር ባልገባበት የፊተኞቹ ተሸንፈው ሲባረሩ አዲሶቹን ጌቶች እየተቀበለ ሲያደገድግ ነው የኖረው፡፡ እዚህም እዛም ያሉት ጎሳዎች፤ ብሄረሰቦች ምንድን ናቸው በአንድ ነው ወይስ በተለያዩ ጌቶች ስር ነው የወደቁት የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጥ አልነበረም፡፡

በመሰረቱ በአንድ ግዛት ውስጥ የትኛው ብሄረሰብ ቁጥሩ ይበልጣል የትኛው ያንሳል የሚለው በህዝብ ቆጠራ በ1970ዎቹ እስከታወቀ ድረስ ምንም ተጭባጭ ማስረጃ አልነበረም፡፡ የሚታወቀውና በወቀቱ አስፈላጊ የነበረው አማራ ይሁን ትግራዋይ፤ ኩናማ ይሁን ቅማንት ምን ያህል ግብር መክፈል የሚችል አባወራ አለ ነው፡፡ ስለዚህ ወልቃይት የአማሮች መኖሪያ ወይም የተጋሩ መኖሪያ ነው በሚል ሳይሆን የሚታወቅበት ይህን ያህል ግብር የሚያፍሱበት የደጃዝማች እከሌ ግዛት ነው ተብሎ ነበር ከንጉሱ መዝገብ ያኘ ዘንድ የተመዘገበው፡፡ ከፍተኛ ግብር የመክፈል አቅም ያለው ግዛት በተፈጥሮ ለም የሆነው ነው፡፡ ይህ አይነት ግዛት የሚሰጠው ደግሞ በንጉሱ ዘንድ ተወዳጅ ለሆነው ገዢ ነው፡፡

አሁን በህገ-መንግስቱ ወደ ኦሮሚያ የተመለሰው ምእራብ አርሲ ቀደም ብሎ የአርሲ ግዛት ከነበረበት ተቆርጦ “ሃይቆችና ቡታጂራ” ተብሎ ወደ ሸዋ ተጠቃሎ ነበር፡፡ ይህ ሃይቆች የበዙበት የቱሪስት ማእከል ለአርሲ ሳይሆን የሚገባው ለሸዋ ነው የተባለ ይመስላል፡፡ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛትን በቀጥታ ከሸዋ ጋር ለማገናኘትም ጠቅሟል፡፡ ሸዋ ከአስራ አራቱ ጠቅላይ ግዛቶች ሰባቱ ጋር ወሰን ትጋራ ነበር (ወሎ፤ ሃረርጌ፤ አርሲ፤ ሲዳሞ፤ ከፋ፤ ወለጋ፤ ጎጃም)፡፡ ሲዳሞ ከሸዋ የገጠመው አርሲን ቆርጦ ነበር፡፡ እንዲህ ነበር የግዛቶች ወሰን ሲወሰን የነበረው፡፡

ከደጋው ወደ ቆላማዎቹ ስፍራዎች የመሳፍንቱን ግዛት ማስፋፋት ተከትሎ ለመስፈር በእግር የሚፈልሰው ህዝብ ኩታ ገጠም ወደሆኑት የቅርብ ርቀት ቆላዎች ወርዶ ይሰፍራል እንጂ እግሩን አስረዝሞ የሸሬው ወደ ቋራ የወገራው ወደ ሑመራ አይሄድም፡፡ ከዛ ወዲህ ላለፉት መቶ አመታት የወልቃይትና ሑመራ ግዛቶች ከቤጌምድርና ከትግራይ ገዢ ሲፈራረቅባቸው ቆይተዋል፡፡ ማእከላዊ መንግስታት ግዛቶችን ከማን ቀምተው ለማን እንደሚሰጡ የሚወስነው

ከቤጌምድርና ከትግራይ ገዢዎች የትኛው ነው ከለም መሬቶቹ ግብር በገፍ ሰብስቦ አቅሙን እንዲያፈረጥምና ለንጉሱ ፈሰስ እንዲያደርግ የሚፈለገው ነው፡፡ የትግራይ እጣ የት እንደሆነ የተሰወረ አይደለም፡፡ አዲስ አበባ ከነበሩት ነገስታት ጋር የማያባራ ፉክክር የገጠሙት የትግራይ መኳንንትና መሳፍንት እንኳን ከሌላው ተቀምቶ ሊጨመርላቸው የያዙትንም ግዛት ከመቀማት አላዳኑም፡፡ ስለዚህ በወልቃይት የባለቤትነት ጥያቄን ለመደገፍ ከሁለቱም በኩል የሚቀርበው የብሄር የግዛት አከላለል በማይታሰብበት ዘመን "ይህ ግዛት አማራ ነበር፤ ይህ ትግራይ ነበር" የሚል የታሪክ ማስረጃ ተጨባጭ ሊሆን አይችልም፡፡ የአሁኖቹ የኢትዮጵያ ክልሎች ከዛም ከዛም የቀድሞ ጠቅላይ-ግዛቶች/ክፍላተ-ሃገራት ተውጣጥተው የተገጣጠሙ ናቸው፡- ሶማሊ ክልል (ሃረርጌ፤ ሲዳሞና የባሌው ኤልከሬ)፤ ኦሮሚያ ክልል (የባሌው ፋሲል አውራጃ፤ አርሲ፤ የሃረርጌ ደጋማ አውራጃዎች፤ አብዛኛው ሸዋ፤ ከፋና ወለጋ)፤ አማራ (ምእራብ ወሎ፤ ምስራቅና ምእራብ ጎጃም፤ አገው ምድር፤ ጎንደር፤ ሰሜን ሸዋና ዋግ-ላስታ)፤ አፋር (ምስራቅ ወሎ፤ ምስራቅ ትግራይ፤ ምስራቅ ሸዋ፤ ምእራብ ሃረርጌ የአዋሽ ሸልቆ ቆላዎች)፤ ትግራይ (በአፋር ተቆርጦ ከተወሰደው የቀረ፤ ወልቃትና ሑመራ)፤ ቤኒሻንጉል (ምእራብ ወለጋ፤ የጎጃም የነበረው መተከል)፡፡

## 2. "የሑመራ ሰሊጥ"፡- ሽፍኑ የአማራና የኤሪትርያ ቢዝነስ ፍላጎት

ወልቃይትና ሑመራ እንደ ቋራ፤ መተማና አብደራፊ ሁሉ የሚታወቁት በሰሊጥ ምርታቸው ነው፡፡ በወልቃይት ክርክር ውስጥ የሰሊጥ ጉዳይ በይፋ ሳይነገር የጎንደር አማራ ከበርቴዎች በአባት አገር ትርክት ሰውረው ፖለቲከኞችን በገንዘብ ሃይል ህዝብን በአገር ፍቅር ስም አሰልፈውታል፡፡ በቋራ፤ መተማና አብደራፊ ከወልቃይትና ሑመራ የሚበልጥ የሰሊጥ መሬትና ምርት እንዳለ የታወቀ ሆኖ እያለ ከሌላ ከትግራይ ክልል ወልቃይትንና ሑመራን መቀማት ለምን አስፈለገ? ተሾመና እሱባለው በሰሊጥ ምርት ላይ ባደረጉት ምርምር እ.ኤ.አ. 2014/15 የሰሊጥ ምርት አመት አማራ ክልል 40 ከመቶ፤ ትግራይ 30 ከመቶ እንዳመረቱ ዘግበዋል፡፡ የትግራይ 30 ከመቶ ሰሊጥ የሚመረተው በወልቃይትና ሑመራ በመሆኑ የአማራ ሃይሎች የፈለጉት ይህን ወስዶ 70 ከመቶ የምርት ባለቤት ለመሆን ነው? ለዚህ ሁሉ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ምስቅልቅል የከበርቴዎች ስግብግብነት ብቻውን በቂ ምክንያት ይሆናል ወይ? አብሮ ማምረት አስፈላጊ ከሆነም በግሎባላይዜሽን ዘመን መደጋገፍ ያልተቻቸለው ለምንድነው?

## 3. ትግራይን የማዳከም ጂኦ-ፖለቲካ?

ከኢህአዴግ በስተቀር አራት ኪሎ የተቀመጡ መንግስታት ምንም እንኳ እርስበርስ የሚጠፋፉበት የፖለቲካ አቋም ልዩነት ቢኖራቸውም ከአንድ ምእተ-አመት በላይ ትግራይን በጂኦ-ፖሊቲካ ለማዳከም በቅብብሎሽ ሲሰሩ ቆይተዋል የሚል የኖረ የትግራይ ልሂቃን ምሬት አለ፡፡ ይህ ከባዶ ጥላቻ ወይም ከስልጣን ተቀናቃኝነት የሚነሳ ህዝብ ማነሳሻ ትርክት አይደለም፡፡ አደባባይ የወጡት ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ ውሳኔዎችና ድርጊቶች በርካታ ከመሆናቸው ጋር በየሶሻል ሚድያው ትግራይን ቁረጧት ፍለጧት፤ ከርክሚት እንዲያውም ከካርታ ፋቋት እያሉ የሚወተውቱትን አሸን የ“ላይክ” ነጋዴ አክቲቪስቶችን ማየት በቂ ነው፡፡

የአሁኑን አያርገውና ቀይ ባህር ከማትገኝበት ሰማይ ቤት ያለች እንቁ ከመሆኗ በፊት አጼ ሚኒሊክ የቀይ ባህሩን ግዛት ለጣልያን የባረኩለት አይናቸውን እንኳን ትንሽም ሳያሹ ነበር፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ ቢገጥም እንኳ የአገር ወሳኝ ክፋይ ለማስቀረት ሞክረው ወድቀው ቢሰበሩ ስም በአርበኝነት ተመዝግቦ ለዘላለም ይዘከራል፡፡ አቅም የነበራቸው የትግራይ መሳፍንት ጣልያንን ጠራርጎ ለማስወጣት ዝግጁ እንደሆኑ ያሳወቁበትና የተከለከሉበት ታሪክ “ካቅም በላይ ሆኖ ነው” የሚባለው ምክንያት “የናቴ መቀነት ጠለፈኝ” ከመሆን አይዘልም፡፡ ጣልያንን ከባህሩ ግዛት ጠራርጎ ለማስወጣት እየተቻለ ያልተደረገው ለምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ ሊሆን የሚችለው አንድ ብቻ ነው፡፡ የሚኒሊክን ዘውድ የሚቀናቀኑት የትግራይ መሳፍንት እርስ በርስ ሲባሉ ዝም ብሎ ከማየት በተደራቢ የባህር መተንፈሻ አግኝተው በቀረጥና በመሳሪያ ግዢ እንዳይደራጁ በባእድ ሃይል በራቸውን መቀርቀር ነበር፡፡

ቀድሞ ያልታየው የባህር በር አስፈላጊነት አሁን የወደብ ጭንቅ ሲመጣ የአሉላን ስም ጨርሰው ከረሱት መቃብር ቆፍረው በማውጣት ከዘመን አውድ ውጪ “ቀይ ባህር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድንበር ነው” አሉ እያሉ የሙት መንፈሳቸውን እረፍት ነስተው ያስለፈልፏቸዋል፡፡ ራስ አሉላ ከነጉልበታቸውና ከነህይወታቸው እያሉ ይህን ቃል ይፈጽሙ ዘንድ ግን አልተፈቀደላቸውም፤ ከጣልያን አርቀው አራት ኪሎ ግቢ ውስጥ የእቴጌ ጣይቱ አጫዋች አደረጓቸው እንጂ፡፡ በውጫሌ ውል አንቀጽ ሶስት ላይ የሚኒሊክ ፊርማ ያረፈው እንኳንና ቀይ ባህር የጥንታዊት አኹሱም አካል የነበረው ከርስትያኑ የኤሪትርያ ከበሳም “የኔ ግዛት አይደለም” ተብሏል፡፡ የባህር በር እንደማንኛውም የንብረት ባለቤትነት ጥያቄ ይርጋ አለው፡፡

መለስ ዜናዊ አህያው ተፈርቶ የሚቀጠቀጠው ዳውላ ሆኗል፡፡ ተገፍትረው የሄዱት የጥንቶቹ አክሱማውያን የአሁኖቹ "የግዴታ ጣልያኖች" ኤሪትርያውያን "ቀይ ባህር የተፋችሁት ስለሆነ መልሳችሁ ለመዋጥ አትሞክሩ" ብለው በንዴት ቢጮሁ ጥፋታቸው የት ላይ ነው? የወረወርክውን እቃ የሚያነሳው የለም ብሎ ፍለጋ መዞር ቂልነት ነው፡፡ ክሰሜን የቀይ ባህር "ኃፈሬዋን" የተላጨችው ትግራይ በዚህ አላለፈላትም፡፡ በመጀመሪያው ወያኔ "ግፍ የበዛብን ኢትዮጵያውያን ነን" ብለው ቢያምጹ በፈረንጅ አውሮፕላን ከመቀጥቀጣቸው ሌላ በችጋር ጊዜ ኀተራቸው የነበረውን ራያንና ወልቃይትን ለሚቀርቧቸው ጠቅላይ ገዢዎች አድለው ትግራይ ቦምብ ብቻ ሳይሆን ድህነትም ይቅጣሽ ተባለች፡፡ ትግራይም ብዙ ጊዜ እንደታጠቡበት ሳሙና ግማሽ ደረሰች፡፡

እንዲህ እንዳለ አብዮት ፍንድቶ፤ ጸላኤ ትግራይ የሆነ መንግስት ተመስርቶ፤ የህወሓት ትግል ወደ ፍጻሜ በተቃረበባቸው አመታት የኤሪትርያ መገንጠል አይቀሬ ነው በሚል ስጋት የቀይ ባህር ዳርቻ ግማሹን የያዘውን አሰብ ወደ አፋር በመቀላቀል ድቡልቡል የሆነች ኤሪትርያ ፈጥሮ "ብትሄድም ትሂድ" ተብላ "ራስ ገዝነት" ተሰጣት፡፡ ጥንቱም ቢሆን ያለ ይሉኝታና ያገር ልጅ ስሜት "የምንፈልገው ወደቦችን ነው" ተብሎ በእብሪት ለተነገረው ማረጋገጫ ሆነ፡፡ ለትግራይም የተደግሰላት ሌላ እርድ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. 1987 በምሁራን ተዘጋጅቶ ሊተገበር ታቅዶ የነበረው የትግራይ ካርታ የሰሜኑ ጦርነት በመባባሱ ይፋ ሳይሆን ቀረ፡፡ ይህ ቋንቋን መሰረት አድርጎ የተሰራው "የብሄረሰብ ራስ ገዝ" አክላለል ትግርኛ ተናጋሪ የሚበዛበትን ወልቃይትን፤ ሑመራን፤ ጸገደን፤ ጸለምቲንና ራያን ሳያካትት፤ በምስራቅ በኩል የነበረውን የትግራይ አጋማሽ በቋንቋ ለአፋር በመማካለል ትግራይን አውራጃ አሳከላት፡፡ ሊንኩን ይከተሉ፡፡

https://en.m.wikipedia.org/wiki/File:Ethiopia_-_Administrative_regions_1987-1991.png

በራሱ ቅራኔ የተጋለጠው "የብሄር ብሄረሰቦች ኢንስቲቱት" ለራስ ገዝ ካርታው መነሻ አድርጎ የተገለገልበትን የብሄረሰብ ቋንቋዎች ስርጭት ካርታ ወልቃይት፤ ሑመራ፤ ጸገደ፤ ጸለምቲና ራያን ትግርኛ ተናጋሪዎች መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ቋንቋን መሰረት ያደረገው የፌደራል ክልሎች ካርታ ደርግ ካዘጋጅው "የብሄር ብሄረሰቦች ኢንስቲቱት" የትግራይ ካርታ አይለይም፡፡ ሊንኩን ይከተሉ፦

https://en.wikipedia.org/wiki/File:Dergue_nationalities_in_Northern_Ethiopia_western_Tigray_1978.jpg

ይህ በሌሎች ክልሎች ያልተሞከረ "ትግራዋይ ብትሆንም አማራ ነህ" የሚባለው በህዝብ ቆጠራ ውጤት (እኤአ 1994) 98 ከመቶ ትግርኛ ተናጋሪ የሆነው ወልቃይት "ሃይል ካለው እውነት አለው" ያሰኛል፡፡ "ሱማሊኛ ብትናገርም አማራ ነህ፤ ኦሮምኛ ብትናገርም አማራ ነህ" የተባለ ህዝብ የለም፡፡ የኢትዮጵያ መሰረት እየተባለች ትግራይን ባዳ ለማድረግ የተያዘው ዘመናት ያስቆጠረ ሰፊ ዘመቻ የህዋን ምስጢር ላወቀው ለአልበርት አንስታይንም እንቆቅልሽ ይሆንበት ነበር፡፡

ትግራይን በኢኮኖሚና በጂኦ-ፖለቲካ ለማዳከም ጥረት የሚደረገው ትግራይ ብትሰፋና ብትጠነክር ለኢትዮጵያ ጠንቅ ትሆናለች ብሎ በአገር ፍቅር ስሜት በመነሳሳት አይደለም፡፡ "ተጋሩ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ወስነዋልና ሳይቀድሙን ቀድመን እናጥፋቸው" የሚለው ድመት ቆፍራ የምታወጣው ዘዴ የኢትዮጵያ ህዝብ አልገባው ብሎ በስልጣን ጥመኛ መሪዎች አይኑ ተከድኖ ወደ እልቂት ይጓዛል፡፡ "ተጋሩ ያጠፏታል" የተባለችው ኢትዮጵያንም ወንጃዩ ሃይል በገዛ እጁ ራሱ ይገድላታል፡፡ ተጋሩ ኢትዮጵያን ማፍረስ ከፈልጉ አሁን ኢትዮጵያ ካለችበት አጋጣሚ የተሻለ ጊዜ አያገኙም፡፡

## 4. የትግራይ መገንጠል ተረት ተረት

"ለውሻው መጥፎ ስም ስጠውና ግደለው" የሚል የእንግሊዞች ተረት አለ፡፡ ገና የሰው ልጅ እርፍ ጨብጦ እርሻ ሳይጀምር የመጀመሪያው የልብ ወዳጁ ውሻ እንደነበረ ታሪክ ያወሳል፡፡ ይህ የሰውና የውሻ ወዳጅነት አሁንም ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ውሻን መግደል አሳዛኝ ድርጊት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ሰው በራሱ ችግር ውሻውን መግደል ቢፈልግ የአካባቢውን ህብረተሰብ አሳምኖ መሆን ስለሚኖርበት ንጹሁ ውሻ "ተናካሽ ሁኗል፤ የትም ውሎ እየመጣ ነው፤ ራቢስ ሳይለክፈው አልቀረም" በሚል የውሻው ባለቤት ግድያው ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ህብረተሰቡም ከተነገረው ውጪ ምስጢሩን ስለማያውቅ ውሻውን እንደ አደጋ ቆጥሮ ግድያውን ያጸድቃል፡፡

ትግራይን ከውሻ ጋር የማመሳሰል አላማ የሌለው ደራሲ የተረቱ ትርጉም ላይ ብቻ አተኩሯል፡፡ የአማራ ሃይሎች ምእራብ ትግራይን በወረራ ከያዙ፡ ተጋሩን ጠራርገው ካባረሩ፤ የራሳችን የሚሉት በገፍ አስፍረው ካበቁ በኋላ ግዛቱን

የራሳቸው ማድረጋቸው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ይሻሉ፡፡ ይህን ማድረግ በህግም በሞራልም ተቀባይነት ስለሌለው በኢትዮጵያ ህዝብ ፊት የትግራይን ስም በማጠልሸትና የኢትዮጵያ ህዝብ ጥርጣሬና ስጋት እንዲያድርበት በማድረግ በወልቃይት ባለቤትነት ላይ ይሁንታን ለማግኘት ቅንነት የጎደለው ጥረት ያደረጋሉ፡፡ “መገንጠል” የሚለው ቃል የኢትዮጵያን ህዝብ ያባንናል፤ ያውም ያገር መሰረት የሆነው ትግራይ፡፡ “ህወሓት ህገመንግስቱ ላይ መገንጠል የሚለው ቃል ያስገባችው ለምታስበው መገንጠል ቀድማ ለማመቻቸት ነው” የሚለው ውንጅላ እንኳንና ብዙም ያልተማረው የኢትዮጵያ ህዝብ ቀርቶ በከፍተኛ ምሁራን ዘንድም ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል ውንጅላ ነው፡፡

“ትግራይ ከተገነጠለች ኢትዮጵያ ስለምትፈርስ ምን ይደረግ?” ለሚለው የተንኮለኞች ጥያቄ ህዝቡ በየዋህነት “ከኢትዮጵያ ስለማይበልጡብን የፈለጋችሁት አድርጓቸው” የሚል አወንታ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በኋላማ “ተጋሩን እንደ ታስማኒያ አንድ ሰው እስኪቀር እናጠፋቸዋልን” ሲባል ጭብጭባ፤ “እንደ ፍየል ስጋ ጠብሰን እንበላቸዋለን” ሲባል ጭብጨባ “ካንሰር ናቸውና በቀዶ ጥገና ተለቅመው ይጥፉ” ሲባል ጭብጨባ፤ “ሰይጣን ደግ ነው ከነሱ አንጻር” ብለው ሊቀ ጳጳሳት ቢራገሙ ጭብጨባ፤ “ትግራይ የሚለው ቃል በህግ ተከልክሎ ወደ አምስት ትቆራረጥ” ሲባል ደማቅ ጭብጨባ፡፡ በዚህ አደገኛ ሂደት ወንጀለኛ የሚሆነው ያበደው የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ያሳበዱት ልሂቃን ናቸው፡፡

ወልቃይትን ለምን ከትግራይ ነጥቀው ለራሳቸው ማድረግ እንደሚፈልጉ በኢትዮጵያ ስም ከትግራይ መገንጠል ጋር ቀጥታ ያያይዙታል፡፡ የኢትዮጵያ ህልውና ጠባቂነት ስልጣን ማን ለነሱ ብቻ እንዳሸከማቸው ባይታወቅም “ወልቃይትና ሑመራን በመቆጣጠር ትግራይ ወደ ሱዳን መውጫ እንዳይኖራት ካደረግን ትግራይ ዙሪያዋን ተከባ ለመገንጠል አቅም አይኖራትም” በሚል ተረት ተረት ትግራይን ወህኒ አስገብቶ እንዳትገነጠል ማገድ! የኤሪትሪያን መንግስት በወዳጅነት በመያዝም ለትግራይ ከሰሜን በኩል ስጋት ፈጥሮ የወልቃይትን ይዞታ ማረጋገጥ፡፡ ይህ ሁሉ የውሸት ግርግር እንደውሃ ፈልቶ ሲያልቅ ከስር የሚቀረው እርባና የሌለው የተጋገረ ጨው ብቻ ነው፡፡ እስከዛ ድረስ ግን ህዝብ ያልቃል፤ ይሰደዳል፤ ንብረቱ ይወድማል፤ ሚስቶች ባሎቻቸውን ሳይቀብሩ ቤት ሙሉ ልጆች ይዘው በድህነት ይኖራሉ፤ ልሂቃኑ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ጂም ይሄዳሉ! አሜሪካ ኢራቅን የወጋችው ጅምላ ጨራሽ አላት በሚል ውሸት ነበር፡፡

በውሸት ትርክት ትግራይን ባለማስገንጠል የኢትዮጲያን ሉአላዊት የሚጠብቁት አጭበርባሪ ፖለቲከኞች ቀደም ብላ ከኢትዮጲያ የተገነጠልችው አገር የኤሪትርያ መንግስትን ሃይል በመጋበዝ ነው፡፡ የትግራይ መገንጠል ወንጅል ሆኖ የኤሪትርያው መገንጠል ግን ወንጀል ሳይሆን ትግራይ ላይ “ህግ አስከባሪ” ሆነ፡፡ ተቀጪዋ ኤሪትርያ ቀጪ ሆና ትግራይን አወደመች፡፡ ሰሙ የትግራይ መገንጠል ቢሆንም ወርቁ ግን የኢትዮጵያን ህዝብ አታሎ እሳት ውስጥ በመጨመር ወልቃይትን በእጅ ማቆየት ነው፡፡

## 5. “መተካካት”፡- አዲስን በጎንደር፤ ዲሬን በወልቃይት፤ ጂቡቲን በባጽዕ

በይፋ ተተንትኖ ባይነገርም “ወልቃይት የኛ ናት” የሚለው የከረረ የአማራ ሃይሎች አቋም ከጀርባው ያዘለው ተራራ የሚያክል ጂኦ-ፖለቲካዊ ሴራ አለ ብሎ መላ መምታት ይቻላል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- ሚኒሊክ የፈጠራት አዲስ አበባ በዚህኛው ዘመን የባለቤትነት ጥያቄ ይነሳባታል ተብሎ አልተገመተም፡፡ ግማሿ ያህል አማራ የሚኖርባትና አብዛኛውን የአማራ የኢኮኖሚ አቅም የምታስተናግደው አዲስ አበባ በጊዜ ሂደት በመጣ የማንነት ግንዛቤ በዙሪያዋ በሰፊ ቀለበት የሰፈረው የኦሮሞ ህዝብ አዲስ አበባን ፊንፊኔ ብሎ የባለቤትነት ጠያቄ አንስቶባታል፡፡ ይህ ከፍተኛ በሆነ የህዝብ ብዛትና የፖለቲካ አቅም የተደገፈው የኦሮሞ ባለቤትነት ጥያቄ የአማራ ክልል ኢኮኖሚን አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቶታል፡፡ አዲስ አበባ የአማራ ከፍተኛ የኢንቨስትመት ማእከል መሆኗ ብቻ ሳይሆን ትልቋ የሸቀጥ ገበያም ናት፡፡

ጉዳዩ በዛ አያበቃም፤ አማራ ልሂቃን ዘንድ ከዛ የባሰ የጂኦ-ኢኮኖሚ ስጋት አለ፡፡ ይህ የባለቤትነት ፉክክር ወደ ፖለቲካ ግድድር በመሸጋገሩ ከአማራ ክልል ወደ አዲስ አበባ የሚደረገው የሰውና የሸቃጣ ሸቀጥ ዝውውር ከፍተኛ ውጥረት ገጥሞታል፡፡ በሁለት መስመሮች ከአማራ ክልል ከ/ወደ አዲስ አበባ የሚወጣውና የሚገባው የአማራ ክልል ህዝብና ኢኮኖሚ በኦሮሞ ሃይሎች እየተደናቀፈ በመሆኑ፤ በፋኖ ላይ አማራ ክልል ውስጥ በፌደራል ጦር የሚካሄደው ዘመቻ በአማራ ላይ የኦሮሞዎች ዘመቻ ነው እየተባለ ስለተተረጎመ የአማራና የኦሮሞ ህዝብን ግንኙነት ዘላቂ የሆነ አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አማራ ክልል የኦሮሚያ ክልል ውስጥ 600 ኪሎሜትር አቋርጦ ያለ ምንም ችግር

የጂቡቲን ወደብ ይጠቀማል ማለት የህልም እንጀራ ነው፤ በተአምር አደገኛው ሂደት እስካልተገለበጠ ድረስ፡፡

አማራ የኦሮሞን ግድግዳ ከመግፋትና የማያባራ ትርምስን ከማስተናገድ አዲስ አበባን በጎንደር፤ ጂቡቲን በምጽዋ የመተካት ሃሳብ እያንሰላሰለ ይሆን ራያን ችላ ብሎ በወልቃይት ላይ አቅሙን አሟጦ በመታገል ላይ የሚገኘው? ትኩረት ሰጥቶ ነጥቦችን ላገጣጠመ ተንታኝ የሚከተለው ስእል ቁልጭ ብሎ ይታያል፡፡ ለእውነትነት በቀረበ መላ-ምት ፍኖተ-ካርታው ይህን ይመስላል፡- ከአማራ ክልል ወደ ምጽዋ ለማለፍ ከሱዳን እስከ አፋር በርሃ ድረስ የተዘረጋችው ትግራይን መዝለል አይቻልም፡፡ ስለዚህ ለአማራ የሚኖረው አማራጭ ትግራይን አሳምኖ ወደ ህብረቱ ማስገባት  ካልሆነ በእንቅፋትነት ፈርጆ “እንቅፋቱን ማንሳት”፡፡ ትግራይን በዚህ እቅድ ውስጥ አካቶ ከአማራ ወደ ምጽዋ በሰላም ማለፍ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ኤሪትርያ የኢትዮጵያ አካል ሆና በቆየችባቸው አርባ ያህል አመታት ከጎንደርና ከጎጃም በሽሬ-ዓድዋ-አዲኳላ መስመር፤ ከወሎ በአላማጣ-መቐለ-ሰንዓፌ መስመር ያለስጋት ገቢና ወጪ ሸቀጦች ይመላለሱ ነበር፡፡

ስጋቱ ሊሆን የሚችለው ትግራይ መተላላፊያ ከሆነች የአማራውን የውጪ ንግድ ትቆጣጠራለች፤ ቀረጥም ትቀርጣለች ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ስጋት ተሞክሮ የለም አይባልም፡፡ ነጻነትን የመረጠችው ኤሪትርያ ከኢትዮጵያ አንቀልባ አልወርድ ብላ የኢትዮጵያን ሃብት መበዝበዝ በመቀጠሏ በትግራይ ዓዲግራት ላይ ኬላ ተሰርቶ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህ ግን የኤሪትርያን የውጭ ንግድ ስርአት ለማስያዝ እንጂ አማራን ለመጉዳት ታልሞ አልነበረም፡፡ አማራ ከትግራይ ጋር ተባብሮ ለመስራት ቢስማማም እንኳ የኤሪትርያ መንግስት አመራሮች ለሃሳቡ ቀና ስሜት ይኖራቸዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የኤሪትርያ መንግስት ህወሓትን እንደ አገልጋይ ቆጥሮ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የመቆጣጠር አላማ ሲይዝ በተቃራኒው ህወሓት “ነጻነትን ከመረጡ ሰብሰብ ማለት ነው እንጂ ከሰው ጓዳ ማንጎዳጎድ አይቻልም” ብትለው የአለም አንደኛ ጠላቱ አደረጋት፡፡

ምንም እንኳ የግራ ጆሮን በቀኝ እጅ በጀርባ ዞሮ ለመያዝ መሞከር አዳጋች ቢሆንም ኤሪትርያና አማራ/ኢትዮጵያ መገናኘት የመረጡት የትግራይን ምእራባዊ ግዛት ቆርጠው ትግራይ የማትቆጣጠረው ኮሪዶር በመፍጠር ነው፡፡ በዚህ መስመር ከጎንደር ምጽዋ የሚደረሰው በሑመራ-ኦምሓጀር-ጋሽ ባርካ አድርጎ

በምእራባዊ የኤሪትርያ ቆላዎች ወደ አስመራ በማምራት ነው፡፡ ወልቃይትን ከትግራይ ቀምቶ የራስ ለማድረግ የመጀመሪያው ማሳመኛ “ትግርኛ ቢናገሩም አማሮች ናቸው” የሚለው ነበር፡፡ የብሄር ማንነት በቋንቋ እንደመሆኑ ይህ ትርክት ገዢ የሌለው ሆነ፡፡ የተተካው ግን ሌላ አደገኛ በሆነና የኢትዮጵያን ሉአላዊነትን በሚጥስ ትርክት ነው፡፡ ይኸውም፡- “ወልቃይቶች የሚናገሩት የኤሪትርያ ትግርኛ ነው፤ የፈለሱትም ከዛው ነው”፡፡ ይህ ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ የሚመታ አመቺ የሆነ ትርክት ነው፡፡ ወልቃይት የትግራይ እንዳልሆነና አማራና ኤሪትርያ የተገጣጠሙት በኤሪትርያውያን መሬት እንጂ ትግራይን ቆርጠው አይደለም በሚል ይተረጎማል፡፡ አማራ ወልቃይት የትግራይ ከሚሆን ለኤሪትርያ ማስረከብ ይመርጣል? በውዴታ ብቻ አይደለም፤ ውሎ አድሮ ኤሪትርያ ለሙን የወልቃይት ግዛት ከአማራ መቀማቷ አይቀርም፤ በምጽዋ ወደብ አጠቃቀም ቅድመ ሁኔታ፡፡

“የአህያ ስጋ አልጋ ሲሉት አመድ” እንደተባለው ሰላማዊውንና ጤናማውን የትግራይ ደጋማ መስመርን ትቶ ደህንነቱ በማያስተማምነውና በወባ በሽታ የተበከለውን የኤሪትርያ ቆላማ መስመር ለግዙፍ የንግድ ምልልስ መጠቀም በእልክ አረፋ ስትጨብጥ ጎርፍ ጠራርጎ ከወሰዳት ሚስት ተረት ጋር ይመሳሰላል፡ አሁን ነገሮች ተቀያይረዋል፡፡ የጥምሮቹ ሃይል ተበታትኖ ጥንድ ጥንድ ሆኖ ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቋል፡፡ የወልቃይት ጂኦ-ኢኮኖሚያዊ ስትራተጂ ሁለት ያጣ ጎመን ሆኗል፡፡ ፈደራል መንግስት ከኤርትርያ ጋር፤ አማራ (ፋኖ) ከፈደራል መንግስት ጋር መጨረሻውን ማየት የማይቻል ግጭት ውስጥ ገብተዋል፡፡ የወልቃይትን የይገባኛል ከርክር የሚያሸንፈው ማነው? ሁለቱም ጎራዎች የፖለቲካና ወታደራዊ አቅማቸው መንምኗል፡፡

### 6. ወልቃይት “ልዋጭ ልዋጭ!”?

በወልቃይት ጉዳይ ላይ የፌደራል መንግስቱ ድብብቆሽ ለአማራ በማድላት ሊሆን ይችላል ቢባልም የራሱ የሆነ አጅንዳም እንዳለው በሚያስጠረጥር ሁኔታ ከአሰብ ጋር “ልዋጭ ልዋጭ” ሊልበት አስቦ ይሆን? ያሰኛል፡፡ የትግራይ ጦርነት ድምጹን አጥፍቶ ቀሪው የህዝብ ህይወት ግን መሬት ሳይነካ አይር ላይ ተንጠልጥሎ ባለበት የኢትዮጵያ ባህር በር ጥያቄ የአገሪቱንና የቀጠናውን የፖለቲካ “ፍሪኴንሲዎችን” አጨናንቆ ይገኛል፡፡ የባህር በር ሲባል ፈጥኖ በኢትዮጵያውያን

አእምሮ ውስጥ የሚከሰተው የቀይ ባህር ወደቦች ጉዳይ ነው፡፡ ድብልቅልቅ ያለ ፉከራና ቀረርቶ፤ በታላላቅ ሰዎች ጥቅሶች የኤሪትርያን ሉአላዊነት ደፍሮ የባህር በር በቋሚነት ማግኘት አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ ወደብ የሚያስፈልጋት መሆኑ የሚያጠያይቅ ባይሆንም እንደ አለም ሃያላን አገሮች አለም አቀፍ ህግ ጥሳ ኤሪትርያን መውረር አትችለም፡፡ ይህ ሙከራ ወደማያባራ ቀጠናዊ ጦርነት የሚያመራ ስለሆነ እንዲህ አይነት አጉል አርበኝነት በእንጭጩ ሊቀጭ ይገባል፡፡ ለአገር ኢኮኖሚ ወሳኝ የሆነውን የባህር በር ለማግኘት ምን አይነት ሰላማዊ እርምጃዎች መውሰድ እንደሚቻል መዘርዘር የዚህ ጽሁፍ አላማ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ መሪዎች አንድ የሰላም አማራጭ ሆኖ የተጠቀሰው ግን እጅግ አነጋጋሪና ከዚህ ትንተና ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው፡፡

በሰላም አሰብን ለማግኘት ኢኮኖሚያዊና ጂኦግራፊያዊ ሰጥቶ መቀበል መርህን መተግበር ይገባል ይላል በአቢይ አህመድ የተነገርው አማራጭ፡፡ የኢትዮጵያ መሪዎች አማራጭ አቋም በኢትዮጵያ በኩል ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ ከቴሌኮምና ከህዳሴ ግድብ ድርሻ ለኤሪትርያ መስጠት በሚል ቀርቧል፡፡ ይህ የመፍትሄ ሃሳብ ወርቅን በመዳብ የመለወጥ አይነት ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ለኢኮኖሚስቶች ትተን መሬት በልዋጭ በመስጠቱ ሃሳብ ላይ ትኩረት እናድርግ፡፡ ኤሪትርያ አሰብን ለኢትዮጵያ ብታስረክብ በምትኩ ማግኘት የምትፈልገውና የኢትዮጵያ መንግስትም ለመስጠት የሚስማማው የትኛውን መሬት ነው? ይህ አማራጭ የኢትዮጵያው መሪ የአፍ ወለምታ አልነበረም፤ ጃዋር መሃመድም በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ሃሳብ እንደዋዛ ወርወር አድርጎበታል፡፡ ጋዜጠኛ ደረጀ፡- “አቶ ጃዋር፤ መሬት በለውጥ መስጠት የተባለው ጉዳይ እንዴት ነው?”፤ አቶጃዋር፡ “ዋይ ኖት!”

ይህ ለልዋጭ የሚቀርበው መሬት የቱ እንደሆነ ከኤሪትርያ ኣዋሳኞች ዝርዝር እየገመገሙና እየሰረዙ መለየት ያቻላል፡፡ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ኩታ ገጠሙ አፋር ለልዋጭ አይሆንም፡፡ ወታደራዊ ፋይዳ እንጂ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሌላቸው ኢሮብ፤ ዛላ አምበሳና ራማ የሚያደርሷት ወደማትፈልገው ትግራይ እንጂ ኤሪትርያ ወደምትመኘው በተፈጥሮ ሃብት የታደለው የኢትዮጵያ ምእራባዊ ኢጋማሽ አይደለም፡፡ ኤሪትርያ በትግራይ አቋርጣ ማለፍ ሳያስፈልጋት በወልቃይት የእድሜ ልክ ምኞቷ ወደ ሆነው የኢትዮጵያ ሃብትና ገበያ ሰተት አድርጎ ያስገባታል፡፡ ልውውጡ በሚስጥር ሊሆን ስለማይችል ኢትዮጵያ

ትግራይን አስቀይማ አሰብን በሰላም መጠቀም አትችልም፡፡ ኤሪትርያም ለትግራይ በምጽዋ ወደብ መጠቀምን ላትፈቅድ ትችላለች፡፡ ይህን ተከትሎ የሚመጣው አለመረጋጋት አንዳቸውም በሰላም ተጠቃሚ የሚሆኑበት እድል የለም፡፡ ጃዋር ሞሃመድ የመሬት ልዋጩ ቢፈጸም ምንድነው ችግሩ ብለው ትከሻቸውን የሰበቁብት ስሜት ከመሬቱ ጋር የሚለወጠው ህዝብ ኦሮሞ ቢሆንስ?

ወልቃይት ሑመራን በአሰብ ለመለወጥ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ዝግጅትም አለ የሚል ወሰጥ ለውስጥ የሚወራው መላምት ህይወት የነበረው መሆኑ የሶማሊላንዱ ውዝግብ ሰሞን ተጋልጧል፡፡ በጥይት ይሁን በለውጥ አሰብን እረከባለሁ እያለ አለምን በአንድ እግሩ አቁሞት የከረመው የብልጽግናው መንግስት ወደ ቀይ ባህር ባለቤትነት የሚወስደውን መንገድ ድንገት በኤደን ባህረሰላጤ በኩል መቀየሩ አስገራሚ ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ከትግራዩ ጦርነት ሳያገግም በኦሮሚያና በአማራ ክልል ውስጥ በስፋት ጦርነት ላይ ተጠምዶ እያለ፤ እንዲሁም የአገሪቱ ኢኮኖሚ በደቀቀበት ሁኔታ ላይ ሆኖ በለኮሰው የአሰብና የቀይ ባህሩ ቱማታ ኤሪትርያን ጭንቀት ውስጥ ከቶ በቀይ ባህርና በምስራቅ አፍሪካ ኢጋር ፍለጋ እንድትኳትን አደረጋት፡፡

በዚህ ምስቅልቅል ያለ የቀጠናው ጂኦ-ፖለቲካ ሂደት አጋጣሚ ነው የወልቃይት ሑመራ በአሰብ የመለወጥ ምስጢር የወጣው፡፡ በ04 ጥር 2016 በኩሉ ሚድያ የዜና ስርጭት ሬድዋን ሁሴን (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የአገር ደህንነት አማካሪ) ተጠቅሶ የቀረበው መረጃ ወልቃይት ሑመራን በአሰብ የመለወጥ የውሳኔ ሃሳብ እንደነበረና የመንገድ ስራና ጥገናም ተጅምሮ እንደነበር ተነገረ፡፡ ይህ ሳይሳካ መቅረቱና በምትኩ በኢትዮጵያ ላይ ቀጠናዊ፤ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ የዲፕሎማሲና ወታደራዊ ጦስ የጎተተባትን የሶማሊላንድ ስምምነት ወስጥ እንደገባች ተዘግቧል፡፡ የብልጽግናው መንግስት የአማራ ሃይሎችን ከወልቃይት ሑመራ እየገፋ በፌደራል ሰራዊት ሲተካ የፕሪቶሪያን ስምምነት ለመተግበር ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነው በሚል ተተርጉሞ ነበር፡፡

## 7. የልሂቃን ህልምና የትግራይ፤ የአማራ፤ የኤሪትርያ ህዝብ ኪሳራ

የተጨበጠና አስተማማኝ የሰነድ ማስረጃ በሌለበት የወልቃይትን የባለቤትነት ታሪክ በየፊናው ስለታሪክ ማውሳት ሳያስፈልግ ከህገ መንግስቱ መጀመር ተገቢ ነው፡፡ ትግራይ አፋርን አጥቶ ወልቃይትን ያገኘው ታሪካዊ ማስረጃ በማቅረብ

ሳይሆን ህገመንግስቱ መላ ኢትዮጲያን በቋንቋ ፌደራሊዝም የውስጥ አስተዳደሩን ጂኦግራፊ በማዋቀሩ ነው፡፡ አማራ ክልልም ቢሆን ህልውና ያገኘው አማርኛ ተናጋሪ ክልል ተብሎ ነው፡፡ በሱማሊም፤ በኦሮሚያም፤ የሆነው ይኸው ነው፡፡ ማናለብኝነትና ህግ ለየቅል ናቸው፡፡ በመንግስታዊ ስርአቱ መሰረት ላይ በወፍራሙ የተነጠፈው የህብረተሰብ ክፍል የሁላችሁም ዳቦ ልብ ልቡ የኔ ነው ከማለት መቆጠቡ ለዘላቂ ሰላም አስተማማኝ ይሆናል፡፡ አማራ ክልል ራሱ የተዋቀረበትን የማካለል መርሆ ትግራይ ላይ አይሰራም ማለት ህጋዊም ሞራላዊም አይደለም፡፡ በወልቃይት ጉዳይ የሚፈራረቅ የጎራዎች የአቅም ልዩነት በመኖሩ ነው ሊደረስበት ይችል የነበረው ሁሉም አሸናፊ ሊሆን የሚችልበት ስምምነት ሳይሳካ ሶስት አመት ሙሉ እልክና መጠፋፋት ብቻ የነገሰው፡፡

አማራ የወልቃይትን ጉዳይ ማንሳት በጀመረበት ወቅት ፖለቲካዊና ወታደራዊ አቅሙ የነበረው ትግራይ መዳፍ ውስጥ ነበር፡፡ ያኔ ትግራይ ድርድርን የመቀበል ፍላጎት አልነበረውም፤ የጥያቄውን አራማጆች ከማሰርና ከማንገላታት በስተቀር፡፡ የትግራይ መሪዎች ከስልጣን ወርደው የአማራው ጎራ በፌደራልና በኤሪትርያ መንግስታት ድጋፍ ከፍተኛ አቅም ሲያገኝ የመረጠው ድርድር ሳይሆን ወረራን ነው፤ ህወሓት ለአማራ ድርድርን ሳይሆን በማናለብኝነት ሃይል መጠቀምን ስላስተማረች፡፡ አሁን የአማራው ጎራ ፈርሶ አማራም ትግራይም አቅመቢስ ሆነዋል፡፡ በወልቃይት ጉዳይ አማራ አሁንም የፌደራል ስልታዊ ድጋፍ አለው፡፡ ሬፈረንደም የሚል ህገ መንገስታዊ ያልሆነ ውሳኔም ትግራይና አማራን እያካረረ ነው፡፡ ፌደራል መንግስት በወልቃይት ጉዳይ ላይ እግሩን እየጎተተ መፍትሄዎችን የሚያወሳስበው በአማራን ጥቅም ለመጠበቅ ነው ወይስ ሌላ ድብቅ አጅንዳ አለው? ይህ ጉዳይ ወደ ኋላ ራሱን ችሎ ይተነተናል፡፡

በህገ መንግስቱ መሰረት ወልቃይት የትግራይ አካል እንደሆነ እንዲቀጥል ቢወሰን እንኳ እዚህ ላይ ግዙፍ ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ አማራም ሆነ ትግራይ ኤሪትርያንም ጨምሮ ወልቃይትን የሚፈልጓት ለምንድን ነው? የዚህ ሁሉ የሚልዮኖች ማለቅና መሰደድ ተጠቃሚ ማነው? ወልቃይት ከዚህም ከዛም ብትሆን ተጠቃሚው ተራው ህዝብ ነው ወይስ ባለስልጣናት፤ ነጋዴዎችና የውጭ ሸሪኮቻቸው? መልሱ ምን እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ ለውይይትና ለጋራ ጥቅም ሳይሆን ለጥፋት ግፋ በለው የሚለው ማን እንደሆነ ለማንም ስውር ስላይደለ፡፡ ለ17 አመታት መቶ ሺዎች የሞቱበት፤ የቆሰሉበት፤ የተሰደዱበት፤

ንብረት የወደመበት በትግራይ የተካሄደው ጸረ-ደርግ ትግል ከተጠናቀቀ በኋላ አዲስ አበባና ትግራይ ላይ ስልጣን የተቆናጠጠው የህወሓት አመራር ለኢትዮጵያ ከፍተኛ እድገት ቢያስመዘግብም ትግሉ ለጥቂቶች በዝምድናና ልከከልህ የተሰባሰቡ የከበሩበትና የታገለውን ህዝብ የረሱበት ነበር፡፡ ይህ ክህደት ሌላ የከፋ ጦርነት ጋብዞ ድሃው የትግራይ ህዝብ ለዳግም ጥፋት ተጋለጠ፤ ትግራይ መቀመቅ የገባችበት ጦርነት!

ህዝብን እንደ ፌስታል ተጠቅሞ መጣሉ ባልበረደው የትግራይ ጦርነት ሲደገም ይታያል፡፡ ሚልዮኖች ያለቁበት፤ የተሰደዱበት፤ መቶ ሺዎች ሴቶች የተደፈሩበት፤ መሰረተ ልማት የወደመበትና የተዘረፈበት፤ ስድስት ሚልዮን ህዝብ መገናኛ፤ ባንክ፤ እርዳታ ተዘግቶበት ሁለት አመት ሙሉ  የተዋረደበት ጦርነት ጋብ ሲል መሪዎቹ ህዝቡን ገና በአግባቡ ሳያረጋጉና ወደ ኑሮው ሳይመልሱ በስልጣንና በጥቅም ሲራኮቱ ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ ይኸው አንድ አመት አለፈ፡፡ ዋናው የወልቃይት ጉዳይ ሳይፈታ፤ የኤሪትርያ ጦር ከሰሜን ትግራይ ሳይለቅ "አሞራው በረረ ቅሉ ተሰበረ፤ ጨዋታው ፈረሰ ዳቦው ተቆረሰ" አይነት የልጆች ጨዋታ የተያዘ ይመስላል፡፡ ባለስልጣኖች የራሳቸውን የግል ደህንነት በአጀብ ሲያስጠብቁ በከተማ ገድለው የሚቀሙ ወሮበሎች ንግድ ፈቃድ ያወጡ ያህል ተዝናንተው ህዝብን ያሸብራሉ፡፡ አገሩ ጠላት ያዘው ሲባል ሸብር፤ ወገን ያዘው ሲባልም ሸብር! እርዳታን የዘረፈው የባለስልጣን ጅብ አልጮህ ሲል ቁሱ ዝም መጽሃፉም ዝም!

በትግራይ የኑሮና የስራ ተስፋ አልታያቸው ያለ ወጣቶች በሁለት መንገድ ስሜታቸውን እየገለጹ ነው፤ ሰልፍ ግን አንዱ አይደለም፡፡ እኔን ያየህ ተቀጣ ሆኖ የባለውለታ አካል ጉዳተኞች ሰልፍም ያተረፈው አስለቃሽ ጋዝ፤ ባዶ መለፋለፍ፤ መወጋገዝና መዘንጋት ነው፡፡ በፕሪቶሪያ ማግስት በመቐለ መንገዶች ላይ የፕራንክ ቪድዮ ሲቀረጽ በአግራሞት ያየ ሰው፤ በመስቀል በአል ርችት ሲተኮስ አምሽቶ ቀጥሎ ደግሞ በመንግስት ሚድያ "መቶ ሰው በረሃብ አለቀ" ሲባል እግዚኦ! ያሰኛል፡፡ መጠጥና ስደት የወጣቶች የሃሳብ መስጫ ሳጥኖች ሆነዋል፡፡ የመጠጥና የትራንስፖርት ኩባንያዎች በዚህ የደራ ገበያ ትርፍ እያጋበሱ ነው፡፡ የመጠጥ ባህሉ ትንሽ ወጣ ያለው የትግራይ ወጣት ፊትም ቢሆን የመጠጥ ፋብሪካዎች አስተማማኝ ደንበኛ እንደነበረ እንደ ሰድብ ሳይወሰድ መራራ ሃቅን መቀበል የግድ ይላል፡፡

አሁን ካለው ጭንቀት ጋር ተያይዞ ጠጪነት በመስፋፋቱ ሆቴሎች ውስጥ በቀን ውሃ ማዘዝ “ጤባ” የሚያሰኝ ሆኗል፡፡ በመላ ኢትዮጵያ ያሉ የቢራ አምራቾች የትግራይ ዝግ ሲነሳላቸው ከእርዳታ በፊት ቀድመው ያደረሱት ኬሻዎችን ሳይሆን ካሳዎችን ነው፡፡ በጦርነት የደቀቀውና ተፈናቃይ ያጥለቀለቀው ሽሬ አቢራውን ሳያራግፍ “እሽሩሩ ካላሽኔ” የሚል የሃበሻ ቢራ ኮንሰርት አይቷል፡፡ ይህ የትውልድ ግድያ ከጥይት የባሰ ነው፤ በፈቃደኛነትም ስለሆነ ቀላልና ዘላቂ ነው፡፡ ጦርነቱ የህዝብ እንደሆነው ሁሉ አጀንዳው የህዝብ ውጤቱም ለህዝብ ቢሆን ፍትሃዊ ነው፡፡ እውነታው ግን ጦርነቱ “ከልሂቃን፤ በልሂቃን፤ ለልሂቃን” ሆኖ ህዝብ እንደ ቼዝ ጨዋታ ከንጉስ ንግስቶቹና ከጳጳሳቱ በፊት “ፓውኖች” ሆኖ የሚረግፍበትና ለመስዋእትነቱም ባዶ ሙገሳ ብቻ የሚቸርለት ነው፡- “ሓየት!፤ ጅግና ተጋዳላይ!፤ ዋዕሮ!” ወዘተርፈ፡፡

ያሁሉ ተረስቶ፤ የትግል ትዝታ ትረካና ዘፈን ብቻ ቀርቶ፤ ህዝብ መቶ ሺዎች ልጆቹን ገብሮና ወደከፋ ድህነት ማጥ ውስጥ ገብቶ፤ በየባለስልጣናቱና በየንግዱ ማህበረሰብ ቤት ግን “ቢዝነስ እንደዱሮ” ሆኖ አሁንም ሚልዮኖች የሚፈስበት ድግስ፤ አሁንም የመኪናና የቤት ምርጫ፤ አሁንም ትግል ጸጉራቸውን እንኳ ያልነካቸው የከበርቴ ልጆች ቅንጦት፤ አሁንም ሙስና፤ አሁንም የስልጣን ሽኩቻ፤ አሁንም የአስተዳደር በደል፤ አሁንም ከህዝብ ጠላቶች ጋር መለሳለስ! ለወልቃይት የተለኮሰው ጦርነት የኤሪትርያን የሰላሳ አመት የትግል ታሪክ ያጨቀየና ህዝባዊ ሞራልን ያኮሰሰ ነበር፡፡ በትግሉ ወቅት የረዳቸውንና ኋላም ነጻነታቸውን ያረጋገጠላቸውን የትግራይን የፖለቲካ አመራር፤ ህዝቡንም ጭምር ለማውደም የኤሪትርያ ታጋዮች ልጆችና የኤሪትርያ ህዝብ ገዳዮች ልጆች በጦር ግንባርና በመላው አለም ጥምረት ፈጠሩ፤ ተቃቀፉ፤ “ያጣላቸው” የትግራይን ህዝብ ረገሙ፡፡ ችግሩ የኤሪትርያ ታጋዮች ልጆችና የኤሪትርያ ህዝብ ገዳዮች ልጆች ግንባር መፍጠራቸው እንጂ ሰላም መፍጠራቸው አልነበረም፡፡

የኤሪትርያ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ያለውን ተጋርቶ የሚችለውን አምርቶና ተነጋግዶ ቢኖር የሚመረጥ ነበር፡፡ ተጠቃሚ ያልሆነውን ህዝብ የሚማግዱበት የመሪዎቹ አላማ ግን ይህ አይደለም፡፡ ችግሩ የተፈጠረው ግንባሩ የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የታለመ እኩይ ተግባር መሆኑ ነው፡፡ የጋራ ጠላት ነው የተባለውን የትግራይን ህዝብ ለማጥፋት የኤሪትርያና የአማራ ልሂቃንና አራጋቢዎቻቸው እንደ ጠላት አርማ ሲቆጥሩ የኖሩትን አንዱ የሌላኛውን ባንዴራ

ለብሰው ሰብአዊ መብት ያስከብራሉ ተብለው በሚታመንባቸው አገሮች አደባባዮች ላይ የህዝብ እልቂት ሲያወድሱና ሲያሞግሱ ቆይተዋል፤ የአሁኑን አያድርገውና፡፡ አንድ ያደረጋቸው የትግራዩ ጦርነት እንዳለሙት ሳይሆን ሲቀር አሁን እርስበርስ ተፋጠዋል፡፡ ድሮውም የኤሪትርያና የአማራ/ኢትዮጵያ ልሂቃን "እባብ ለእባብ ይተያያል በካብ" እንደሚባለው ኤሪትርያ የኢትዮጵያን ሃብትና ገበያ ኢትዮጵያ ደግሞ የኤሪትርያን ወደቦች በስስት ሲያዩ ነው የኖሩት፡፡ የመሪዎቹ የፍላጎት ልዩነት የወለደው ቅራኔ የሚያግባባ ሳይሆን የሚያጠፋፋ ጽንፍ የረገጠ ነው፡፡ ትግራይ የሁለቱም የማይታረቅ ፍላጎት እንቅፋት ሆና ስለታየቻቸው ነው ከታሪክና ከግብረ ገብነት መስመር ርቀው የጥፋት ግንባር የፈጠሩት፡፡ ቆም ብሎ ላሰበ ግን ትግራይ የሁለቱም እናት ሆና በሰላም ለጋራ ጥቅም እንዲሰሩ ማግባባት ይቻላት ነበር፡፡

በርግጥ ትግራይ ሲነካ ዘራፍ ብሎ የመጣበትን የሚመልስ የጦር አዋቂ እንጂ ረዥም እይታ ያለው የሰከነ ፖለቲካና ዲፕሎማሲን የሚያራምድ ልሂቅ አልታደለችም፡፡ "ትግራይ ስትራተጂክ አመራር የላትም" ብለው መሪዎቹ በአደባባይ የሚናገሩትም ሊያፍሩበት የሚገባውን ሃቅ ነው፡፡ ለወልቃየት የተለኮሰው ጦርነት የህዝባዊነት ሽታ የሌለው መሆኑ ሌላው ምስክር ከፍተኛ የሃይማኖት መሪዎች ከመንፈሳዊ ሰላማዊና ሰማያዊው አላማቸው አፈንግጠው ለስጋዊና አለማዊ ህይወታቸው አድልተው፤ አስርቱን ቃላተ ኦሪት ሽረው "ፍጀው፤ ዝረፈው፤ እሰረው፤ አባረው፤ ድፈራት፤ አዋርዳት" እያሉ ህዝብ በህዝብ ላይ ሲያነሳሱ "ፍካሬ እየሱስ ያለው ነው" በማለት እኩይ የጭካኔ ድርጊታቸውን በሰማዩ ጌታ ላይ ያላክካሉ፡፡

በሲኖዶስ የስልጣንና የሃብት ስስታቸውንና ሽኩቻቸውን፤ ለጭፍን የዘር ጥላቻቸው መተንፈሻ ለመስጠት ለሃይማኖት ደንታ ከሌላቸው አምባገነኖች ጋር አብረው በራሳቸው ምእመናን ላይ ጥፋት ፈርደዋል፡፡ ከፍተኛ ነጋዴዎችና ከፍተኛ የሃይማኖት መሪዎች ትከሻ ለትሸሻ እየተሻሹ መድረክ ላይ ቆመው፤ ጦር ግንባርም አብረው የተጓዙበትና ከወንጌል ይልቅ "ግፉ በለው"ን የሰበኩበት "ህዝባዊ አላማ"ስ ምን ይሆን? የትግራይ ህዝብ ሰቆቃ እንዲያበቃ ይረዳ ይሆናል የተባለውን የፕሪቶሪያው ስምምነት በህዝብ ጥላቻና በጭካኔ ስሜት በመቃወማቸው የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች ከፈራሚው ፌደራል መንግስት ጋር ከፍተኛ የሆነ አተካራ ውስጥ ገቡ፡፡ አሁን ፌደራል መንግስት በአማራ ሃይል ላይ ሰፊ ውጊያ በመከፈቱ የአማራ

የፕሮፓጋንዳ ስርአት "ኣርቱን" ቀይሯል፡፡ የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች "አቢይ ነቢይ" እያሉ በጀርባቸው አዝለው ስልጣን ላይ እንዲቆናጠጥና ታሪካዊ ተቀናቃኛቸው አድርገው የሚቆጥሩትን ግን አምሳያቸው የሆነውን ትግራይን እንዲያጠፋላቸው ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ከተሸካከሩ ወዲህ ግን እነዚህ ሃይሎች አይናቸውን በጨው አጥበውና ኮታቸውን ገልብጠው የትግራይ ጠበቃዎች ሆነዋል፡፡ ግፍን በራሳቸው ክንድ ብቻ የሚለኩት የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች "ትግራይ ላይ የተደረገው ፍትህ ነው፤ ሰይጣንና ካንሰርን ቢያጠፉት ጽድቅ ነው፤ አሳውን ለመያዝ ባህሩን ማድረቅ" ሲሉ እንዳልነበር እነሱ ላይ ሲደርስ "የትግራዩ ሰቆቃ እኛ ላይ እየተደገመ ነው" በማለት በትግራይ ሰቆቃ የነበራቸውን የወሳኝነት ሚና ከአለም አእምሮ ሊፍቁ ይታገላሉ፡፡ ቢላዋ የሌላውን እጅ ሲቆርጥ ቡራኬ የራስን እጅ ሲቆርጥ ጭካኔ! ትግራይ ውስጥ "የሞተ ተጎዳ" ሆነና ሌላው ሞቶላቸው በህይወት የተረፉት ፈላስፎች ሆነዋል፡፡ "የአማራ ልሂቃን ትግራይ ላይ የፈጸሙት ቆጭቷቸዋል፤ ድሮውም ቢሆን ከሰሜኑ ስልጣን ለመቀማት አቢይና የኦሮም ልሂቃን ነበር ያጣሉን" እያሉ ለገዳዮች ንስሃ ይገቡላቸዋል፡፡

ኸረ ከዚህም የባሰ አለ! "የትግራይ ህዝብ ያለቀውና ትግራይ የወደመቺው በራሷ ሃጥያት ነው" እያለ በቀል ባያስፈልግም ወንጀለኛ እንዳይጠየቅ ሽንጡን ገትሮ የገዳዮች ተከላካይ ጠበቃ የሆነ ቁጥሩ ብዙ ነው፡፡ "የትግራይ ህዝብ ያለቀው ራሱ እይተጠቋቆመ ነው" የሚል ሌላ ጉድም አለ፡፡ "የአኹሱም ፍጅት የመጠቋቆምና የሚሊሻዎች አጉል ድፍረት ውጤት ነው"ስ እየተባለ አይደል!? ይህ ቁሶች ሳይቀሩ በሚሳተፉበት ራስ-ውንጅላ ከመጠየቅ የሚድነው ማነው? ህወሓት? ሻዕቢያ? ብልጽግና? በመላ ይሁን በአጋጣሚ የትግራይ ህዝብ በአንድ ነገር ላይ አተኩሮ ረሃቡን ያስራቡትንም፤ እልቂቱን ያሳለቁትንም፤ መፈናቀሉን ያፈናቀሉትንም፤ አጠቃላይ ድህነቱን ያደኸዩትንም እንዳያስብ በጭንቀት ተወጥሯል፡፡ የትግራይ ፖለቲከኞች እርስ በርስ ከተፋጠጡ አመት አለፋቸው፡፡ ህዝብ ሁሉንም ትቶ ስጋት ውስጥ ገብቷል፡፡ "እየተባሉ እንደገና ያስበሉን ይሆን?" እያለ "እህ!" ሲል ያድራል፡፡

የአማራ ህዝብ አሁን ያለበት ፍዳ በቃላት ሊገለጽ የሚችል አይደለም፡፡ ክልሉ ውስጥ ውጊያ የሌለበት ሰፈር የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ሆኖም በሃገር ውስጥም ከውጪው አለምም ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የለም፡፡ የአማራ ልሂቃን ከወገኑ ጋር ደም ተቃብቶ ዘላቂ ቂም በቀል ካልሆነ በስተቀር ምንም ሌላ የሚያተርፈው ነገር ሳይኖረው በትግራይ ላይ ግፉ በለው ሲሉት ይቺ እሳት ነገ የኔን

ጎጆ ትበላላለች ብሎ እንዳያስብ አድረገው አደንዝዘውት ነበር፡፡ አሁን ትግራይን ላጠፋ ወራሪ ማን አዘኔታ ይኑረው? ለአማራ ህዝብ ማዳበሪያ እንደማቅረብ፤ በሰፊ ኢንቨስትመንት የስራ እድል እንደመክፈት፤ ከተሞችን እንደማልማት፤ አዳዲስ የግብርና ዘዴዎችን እንደማስተማር በድህነት አዘቅት ውስጥ ሆኖ ለልሂቃን ቅዠት ነፍጥ አንግቦ በየጥሻው ተደፍቶ እንዲቀር ተደርጓል፡፡ እንደነ ወርቁ አይተነው የመሳሰሉ በህዝብ ደም የሚነግዱ የአማራ ከበርቴዎች ህዝቡን አጋፍጠው ኮብልለዋል፡፡ ይብላኝ በአባወራ ሞት ጦም ያደረ ማሳና የተበተኑ ልጆች፡፡ የአማራ ልሂቃን የአማራን ህዝብ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ጋር አጣልተውታል፡፡ በዚህ ምእራፍ ለአማራ የጦርነት ጎራ ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ኢሳያስ አፈወርቂን በማባበልና በማደፋፈር አቢይ አህመድን በመደገፍና በማስገደድ የአማራ ልሂቃን በትግራይ ጦርነት መጀመርና ተጀምሮ መቀጠል ቁልፍ ሚና እንደነበራቸው በማምን ነው፡፡

“የሃብታም ልጅ ሲዳር የድሃ ልጅ ተረግጦ ይሞታል” እንደሚባለው የትግራይ፤ የአማራና የኤሪትርያም ህዝብ በልሂቃን ስግብግብነት ተረግጦ ሞቷል፡፡ ያልተበላሸ አእምሮ ያለው ሰው የኤሪትርያ ህዝብ ከትግራይ መጥፋት ተጠቃሚ ይሆናል ብሎ ሊያስብ አይችልም፡፡ የኢሪትርያው አምባገነን መሪ በወልቃይት አማራን ይዞ፤ በአማራ ኢትዮጵያን ይዞ፤ በኢትዮጵያ ምስራቅ አፍሪካን ቢቆጣጠር የኤሪትርያ ህዝብ እራት በልቶ ያድራል? ልጆቹ ባህር ውስጥ ከመስጠምና ኩላሊታቸውን ከሌቦች ያድናል? ጌጥ ይመስል “ኤሪትርያ የስደተኞች አገር ናት” መባሉን ያስቀራል? ዳያስፖራ ያለው ኤሪትርያዊ የሚኮራው የጉልበት  ስራ ሰርቶ እንጀራ በሚያገኝበት አገር ኑሮ ነው ወይስ ኤሪትርያ ውስጥ ባለው የኢኮኖሚ ድቀት?

እንዳለመታደል ሆኖ ኤሪትርያ አገር ቤት ውስጥ የቀሩት ወጣቶች በማይመለከታቸው የትግራይ ጦርነት ሄደው ሲማገዱና በህዝብ ላይ ግፍ ሲሰሩ አውሮፓና አሜሪካ ሆኖ ባንዴራ እያውለበለቡ መጨፈር ምን የሚሉት አባዜ ነው? ኤሪትርያውያን የባህል አብዮት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በፊት ሁለተኛ ዜጋ ሆነው በኖሩበት፤ ከአራተኛ ክፍል በላይ እንዳይማሩ ተከልክለው መሃይም በሆኑበት፤ “አስካሪስ” እየተባሉ በየትሪፖሊ/ሊብያና በዓድዋ ጦርነት የጣሊያን ወታደሮች ሆነው ባለቁበት ቅኝ አገዛዝ የሚመኩበት ምስጢሩ ምንድነው?  አሁንስ በስደት የሚኮሩብት የእንቆቅልሹ ፍቺ የሚያውቅ አለ?፡፡ ለእንደነዚህ አይነት ልበቢሶች ቢሰወራቸውም በውጪው አለም አይን ኤሪትርያ የአፍሪካ ሰሜን ኮሪያ ናት፤ ተስፋ ያጣ ህዝብ መኖሪያ፤ የምድር ሲኦል! ኤሪትርያውያን በኤሪትሪያው መንግስት ላይ የመረጡት የትግል ስልት ለታሪካቸው አዲስና ስኬቱም የሚያጠራጥር ነው፡፡

በአውሮፓና አሜሪካ የሚኖሩ ስደተኛ ኤሪትርያውን የህግደፍና ጸረ-ህግደፍ በሚል ተቧድነው እርስ በርሳቸው በድንጋይ ቢቀጣቀጡ ምን ያህል አስመራ ላይ የተደላደለውና በቀጠናው ዲፕሎማሲያዊ ተሰሚነት ያተረፈውን መንግስት መነቅነቅ እንደሚችሉ የታወቀ ነገር የለም፡፡ ኤሪትርያውያን ግማሽ ልብ ሆነዋል፤ ኢሳያስን ለማስወገድ ሲጯጩሁ ቆይተው አቢይ አህመድ የባህር በር ጉዳይ ሲያነሱ የኤሪትርያውን መንግስት ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት ቀየሩ፤ አሁንስ?




*******************************************************************

# ምዕራፍ ፭

# የጦርነቱ ተዋናዮች፤ ደጋፊዎችና አጋጋዮች

## 5.1. የአራቱም ጎራዎች የጦርነቱ ተዋናዮችና ደጋፊዎች

### 1. ኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት ጎራ ተዋናዮችና ደጋፊዎች፡-

**የወረራው ቁንጮ የፖለቲካ አመራር**

- ዶር. አቢይ አህመድ
- ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
- አንዳርጋቸው ጽጌ*
- ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

**የፌደራል ወታደራዊ ሹመኞች**

- ጄኔራል ብርሃኑ ጁላ
- ጄኔራል አበባው ታደሰ*
- ጄኔራል ባጫ ደበሌ
- ጄኔራል ይልማ መርዳሳ
- ጄኔራል ብርሃኑ በቀለ

**የፌደራል ሲቪል ሹመኞች**

- ተመስገን ጥሩነህ*
- ገዱ አንዳርጋቸው*
- ደመቀ መኮንን*
- ንጉሱ ጥላሁን*
- ታገሰ ጫፎ
- አደም ፋራህ
- አም. ሳህለወርቅ ዘውዴ*
- ሬድዋን ሁሴን
- መአዛ አሸናፊ*
- ብርቱካን ሚደቅሳ
- አህመድ ሺዴ
- ሙፈሪያት ከማል
- ዳግማዊት ሞገስ*
- ጊዴዎን ጢሞቴዎስ
- ዶር. ዳንኤል በቀለ
- ዮሃንስ ቧያለው*
- አም. ታየ አጽቀስላሴ*

**የክልል ሲቪል ሹመኞች**

- ሺመልስ አብዲሳ
- አዳነች አቤቤ
- ሙስጠፌ ዑመር
- አወል አርባ

**የጥላቻ ሚድያ ጋዜጠኞች**

- መሳይ መኮንን*
- ታማኝ በየነ*
- ግዛው ለገሰ*
- አበበ ገላው*
- ሃብታሙ አያሌው*
- ዘመድኩን በቀለ*

**<u>የወረራ ርእዮተ አለም ጉሩዎች</u>**

- ንአምን ዘለቀ*
- ስዩም ተሾመ*
- ዶ/ር. ዳኛቸው አሰፋ*
- እስክንድር ነጋ*
- ትንግርቱ ገብረጻዲቅ*
- ታየ ደንደአ
- አቻምየለህ ታምሩ*
- ሄርሜላ አረጋዊ
- ፕሮፌሰር ጥላሁን ይልማ*

**<u>የ“ሃይማኖት ለወረራ” አራማጆች</u>**

- አቡነ ጴጥሮስ*
- አቡነ አብርሃም*
- አቡነ ህጻን*
- አቡነ ሚካኤል*
- አቡነ ፋኑኤል*
- በቀለ ወልደ ኪዳን
- ሃይለማርያም ደሳለኝ

**<u>የ“ኪነት ለወረራ” አራማጆች</u>**

- ደበበ እሸቱ*
- አብራር አብዶ
- ችሮታው ከልካይ*

**<u>የ”ቢዝነስ በውረራ” አራማጆች</u>**

- ወርቁ አይተነው*
- ሃይለ ገብረስላሴ*

**<u>የህወሓት ተቃራኒ የትግራይ ተወላጆች</u>**

- ዶ/ር. አብርሃም በላይ
- ዶ/ር. አርጋዊ በርሄ
- ዶ/ር. ሊያ ታደሰ
- ዶ/ር. ሙሉ ነጋ
- ዛዲግ አብርሃ
- ፕሮፌሰር ሃረገወይን አሰፋ
- ጀኔራል ዮሃንስ ገብረመስቀል

**<u>የውጪ “ባላዎች”</u>**

- ሞሃመድ ቢን ዛይድ
- ጣይብ ኤርዶጋን
- ሞሃመድ ፎርማጆ
- ቭላድሚር ፑቲን
- ዢ ጂንፒንግ
- ሙሳ ፋቂ
- አንቶኒዮ ጉተሬዝ

## የወረራው መሪና አጋዥ <u>ተቋማት</u>

- ብልጽግና ፓርቲ
- የፌደራል መከላከያ
- ኢዜማ ፓርቲ
- ኢትዮጵያ አየር መንገድ
- ፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች
- የመንግስትና የግል ባንኮች
- ታላላቅ ኩባኒያዎች
- ወሳኝ አገልግሎት ሰጪዎች

## 2. የአማራ ክልል ጎራ ተዋናዮችና ደጋፊዎች፡-

**የክልሉ መሪዎች**

- አገኘሁ ተሻገር
- ዶር. ይልቃል ከፋለ

**ርእዮተ አለም መሪዎች**

- ዶር. ደሳለኝ ጫኔ
- ክርስትያን ታደለ
- በለጠ ሞላ
- ዳዊት ወልደጊዮርጊስ

**ልዩ ሃይል አመራሮች**

- አበረ አዳሙ
- ጀኔራል ተፈራ ማሞ

**የወልቃይት "ኮማንደር"**

- ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ

**የአማራ ፋኖ ጦር አዛዦች**

- ዘመነ ካሴ
- መሳፍንት ተስፋ
- ማስረሻ ሰጤ
- ምሬ ወዳጆ

**መሪና ደጋፊ ተቋማት**

- አማራ ብልጽግና
- አማራ ልዩ ሃይል
- አማራ ፋኖ
- አማራ ብሄራዊ ንቅናቄ

* ይህ ምልከት የተደረገባቸው ተዋናዮች በፌደራል ስር ቢዘረዘሩም የአማራው ጎራ ቀንደኛ ተዋናናዮችም ናቸው፡፡ የነዚህ አይነት ተዋናዮች በፌደራል ቁጥራቸው በርካታ ከመሆኑ የተነሳ የጦርነቱ ማስነሻ ቁልፍና የጦርነቱ ሂደት ማርሽ መቀያየሪያ ማን እጅ እንደነበር መረዳት አያዳግትም፡፡ "ከላይ ያለው አረፋ ነው" ዮሃንስ ቧያለው

## 3. የኤሪትርያ መንግስት ጎራ ተዋናዮችና ደጋፊዎች፡-

**የወረራው "አያቶላዎች"**

- ኢሳያስ አፈወርቂ
- የማነ ገብረአብ
- ጀኔራል አብርሃ ካሳ
- ጀኔራል ፊሊጶስ ወልደ ዮሃንስ
- አም. ሶፍያ ተስፋማሪያም

**የጥላቻ ነብያት**

- ጀናይ ገብረ ገርግሽ
- አወል ሰዒድ

## 4. የትግራይ ጎራ ተዋናዮችና ደጋፊዎች፦

**የመከላከል ሲቪል የበላይ መሪዎች**

- ዶር. ደብረጽዮን ገብረሚካኤል
- ጌታቸው ረዳ
- ፈትለወርቅ ገብረ እግዚአብሄር
- አለም ገብረዋህድ
- ጌታቸው አሰፋ
- መሓሪ ዮሃንስ

**የመከላከል ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦች**

- ጄኔራል ጻድቃን ገብረተንሳይ
- ጄኔራል ታደሰ ወረደ
- ጄኔራል ምግበይ ሃይለ
- ጄኔራል አብርሃ ተስፋይ
- ጄኔራል ተኽላይ አሸብር
- ጄኔራል ዮሃንስ ወልደ ጂውርጊስ

**የውጭ አገር ዜጋ ደጋፊዎች**

- ንዒማ ኤልባግር
- ፕሮፌሰር ያን ኒሰን
- ማርቲን ፕላውት
- ጀቲል ትሮንቮል
- ፕሮፌሰር አሌክስ ዴዋል
- ሚካኤል ዋላስ
- ፔካ ሃቪስቶ
- አማኑኤል ኢያሱ

**የመከላከል ሚድያ ጋዜጠኞች**

- ስታሊን  ገብረስላሴ
- ሃይለ አረፋይነ
- ኤድሞንድ ብርሃነ
- ሃይለ ሚካኤል
- ማርያማዊት ሃይሌ

**ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሰጡ ነብዮች**

- ስዩም መስፍን
- ስየ አብርሃ

**የመከላከል አክቲቪስቶች**

- ዶር. ቴድሮስ አድሓኖም
- መአዛ ጊደይ
- አም. ፍስሃ አስገዶም
- ካሳ ሃይለ ማርያም
- አበበ ጊደይ
- መሓሪ ታደለ
- ዶር. ገላዲዮስ አርአያ

**የመከላከል የሃይማኖት መሪዎች**

- አቡነ ሰረቀ ብርሃን

**የመከላከል ጤና ታጋዮች**

- ዶር. ቴዎድሮስ ተፈራ

<u>**ኪነት ለህዝባዊ መከላከል**</u>

- ሰለሞን
- ዘአማን
- አበበ
- ተኽላይ
- ጠርጣራው
- ገብሩ
- ትምኒት
- ንጉሰ
- ኤልሳ
- ግርማይ
- ኪዳነ
- ሚላው
- አብርሃም
- ኤደን
- ብርሃነ
- መርከብ
- ማህሌት
- ሸዊት
- ሰለሞን
- ሳምራዊት
- ክፍሎም

## 5.2. የጦርነቱ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት

**1. የኢትዮጵያ አየር መንገድ** (ንዒማ ኤል ባግርና ባልደረቦች 28 መስከረም 2014)

"የኢትዮጵያ መንግስት 09-19 ህዳር 2013 ቢያንስ ለስድስት ጊዜያት ወደ ጎረቤት ኤሪትርያ የጦር መሳሪያዎችን ለማጓጓዝ የሀገሪቱን ዋና የንግድ አየር መንገድ ተጠቅሟል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ የጦር መሳሪያዎችንና ጥይቶችን ያጓጓዘበት በአስር ሺዎች የሚቆጠር ዶላር የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴርን አስከፍሏል። ታንኮችና ከባድ መሳሪያዎች ወደ አዲስ አበባ በሚመጡ አውሮፕላኖች ላይ ተጭነዋል፣ ትናንሽ መሳሪያዎች፡- ሞርታር፣ ላውንቸር ወደ አስመራ ተልከዋል።

**2. "የተማረ ይግደለኝ"፡ በፌደራል ዩኒቨርሲቲዎች የተደረገ የጦርነቱ ድጋፍ**
(ተክለሃይማኖትና ባልደረቦቹ፤ ትግሃት 2014)

<u>**ከዩኒቨርሲቲዎች ለኢትዮጵያ መከላከያ የገንዘብ ያልሆነ ድጋፍ**</u>

- ሰራተኞች ደመወዛቸውን ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰጥተዋል
- የተማሪዎች በጀት ወደ ኢትዮጵያ መከላከያ ተዋውሯል
- የዩኒቨርሲቲ የህክምና ባለሙያዎች ወደ ግንባር ተልከዋል
- ለሠራዊቱ የቁሳቁስ ልገሳ
- ለኢትዮጵያ መከላከያና ለፋኖ የምግብ ዝግጅትና ልገሳ
- ለኢትዮጵያ መከላከያ የቁም እንስሳት ልገሳ፡- የግብርና ኮሌጅ ከብቶች
- በዩንቨርስቲው ሰራተኞች ደም ልገሳ
- ዩኒቨርሲቲዎች ለጥላቻ ሰባኪዎች ምሽጎች ሆኑ

- ዓለም አቀፍ ተባባሪዎች ፀረ-ጦርነት ናችሁ ተብለው ተዋክበዋል
- በባህር ዳርና በወሎ ዩኒቨርሲቲዎች የትግራይ ተወላጅ ሰራተኞች ተገደሉ
- የትግራይ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ሰራተኞች በእስር ካምፖች ውስጥ ይገኛሉ
- የትግራይ ተወላጅ ዩንቨርስቲ ሰራተኞች ከዩኒቨርሲቲ መኖሪያ ቤት ተባረሩ
- የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች በድንጋይ ተወግረው ተገደሉ
- የትግራይ ተወላጆች ሰራተኞች ስም ዝርዝር ለህዝብ ተሰራጭቷል
- የዩኒቨርሲቲ ግቢዎች ለወታደራዊ አገልግሎት ውለዋል፡- ስታዲየሞ፣ ሕንፃ
- **የዩኒቨርሲቲ ባለስልጣናት በምዕራብ ትግራይ የጦር ግንባር ጎብኝተዋል**



- የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች ወታደራዊ ስልጠና ወስደዋል
- የክብር ዲግሪ ከጸረ-ጦርነት ተሸላሚ ተነጠቀ
- በምዕራብ ትግራይ የተፈፀመውን ጭፍጨፋ ማስረጃ ማስወገድ
- የትግራይ ዩኒቨርሲቲዎች የባንክ አካውንቶች ተዘጉ
- የትግራይ ዩኒቨርሲቲዎች በጀት አልተለቀቀም
- የሰራተኞች ደሞዝ በምግብ እርዳታ ላይ የተመሰረተ ሆነ
- ለትግራይ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ምግብ የለም ተባሉ
- ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የትግራይ ተወላጆች ከግቢ ተባረሩ፤ የትም መሄድ አልቻሉም፤ የተወሰኑት ታስረዋል፣ሌሎች ተደብቀዋል
- በትግራይ የዩንቨርስቲ ግቢዎች የአየር ድብደባ ተፈጸመ
- የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ዝምታ ዋጠው

**<u>ከዩኒቨርሲቲዎች ለኢትዮጵያ መከላከያ የገንዘብ ድጋፍ</u>**

- የአውሮፓ ህብረት ለጤናና ትምህርት 81.5 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ ያደርጋል።
- የፌዴራል ዩንቨርስቲዎች ደግሞ 211 ሚሊዮን ብር ለኢትዮጵያ መከላከያ ድጋፍ ማድረጋቸውን በኩራት አስታወቁ

- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 60 ሚሊዮን
- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 50 ሚሊዮን
- ሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ 45 ሚሊዮን
- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 39 ሚሊዮን
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ 35 ሚሊዮን
- ዲላ ዩኒቨርሲቲ 30 ሚሊዮን
- አርሲ ዩኒቨርሲቲ 30 ሚሊዮን
- አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ 28 ሚሊዮን
- መቱ ዩኒቨርሲቲ 21 ሚሊዮን
- ሚዛን ቴጲ ዩኒቨርሲቲ 20 ሚሊዮን
- አዲስ አበባ ሳ.ቴ ዩኒቨርሲቲ 16 ሚል.
- ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ 15 ሚሊዮን
- አዳማ ሳ.ቴ ዩኒቨርሲቲ 11 ሚሊዮን
- ሰማራ ዩኒቨርሲቲ 3 ሚሊዮን
- ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 1.5 ሚሊዮን
- ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ 1.2 ሚሊዮን
- ጅጅጋ ዩኒቨርሲቲ 1 ሚሊዮን
- ወራቤ ዩኒቨርሲቲ 1 ሚሊዮን

**3. የኢትዮጵያ ባንኮች ለኢትዮጵያ መከላከያ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ**

- የኢትዮጵያ ባንኮች ማኅበር 200 ሚሊዮን ብር ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰጠ። (የኢትዮጵያ ሄራልድ 03 በታህሳስ 2013)
- ከ400 ሚሊዮን ብር በላይ ለኢትዮጵያ መከላከያ መሰጠቱን የኢትዮጵያ የባንክ ስራ አስፈፃሚዎች ተናግረዋል፤ የባንኮቹ ማንነት እንዳይገለጽም ተማጽነዋል፡፡ (ፋሲካ ታደሰና ሲሞን ማርክ ብሉምበርግ 13 ነሃሴ 2013)
- "ለተፈናቀሉ ዜጎች ሰብአዊ ድጋፍ" የሚውል በሚል ባንኮች 1. 23 ቢሊየን ብር ለግሰዋል። እርዳታ ካበረከቱት ባንኮች አዋሽ፣ ዳሸን፣ ሕብረት፣ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክና አቢሲኒያ ሲገኙበት ከስጦታው ውስጥ ግማሹን ያበረከተው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው። (አዲስ ፎርቹን 05 ህዳር 2013)
- ባንኮች በተፈጥሮ ሰላም ሲሆን ብቻ መንቀሳቀስ የሚችሉ የእድገት መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በትግራይ ጦርነት የታየው ግን የተገላቢጦሽ ነው፡፡ ባንኮች የከፈሉት ለሰላም ሳይሆን ለጦርነት ነበር፡፡ ይህ ጦርነት ከትግራይ ደምበኞቻቸው ጋር የነበረውን በህጋዊ ውል ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያፈረሰ፤ የደምበኞቻቸውን ህይወትና ገንዘብ ያሳጣ፤ የባንኮቹን ቅርንጫፎች አዘግቶ ባንኮችን ለኪሳራ የዳረገ፤ የባንኮች ገንዘብ እንዲዘረፍና

ህንጻዎቻቸውም እንዲጎዱ ያደረግ ነበር፡፡ ስማቸው ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ባንኮች ትግራይ ካሉት የባንክ ቅርንጫፎች 60 ከመቶውን የያዙ ናቸው፡፡

**3. ሌሎች የቢዝነስ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ መከላከያ ያደረጉት የገንዘብ ድጋፍ**
(አዲስ ፎርቹን 05 ህዳር 2013)

- ሚድሮክ ኢትዮጵያ 100 ሚሊዮን ብር
- የኮንስትራክሽን ተቋራጮች ማኅበር 100 ሚሊዮን ብር
- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን 50 ሚሊዮን ብር

## 5.3. የጦርነቱ አጋጋዮች (ታዋቂ ሰዎች፤ ፖለቲከኞች፤ አርቲስቶች)

የትግራይ ጦርነት ከዚህ በፊት ከነበሩት ጦርነቶች ልዩ የሚያደርገው ጦርነቱ የተካሄደው በጦር ሜዳ ብቻ አይደለም፤ ህይወት በማይጠፋበት ነገር ግን የበለጠ ህይወት እንዲጠፋ በሚቀሰቀስበት ሚድያ ጭምር እንጂ፡፡ ሚድያው ጎራ ለይቶ ሲራኮት የሚጠቀምባቸው ቃላት የህዝቡን ለዘመናት የኖረ የትስስርና የመከባበር የባህል እሴቶችን አውድሟል፡፡ በርካታ ምሁራን፤ የሃይማኖት መሪዎችና የስነጥበብ ባለሙያዎች በጦርነት ቅስቀሳ ላይ ተሰማርተው ነበር፡፡ የትምህርት፤ የሃይማኖትና የስነጥበብ መሰረቱና ግንቡ ሰላምና ልማት ነው፡፡ በትግራይ ጦርነት ይህ ጊዜ የማይሽረው መርሆ በጭንቅላቱ ቆሟል፡፡ ከሚሊኔሙ መባቻ ወዲህ የኢንተርኔት አግልግሎት መስፋፋት ፈጣን የመረጃ ስርጭትን ወደ ቢልዮኖች ለማድረስ እጅግ አመቺ አድርጎታል፡፡ ይህ ስርጭት ለእድገትና ልማት፤ ለመልካም አብሮነትና ለተደላደለ የህዝብ ህይወት መስፈን የሚያመቻች ሲሆን ምርቃት ነው፡፡ ይህ የአለም መገናኛ መረብ ባመዛኙ እየዋለ ያለው ግን ግጭትን ለመፍጠር፡ ለማባባስና ለማራዘም ነው፡፡

የትግራይ ጦርነት ለዚህ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው፡፡ ቁጥር ስፍር የሌለው ተከታይና ተመልካች ያላቸው ግዙፍ ሚድያዎች የጥላቻ ይዘታቸውንና ቅስቀሳቸውን በአጭር ጊዜ ለምን ብለው ለማይጠይቁት ተመልካቾቻቸው አድርሰው ስሜትን በመቀስቀስ ለጭፍን እርምጃ ያመቻቻሉ፡፡ ወረራን ለማስቻል ሲተጉ የነበሩት ሚድያዎች ከነተከታዮቻቸው፡- የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖራሽን (1.3 ሚልዮን)፤ ፋና ቴሌቪዥን (1.23 ሚልዮን)፤ ኢትዮ360 (576 ሺ)፤ አማራ ሚድያ (630 ሺ)፤ ዋልታ (282 ሺ)፤ ኢሳት (642 ሺ)፤ ኤሪቲቪ (477 ሺ)፡፡ ጎላ

ኅላ ያሉት ተጠቀሱ እንጂ በዚህ ተግባር ላይ ተሰማርተው የከረሙት ጦረኛ ሚድያዎች ለቁጥር የሚያታክቱ ናቸው፡፡ ቀደም ብለው ከተዘረዘሩት የጥላቻ ሚድያ ጋዜጠኞች ጋር ከላይ የተዘረዘሩት ሚድያዎች በትብብር የጥላቻና የጦርነት ቅስቀሳ መልእክቶቻቸውን ሲይሳተላልፉ የነበሩት ደግሞ ምሁራን፤ የሃይማኖት መሪዎች፤ የስነጥበብ ሰዎችና የታጠቁ ሃይሎች መሪዎች ናቸው፡፡

“በኢትዮጵያ መንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ ሚዲያዎችና በኋላም በማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ በወቅቱ በኢትዮጵያ የፌደሬሽን አካል ላይ የትጥቅ ጥቃት ሲፈጽሙ ለነበሩት ወታደራዊ ሃይሎች ድጋፋቸውን በሚገልጹ በካህናት፣ በፓስተሮች፣ በሼኮችና በታዋቂ ሰዎች ስዕሎች ተጥለቅልቀዋል፡፡”

ሜሮን ቲ. ገብረአናንያ፤ ትግሃት፤ እ.ኤ.አ. 14 የካቲት፣ 2021

የውሸት ወሬዎች እንደ ዘጋቢ ፊልም ተለቀቁ፡- “የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬሽን፣ ዋልታና ፋና “የፍትህ ሰቆቃ” የሚል ርእስ አቀጣጣይ የሆነ ዘጋቢ ፊልም አቅርበዋል፤በጥሬ ትርጉሙ የፍትህ ስቃይ ማለት ነው፡፡ በአዲስ አበባ እስር ቤቶች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ከእስር ቤት አስተዳዳሪዎች መካከል በትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ እንደተፈጸመ ይተርካል፡፡”

በኢዮብ ታደሌ ገብረሂወት ትግሃት እ.ኤ.አ. 22 ሰኔ ፣ 2022

1. <u>ዲያቆን ዳንኤል ክብረት (የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማህበራዊ ጉዳይ አማካሪ)</u>



“ወያኔ (የትግራይ ህዝብ ለማለት) ልንረዳው የምንችለው ነገር አይደለም፤፤ ማጥፋት ብቻ ነው የምንችለው፡፡ ለምሳሌ በደቡባዊ አውስትራሊያ የምትገኝ ታዝማኒያ የምትባል ደሴት አንድ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ የታዝማኒያ ነገዶችን አወደሙ፤ አንድ ሰው ብቻ! ሙሉ በሙሉ አጥፍቷቸዋል፡፡ በማጥፋት ብቻ ነው ቀደም ብዬ እንዳልኩት ወያኔነት የተባለውን በሽታ በማጥፋት ብቻ ነው፡፡ በመጀመሪያ በአካል በሁለተኛ ደረጃ በሀሳብ ወያኔነት በፍፁም ሊኖር አይገባም፤ በሃሳብ መልክ እንኳን፡፡ ሰዎች “ወያኔ” ካሉ ሌላው ሰው “በስመ አብ” ማለት አለበት! ሁሉም ሰው! (ጭብጨባ)፡፡ በጭራሽ! ለልጆቻችን መንገር ያለብን ይህ ነው! ወያኔ ይህን ያደረጉት

በዚህ’ ምክንያት ነው ማለት የለብንም፡፡ ኢትዮጵያን በከፋ መልኩ ያጠቃው ወያኔ የሚባል በሽታ ስላለ ስሙ ቢጠቀስም እንኳ “በስመ አብ” በሉና ከእሱ ራቁ፡፡ ስሙ በተጠቀሰበት ቦታ የትም አትሂዱ፡፡ ስለ እሱ የተጻፈ መጽሐፍ አታንቡ፡፡ ስለ እሱ የተጻፈውን ምስል አትመልከቱ፡፡ ፎቶውን አትዩ፤ በጭራሽ! ይለከፋችኋል፤ ሳታውቁት በውስጣችሁ ይሰራጫል፡፡ ስለዚህ ከሱ ራቁ፡፡ ሦስተኛው ከታሪክ ነው፡ በማንኛውም ሁኔታ ታሪኩ መቀጠልና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቦታ ሊኖረው አይገባም፡፡ በቂ ነበረው፤ ከአሁን ጀምሮ ታሪክ ሊኖረው አይገባም፡፡ በማንኛውም ሁኔታ! ወደፊት ሀገሪቱ ስትለወጥ ነገሮች ሲመጡ እንዲታወስ የሚያደርጉ ምልክቶች ሁሉ እንዳይኖሩ መደረግ አለባቸው፡፡ ያቆማቸው ሃውልቶች፤ የሰጣቸው ስሞች የሰየሟቸው፣ የሚታወሱት በፍፁም እንዳናስታውሰው፡፡

<u>ይህን የዘር ማጥፋት ቅስቀሳ የአሜሪካ መንግስት አውግዟል</u>፡-

“የጥላቻ ንግግሮች አደገኛና ተቀባይነት የሌላቸው ናቸው፡፡ የዳንኤል አስተያየት በእውነት የሚረብሽና ግድየለሽነት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ እየደረሰ ያለውን ገዳይ የኃሳ ጥቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት በአጠቃላይ ከትግራይ ተወላጆች ይልቅ ስለ ህወሓት ብቻ ነው የተናገረው የሚለው አባባል ዋጋ ሊሰጠው አይችልም።”

<u>ቦርከና እ.ኤ.አ. 23 መስከረም 2021 ለአሜሪካ ተቃውሞ መልስ ሰጠ፡-</u>

“የባይደን አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንደሚጥል ከተገለጸ ከአንድ ሳምንት በኋላ አሜሪካ በዳንኤል ክብረት ላይ እያነጣጠረች ነው፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ መግባቷን አንድ እርምጃ የወሰደች ይመስላል፡፡ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ለትግራይ አማፂያን ያላቸው አመለካከት ከዳንኤል ክብረት የተለየ አይደለም፤ እንዲያውም የበለጠ ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ አሜሪካ በዳንኤል ክብረት ላይ የሰነዘረችው ትችት በኢትዮጵያውያን ላይ ቁጣ ቀስቅሷል፡፡ በማህበራዊ፣ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የጻፈውን ጽሁፍ ከፍ አድርገው የሚመለከቱት የአሜሪካን ትችት ተገቢ እንዳልሆነ አድርገው ይመለከቱታል።”

## 2. <u>አንዳርጋቸው ጽጌ በወታደራዊ ዩኒፎርም</u> <u>(ቴሌግራፍ እ.ኤ.አ. 28 ህዳር 2021)</u>

ጦር ግንባር ለነበሩ ወታደሮች ያደረጉት ንግግር

“እየነገርኳችሁ ነው! የትግራይ ሃይሎች ሲገጥሟችሁ በጣም አረመኔያዊ የሆነ የጭካኔ ድርጊቶችን ከመፈጸም ወደ ኋላ ማለት የለባችሁም፤ ምህረት የለሽ መሆን አለባችሁ፤ የአማራ ወይም የኢትዮጵያ ባህላዊ እሴቶቻችን ከሚፈቅዱት በላይ እርምጃ መውሰድ አለባችሁ”

**3. <u>የአርቲስት አብራር አብዶ በመንግስት ቴሌቪዥን የተላለፈ ንግግር (ከቪድዮ)</u>፦**

“በውስጤ ታምሜአለሁ! ማውራት የማልፈልጋቸው ብዙ ነገሮች አሉኝ፤ ምንድን ነው? እነሱ (የትግራይ ሃይሎች) ሊያጠፉን ሲመጡ፤ ኢትዮጵያን ሊያወድሙ ሲመጡ ሁለት አማራጮች አሏቸው አንደኛው እኛን መግደልና ኢትዮጵያን ማጥፋት ነው፡፡ ሁለተኛው ከተሸነፉ እጃቸውን ይሰጡና እንመግባቸዋለን፡፡ የኛዎቹ ወታደሮች እጃቸውን ሲሰጡ እነሱ (የትግራይ ሃይሎች) ዩኒፎርማቸውን ቀምተው ራቁት አስቀርተው ይቅርታ ያደርጉላቸዋል፡፡ ቪዲዮ አንስተው የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚገድሉት በዚህ መንገድ እንደሆነ ለአለም ይነግሩታል፡፡ እንዴት እናዝንላቸዋለን? እንደ ኢትዮጵያውያን እንደ ወገኖቻችን ደጋግመን የምንቀጥራቸው እንዴት ነው? ይህ ፈጽሞ መሆን የለበትም! አይደሉም! የሚፈልጉት ኢትዮጵያን ማውደምና ኢትዮጵያን ማጥፋት ነው፡፡ከእነሱ ጋር የሚተባበሩ አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ስትፈርስ የተወሰነ ቁራጭ እየጠበቀ ያለ ቡድን አለ፡፡ በጉዳዩ ላይ ወዲያና ወዲህ መሄድ ያለብን ነገር የለም፡፡ አንድ አማራጭ ብቻ አለን፤ ለኢትዮጵያ መሞት!”

**4. <u>አርቲስት ቺሮታው ከልካይ በመንግስት ቴሌቪዥን የተላለፈ ንግግር (ከቪድዮ)</u>፦**

“እነዚህ (የትግራይ ሃይሎች) አብያተ ክርስቲያናትንና መነኮሳትን ያረከሱ ሰዎች ናቸው፡፡ በአብያተ ክርስቲያናት መቅደስ ውስጥ ሰዎችን ይጨፈጭፋሉ፡፡ ይህችን ሀገር ማጥፋት ማለት እሴቶቹንና ወጎችን ጨምሮ ያለውን ሁሉ ማጥፋት ማለት ነው፡፡ እነዚህ የራሳችን ሰዎች እንዴት ሊሆኑ ይችላሉ? ጭንቅላት የሚረብሽ ነው፡፡ ለምን እናዝንላቸዋለን? ምንስ እየጠበቅን ነው? ወደዚህ መጥተው እስኪገድሉን ድረስ? ሰብአዊነት የለም! እኔ እንደማስበው ሰይጣን በቅናት ሳይበግን አይቀርም፡፡ ሰይጣን እነሱ (የትግራይ ሃይሎች) እንደበለጡት ሳይሰማው አይቀርም፡፡ እነዚህ እንዲህ አይነት ሰዎች ናቸው፡፡ እዚያ ያለው እሳት (ጦርነት ሜዳ) እዚህም ሊቃጠል ይችላል፡፡ ጎረቤቴ ጥልፍ ሠሪ ነበር፡፡ ከኛ ጋር እንደ ወንድማችን ሆኖ ተራ ህይወት ኖረ፡፡ ቤቱ ሲፈተሽ የተገኘው ብታይ ጭንቅላትህን ይዘህ ትጮህ ነበር፡፡ ባከማቸው ሁሉ መግደል የፈለገው ማንን ነበር? ቀኝ እግራችን ግራችንን እየገደለ ከሆነ እንዴት መኖር እንችላለን? ስለዚህ ከአገር በፊት ምንም ነገር አይመጣም፡፡ በኃጢአት የተበከለ አየር እየተነፈስን ነው፡፡ ምርኮኞቻቸውን እናስተናግዳለን፣ እንመግባቸዋለን፣ አልጋ፣ ብርድ ልብስና አንሶላ እናቀርባቸዋለን፡፡ ነገር ግን የእኛ የጦር ሃይሎች ተግፈው፤ ታርደው፤ ለጅቦችና ለሌሎች የዱር አራዊት ሜዳ ላይ ይጣላሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ኢሰብአዊነት ሰምተን አናውቅም፡፡”

**5. <u>አርቲስት ደበበ እሸቱ በመንግስት ቴሌቪዥን የተላለፈ ንግግር (ከቪድዮ)</u>፦**

“እነሱ (ትግራይ) እየተቃጠሉ ነው፣ አላዝላንቸውም፣ ይቃጠሉ፣ ይገባቸዋል.”

6. <u>ወርቁ አይተነው (ከበርቴ) </u>በወታደሮች ማሰልጠኛ ያደረጉት ንግግር (ከቪድዮ)፡-



“እነሱ (ትግራይ) ባንዳ (ከዳተኞች) ናቸው! የጣሊያን ወታደሮችን እየመሩ ወደ አማራ ምድር ሄደዋል፡፡ ከ12 እስከ 60 ዓመት የሆናቸው ቀጥረው እየወረሩን ነው፤ በብዛት እየመጡ ነው፤ አማራን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ተስለዋል፡፡ ታዲያ መኖር እንፈልጋለን ወይስ አንፈልግም?”

7. <u>መስፍን ተስፉ (የፋኖ አዛዥ) ትግራይ አፐዴት እ.ኤ.አ. ነሓሴ 26፣ 2021</u>፡-

“እኔ ብቻ ሳልሆን ታውቃላችሁ፣ እሷ (ትግራይ) ምንም አቅም እንደሌላት፡፡ እኛ አቅሟ ነን፣ እኛ አሰልጣኞቿ ነን፣ ዘዴ እናስተምራታለን። እኛም እንመግባታለን፤ አለበለዚያ እሷ ምንም አቅም የላትም፡፡ እሷ በተግባሯ መጥፎ ነች፣ የሰይጣን ሴት ልጅና የሰይጣናት ዘር።”

8. <u>ክርስትያን ታደለ (የአማራ ፓርቲ አመራር) ያደረጉት ንግግር (ከቪድዮ)</u>፡-

“ከፊት ለፊታችን የቆመው ጠላት (የትግራይ ሃይል) ጉንፋን፣ የተለመደ ጉንፋን ብቻ ነው፤ ከጉንፋንም ያነሰ ነው፤ የተዳከመ ሊጥ ደፊ ነው፤ እንደ ውሻ በአካባቢው ይንከራተታል እናም ሊጡን ያፈሳል፡፡ እነዚህን ዱርየዎች እነዚህን ውሾች ማሳደድ የናንተ ግዴታ ነው፡፡ እውነት ነው! ሊጥ የሚደፋ ውሻ የሶስት ወይም የአራት አመት ልጅም ቢሆን ሊያሳድደው ይችላል፡፡”

9. <u>እስክንድር ነጋ (ኢዮብ ታደለ ገብረሂወት ትግሃት እ.ኤ.አ. 22 ሰኔ፣ 2022)</u>

“ሽፍቶቹ (ትግራይ) እንዴት በወታደራዊ ኃይል አሸንፈው ስልጣን ያዙ? የታጠቀው ሰራዊታችን ለመሐላው ታማኝ ባለመሆኑ በአሁኑ ጊዜ እየገዙን ያሉትን ተኩላዎች ከምድር ገጽ ማጥፋት አልተቻለም፡፡ በእርግጠኝነት የሚቻል ነበር፡፡ ከታሪክ ምን መማር እንችላለን? ምን ተምረናል? በናዚ ቆራጥ አመራር በዝባዥ አይሁዶች ላይ ወሳኝ አቋም የወሰዱት የጀርመን ሕዝብ ጀግንነታቸውን በተግባር አሳይተዋል፡፡ ይህ ለእውነተኛ ኢትዮጵያውያን ምን ይነግረናል? ትምህርቱ ለእኛ ምንድን ነው?”

10. <u>ሃይሌ ገብረሰላሴና ፈይሳ ሌሊሳ ቢቢሲ እ.ኤ.አ 22. ህዳር፣ 2022)</u>

“ኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ጀግኖች ኃይለ ገብረስላሴና ፈይሳ ሌሊሳ ከአማፂ ሃይሎች ጋር በሚደረገው ጦርነት ወደ ጦር ግንባር ለመሄድ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል፤

ቀደም ሲል ኃይለ ገብረስላሴ ወደ ጦር ግንባር መሄድን ጨምሮ የሚፈለገውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነኝ ብሏል. ሌሊሳ ፌይሳ የአባቶቹን ገድል መነሻ በማድረግ ሀገሩን ለማዳን ወደ ጦር ግንባር ለመሄድ ዝግጁ መሆኑን ተናግሯል።"
ፕሮፌሰር ቲላሁን ይልማ

**11. <u>ፕሮፌሰር ጥላሁን ይልማ (ከቪድዮ)</u>፡-**

"አንድ የካንሰር ሕዋስ እንኳን በህይወት ቢቀር ሰዎችን ሊገድል ይችላል፡፡ ወያኔ (ትግራይ) ካንሰር ነው፡፡. ልክ አሳ ሲበላ እያንዳንዷን አጥንት እየለየን እንደምናወጣ አንድም ወያኔ እንዳይቀር አድርገን የምናስወግድበትን ፕሮግራም መንደፍ አለብን"

**12. <u>መሳይ መኮነን ኢሳት ቲቪ (ኢዮብ ታደለ፤ ትግሃት እ.ኤ.አ. 22 ሰኔ፣ 2022</u>**

"የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይ ህዝብ ቢያንስ ገለልተኝነቱን እንዲያሳይ (ቡድኑን ከመደገፍ እንዲቆጠብ) በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥሪ አቅርቧል, ግን ምንም ጥቅም የለውም፡፡ እነሱ (ትግራውያን) ሞክረው አያውቁም፤ ይባስ ብለውም የነሱ መንፈሳዊ ልጆች መሆናቸውን አጥብቀው በመንገር የስነ ልቦና ጦርነት ያካሂዳሉ፤ ይስቃሉ፤ ያፌዙብናል፤ በምላሹ ያገኘነው ውርደትና እልቂት ብቻ ነው፡፡"

**13. <u>መሳይ መኮነን ኢሳት ቲቪ (ኢዮብ ታደለ፤ ትግሃት እ.ኤ.አ. 22 ሰኔ፣ 2022</u>**

"ለኢትዮጵያ ህዝብ አስቸኳይ ጥሪ፡- ትግላችን በመላው አለም እንደተለመደው ጨቋኝ መንግስት እየተባለ በሚጠራውና በተጨቆኑ ህዝቦች መካከል የሚደረግ ትግል አይደለም፡፡ አንድ ጎሳ (ተጋሩ) ሌሎችን ለመግዛትና በማያቋርጥ ጭንቀት ውስጥ ያለውን የኢትዮጵያን ህዝብ በማጥፋት የበላይ ሆኖ መቀጠል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ምን እየጠበቅን ነው? አንድ በአንድ እስኪጨርሱን ነወይ የምንጠብቀው? ከእንግዲህ መፍትሄን በውይይት ለማግኘት ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ወደድንም ጠላንም ያለው አንድ አማራጭ ብቻ ነው፡፡ በራሳቸው ሳንቲም ሊከፈላቸው ይገባል፤ ነጻነታችንም ለማስመለስ ሃይል መጠቀም፡፡ የበሰበሱ ዓሦችን ለማስወገድ አንዱ መንገድ ባሕሩን ማፍሰስ ነው፡፡"

**14. <u>አገኘሁ ተሻገር የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት (ከቪድዮ)</u>፡-**

"ጠላት (ትግራይ) እስኪወገድ ድረስ ማረፍ አንችልም፡፡ ይህ ህዝብ የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት ነው፤ የኦሮሞዎች ጠላት፤ የአፋር ጠላት፤ የጋምቤላ ጠላት፤ የሶማሌ ጠላት ነው፡፡"

**15. <u>ትንግርቱ ገብረጻዲቅ (የማህበረ ሰብ ጥናት ረዳት ፕሮፌሰር በአማራ ሚድያ)</u>**

"አሁን አስቀደመን ንቁ ሆነን መጪዎቹ ሺ አመታትን ለመቅረጽ ይህን የትግራይ ትውልድ አሸንፈን በቋሚነት ማዳከም፤ እስከመቼም ለሃገራችንና ለህዝባችን አደጋ እንዳይሆን ለማድረግ ማህበራዊ ምህንድስናን መስራት፡፡ ይህን አደገኛ ማህበረሰብ ለማሸነፍ ብዙ ስራ መስራት ይኖርበታል፤ እጅግ ብዙ ስራ! ትግራይ የሚለውን ስም ራሱ ልናስብበት ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- የናይጅሪያ መንግስት "ቢያፍራ" የሚል የግዛት ስያሜ በህግ አግዷል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ስሙን (የትግራይን) ወንጀል ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ካወደሙ በኋላ ይህን ስም እንደጣኦት ማየት የለብንም፡፡ ስሙን ብቻ ሳይሆን አስተዳደሩንም እንደገና የማካለል ጉዳይ መልሰን ማየት ይኖርብናል፡፡ ይህን የወንጀል ማህበር ለማጥፋት ትግራይ ወደ አራት ወይም አምስት ከልል ወይም ዞን ልትከፋፈል ትችላለች፡፡"

**16. <u>ጀናይ ገብረ ገርጊሽ (የህግደፍ ረዮተ አለም ጉሩ) እ.ኤ.አ. 3 ጥቅምት ፣ 2020</u>**

በሃየት አለም፤ ትግሃት 29 ታህሳስ፣ 2021፤ የዚህ መጽሃፍ ደራሲ እንዳሳጠረውና መልሶ እንደጻፈው፡- <u>"የመጨረሻ መፍትሄ ለትግራይ ችግር"</u>

"ለኤሪትርያውያን ኤሪትርያን እንዴት ኃያል ማድረግ እንደሚቻል ከማሰብ የበለጠ ሌላ ምንም አስፈላጊ ነገር የለም፡፡ በትግራይ ህዝብና በኤሪትርያ መካከል ዘላቂ ሰላም እንዲኖር ትግራይ የሚባል ክልል መኖር የለበትም፡፡ ስነ ምግባርና ሰብአዊነት ከብሔራዊ ጥቅም አንጻር እርባና ቢስ ናቸው፡፡ ባለፉት 500 ዓመታት ኤሪትርያ ኃያል ሀገር እንዳትሆን ሲከዳ፣ ሲያጠቃ ሲያደናቅፍ የነበረው የትግራይ ህዝብ ነው፡፡ ኢትዮጵያና ኤሪትርያ ቢታረቁ እንኳ ትግራይ ሁሌም ጸረ-ኤሪትርያ እንደሆነች ትቀጥላለች፡፡ በጊዜ ሂደት እነዚህ ራሳቸውን በትግራዋይነት የሚመድቡት ኤሪትርያውያን የአቢሲኒያ ወይም የትግራይ አስተሳሰብ እያንጸባረቁ ጸረ-ኤሪትርያ ማንነት ያዳብራሉ፡፡ ህወሓት እንጂ ህዝብ ጠላታችን አይደለም ልንል እንችላለን። ነገር ግን ህወሓት ቢጠፋም በትግራይ ሌላ ፀረ-ኤሪትርያ ድርጅት ይኖራል፡፡ ስለዚህ ከህወሓት በኋላ ከቅዱስ አቡነ አረጋዊ የሃይማኖት ማኅበር አይነት አነስተኛ የፖለቲካ መዋቅር የበለጠ መፈጠር የለበትም፡፡ ኤሪትርያ በየስድስት ወሩ ተከታትላ እንደ ያልተፈለገ እርግዝና ማስወረድ አለባት፡፡"

"ትግራይ ከኤሪትርያ ጋር ሰላም ቢፈጠርም የትግራይ ተወላጆች በወደቦች መቅናታቸው አይቀርም፡፡ ትግራይ ለመኖሪያ የማትሆን፤ ደረቅ፤ ለእርሻ የማትመችና የተገገለች አካባቢ ናት፡፡ ከሌሎች ጋር ተጠግተው ካልሆነ ለብቻ ማደግና መበልጸግ አይችሉም፤ ይህም ወደ ኤሪትርያ ይገፋፋቸዋል፡፡ ትግራይ ባላት ውስን ሃብት ከአንድ ሚሊየን በላይ ህዝብ ማስተናገድ አትችልም፡፡ በሁሉም መለኪያ የትግራይ ክልል ለትግራይ ህዝብ አትሆንም፡፡ ባህላቸው ተመርዟል. የራሳቸው ያልሆነ ነገር እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ትግራይ እንደዚሁ ከቀጠለች ጥንታዊ ታሪካችንን ለመዝረፍ፣ ባህላችንንና ቋንቋችንን ለመበረዝ እንቅልፍ የሚነፍጉን ሰርጎ ገቦችን

ይልካሉ፡፡ ለተባለው ሁሉ ታሪክ ምስክራችን ነው፡፡ ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ የትግራይ ተወላጆች በአያቶቻችን ላይ እንዳደረጉት በአዲሱ ትውልድም ላይ ሁሉንም ነገር አድርገዋል፡፡ ከዚህ አይነት የጥላቻ ጎረቤት ጋር ለ500 አመታት ተዋግተናል፤ ሁሌም ጀርባህን ሳታይ በሰላም መኖር አትችልም፡፡”

“መፍትሄው ለትግራይ ህዝብም ጠቃሚ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ በቫይታሚን እጥረት ፊታቸው የቆሸሸ ጨርቅ መስሎ በእርዳታ ላይ ጥገኛ ከመሆን የተሻለ ኑሮ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እንደ አኹሱም ያሉ ታሪካዊ ቦታዎችን ለመጠበቅ ጥቂት ሰዎች ሲኖሩ ቀሪው አምስት ሚሊዮን ሰዎች ወደ ኢትዮጵያና ወደ የመን መገፋት አለባቸው፡፡ ከኢትዮጵያና ከየመን ሙሉ በሙሉ ለመዋሃድ 150 አመታት ይወስዳል፡፡ እስከዚያ ድረስ ኤሪትርያ የፖለቲካ ተጽእኖዋን ማስፋት ትችላለች፡፡ ያኔ የትግራይ ተወላጆች በየመን አዲስ ስልጣኔ መጀመር ከቻሉ ከእኛ ጋር መተባበር ይችላሉ፡፡ ከትግራይ ሊፈጠር የሚችለው ስጋት ከተወገደ በኋላ የኤሪትርያን ማንነትና ብሄርተኝነት በማጠናከር ከ100 ዓመታት በፊት በቀይ ባህር ላይ ወደነበረን ክብርና ተጽእኖ ፈጣሪነት ሊመልሰን የአዲሱ ትውልድ የቤት ስራ ይሆናል፡፡ እኛ በእርግጥ ትኩረት እየሰጠን ከሆነ አባቶቻችን በአፍሪካ ቀንድ ዙፋናችንን እየሰጡን ነው፡፡

የግዛቱ መቀመጫም ከአስመራ ወደ ቀድሞ የዙፋን መቀመጫ ዱባርዋ (አዲ-ሃሎ) እየተዘዋወረ ነው፡፡ የሚቀረው የአረብ ባህረ ሰላጤውን የበላይነት መልሶ መውሰድ ብቻ ነው፡፡ ለኤሪትርያ ማንነት ጠንቅ የሆነውን ትግራይን በትክክል ለመምታት በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ክልሎች ወደ ትናንሽ ዞኖች በማፍረስ የኢትዮጵያዊነትን ማንነት ማጠናከር አለብን፡፡ ትግራይን በታትኖና ወደ ተለያዩ ክልሎች አስገብቶ ማሟሟት፡፡ ኤሪትርያን ከትግራይ ተጽእኖ ለመከላከል በትግራይና በኤሪትርያ ድንበር ላይ የመከለያ ቀጣና በመፍጠር የማህበራዊ ምህንድስና መፍትሄን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ተራ ጂኦግራፊያዊ ድንበር በቂ አይደለም፤ ማህበረ-ባህላዊ ወሰን የግድ ነው፡፡ በትግራይና በኤሪትርያ አዋሳኝ አካባቢዎች ሌሎች የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ያልሆኑትን ማስፈር እንችላለን፡፡”

## 5.3. የጦርነቱ አነሳሾች

በኢትዮጵያ የ2018ቱን ለውጥ በሚመለከት ሁለት ጽንፍ የረገጡ ግን ደግሞ የአንድ ሳንቲም ሁለቱ ገጽታዎች ሆነው በአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ የሰፈሩ አቋሞች ነበሩ፡፡ አንደኛው ህወሓትን ከነህዝባዊ መሰረቷ መጥፋት አለባት የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አቢይ አህመድ ለሶስት አስርት አመታት ሰፍኖ የቆየውን “መከራና ስቃይ” ለማስወገድ የሰማዩ ጌታ ያወረደው መልእክተኛ ነው ብሎ ማምን ነበር፡፡ በመጀመሪያው ገጽታ ላይ የሁሉም ስምምነት ነበር፡፡

በአቢይ አህመድን መሲህነት ከልብ አምነውበት ያንጸባረቁ እነማን ነበሩ? ጠቅላይ ሚኒስትሩን በውዳሴ አሟሙቀው አጀንዳቸውን እንዲፈጽሙላቸው የተወኑትስ እነማን ነበሩ?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በነበራት/ባላት ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ አቅም በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ብዙም የመስፋፋት እድል አላገኘም ነበር፤ በደቡባዊ ኢትዮጵያ ካልሆነ በስተቀር፡፡ የፕሮቴስታንት አንዱ ዘርፍ የሆነው የብልጽግና ወንጌል ተከታይ የሆኑት አቢይ አህመድ የአገሪቱ መሪ ሲሆኑ ፕሮቴስታንቶች ከሰማይ የወረደ ነው ብለው ቢሉ ሲያንስ እንጂ አይበዛም፡፡ ይህ ክስተት በርካታ አዳዲስ አባላት ለማፍራት ባያስችላቸውም አቢይ አህመድ ሳይተኩ ለዘለቄታው አመራር ላይ እንዲቆዩና መጪዎቹ ዘመናት ለሃይማኖታቸው መስፋፋት አመቺ ሁኔታን እንዲፈጥሩ መመኘታቸው አልቀረም፤ የመጀመሪያው ፕሮቴስታንት የኢትዮጵያ ንጉስ በማድረግ፡፡ ነጉስ ኖሮ ያወርሳል እንጂ በምርጫ አይተካም፤ በህዝብ ሳይሆን "በእግዚአብሄር የተቀባ" ስለሆነ፡፡ ከግማሽ ምእተ አመት በኋላ ዘውድ ተመልሶ ሰው ራስ ላይ ሊደፋ ከሆነ ህዝብን ማሳመን ሊያስፈልግ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከራሳቸው ከአቢይ አህመድ ጀምሮ "የፈጣሪ መልክተኛነት" ትርክት በተገኘው የሚድያ አጋጣሚ የሚሰበከው፡፡ ዶር. አቢይ አህመድ የተቀቡ መሆናቸውን ራሳቸው ተናግረዋል፡-

"ከሃያ ዓመታት በፊት በወቅቱ ከማውቃቸው ሰዎች ጋር ፎቶ ከመነሳት እቆጠብ ነበር፡፡ እኔ ከነናቸው ሆኜ የተነሱት ፎቶ ከያዙ ንጉስ ስሆን ከዚህ ቀደም ከእኔ ጋር አብረው እንደነበሩ እየኩራሩ ፎቶውን ለሌሎች ያሳያሉ ብየ እፈራለሁ፡፡ በባድሜ ጦርነት ወቅት ለሳሞራ ንጉሥ ስሆን እንዴት መሆን እንዳለበት እየነገርኩት ነበር፡፡ በመጀመሪያ ሰዎች እየቀለድኩ ነው ብለው ያስቡ ነበርና ከቁም ነገር አልወሰዱኝም፡፡

የአቢይ አህመድ የላይ መልክተኛ መሆን ስልጣን ከመልቀቃቸው ጋር አያይዘው የገለጹት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪአም ደሳለኝ ናቸው፡፡ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የሆኑት ሃይለማሪያም ደሳለኝ እንዲህ አሉ፡-

"እግዚአብሔር ለውጥን ማስተዋወቅ ሲፈልግ በራሱ ከሰማይ አይወርድም በሰዎች በኩል ያደርገዋል፡፡ ለውጡን እንዲመሩ እግዚአብሔር ጠቅላይ ሚኒስትራችንን እንደመረጠ ገና ከጅምሩ አውቅ ነበር፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር እንደሚሆኑ ብቻ ሳይሆን በሱ መመረጣቸውን አውቅ ነበር፡፡"

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስም ለዚህ አባባል ድጋፍ ሰጥተዋል፡

ኤጲስ ቆጶስ ገብረ ጊዮርጊስ፡- "በጌታ የተላከ ነቢይ አድርገን እንቆጥረዋለን፡፡ በጣም የበለጸገ ቋንቋ አለው፡- ስለ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ውይይትና ጦርነት ማስወገድ አስፈላጊነት ይናገራል፡፡ በእሱ አስተያየት የጦር መሳሪያዎች መጠቀም ሁልጊዜ ሽንፈት ነው፡፡"

የአምላክ መልእክተኛ ነው ከተባለ ለሱ የማይገዛ፤ እሱን የሚቃወም ሁሉ ከአምላክ የተጣላ ሊሆን ነው፡፡ ለሱ የማይታዘዝ ሃጥያተኛ፤ ሰይጣንም ነው! ስለዚህ የሚቀናቀነው መጥፋት አለበት፡፡ በገዛ ተግባሯም፤ እንዳለመታደለም ሆኖ በዚህ የሃይማኖትና ፖለቲካ ጥልፍልፍ ትርክት ውስጥ የተጠለፈችው ህወሓት ናት፤ የአቢይ ነቢይ ብቸኛ ጠንካራ ተቀናቃኝ፡፡ ለዚህ ነበር እልፍ አእላፍ መንጋጋ ጥርስ ውስጥ የገባቿው፤ ለዚህ ነበር ከሰማይ እንደተወረወሩ ያመጹ መላእክት የተቆጠረችው፡፡ በአቢይና ህወሓት መካረር የትግራይ ጦርነት ሲጀመር ብርቱ ድጋፋቸውን ከሰጡት የሃይማኖት መሪዎች አንዱ የፕሮቴስታንት ፓስተር በቀለ ወልደ ኪዳን ነበሩ፡-

"ፍትሃዊ አይደለም፡፡ ቀደም ብለን እንደተናገርነው ጠላት የመጣው በኢፍትሃዊነት ነው፡፡ አምላክ የሚለው ይህንን አይደለም፡፡ እሱ የሚለው እነሱ (ትግራይ) ፍርዴ ናቸው፡- ጦርነት፤ ረሃብ፤ ጨነፈር፤ እና የዱር አራዊት፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ከ2016 በአለም ላይ ተከስተዋል፡፡ እኛ የምንለው የኛ ፍትሃዊ ነው፤ ጦርነታችን ፍትሃዊ ነው፡፡ በኢፍትሃዊነት የመጣብን ጠላት አለ፡፡ ወጥተን ለፍትህ እየተዋጋን ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ተገደናል፤ ወደዚህ ተጎትተን ገብተናል፡፡ ፍላጎታችን አይደለም፤ አማራጮችን ስለጨረስን ነው፡፡ ሰዎች ሁሉ ገርሟቸው ይታዘቡን ነበር፡፡ የራሳቹን ሰዎች ዋጋ እንደሌለን ቆጠሩን፤ ሰደቡን፤ አዋረዱን፡፡ ለዚህ ሁሉ ታግሰን ቆየን፡፡ ሁሉም የሚጠይቀን ለምን ድፍረትን እንደፈቀድን ነበር፡፡ እኛ ለፍትህ ነን፤ እንዲህ መሆናችን አምላክ ደስ ይለዋል፡፡ አምላክ ከጎናችን እንደሆነ እናምናለን፡፡"

ዶር. አቢይ አህመድን ወደ ስልጣን ለማብቃት የአማራ ልሂቃን ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡ ይህን ያደረጉት ጸረ-ህወሓቱን ትግል በግንባር ቀደምትነት የመራው የኦሮሞው ኦህዴድ በመሆኑ ከሱ እጅ ፈልቅቆ ስልጣን ለራስ ማድረግ "ከአንበሳ መንጋጋ..." ስለሆነባቸው የፖለቲካ ባህላቸው የሆነውን "ተመሳስሎ በትእግስት መጠበቅ"ን መርጠዋል፡፡ የፈለጉትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ "በሬን በቀንዱ" የማይታገሉት የአማራ ልሂቃን "መጀመሪያ የመቀመጫየን" እንዳለቺው ፍጡር በቅድሚያ ከኦህዴድ በቁጥር ያነሰች ግን ከነሱ በላይ በልምድ የፈረጠመችውን ህወሓትን ማጥፋት ወይም እንዳትነሳ አድርጎ ማዳከምን መረጡ፡፡ ለዚህም አላማ ከኦህዴድ ጋር ስር-አልባ የሆነ "የጋራ ስጋት" ግንባር (ኦሮማራ) ፈጠሩ፡፡

በኦህዴድና በአማራ/ብአዴን የተመሰረተው ጸረ-ህወሓት ህብረት ባመዛኙ የአማራ/ብአዴንን ግቦች ለማሳካት የቆመ እንጂ ኦህዴድ ከህወሓት ጋር ይህን ያህል ለጦርነት የሚያዳርስ ቅራኔ አልነበረውም፡፡ በፌደራሊዝምና በህገ-መንግስቱ ጉዳይ ላይ ከአፈጻጸም ውዝግብ በስተቀር ከህወሓት ጋር መሰረታዊ ልዩነት ያልነበረው ኦህዴድ ጊዜያዊ የስልጣን ቆይታውን ብቻ አስልቶ ፌደራሊዝሙንና ህገ-መንግስቱንም ማስወገድ ከሚፈልጉ የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች ጋር ግንባር ፈጠረ፡፡ በሌላ ቋንቋ ኦህዴድ ወዳጆቹን ለማጥፋት ከጠላቶቹ ጋር ግንባር ፈጠረ፤ ይህ ጊነስ ቡክ ኦፍ ሬኮርድስ ሊገባ የሚችል አስደናቂ ውሳኔ ነበር፡፡ ኦህዴድ በትግራይ ጥፋት ላይ ዋና አጋሩ ከነበረው የአማራ የፖለቲካ ሃይል ጋር መዋጋት ሲጀምር ከፊቱ የበለጠ አስገራሚ ነገር ሰራ፡- በፋኖ ላይ ለመዝመት ትግራይን ለአጋርነት መጠየቁ፡፡ በፖለቲካ እስኪበስሉ ጠብቀው ወደ ፖለቲካ የሚገቡ ብጹአን ናቸው!

የኦህዴድ መሪ አቢይ አህመድ እንዲህ አይነቱ ስትራተጂክ የፖለቲካ አላማው ለየቅል የሆነ ግንባር መርተው ኤሪትርያን በመጋበዝ፤ አማራ ክልል ትግራይ ክልልን እንዲወር በመፍቀድ የራሳቸው ስልጣንና የኦሮሚያ ክልል ህልውና የቆመበትን ህገመንግስት ናዱት፡፡ አቢይ አህመድ ለምን ለራሳቸውም የማይበጅ እንዲህ አይነት ታሪካዊ ስህተት ሰሩ ቢባል መልሱ እንደሚከተለው ነው፡፡ ኦህዴድ ምንም እንኳን አቢይ አህመድን ወክሎ ስልጣን ላይ ቢያወጣቸውም እስካሁን አቆይቷቸው የነበረው ግን የአማራ የፖለቲካ ሃይሎች “ከጳጳሱ ቄሱ” የሆነ ድጋፍ ነው፡፡ የአማራ ልሂቃን በተለይም የወልቃይትን አጀንዳ ያነገቡት ጎንደሮች አብይ አህመድን በሙገሳ ቃላት አስክረዋቸው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ “የአማች-ጎኔ” ነገር ማበሳሰያ ታክሎበት የአማራ ሃይሎች የታማኝ በየነ ጫማ መሳም፤ የፋሲል ደሞዝ “እንዲያንዲያ”፤ የታየ ቦጋለ “ምጥቀት” አሳሳች ነበሩ፡፡ ይህ ሙገሳን እንደዶፍ ያወረደው ልሳን አሁን አብይ አህመድን እያራከሰ ነው፡፡

**<u>ድምጻዊ ፋሲል ደሞዝ</u>**

“በመጨረሻ አቢይ መጣልንና ፀሐይ ወጣልን፡፡ ህዝቡ እስከ አድማስ ተዘርግቷል፣ ህይወት ለስላሳ ሆናለች፤ ገበያውም ሞልቷል፡፡ ከጥበብ በተወለደ ምሁር የጭንቀት ህይወታችን አበቃ፡፡ በብሔራዊ አንድነት ቀመር እንደመር! በምድሬ ሰማይ ላይ ፀሐይ ጠልቃ ቀረች፤ አሁን ግን አዲስ ቀን ማየት ችያለሁ፡፡እስከ ትናንት ድረስ

በመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ነበርኩ፡፡ አብይ መጥቶ እንድኖር ኢንሹራንስ ሰጠኝ፡፡ አብይ የህዝብ ጠበቃ ሆኖ መጥቷል፣ ህመሙ አብቅቶ ስቃዩ አልቋል።”

<u>**ታየ ቦጋለ አረጋ**</u>

“አንተ በሃሳቦችህ ውስጥ ያለው የበላይነት አስደናቂ ነው፡፡ ሁልጊዜ እንደ ንስር ከፍ ብለው መብረርን ይቀጥላሉ;፡፡ ለአፍታ እንኳን ቆም ብለህ አታውቅም፡፡ የጦር መኮንን፤ የላቀ ጸሐፊና ተመራማሪ፤ የዓለም መሪዎችን አስደነቅካቸው፤ በታላቅ ችግር ጊዜ መሪ ነህ! አንተ ብዙ ነህ፣ ብዙ የኛ አብይ ነህ! እኛን ከፍ ለማድረግ ሳትታክት እየሰራህ ነው፡፡ በፌስቡክ እያስተማርከን ነው፤ እግዚአብሔር ይባርክህ፤ እስክንረዳ ድረስ ድካም አይሰማህም።”

የኦህዴድ ከአማራው ብአዴን ጋር ግንባር መፍጠሩ ህወሓትን ለማዳከም ከነበረው የ”አጭር” ጊዜ እቅድ ብቻ ተነስቶ አይደለም፤ ሌላ የረዥም ጊዜ የኦሮሙማ አጀንዳ ስላለው ነው የሚሉ አሉ፡፡ ይህ ፊንፊኔ (አዲስ አበባ)ን ማእከል ያደረገ “ታላቋ ኦሮሚያ”ን የኢትዮጵያ ገዢ የፖለቲካ ሃይል ማድረግ ወይም የራስ ነጻ መንግስት መመስረት ህልም ሳይሆን በተግባር እየተከናወነ ያለ እውነታ ነው በሚልም የሸገር ሲቲ በአዲስ አበባ ዙሪያ መገንባትን፤ በደቡብ ክልል አርቀው ባላዩ የክልሉ ልሂቃን “ክልል በመሆን ጉጉት ደንዝዘው” ወደ አራት አምስት አመቺ ክልሎች የተበተኑበት “ሴራ”ን እንደ ማስረጃ ይጠቅሳሉ፡፡




ኦዲስ አበባን ከቦ በመዋጥ፤ ደቡብን በታትኖ በማከሰም፤ ሶማሊንና አፋርን አሰብንም ጨምሮ በኩሽ ህዝብነት ስም ጠቅልሎ በምስራቅ አፍሪካ ታላቅ አገር

በመፍጠር የአማራን የተስፋፊነት ህልም ማክሸፍ፤ ትግራይንም ትርጉም አልባ የሆነ የፖለቲካ ሃይል እንዲሆን አድርጎ ማሽመድመድ፡፡ ይህ "እቅድ" የጥቂት የፖለቲካ ህልመኞች ምኞት ነው ወይስ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው እየተሰራበት ያለ የኢትዮጵያ መበታተን የመጨረሻው መጀመሪያ? የአህዴድና ሌሎች ፖለቲከኞች ህወሓትን ከስልጣን ያስወገደው አመጽ ኦሮሚያን በሚጠቅም መልኩ የተነደፈ የረቀቀ የፖለቲካ "ሴራ" እንደነበር ሆን ብለውም በአፍ ወለምታም የሚናገሩ፤ ቀጠታ ባይሉትም ይህንን የሚጠቁሙ ቃላት የሚሰነዝሩ አሉ፡፡ ለምሳሌ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት በአንድ ወቅት ከብአዴን ጋር ስለፈጠሩት "የትግል ግንባር" በሚመለከት ሲናገሩ "ባህር ዳር ሄደን ኮንቪንስ ኤንድ ኮንፊዩዝ" (የምናሳምነውን አሳምነን ግራ የምናጋባውን ግራ አጋብተን) ብለው በድፍረት ያጋለጡት ምስጢር የሚሰጠው ፍንጭ አለ፡፡

የአማራ ልሂቃን ህዝባቸውን የማይወክለውን ነገር ግን ወደየጦር ግንባሩ እየተነዳ ሄዶ የሚያልቅበትን "የአማራ በኢትዮጵያ ላይ የባለቤትነትና የበላይነት" አባዜ እውን ለማድረግ ተቃራኒ ከሆነው ከኦሮሞ ልሂቃን የ"ታላቋ ኦሮሚያ" ወይም "ኩሽ ምድር" አላማ ጋር ኢትዮጵያን ሊያወድም የሚችል የ"ታይታኖች ግጭት" እያካሄዱ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያን መፍረስ የሚያፋጥነው ግጭት ሲላከክ የቆየው በትግራይ የፖለቲካ ሃይሎች ላይ ነበር፡፡ በትግራይ ጦርነት ወቅት በደረሰበት ተስፋ ቆርጦ ጥብቅናውን እርግፍ አድርጎ ተወው እንጂ የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያን የመጠበቅ እንጂ የማፍረስ አላማ ኖሮት አያውቅም፡፡ ይህ ሁሉ ውድመት የደረሰበት ግን በሁለቱም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ዝሆኖች "የትግራይ የፖለቲካ ሃይሎች ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ ወስነዋል" የሚል አደገኛ ቅስቀሳ ሲደረግ ስለነበር ነው፡፡ አሁን ይህ ፕሮፓጋንዳ "የአባየን...ወደማየ ልክክ" ሆኗል፡፡

## 5.4. የጦርነቱ አጋጋዮች (የሃይማኖት መሪዎች)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ተፈጥራ ያበበችው አሁን ትግራይ ውስጥ በምትገኘው በአኹሱም ማእከልነት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የፖለቲካ ሃይል ከዛግዌ ስርወ-መንግስት ወደ ሰለሞናዊው የአማራ ስርወ-መንግስት ከተዛወረ ወዲህ ቤተክርስትያኒቱ የአማራ ልሂቃን የፖለቲካ መሳሪያ በመሆን መሰረታዊ አላምዋን ስታ ከመስመር ከወጣች ዘመናትን አሳልፋለች፡፡ "የቄሳርን ለቄሳር ስጡ፤ የአምላክንም ለአምላክ" የሚለው የመድሃኒታችን ቃል "ፖለቲካን ለፖለቲከኞች፤

ሃይማኖትን ለአማኞች” የሚል መንፈሳዊ ትርጉም ሊሰጠው ሲገባ ሁለቱን በመቀላቀል የቤተከርስትያኗ መሪዎች ከፖለቲከኛው በላይ ፖለቲከኛ ከሃይኖተኛውም በላይ ሃይማኖተኛ ሆነው ውግዘትን ሆነ ቡራኬን በአድላዊ ሚዛን እየለኩ ሲያከፋፍሉ ኖረዋል፡፡

ለፈጣሪ ሳይሆን ለንጉስ አልሰግድ አላችሁ ብለው መነኮሳትን በግፍ ያስጨፈጨፉት የቤተክርስትያኗ መሪዎች ለስልጣናቸው ሲሉ የማይጥሱት የአምላክ ቃል የሌላቸውን ነገስታት የቤተክርስትያኗ የበላይ ጠባቂዎች አድርገው በስማቸው ሲቀድሱና ሲያወድሱ ኖረዋል፡፡ በደርግ ጊዜም ቢሆን መንግስትን የማያወድሱ ጳጳሳት መድረሻ አልነበራቸውም፡፡ ለቤተከህነቱ ኮሚኒስት ስራ አስኬያጅ የመደቡ ፓትሪያርክ ግን የተቀደሱ ሆነው ነበር፡፡ የኋለኞችም ከዚህ ተግባር የወጡ አልነበሩም፤ የጎጥ ፖለቲካን ሲኖዶስ ውስጥ አስገብተውት ነበር፡፡ ህወሓት ለምን አዲስ አበባ ገብታ ስልጣን ያዘች ለማለት በቂ ምክንያት ካለው ማለት ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ እንጂ ቤተ ክርስትያኗ መሆን አይገባትም ነበር፡፡ ማውገዝ ካለባት ጥቁር ይሁን ነጭ ለህዝብ ያልቆመውን መንግስት እንጂ ዘር እየለዩ አንዱን አምባገነን አወድሶ ሌላውን አምባገነን ማውገዝ ነውሯ ነው፡፡

በአንድ በኩል ሃይማኖት አገር የለውም፤ አገሩ የሰማዩ መንግስት ነው እየተባለ በጳናጽልና በዜማ ታጅቦ ሲነገር በሌላ ጎን ደግሞ ጽንፍ የረገጠ አካባቢያዊነት! ሚዛናዊ ለመሆን፤ ነገር ግን ሃቅም መስመሯን እንዳትስት ከልብ የታገሉት ፓትሪያርክ አቡነ ማትያስ ደብር እንደገባ ውሻ በዚህም በዛም ሲያዋክቧቸው “ወንጀላቸው” ራሳቸውም ቢሆን ብዙም የማያዳምጡት ትውልዳቸው ነበር፡፡ በተግባርህ ሳይሆን በትውልድህ መወንጀል ከፖለቲካ ዘሎ ወደ ቤተክርስትያን ገባ፡፡ አብረው የሚጸልዩ ነገር ግን ውስጣቸው ጥላቻን ያረገዙ አማኞች! እንደ ህወሓት ተወካይ ተቆጥረው በአቡነ ማትያስ ላይ ማነሳሳት የተጀመረው ከትግራይ ጦርነት ከአራት አመት በፊት ነው፡፡ የትግራይ ትውልድ ያለው ቤተክርስትያኒቱን መምራት አይችልም የሚል ደንብ መቼ እንደወጣ አይታወቅም፤ አማራ ብቻ ይምራት የሚል የተጻፈ ህግ ግን የለም፡፡ ሃዋርያት የመሩት የትውልድ ስፍራቸውን ህዝብ ነበረን? ጴጥሮስ በሮም፤ ማርቆስ በእስከንድርያ፤ ቶማስ በህንድ፡፡

በቅድሚያ በፓትሪያሪኩ ላይ የተነሳውን አመጽ እንይ፡፡ አመጹ የተነሳው ፓትሪያሪኩ የህወሓት ተወካይ ናቸው በሚል ነበር፡፡ አመጸኞቹ ራሳቸው ከጸረ-ህወሓት ፖለቲካ ቡድኖች ጋር የተሳሰሩ ነበሩ፡፡ የአመጽ መግለጫቸውን ያነበበላቸውም ቀንደኛው የትግራይ ዘር ማጥፋት ዘመቻ የሚድያ አባት መሳይ መኮነን ነበር፡፡ “ከአይንህ ውስጥ ያለውን ምሶሶ ትትህ ከሰው አይን ያለችውን ቅንጣት አትይ” ይላል ክርስቶስ፡፡ ፓትሪያሪኩ ከሃይማኖት አመራር ጋር የተያያዘ ጥፋት ከነበራቸውስ ጥፋቱን ማየት የቻሉት የጎጃምና የጎንደር አይኖች ብቻ ነበሩን? ከጎጃምና ጎንደር ውጪ ያለው በአስር ሚልዮኖች የሚቆጠር የቤተክርስትያኒቱ ተከታይ በፓትርያሪኩ ጥሰት ስላልደረሰበት ነው ዝምታን የመረጠው? በኢሳት ቴሌቪዥን የተነበበው መግለጫ፡-

**የጎንደርና ጎጃም ካህናትና መነኮሳት መግለጫ እ.ኤ.አ. መስከረም 2016 ኢሳት ቲቪ**

“እኛ በጎንደርና በጎጃም ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት የተውጣጣን ካህናትና መነኮሳት ራሳችንን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስና በአቡነ ማቲያስ ከሚመራው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በይፋ ለይተናል፡ በዚህ ውጥረት ወቅት ከህዝቡ ጎን መቆም የሚችል የሃይማኖት መሪ ወይም ሽማግሌ የለም፡፡ ይህም አገራችን ምን ያህል በጨካኝ አምባገነኖች እጅ እንደወደቀች ያሳየናል፡፡ እነዚያ አባቶቻችን ለህዝቡ ጉዳይ ሲሟገቱና ሲታገሉ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፣ ታስረዋል ወይም ወደ ግዞት ተልከዋል፡፡ በዚህ አዝነናል፣ ለሀገራችንና ለህዝባችን ሁሉን ቻይ ለሆኑት አለቀስን፡፡”

“የህወሓት አገዛዝ በተራዘመበትና ወጣቶቻችን ለህዝባቸው ነፃነትና ለሀገራቸው እድገት በተነሱበት ወቅት የህወሓት ጎን በሆኑት በአቡነ ማቲያስ በተላለፈው መልእክት ቅር ተሰኝተናል፤ ይህንን ከሃይማኖት መሪና ከአረጋዊ ሰው አንጠብቅም፡ ዓለም አቀፋዊ የጸሎትና የጾም ጊዜ እንዲታወጅ እንጠይቃለን፡፡ ከዛሬ ጀምሮ በአቡነ ማትያስ የሚመራው፤ መቀመጫውን አዲስ አበባ አድርጎ የክርስቲያኑን ህዝብ የማይወክልና መንጋውን ለዱር እንስሳት የተወ ሲኖዶስና የቤተክርስቲያን አስተዳደር የማንቀበል መሆኑን አጥብቀን እንገልፃለን፡፡ ጦርነት በእኛ ላይ በግልጽ ታውጇል፡፡ መብታቸው እንዲከበር በጠየቁ በገዛ አገራቸው ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ታውጇል፡፡ ይህንን እጆቻችንን አጥፈን አንመለከትም፡፡ ክህነታችንን፣ ገዳማዊ ህይወታችንንና ለቤተክርስቲያን ያለንን አገልግሎት የተቀበልነው ምንም ላለማድረግ አይደለም፡፡”

“እንደ ታላቁ ሰማእትና የቤተ ክርስቲያን መሪ ቅዱስ ጴጥሮስ የጎንደርንና የጎጃምን ህዝብ ለመግደል ከመጣው ፋሺስቱ ህወሓት ወራሪ ሃይል ታንኮችና መትረየስ

አፍሙዞች ፊት ለፊት እንቆማለን፡፡ ከፉውን መንግስት ለማውገዝና መስዋዕትነት ለመክፈል መወሰናችንን ሁሉም ኢትዮጵያውያንና የአለም ክርስቲያኖች እንዲያውቁ እንፈልጋለን፡፡ ሁሉም የሃይማኖት አባቶችና በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን አገልግሎት ላይ ያሉ ሰዎች የእኛን መንገድ እንዲከተሉና ጨቋኙን መንግስት እንዲያወግዙ እንጠይቃለን፤ ሁሉን ቻይ በሆነው አምላክ ስም እንለምንናለን፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ችግር ውስጥ ብትገቡም መንጋውን ለመጠበቅና የመጨረሻውን መስዋዕትነት ያለ ፍርሃት ለመክፈል የእግዚአብሔርን ቃል አስቡ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ በጎንደርና በጎጃም የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በህወሓት የተሾሙትን አቡነ ማቲያስን አንቀበልም፡፡"

የጎንደርና የጎጃም አመጸኛ ቀሳውስትና መነኮሳት አላማ አቡነ ማትያስን አንስቶ በስደት ላይ ባሉት የቀድሞ ፓትሪያርክ መተካት ነበር፡፡ አቡነ ማትያስን ለማንሳት "ሿሚያቸው" ናት የተባለችውን ህወሓትን ከስልጣን ማስወገድ ያስፈልግ ነበር፡፡ ህወሓትን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን ድራሿን ለማጠፋት የየራሳቸው ጸረ-ህወሓት አጅንዳ ይዘው ያሰፈሰፉ ሃይሎች ጋር ግንባር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ፡፡ ለዚህ አንዱና ዋናው አጋር የኤሪትርያው ኢሳያስ አፈወርቂ ነበር፡፡ በህውሓት ላይ ከፍተኛ የሆነ የበቀል ስሜት ያዘለው የኤሪትርያው መሪን ድጋፍ ፍለጋ የሲኖዶሱ ከፍተኛ ሃላፊ የሆኑት አቡነ አብራሃም ትግራይ ውስጥ የሚገኘውን የአኹሱም ሃውልት ያለበት ገጸ-በረከት ይዘው አስመራ ድረስ ሄደዋል፡፡ ሃውልቱ የአማራ ነው በሚል (ኤሪትርያ የአኹሱም መንግስት አካል ያልነበረች ይመስል) ነበር ስጦታ ሆኖ ለኢሳያስ ገጸ-በረከት የሆነው፡፡

ህወሃትን ለማስወገድ ይህ የገጸ-በረከት ይዘት ሌላ ከባድ መልእክት ያዘለ ነበር፡- የአማራ የአኹሱም ባለቤትነት! በህወሓትና በትግራይ ላይ የአማራን ህዝብ ለማነሳሳት ይህ አንዱ የፕሮፖጋንዳ መስክ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉ ላይ የወልቃይት ጥያቄ ሲጨመርበት ህወሓትን አስወግዶ ትግራይን ለማምበርከክ በተለይ የጎንደር ህዝብን ድጋፍን አስገኝቷል፡፡ አኹሱምን በሚመለከት ስብሰባ ላይ የተነገረ፡-

**ስሙ ያለተገልጸ አክቲቪስት (ታይም ሚዲያ እ.ኤ.አ. 9 የካቲት 2023)**

"ወደዳችሁም ጠላችሁም፤ ብታምኑም ባታምኑም ኢትዮጵያ የምትድነው በአማራ ህዝብ ብቻ ነው፡፡ የአማራ ህዝብ ነን ስንል ማረጋገጫችን ምንድነው? ፊደላችን! ከእንግሊዝ ቀጠሎ ፊደል የፈጠረው ማነው? አማራ! (ተሰብሳቢዎች)፡፡ ፍልስፍናውስ? አማራ! (ተሰብሳቢዎች)፡፡ ሃይማኖቱስ? አማራ! (ተሰብሳቢዎች)፡፡ ስልጣኔውስ? አማራ! (ተሰብሳቢዎች)፡፡ የአኹሱም ባለቤት ማነው? እውነቱን

እንናገር! አማራ! (ተሰብሳቢዎች)፡፡ አኹሱም የአባቶቻችን የጣት አሻራ ነው! በአኹሱም የመጀመሪያው ነበርን፡፡"

የጎንደርና የጎጃም ቀሳውስትና መነኮሳት አመጽ ከታወጀ ከሶስት ወር በኋላ በጎንደር የወልቃይት ጉዳይ የወለደው ጸረ-ትግራይ እንቅስቃሴ ከዛ ቀደም ከነበረው ብሶ ተቀጣጠለ፡፡ **ዊልያም ዴቪድሰን እ.ኤ.አ. 22 ታህሳስ 2016 ይህንን ዘገበ፡-**

"ከተማዋ (ጎንደር) ውስብስብ ታሪክ ያላቸው አዳዲስ ውጥረቶች እያጋጠሟት ነው፡፡ በአማራ ክልልና በአጎራባች ትግራይ መካከል ያለው የግዛት ውዝግብ ቢያንስ ለ25 ዓመታት ሲጋጋም ቆይቷል፡፡ ከቅርብ ወራት ወዲህ እነዚህና ሌሎች ቅሬታዎች በጎንደር ተቃውሞ፣ አድማ፣ ውድመትና ግድያ አስከትለዋል። አስፈሪ የሆነ የትግራይ ተወላጆች መሰደድ፤ የትግራይ የንግድ ድርጅቶች ኢላማ እየተደረጉ ሲሆን የትግራይ ተወላጆችም ጥቃት እየደረሰባቸው ነው።"

የአማራ ትውልድ ያላቸውና የሲኖዶሱን ከፍተኛ ስልጣን የጨበጡት ሊቃነ ጳጳሳት በትግራይ የተካሄደውን ጦርነት ሲደግፉ ተጠቂው ህዝብ የራሳቸው ቤተከርስትያን አባል መሆኑ ለሰከንድ እንኳ ማሰብ አልቻሉም፤ ፖለቲካዊ ሃይማኖት ህሊናቸውን በወፍራም ብርድ ልብስ ስለሸፈነው፡፡ ሊቀ ጳጳሳቱ ሲናገሩ የነበሩት የ"አጥፋው አውድመው" ቅስቀሳ፤ የፓትሪያሪኩ የትግራይ "ምእመናንን እናድን" ተማጽኖ፤ እንዲሁም ለዚህ ተማጽኖ የተሰጡት ተገቢ ያልነበሩ ምላሾች ቀጠሎ በተከታታይ ይቀርባሉ፡-

"ጁንታ(ትግራይ) ከሚገዛን ሰይጣን ቢግዛን ይሻላል፤ ሰይጣን እግዚአብሔርን ስለሚፈራ (አቡነ ሚካኤል)፤ እነሱ (ትግራይ) ኢትዮጵያን ለማፍረስ እስከ ገሃነም ድረስ እንሄዳለን ብለዋል፤ በጅብ (ትግራይ) ከመበላት ጅቡን በልቶ መቀደስ፤ ከአሸባሪ ጋር መደራደር ፍትሃዊ አይደለም፤ እጅ ከሰጣችሁ በኋላ ጠላ እየጠጣችሁ ማውራት ምን ይጠቅማል? የዋልድባን ገዳም አስረከባችሁ! ወኔ ሊኖረን ይገባል፤ ጀግንነቱ ሊኖርን ይገባል፤ ከላሸን ያዝና አገርህን ጠብቅ፤ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሆነችው በአማራ ነው"፡፡ ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ሊቀ ጳጳሳት አሜሪካ ኮንግረስ ድረስ ሄደው የትግራዩ ጦርነት እንዳይቆም ተማጽነዋል፡፡ ጦር ሜዳ በመሄድም የጦር ሜዳ መነጽር ይዘው የተቃራኒ ምሽጎችን ቃኝተዋል፡፡

**ፓትሪያርክ አቡነ ማትያስ በትግራይ ጦርነት በህዝብ ላይ እየደረሰ ስለነበረው፡-**

"ብዙ ጊዜ ሞክሬያለሁ፤ ነገር ግን በትግራይ ሲካሄድ የነበረውን አረመኔያዊ ድርጊት ማስቆም አልቻልኩም፡፡ መግለጫዎቼን ብዙ ጊዜ ወደ ሚዲያ ልኬ ነበር፤ ነገር ግን

ሁሉንም መልሰው ላኩልኝ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ አንድ ቃል ለመናገር ምንም ፈቃድ አላገኘሁም፡፡ በትግራይ ያለው ችግር እጅግ የከፋ ነው፡፡ በዚያ ብዙ ጭካኔ መፈጸሙ ለእኔ ይቅርና በመላው ዓለም ይታወቃል፡፡ ሰዎችን ማጥፋት እየተከሰተ ነው፡፡ እነሱ (ወታደሮች) ወደ ከተማ፤ ወደ መንደሮች፣ ወደ ሰፈሮችና ወደ መኖሪያ ቤቶች ይንቀሳቀሳሉ፣ ወጣቶችን ይገድላሉ ከገደልም ውስጥ ይጥሏቸዋል፡፡ ከገደሉ በኋላ ተገቢውን ቀብር አይፈቅዱም፡፡"

እግዚአብሔር ጭካኔን ለመቀልበስ የራሱ መንገዶች ሊኖሩት ይችላል፤ ነገር ግን ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች እየሞቱ ነው፡፡ ሴቶች እየተደፈሩ ነው፤ ከዚያ በኋላ የበለጠ እየተሰቃዩ ነው፡፡ ሙታን የተሻሉ ናቸው፤ የተደፈሩት ሴቶች በሕይወት እስካሉ ድረስ በአእምሯቸው ውስጥ ቋሚ ጠባሳ ይኖራቸዋል፡፡ በትግራይ ንብረትም ሙሉ በሙሉ ተዘርፏል፡፡ ሰዎች ህይወት፣ ንብረታቸውና መብታቸው ጠፍቷል፤ ሁሉንም ነገር አጥተዋል፡፡ ለማጥፋት ወስነዋልና እስከ አሁን ድረስ እያደረጉት ነው፡ ፡ ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ምንም አይነት ርህራሄ የላቸውም፡፡ ይባስ ብሎ አርሶ አደሮች መሬታቸውን እንዳያርሱ ምግባቸውን እንዳያመርቱ እየከለከሉ ነው፡፡ የእርሻ መሳሪያዎችን እያቃጠሉ ነው፡፡ ሁሉም እንደሚሞቱ ለገበሬዎች ይነግራሉ፤ በምድር ላይ እንዲኖሩ እንደማይፈቀድላቸው፡፡ መኖር እንደማይችሉ አስቀድሞ ሲወሰን መሬቱን ማልማት እንደማያስፈጋቸው ነው፡፡

አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ይቃጠላሉ፡፡ በደብረ ዳሞ በርካታ ዙር የተኩስ እሩምታ የመነኮሳትን መኖሪያ በማውደም ከመካከላቸው አንዱን ገድሏል፡፡ ምእመናን የአኹሱም ቅዱስ ንብረቶችን ለመጠበቅ ሲሞክሩ ጽዮን ማርያም ውስጥ እንደቅጠል ረገፉ፡፡ በማርያም ደንግላት ምእመናን ጸሎታቸውን ጨርሰው በቤተክርስቲያኑ ኮሪደሮች ውስጥ ሳሉ ሁሉም በጥይት ተረሽነዋል፡፡ በአሲምባ (ኢሮብ) የሚገኘው በዘዌንጌል ስም በሚታወቀው መነኩሴ የተመሰረተው ቤተክርስቲያን ተመታ፡፡ የዋልድባ ገዳም መነኮሳት ሕይወታቸውን በሙሉ እዚያ ይኖሩ ነበር፤ ነገር ግን በኃይልና በጭካኔ ተባረሩ፡፡ አርጋውያኑና አቅመ ደካሞቹ ወደ የትም ሳይሄዱ ሞቱ፤ በሁሉም አቅጣጫ ተበታትነውም ነበር. በደህና ማምለጥ የቻሉት ወጣትና ጠንካራ የነበሩት ብቻ ናቸው፡፡ በትግራይ ከአስፈሪው ሞት የጸዳ ቦታ የለም፡፡ ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ከምድር ፊት ካልጠፉ በቀር አርፈን መተኛት አንችልም ብለዋል።"

## *ፓትሪያሪክ አቡነ ማትያስ በተናገሩት ላይ አስጽያፊ ተቃውሞ (በቪድዮ)፡-*

"እነህ አባት ለኢትዮጵያ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ናቸው" (ዳናኤል ክብረት)፤ "ይህ ሰው በህወሓት ፖለቲካ ውስጥ የተነከረ ነው" (ስዩም ተሾመ)፤ "የሚናገሩት ተቃራኒውን ነው" (አባ ህጻን)፡፡ የሲኖዶሱ ሁለተኛው ሰው አቡነ ጴጥሮስ ግን ረዘም ያለና አሉታ የበዛበት ተቃውሞ ነበር ያቀረቡት፡፡ "ሚኒሊክ የትግራይን ህዝብ

እንደራሳቸው ህዝብ አላዩትም" ብሎ ገብረህይወት ባይከዳኝ ያማረረው ከመቶ አመታት በፊት ነበር፡፡ መቶ አመት የሚዘልቅ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካለ የተፈጥሮ ህግ ሆኗል ማለት ነው፡፡ ገብረህይወት ከሞት ቢመለሱ ምን ይላሉ?

<u>**የአቡነ ጴጥሮስ ተቃውሞ ለፓትሪያሪክ አቡነ ማትያስ ንግግር (በቪድዮ)፡-**</u>

"በአኹሱም ስለተፈጸመው እልቂት የሚነገረው ንግግር የውሸት ዜና ነው፡፡ ከአኹሱም ስለ ጉዳዩ ሲነገር አልሰማሁም፡፡ ከውጪ የመጡ ብዙ ሰዎች ስለሱ ዜና ከውስጥ ካሉት የበለጠ እያዳነቁ ነው፡፡ የሰማሁት በጦርነት 20 ንፁሀን ዜጎች በተኩስ መሞታቸውን ነው፡፡ በአኹሱም 700 ወይም 1000 ንፁሀን ዜጎች ተገድለዋል የሚሉት ነገር እውነት አይደለም፡፡ የመቐለ ከተማ ነዋሪዎች በመከላከያ ከመያዙ በፊት ከከተማው ውጭ በተተኮሰው የመድፍ ተኩስ መረበሻቸውን ዘገባ ሰምቻለሁ፡ ይህ በእውነቱ በፖለቲከኞች ተጽዕኖ ሥር ከነበሩት ሰዎች ንግግር ነበር፡፡ ምግብ የሚያስፈልጋቸው ወደ 500,000 የሚጠጉ ተፈናቃዮች አሉ፡፡

ከአማራ ግዛት (ምእራብ ትግራይ) የተፈናቀሉት አብዛኞቹ የህወሓት ካድሬዎችና ደጋፊዎች በመሆናቸው ነው፡፡ የትግራይ አስተዳዳሪዎች ህዝቡን ትተው ሲወጡ ትግራይውያን ወደ ኋላ ለመቆየት በጣም ፈሩ፡፡ ማንም እንዲለቁ አላስገደዳቸውም፤ ስለፈሩ ተፈናቅለዋል፡፡ ግማሾቹ ወደ ሱዳን፣ የተቀሩት ደግሞ ወደ ትግራይ መሀል ሄዱ፡፡ የምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሶስት ሚሊዮን ሰዎች እንዳሉ ይነገራል። ከነዚህ 1.8 ሚሊዮን የሚሆኑት ከጦርነቱ በፊት በሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ውስጥ ነበሩ፡፡ ህወሓት ለ20 አመታት ምግብ ለመግዛት ገንዘብ እንኳን አልነበረውም፡፡"

## 5.5. ሌላው ገጽታ፡-የትግራይ ጦርነት እንዳይጀመር ያለሰሚ የታገሉ

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት የነበሩ የትግራይ ተወላጆች የትግራይ ጦርነት መጀመር መጀመሪያውን እንጂ መጨረሻውን መቆጣጣር እንደማይቻል ካላቸው ሰፊ ልምድ ለኢትዮጵያ ህዝብም ለመሪዎቹም የነብያት ያህል ማስጠነቀቂያ ሰጥተዋል፡፡ ችግሮች ከጠርሙስ እንደወጣ ጂኒ እንዳይሆኑ መክረዋል፡- ሰዩም መስፍን፤ ጻድቃን ገብረተንሳይ፤፤ ሰየ አብርሃ፤ አባይ ጸሃየ፡፡

<u>**ሰዩም መስፍን**</u> (ለ20 አመታት የኢትዮጵያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ፤፤ የተሰዉ)

"የኤሪትርያው ኢሳያስ አፈወርቂና የኢትዮጵያው አብይ አህመድ ትርምስ እየፈጠሩ ነው፤ ነገሮቹን ሁሉ አወሳስበው የእርስ በርስ ጦርነት ሊያስጀምሩ ነው፡፡ በጊዜ ከሰልጣናቸው መወገድ አለባቸው፡፡"

**<u>ስየ አብርሃ</u>** (የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር የነበሩ)

“ጦርነቱ ከተጀመረ ውጤቱ እጅግ አስከፊ ይሆናል፡፡ በትግራይ ጦርነት ከተጀመረ የአካባቢ አነስተኛ ግጭት ብቻ አይሆንም፤ ሙሉ ጦርነት ነው የሚሆነው፡፡ ይህን የምለው ሰዎችን ለማስፈራራት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ እውነታውን እንዲያውቅ ስለምፈልግ ነው፡፡ ጦርነቱ ከተጀመረ ድንበር አይኖረውም፡፡ ከቀጣናዊ የኃይል ጣልቃገብነት ሁኔታና በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ከሚታየው ጦርነት አኳያ እዚህ ላይ ጥይት ከተጨመረ ሃገሪቱ ማንም የሚፈነጭባት የኮማሪ ቤት ትሆናለች፡፡”

**<u>ጀኔራል ጻድቃን ገብረተንሳይ</u>** (የኢትዮጵያ መከላከያ ኤታ ማጆር ሹም የነበሩ)

“አዲስ አበባ ውስጥ አብይ አህመድን ሶስት ጊዜ አገኘሁትና በጉዳዩ ላይ ተወያይተናል፡፡ ነገር ግን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ምንም ፍላጎት እንደሌለው ግልጽ ሆኖልኛል፡፡ በተለይም በመጨረሻ ላይ ያነሳሁለት ነጥብ ከትግራይ ህዝብ ጋር እየተዋጋህ ነው፤ በሰላም ካልተፈታ አገሪቱን ወደ አደገኛ ሁኔታ ይወስዳታል፡፡ ስለነበረኝ ቃለመጠይቅ አነሳልኝ፡፡ በቃለ መጠይቁ ላይ የትግራይ ህዝብ ብዙ አመቺነቶች እንዳለው፡- አንድ ህዝብ መሆኑ፤ የርእዮተ አለም መካርር የሌለው መሆኑና አንድነት ያለው መሆኑ፡፡ በተጨማሪ የተናገርኩትም፡- የትግራይ ህዝብ አንድ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ መሆኑ የፖለቲካ እውቀቱና ሚዛናዊ አስተሳሰቡ ራሱን ችሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ይረዳዋል፡፡ ተጋሩ የበለጸገ የወታደራዊ ባህል አላቸው፤ በታሪክም በብዙ ጦር ሜዳዎች ለነጻነታቸው ተዋግተዋል፡፡ የምለው ነገር አምኜበት እንደሆነ ወይም እንዲሁ ፖለቲካውን ለማጣፈጥ እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ የምለው ሁሉ ፖለቲካን ለማጣፈጥ ሳይሆን የምለውን ሁሉ እንደማምንበት ስነገረው የአቢይ መልስ እንዲህ ነበር፡- አትሳሳት በሃልይና በገንዘብ የማይንበረከክ ህዝብ የለም፤ ይህ ለትግራይ ህዝብም ይሰራል፡፡ እኔም በበኩሌ አስጠነቀቅሁት፡- የምታምነው እንደዚህ ከሆነ፤ ፖሊሲህ ይህ ከሆነ ተሳስተሃል፡፡ እንዲህ ብሎ መለሰልኝ፡- ለትግራይ ህዝብ ከመጠን በላይ አትጨነቅ፤ ስለትግራይ ህዝብ ብለህ እንቅልፍ አትጣ፤ እንደሆነ አድርገን እንፈታዋለን፡፡ በዚህ ጊዜ ነገሮች ግልጽ ሆኑ፡፡ በዚህ መሃል ሃጫሉ ሁንዴሳ ተገድሏል፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ነገሮችን በውይይትና በሰላም የመፍታት እድል እየጠበበ የሃይል አጠቃቀሙ የማይቀር መሆን ጀመረ፡፡ እኔም ወደ ትግራይ መጣሁ፡፡”

**<u>አባይ ጸሃየ</u>** (ከህወሓት መስራች አመራሮች አንዱ የነበሩ፤ በጦርነቱ የተሰዉ)

ጦርነቱ እየመጣባቸው እንጂ እየሄዱበት እንዳልሆነ ያሳወቁበት፡- “ዋጋ ልንከፍል እንችላለን፡፡ ይህ ግትርነት አይደለም፤ ታዲያ ወዴት እንሂድ? እነሱ ካልተንበረከካችሁ እናጠፋችኋለን እያሉን ነው፤ ያለ ምንም ተቃውሞ ካልሰገዳችሁ፤ ይህ ነው እየተባለ ያለው፡፡ እኛ ደግሞ አንምበረከክም እያልን ነው”*************

# ምዕራፍ ፮

# የጦርነቱ ዋዜማና የመጀመሪያው ምእራፍ

## 6.1 የጦርነቱ ዋዜማ

ዋዜማ የሚለው ቃል አጠቃቀም በተለምዶ ከክስተቱ አንድ ወይም ጥቂት ቀናት በፊት የሆነውን ለመግለጽ ነው፡፡ የትግራይ ጦርነት ዋዜማ ግን በቀናት ሳይሆን በዘመናት የሚቆጠር ለመሆኑ ቀደም ባሉት ምእራፎች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ የአኹሱም ስልጣኔ ወራሽ የሆነው የትግራይ ህዝብ ከቀይ ባህር የባህል ማእቀፍ ወጥቶ በከርስትና ሃይማኖት ቀጭን ገመድ አሁን ከሚገኝበት የባህል ማእቀፍ ጋር የተሳሰረው እንደቤት ሳይሆን እንደጎረቤት ልጅ ሆኖ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ በተቀላቀለው ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ አውድ ውስጥ የሚታየው ዝቅ ሲል እንደ አናሳ ከፍ ሲል እንደባዳ ነው፡፡ አናሳ የሚባለው ከስነ-ህዝብ ወይም ከሰው ቁጥር እንጂ ስልጣኔን የሚገልጽ ጽንሰ-ሃሳብ አይደለም፡፡

የትግራይ ህዝብ እንደ ቁጥሩ ሟምቶ መቀላቀል ቢችልም እንደ ስልጣኔው ግን ጥሬ ሆኖ ቀርቷል፡፡ እንዲህ አይነቱ ማህበረ-ባህላዊ አለመገጣጠም የትግራይን ህዝብ ስልጣኔው፤ ማንነቱና ክብሩ ተጠብቆለት እንደየአቅሙና ችሎታው ኢትዮጵያን ተጋርቶ እንዳይኖር አድርጎታል፡፡ አልገጥም ሲልና የዘመናት መከራ ሲበዛበት የትግራይ ሀዝብ ወደ ጥንቱ የቀይ ባህር የባህል ማእቀፍ የሚመለስበት እድሉ እጅግ የጠበበ ቢሆንም መመኘቱ ግን አልቀረም፡፡ ካለው ጭንቀት፤ ግራ መጋባትና ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ይህ የጥንቱን ታሪክ ወደኋላ መልሶ መኖር በሃሳብ ደረጃ ህይወት ያለውና ጠንከር ያለ የፖለቲካ አቅም የገነባ እንቅስቃሴ ነው፡- "የአጋዚያን ምድር፤ ትግራይ ትግርኚ" ወዘተ፡፡

ይህ አቃፊ መሆን የሚገባው ህዝብ ግትርነት የወለደው የትግራይ ህዝብ የመራቅና የመለየት ፍላጎት የሚያባብሰው እንጂ የሚያለሰልሰው ነገር አልተገኘም፡፡ በቁጥር አናሳ ነህ በሚል የሃገር አመራር እድሉ በጨለመበት ሁኔታ ላይ እያለ የቀረችውን አንዲት ንብረት ቀምተው ባዶ ቀፎ ሊያደርጉት እየታገሉ ነው፡- "የአኹሱም ስልጣኔ የኛ ነው" የሚሉት የአማራ ልሂቃንና "አኹሱምን የሚጠብቅ ጥቂት ሰው ትተን የትግራይን ህዝብ እንበትነው" እያሉ መአት የሚያወሩት የኤሪትርያ ልሂቃን!

ከአናሳነቱ ላይ አግልለህና ፈጅተህ፤ ስልጣኔውንም ገፈህ ወገን አድርጎ ማኖር እንዴት ይቻላል? እዚህ ላይ የተባለው ሁሉ ስለ ተራው የትግራይ ህዝብ እንጂ በየዘመናቱ የነበሩ እስካሁንም ድረስ ያሉትን የትግራይ መሪዎች የሚያካትት አይደለም፡፡ መሪዎቹማ ከሌላው ወገን ባልተለየ፤ አንዳንዴም በከፋ ሁኔታ የትግራይን ህዝብ መበደልና መገለል ለራሳቸው የስልጣን ቁማር ሲገለገሉበት እንደኖሩ ታሪክ ይመሰክራል፤ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የትግራይ ባለስልጣኖች የሚኖሩት እንዲህ ነው፡- የህዝቡን ህይወት ተጠቅመው ሲገዳደሩ፤ የህዝቡን መስዋእትነት ረስተው ሲደራደሩ! የትግራይ ህዝብ "ሁለት ያጣ ጎመን!"

የትግራይ ጦርነት ስሩ ረዥም ብቻ ሳይሆን ውስብስብ መሆኑ በቂ ግንዛቤ መፍጠር ከተቻለ ዋዜማ ወደተባለው የጊዜ አውድ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ምእራፍ የጦርነት ዋዜማ የተባለው ከጦርነቱ በፊት የነበሩት ሁለት አመታት ናቸው፡፡ አመታቱ የሚጀምሩት ህወሓት ከስልጣን ከተገለለች ወዲህ ነው፤ ለህወሓትና ለትግራይ "የመጨረሻ መፍትሄ" ለመስጠት ዝግጅት የተደረገባቸው እጅግ የተወጠሩና አስጨናቂ አመታት! ቀጥሎ ሂደቱ በቀናት ሰልዳ ይቀርባል፡-

## 1. <u>ቅድመ-ዋዜማ</u>

ጸረ-ህወሓት እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ (በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ) የሚበርድና የሚሞቅ የሰላማዊ ትግል መልክ የያዘ ነበር፡፡ በዲያስፖራ ከተለያዩ የአገር ውስጥ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በአባልነት የተመዘገቡና በደጋፊነት የሚታወቁ አክራሪዎችም ለዘብተኞችም ነበሩ፡፡ ጎን ለጎን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ውስጥ በነበረው የስልጣን ውዝግብ አሜሪካ ላይ ጸረ-ህወሓት ሲኖዶስ ቁጥር ሁለት ፈጥሮ የዘር ፖለቲካን እያቀጣጠለ ነው፡፡ የኤሪትርያ መንግስት በህወሓት ላይ ሰላማዊ ያልሆነ ትግል ስልት የመረጡትን የአንድነት (ግንቦት 7)፤ የኦሮሞ (ኦነግ)፤ የአማራ (አርበኞች፤ እ.ኤ.አ. 10 ሓምሌ 2011 ጅምሮ) እና የትግራይ (ደምሂት) ሃይሎችን አስጠልላ የስልጠና አገልግሎትና የጸረ-ህወሓት ወታደራዊ ዘመቻ ማቀናበሪያ ካምፖችን ሰጥታለች፤ግብጽም ለድጋፍ እጇን ሰዳለች፡፡

የአርበኞች ግንባሩ አባይ ሚድያ በሻዕቢያ እንደሚረዳና ይህም ግንኙነት በዲጄ ግሩም ይልማ ሚስት እንደሚመራ ተረጋገጠ፡፡ የዲጄ ግርማ ሚስት የአንድ የሻዕቢያ ጄኔራል ልጅ ናት፡፡ ብርሃኑ ነጋ ግንቦት ሃያንና ኢሳት ቴለቪዥን ለማጠናከር ከግብጽ መንግስት ግማሽ ሚልዮን ዶላር ተቀብሏል (ከራሱ

እንደበት)፡፡ ጸረ-ፓትሪያሪክ አመጽ በጎንደርና በጎጃም፤ ጸረ-ትግራይ መነሳሳት በጎንደር የትግራይ ተወላጆችን በሺዎች አፈናቀለ (እ.ኤ.አ. 2016)፡፡

**2. <u>ከአቢይ ሹመት እስከ ኮቪድና ምርጫ መራዘም</u>**

ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ በበአለ ሲመታቸው እለት 25 መጋቢት 2010 ባደረጉት ንግግር፡- "ከኤሪትርያ መንግስት ጋር ለዓመታት የዘለቀው አለመግባባት እንዲያበቃ ከልባችን እንፈልጋለን፤ ልዩነቶቻችን በውይይት ይፈታል፡፡ ለጋራ ጥቅማችን ብቻ ሳይሆን በህዝቦች መካከል ላለው የጋራ የደም ግንኙነትም፡፡" (የደም ግንኙነቱ በተለይ በትግራይና በኤሪትርያ መካከል እንደሆነ ልብ በሉ)፡፡ የኤሪትርያው ፕሬዚደንት ኢሳያስ አፈወርቂ ለአቢይ አህመድ የሰላም ጥሪ መልስ የሰጡት ከሶስት ወራት በኋላ (13 ሰኔ 2010) ነበር፡፡ መልሳቸውም በውያኔ ውግዘት የተለወሰ ነበር፡፡ የሰላም መንፈስ የራቀው የከረረ ንግግር፡- "የወያኔ እብሪት አበቃ፤ ጌም ኦቨር ተባለ"፡፡ ይህን ቋንቋ ይዞ ወደ ሰላም?

አሁን ነገሮች መጣደፍ ጀመሩ፡፡ በቀጣዩ ወር ውስጥ የአስመራው ሰምምነት በኢሳያስ አፈወርቂና በአቢይ አህመድ ተፈረመ፡፡ (ዋሺንግተን ፖስት 02 ሃምሌ 2010) አቢይ አህመድ፡- "በመካከላችን ያለውን ግድግዳ ለማፍረስ ተስማምተናል፤ አሁን በኢትዮጵያና በኤሪትርያ መካከል ድንበር የለም።" (የፊቱን እያሰቡ በተገባው ቃል መሰረት ድንበር ስለቀረ የኢሪትርያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ/ትግራይ ገባ)፡፡ ኢሳያስ አፈወርቂ ግን ስለድንበር ትንፍሽ ያሉት ነገር አልነበረም፡- "መጪውን ጊዜ አንድ ላይ ሆነን እንደምንጋፈጠው እናረጋግጥላችኋለን፤ እንደ አንድ ሆነንም እንሰራለን፡፡"

ከትግራይ ጋር ነገር እንዳለ የሚጠቁመው ሌላው ምልክት አብይ አህመድን አጅበው ለፊርማው ከሄዱት ባለስልጣናት ማንነት ነበር፡፡ ከአቢይ ጋር ከተጓዙት መካከል የአፋር ክልሉ ፕሬዚደንት ነበሩ፡፡ የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት አለመኖሩ ነገሩን አስገራሚ አድርጎት ነበር፡፡ ኤሪትርያ ከኢትዮጵያ ጋር ካላት ድንበር ከግማሽ በላዩን የምትጋራው ከትግራይ ጋር ነው፡፡የሶማሊያ ብሔራዊ የዜና አገልግሎት 8 ሃምሌ 2010 በጉዳዩ ላይ በሰጠው አስተያየት "የተጋበዘው አፋር ነው ትግራይ አይደለም! በወቅቱ

ህወሓት የትግራይ ህጋዊ መሪ ነበር። ይህ ለችግሩ (ግጭት) ፍንጭ ሰጪ ነው፡፡" (የአፋሩ ፕሬዚደንት ትግራይን ለማስወረር አፋርን ለኤሪትርያ ጦር ክፍት አድርጎት ነበር)፡፡

የአስመራው ስምምነት ከተፈረመ በሁለት ሳምንት ውስጥ 27 ሃምሌ 2010 የአረብ ኢሚሬቱ መሃመድ ቢን ዛይድ የአገሩን ከፍተኛ ሜዳሊያ ሸለማቸው፡፡ ነገሮች ፕሮግራም የወጣላቸው ይመስል በፍጥነትና ያለ ምንም እንቅፋት እየትጓዙ ነው፡፡ በኢትዮጵያና በኤሪትርያ መካከል ሳይሆን በአቢይና ኢሳያስ የተፈጠረውን ዲፕሎማሲ ያልዳሰሰው የጠበቀ የግል ግንኙነት ጉዳይ በሚመለከት መሪውን የጨበጠው ማን እንደሆነ ብዙም ሳይቆይ በግልጽ ታወቀ፡፡ የፋርስ ባህረ ሰላጤ አገር ብትሆንም ኢምሬትስ ባለጸጋ ሆና ቀይ ባህር ላይ እጇን ማስገባት ስትመኝ ያገኘችው ከሰማይ የወረደ መና ይህ የሁለቱ መሪዎች አዲስ ግንኙነት ነበር፡፡ ምእራባዊያን በአሜሪካ እየተመሩ ሊበራሊዝምን በኢትዮጵያ ለማንገስ "ኮሚዩኒስት" የሚሉት ህወሓትን አስወግደው አቢይ አህመድን በተገኘው የለውጥ አጋጣሚ ለሰልጣን አበቁት፤ የሰላም ኖቤልንም አሸለሙት፡፡ ኢሚሬትም ሌሎች ያቦኩላትን ያለምንም ድካም ጋገረችው፡(ኢሚሬትስ በድሮኖቿ የጦርነቱን ሄደት መቀየር ችላለች)፡

በሰለጠነ ባለሙያ እንደተነደፈ ኬሪዮግራፊ ከኢሚሬትስ መልስ ከሁለት ሳምንት በኋላ የአማራ ክልል ተወካዮች ወደ አስመራ ለጉብኝት ተጓዙ፡፡ ይህ የሆነው 09 ነሃሴ 2010 ነው፡፡ ሌላ ስውር አላማ ካልተያዘ በስተቀር አንድ ክልል ከሌሎች ክልሎች ተነጥሎ ከሌላ አገር መንግስት ጋር የብቻ ግንኙነት መፍጠርን የዲፕሎማቲክ ፕሮቶኮል ይከለክላል፡፡ ስለስምምነቱ "ደስታቸውን ለመግለጽ" በሚል የተሰጠው ምክያትም በቀላሉ "ደሮ ጭራ የምታወጣው" ነው፡፡ በአገር ደረጃ ስለተደረገ ስምምነት ደስታን ለመግለጽ ዘጠኝ ክልል አስመራ መግባት የለበትም፡፡ በኤሪትርያው ጋዜጣ ሻባይት የሰፈረው አንድ አረፍተ ነገር ግን ስለጉብኝቱ ትክክለኛ አላማ ፍንጭ የሚሰጥ ነበር፡፡

የአማራ ክልል ተወካዮች ካደረጉት ንግግር መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡- “የኤሪትርያ ህዝብና መንግስት በችግር ጊዜ ለኢትዮጵያ ህዝብ ላደረጉት ድጋፍ አድናቆት እንገልጻለን።” በጦርነት እንጂ በውለታ አልተለያዩ! ይህ ምስጋና ሊሆን የሚችለው ልክ በትብብር መጠየቂያ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ እንደሚጻፈው፡ “ለሚደረግልን ትብብር በቅድሚያ ምስጋና እናቀርባለን!”፡፡ የአማራ፤ በተለይ የጎንደርና የኢሳያስ አፈወርቂ ፍቅር ተሟሙቆ ቀጠለ፡፡ እ.ኤ.አ. 09 ህዳር 2018 በሻባይት እንደዘገበው፡ “ፕሬዝደንት ኢሳያስ አፈወርቂ በጎንደር ከተማ ጎዳናዎች ላይ በከተማው ነዋሪዎች አቀባበል ተደርጎላቸዋል. ኢሳያስ የጎንደር ዩኒቨርሲቲንና ሌሎች የልማት ቦታዎችን ጎብኝተዋል።’’ በዚህ አጋጣሚ ነበር የኢሳያስ አፈወርቂ አያት የተቀበሩት ጎንደር መሆኑ “የተበሰረው”፤ ይህ ሁሉ ለምን?

የትግራይ ወረራ ዘገየብን ብለው ባደባባይ ይናገራሉ ተብለው ከማይታሰቡት ግንባር ቀደሟ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት የነበሩት የተከበሩ መአዛ አሸናፊ ናቸው፡፡ የአስመራው ስምምነት ከተፈረመ በአመቱ (21 ነሃሴ 2011) መአዛ አሸናፊ በአንድ የአሜሪካ ግዛት የተወሰደውን እርምጃ እንደ አብነት ወስደው በትግራይ ላይ በጦር ሃይል እርምጃ እንዲወሰድ ወተወቱ፡፡ በዚህ ጉዳይ ብቻቸውን እንዳልሆኑ ግልጽ ነው፤ እሳቸውን የመሰለ የህግ ሰው ግን ሰላማዊን እንጂ የሃይል መፍትሄ ይመርጣል ተብሎ አይታሰብም፡-

https://aigaforum.com/article2019/Her-Honor-Meaza-Ashenafi.htm

አቢይ አህመድና ብልጽግና ፓርቲ ስልጣን አደላድለው ሳይጨርሱ የብሄራዊ ምርጫ ቀን ደረሰ፡- ምን ይሁን ምን የአስመራው ስምምነት ሳይተገበር፡ የኖቬል ሰላም ሽልማቱ ሙቀት ሳይበርድ፤ የአቢይ አህመድ የንግስና ትንቢት እውን ሳይሆን! የኮቪድ ወረርሺኝ አለምን ኢትዮጵያንም እያተራመሰ ነበር፡፡ ሁለት ሚልዮን የጌዴዎ ተፈናቃዮች ጉዳይ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ስም ማጠልሸት ጅምሯል፡፡ የጫጉላ ሽርሽሩ አሰናካይ ካፍያ እየወረደበት ነው፡፡ የመጀመሪያው የኮቪድ በሽተኛ ሪፖርት የቀረበው 04 መጋቢት 2012 ነበር፡፡ በ22 መጋቢት 2012 መንግስት የ23ቱ ነሃሴ 2012 ምርጫ መራዘሙን ሲያስታውቅ የፖለቲካ ማእበሉ ተነሳ፡፡ ወረርሺኙ ለብልጽግና ፓርቲ እግዚአብሄር የላከው እርግማን መስሎ ምርቃት ነበር፡፡

አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እዚህም እዛም የምርጫውን መራዘም ተቃውመው ቢንጫጩም ከትግራይ ሲመጣ የነበረው የተቃውሞ ድምጽ ግን አቢይ አህመድን እስከማጨነቅ የደረሰ በጣም ጎርናና ነበር፡፡ ለተፈጠረው የምርጫ ማራዘም የህግ አጣብቂኝ መፍትሄ ተብለው የቀረቡት የህግ አማራጮች የሚከተሉት ነበሩ፡- ፓርላማውን ማፍረስ፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ፣ የህገ መንግስት ትርጉምና የህገ መንግሥት ማሻሻያ፡፡ ነገር ግን የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ህገ መንግስቱን እንዲተረጉም አደራ ተሰጥቶት ምርጫውን ላልተወሰነ ጊዜ አስተላልፏል፡ ለዚህ ውሳኔውም የተሳሳተ ምክንያት አቅርቧል፡፡ በ02 ሰኔ 2012 የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና የህወሓት አመራር አባሏ ኬሪያ ኢብራሂም የምርጫ ማራዘሙን ውሳኔ በመቃወም ከሃላፊነታቸው ራሳቸውን አግልለዋል፡-

"ህገ መንግስቱ እየተጣሰ አምባገነን መንግሥት ሲቋቋም እያየሁ ነው፡፡ የዚህ ተሳታፊ መሆን አልፈልግም፡፡ ሕገ መንግሥቱን ማክበርና መተግበር ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነቴ እንዲሁም እንደ ዜጋ ያለኝ ግዴታ ነው፡፡ በፀረ-ህገ-መንግስታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ አልችልም፡፡ በህገ መንግስታዊ አተረጓጎም ሽፋን ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ከፍተኛ አደጋ ላይ ነው፡፡ ወደ አምባገነናዊ አገዛዝ ሊያመራ የሚችል የህገ መንግስት ትርጓሜ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ህሊናዬ ለዚህ ታሪካዊ ስህተትና የፖለቲካ ሴራ ተባባሪ እንድሆን አይፈቅድልኝም፡፡ የትግራይ ህዝብ ህገ መንግስታዊ መብቱን ተጠቅሞ የራስን እድል በራስ የመወሰንና መሪ ለመምረጥ ሲወስን የፌደራል መንግስት የሚወስነውን እንዲቀበል ተነግሮታል፡፡ የትግራይ ህዝብ ካልታዘዘ በወታደራዊ ወረራ እያስፈራራው ነው፡፡ ለወታደራዊ ወረራ ስጋት ሕገ መንግሥታዊ ሽፋን ለመስጠትም ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤነት ስራ መልቀቄን በራሴ ፈቃድ አውጃለሁ፡፡"

በእቅድ ይሁን በአጋጣሚ የምርጫ መራዘም ውዝግቡን አቅጣጫ የሚያስቀይር ከባድ ነገር ተከሰተ፡- 23 ሰኔ 2012 ዝነኛው የኦሮሞ ባህል አቀንቃኝ ሃጫሉ ሁንዴሳ ተገደለ፡፡ ከዛ በኋላ የተፈጠረው ግርግርና እስራት የዴሞክራሲን ተስፋ ያጨለመ ነበር፡፡

### 3. <u>የትግራይ ምርጫና ወረራ</u>

ትግራይን በመምራት ላይ የምትገኘው ህወሓት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምርጫውን ላልተወሰነ ጊዜ ማራዘሙን በመቃወም ግንባር ቀደም ሆነች፡፡ የሌሎች ክልሎች

ገዢ ፓርቲዎች ብልጽግናን ተቀላቅለው ስለነበር ህወሓት ትግራይን ይዛ እንደ አፈንጋጭ ተቆጠረች እንጂ ከጎኗ የቆመ አልነበረም፡፡ ውሳኔው ህወሓት ምርጫው ከመራዘሙ ጋር ስልጣን ላይ እንድትቆይ የሚፈቅድ ቢሆንም የብልጽግና አባል መሆን አሻፈረኝ ያለችው ህወሓት ህልውናዋ በብልጽግና እጅ እንዲወድቅ አልፈለገችም፡፡

ብልጽግና ህወሓት በእጁ ከገባች እንደሚያሟሟት አያጠራጥርም፡፡ የስልጣኑ ከባድ ፈተና የሆነች ፓርቲ ራሷን ችላ ካጠገቡ እያለች እንቅልፍ እንደማይወስደው እሙን ነው፡፡ ለብልጽግና የቀረው አማራጭ ይቺን የማትቆረጠም ጥሬ ወፍጮ ውስጥ አስገብቶ "ዱቄት" ማድረግ ነበር፡፡ ይህን ለማድረግም የመላ ኢትዮጵያ ፖለቲከኞችና የኤሪትርያ መንግስት ድጋፍ ነበረው፡፡ ከትግራይ ጦርነት በኋላ አቢይ አህመድ እውነቱን አውጥቶታል፡-"ህወሓት ብልጽግናን ብትቀላቀል ኖሮ እንዲህ ያለ መከራ አይደርስባትም ነበር፤ ቢያንስ ሃብትና ንብረቷን እንደያዘች በሰላም ትቆይ ነበር" በማለት፡፡

ህወሓት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት ስልጣን ላይ መቆየት ቢፈቀድላትም በርካታ የትግራይ ተቃዋሚ ድርጅቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ከብልጽግና ጋር ተቀራርበው ሲሰሩ ስለነበር በጊዜ ሂደት አቢይ አህመድ እነዛን ተቃዋሚዎች ይዘው ከስልጣን ያስወግዱኛል የሚል ስጋት የነበረባት ይመስላል፡፡ ለግማሽ ምእተ አመት የትግራይን ህዝብ ብትመራም ህወሓት ከስልጣን ውርዶ በሌላ ፓርቲ መተካት የሚለው ሃሳብ በህልሟም ማየት አትፈልግም፡፡ ለትግራይ ህዝብ ፍቅር ያለው ድርጅት ህዝቡ ብዙ አማራጮች እንዲኖረው የሚያደርግ ነው፡፡ ህዝብ በህወሓት ተመርቶ ለከፈለው መስዋእትነት ህወሓት የምትከፍለው ራሷን በስልጣን ላይ አደላድላ ዝንተ አለም መቆየት ሆኗል፡፡ ችግር በመጣባት ቁጥር ብቻ የምታስታውሰው ህዝብ የምታየው እንደ ቅጥር ወታደር ነው፤ የእርዳታ ስንዴ ቅጥር!

ስለዚህ ለህወሓት በስልጣን የመቀጠል ብቸኛ ተስፋ አድርጋ የወሰደችው የራሷ የክልል ምርጫ አካሂዳ በመሸባት ማደር ነበር፡፡ በዚህ ውሳኔ መሰረት የራሷ የሆነ የክልል ምርጫ ቦርድ አዘጋጀች፡፡ በአገሪቱ ህግ መሰረት የክልል ምርጫ ቦርድ የሚባል ነገር የለም፡፡ የክልሎችን ምርጫ የሚመራው የፌደራሉ ምርጫ ቦርድ ብቻ ነው፡፡ ይህ ህወሓት በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ በነበረችበት ወቅት ተከራክራ

ያጸደቀችው ህግ ነው፡፡ የምርጫ ቦርድ ሰው ተቀየረ እንጂ ህግ አልተቀየረም፡፡ ህወሓት የፌዴሬሽን ምክር ቤቱን የህገ መንግስት ጥሰት ስትቃወም ራሷ ህገ መንግስት ጥሰት ውስጥ ገባች "እሾህን በእሾህ" እንደሚባለው፡፡ የምርጫ ህግ ማፍረስ ካዋጣ የሚያዋጣው ለጉልበታሙ ነው፡፡ ብልጽግና መላ ኢትዮጵያንና ኤሪትርያን ከጀርባው አሰልፎ እንኳንና የሰው ህግ የአምላክ ህግም ቢጥስ ጠያቂ የለውም፡፡ በትግራይ ጦርነት የሆነውም ይኸው ነው፤ የሰውም የአምላክም ህግ ተጥሶ የተጠየቀ የለም! ህወሓት እዚህ ላይ በስሜት ከመመራት ይልቅ ብስልና ብልጥ መሆን ነበረባት፡፡

በእልክ ከግድግዳ ጋር በመጋጨት የማን ጭንቅላት እንደሚሰበር ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ የተጋጨው እድለኛ ሆኖ ወይም በራስ ቅሉ ጥንካሬ ከሞት ይተርፍ እንደሆነ ነው እንጂ በጠባሳ ብዛት ተኀጎርጉሮ እድሜውን መፍጀቱ አይቀርም፡፡ ህወሓት መቐለ ስቴድዮም ላይ ወታደራዊ ሰልፍ ስታሳይ ለማንም ሰውም ቢሆን ሰላም ፈላጊነትን አያሳይም፡፡ ተጠቂ ነኝ የሚል ህዝብ አቅም ቢኖረውም እንኳ ባዶ እጁን ዘርግቶ አድኑኝ ብሎ ይማጸናል እንጂ "ብትነኩን ታልቃላችሁ" የሚል አይነት መልእክት ያዘለ ሰልፍ ካካሄደ አለም የሚለው "በሉ ይዋጣላችሁ!" ነው፡፡ ታስቦበት ይሁን ተተርጉሞ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ ከትግራይ ሲተላለፍ የነበረው መልክት ከሩብ ሚልዮን ያላነሰ ጦር እንደተዘጋጀ ነበር፡፡ ይህ "ማስፈራሪያ" የሚኖረው ውጤት ከታሰበው በተቃራኒ ነው፡፡ የትግራይ ተቃራኒ ወገን መሸነፍና ማፈር ስለማይፈልግ የቻለውን ያህል ሃይል ያሰባስባል፤ የትግራይን ሃይል ለማሸነፍም የማይቆፍረው ጉድጓድ አይኖርም፡፡ ትግራይ ምንም ተጠቂ ሆና የሞራል የበላይነት ቢኖራት በጀቷ፤ የሙብራት፤ የስልክና  የባንክ አገልግሎት፤ የሸቀጣ ሸቀጥ አቅርቦት፤ የመከላከያ ሃይልና የውጭ ግንኙነት በተቃራኒው እጅ ባለበት በረዥም ገመድ ታስሮ ለማምለጥ እንደመሞከር ነው፡፡

በአንድ በኩል አቢይ አህመድ በትግራይ ላይ የሃይል እርምጃ እንደማይወስድ በትግርኛም በአማርኛም ቋንቋዎች መግለጫ በመስጠት አለምን ለማረጋጋት እየሞከረ ነበር፤ ህወሓት አደገኛ ስህተት ፈጽማ ህግ ጠቅሶ እስኪሄድባት ድረስ፡፡ መቀመጫቸውን አዲስ አበባ ያደረጉ የህወሓት ተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችም (አረጋዊ በርሄና አብርሃ ደስታ) የወረራው ትርክት "ህወሓት ህዝቡን አስፈራርታ በስልጣን ለመቆየት የምትፈበርከው ዘዴ ነው" እያሉ የማዘናጋት ሚና እየተጫወቱ

ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ የትግራይ ክልል ፕሬዚደንት ለተያዩ መንግስታትና አለም አቀፍ ተቋማት ሲልኩ የነበረውን የወረራ ስጋት መልእክት ተአማኒነት አጥቷል፡፡

አገር አቀፍ የውጥረት ስሜቱ እንዳለ ሆኖ ህወሓትን አገር በጥባጭ አድርጎ ለመሳል የሚካሄደው ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በመላ ኢትዮጵያ ጥቃት በተፈጸመ ቁጥር፤ ሰው በጅምላ በተገደለ ቁጥር "የህውሓት እጅ አለበት" የሚል ውንጀላ የእለት ተእለት የዜና ርእስ ሆነ፡፡ ህወሓት መቐለ ተቀምጣ በመላው ኢትዮጵያ እየተገኘች ግጭት የምትለኩስና ሰው የማታስፈጅ መንፈስ ሆነች፡፡ "አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ" እንዳለችው "የአደፈረስሺብኝ" ውንጀላ የታከታት አህዩት፡፡

የአለም ሚድያ አይኑን ትግራይ ላይ ተከለ፤ ትግራይ በሰራችው የህግ ጥሰት ላይ ብቻ አተኮረ፡፡ ምክንያት ነበረው፤ ትግራይ ፍሪምባና ሻኛ አቅራቢ አይደለችም! ኦክስፎርድ አናሊቲካ በ27 ግንቦት 2020 "ትግራይ ላይ ሊካሄድ የታቀደው ምርጫ ህገ መንግስታዊውን ቀውስ ሊያባብሰው ይችላል" የሚል አስተያየት ሰነዘረ፡፡ በትግራይ ምርጫ ዋዜማ (03 ጳጉሜ 2012) የዶቼ ቬሌዋ ክሪስቲና ክሪፓል "የትግራዩ እምቢተኝነት በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ጫና እየፈጠረ ነው፡፡" በማለት ከሁለት ህግ አፍራሾች መካከል የቀለላትን ወይም የጠላችውን መረጠች፡፡

በመጨረሻም የትግራይ ምርጫ በ04 ጳጉሜ 2012 ተካሄደ፡፡ ከምርጫው በፊት የጀመረው በትግራይ ላይ የአለም ሚድያ ርብርብ ከምርጫ በኋላም ተባብሶ ቀጠለ፡፡ በ04 ጳጉሜ 2012 የቪኦኤው ሲሞን ማርክስ ምርጫውን "በመንግስት ላይ እምቢተኝነት" ብሎታል፤ ኦክስፎርድ አናሊቲካም "ምርጫው የትግራይና የፌደራል መንግስት መራራቅንንና አለመግባባትን ያባብሳል"፡፡ የሮይተሯ ጁልያ ፓራቪቺኒ፤ በ05 ጳጉሜ 2013 ደግሞ የኒው ዮርክ ታይምሱ ሲሞን ማርክስና አብዲ ለጢፍ ዳሂር በተመሳሳይ ምርጫውን "እምቢተኝነት" ብለውታል፡፡ በ01 መስከረም 2013 የአዲስ ስታንዳርዱ መድሃኔ ዑቕባ ሚካኤል ምርጫውን "እንዲያውም ከእምቢተኝነት በላይ ነው" ብሎታል፡፡ በ02 መስከረም 2013 የኳርትዙ ሳሙኤል ጌታቸው "አከራካሪው ምርጫ "የፌደራል መንግስቱን ዋጋ ያስከፍለውል" በማለት ለእውነታ የቀረበ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

የትግራይ ምርጫ ከተካሄደ ከአንድ ወር በኋላ (27 መስከረም 2013) ነበር የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምርጫው ህጋዊ አይደለም ብሎ የወሰነው፡፡ ከውሳኔው

ጋር ተያይዞም ለትግራይ የበጀት ድጎማውን አግዷል፡፡ ለዚህ “በአይነቱ አዲስ” ለሆነው ውሳኔ የትግራይ መንግስት የሰጠው መልስ ከረር ያለ ነበር፡ “የጦርነት አዋጅ አከል የሆነ ህጋዊነት በሌለው አካል የተወሰነ ህገወጥ ውሳኔ”፡፡ ከዚህ በኋላ የቁልቁለት መንገዱ ተጅመረ፡፡ እንደ ኦክስፎርድ አናሊቲካ ሪፖርት 03 ጥቅምት 2013 የኤሪትርያው ፕሬዚዳንት ለይፋዊ ጉብንት አዲስ አበባ ገቡ፤ ይህ የትግራይና የፌደራል መንግስት ውጥረትን ያባብሳል ተብሏል፡፡ በዚህ ጉዞ የቢሾፍቱን የአየር ሃይል ስፈር ጎብኘተዋል፡፡ የጉብኝቱ መልእክት ግልጽ ነበር፡፡

ኸርማን ኮኸን ስለፕሬዚዳንቱ ጉብኝት ሲናገሩ፡- “ለትግራይ ክልል ባለስልጣናት በአቢይ አህመድ የሚመራው የኢትዮጵያ ማእከላዊ  መንግስትን በጦር ሃይል ለመቋቋም እንዳይሞክሩ ጠንካራ መልእክት የሚያስተላልፍ ነው” ብለውታል፡፡ ጆቲል ትሮንቮል ለኸርማን ኮኸን በሰጡት ምላሽ፡- “ጉዳዩን በጭንቅላቱ ማቆም አይሆንም ወይ? የትግራይ ህዝብና ህወሓት የፕሬዚዳንቱን ጉብኝት እነሱን በጦር ሃይል ለማጥቃት የሚደረግ ዝግጅት እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ”፡፡ ማርቲን ፕላውት በዚህ መሃል ምክር ለግሶ ነበር፡- “በኤሪትርያና በኢትዮጵያ መካከል የሚኖረው መልካም ግንኙነት ሊሳካ የሚችለው ሁለቱም አገሮች የትግራይን መብት ሲያከብሩ ብቻ ነው”፡፡

ትግራይ ክልል በበኩሉ የማካረር አስተዋጽኦውን የሰሜን እዝ ባለስልጣናት ሹመትን ባለመቀበል አሳየ (አዲስ ስታንዳርድና አልጀዚራ 19 ጥቅምት 2013)፡፡ አደጋውን ያስተዋሉት የአውሮፓ ህብረት የውጭ ፖሊሲ ሃላፊ ጆሴፍ ቦሬል ጦርነት ሊጀመር አንድ ቀን ሲቀረው (23 ጥቅምት 2013) ወታደራዊ ዝግጅቱ እንዲቆም ጥሪ አቀረቡ፡፡ ቀደም ብሎ ጣልቃ ያልተገባበት መካረር የማይቀለበስበት ደረጃ ላይ ሲደርስ እንዲቆም መጠየቁ “ብለን ነበር” ከማለት ያለፈ ፋይዳ የለውም፡፡ ይህ የተለመደ የአለም አቀፉ ማህበረሰብ እርምጃ እንደመሆኑ ጫፍ ላይ ደርሰው የተቀለበሱ ግጭቶች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በ24 ህዳር 2013 ሌሊት ላይ የትግራይ ሃይሎች የሰሜን እዝን አጠቁ፡፡

በእግር ጣቱ ቆሞ ጦርነቱን የምትለኩስ አንዳች አጋጣሚ እንድትፈጠር በጉጉት ሲጠባበቅ የነበረው የኤሪትርያው ሃይል፤ የአማራው ሃይልና የፌደራል ሃይል ከሁሉም አቅጣጫ ወደ ትግራይ ተመመ፡፡ ትግራይ የተጠቃችው የሰሜን እዝ በመጠቃቱ ብቻ ከሆነ ሌሊት ላይ ለደረሰ ጥቃት ሲነጋ እንዴት ትግራይ በሁሉም

አቀጣጫ በጦር ተጥለቀለቀች? ይህ ስእል ነጥቦችን ማገጣጠም አላስፈለገውም፡፡ ከፌደራል ጦር ጋር ሳይናበቡ የራሳቸውን የወረራ እቅድ ሲያወጡ የከረሙት የአማራ ልዩ ሃይል በሑመራ የኤሪትርያ የከባድ መሳሪያ ደጋፍ እንደተደረገላቸው ይነገር ነበር፡፡ የአማራ ክልል የድርጊት ነጻነቱ ምን ያህል እንደነበር ሲታይ ትግራይን የመውረር ጉጉት የበዛው ከዛ ጎራ እንደነበረ ነው፤ የዚህ ሁሉ ፍጅት ማእከሉ ወልቃይትና ሑመራ ወሮ መያዝ ስለነበር፡፡ በምእራብ ትግራይ በኩል የተፈጠረው ሁኔታ ለሰሚው ፈገግ የሚያሰኝ ነበር፤ ደም እንደጎርፍ ባፈሰሰ ጉዳይ ላይ አይሳቅም እንጂ፡፡

የአማራ ልዩ ሃይል የምእራብ ትግራይ ወረራ የጀመረው የኢትዮጵያ ኤታ ማጆር ሹም ጄኔራል (ፊ.ማ) ብርሃኑ ጁላ ስለ ጉዳዩ ሳይሰሙ ነበር፡፡ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ብዙም ሳይቆይ አበረ አዳሙ የአማራ ክልል የፖሊስ ኮሚሽነር መግለጫ ለመስጠት መድረክ ያዙ፡፡ ደስታ እየፈነቀላቸው የትኛውን እንደሚያስቀድሙ የተቸገሩ ይመስሉ ነበር፡፡ ጦር ሜዳ ካለው የልዩ ሃይል አዛዣቸው (ቢሰጥ) የሰሙት መልእክት “ትግራይ የነበርውን ሜካናይዝድ ብርጌድ በትኩስ ሽፋን ወዳሉብት እንደሳቡትና አሁን ከልዩ ሃይሉ ጋር ተሰልፎ እንሚገኝ” የሚል ነበር፡፡ ቀደም ብለው ከሜካናይዝድ ብርጌዱ አዛዥ ጋር ከጦሩ የእዝ መስመር ውጪ በሬድዮ እየተገናኙ ይመካከሩ እንደነበር ሲናገሩ “ይህ እኮ ጦር ፍርድ ቤት ያስቀርባል” የሚላቸው አላገኙም፤ ስካሩስ?

አበረ አዳሙ እዚህ ላይ አላቆሙም፡፡ ለጄኔራል (ፊ.ማ) ብርሃኑ ጁላ ደወሉ፡፡ የክልል ፖሊስ አዛዥ ወደ አገሪቱ መከላከያ ኢታማጆር ሹም ቀጥታ ስልክ ሲደውል! ማንም ሰው ጄኔራሉን ቢሆን አበረ አዳሙ ታስረው በሄሊኮፕተር እንዲመጡለት ያዝ ነበር፡፡ ሰውየው አለቀናቸው የሞት ቀጠሮ የያዙ ይመስሉ ነበር፡፡ ጄኔራል (ፊ.ማ) ብርሃኑ ጁላ ስለ ሜካናይዝድ ብርጌዱ ጉዳይ ሲሰሙ ተደናግጠው እንደነበር አበረ አዳሙ ተናገሩ፡፡ ቀጠሎም አበረ አዳሙ “የሆነው ሆኗልና ለሰራዊትህ ከኛ ጎን ሆኖ እንዲዋጋ ትእዛዝ ስጥ” ብሎ ለጄኔራል (ፊ.ማ) ብርሃኑ ጁላ አሻቅቦ መመሪያ ሰጧቸው፡፡

ይህን ያህል የአበረ አዳሙ በራስ መተማመን ከየት መጣ ቢባል፡- “...........ን ለምን ትፈራታለህ” ሲባል “ከግድገዳ የሚያላጋ ልጅ አላት” አለ ይባላል፡፡ የፌደራል መንግስቱን መዋቀር ጠፍንገው ለያዙት የአማራ ልሂቃን ይህ የእዝ ሰንሰለት ቅሌት

የጤፍ ያህል ያነሰ ነው፡፡ በአበረ አዳሙ የተጀመረው የፌደራል ሰራዊት "የራስን እድል በራስ የመወሰን" መብት መገፈፍ በጦርነቱ አመታት በከፋ ሁኔታ በኤሪትርያ ጀኔራሎች ሲፈጸም ነበር፡፡

## 6.2 የጦርነቱ የመጀመሪያው ምእራፍ

### 1. ከሰሜን እዝ ጥቃት እስከ መቐለ መያዝ

በ24 ህዳር 2013 ሌሊት ላይ የትግራይ ሃይሎች የሰሜን እዝ ማጥቃታቸውን ተከትሎ በማግስቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ "የህግ ማስከበር ዘመቻን"፤ ስድስት ወር የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅንና የስልክና የሙብራት መቋረጥ ውሳኔን አስተላለፉ፡፡ የትግራይ ፕሬዚዳንት የሰሜን እዝ አብዛኛውን የጦር መሳሪያ እንደተቆጣጠሩና የኢትዮጵያ ወታደሮችም ወደ እንሱ ወገን እንደከዱ አሳወቁ፡፡ በዛው እለት (በ24 ህዳር 2013) አምኔስቲ ኢንተርናሽናል የተቋረጠው መገናኛ እንዲቀጥልና የሰዎች የመናገር መብታቸው እንዲጠበቅ አሳሰበ፡፡ ከሁለት ቀናት በኋላ (በ26 ህዳር 2013) የተባበሩት መንግስታት ጦርነቱ እንዲገታና ችግሩ በሰላም እንዲፈታ ጥሪ አቀረበ፡፡

የተባበሩት መንግስታት ጥሪ ውጤት ሊኖረው ያልቻለው አቢይ አህመድ የትግራይን ሃይሎች አሸንፎ መድረሻ እንዳሳጣቸው አይነት ስሜት እየተሰማው ስለነብረ ነው (አሶሴትድ ፕሬስ 26 ህዳር 2013)፡፡ ወደኋላ የኒውዮርክ ታይምሱ ዴክላን ዋልሽ እንቆቅልሹን እንዲህ ሲል ገልጾታል፡- "የጦርነት ጎዳናን የጠረገ የኖቤል የሰላም ሽልማት"፡፡ ቢቢሲና ሬውተርስ (09 ህዳር 2013) እንደዘገቡት የሰሜን እዙ ጥቃት ተባባሪ ነበራችሁ ተብለው 76 የትግራይ ተወላጅ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡ በድላቸው የተማመኑት አቢይ አህመድ 14 ህዳር 2013 የትግራይ ሃይሎች በ72 ሰአታት ውስጥ እጃቸውን እንዲሰጡ የቀን ገደብ አስቀመጡ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የድል ስሜት በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ በጊዜ ያገኟትን ወርቃማ እድልንም ገፍተዋታል፡፡ በ14 ህዳር 2013 የአፍሪካ ህብረት ለሰላም ውይይት ግብዣ አድርጎላቸው ነበር፡፡ ይህንን ግብዣ አልቀበልም ሲሉ ቀልድ ቢጤ አክለው ነበር፡- "ወይይት የማካሂደው ከትግራይ ህጋዊ ተወካዮች ጋር ነው"

(አልጀዚራ፤ አሶሴትድ ፕሬስ)፡፡ እነዚህ ህጋዊ ተወካዮች የትግራይ ብልጽግና አባላት መሆናቸው ነው፤ ከራስ ጋር ውይይት! ከ14 ህዳር 2013 ጅምሮ የምእራብ ትግራይ አስተዳደር በአማራ ክልል ባለስልጣናት የተያዘ መሆኑ አስታወቀ፡፡ ከዚህ በኋላ መቐለን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ወታደራዊ ዘመቻ ተከፈተ፡፡ ኮሎኔል ደጀኔ ጸጋየ የተባሉ የመከላከያ ከፍተኛ መኮንን ቢቢሲና አሶሲይትድ ፕሬስ በ13 ህዳር 2013 እንደዘገቡት ለከተማው ህዝብ አስፈሪ የሆነ ማስጠንቀቂያ ሰጡ፡- “መቐለ ለመግባት ከተማው ተከቦ በከባድ መሳሪያ ስለሚመታና ምንም ምህረት ስለማይኖር ሲቪሎች ከወታደራዊ ተቋማት ርቀው መጠጊያ መፈለግ አለባቸው”፡፡ ሲቪሎች በምን መንገድ ወታደራዊ ተቋማት የት እንዳሉ ያውቃሉ? ለሲቪሎች ጥንቃቄ የጎደለው፤ ለግድያም አመቺ የሆነ!

መቐለ ከከባድና ኢላማ ያልመረጠ የመድፍ ድብደባ በኋላ፤፤ የአራት አመት ህጻን ጨምሮ 27 ሲቢሎች ተገድለው፤ በ19 ህዳር 2013 በመከላከያ እጅ ገባች (ሂዩማን ራይጽ ዎች፤ ኒውዮርክ ታይምስ)፡፡ በቀጣዩ ቀን አቢይ አህመድ፡- ”የትግራይ ክልል ወታደራዊ ዘመቻ ተጠናቀ ተኩስ ያቆምን መሆናችንን በደስታ እገልጻለሁ” አለ፡፡ በዛው እለት የትግራይ ሃይሎች ዓቢይ ዓዲ ላይ ሚግ-23 ጀት መተው መጣላቸውን አስታወቁ፡፡ የጦርነቱ መጀመሪያ እንጂ ማለቂያው እንዳልሆነ በግልጽ ታየ፡፡ ታህሳስ 2013 የአዣንስ ፍራንስ ፕሬሱ ኮሬ-ቡሌ “አቢይ ድሉን ካወጀ በኋላ የትግራይ መሪዎች ውጊያቸውን እንደሚቀጥሉ ዝተዋል” በማለት ዘግቧል፡፡

## 2. የጦርነቱ የመጀመሪያ ምእራፍ የጊዜ ሰሌዳ

| | |
|---|---|
| **23 ጥቅምት 2013** | • የሰሜን እዝ ተጠቃ (ሌሊት) |
| **24 ጥቅምት 2013** | • አቢይ አህመድ በትግራይ ላይ ጦርነት አወጀ |
| **25-26 ጥቅምት 2013** | • የትግራይ ከባድ መሳሪያዎች በአየር ጥቃት ወደሙ-- ዋሺንግተን ፖስት፤ ቢቢሲ፤ አልጀዚራ፤ ዘ ጋርድያን |
| **26 ጥቅምት 2013** | • አቢይ ተጨማሪ ወታደሮች ወደ ትግራይ አስገባ-- ዋሺንግተን ፖስት |
| **28-29 ጥቅምት 2013** | • ሺግል ጅምላ ግድያ (ሊያጠፉን አስቧል) |

| | |
|---|---|
| **30 ጥቅምት 2013** | • የብልጽግና መንግስት በመቐለ |
| **30 ጥቅምት-02 ህዳር 2013** | • ማይ ካድራ ጅምላ ግድያ |
| **01 ህዳር 2013** | • "ኤሪትሪያ ትግራይ ውስጥ እየተዋጋች ነው" ዶር. ደብረጽዮን ገብረሚካኤል<br>• 2500 ስደተኞት ወደ ሱዳን-ሬውተርስ፤ አልጀዚራ |
| **04-05 ህዳር 2013** | • ዳንሻ ፍጅት |
| **04-05 ህዳር 2013** | • ባህር ዳር ጎንደር አስመራ ሚሳይል ጥቃት--ኤኤስ፤ ኒውዮርክ ታይምስ፤ሬውተርስ፤ ዶቸ ቬለ፤ ፍራንስ 24፤ ቪኦኤ፤ አልጀዚራ፤ አሶሴትድ ፕሬስ |
| **06 ህዳር 2013** | • ውቕሮ ኢላማ የሌለው ድብደባ--ፍራንስ 24 |
| **26 ጥቅምት-<br>10 ህዳር 2013** | • ወደ ሱዳን ሽሽት 25000--አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ<br>• የኢሚሬትስና የቻይና ድሮኖች በትግራይ ሰማይ--አውሮፓ የውጪ ፕሮግራም ለአፍሪካ ሁኔታ ሪፖርት |
| **08 ህዳር 2013** | • ሽረ ፍጅት (እንደ ደሮ አረዱን)--አሶሴትድ ፕሬስ<br>• መቐለ አየር ድብደባ |
| **12 ህዳር 2013** | • ዓዲግራት ፍጅት<br>• ዕዳጋ ሓሙስ ፍጅት |
| **14 ህዳር 2013** | • ሑመራ በመድፍ ተደበደበች |
| **18-19 ህዳር 2013** | • ዉቕሮ ፍጅት |
| **19 ህዳር 2013** | • መቐለ በፌደራል ጦር ተያዘች<br>• አኹሱም ፍጅት (በኤሪትርያ ጦር) |

## 3. "መኸተ" ከመቐለ ወደ መቐለ (19 ህዳር 2013-21ሰኔ 2013)

| | |
|---|---|
| **19 ህዳር 2013** | • የህወሓት አባላት፣ የትግራይ አስተዳደር፤ ልዩ ሃይል፣ ወረራውን የተቃወሙ ሌሎች ግለሰቦችና ቡድኖች መቐለን ለቀው ወጥተዋል |

**21 ህዳር 2013**

- ሚግ-23 በዓቢዪ ዓዲ-ተምቤን አቅራቢያ በትግራይ ሃይሎች ተመቶ ወድቋል

**21 ህዳር 2013**

- ድር. ደብረጽዮን አቢይ አህመድ የእብደት እርምጃውን ያቁም አለ

**22 ህዳር 2013**

- የኤሪትርያ ወታደሮች ውቕሮ ላይ ተያዙ

**28 ህዳር 2013**

- አቢይ አህመድ ህወሓት የትጥቅ ትግል ለማካሄድ አቅም የላትም አለ

**12 ታሕሳስ 2013**

- ከ20 በላይ ታንኮችና ብረት ለበስ መኪናዎች በቲዲኤፍ ወደሙ፤
- አንድ ቢ.ኤም ማይ ቀያሕ-ሒዋኔ መንገድ ላይ ተማርኳል.

**13 ታሕሳስ 2013**

- የፌደራል ሰራዊት ከመደባይ ዛና ተገፍቶ ወጥቷል
- በመቶዎች የሚቆጠሩ የፌደራል ወታደሮች ናዕዴር-ዓዴት፤ አስገደ-ጽምብላ በቲዲኤፍ ተገድለዋል
- ቤት መራ ላይ አውሮፕላን በቲዲኤፍ ተመቶ ወድቋል

**13 ታሕሳስ 2013**

- አንድ ትግራዋይ ዓዲግራት ውስጥ ቤቱን ሲዘርፉ የነበሩትን 14 የኤሪትርያ ወታደሮችን ከገደል በኋላ ተገድሏል

**22 ታሕሳስ 2013**

- 800 የፌደራልና የኤሪትርያ ወታደሮች ከአጉላዕና ከማይ መኸደን መደ መቐለ አፈገፈጉ
- የፌደራሉ አራተኛ ብርጌድ ዞንጊ (በዓድዋና ዕዳጋ ዓርቢ መካከል) ላይ ተመቶ 124 ሲገደሉ 144 ቆስለዋል፤ የብርጌዱ አዛዥ አለሙ ስሜ ተማርኳል
- የኤሪትርያ ሃይሎች ዝባን ጕላ ሲዘርፉ ተባረዋል

**24 ታሕሳስ 2013**

- የፌደራል ሰራዊቱ ቲዲኤፍን ከተራራማ ቦታዎች ማስለቀቀ አልቻለም

**25 ታሕሳስ 2013**

- መቐለ የነበሩት የፌደራል ሰራዊት አባላት በትግራይ ተራሮች ላይ ከመሸገው የቲዲኤፍ ሰራዊት ጋር አንዋጋም ብለው እርስበርስ ተታኰሱ

**28 ታሕሳስ 2013**
- መቐለ ዙርያ ባሉት ገጠራማ ቦታዎች ውጊያ እንዳለ ተዘገበ

**03 ጥር 2013**
- ቲዲኤፍ ደባኖ (ተምቤን) ላይ የፌደራል ጦሩን መቷል

**05 ጥር 2013**
- ቲዲኤፍ ሩቫ ገረድ ላይ የፌደራልና የኤሪትርያን አንድ ባታሊዮን ጦር ደመሰሰ

**07 ጥር 2013**
- ቲዲኤፍ ዳዕሮ ሓፋሽ (አኹሱም) ላይ የፌደራልና የኤሪትርያን 4000 ወታደሮች ገድሎ  በርካታ የጦር መሳሪያ ማርኳል

**09 ጥር 2013**
- ቲዲኤፍ ወጀራት ላይ 30 የኤሪትርያን ወታደሮች ማርኳል

**10 ጥር 2013**
- የፌደራል ሰራዊቱ ሴሮ ላይ ትቃት ተሰንዝሮባቸው 10 የጭነትና 4 ብረት ለበስ መኪናዎች፤ እንዲሁም አንድ ጸረ-አውሮፕላን ወድመዋል

**22 ጥር 2013**
- ዳዕሮ ሓፋሽ፤ ሰመማ፤ ማህበረ ዴጎ፤ ፈረስ ማይ፤ ነበለት፤ ዕዳጋ ዓርቢ፤ ሓውዜን ላይ ውጊያ ቀጥሎ ነበር

**30 ጥር 2013**
- በሳምረ፤ ነቅሰገና ኮረም ቲዲኤፍ አንድ ከፍተኛና ሁለት መካከለኛ መአርግ ያላቸው የፌደራል መኮንኖችን  ገደሉ

**05 የካቲት2013**
- የቲዲኤፍ ሃይሎች ባንድ ጊዜ በበርካታ ግንባሮች እየተዋጉ ስለሆነ የፌደራል ሰራዊቱ ተጨማሪ ሃይል እንዲላክለት ጠየቀ

**07 የካቲት 2013**
- የፌደራሉ 32ኛ ክፍለጦር ሳምረ ላይ ተደመሰሰ

**08 የካቲት 2013**
- ከፌደራሉ 32ኛ ክፍለጦር የተረፉትና የ11ኛ ክፍለጦር አንድ ብርጌድ ግጀት ላይ ተደመሰሱ
- ማይቅነጣል 2000 የኤሪትርያ ወታደሮች ተገደሉ
- ከአራት ቀን ጦርነት በኋላ ቲዲኤፍ ሳምረ፤ ግጀት፤ ማይቅነጣልን ተቆጣጠረ
- የፌደራል መከላከያ መቐለ ዙሪያ ምሽግ መቆፈር ጀመረ

**09 የካቲት 2013**
- ሽሬና ወጀራት ላይ ውጊያ እየተካሄደ ነበር

**20 የካቲት 2013**
- በመላ ትግራይ በተለይ በማእከላዊ ዞን ጦርነት እየተጧጣፈ እንደሆነ ተዘገበ

**25 የካቲት 2013**
- ቲዲኤፍ አላጀ ላይ የፌደራልና የኤሪትርያን ጦር ጥቃት

| | |
|---|---|
| | መክቶ 640 ወታደሮችን ገድሎ 1000ውን አቁስሏል<br>• የፌደራሉ ሃይል ማይ መገልታ በቲዲኤፍ በተቀበረ ፍንጂ አንድ መኪና ሲወድም፤ 8 ወታደሮች ተገድለው፤ 9 ቆስለዋል፡፡ |
| **26 የካቲት 2013** | • ቲዲኤፍ ቀይሕ ጎቦ/ ሳምረ ላይ የደረሰበትን ጥቃት ከመከተ በኋላ ከ100 በላይ የሆኑ የፌደራሉና የኤሪትርያ ወታደሮችን ገድለዋል |
| **30 የካቲት 2013** | • የፌደራሉ ጦሩ ከዓብዪ ዓዲ ለቆ ወጣ |
| **26 መጋቢት 2013** | • በስምንት ጦር ግንባሮች እየተዋጋ እንደሆነ አቢይ አህመድ አመነ |
| **12 ሚያዝያ 2013** | • በማእከላይና በሰሜን ምእራብ ትግራይ ውጊያ ቀጥሏል<br>• ቲዲኤፍ አንድ ኤም አይ 35 ሄሊኮፕተር ጉያ ላይ መትቶ ጣለ፤ የምስራቅ አየር ምድብ ምክትል አዛዥ የነበረውንም አብራሪ ገድሏል |
| **18 ሚያዝያ 2013** | • ቲዲኤፍ አማራ ክልል ወስጥ ገብቶ፤ የአማራ ልዩ ሃይልንና ከባድ መሳሪያቸውን ከደመሰሰ በኋላ የጦር መሳሪአና መድሃኒት ማርኳል |
| **10 ሰኔ 2013** | • ቲዲኤፍ ሸውዓተ ሕጉም (የጭላ) ላይ የፌደራሉን ሰራዊት አሸነፈ |
| **14 ሰኔ 2013** | • ቲዲኤፍ ዓዲግራትና ውቕሮን ሲቆጣጠር በርካታ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን አውድሞ ወታደሮችን ማርኳል |
| **11– 21 ሰኔ 2013** | • በተምቤን ጦርነት የፌደራልና የኤሪትርያ ጦር ተሸነፈ<br>○ የኢትዮጵያ ክፍለጦሮች 11፣20፣21፣24፣25፣31፣32፣<br>○ የኤሪትርያ ክፍለጦሮች 21፣ 32<br>○ ቲዲኤፍ 10000 ወታደሮች ገድሎ 3356 ማርኳል |
| **14 ሰኔ 2013** | የኢትዮጵያ አየር ሃይል ሎክሂድ ሲ-130 ሄርኩለስ አውሮፕላን በቲዲኤፍ ተመታ ወደቀች |
| **19 ሰኔ 2013** | • የትግራይ ሃይሎች መቐለን ተቆጣጠሩ |

# ምዕራፍ ፯

# ጅምላ ግድያ በትግራይ ጦርነት

**አንቶኒ ጆን ብሊንከን** (የአሜሪካ የወጪ ጉዳይ ሚኒስትር 01/ 07/ 2013)

“በተለይም በትግራይ ስላለው ሁኔታ በጣም ተአማኒነት ካለው መረጃ የሰብአዊ መብት ረገጣና ግፍ እያየን ነው። ወደ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በተለያዩ አጋጣሚዎች ስልክ ደውዬ ነበር። ከክልሉ፤ ከአህጉሪቱና ከአካባቢው መሪዎች ጋር ተነጋግሬአለሁ፡፡ ዛሬ በትግራይ ያለው ሁኔታ ተቀባይነት የለውም፤ እናም መለወጥ አለበት፡፡ ከኤሪትርያ የመጡ ሃይሎች አሉ፤ ከአማራ ክልል የመጡ ሃይሎችም አሉ። መውጣት አለባቸው። ኃይሎቹ በምዕራብ ትግራይ ያየነውን አይነት የትግራይን ሕዝብ ሰብአዊ መብት መርገጥ አይችሉም፤ የዘር ማፅዳት መፈጸም አይችሉም፡፡ ይህ መቆም አለበት። ስለተፈጠረው ሀሉ ተጠያቂነትና ገለልተኛ ምርመራ ያስፈልገናል።”

**"ከዚች ምድር እናጠፋችኋለን"** (የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ሪፖርት)

“በምዕራብ ትግራይ አዲስ የተሾሙ ባለስልጣናትና ከአጎራባች የአማራ ክልል የጸጥታ ሃይሎች፤ በኢትዮጵያ ፌዴራል ሃይሎች ድጋፍና ተሳትፎ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆችን ዛቻ፣ ህገወጥ ግድያ፣ ጾታዊ ጥቃት፣ የጅምላ እስር፣ በዘፈቀደ ከመኖሪያ ቤታቸው አፈናቅለዋል፤ እንዲሁም ዘረፋ፣ የግዳጅ ዝውውርና የሰብአዊ እርዳታ መከልከልን ፈጽመዋል። እነዚህ በትግራይ ሲቪል ህዝብ ላይ የተስፋፉት ስልታዊ ጥቃቶች በሰው ልጆች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችና የጦር ወንጀሎች ናቸው።

<u>ማስታወሻ</u>፡-

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የጅምላ ግድያዎች አባይን በጭልፋ ያህል ናቸው፤ ለአለም አቀፍ ሚድያ የበቁትን እንጂ ቀሪው ሚልዮን ቤቱ ይቁጠረው፡፡

**<u>የሲቪሎች የጅምላ ግድያ ዋና ምክንያቶች</u>፡-**

- በዛው ቀን ወይም ከዚያ በፊት በተደረጉ ውጊያዎች ሲሸነፉ ለመበቀል
- የህወሓት መሪዎች የት እንዳሉ በማሸበር መረጃ ለማውጣት
- የህወሓት ታጋዮች ቤተሰብ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎች
- ባጠቃላይ መላውን የትግራይ ማህበረሰብን ለማሸበር

1. **<u>የማይ ካድራ እልቂት</u>**

- ማይ ካድራ በምእራብ ትግራይ ቃፍታ ሑመራ የምትገኝ ከተማ ናት
- ጥቅምት 30 እስከ 01 ቀን 2013፤ ከ600-1000 የሚጠጉ የትግራይ ተወላጆች በወራሪው የአማራ ጦር ተገድለዋል
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የትግራይ ተወላጆች በማይ ካድራ አማራን ጨፍጭፈዋል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል። "የአይን ምስክሮች"፣ ወታደራዊ አባላትና የመንግስት ባለስልጣናት "ትግሬዎች አማራን ገድለው ወደ ሱዳን አምልጠዋል" ይላሉ። ምንጮቹ የአንድ ወገን ናቸው፡፡

2. **<u>የዳንሻ እልቂት</u>** <u>(አኒስና ጓደኞች 2013፤ ትግሃት)</u>

- ዳንሻ በምእራብ ትግራይ ፀገደ ወረዳ በሰሜን አማራና በምእራብ ትግራይ አዋሳኝ አቅራቢያ የምትገኝ ከተማ ናት
- የአማራ ፋኖ ሚሊሻ ጥቅምት 30 እስከ 10 ህዳር 2013 በዘለቀው ግድያ 21 ሰላማዊ ዜጎችን ጨፍጭፏል
- ተጎጂዎች አብዛኛዎቹ በቢላዋ ተወግተዋል፤ በሜንጫ ተቆራርጠዋል
- የጭፍጨፋው ዋና አላማ የትግራይ ተወላጆች የዘር ማፅዳት ነበር

3. **<u>የሽግሊል እልቂት</u>** <u>(አኒስና ጓደኖች 2013፣ ጁልያ ስቲርስ፣ ኢሮብ.ኦርግ)</u>

- ሽግሊል በምዕራብ ትግራይ ዞን ቃፍታ ሑመራ ወረዳ የሚገኝ መንደር ነው
- ጥቅምት 30 እስከ 01 ህዳር 2013 የአማራ ፋኖ ሚሊሻ ሰባት የአንድ ቤተሰብ አባላትን ገደለ.
- ሚሊሻዎቹ ልብሳቸውን ገፈው ባደባባይ ከደበደቧቸው በኋላ ሁሉም ሞቱ

4. **<u>ሑመራ እልቂት</u>** <u>(ዴይሊ ቴሌግራፍ፣ ኒውዮርክ ታይምስ፣ ዘ ጋርዲያን)</u>

- ሑመራ በሱዳንና በትግራይ አዋሳኝ ላይ በተከዜ (አትባራ) ወንዝ ዳርቻ የምትገኝ  የስራ እንቅስቃሴ የሚበዛባት ከተማ ነች
- ህዳር መጀመሪያ 2013 ላይ ከአማራ ክልል የመጡ ቢላዋ የታጠቁ ሚሊሽያዎች የትግራይ ተወላጆች ላይ ጥቃት አድርሰዋል፡፡ ለምሳሌ

ታክሲው ውስጥ የትግራይ ፕሬዝደንትን ምሰል በፖስተር ለጥፎ ያገኙትን የታክሲ ሹፌሩንና ሁለት ሌሎች ሰዎችን ታክሲ ውስጥ ገድለዋል

- ሚሊሻዎቹ የሰዎችን ጭንቅላት በሜንጫ እየቆረጡ ነበር
- ፋኖዎች ሑመራን አጥፍተው ትግራውያንን እንዲጨርሱ ታዘዋል

5. **<u>የሽረ እልቂት</u>** (ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ዘ ጋርዲያን፣ ትግሃት)

- ሽረ የትግራይ ሰሜን ምዕራብ ዞን ዋና ከተማ ነው
- 08 ህዳር 2013 አስር ሰላማዊ ሰዎች በጥይት ተገደሉ
- የሽረ ኗሪዎች ግድያውን ለሚድያ የገለጹት እንደዚህ ብለው ነው፡- "ሰዎች እንደ ዶሮ እየታረዱ ነው"
- የፌደራልና የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ከተማ ውስጥ ከገቡ በኋላ 200 ሰዎች ገድለዋል
- አስከሬኖች ሳይቀበሩ ጅብ እንዲበላቸው ከወጪ ቀርተዋል
- አብዛኛው ግድያ የተፈፀመው በኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ነው
- ፋብሪካዎች፣ ሆቴሎች፣ መስጊድ፣ አብያተ ክርስቲያናትና የኮንዶሚኒየም ህንፃዎች በፌደራልና የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ወድመዋል
- ሁሉም የመንግስት ንብረቶች ወድመዋል ተዘርፈዋል

6. **<u>የውቅሮ እልቂት</u>** <u>(አኒስና ጓደኞች 2013፣ ፊረንሳይ 24)</u>

- ውቅሮ ከመቐለ በስተሰሜን 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት
- 18-19 ህዳር 2013 የፌደራልና የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ውቅሮ ከተማ ውስጥ ገብተው 245 ሰዎችን ገድለዋል።
- ወታደሮቹ ወደ ከተማዋ ሲገቡ ነዋሪዎች ወደ አካባቢው ተራራዎች ሸሹ
- የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት መኖሪያ ቤቶች፣ ባንኮችና ፋብሪካዎችን ዘረፉ

- የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት የህወሓት ደጋፊዎች ናቸው ብለው የጠረጠሯቸውን ወጣቶች እየተኮሱ ሲገድሉ ነበር

7. **<u>ዕዳጋ ሓሙስ</u>** <u>(አኒስ እና ሌሎች 2013፣ ዴይሊ ቴሌግራፍ)</u>

- ዕዳጋ ሓሙስ በትግራይ ምስራቃዊ ዞን የምትገኝ ትንሽ ከተማ ናት
- 12 ህዳር 2013 የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ከቲዲኤፍ ጋር ተዋግተው ከባድ ኪሳራ ከደረሰባቸው በኋላ ከ24 እስከ 30 ንፁሃንን ተገድለዋል

8. **<u>የዛላምበሳ እልቂት</u>** (ትግራይ ኦንላይን)


- ዛላምበሳ የሰሜን ትግራይ ከተማና ለኤሪትርያ ድንበር ቅርብ የሆነች ናት ከዓዲግራት ከተማ (ምስራቅ ዞን) በስተሰሜን 40 ኪሎ ሜትር ርቀት
- እልቂቱ የተፈፀመው 04-08 ህዳር 2013 ነው
- በ08ኛ ህዳር 2013 የፌደራልና የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ለ13 ተከታታይ ሰአታት ኢላማ-ቢስ የሆነ ድብደባ ካካሄዱ በኋላ ወደ ከተማዋ ገቡ
- ቤት ለቤት እየዞሩ ሰላማዊ ዜጎችን በዘፈቀደ ገድለዋል
- ቀብር በመከልከሉ ሬሳ በየመንገዱ ወድቆ በጅቦችና ውሾች ተበልቷል
- ከግድያዎቹ ሁሉ የሚዘገንነው፡-
  - ወታደሮች አንድ ቤት ውስጥ ገቡ
  - ሁለቱንም ባለትዳሮች ገደሉ
  - ቤቱ ውስጥ ሰፈሩ፤ ለ12 ቀናት ቆዩ
  - የቤተሰቡን ፍየሎች እያረዱ 30ዎቹን በልተዋል።
  - ሲጨርሱ የትዳር ጓደኞቹ አስከሬኖች እንዲቀበሩ ፈቀዱ

9. **<u>የቢሶበር እልቂት</u>** <u>(አኒስና ጓደኞች 2013፣ ፍራንስ 24፣ ዎርልድ ራዲዮ)</u>

- ቢሶበር በትግራይ ደቡባዊ ዞን ጨርጨር የሚገኝ መንደር ነው
- 05-08 ህዳር 2013 የፌደራል ሰራዊት አባላት መጀመሪያ መንደሩን በከባድ መሳሪያ ደብድበው 21 ሰላማዊ ሰዎችን ገደሉ፡፡
- ቀጥለው መንደሯን ከተቆጣጠሩ በኋላ 6 ተጨማሪ ሰላማዊ ሰዎችን ገደሉ

**<u>እልቂቶች በካርታ፤ ለካርታዎች የመረጃ ምንጮች፡-</u>**

አዲስ ስታንዳርድ፣ አፍሪካ ኒውስ፣ አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ፣ አልጀዚራ፣አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣አሶሴትድ ፕሬስ፣ ቤሊንግካት፣ክራይሲስ ግሩፕ፣ዴይሊ ቴሌግራፍ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት፣ ፋይናንሺያል ታይምስ፣ ፈረንሳይ 24፤ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ድንበር የለሽ ሐኪሞች፣ ሮይተርስ፣ የሁኔታ ሪፖርት የአውሮፓ የውጭ ፕሮግራም ለአፍሪካ፣ ስካይ ኒውስ፤ ዘ ጋርዲያን፤ዘ ኒው ዮርክ ታይምስ፤ዋሺንግቶን ፖስት፤ትግራይ ቲቪ፤ አኒስና ባልደረቦች



## 10. <u>የአኹሱም እልቂት</u>

(ማርቲን ፕላውት፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፤ አሶሴትድ ፕሬስ፤ ሬውተርስ፤ ለአፍሪካ የአውሮፓ የውጪ ፕሮግራም)

---

- አኹሱም በትግራይ መእከላዊ ዞን የምትገኝ ከተማ ነች። የጥንታዊቷ የአኹሱም መንግስት ዋና ከተማ ነበረች
- ከተማዋ በዚህ የአፍሪካ ክፍል ውስጥ በጣም ቅድስቲቱ ከተማ ናት ምክንያቱም ክርስትና የተጀመረባት በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው
- 19-20 ህዳር 2013 የአማራ-ኢትዮጵያ-ኤሪትርያ ጦር ትግራይን ከወረረ ከሶስት ሳምንታት በኋላ ታላቁ የክርስቲያን መቅደስ በደም ተጨማልቋል
- 09 ህዳር 2013 በአኹሱም ዙሪያ ያሉ ኮረብታዎች በታንክ፣ በመድፍና በጄት ተዋጊዎች ጥይትና በቦምብ ተደበደቡ። ትራንስፖርትና ኮሙዩኒኬሽን ተቋርጦ የትግራይ አስተዳደርና የጸጥታ ሃይሎች ከከተማው ለቀው ወጡ
- ከ10 ህዳር 2013 ጀምሮ የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ወደ አኹሱም ገብተው በየመንገዱ ያገኙትን በቀን አሥር ያህል ሰው ተኩሰው ገድለዋል
- የአኹሱም ሆስፒታልንም ዘርፈዋል
- ብዙ ሰዎች አኹሱምን ለቀው ሲሄዱ ሌሎች ደግሞ በቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተጠልለዋል
- የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ከተማዋን ለቀው ወጡ፤ ግን ከሳምንት በኋላ ተመልሰው በመምጣት በከተማዋ በሚገኙ ሱቆች ላይ ከፍተኛ ዘረፋ ጀመሩ ፣ሆቴሎችን፣የጌጣጌጥ ሱቆችን፣ ቡቲኮችን ወረሩ፤ ሁለት የዱቄት ፋብሪካዎችንም አወደሙ

- ሚሊሻዎችና የአኹሱም ከተማ ኗሪዎች ማይ ኩሆ (የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት የመሸጉበት) ላይ ጥቃት ሰንዝረው ብዙ የኤሪትርያ ሰራዊት አባላትን ገደሉ
- ለኤሪትርያ ሰራዊት ተጨማሪ የሰራዊት ድጋፍ ሲመጣ ሚሊሺያዎቹ አፈገፈጉ
- ከዛ ቀጥሎ የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት 19-20 ህዳር 2013 በሰላማዊ ሰዎች ላይ ማንም ሳይለዩ ተኮሱ፡፡ በዚህ ግድያ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጨፍጭፈዋል
- 21 ህዳር 2013 የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮችና የፌደራል ፖሊስ አባላት ደርሰው ህዝቡ አስከሬን እንዲሰበስብና እንዲቀብር የኤሪትርያ ሰራዊት አባላትን አሳመኑ
- ከአውቶብስ መናኸሪያ እስከ ፓርኩ ድረስ ያለው ከተማ በሙሉ በሰው አካል ተሸፍኗል
- የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት ከአራት አመት እድሜ በላይ የሆናቸው የትግራይ ተወላጆችን በሙሉ እንዲገድሉ መታዘዛቸውን ተናግረዋል።
- የኢትዮጵያ ወታደሮች ግድያውንና ዘረፋውን ለማስቆም ምንም አላደረጉም፤ የሞከሩት ማስጠንቀቂያ ስለተሰጣቸው
- 06 ታህሳስ 2013፤ አኹሱም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደብቀው የነበሩ 750 ሰዎች ቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት ባለው አደባባይ ላይ በኢትዮጵያ ወታደሮችና በአማራ ታጣቂዎች በጥይት ተገድለዋል

## 11. <u>የማህበረ ዴጐ እልቂት</u>


(ሲኤንኤን ኒማ ኤልባጊር፣ ጂኤንኤን፣ ትጋት-ሜይል፤ ኦንላይን-ራቸል ቡኒያን፣ ቢቢሲ፣ አኒስና ባልደረቦች 2013፣ ቤሊንግካት)

- ብዛት ያላቸው ያልታጠቁ ሰዎች መሳሪያ በታጠቁ ወታደሮች ታጅበው ሜዳ ላይ በሰልፍ ሲሄዱ ይታያል
- ይህ የሆነው 08-18 ጥር 2013 ባለው ጊዜ ውስጥ ነው


- ግድያ ቦታው ላይ ከደረሱ በኋላ ያልታጠቁቱ ሰዎች በወታደሮች ተከበው በረድፍ ተቀምጠዋል
- ወታደሮቹ የኢትዮጵያ ሰራዊት ዩኒፎርም ለብሰው አማርኛ ነበር የሚናገሩት
- አንድ ወታደር "እነዚህን ሰዎች ነፃ ልንልቅ አይገባም፤ አንዳቸውም እንኳ መዳን የለባቸውም" ሲል ይሰማል
- ሌላኛው ደግሞ "እነዚህ ሰዎች እንዴት እንደሚሞቱ በቪዲዮ መቅረጽ አለብን" ሲል ሃሳብ ያቀርባል
- ሰዎቹ ወደ ገደል አፋፍ ተመርተው ከሄዱ በኋላ ጭንቅላቶቻቸው ላይ ከጀርባ በጥይት ተመትተዋል
- ከዚያም ወታደሮቹ የተመቱት ሁሉም "መሞታቸውን አጣሩ" ተባሉ
- ወታደሮቹ "ሹተው! ሹተው! (በአራዳ ቋንቋ ተኩስበት ለማለት)፤ወታደሮቹ በሕይወት ያሉትን ተኩሰው ጨረሷቸው
- ቀጥለው በሙታኑ መሳለቅ ጀመሩ፡፡
- አንደኛው ወታደር እንዲህ ሲል ይሰማል፡-"እነዚህን ሰዎች የሚያቃጥል ጋዝ ቢኖር ጥሩ ነበር፤ እንደ ህንዶች ያቃጥሉ"
- የሟቾቹ አስከሬኖች መሬት  ላይ ተዘርረዋል፤ ወደ ገደልም ተወርውረዋል



## ትግራይ የሲቪሎች ጅምላ ግድያ 25 ጥቅምት-19 ህዳር 2013




## ትግራይ የሲቪሎች ጅምላ ግድያ 21 ሰኔ 2014–24 ጥቅምት 2015



## 12. ‘የተራሮቹ እልቂት” (ማርያም ደንገላት)

አርቫኒቲዲስና ባልደረቦች 13 መጋቢት 2013፤ በኒዒማ ኤልባጊር የተነገረው የቪዲዮ ታሪክ (ለአቀራረብ እንዲመች ሆኖ አጠር ብሎ ወደ ጽሁፍ የተቀየረ)



- ደንገላት በትግራይ ምስራቃዊ ዞን የምትገኝ መንደር ናት
- በ21 ህዳር 2013 ነዋሪዎች የጽዮን ማርያም አመታዊ በአል እያከበሩ ነበር
- የኤሪትርያ ወታደሮች መጥተው ሰላማዊ መስለው ቆሙ
- ያልጠረጠረው ህዝብ የኤሪትርያን ወታደሮች ወደ ድግሱ ጋበዛቸው
- ቆየት ብለው የኤሪትርያ ወታደሮች በምእመናኑ ላይ ተኩስ ከፈቱ
- ሰዎች በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ ቤቶች እየተሯሯጡ ሸሹ፤ ወደ ገደል ገብተውም ለማምለጥ ሞከሩ
- ወታደሮቹ ተከትለው ተራራውን በጥይት ረጨት
- የኤሪትርያ ወታደሮች ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ እየተሳደቡ “ውጡ” አሉ
- አንዳንዶቹ ሰዎች ሰላማዊ ሰዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ መታወቂያቸውን ይዘው ወደ ውጭ ወጡ፤ ግን ሁሉም በጥይት ተመትተዋል
- ወታደሮቹ ከውስጥ የቀሩትን እየጎተቱ፣ እጃቸውን አስረው፤ ሌሎች እንዲያስሩላቸውም እያስገደዱ ራስ ራሳቸው ላይ ተኩሰው ገደሏቸው
- ወታደሮቹ ጥይት ለመቆጠብ ሲሉ ነበር አስረው ጭንቅላት ላይ የተኮሱት
- እናቶች ልጆቻቸውን ለማሰር ተገደዱ፤ ከፊታቸው ላይም ተገደሉ
- በህይወት የተረፉት ሰዎች የተገደሉትን ጅቦች እንዳይበሏቸው አስከሬናቸውን ወደ ቤታቸው እየጎተቱ አስገቡ
- የኤሪትርያ ወታደሮች በአካባቢው እያሉ መቅበር ስላልቻሉ ሰዎቹ ከአስከሬኖቹ አጠገብ ተኝተው አድረዋል

- በ23 ህዳር የኤሪትርያ ወታደሮች ህዝቡ አስከሬኖችን ከቤተክርስቲያኑ አርቆ መደበኛ ያልሆኑ የቀብር ሥነ ሥርዓቶች እንዲፈጸም ፈቅደዋል፤ ነገር ግን ሲያዝን ያዩትን እንደሚገድሉ አስፈራርተዋል
- የኤሪትርያ ወታደሮች በህይወት የተረፉትን ሰዎች በአይነ ቁራኛ እያዩ ስለነበር እምባቸውን ተቆጣጥረው የህጻናትንና የታዳጊዎችን አስከሬን በመደርደር መታወቂያቸውን እየፈተሹ፤ የልብሳቸውንና የጸጉራቸውን ሁኔታ መዘገቡ
- ከሟቾቹ መካከል ካህናት፣ አዛውንት፤ ወደ ሃያ የሚሆኑ የሰንበት ተማሪዎች ይገኙበታል
- በደም የተነከረ ነጭ የቤተክርስቲያን ልብስ የለበሱ አስከሬኖች በየሜዳውና በየወንዙ ተበትነዋል ይታዩ ነበር
- ጥቂቶቹ ፊታቸው ላይ በጥይት ስለተመቱ ማንነታቸውን መለየት አልተቻለም
- የትናንሽ ልጆች አስከሬኖች በሁሉም ቦታ እጆቻቸው እንደታሰሩ ይታዩ ነበር
- መንደሩ በአስከሬን ሽታ ተበክሎ አሞራዎች ከላይ ይሽከረከራሉ፡፡ ይህ ያልተቆጠሩ ብዙ አስከሬኖች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚያሳይ ምልክት ነበር ለማምለጥ ሲሞክሩ ከሩቅ ሜዳ ላይ የተገደሉት ብዙዎቹ በአሞራ ተበልተዋል
- በጊዜያዊው የመቃብር ቦታ ብዙ አስከሬኖች ተቀበሩ፤ በአፈር፤ በእሾህና በዛፍ ቅርንጫፎች ተሸፍነዋል፡፡ ይህ የተደረገው እንዳይሆኑ ለመከላከል ነው።በጅቦች እና በአሞራዎች የተወሰዱ
- የተቀበሩት ሰዎች ጫማዎች የቤተሰባቸው አባላት ለመለየት እንዲረዳቸው በተቀበሩበት ላይ ተቀምጧል
- ከመቶ በላይ የሚሆኑ በጥይት ተመተው ተገድለዋል ተብሎ ይታመናል
- አዲስ የተጋቡ ጥንዶች ባል ከነፍሰ ጡር ሚስቱ ተነጥሎ ተገድሏል
- ቤተክርስቲያኑ በመድፍ ተኩስ ተመቷል

**13. የደብረ አባይ እልቂት** (የሚሞትን የሚሳደብ ወታደር) ትግሃት 08 የካቲት 2013

- በ27-28 ታህሳስ 2013 በምዕራብ ትግራይ ደብረ አባይ ገዳም አካባቢ እልቂት ተፈፀመ፡፡ የኢትዮጵያና የኤሪትርያ ሰራዊቶች ማይ ሀርማዝ ከተማን ከሩቅ መምታት ጀመሩ። በዚህም ቤቶች ወድመዋል ህፃናትም ተገድለዋል፤ከተማዋ ጋ ሲደርሱ ከትግራይ ሰራዊት ገጥመው ጦርነቱ ለሁለት ቀናት ቆየ

- በዚህ ጦርነት 500 የኢትዮጵያና የኤሪትርያ ወታደሮች ተገድለዋል
- ረዳት ሃይል ቢላክም ጦርነቱ ቀድሞውኑ አብቅቶ የትግራይ ሃይሎች ለቀዋል
- የተበሳጨው ረዳት ሃይል በከተማው ሲቪሎች ላይ ተኩስ ከፍቶ 100 የሚሆኑትን በጅምላ በመጨፍጨፍ ሱቆችንና ቤቶችን ዘርፏል



**የተጨፈጨፉት በቪዲዮ ቀረጻ**

- በቡድን ወደ 24 የሚጠጉ አስከሬኖች ይታያሉ
- አማርኛ ተናጋሪዎች ይሰማሉ፤ ወታደሮች መሆን አለባቸው
- ከመካከላቸው አንዱ (ቪዲዮ ቀራጩ) አንድ በህይወት የተረፈ ሰው አይቷል
- (ቪዲዮ ቀራጩ) "የተረፈውን ማስወገድ አስፈላጊ ይመስለኛል"
- (ቪዲዮ ቀራጩ) “በመጀመሪያ ለምን ገባህ?”
- (ቁስለኛ) "እዚህ ቤት አለኝ"
- (ቪዲዮ ቀራጩ) ወደ ሌላ አስከሬን እየጠቆመ “ይህ እንድትገባ ያደረገህ ነው?”
- (ቁስለኛ) "አዎ የኔ ነው"
- (ቪዲዮ ቀራጩ) በድጋሚ "ይህ ነው እንድትገባ ያደረገህ?"
- (ቁስለኛ)"አዎ የኔ ነው"
- አልተግባቡም
- (ቪዲዮ ቀራጩ) "አማርኛ አትናገርም?"
- (ቁስለኛ) "ከቤቴ አንዱ ይሄ ነው፣ ቆርቆሮ ያለው"
- (የሴት ድምፅ) “አማርኛ መናገር ይችላል”
- (ቪዲዮ ቀራጩ) “ተናገር በአማርኛ”
- (ቪዲዮ ቀራጩ) "እናትህን......."
- (በመሞት ላይ ያለ ተጎ) "እኽ!"
- (ቪዲዮ ቀራጩ) “ተናገር! ዉሻ ልጅ”

**14. አብዓላ/አፋር የድንበር ላይ እልቂት** አልጃዚራ (ሉሲ ካሳ)

- አብዓላ በአፋርና ትግራይ አዋሳኝ ላይ የምትገኝ ትንሽ ከተማ፤ ከመቐለ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ክልል ከመፈጠሩ በፊት አብዓላ "ሸኸት" በመባል ትታወቅ የነበረ ሲሆን የትግራይ አካል ነበረች። ስለዚህም 70 በመቶው የከተማው ህዝብ ትግራዋይ ነበር
- አፋሮች ደርግን በትጥቅ ትግል ለመጣል የህወሓት አጋሮች ነበሩ
- ከተማዋ በአፋር ክልል ስር ከሆነች በኋላ በአብዓላ በትግራይ ተወላጆች ላይ ምንም አይነት የደህንነት ችግር አልተፈጠረም
- ብልጽግና ፓርቲ ወደ ስልጣን ሲመጣ ከትግራይ ጋር ወዳጅ የነበረው የአፋር ገዥው ፓርቲ ወደ ብልፅግና ፓርቲ ተቀላቅሎ ከኤሪትርያ ጋር ተባብሮ ትግራይን ወጋ
- የአፋር ገዥ ፓርቲ የትግራይን ወረራ በማመቻቸትና በመሳተፍ ብቻ ሳይሆን ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ለስድስት ሚሊዮን ትግራይ የሚደርሰውን ሰብአዊ እርዳታ በመዝጋት በትግራይ ላይ ብዙ ጥፋት አድርሷል
- የወዳጅ ጠላት ለሆነው የአፋር ሚሊሻ ይህ በቂ አልነበረም። አብዓላ ከተማን ዘር ለማጽዳት በትግራይ ተወላጆች ላይ ግድያ ፈጽመዋል
- ከ15 ታህሳስ 2015 ጀምሮ የአፋር ሚሊሻዎችና የኤሪትርያ ወታደሮች ከአምስት ተከታታይ ቀናት በላይ በቀጠለው ዘመቻ የትግራይ ተወላጆችን ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ ፍጀጅተት ፈጽመዋል
- ወታደሮች ወደ ቤት እየገቡ፣ እየዘረፉ ልጃገረዶችን በቡድን ደፈሩ
- በኋላ በመቶዎች የሚቆጠሩ አስከሬኖች በየመንገዱ ተጥለው ታይተዋል፤ ወጣት ወንዶች፣ ህፃናትና ነፍሰ ጡር እናቶች ሳይቀሩ
- አንዲት ሴት ከቤቷ ወጥታ ከመሸሿ በፊት የባሏን አስከሬን እያየች ቀናትን አሳለፈች። የአፋር ሚሊሻዎችና የኤሪትርያ ወታደሮች ባለቤቷንና ሌሎች 11 የትግራይ ተወላጆችን ተኩሰው ገድለዋል፤ ከመካከላቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ አራት ወንዶች ልጆች ይገኙበታል፡፡

- በ278 ሰዎች ስም ዝርዝር መሞታቸው ተረጋግጧል፡፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ አስከሬኖች በቡልዶዘር ተሰብስበው ራቅ ባሉ ጉድጓዶች ውስጥ ተጥለዋል፤ አንድ ሰው ከ16 ቤተሰቡ ጋር ተገድሎ አስከሬናቸው ማይ ሸነላ ውስጥ ተጥሏል
- በመቶዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች በከባድ መኪናዎች ተጭነው በአፋር ዋና ከተማ ሰመራ ወደሚገኙ የእስር ካምፖች ተወስደዋል
- መቐለ አቅራቢያ ከአብዓላ እልቂት የተረፉት በአራት የተፈናቃዮች ማእከላት ተጠልለዋል፡- ወደ 7000 የሚጠጉ ሰዎች 26 የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎችን ጨምሮ፡፡
- በተፈናቃይ ማእከላት የነበሩ ሰዎች ያዩትን ካዩ በኋላ ወደዛው የሚመለሱበት ምንም ነገር እንደሌለ ተናግረዋል

**15. የቶጎጋ ገበያ እልቂት** (አሶሴትድ ፕሬስ 16 ሰኔ 2013)

- በቶጎጋ መንደር (ከመቐለ 60 ኪሎ ሜትር ይርቃል) በተጨናነቀ ገበያ ላይ በአየር ድብደባ ቢያንስ 51 ሰዎች ሲሞቱ ከ100 በላይ ሰዎች ቆስለዋል (50 ከባድ)፤ ቢያንስ 33 ሰዎች ጠፍተዋል
- ከቆሰሉት የ2ና የ6 አመት ህጻናት ይገኙበታል
- ከቆሰሉት 25 በላይ የሚሆኑት በሚቀጥለው ቀን ሆስፒታል ደረሱ
- የህክምና ቡድኖች ወደ ቦታው እንዳይሄዱ በወታደሮች ተከልክለዋል
- ወደ ቶጎጋ ለመድረስ ሲሞክሩ የነበሩ አምቡላንሶች ከመቐለ በ25 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በወታደሮች ወደ ኋላ ተመለሱ
- የሄደ ሁሉ የህወሓት ታጋዮችን ይረዳል ብለዋል
- መንገዱ ለሁለት ሰዓታት ያህል ተዘግቶ ነበረ፤ በመንገድ አንድ ሕፃን ሞተ
- አንድ የሕክምና ሠራተኞች ቡድን በተለየ መንገድ ወደ ቦታው ደረሰ
- የቀይ መስቀል አምቡላንስ ወደ ስፍራው ለመድረስ ሲሞክር በወታደሮች በጥይት ተመትቷል
- የአውሮፓ ህብረት ሆን ተብሎ ሲቪሎችን ማጥቃትን አጥብቆ አውግዟል

**16. የደደቢት እልቂት "የት እንሂድ?"** (ዋሽንግተን ፖስት፤ ሂዩማን ራይትስ ዎች)

- በ15 መጋቢት 2014 የኢትዮጵያ ሰው አልባ አውሮፕላን የደደቢት ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢን ሶስት ጊዜ መታ
- የተፈናቀሉ የትግራይ ተወላጆች በተለይም አዛውንቶች፣ ሴቶችና ህጻናት በፕላስቲክ ድንኳን ውስጥ እና በትምህርት ቤት ህንጻ ውስጥ እንዳሉ ህይወታቸውን አጥተዋል
- የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ቀንድ ዳይሬክተር ድርጊቱን አውግዘዋል



- **በህይወት የተረፈ ሰው ምስክርነት፡-**
  - ወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ገና ሌሊት ነበር
  - የመጀመሪያው ድብደባ ሲደረግ እኔ ከቤተሰቦቼ ጋር ተኝቼ ነበር
  - እሳት የመታን ያህል ተሰማኝ
  - እየሆነ ያለውን ሳላውቅ ተነሳሁ
  - ምን እየተፈጠረ እንዳለ ሳልገነዘብ ሁለተኛው ድብደባ ተከሰተ
  - ከዛ ሶስተኛው
  - መጀመሪያ ላይ በካምፑ ውስጥ ጦርነት የተቀሰቀሰ መስሎኝ ነበር
  - ከዚያ በኋላ ግን አካላት ተበታትነው፣ ራሶች ተለያይተው አየሁ

**17. የዓዲ ዳዕሮ እልቂት** (ቢቢሲ 17 ጥቅምት 2015)

- ከሽረ በስተሰሜን ምዕራብ በምትገኝ ከተማ የአየር ድብደባ ተፈጸመ
- ከባድ ውጊያ ወደሚካሄድበት ግንባር ቅርብ ነበር
- ቢያንስ ስምንት ሰዎች ሲሞቱ ከአስር በላይ ቆስለዋል



- አንድ በህይወት የተረፈ ሰው እንዲህ አለ፡-
  - ከልጆቼ ጋር ቴሌቪዥን እየተመለከትኩ ሳለ የአየር ጥቃቱ ቀበረን
  - እኛን ለመቆፈር መጡ በመጀመሪያ ልጆቹን እንዲያድኑ ጠየቅኳቸው
  - ነፍሰ ጡር ሴት ልጄ ራሷን ስታ ወደ ውጭ ተጎትታለች
  - የልጅ ልጄ ወዲያው እንደሞተ ነገሩኝ

**18. የአዩሲድ. ቤኒሻንጉል የተጋሩ ወጣቶች ጥብስ**

(ትግሃት.03.መጋቢት.2014፤ማርቲን.ፕላውት/ሓርነት.ኦርግ06መጋቢት.2014፤ ቢቢሲ.አማርኛ.ዜና፤ ኢትዮ360፤ ሬውተርስ 03.መጋቢት.2014 )

https://www.tghat.com/wp-content/uploads/2022/03/10000000_1112200552894096_5850767328899841335_n.mp4



- በ03 መጋቢት 2014 አማርኛ ተናጋሪ የኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች ዩኒፎርም ለብሰው የትግራይ ተወላጆችን በቁም ሲያቃጥሉና ሲያፌዙ የሚያሳይ አስደንጋጭ ቪዲዮ በማህበራዊ ሚዲያ ወጣ
- ከግልገል በለስ ከተማ ወደ ህዳሴ ግድብ ሲጓዝ በነበረ የኢትዮጵያ ወታደሮች ኮንቮይ ላይ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሰራዊት ጥቃት ተፈጸመ፡፡ ጥቃቱን ተከትሎ 12 (13) የትግራይ ተወላጆች በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዳንጉር ወረዳ ታስረዋል

- ሌሎች ደግሞ ትግራይ ተወላጆቹ በቁጥጥር ስር የዋሉት የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ ሳይሆን በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እንደሆነ ቀደም ብለው ተናግረዋል

- በአካባቢው የደቡብና የአማራ ልዩ ሃይሎች አንድ ላይ ሆነው እንደሚንቀሳቀሱ ተነግሯል፡፡ በቪድዮው ላይ እንደሚታየው የወታደሮቹ ዩኒፎርም ከደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች የተውጣጡ ልዩ ኃይሎች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ብሄራዊ መከላከያ ሰራዊት ዩኒፎርምም ታይቷል፤ የአማራ ክልል ልዩ ሃይልና የፋኖ አከራሪዎችም ጭምር

- ቪድዮው ላይ ተጎጂዎቹ የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው የሚያመለክተው ወንጀለኞቹ “ጁንታ” እያሉ ሲጠሯቸው ስለነበረ ነው፡፡

- ወታደሮቹ በኦነግና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ሃይሎች ለደረሰባቸው ጥቃት 12ቱ የትግራይ ተወላጆች ላይ የ”አጸፋ” እርምጃ ወሰዱ። “አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ” እንደሚባለው ከኦሮሞና ቤኒሻንጉል ሰዎችን ላለመንካት

- ቪድዮው የጸጥታ ሃይሎች ክፉኛ የተደበደበውን ሰው ወደ እሳቱ ሲጎትቱ ያሳያል፡፡ ተጎጂው ራቁቱን ይመስላል፤ አንድ ሰው የልብሱን ቁራጭ በእንጨት ላይ አንጠልጥሎ ይታያል

- ሶስት ወይም አራት አዲስና በከፊል የተቃጠሉ የወንዶች አካላት በእሳቱ ውስጥ ይታያል፡፡ አንዱ ወታደር ስለተቃጠሉት ሌሎች ሰዎች ማንነት ሲናገር “የሱ ናቸው“ ይላል (ወደ እሳቱ እየተጎተተ ያለው ሰው ወንድሞች/ጓደኞች ናቸው ማለቱ ነበር)

- ቀጥሎ የሚጎትቱትን ሰው ወደ እሳቱ ለመጣል “ብድግ አድርገው! ብድግ አድረገው! አንድ፤ ሁለት፤ ሶስት!” ብለው ቆጥረው በህይወት ያለውን ሰው ከሚንቀለቀለው እሳት ላይ ወረወሩት፤ ደረቅ ሳርና ማገዶም ጨመሩበት

- ተጎጂው ከእሳቱ ለመውጣት ሲታገል ይታያል፤ ገዳዮቹ በዱላ ወደ እሳቱ ገፍተው ይመልሱታል፡- “ግባ! እናትክን...!”፤ ማገዶና ሣርም ይጨምራሉ

- “አቃጥለው! አቃጥለው! ሳሩን አንሳና ጨምር!” ይሉና እርስ በርሳቸው ግን “እናንተ ከጪሱ ላይ ዞር በሉ! አንተ ውጣ ከዚህ ጭስ ላይ!” እየተባባሉ ይጯጯሃሉ፤ ጎማ እያቃጠሉ ያሉ ይመስል፤ እነሱ እንዳይታመሙ!

- ወታደሮቹ ትናንት በነበረው ጥቃት ሻለቃቸው ተገድሎ ነበረና በቪዲዮው ላይ እንደሚሰማው የበቀል እርምጃ መሆኑ ያመለክታል፡- “ትናንትና ያቃጠሉን በዚህ መንገድ ነበር! ሻለቃን ያደረጋችሁት ይህንን ነው”

- አንዱ "አልሞተም እሳካሁን" ይላል፤ ሌላው ደግሞ "ሞራ ሆነ" ብሎ ይቀልዳል፡፡ ወንጀለኞቹ በተቃጠሉት አካላት ላይ ይሳለቃሉ።
- አቃጣዮቹ ተጎጂውን እየተቃጠለ እንዲናገር ይጠይቁታል፡-"ተናገር!" ተጎጂውም እሳት እያንከባለለው "ምን ልነግርህ እችላለሁ? እባካችሁ!"
- ከወንጀለኞቹ አንዱ፡- "የተጠበሰ ሥጋቸው እንዴት እንደሚጣፍጥ፤ በእንጀራ ይሻላል?" ሲል ሌላው ጓደኛው "በዳቦ የተሻለ ነው" ሲል መለሰ
- ቪድዮው መጨረሻ ላይ ሁለት ሰዎች እንዲህ ተባባሉ፡- አንደኛው "ፈጣሪየ እየቆየህ ምን ታሳየኛለህ?" ሲል ሌላው "በጣም!" ይላል፡፡ ምን ማለት ይሆን?

**19. የምእራብ አባያ እልቂት** (ካትሪን ሁሬልድ፤ዋሽንግተን ፖስት 25 ህዳር 2015)

- ምእራብ አባያ በደቡብ ኢትዮጵያ በጋሞ ጎፋ ዞን የሚገኝ ወረዳ ነው፤ ስሙ እንደሚያመለክተው የአባያ ሃይቅ ምእራባዊ ዳርቻ ነው፤ ቦታው በሰፋፊ የሙዝ የአትክልት ስፍራዎች ይታወቃል
- ከ2000 እስከ 2500 የሚደርሱ በስራ ላይ የነበሩና ጡረታ የወጡ የትግራይ ተወላጅ ወታደሮች ከታሰሩባቸው እስር ቤቶች አንዱ የምእራብ አባያ እስር ቤት ነው
- ብዙዎቹ በሱዳንና በሶማሊያ ሰላም በማስከበር አገልግለዋል፡፡ አንዷ ሴት ሻለቃ በሱዳን ሰላም አስከባሪ ሆና አገልግላለች፣ ሌላ ሻለቃ ደግሞ በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ የሚያስተምር መሃንዲስ ነበር። በአቢዬ የዩኤን ሰላም አስከባሪም ነበር
- የታሰሩት የትግራይ ወታደሮች ህዳር 2014 የቅዱስ ሚካኤልን በአል ሲያከብሩ በነበረበት ነው ግድያው የተጀመረው
- ከፊሎቹ በጠባቂዎቻቸው በጥይት ተመትተው የተገደሉ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በዙሪያው ወደሚገኘው ጫካ ሮጡ። የአካባቢው ነዋሪዎች ሲያገኙ እርዳታ እንዲሰጧቸው ለመኑዋቸው። በተቃራኒው የአካባቢው ነዋሪዎች "የሚገባችሁን እንሰጣቹኋለን" ብለው እስረኞችን ማጥቃት ጀመሩ
- የከተማው አስተዳዳሪዎች ኗሪዎች እስረኞቹን እንዲገድሉ ለመቀስቀስ ድምጽ ማጉያዎችን ተጠቅመዋል፡፡ ያመለጡት የጦር እስረኞች መሆናቸውን በጦርነቱ ወቅት ከአካባቢው የዘመቱትን ወገኖቻቸውን የገደሉ እንደሆኑ በተሳሳተ መንገድ ተነግሯቸዋል።

- ከ150 እስከ 200 የሚጠጉ ሰዎች ያመለጡትን እስረኞች በሜንጫ፣ በዱላና በድንጋይ ደበደቡዋቸው፡፡ ሰፈሩ በሬሳ ተጥለቀለቀ፣ አስከሬኖችም እንደ እንጨት ተደራርበው ነበር፡፡ እስረኞች ከህዝቡ ለማምለጥ ሲሉ በአዞ ወደ ተበከለው አባያ ሀይቅ ሮጠው ገቡ
- ጥቃቶች እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ቀጥለው ነበር፡፡ አብዛኞቹ የተገደሉት ምህረትን እየለመኑ እያሉ ነው። ወደ 83 የሚጠጉ እስረኞች ሲሞቱ ሌሎች ጠፍተዋል፡፡ አገዳደሉ የሚዘገንን ነበር፡=
    - የሴት ድምፅ ይሰማል "ልጄ ሆይ! ልጄ!" የሚል፤ ቀጥሎ የጥይት ድምጽ ተሰማ እሷም ሞተች
    - አንድ እስረኛ እጆቹ ተቆርጠዋል፤ እግሮቹም እየደሙ ነበር፤ እንዳይገድሉት ሳይሆን እንዲገድሉት ይማጸናል
    - ገዳዮቹ ግን ተጎጂውን መንገዱ ላይ ወታችና ወደላይ እየጎተቱ "ቀስ በቀስ ነው የምንገድልህ" አሉት
    - በመጨረሻም ወደ እስር ቤቱ በር እየጎተቱ ወስደው በጥይት ገደሉት
    - አንድ ሌላ እስረኛ ደግሞ ከሞተር ሳይክል ጀርባ እየተጎተተ ነበር
- አስከሬኖች እስር ቤቱ በር ጥግ በኩል በተቆፈረ የጅምላ መቃብር ውስጥ ተጥለዋል። መቃብሩንና ግቢውን ፎቶግራፍ ማንሳት አልተፈቀደለትም

---

❖ **በጅግጅጋ፣ በሀዋሳ፣ በዲዴሳና በብላቴ** አካባቢ በነበሩ እስር ቤቶችም ግድያ ተፈጽሟል፡፡ ብዙዎች የራሳቸውን መቃብር እንዲቆፍሩ ተጠይቀው ነበር፡፡ ህይወታቸው ካለፈ በኋላም ለረጅም ጊዜ ጥይት ይተኩሱባቸዋል፤ ጥይቱ ከመብዛቱ የተነሳ አስከሬኖቹ ተበጣጥሰዋል፡፡ ሬሳቸውን ከእስር ክፍሉ እየጎተቱ በማውጣት ለጅቦች ወደ ውጭ ይጥሉ ነበር

**20**. ***የወረታ ግድያ*** (04 ሃምሌ 2013 ኤቨሪቦዲ ዊኪ፤ ኢ.ኢ.ፒ. ኤ የሁኔታ ሪፖርት)

- ወረታ በባህር ዳርና ጎንደር ዋና መንገድ ላይ የምትገኝ መካከለኛ ከተማ ነች፤ በወረታ-ወልድያ በአዲስ አበባ-ጎንደር አውራ ጎዳናዎች መጋጠሚያ ላይ ትገኛለች፤ ለጭነት መኪና አሽከርካሪዎች አንድ ምሽት የሚያድሩበት ታዋቂ ፌርማታ ነች።

- ከወረታና አካባቢው ፎገራ ወረዳ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሚሊሻ በትግራይ የሚትገኘውን ዲማ ወረዳ ከተማ የሆነችው ፊየል ውሃን ተቆጣጥሮ ነበር፡ ፡ ሆኖም በ03 ሐምሌ 2013 በትግራይ መከላከያ ሰራዊት ተሸነፈ፤ የፎገራ ወረዳ የሰላምና ደህንነት ቢሮ ሃላፊም ተገድለዋል

- በፍየል ውሃ ጦርነት የሞቱት የአማራ ሚሊሻ አስከሬኖች ወረታ ከተማ ሲመለሱ ነበር በትግራይ ተወላጅ ኗሪዎች ላይ የበቀል ግድያ የተጅመረው፡፡ ሶስቱን ገድለው አስከሬናቸውን ከሶስት ባጃጅ ባለሶስት ጎማዎች ጀርባ አስጎተቱ፡፡ ሟቾቹ፡- ሰዓረ አረጋይ፤ ጎደፋይ ተኸለ፤ ርግበ ዓወት

- ከዛም በከተማው የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች መኖሪያ ቤቶች፣ ሆቴሎችና ሌሎች የንግድ ተቋማት በአማራ ወጣቶች ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል፣ ወድመዋል

**21. የፕሮፌሰር መዓርግ አማረ ግድያ** (አዲስ ስታንዳርድስ 11 ታህሳስ 2015)

- ፕሮፌሰር መዓርግ አማረ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኬሚስትሪ ትምህርት ክፍል የኬሚስትሪ መምህር ነበር፡፡ በአካባቢው ያለውን ሙያውን የሚመለከት ትምህርት አሰጣጥ ለማሻሻል የሚጥር የአማራ ክልል የትምህርት ዘርፍ አጋዥ ክንድ ነበር

- ሽልማት ሲገባው ለሞት ያበቃችው ግን አንዲት "ችግር" ነበረችበት፡- የትግራይ ተወላጅ መሆኑ፡፡ በስተቀረ ብዙም ወደ ትግራይ የሚያደላ ሃሳብም ተግባርም አይታይበትም ነበር

- በ14 ነሃሴ 2013 የፖሊስ መኮንኖች እሱ በሌለበት እየፈለጉት ነበር፤ በንፁህነቱ ሙሉ በሙሉ በመተማመን በሆነው ነገር አልተደናገጠም፡፡ እንደ አንድ ህግ አክባሪ ዜጋ ፕሮፌሰር መዓርግ ባህር ዳር ልዩ ዞን ፖሊስና ጸጥታ ጽህፈት ቤትን፤ የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን በመሄድ ሃላፊዎችን አነጋግሯል

- በ29ና 30 መስከረም 2014 ከ50,000 በላይ ተከታዮች ያሉት "ቢዲዩ ስታፍ" የፌስቡክ አካውንት መዓርግ አማረን በሚወነጅሉ ቃላት ማስፈራሪያ ተጻፈ፡- "…በምስራቅ አማራ ወሎ ጦርነትን በመምራት የትግራይን ሃይል በገንዘብና በቁሳቁስ ሲደግፍ ቆይቶ ወደ አሜሪካ የተሰደደ የትግራይ ተወላጅ ነው"

- በ24 ጥቅምት 2014 ፕሮፌሰር መዓርግ ባህር ዳር ከተማ ውስጥ ከሚገኘው ቤቱ  ፊት ለፊት በጥይት ተመቶ ወደቀ። የአማራ ልዩ ሃይል የደንብ ልብስ የለበሱ ሶስት ታጣቂዎች ነበሩ የተኮሱበት። ከገዳዮቹ አንዱ ጭንቅላቱን በጭንብል ሸፍኖ ነበር

- ፕሮፌሰሩን ወደ ሆስፒታል ሊወስዱ የሞከሩ የአካባቢው ሰዎች በታጣቂዎቹ ተከልክለዋል። የእርዳታ ጥሪም ሆነ አስከሬኑን መሸፈን አልፈቀዱም፤ አስከሬኑን ‘ጁንታ’ ብለው ጠሩት

- የፕሮፌሰር መዓርግ ባለቤት የሟቹን ማንነት ማረጋገጥ ተገዳለች። ገዳዮቹ የሷን ዘር እንድትነግራቸው በጩኸት ይጠይቃሉ፡፡ እርሷንም እንዲገድሏት ብትማጸንም ‘ጁንታ’ ብለው እየጠሯት ጥይታቸውን ማባከን እንደማይፈልጉና ህይወቷን ሙሉ እንድታለቅስ እንደሚፈልጉ ነገሯት

- አስከሬኑ ለሰባት ሰአታት ከወደቀበት ከቆየ በኋላ ማዘጋጃ ቤቱ ባልታወቀ መቃብር ስፍራ ቀብሮታል፡፡ ፖሊስ የፕሮፌሰር መዓርግን ሚስት ወስዶ ለሁለት ቀናት እስር ቤት አቆያት። ነፍሰ ገዳዮች የተጎጂዎችን የግል መኪና ወሰዱ

- በፕሮፌሰር መዓርግ ግቢ ውስጥ በሚኖሩ ተከራዮች በመታገዝ ወንጀለኞቹ ገንዘብ፣ ጌጣጌጥ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ የቤት እቃዎች፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ መጽሃፎችና ሰነዶችን ወስደዋል፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ የአማራ ልዩ ሃይል የፕሮፌሰር መዓርግን መኖሪያ ቤት ወርሶ ባለቤቱን ከተማዋን ለቃ እንድትወጣ አስገደደ

- የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲም ሆነ የአማራ ክልል አስተዳደር በግድያው ላይ መግለጫም ሆነ ምርመራ እንዲደረግ ትእዛዝ አልሰጡም። ዩኒቨርሲቲው የጋዜጠኞችን ጥሪና ኢሜል መልእክቶችን ውድቅ አድርጓል

- ፌስቡክ ፕሮፌሰር መዓርግን ለሞት ያበቃውን ውንጀላ ቀድሞ ባለማስወገድ ለሞቱ ተጠያቂ ነው ተብሎ ተከሷል

## 22. የታጠቀ ረሃብ፡-“ሰላማዊው” እልቂት



## “እንደ ቅጠል መርገፍ”፡- በትግራይ በረሃብ ምክንያት የዘር ማጥፋት ወንጀል

ሮይተርስ፣ ግሎብ ኤንድ ሜይል፣ ዘ ኢኮኖሚስት፤ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር፣ ፈረንሳይ 24፣ ሪሊፍ ዌብ፣ (አና ካራ)፣ አሶሴትድ ፕሬስ፤ ኦቻ፣ ዎርልድ ፒስ ፋውንዴሽን፣ ፒ.ቢ.ኤስ፣ ሂዩማን ጂኦግራፊ (ተከለሃይማኖት ገብረማርያም)፣ አልጀዚራ እንግሊዝኛ፤ ፋሚን ኤርሊ ዎርኒንግ ሲስተምስ፣ ቢቢሲ፣ ዳብሊው.ኤፍ.ፒ

---

- ህዝብን መፍጀት የሚፈልጉ ዲያብሎሳዊ ሃይሎች እንደ ረሃብ ያለ አመቺና ወጪ የሌለበት መሳሪያ አያገኙም፡፡ ረሃብ ስለማይጮህ አያሳጣም፡፡ ለሚድያ የሚበቃውም ዘግይቶ ነው፤ ወይም አይደርስም
- በረሃብ ህዝብን መፍጅት የሚቻለው ምሽግ ሳይቆፍሩ፤ ሳይሞቱ ሳይቆስሉ፤ ጥይት ሚሳይል ታንክ ሳይገዙ፤ እየበሉ እየጠጡ እየተዝናኑና ጥሩ እንቅልፍ እየተኙ ነው
- ይህንንም የሚያገኙት ልክ የሚጎዳቸው ነገር ያለ ይመስል ተግደርድረው፤ ተከራክረው፤ ተደራድረው ነው በጦር መሳሪያ የተደግፈውን እልቂት የሚያቆሙት፡፡ በሰላም የተደገፈው እልቂት ግን ይቀጥላል፤ አለም ስለ ሰላም ስምምነቱ ደስታዋን ትገልጻለች፤ የጥይት ጩኸት ካልተሰማ ሀዝብ ይረሳል!
- በትግራይ ጦርነት እስከ ግማሽ ሚሊዮን የሚደርሱ በጥይትና በረሃብ አልቀዋል። መጋቢት 2014 እንደተዘገበው በትግራይ 90 በመቶው ህዝብ የምግብ እርዳታ ፈላጊ ነበር፤ ለከፍተኛ ረሃብ የተጋለጡት ደግሞ እስከ 47 በመቶው ደርሷል፡፡ በሌላ ግምት 4.5 ሚሊዮን ሰዎች አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል
- የፌደራል መንግስት ባለሥልጣናት ለዚህ ምግብን የማገድ ድርጊታቸው የሚሰጡት የማያላውስ ወታደራዊ ምክንያት ነው፡፡ ህዝብ አስርቦ መፍጀትን “አመጸኞቹን ማስራብ” የሚል አሳሳች ስም ሰጥተውታል፡፡ በመሰረቱ አመጸኛ አይራብም፤ ከልካዮቹ ማን እንደሚሞት ያውቃሉ
- የኢትዮጵያና የኤሪትርያ መንግስታት ሆን ብለው የእርዳታ አቅርቦቶችን በማደናቀፍ ለረሀብ መንስኤ ሆነዋል፤ 80 በመቶ የትግራይ ህዝብ በሰብአዊ እርዳታ ሊደረስ አልቻለም፡፡ በክልሉ በየ48 ሰከንድ አንድ ሰው

በረሃብ እየሞተ ነው ተብሏል። በጥቂት ወራት ውስጥ አንድ ሚሊዮን ሰዎች ሊሞቱ ይችላሉ የሚል ግምት ነበረ

- <u>የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት፡-</u> "1.8 ሚሊዮን ሰዎች በረሃብ አፋፍ ላይ ነበሩ"፡፡ የተፈናቀሉት ሰዎች ካምፕ የደረሱት ቆዳቸው በቀጥታ ከአጥንታቸው ላይ ተጣብቆ ነው፡፡ ሣርንና ሥር ለመብላት ተገደዋል፡፡ ብዙዎች በእንቅልፋቸው ውስጥ እያሉ ይሞቱ ነበር
- <u>ዘ ኢኮኖሚስት፡-</u> "የረሃቡ ቀጥተኛ ምክንያቶች- ድምላ መፈናቀልና ጦርነት ያስከተለው ምርት ማጣት፣ የአንበጣ መንጋ፤ የሰብሎች መቃጠል፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ሆን ብሎ ምግብ መከልከል
- <u>ማርክ ሎውኮክ (ኦቻ)</u>፡- "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት ሆን ብሎ ትግራይን እያስራበ ነው፣ ርዳታ ወደ ውስጥ መግባትን ለማስቆም የተራቀቀ ዘመቻ እያካሄደ ነው፤ ስድስት ሚሊዮን ህዝብ ለማስራብ ብቻ ሳይሆን እየሆነ ያለውን ነገር ለመደበቅ ሙከራ አድርጓል"
- <u>ተክለሃይማኖት፡-</u>"የኢትዮጵያና የኤሪትርያ መንግስታት ለረሃብ መንስኤ የሚሆኑ ቁልፍ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል- ስልታዊ ዘረፋና የመሰረተ ልማት ውድመት፣ የገንዘብ አቅርቦትን የሚገታ የባንኮች እገዳ፤ ሰብአዊ እርዳታን የሚያደናቅፍ ከበባ
- <u>የረሃብ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርአቶች አውታረ መረብ:</u> "ለደረጃ 4 አጣዳፊ የምግብ ዋስትና እጦት ቁልፍ ምክንያቶች- የትጥቅ ግጭትና የተደራሽነት ገደቦች፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፤ ከፍተኛ የገቢ ማስገኛና የገበያ እንቅስቃሴ መስተጓጎል"
- ሌሎች ፈተናዎች፡- በየመዳረሻ ኬላዎች የፌደራል መንግስት ፍቃድ፣ ከአጎራባች የክልል መንግስታት ፍቃድ፤ የአካባቢ ታጣቂ ሃይሎች የደህንነት ስጋትን ምክንያት በማድረግ ክልከላ፤ እርዳታው ለትግራይ ሃይሎች ለምግብነት እንዳይውል ስጋት መኖሩ
- የምግብ አቅርቦት በሚኖርበት ጊዜም አሽከርካሪዎች ለደህንነታቸው ይፈራሉ፤ የእርዳታ ድርጅቶችም መቐለን ለቀው መውጣት ፈሩ
- አንድ የፌደራል የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን በኢትዮጵያ ረሃብ የለም ሲሉ ተናግረዋል። ይህ አባባል ከፕሪቶሪያ ስምምነት አንድ አመት በኋላም በተመሳሳይ ቀጥሏል፡፡ ********************************

# ምዕራፍ ፰

# ማህበረ-ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጥፋቶች

## 8.1 መግቢያ

በትግራይ ጦርነት አንድ ሚልዮን ይሆናል ተብሎ የተገመተ የሰው ህይወት ጠፍቷል፡፡ ሰው ሰራሽ መቅሰፍቱ በሰው ህይወት እንደቅጠል መርገፍ ብቻ አላበቃም፡፡ ቁጥር ስፍር የሌለው ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ውድመትና ምስቅልቅልም ፈጥሮ እስከ ወዲያኛው የማይድን ቁስልና ጠባሳ ትቶ ሄዷል፤ ሄዷል? በዚህ ምእራፍ በማህበራዊው ዘርፍ፡- የሴቶች መደፈር፤ የሃይማኖት ተቋማት ውድመት፤ በሱዳን የትግራይ ስደተኞችና በትግራይ የውስጥ ተፈናቃዮች፤ በሚዛን ተፈሪ የተጋሩ ማጎርያ፤ በኢሮብና በኩናማ ላይ ያንዣበበው ጥፋት፤ እንዲሁም ጥላቻ በትዳር ላይ ያስከተለው መዘዝ ከጎንደር አንድ አብነት፤ የሚሉ ርእሶች ተካተዋል፡፡ በኢኮኖሚው መስክ፡- የትግራይ የኢንዱስትሪ እድገት በአጭር ተቀጨ፤ የጤና ተቋማት ውድመት፤ የገጠር ቤቶችና የእርሻ ቦታዎች ውድመት፤ የንብረት ዝርፊያ በባእድ ሃይል፡፡ በመጨረሻ የተፈጥሯዊ አካባቢ ጉዳት፡፡

## 8.2 የሴቶች መደፈር

ምልእተ ብርሃነ መስቀል- “የዘር ማጥፋቶች ሁሉ የየራሳቸው ፊርማ አላቸው፤ የዚህኛው አስገድዶ መድፈር ነው”

የተባበሩት መንግስታት- “የጾታዊ አመጹን የጭካኔ መጠን መረዳት ያዳግታል”

ግሎባል ቮይስስ- “ማሰብ የማይቻል እንደ ቅዠት የሆነ ነገር”



ወርልድ ፒስ ፋውንዴሽን (ዲያን ማዙራና)፣ አልጀዚራ ኢንግሊሽ (ፕራሚላ ፓተን)፣ ቢቢሲ ኒውስ (ወይኒ አብራሃ-ይኮኖ)፣ ዘ ዴይሊ ቴሌግራፍ፣ ሲቢኤስ ኒውስ፣ ሲኤንኤን፣ ኦቻ (ማርክ ሎውኮክ)፣ ኤሪትርያ ሃብ፣ ኢኢፒኤ ሆርን፣ ዘ አይሪሽ ታይምስ፤ ሉሲ ካሳ፤ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ አምኔስቲ ኢንተርናሽናል፤ ፎርቤስ (ዶር. ኢዌሊና ዩ. ኦቻብ)፣ ግሎባል ቮይስስ፣ ዩኤንኤፍፒኤ፤ ኒው ዮርክ ታይምስ፣ ኦምና ትግራይ

**ማስታወሻ** ፡- የወለደቻቸው ሴት፤ እህታቸው ሴት፤ ሚስቶቻቸው ሴት መሆኑን እንተወውና፤ በክርስትያን ህዝቦች ዘንድ ሴት በማሪያም ትመሰላለች ማህጸኗም ደግሞ መድሃኒታችንን የወለደ ነው በሚል እምነት ክቡርና የተቀደሰ ነው፡፡ እነዚህ ደፋሪዎች "ድንግልን" እያሉ የሚምሉና የሚገዘቱ፤ የእግዚአብሀርን ስም ከማንሳት የማሪያምን ስም ሲጠሩ የሚውሉ፤ የማሪያም ንግስ በተባለ ቁጥር ገደል እየወረዱና እየወጡ ሄደው የሚባረኩ ናቸው፡፡ የዘር ዛራቸው ሲወርድ ግን ሁሉም ፈረሰ፡፡

**1. ተጎጂዎቹ እነማን ነበሩ፡-**

- ትናንሽ ልጃገረዶችና በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች
- በሁሉም እድሜ ያሉ ሴቶች (እርጉዝና የሚያጠቡ ሴቶችን ጨምሮ)
- አያቶችና ቅድመ አያቶች
- ትናንሽና ትልልቅ ወንዶች

**2. የሴቶች መደፈር በሚንቀሳቀሱ ወታደሮች፡-**

- ልጃገረዶችንና ሴቶችን እንደ ወሲብ ባሪያዎች ያስቀምጧቸው ነበር
- ሲንቀሳቀሱ ጥለዋቸው ይሄዳሉ ወይም ይወስዷቸዋል
- በተዛወሩበት መደብ እንዳዲስ ሴቶችን በቁጥጥር ስር እያደረጉ ይደፍራ

**3. አስገድዶ መድፈር እንዴት እንደተደረገ**

- በቤተሰቦቻቸው ፊት፤ በተጎጂዎች ቤቶች ውስጥ ይደፍራሉ
- ወታደሮች ባሎችን/ወንዶችን አስፈራርተው ካባረሩ ወይም ከገደሉ በኋላ ሴቶቻቸውን ይደፍራሉ

- ወታደሮች ሴቶች ሲደፈሩ ያዩትን ወይም ለመርዳት የሞከሩትን ነዋሪዎች ተኩሰው ይገድላሉ፤ ከዛ በኋላም መርዳት መሞከር ቀረ
- ሰዎች የቤተሰብ አባላትን እንዲደፍሩ ተገደዋል
- እናቶችና ሴቶች ልጆች ጎን ለጎን ተደፈሩ
- ከቤት ጎትቶ በማውጣት በአደባባይ ደፍረዋል
- ሴቶች ምግብና ውሃ ሲፈልጉ ተደፍረዋል
- መሠረታዊ ሸቀጦች በለውጥ ለመስጠት አስገድዶ መድፈር
- የአይደር ሪፈራል ሆስፒታል ተማሪዎች ከቤተመፃህፍት ወደ ማደሪያ ቤታቸው ሲሄዱ በመከላከያ ተደፍረዋል
- ወንጀለኞች ተጎጂዎቻቸውን ያዋርዳሉ፡- በብሄር ስድብ፤ ሌላ ተራ ሰድብ፤ ማስፈራሪያና አዋራጅ አስተያየቶችን ይሰጣሉ
- በአንድ ላይ በርካታ ወንዶች አንዲት ሴት ላይ ግብረ ስጋ መፈጸም
- አስነዋሪ የሆኑ ወሲባዊ ድርጊቶች (ግብረ ሰዶማዊ፣ በፊንጢጣ፣ በአፍ፤ ሌሎች ነገሮች በመጠቀም)፤ እምቢ ያሉትን ማስገደድ
- ጡታቸውና በጡታቸው ዙሪያ ተቧጭረዋል ቆስለዋል
- አስገድዶ መድፈርን የተቃወሙት የውስጥና የውጭ ጭናቸው ላይ በቢላዋ ተቆራርጧል፤ በትኩስ ብረት ጭናቸውና በውጫዊ ብልታቸው ላይ ተጠብሰዋል
- በአስገድዶ መድፈር ምክንያት በብልት አካባቢ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡- አንዳንዶች በፊንጢጣና በሴት ብልት በዱላ፣ በጋለ ብረት፣ በምስማር፣ በጠጠር፣ በብረት፤ በፐላስቲክ፤ በሌሎች ነገሮች በመድፈር በፊንጢጣና በሴት ብልትና ዙሪያ ስምብራትና መበሳት ታይቶባቸዋል

**4. በተጎጂዎች ላይ ውጤቱ**

- የሴት ብልት በትኩስ ብረቶች ከተደፈረ ጣባሳ ስለሚሆን በወሊድ ጊዜ አስቸጋሪ ነው፡፡ የወሊድ ቦይና ማህፀን ስለሚበከልም ማህፀንን በቀዶ ጥገና ማስወገድ ያስፈልጋል

- ከተፈሩ በኋላ በሕይወት የተረፉት ከባድ የአካል፣ የአዕምሮና የስሜት ጉዳት ደርሶባቸዋል
- የቤተሰባቸው አባላትና ጎረቤቶች ሲገደሉና ቤታቸውና ማህበረሰባቸው ሲወድም በማየታቸው በተጨማሪ ተጎድተዋል
- ከጾታዊ ጥቃት የተረፉ አንዳንድ ሴቶች አሁን እርጉዝ ናቸው
- አንዳንዶች ፅንስ ለማስወረድ የጤና አገልግሎት ቢያስፈልጋቸውም አብዛኛው የጤና አገልግሎት ወድሟል የህክምና እርዳታም ታግዷል
- ስለዚህ በራሳቸው በአደገኛ ሁኔታ ፅንስ ለማስወረድ ተገደዋል
- በኤችአይቪና ሄፓታይተስ የተያዙም አሉ፡፡ አስገድዶ ደፋሪዎች ለተጎጂዎቻቸው ኤችአይቪ ፖዘቲቭ እንደሆኑና እነሱን መበከል እንደሚፈልጉ ነግረቻቸዋል
- በፊንጢጣ መደፈር እጣ የገጠማቸው ወንዶች በደረሰባቸው ጉዳት አእምሯቸው ተበላሽቷል
- የተደፈሩት ህብረተሰብ ውስጥ መገለል ደርሶባቸዋል

5. **አንዳንድ ያልተለመዱ ነገሮች**

- የመከላከያ ደፋሪ የካህን ሚስት በባሏ ፊት ደፈረና ባሏን ገደለው
- አንዲት እናት በመከላከያ አባላት ለብዙ ሰዓታት ከትንሽ ልጇ ፊት በቡድን ተደፍራለች። ራሷን ስታ ከነቃች በኋላ የአራት አመት ልጇ ተገድሎ በእግሯ ላይ ወደቆ አገኘችው
- አንዲት ሴት በየተራ ደፈሯት፡ ኋላ ስትጠየቅ “እርጉዝ መሆኔን ብቻ ሳይሆን ሰው መሆኔንንም የተገነዘቡ አይመስሉም” ብላለች
- ሞናሊሳ በተባለች ወጣት ላይ በተደረገ የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ሰባት ጊዜ ተተኩሶባት ከቆሰለች በኋላ አንዱ ክንዷ ተቆርጧል፡፡ አያቷ አስገድዶ መድፈርን ከሃይማኖት አኳያ ሲቃወሙ ደፋሪዎቹ እግራቸው ላይ ተኩሰው ኩሽና ውስጥ ዘግተውባቸዋል
- የተጎጂዋን ፎቶ አንስተው አልኮል አፍስሰውባት ሲሳለቁ የ12 አመት ልጇንም በጥይት ገድለዋል

- የ15 ዓመቷ ወጣት ወንድሟን ጨምሮ በግዳጅ ምስክሮች ፊት ተደፍራለች
- ስድስት ሴቶች ለ10 ቀናት በኤሪትርያ ወታደሮች በቡድን ተደፍረዋል
- የኤሪትርያ ወታደሮች እየቀለዱ፤ ፎቶ እያነሱ፤ አደንዛዥ እፅ በመርፌ እየወጉ፣ ከድንጋይ ላይ አስረው፣ ልብሷን ገፈው፤ በስለት ወግተው፤ ደጋግመው ደፈሩ
- አንዲት ሴት ሁለት ሴት ልጆቿ ከፊቷ ተደፍረው፤ በቡድን ከደፈሩ በኋላ ብልታቸውን ደበደቡዋቸው
- አንዲት ልጅ ተደፍራ በከተማ ጎዳና ላይ ተጥላ ተገኘች። የኤሪትርያ ወታደሮች ውጫዊና ውስጣዊ የብልት ክፍሎቿን ከብሪትና ሙቅ ብረት ዘንግ ተጠቅመው አቃጥለው ነበር፤ ልጅቷ ሞተች
- ሴቲቱ ልጇን እንድትመግብ ፈቅደው አስገድዶ መድፈር አቋርጠው የቀጠሉ

## 6. አስገድዶ ደፋሪዎች ለተጎጂዎቻቸው ምን ይላሉ?

“እናንተን ያለተጠያቂነት መግደልና መድፈር እንደምንችል በመንግስት መመሪያ ተሰጥቶናል፡፡ የምንፈልገውን ሁሉ ልናደርጋችሁ እንችላለን፡፡ ተጋሩን ካስወገድን ይህንን መሬት ለኤሪትርያ ልንሰጠው እንችላለን፡፡ ሁላችሁንም ማጽዳት እንፈልጋለን፣ ከትግራይ ማንነታችሁን ማጽዳት እንፈልጋለን፡፡ የትግራይ ተወላጆችን ዘር በኢትዮጵያ እንድታስቀጥሉ አንፈልግም”

## 7. አስገድዶ ደፋሪዎች ለምን ይህን ይፈጽማሉ?

- ደፋሪዎች በትግራይ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ጥቃት በመፈጸም በባሎቻቸው፤ በወንድሞቻቸው፤ በአባቶቻቸውና ባጠቃልይ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ የበላይነታቸውን ለማሳየት ነው
- ይህ ሆን ተብሎ የተደረገው የህዝቡን ሞራል በመስበርና በማስፈራራት ትግሉን ለማስተው ነው
- “የሴት ልጅ አባት ዶር. ደብረጽዮን፤ የወታደሩ አባት ዶር. አቢይ” በማለት አስገድዶ መድፈሩ ስልታዊ የጦርነቱ አካል መሆኑን ያረጋግጣሉ
- የትግራይን ደም ማጽዳት በብሄራቸው አማራ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል ወይም የትግራይ ማንነታቸውንና የዘር ሃረጋቸውን ያቋርጣል

- የትግራይ ወንዶች ሴቶቻቸውን፣ ሴት ልጆቻቸውንና ብሄራቸውን ለመጠበቅ እንደ ወንድነታቸው አቅም እንዳጡ ሆኖ እንዲሰማቸው ያደርጋል
- ተጎጂዎችንም ሆነ ብሄራቸውን የማሸበርና የማዋረድ ስልት ነው
- ወንጀለኞቹ እንዲህ ያለው አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጥቃት ለአሁንና ለወደፊት በትግራይ ልጃገረዶችና ሴቶች ላይ የማይቀለበስ አካላዊ፤ ስነ ልቦናዊ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዝ እንዳለው ያውቃሉ
- ጾታዊ ጥቃት የመራቢያ አቅምን በዘላቂነት በመጉዳት ማህበረሰቦችን ሆን ተብሎ የማምከን ዘመቻ ነው
- የጦር መኮንኖች የበታቾቻቸውን አስገድዶ መድፈር እንዲፈጽሙ ያበረታታሉ፤ በጉዳዩም ላይ ይቀልዳሉ
- ጾታዊ ጥቃት አስቀድሞ የታቀደ የጦርነት መሳሪያ በመሆኑ ለመድፈር ፈቃደኛ ያልሆኑ ወታደሮች በጓደኞቻቸው ይሾፍባቸዋል በአለቆቻቸውም ይቀጣሉ
- አብዛኛው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈጸመው በኤሪትርያ ወታደሮችና ከአማራ ሃይሎች ነው
- አስገድዶ መድፈር የተፈጸመው በሰፊ ዘመቻ ስለሆነ የተዘገበው ከአባይ ውሃ በጭልፋ ያህል ነው

**8. የአስገድዶ መድፈር ካምፖች**

- የአስገድዶ መድፈር ካምፖች ሆስፒታሎች፣ የግንባታ ቦታዎችና ወንዝ ዳርቻዎች ናቸው
- በአቅራቢያ ካሉ አካባቢዎች የተያዙ ልጃገረዶችና ሴቶች በሆስፒታል ክፍሎችና አልጋዎች ታግተዋል፡፡ አልጋዎቹ ልጃገረዶችን፣ ሴቶችን እና ወንዶችን ለመደፈር ያገለግላሉ.
- ተጎጂዎቹ እንዳያመልጡ ከአልጋው ጋር ይታሰራሉ ወይም በሮች ይዘጋሉ
- አንዳንድ ወታደሮች በተፈናቃይ ካምፖች ውስጥ ይደፍሩ ነበር
- ወታደራዊ ካምፖች፤ መኖሪያ ቤቶች ወይም ግቢዎች ጥቅም ላይ ውለዋል

## 9. ስለ አስገድዶ መድፈር የተሰጡ ምላሾችና አስተያየቶች

- ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ የሰጡት የመጀመሪያ ምላሽ በሰሜናዊው እዝ ወታደሮችና በአስገድዶ መድፈር ሰለባዎች መካከል ያለው ንፅፅር፦ "ሴቶቹ በወንዶች ተደፈሩ፤ ወታደሮቻችን በሳንጃ ተደፈሩ"
- በሌላ ቀን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው እንዲህ ብለዋል፦ "የትግራይ እህቶቻችንን የሚደፍር ማንኛውም ሰው በህግ ፍርድ ቤት ይጠየቃል"
- የኢትዮጵያ ባለስልጣናት ሶስት የኢትዮጵያ ወታደሮች ጥፋተኛ መሆናቸውንና ሌሎች 25 ሰዎች ደግሞ በአስገድዶ መድፈርና በሌሎች ጾታዊ ጥቃቶች መከሰሳቸውን አስታውቀዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ ፍርድ ቤት ጉዳይ ምንም አልተሰማም
- አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ፤ ለሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስትር ጽፏል፡፡ ለኤሪትርያ የማስታወቂያ ሚኒስትርና ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ከፍተኛ አማካሪ ስለ ጾታዊ ጥቃቶቹ ቢጽፍም ከሁሉም ምንም ምላሽ የለም
- ሁሉም የመንግስት አካላትና የመንግስት ደጋፊው ካምፕ በህይወት የተረፉትን ተጎጅዎች ዝም ለማሰኘት ተንቀሳቅሰዋል
- በትግራይ የተፈፀመውን አስገድዶ መድፈር ማጋነን አያስፈልግም የሚል ፕሮፓጋንዳ እየተሰራጨ ነበር፡፡ አንዳንዶችም ጉዳዩን ከአውዱ አውጥተው "በትግራይ አስገድዶ መድፈር የተለመደ ነው" በማለት ካረገበት የግፍ ከፍታ ወደ መሬት አውረደው ሊጥሉት ይታገላሉ
- የኢትዮጵያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ የአስገድዶ መድፈርን ዜና በጥርጣሪ አይን እንደሚያየው ገለጸ
- በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር "ሴቶቹ ተደፈርን ብለው የሚያቀርቡት ምስከርነት ሃሰት ነው" ብልዋል
- ከኢትዮጵያ የሴቶች መብት ተከራካሪዎች አንድም ቃል አልተሰማም

## 8.3 **የገዳማትና መስጊድ መውደም** (ኢኢፒኤ-ሆርን፣ ትግሃት)



- የአረብ ባለ ሥልጣናት ነብዩ መሐመድንና ጥቂት ተከታዮቻቸውን እያደኑ በነበሩበት ወቅት በአኹሱም መንግሥት ውስጥ የነበረ ክርስቲያን ንጉሥ እስልምናን ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ ሌላ መንገድ አድርጎ የተቀበለው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር
- በምስራቅ ትግራይ ዞን ዓዲግራትና ውቅሮ ከተሞች መካከል የሚገኘው የአል ነጃሺ መስጂድ አክሱማዊው ንጉስ እስልምናን እንዴት እንታደገ የሚያሳይ ለምእተ አመታት የኖረ ህያው ምስክር ነው
- መስጂዱ ከ7ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአፍሪካ ውስጥ እጅግ ጥንታዊው መስጊድ ነው ተብሎ ይታሰባል። የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ሲሆን ቀደም ብሎም እድሳት ተደርጎለት ነበር
- የትግራይ ጦርነት ከተጀመረ በአንድ ወር ውስጥ መስጂዱ በመጀመሪያ በቦምብ ተደበደበ፤ በኋላ በኢትዮጵያና በኤሪትርያ ወታደሮች ተዘርፏል፤ መስጂዱን ለመጠበቅ ሲሉም ሰዎች ሞተዋል
- በአራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በመካከለኛው ምስራቅ ክርስትና የተጀመረባቸው ጥቂት ቦታዎች ነበሩ፤ አኹሱም አንዷ ነበረች
- በዚህ ምክንያት የትግራይ ክርስትና ሀይማኖት ብቻ ሳይሆን ከጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ጋር አብሮ የተዋቀረ ታሪክና ባህልም ነው
- ከእንደዚህ ዓይነት ሃይማኖታዊ ታሪካዊ ሀብቶች መካከል በጣም ታዋቂው የስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመኑ ደብረ ዳሞ ገዳም ነው

- በሺዎች የሚቆጠሩ ምእመናንና አለም አቀፍ ቱሪስቶች ወደ ስፍራው ይጎርፋሉ፡፡ ጎብኝዎችም ገዳሙ የሚታወቅበትን አስፈሪ ገደል በመውጣት ድፍረትንና እምነታቸውን ይፈትናሉ
- የኤሪትርያ ወታደሮች የደብረ ዳሞን ገዳም በመድፍ ሲደበድቡ ቤቶች ተጎድተው አንድ መነኩሴ ሞቷል
- በትግራይ የሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ጥቃት ደርሶባቸዋል
- በ11 ህዳር 2013 በዛላምበሳ የምትገኘው የጨርቆስ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በኤሪትርያ ወታደሮች ተኩስ ውድመት ደረሰባት

## 8.4 በጦርነት የተሰደዱና የተፈናቀሉ ሱዳንና ትግራይ ውስጥ

(ናሪማን ኤልሞፍቲ አሶሴትድ ፕሬስ፤ ዩኤን.ኦቻ፤ ዩኤን.ኤችሲአር፤ ኢትዮጵያ ኢንሳይት፤ ዎርልድ ኤድ፤ ሜዲሲን ሳን ፍሮንቲር 20 መጋቢት 2013፤ ኒውስ ግሎባል



- በምዕራብ ትግራይ ጦርነት ሲጀመር ከ50,000 በላይ የትግራይ ተወላጆች ወደ ሱዳን ተሰደዋል።
- በ14 መጋቢት 2013 ዩኤን.ኤችሲአር ከ62,000 በላይ የትግራይ ስደተኞችን መዝግቧል
- ስደተኞች በድንበር አቅራቢያ ከሚገኘው ሃምዳይት ከሚባለው የመሸጋገሪያና ጊዜያዊ የማቆያ ማእከል በ7o ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ኡም ራኩባ ተወስደዋል።
- የስደተኞችው ጎርፍ የመስተናገድ ፍላጎቱ ካቅም በላይ ስለነበር የእርዳታ ድርጅቶች ተጨናንቀዋል
- ይህ ከ50,000 በላይ የሚሆኑ ስደተኞች በድንገት በሱዳን በርሃ አሸዋማ ሜዳ ላይ ራሳቸውን ያገኙበት አሳዛኝ ታሪክ ነው።

- ከነዚህ መካከል ንግስቲ አንዷ ነች፡፡ በከባድ መኪና ሹፌርነት በእርሻ ቦታ ከሚሰራ ባለቤቷ ጋር የቤት እመቤት በመሆን መልካም ህይወት ታሳልፍ ነበር፡፡ አሁን ሁሉንም ነገር ወደ ኋላ ትታ እዚህ ተግኝታለች፤ ለምን እንደሆነ አታውቅም ነገር ግን የት እንዳሉ ስለማታውቀው ዘመዶቿ ተጨንቃለች፤ የወደፊት እቅዳቸውን አጥተዋል፤ የለፉበት ሁሉ ጠፍቷል

- አሁን ሱዳን ውስጥ ባለው የእርስ በርስ ጦርነት የትግራይ ስደተኞች ሊደርስባቸው የሚችለው አደጋ ከባድ ሊሆን እንደሚችል መረዳት አያዳግትም፡፡ የተሰደዱበት መንገድ "ከመጥበሻው ዘሎ ወደ እሳቱ!"

- በትግራይ የውስጥ ተፈናቃዮች ግንቦት 17/ 2013 በተለቀቀ ጥናት ወጤት (አያ.ኦ.ኤም./ ኒውስ ግሎባል) 1,645,944 (ሽረ 575,115፤ ዓድዋ 188,910፤ ሽራሮ 165,223፤ መቐለ 200,909) ነበሩ፡፡

- አሉ የሚል ግምት አለ፡፡ ብዙዎቹ የሚኖሩት በትምህርት ቤቶችና ባዶ ህንጻዎች ውስጥ ነው፡፡ የውሃና የመብራት መሰረታዊ አገልግሎት በሌለባቸው ስፍራዎች፡፡ ትልቁ ቁጥር ያለው ሽረና አኹሱም ከተሞች ውስጥ ነው

- የውስጥ መፈናቀሉ ሲጀመር በአብዛኛው በዘመድ አዝማድ ወይም በሚያውቋቸው ሰዎች ቤት ውስጥ መቆየትና የተገኘውን መጋራት ነበር፤ አስተናጋጅ ማህበረሰቦችም ያልተቆጠበ ድጋፍ ያደርጉ ነበር

- መፈናቀሉ እየተባባሰ ሲሄድ ከዘመድም ከማህበረሰቡም አቅም በላይ ሆኖ ተፈናቃዮቹ የማስተናገድ አቅም በሌላቸውና ለእነሱ አገልግሎት ማቅረብ በማይችሉ መደበኛ ባልሆኑ ጣቢያዎች ውስጥ ሰፈሩ

- ተፈናቃዮቹ ከቤታቸው ይዘው የወጡት ህይወታቸውን ልጆቻቸውንና የደረቡትን ልብስ ብቻ ነበር


- ከምእራብ ትግራይ የተፈናቀሉት ትልቁ ድርሻ የያዙ ሲሆን በተወሳሰበው የምእራብ ትግራይ ፖለቲካ የፕሪቶርያ ስምምነት ተተግብሮ ወደ ቀያቸው መመለስ አልቻሉም፡፡ በትግራይ መሪዎች የውስጥ ውዝግብና በፌደራል መንግስቱ ዳተኛነት ወይም በጉዳዩ ላይ በያዘው ድብቅ አጀንዳ ተፈናቃዮቹ የመመለስ ተስፋቸው እየጨለመ መጥቷል

- ትምህርት ለማስጀመር ተፈናቃዮቹ ከትምህርት ቤቶች ህንጻዎች እንዲለቁ የሚደረገው ግፊት ጭንቀት ውስጥ ይከታል፤ ትምህርት መጀመር አለበት ተፈናቃዮችም መጠለል አለባቸው!

- ተፍናቃዮች ጦርነትን ሸሽተው ቢሰደዱም ካሉበት ድረስ እየተከተለ አለቀቃቸውም፡፡ ቀደም ባለው ምእራፍ እንደተጠቀሰው በደደቢት የተፈናቃዮች ካምፕ ላይ የተፈጸመው የድሮን ጥቃት “የት እንሂድ” አሰኝቷል

## 8.5 “አስዊሽ” በሚዛን ተፈሪ

አዲስ ፎርቹን፤ ኢኢፒኤ-ሆርን፤ ሬውተርስ (11 ሰኔ 2014)



ተጋሩ፡- ለሚዛን ተፈሪ ማጎሪያ ቤት ማቆያ አባ ሳሙኤል እስር ቤት

- ሚዛን ተፈሪ በደቡብ ኢትዮጵያ የቤንች ሸኮ ዞን የአስተዳደር ማዕከል ናት
- ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 580 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች
- በአዲስ አበባ ከተማና አካባቢዋ የትግራይ ተወላጆች በመሆናቸው ያለልዩነት ታስረዋል። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሲናገሩ ወይም የትግራይ ስም ያለው መታወቂያ ካርድ በማሳየታቸው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለዋል
- በድሬዳዋ፣ በጅግጅጋ፣ በአዳማና በሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍሎች የትግራይ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለው የጅምላ እስር ቀጥሏል
- በአዲስ አበባ ሃርመኒና ካሌብ ሆቴሎች የትግርኛ ሙዚቃ በማጫወታቸው ተዘግተዋል፤ የአኩሱምና የካፒታል ሆቴሎች ባለቤቶች ታስረዋል
- በአዲስ አበባ ከ48,000 በላይ የትግራይ ተወላጆች የንግድ ድርጅቶች ተዘግተዋል
- ከመላ አዲስ አበባ የታፈሱት ተጋሩ መጀመሪያ ወደ ጊዜያዊ ማቆያ ካምፖች (ጎተራ ኮንዶሚኒየም አካባቢ፤ አባ ሳሙኤል እስር ቤት) ተወስደዋል
- የትግራይ ተወላጅ እስረኞች በአሮጌ ሲኒማ ቤቶች፣ በዩኒቨርስቲ ግቢዎች፣ በቀድሞ የዶሮ ፋብሪካ፣ በኢንዱስትሪ ፓርክና በግንባታ ቦታዎች ተጨናንቀዋል
- ከታሳሪዎቹ መካከል ሴቶችና ህጻናት ይገኙበታል
- አብዛኛዎቹ መገልገያዎች የተጨናነቁ፤ የቆሻሻ ሽታ ያላቸው ነበሩ፡፡ ድብደባ የተለመደ ነበር፡፡ የታመሙ እስረኞች ለሳምንታት ህክምና ተከልክለዋል

- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ግምት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ የታፈሱት የትግራይ ተወላጆች ቁጥር ከ15,000 በላይ ነ፤ ሮይተርስ ደግሞ በዚህ ግምት ላይ 3,000 ይጨምራል
- አብዛኞቹ እስረኞች ከአዲስ አበባ 580 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ሚዛን ተፈሪ ማጎሪያ ካምፖች ተጭነዋል
- የውሃ ችግር በመኖሩ እስረኞች በውሃ ጥም ተቃጥለው ይወራጩ ነበር፤ በተባይና በበሽታም ተሰቃይተዋል
- ፍራሽ የለም፤ ብርድ ልብስ የለም፤ እስረኞች በጀርባቸው መተኛት እስኪያቅታቸው ድረስ ክፍሎቹ ተጨናንቀው ነበር፡ እንደ "ሰርዲን" ታጭቀዋል
- ለእስረኞች በቀን ሁለት የ15 ደቂቃ የመታጠቢያ ቤት እረፍቶች ይሰጡ ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ወረፋው ረዥሙም ወይም እስረኞች በጣም ስለሚታመሙ እስረኞች እየጠበቁ እያሉ እራሳቸውን ያበላሹ ነበር፡፡ በነዚህ ሲኦልን የሚያስንቁ ማጎሪያ ቤቶች ከ17 ያላነሱ የትግራይ ተወላጆች ሞተዋል

## 8.6 የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው ኢሮብና ኩናማ

ኢትዮጵያ ኢንሳይት (ጃን ኒሰን፤ ጀቲል ትሮንቮል)፡ ዴቪድ ቶማሲን




- ኢሮብ በትግራይ ውስጥ የሚገኝ አናሳ ብሄረሰብ ነው፡፡ በኤሪትርያና በትግራይ ውስጥ በድንበር ተከፍሎ ስለሚገኝ ለጥቃት የተጋለጠ ነው
- ኢሮቦች የሚኖሩት በትግራይ ሰሜናዊ ምስራቅ አቅጣጫ ባለ ወጣ ገባ ተራራማ ቦታ ነው
- የኤሪትርያና የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚሽን የትግራይ ኢሮብ መሬትን በከፊል ለኤሪትርያ ሰጥቷል፤
- የኤሪትርያ ወታደሮች ኢሮብን ኤሪትርያዊ በማለት የተቃወሙትን ግድያ፣ ዝርፊያና አስገድዶ ማንነትን ማስቀየር ፈጽመዋል
- ዘረፋው ከመብዛቱ የተነሳ ሰዎች የነበራቸው የለበሱት ልብስ ብቻ ነበር

- ብዙዎች ወደ ተራራ ሸሽተው በዋሻ ውስጥ ተደብቀዋል
- አንድ አዛውንት ምግብ እንደሌላቸው፣ ገንዘብ እንደሌላቸው ተናገሩ፤ ሁለት የልጅ ልጆቻቸውን ገደሉባቸው
- ኩናማ በሰሜን ምእራብ ትግራይ አድያቦ የሚገኝ በትግራይ ውስጥ ሁለተኛው አናሳ ብሄረሰብ ነው፡፡ የሚኖሩት በሽራሮ ሜዳ ለግጭት የሚጋለጥ አካባቢ ነው
- ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ የኩናማ ህዝቦች በትግራይ ይኖራሉ፣ ነገር ግን አብዛኛው በጋሽ ባርካ የኤሪትርያ ክልል ውስጥ ነው
- የኢሮብና የኩናማ ህዝብ እጣ ፈንታ በእርግጠኝነት አይታወቅም፤ በአደገኛ ሁኔታ በሁለት ተዋጊ ኃይሎች መካከል ተቀርቅሯል

## 8.7 "የተጋመደ ህዝብ"? በጎንደር የዘር ጥላቻ የበተነው ትዳር

(ኢትዮጵያ ኢንሳይት 19 ታህሳስ 2015)



**የደራሲው ትዝብት**

ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ጨርሰው ሳይጠፉ የቀሩ ጊዜ አንድ እየገፉ የመጣ አባባል አለ፡- "ሁለቱም ህዝቦችኮ የተዋለዱ የተጋመዱ ናቸው፤ ሆን ብለው ያፋጁን ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ነገር እንርሳውና አንድ ላይ ሆነን የኦሮሞን ሴራ እናክሽፍ"፡፡ ስሌቷ ጫጨት ጭራ የምታወጣት ናት፤ ይህን አስተሳሰብ የሚቀበል ካለ በአዛባ የተሞላ ራስ ቅል ብቻ ነው፡፡ ድንጋይ አንዴ ቢያደናቅፍህ ድንጋዩ ራሱ ነው፤ እንቅፋቱ ከደገመህ ግን ድንጋዩ አንተ ነህ ይባላል፡፡ በታሪክ ትግራይ አስር ጊዜ ያህል ተወራለች፤ አስር ጊዜም ይቅር ብላ አስር ጊዜ ድንጋይ ሆናለች፡፡ አንደኛው ድንጋይነቷ ቀጣዩን እየጠራ እዚህ ደረሰች፡፡ አሁን እንድትሆን የተፈለገው አስራ አንደኛው ድንጋይ ይሆን?

ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ “የልብን ሰርቶ ይቅር በሉኝ፤ ምንስ አጠፋሁ ምን በደልኩኝ.......ቂምን በሆድ ይዞ መታረቅ፤ ይቅርታ’ርጉ እያሉ መራቀቅ፤ አጉል ነው ከንቱ መበሻሸቅ” ብሎ ያዜመው ለእንደዚህ አይነቱ አይነ ደረቅነት ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ በጋብቻ መተሳሰር ብቻ አልነበረም ለጎንደር ህይወቱ ሰጥቶላታል፤ በቀር በመተማ ከመጣው ድርቡሽ ጋር የትግራይ ህዝብ በየት ተገናኝቶ? ያሁኑን አያድርገውና የያኔው ደጋጉ የጎንደር ህዝብ አመስግኗል፦ “ጎንደር ስትቃጠል ስትነድ ስትጨስ፤ አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሓንስ”፡፡ የአጼ ዮሃንስ ሰራዊት ሁሉም ማለት ይቻላል የትግራይ ሰው ነበር፡፡ የአሁኑ የጎንደር ትውልድ አቅጣጫ የጠፋው፤ ወዳጁንና ጠላቱን በቅጡ መለየት የማይችል፤ አይነ ጠባብና ጥቅመኛ ትውልድ ነው፡፡ ሃይማኖቱ ከትግራይ የተቀበለው መሆኑን ዘንግቶ “ትግሬ ለምን ፓትሪያርክ ሆነ” ብሎ ቡራ ከረዩ የሚል ነው፤ አኹሱም የኛ ናት እያለ የሚያቅራራ፤ ወልቃይት ርስቴ ናት ትግሬ እንዳይኖርባት ብሎ ወገኑ የሆነውን ህዝብ በጎጠኝነት ስሜት የሚያፈናቅልና የሚፈጅ ነው፡፡ ይቅር መባባል አፈር አፍሶ፤ ማቅ ለብሶ አልቅሶ፤ አጎንብሶ፤ ፍትህን አንግሶ ነው!

---

- ሓዳስ ከዳንሻ (ምእራብ ትግራይ) የተገኘች ትግራወይቲ ሴት ናት፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ተምራለች፤ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ከወደፊት ባለቤቷ ጋር ተገናኘች
- ተጋብተው ወደ ባሏ የትውልድ ከተማ ወደ ጎንደር ሄዱ፤ ሓዳስ በጎንደር የውሃ አገልግሎት ውስጥ ተቀጥራ ትሰራለች
- በጎንደር የሰባት ዓመታት ቆይታዋ አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለች፤ ትዳሯ ላይ ብዙ ችግሮች አላጋጠሟትም
- የትግራይ ጦርነት ሲጀመር በትግራይ ተወላጆች ላይ አሰቃቂ ጥቃት መፈጸምና ንብረቶቻቸውን በስፋት የመውረስ ተግባር በጎንደር ተጀመረ
- ከዚያን ቀን ጀምሮ ባሏ ለትግራይ ተወላጆች ያለው ጥላቻ ጎልቶ መታየት ጀመረ፤ ለእሷ ያለው ታማኝነትም እየቀነሰ መጣ
- ሓዳስ በከተማዋ በትግራይ ተወላጆች ላይ የተፈጸመው ግፍ በእሷም ላይ እንዳይደርስ ፈርታለች፤ ባሏ ሊጎዳት እንደሚችልም ጠረጠረች፤ ከዚያም ባሏን ትታ ከአንድ ልጇ ጋር ሌላ ቦታ መኖሪያ ቀየረች
- ደስተኛ ትዳር የመመሥረት ተስፋዋ፣ መውለድ የምትፈልጋቸው ልጆች ህልም በሙሉ ጠፍቷል፤ ሕይወት ያለ ማስጠንቀቂያ በድንገት በስሜት የሚንከባለል ሆነ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ፖሊሶች ያዟት

- ሓዳስ ልጇን በማን እንክብካቤ ስር እንደምታስቀምጥ አላወቀችም፤ ፖሊሶች ስለ ልጇ እጣ ፈንታ ግድ አልሰጣቸውም፤ እንደ እድል ሆኖ አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት እስክትፈታ ድረስ ልጇን እንደሚንከባከበው ቃል ገባ
- በከተማው ውስጥ ካሉ ታዋቂ እስር ቤቶች ወደ አንዱ ተወሰደች፤ ሓዳስ ምንም ጠያቂ ሳይኖራት ለስድስት ወራት በእስር ቤት ውስጥ ቆየች
- በእስር ቤት ውስጥ ያሉ የትግራይ ተወላጆች በድብደባ ይመረመራሉ፤ በሌሊት ይወሰዳሉ፤ ብዙዎች አይመለሱም
- በመጨረሻ ተፈታች፤ ከልጇም ጋር ተገናኘች፤ ጎንደር ውስጥ መቆየት ስለመቻልዋ እርግጠኛ መሆን ስላልቻለች ከተማዋን ጥላ ሸሸች፤ ልጇ አሁንም በበጎ አድራጎት ድርጅት እንክብካቤ ውስጥ ነው፡፡
- አሁን በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ጓደኞቿ ጋር ትኖራለች፤ ከጎንደር ስትሰደድ የትምህርት ማስረጃዋ በእጇ አልያዘችም፤ የመረጃዎቿ ትክ ስትጠይቅ ውድቅ ተደረገባት፡፡ ልጇን ትናፍቃለች፤ ስለ ቤተሰቧ አባላት እጣ ፈንታ የምታውቀው ነገር የለም

## 8.8 ባጭር የተቀጨው የተቀጨው የትግራይ የኢዱስትሪ እድገት

(ኢትዮጵያ ኢንሳይት፡ ማርቲን ፕላውት፡ ኤሪትርያ ሃብ፡ ወርልድ ፒስ ፋውንዴሽን)



- እስከ 1980ዎቹ ድረስ ትግራይ የነበራት የዱቄትና የዘይት ፋብሪካዎች ብቻ ነበሩ የአካባቢውን ህዝብ ፍላጎት የሚሸፍኑት
- የትግራይን ህዝብ ከድህነት ለማላቀቅ ለ17 አመታት የተካሄደው የትጥቅ ትግል ወደ ድምዳሜው በማድረስ ህዝቡ የስራ ፈጠራ ችሎታውን በመጠቀም ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት የሚያስችል ነፃነት አግኝቷል

- ምንም እንኳ በፖለቲካና በዝምድና መረብ በተያያዙ ጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ቁጥጥር ስር ያሉ ሆነው ህዝባዊ ተሳትፎ የራቃቸው ቢሆኑም በ20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በትግራይ በርከት ያሉ የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት ተገንብተዋል፡፡
- የማኑፋክቸሪንግ ተቋማቱ በስራ ፈጠራ፤ ገበያንና ገቢን በማስፋፋት የካፒታል ክምችትን ከመዳበሩ አኳያና ቴክኖሎጂን ወደ ክልሉ በማስተዋወቅ ረገድ ያደረጉት አስተዋጻኦ እጅግ የላቀ ነበር፡፡ በጎንዮሽና በኋላ-ፊት የኢንዱስትሪዎችና የተዛመዱ አገልግሎቶች መስተጋብር የተቋማት መረባትን አስከትሎ ነበር
- ማርቲን ፕላውት እንዲህ ሲል በትግራይ ፋብሪካዎች ውድመት ሃዘኑን ገለጸ፡-

"በኤሪትርያና በኢትዮጵያ ሃይሎች በትግራይ የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ላይ የደረሰው የበቀል ዘረፋና ውድመት የትግራይ ጦርነት እጅግ አሳዛኝና ትርጉም አልባ ገጽታዎች አንዱ ነው።"

- የአየር ጥቃቶች የወልቃይት ስኳር ፋብሪካንና የተከዘ ግድብን ጎድተዋል፤ ነገር ግን አብዛኛው የመሰረተ ልማት ውድመት የደረሰው ከመቐለ መያዝ በኋላ ነው፡
- ይህ በግልጽ የሚያመለክተው "የትግራይ ጦርነት ዋና አላማ የህወሓት መሪዎችን በቁጥጥር ስር አስገብቶ የትግራይን ህዝብ ሰላማዊ ህይወት ለማስቀጠል ነው" የሚለው የወራሪዎቹ አዋጅ ቅጥፈት መሆኑን ነው
- በአንጻሩ የኢትዮጵያ ጦር ሃይሎች ምክትል ኤታ ማጆር ሹም ጄኔራል አበባው ታደሰ የትግራይን ጦርነት ስኬቶች ሲዘረዝሩ እንዲህ አሉ፡-

  "የፖለቲካ ማዕከሉ ወድሟል፤ የኢኮኖሚ ማዕከሉ ወድሟል፤ ሁሉም መሠረተ ልማቶች ወድመዋል፤... ያ የጦርነቱ አላማ ነበር"

- የኤሪትርያ ጦር ነበር በትግራይ ያሉትን ዋና ዋና ፋብሪካዎች ዘርፎ ያወደማቸው፡-
  - የጠርሙስና መስተዋት ፋብሪካ 23 ህዳር 2013 ወደመ
  - ሰባ በመቶ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ሲሸፍን የነበረው አዲስ ፋርማሲዩቲካል ፋብሪካ 01ታህሳስ 2013
  - በ17ታህሳስ 2013 አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ በኤሪትርያ ወታደሮች እጅ ተዘርፎ ወድሟል፡፡ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ከ5,300 በላይ ሰዎችን በመቅጠር ግንባር ቀደም የጨርቃ ጨርቅ አምራቾች አንዱ ነበር

- የመሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ንብረት የሆኑ ከባድ መኪናዎችም ከትግራይ ውጭ ተወስደዋል። ከትራንስ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ መንግስት 179 የጭነት መኪናዎች ተዘርፈዋል
- እስከ የካቲት 2013 መገባደጃ ድረስ በትግራይ ማእከላዊና ምስራቃዊ ዞኖች ውስጥ የነበሩ ፋብሪካዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፤ ለእድሳት ቢያንስ 100 ቢሊዮን ብር ያስፈልጋል

## 8.9 የጤና ተቋማት ውድመት፡- የህዝብ መፍጃ ዋና መሳሪያ

ሜዲሲን ሳን ፍሮንቲር (06 መጋቢት 2013) ሃይላይና ባልደረቦች (2013)



1. **በፊት በትግራይ የነበረው የጤና ስርአት (ሃይላይና ባልደረቦች)**
    - 2 ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች
    - 16 አጠቃላይ ሆስፒታሎች
    - 29 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች
    - 233 ጤና ጣቢያዎች
    - 712 ጤና ኬላዎች ነበሩ
    - 280 አምቡላንሶች

---

- 24,000 የስኳር ህመምተኞች
- 20,000 ከፍተኛ የደም ግፊት
- 43,000 ኤች አይ ቪ
- 1,500 በላይ ሳንባ ነቀርሳ
- 180,000 ሥር የሰደዱ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች

**2.** በጤና ሥርአቱ ላይ ጦርነቱ ያደርሰው ጉዳት (ሃይላይና ባልደረቦች)

- ጦርነቱ በተጀመረ ስድስት ወራት ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት
  - 27.5% ሆስፒታሎች
  - 17.5% ጤና ጣቢያዎች
  - 11% አምቡላንሶች
- ከ712 ጤና ኬላዎች አንዳቸውም በተሟላ ሁኔታ አይሰሩም ነበር
- 90% የሚሆኑት አምቡላንሶች የት እንዳሉ አይታወቅም
- ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ከ50% በላይ የሚሆኑት የክልሉ የጤና ሰራተኞች ወደ ሥራ ተቋሞቻቸው ሪፖርት ማድረግ አልቻሉም
- በመቐለ በተፈናቃይ ካምፖች 2000 የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች መዝግበዋል
- ተላላፊነና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታች ታማሚዎች ከትትል አጡ

**3.** በጤና ሥርአቱ ላይ ጦርነቱ ያደርሰው ጉዳት (ሜዲሲን ሳን ፍሮንቲር)

- ሜዲሲን ሳን ፍሮንቲር ከጎበኟቸው 106 የጤና ተቋማት ውስጥ 70 በመቶው የተዘረፉ ሲሆን ከ30 በመቶ በላይ የሚሆኑት ጉዳት ደርሶባቸዋል። በመደበኛነት የሚሰሩት 13 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው።

- ወይም 65 በመቶው ሙሉ በሙሉ የማይሰሩና ምንም ሰራተኛ ወይም ቁሳቁስ ያልነበራቸው ናቸው፤ 73 በመቶው ተጎድተዋል ወይም ተዘርፈዋል፤ 20 በመቶው በታጠቁ ቡድኖች ተይዘው ለሲቪሎች አገልግሎት የማይሰጡ ነበሩ፡-

  - 20 አምቡላንሶች ከዓዲግራት ሆስፒታል በአቅራቢያው ከሚገኙ ጤና ጣቢያዎች ተወስደዋል

  - ከነዚህም መካከል የተወሰኑት በኤሪትርያ ድንበር አካባቢ ወታደሮች እየተጠቀሙባቸው ነው

- ታካሚዎች ወደ ጤና አገልግሎት ለመድረስ ረጅም ርቀት አንዳንዴም ለቀናት በእግር መጓዝ ነበረባቸው

- አንዳንዶቹ በፍርሃት ተሰደዋል፤ ሌሎች ደግሞ ደመወዝ ስላልተከፈላቸው ወደ ሥራ አልመጡም

- በአምቡላንስ እጦት፣ በመንገዶች ላይ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ወደ ሆስፒታል መሄድ ባለመቻላቸው ሴቶች በወሊድ ምክንያት ሞተዋል፤ሌሎች ሴቶች ደግሞ መደበኛ ባልሆነ ዘዴ ተፈናቃይ ካምፖች ውስጥ ንጽህና በጎደለው ሁኔታ ይወልዳሉ

- የቅድመ ወሊድ ወይም የድህረ ወሊድ እንክብካቤ ያገኙት ሴቶች በጣም ጥቂት ናቸው

- ህጻናት አልተከተቡም፤ ይህም ለወደፊቱ ለተላላፊ በሽታዎች የመጋለጥ እድልን ይጨምራል

- እንደ የስኳር በሽታ፣ የደም ግፊትና ኤችአይቪ ያሉ ሥር የሰደዱ በሽታዎች፣ እንዲሁም የአእምሮ ሕመምተኞች ሕይወት አድን መድኃኒት ሳይወስዱ ቀርተዋል

- ከሁሉም የከፋው ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች አብዛኛዎቹ የሕክምናና የሥነ ልቦና እንክብካቤ ማግኘት አልቻሉም

## 8.10 የገጠር ቤቶችና የእርሻ ቦታዎች ውድመት

(ተክለ ሃይማኖት ጂ. ወልደሚካኤል 29 ሚያዚያ 2013)



**1. የመንደሮች ውድመት**

- በትግራይ ገጠርና ከተሞች ብዙ ቤቶች ወድመዋል። ዋና የጦር ግንባሮች ከነበሩት የገጠር መንደሮች የጠፋው የመኖሪያ ቤትና ቁምና ክምር ሰብል ለመቁጠር የሚታክት ነው፡፡ በጦር ሜዳዎች ለደረሰባቸው ሽንፈት ወታደሮች የበቀል እርምጃ ሲወሰዱ የነበረው የገበሬ ቤቶችን በማውደም ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ጦር በትግራይ ክልል ሽንፈትን ተከትሎ 500 ህንፃዎች ተቃጥለዋል

- በማዕከላዊ ትግራይ በናዕዴር ዓዴት በኤሪትርያ ወታደሮች የወደሙ፤ በምስራቅ ትግራይ የጉሎመኸዳ ክፍለ ከተማ ፍሬዳሹም ከ595 በላይ የገበሬዎች ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሱቆች፤ አንድ ጤና ጣቢያ በኤሪትርያ

ወታደሮች የተቃጠሉ፡፡ በክልተ አውላዕሎ፣ በአጽቢ ወምበርታ፣ በሳምረ የተቃጠሉ ቤቶች ተዘግበዋል

- በማዕከላዊ ትግራይ የሚገኘው ዓዲ መንዲ መንደር የኤሪትርያ ወታደሮች 478 የመኖሪያ ቤቶችን በማውደም መንደሯን ወደ ምድረበዳነት ቀይረዋል፤ ብዙ ገበሬዎች በቤታቸው ውስጥ በህይወት የተቃጠሉ አሉ
- በምዕራብ ትግራይ የደረሰው ውድመት የከፋ ሲሆን የሳተላይት ምስሎች እንደሚያሳዩት በዞኑ የሚገኙ በርካታ መንደሮች አካባቢውን በተቆጣጠሩት የአማራ ታጣቂዎች ወድመዋል

**2. የእርሻ ውድመት**

- 10 በመቶው አነስተኛ የህዝብ መስኖ መሰረተ ልማቶችና ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆነው የግል ባለሀብቶች የመስኖ መሰረተ ልማት ስልታዊ በሆነ መንገድ ወድሟል፡፡ ከ70 በላይ የፍራፍሬ የችግኝ ማምረቻ ጣቢያዎች ወድመዋል፤ የእንስሳት መኖ ተዘርፏል፡፡ ሳምረ ከ22000 በላይ የፍራፍሬ ዛፎች በ850 ሄክታር መሬት፤ ደጉዓ ተምቤን 35 ሄክታር 3000 በላይ የፍራፍሬ ዛፎች፡፡

## 8.11 የኤሪትርያ ወታደሮች ዝርፊያና የመቐለ ህዝብ ትግል

ኤሪትርያ ሃብ፣ ሮይተርስ፣ ኢትዮጵያ ኢንሳይት፣ አሶሺየትድ ፕሬስ (ካራ አና)



**ላይኛው ፎቶ፡-** የተዘረፈውን ወደ ኤሪትርያ ለማጓጓዝ ግመሎችን፣ ታንኮችን፣ መኪናዎችንና አህያዎችን ተጠቅመዋል፤ **ታችኛው ፎቶ**፡- የመቐለ ከተማ ነዋሪዎች በኤሪትርያ ወታደሮች ርትራ የተዘረፉ እቃዎችን ከከተማዋ እንዳይወጡ ለማድረግ ሲሞክሩ ያሳያል

- የኤሪትርያ ወታደሮች ምግብ፣ ተሸከርካሪዎች፣ ወርቅ፣ በርና መስኮት ሳይቀር እየነጠቁ ነበር፤ የኤሪትርያ ወታደሮች ኪስ ውስጥ የተሰረቀ ጌጣጌጥ ሲንሿሿ ይሰማል፤ የተዘረፉ ልብሶች ቀሚሶችን ሳይቀር ይሞክሩ ነበር፤ ዳይፐር እንኳን ሳይቀር ወስደዋል

- የተዘረፉትን እቃዎች ኤሪትርያ ለማድረስ የተዘጋጁ ሣጥኖችን የጫኑ የጭነት መኪናዎች ቆመወው ይታዩ ነበር፤ አንዳንዴ ወደ ኤሪትርያ በሚገቡ ዋና ዋና መንገዶች ላይ በሚፈጠረው ግጭት ምክንያት የኤሪትርያ ወታደሮች ከትግራይ የተዘረፉ ዕቃዎችን ለማሻገር የሚቸገሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ
- በህዝብ ላይ የደረሰውን ጉዳት ያየ ህሊና አይፈቅድም እንጂ ፈገግ የሚያሰኘው ነገር፡- የኤሪትርያ ወታደሮች የኢትዮጵያን ሰራዊት በውጊያ ላይ ከመርዳት ይልቅ ከቲዲኤፍ ጋር አጋፍጠውት በዘረፋ ላይ ተጠመዱ

  http://www.aigaforum.com/article2021/are-eritreans-not-worried.htm

## 8.11 በትግራይ ጦርነት በተፈጥሮ ስነ-ምህዳር ላይ የደረሰ ጉዳት




ኢትዮጵያ ኢንሳይት (እምነት ነጋሽ፣ እምሩ ብርሃነ) 15 የካቲት 2015፤ ናሳ ብላክ ማርብል ኢሜጅ፤ (የግራ ሳተላይት ፎቶ) የመቐለ መብራት ሁኔታ፤ የማገዶ እንጨት (ምስጢር ሰው)፤ የወደመ ደንና የማክሰያ ጉድጓዶች፤ ተክለ ሃይማኖት ጂ. ወልደሚካኤል 29 ሚያዚያ 2013

---

- መላው የትግራይ ህዝብ ለሁለት አመታት መሰረታዊ አገልግሎቶች ተከልክሎና ተከቦ ነበር፤ 2.6 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ ተፈናቅለዋል፤ ለምግብ ማብሰያ ያገኙትን ማንኛውንም ነገርም እያቃጠሉ ነበር//ነው
- በዝጉ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ሲቋረጥ በኤሌክትሪክ ሃይል ይተማመኑ የነበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች ለማብሰል፤ ለማሞቅና ለሌሎች መሰል የሃይል ፍላጎቶች የእንጨት ማገዶና ከሰል መጠቀም ነበረባቸው፤ ከዚህም የተነሳ በደኖች ላይ ከፍተኛ ጫናን ፈጥረዋል

- በከተሞች አቅራቢያ ያሉ ደኖች በብዛት ተጎድተዋል። በርዕሱ ስር ያለው ምስል (ቀኝ) ከዓዲግራት በስተምስራቅ ኮማ ሲዊሃ የሚባለውን አካባቢ ያሳያል፣ይህም ኮረብታ በጥቂት ወራት ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተጨፈጨፈ የደን ሃብት ነው።
- የትግራይ ሃይልን ጨምሮ የአራት የጦርነቱ ተሳታፊዎች ከሚልዮን ያላነሱ የሰራዊት አባላት ትግራይ ላይ ፈሰው ነበር፡፡ ይህ ግዙፍ የኃይል አቅርቦት እንደሚያስፈልገው እሙን ነው፡፡ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በሌለበት ለማገዶ እንጨት መደበኛ ገበያም በቂ ባልሆነበት ወታደሮች ምግብ ለማብሰል በአካባቢው ደንኖች ላይ ጥገኛ መሆን ነበረባቸው፤ የቤትክርስትያን አጸድ ደኖችም ተበዝብዘዋል
- በተራራ ጫፍ የደን መልክአ ምድሮች (ሕጉም ብርዳ፤ ግራት ካሕሱ፤ ዴስአ) ለመከላከያ ምሽግነት ተመራጭ ነበሩ። ስለዚህ ሰፋፊ ጉድጓዶች፣ ቦዮችና ጊዜያዊ መንገዶች ተሠርተዋል። የተራራ ደኖች የጦር ሜዳዎች ሆነው ነበር
- ብዙ አገር በቀል የደን ዝርያዎች ተመናምነዋል፡፡ የዱር እንስሳትም መኖሪያቸው በመውደሙና በአደን ክፉኛ ተጎድተዋል
- የተተከሉ ችግኞች በወታደሮችና በተሽከርካሪዎች ተረግጠዋል፤ 237 የችግኝ ማቆያ ቦታዎች ጠፍተዋል
- በቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ የዝሆኖች መጠለያ ውስጥ ዝሆኖች ተፈናቅለዋል፣ ተገድለዋል። የፓርክ ተሽከርካሪዎች ተዘርፈዋል፤ መሰረተ ልማቶች ወድመዋል፡፡ የኤሪትርያ ሃይሎች ፓርኩ የሚገኝበትን አካባቢ በመያዝ ፓርኩን ጎድተውታል
- የአማራ ታጣቂ ቡድኖች በፓርኩ የነበሩትን የዱር እንስሳት እየገደሉ አቅራቢያ በሚገኘው ከተማ 'የጫካ ሥጋ ሬስቶራንት' ከፈቱ
- በትግራዩ ጦርነት በርካታ የገጠር መንደሮች ቤቶች ወድመዋል፡፡ ይህ በአካባቢ ላይ የሚኖረው የወደፊት ተጽእኖ ከባድ ነው፡፡ የትግራይ የገጠር ቤቶች በአብዛኛው የተገነቡት ከድንጋይ፣ ከእንጨትና ከጭቃ፣ ከድንጋይ የተሠሩ ግድግዳዎች ከእንጨትና ከጭቃ ጣራዎች ጋር በማጣመር ነው፡፡ ጦርነቱ ሲያበቃ የወደሙት ቤቶች እንደገና መገንባት ሊኖርባቸው ነው፡፡
- እዚህ ላይ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ሌላ አይነት የህንጻ ማቴሪያል ካልቀረበ የደኖች ውድመት በዚህ ሰበብም ሊቀጥል ይችላል

**************************************************

# ምዕራፍ ፱

# ሁለተኛው የትግራይ ወረራና የፕሪቶሪያው ስምምነት

## 9.1 መግቢያ

የተምቤን ጦርነትን ተከትሎ በ19 ሰኔ 2013 የትግራይ ሃይሎች መቐለን መልሰው ተቆጣጠሩ፡፡ እስከ ሃያ ሺ የሚደርሱ የመከላከያ ሰራዊት ምርኮኞች በትግራይ ሃይሎች እጅ ነበሩ፡፡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በትግራይ ቆይታው በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት የተነሳ ትግራይ ውስጥ መቆየት የማይችልበት ደረጃ ደረሰ፡፡ የኤሪትርያ ጦርም ቢሆን ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶበት ነበር፤ አምኖ ባይቀበልም፡፡ የአማራው ሃይል በበኩሉ ብዙ ሰው እያለቀበት ነበር፤ ሆኖም በግትርነት ጦርነቱ እንዲቀጥል መፈለጉ አልቀረም፡፡ የኤሪትርያ ሃይል ሰሜን ትግራይን እንደያዘ፤ የአማራው ደግሞ ምእራብና ደቡብ ትግራይ ዞኖችን ተቆጣጥሮ እያለ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ከትግራይ መልቀቁን በይፋ አሳወቀ፡፡

ይህ ውሳኔ በአስገዳጅ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም በጠቅላይ አዛዡ የተሰጠው ምክንያት ግን የራስንንና የሰራዊቱን ሞራል ለመጠበቅ የታሰበ እንደሆነ ግልጽ ነበር፡- “ወደ ደጅን ህዝባችን ለመመለስ፤ የትግራይ ገበሬዎች በየገጠር መንደሩ የሚያገኟቸውን የመከላከያ ስራዊት አባላት በተለያየ ዘዴ እየገደሉ ስለነበር ከህዝብ ጋር መጣላት ስለከበደን፤ የትግራይ ህዝብ ቆም ብሎ እንዲያስብና የግብርና ስራውንም በሰላም እንዲያከናውን እድል ለመስጠት”፡፡ ትግራይን የወረሩት የተባበሩት ሃይሎች አንድነት ላይ የመጀመሪያው ሰፊ ስንጥቅ የተፈጠረው በዚህ የኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል የተናጠል ውሳኔ ነበር፡፡

የአማራ ሃይሎች በውሳኔው ተከፉ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ ላይ የነበራቸው እምነትም ነፋስ ሸው አለበት፡፡ የኤሪትርያው መሪ ቁጣ ግን ከልክ ያለፈ ሆነ፡- “ተካድን” አሉ ኢሳያስ አፈወርቂ! ነገሩ አስደማሚ ነው፤ የኤሪትርያ ጦር ትግራይ የገባው የኢትዮጵያን መከላከያ ለማገዝ ከነበር “ተካድን”ን ምን አመጣው? ድጋፍ የጠየቀው ሰራዊት ሲለቅ አብሮ መልቀቅ እንጂ! የኢትዮጵያ መንግስት ትግራይን ሲለቅ ከሰጣቸው ምክንያቶች አንዱ “ወደ ደጅን ህዝባችን መመለስ” የሚል ነበር፡፡ ይህ አባባል የአፍ ወለምታም ቢሆን በአገር ክህደት ወንጀል የሚያስጠይቅ

ነበር፤ የአፍ ወለምታ አልነበረም እንጂ፡፡ ይህ አባባል የትግራይ ህዝብ ደጅን (ወገን) አይደለም ማለት መሆኑ ለመረዳት ሊቅነት አያስፈልገውም፡፡

በትግራይ ጉዳይ ላይ የአሁኑን የኢትዮጵያ ስርአተ መንግስት ልዩ የሚያደርገው የትግራይን ህዝብ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ ጆሮ ታምቡሩ እስኪበሳ ድረስ ደጋግሞ መንገሩ ነው፡፡ ሚኒሊክ፤ ሃይለስላሴ፤ ደርግ ትግራይን ሲወሩ የትግራይን ህዝብ አንድም ቀን በኢትዮጵያዊነቱ ላይ የሚተነፍሱት ህገወጥና ኢሞራላዊ ቃል አልነበራቸውም፡፡ የውጭ ወራሪዎች በየተራ ኢትዮጵያን ለመውረር በትግራይ በኩል በገቡ ቁጥር "ደሃና ረሃብተኛ" እስኪባል ድረስ በጦርነት ህይወቱንና ሃብቱን ያጣው ህዝብ ወገን እንዳልሆነ መቁጠር የሶስት ሺ ዘመናት እውነታ ነኝ ለሚለው ኢትዮጵያዊነት የሚመጥን አይደለም፡፡

"የትግራይ ህዝብ ቆም ብሎ እንዲያስብና የግብርና ስራውንም በሰላም እንዲያከናውን እድል ለመስጠት" የተባለው ለካ ሰሙ እንጂ ወርቁ አልነበረም፡፡ ወርቁ "በጦር መሳሪያ ካልተሳካ በድምጽ አልባ መሳሪያ አላማን ማስፈጸም" በሚል ውስጠ ወይራ የሃይል፤ የመገናኛ፤ የምግብ እርዳታ፤ የፋይናንስ ዝጉና ከበባው ላልተወሰነ ጊዜ ሲቀጥል ወጪ የሌለው እልቂት እውን ሆነ፡፡ እዚህ ላይ ነበር ዝጉን ከመነሻው ለማስቆም የትግራይ ሃይል ወደ አማራና አዲስ አበባ ዘመቻ የጀመረው፡፡ ዝጉን ለማስከፈት ዘጊዎቹን ማስወገድ የሚል አላማ ይዞ የተንቀሳቀሰው የትግራይ ሃይል በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ በሰፊው ተዘርግቶ ባደረጋቸው በርካታ ውግያዎች የአማራና የፌደራል ፖለቲከኞች የኢትዮጵያን ህዝብ ለዘመቻ ለማነሳሳት አመቺ ሆኖላቸው ነበር፡- "ቲ.ፒ.ኤፍ ኢትዮጵያን ሊያፈርስ ነው" በሚል፡፡

የአማራና የአፋር ክልሎች ወታደራዊ ድሎችን ተከትሎ የትግራይ ሃይሎች አዲስ አበባ ጥግ ደረሱ፡፡ የፍጻሜው ፍልሚያ በመሰለበት፤ አለም በአዲስ አበባ የመንግስት ለውጥ እንደሚኖር እርግጠኛ በሆነበት አጋጣሚ በአለም አቀፍ ጫናና በድሮኖች ፋታ የለሽ ጥቃት የተወጠረው የትግራይ ሃይል ከሃምሌ 2013 እስከ ታህሳስ 2014 ያካሄደውን ወታደራዊ ዘመቻ አቋርጦ ወደ ትግራይ ተመለሰ፡፡ የትግራይ ሃይሎች ለስድስት ወራት ያህል በአማራና በአፋር ክልል ያካሄዱት በድሎች የታጀበ ሰፊና አውዳሚ ጦርነት የትግራዩን ዝግ ከማራዘምና ከማባባስ አልፎ የፈየደው ነገር አልነበረም፡፡ የትግራይ ህዝብ በረሃብ እያለቀ በአማራና በአፋር ክልሎች ሲገኙ የነበሩት አስደናቂ ድሎች ለአዛዦቹና ለሰራዊቱ ወንዝ የማያሻግር ጊዜያዊ ዝናን አስገኝቶላቸዋል፡፡ ዝጉና

ከበባው ባስከፊ ሁኔታ ቀጠለ፤ ትግራይን የዘጋው አካል ግን እንኳንና በጦር እየተወጋሁ ነው የሚል በቂ ምክንያት አግኝቶ ጨርቁን ባይነኩትም ዝጉና ከበባው ተመችቶት ነበር፡፡

የትግራይ ህዝብ ህወሓትን አሳልፎ እስካልሰጠ ድረስ ህዝቡን ማስራብ ህወሓትን ማስራብ ማለት እንደሆነ ተተርጉሞ ዝጉና ከበባው የህጋዊነት መልክ እንዲኖረው ተሰርቶበታል፡፡ የፌደራል መንግስት የልብ ወዳጅ የነበረው የኢሳት ቲቪ ጋዜጠኛ ግዛው ለገሰ ዝጉንና ከበባውን በሚመለከት የነበረውን መደበኛ አስተሳሰብ እንዲህ ሲል አንጸባርቆታል፡-

*“ለትግራይ ህዝብ ምንም አይነት መሰረታዊ አገልግሎት የለም፣ እንደ ባንክ፣ በጀት፣ መብራት፣ ንፁህ ውሃ፣ ስልክና ኢንተርኔት ያሉ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ከፈለጉ መቶ ወይም ከዚያ በላይ ወንጀለኞችን ማስረከብ አለባቸው”*

(በኢዮብ ታደለ ገብረ ህይወት 15 ሰኔ 2014፣ ትግሃት)

ይህ መጽሃፍ በአማራና በአፋር የተካሄዱ ውግያዎች ዝርዝር ሁኔታን የሚያካትት አይደለም፡፡ በዚህ ምእራፍ ከትግራይ ውጪ የነበረውን ውጊያ በመዝለል ከሰኔ 2013 እስከ ነሃሴ 2014 ድረስ የዘለቀው የዝግና የከበባ ጨለማ ባለበት የተካሄደው ሁለተኛው ዙር የትግራይ ወረራ፤ ፕሪቶሪያና ድህረ-ፕሪቶሪያን ይተነትናል፡፡

## 9.2 ሁለተኛው ዙር ወረራ (18 ነሃሴ 2014-24 ጥቀምት 2015 ኢ.ኢ.ፒ.ኤ.)

**18 ነሃሴ 2014**
የኢትዮጵያ ፌደራል ጦርና የአማራ ሚሊሻዎች በደቡብ ትግራይ (ቾቤ በር፣ ጃኖራ፣ ጉባጋላ፣ ያሎው፣ አላማታ፣ ባላና ቢሶ በር) መጠነ ሰፊ ጥቃት ጀመሩ.
በዚህ የተሳተፉት የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር 6ኛና 8ኛ እግረኛ ዕዞች፤ 2ኛ፣ 6ኛና 8ኛ ሜካናይዝድ ብርጌዶች

**23 ነሃሴ 2014**
ቲ.ዲ.ኤፍ ጥቃቱን በመመከት በአማራ ክልል ቆቦ፣ ወልዲያ፣ ጉጉዶ፣ ፎኪሳ፣ ዞብል፣ መንደፈራ፣ ሮቢት፣ ሺዎች ማርያምና ቱክሎሽን በቁጥጥር ስር አውሏል

**26 ነሃሴ 2014**
የኤሪትርያ ወታደሮች በሰሜን ትግራይ ጥቃት ጀመሩ፤
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት አራት አቅጣጫ ያለው ጥቃት ጀመሩ፡-

- ከፊቂያ ገብረ ወደ አዳመይቲ
- ከሰላሞ ወደ ሸራሮ

- ከጎቦ ጽናን ወደ ዕርዲ ማቲዮስ
- ከዓዲ አሰር

የከባድ መሳሪያ ድብደባ ከዓዲ ጎሹ ወደ ዓዲ አሰር
ኮ/ል መኳንንት የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር 11ኛ እግረኛ ክፍለጦር አዛዥ በደቡብ ግንባር ተያዙ

**27 ነሃሴ 2014**

ውጊያው በተለያዩ ግንባሮች ቀጥሏል
የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር ትግራይን ከኤሪትርያ በኩል ለማጥቃት ወደ ኤሪትርያ ገባ

**02 ጳጉሜ 2014**

አብይ የህወሓትን የሽምቅ ውጊያ አቅም አቃለለ
በደደቢት የትግራይ ሃይሎች ከኤሪትርያ ጦር ጋር ገጠሙ
የኤሪትርያ ጦር በርካታ ግንባሮች ጥቃት ከፈተ፡- ራማ፣ ጾሮና፣ ዛላምቤሳና ዳሎል
የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር ዓዲ አርቃይን ከትግራይ ሃይሎች ቀማ ነገር ግን ደባርቅና ዳባት ሆስፒታሎች በቆሰሉ ወታደሮች ተጥለቀለቁ
የትግራይ ሃይሎች ከሱዳን በኩል የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር አጠቁ ተባለ(?)
ውጊያ በተከዜ ወንዝ፤ ወደ ደባርቅ በሚወስደው አውራ ጎዳና ላይ፤ በአበርገለ ግንባርና በአማራው ቆቦ ዙሪያ እየተካሄደ ነበር
የትግራይ ሃይል በሽራሮና በድንበር አካባቢዎች ከኤሪትርያ ጦር ጋር ገጥሟል

**03 ጳጉሜ 2014**

ኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ሁሉንም ተፋላሚ ወገኖች "ተያይዛችሁ እንጦሮጦስ እንዳትገቡ" ብሎ አስጠነቀቀ
በዩክሬን ያለው ጦርነት የምእራባውያንን ቀልብ ከትግራይ አርቆት ነበር
የተሰጡ አስተያየቶች፡- "ኢትዮጵያና ትግራይ ከውጊያው የሚያተርፉት ነገር የለም፤ ውጊያው ለሁለቱም ወገኖች አደገኛ ነው፤ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር ከፍተኛ ግጭት ይገጥማታል፤ ትግራይም በእገዳው ስር ትቆያለች፤ በአፍሪካ ህብረት ሽምጋይነት እርቅ መጀመር አለባቸው"

**04 ጳጉሜ 2014**

የትግራይና የኢትዮጵያ የሰላም ድርድር በጅቡቲ
የትግራይ ሃይል የመከላከል መስመሩን እንደጠበቀ ነው
የኤሪትርያ ጦር በሽራሮ ላይ ከባድ መሳሪያ 34 ጊዜ ተኩሶ ቤቶችን በማውደም ብዙ ሰላማዊ ዜጎችን ገድሏል አቁስሏል
የትግራይ ፕሬዝዳንት ደብረፂዮን ገብረሚካኤል ለተባበሩት መንግስታት ሴኩሪቲ ካውስል፤ ለፈረንሳይና ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ መልእክት ልከዋል፡- "ትግራይና ህዝቦቿ እንዲጠፉና እንዲሸነፉ ከሚፈልጉ ሃይሎች ጋር

ለራሳቸው ህልውናና ክብር እየታገሉ ነው”

- እገዳውን በአስቸኳይና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማንሳት
- አገልግሎቶችን እንደገና መጀመር
- ያልተገደበ የሰብአዊ ረድኤት
- የኤሪትርያ ኃይሎችን መልቀቅ
- የትግራይ መሬትና ድንበር ወደ ቅድመ ጦርነት ሁኔታ መመለስ

ጦርነቱ አሁንም በተለያዩ ግንባሮች እየተካሄደ ነው

ምግብና መድሃኒት በመፍቀድ ነገር ግን ነዳጅና ጥሬ ገንዘብ በመከልከል የሰብአዊ እርቁ ተበላሽቷል

**02 መስከረም 2015**

የትግራይ መንግስት በአፍሪካ ህብረት መሪነት የሰላም ሂደት ላይ ለመሳተፍ መዘጋጀቱን አስታወቀ

አሜሪካ የአማራ ሃይሎች ከምእራብ ትግራይ እንዲወጡ ጥሪ ሳያቀርብ የትግራይ ሃይል ከአማራ እንዲወጣ ጥሪ አቅርቧል

**04 መስከረም 2015**

የትግራይ ሃይል  ከኢትዮጵያ ፌደራል ጦር፤ ከአማራና ከኤሪትርያ 100 ምድቦች ጋር ተዋግቶ አብዛኞቹን አሸንፏል

የትግራይ ሃይል የኢትዮጵያ ፌደራል ጦር 23 የእግረኛና አንድ ሜካናይዝድ ክፍለጦሮችን አሸንፏል

የትግራይ ሃይል  3 የአማራ ሃይል ምድቦችን በደደቢትና በዓዲ አርቃይ ግንባር አሸንፏል

**05 መስከረም 2015**

የትግራይ ሃይል አሁንም መስመሩን እንደያዘ ነው፤ ወደ ፊት ሊገፋ ይችላል፣ ነገር ግን በስትራቴጂካዊ ምክንያቶች ካለበት መቆየትን መርጧል

ሽራሮና አደሚቲ በኤሪትርያና ኢትዮጵያ ጦር ተይዘዋል፤ ነገር ግን ተጨማሪ ግስጋሴአቸው ተገቷል

በደደቢት የተከዜን ወንዝ የተሻገሩት 70,000 ኢትዮጵያ ወታደሮች ከደረሱበት ላይ ተገተዋል

በኤሪትርያ አጠቃላይ ንቅናቄ ታውጇል፤ እስከ 55 አመት እድሜ ያለው በሙሉ እንዲመዘገብ ታዟል

**10 መስከረም 2015**

ማይ ኩሕሊ፣ ዝባን ገደና፤ አዲ አውዓላ (አዲያቦ)፣ ራማ፣ ጾሮና፤ ዛላምበሳ (ሰሜናዊ ድንበር) ከባድ ውጊያ እየተካሄደ ነው

ኢትዮጵያ ጦር ምስራቃዊ እዝ፣ የሰሜን ምዕራብ እዝና ሶስት የኮማንዶ

ክፍለጦሮች ከኤሪትርያ ሰራዊት ጎን ሆነው ይዋጋሉ
የኢትዮጵያ ጦርና የኤሪትርያ ሰራዊት ከተከዜ (ትግራይ ሰሜናዊ ምእራብ ጽንፍ) እስከ ኢሮብ (ትግራይ ሰሜናዊ ምስራቅ ጽንፍ) ተዘርግተዋል
የትግራይ ሃይል ዓዲ አርቃይን መልሶ ያዘ፤ የኢትዮጵያ ጦርና የአማራ ሃይሎች ወደ ዛሪማ አፈገፈጉ

**17 መስከረም 2015**

የኤሪትርያ ሰራዊት ኢሮብና ዓዲግራትን በመድፍ ደበደበ፤፤ ኢትዮጵያ ጦር ሽረ ላይ የሮኬት ጥቃት አደረሰ፣ መቐለና ዓዲ ዳዕሮ (በኤሪትርያ አየር ሃይል?) የአየር ድብደባዎች ተካሄዱ

**18 መስከረም 2015**

የኤሪትርያ ሰራዊት ትግራይን ከበራሕለ (አፋር) በኩል አጠቃ
የኤሪትርያ ሰራዊት ክፍለጦሮች፡ 22፣ 30፣ 38፣ 61ና 67 ተሸንፈዋል
ሽረ አቅራቢያ የኤሪትርያ ሰራዊት በዓዲ ኾኾብ ላይ የአየር ድብደባ አካሄደ

**20 መስከረም 2015**

የኤሪትርያ ጦር በተለያዩ ግንባሮች ወታደሮችን ለማቆየት የሎጂስቲክስ ፈተና ገጥሞታል

**23 መስከረም 2015**

የትግራይ ሃይሎች የኢትዮጵያ፤ የአማራና የኤሪትርያ ሃይሎችን መጠነ ሰፊ ጥቃት በተሳካ ሁኔታ መቋቋሙን ቀጥሏል፤ እስከ አሁንም ከ93,000 በላይ የኢትዮጵያ የአማራና የኤሪትርያን ወታደሮች ገድሏል፤ አቁስሏል ከ10,000 በላይ ወታደሮችም ተማርከዋል
16 ታንኮችን ጨምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው ከባድ መሳሪያዎች ወድመዋል። 3 ቲ-72 ታንኮች፣ መካከለኛና ቀላል የጦር መሳሪያዎች፤ ወታደራዊ የመገናኛ ራዲዮዎችን፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ከባድ መሳሪያዎች ተማርከዋል

**27 መስከረም 2015**

የተሳተፉት የኢትዮጵያ ወታደሮች 750.000 የትግራይ ሃይሎች ደግሞ 250,000 ያህል ተገምቷል

**02 ጥቅምት 2015**

የኢትዮጵያና የኤሪትርያ ወታደሮች ዓዲ ዳዕሮንና አዲ ኾኾብን ያዙ፤ በሽረ ላይ ከፍተኛ የቦምብ ጥቃት ፈጽመው ወደ ከተማዋ እየገሰገሱ ነው

**04 ጥቅምት 2015**


በትግራይ-አፋር ድንበር በራሕለ አቅራቢያ ከባድ ውጊያ ቀጥሏል
በአዲያቦ፣ ዛላምበሳና ራማ ግንባሮች ከከሸፈባቸው በኋላ የኢትዮጵያ፤ የአማራና

የኤሪትርያ ሃይሎች በደቡብና በዓዲ አርቃይ ግንባሮች አዲስ ወረራ ጀመሩ
**07 ጥቅምት 2015**
የኢትዮጵያ ሰራዊት በደቡብ ትግራይ በዋጃ፣ ጥሙጋ፣ አየር ማረፊያና አላማጣ ላይ ከባድ መሳሪያ ተኮሰ
ትግራይ የአፍሪካ ህብረት አፋጣኝ የተኩስ አቁም ጥሪን በደስታ ተቀበለች። ነገር ግን የህልውና ትግሉን ለመቀጠል ቃል ገባች
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት በትግራይ ከተሞች ላይ የመደዳ ቦምብ ጥቃት ፈጽመዋል (ቴዎድሮስ አድሓኖም እንደገለጹት)
በመቐለ ዙሪያ ያሉ ሰዎች መኖሪያቸውን ለቀው ደህንነቱ ወደተጠበቀው ወደ ኢትዮጵያ ሰራዊት እንዲሄዱ የሚያስጠነቅቁ በራሪ ወረቀቶች ተበተኑ
**08 ጥቅምት 2015**
የትግራይ ማዕከላዊ ዕዝ ሁሉም አቅም ያላቸው የትግራይ ተወላጆች የትግራይ ሃይሎችን እንዲቀላቀሉና ሁሉም የትግራይ ተወላጆች ህልውናቸውን ለማረጋገጥ ትግላቸውን እንዲቀጥሉ ጠይቋል
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት ሽረን፣ አላማጣንና ኮረምን ያዙ
ከሽሬ ወደ አኹሱም በሚወስደው መንገድ ላይ በሰለኽለኻ ውጊያ ቀጠለ
በአኹሱም ላይ ሰው አልባ አውሮፕላን ብዙ ሰዎችን ገደለ አቆሰለ
**09 ጥቅምት 2015**
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት አባላት ሽረ ውስጥ ወጣቶችን ገድለዋል፣ የተዘረፉ እቃዎችን ወደ ኤሪትርያ ጭነዋል
**10 ጥቅምት 2015**
ወራሪው ሃይል የትግራይን ሃይል ለማሸነፍና ትግራይን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ከፍተኛ ሃይል ተጠቅሟል፤ "ከፀሀይ በታች ያለውን ሁሉ" እያደረገ ነበር
በጀግንነት ቢዋጋም የትግራይን ሃይል ማለቂያ የሌለውን የጦር መሳሪያና የሰው ማእበልን ማሸነፍ አልቻለም
በትግራይን ሃይል በኩል መራራ ውሳኔ የሚወሰንበት ሰአት ደረሰ
የኢንተርናሽናል ክራይሲስ ግሩፕ ባልደረባ ዊልያም ዴቪሰን የትግራይ ሃይል የትጥቅ ትግል ለመጀመር ማሰቡን በመቃወም ምክር ለግሷል፡- "የትግራይን ህዝብ የተቃውሞ መንፈስ ለመስበር የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት በሰላማዊ ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ከባድ እርምጃዎች ሊወስዱ ይችላሉ"
አንዳንድ ዲፕሎማቶች ባሾለኩት ምስጢር መሰረት ኢትዮጵያና ኤሪትርያ ህወሓትን ከህዝብ ድጋፍ ለማግለል የህዝብ ማጎሪያ ካምፖችን እያቀዱ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠቁመዋል
የትግራዩ ጀኔራል ጻድቃን "አለም ሌላ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊያይ ይችላል" ሲሉ አስጠንቅቀዋል

**11 ጥቅምት 2015**
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት አኹሱም ላይ ተገናኙ
የትግራይ ሃይል 9000 ምርኮኞችን ለቀቀ
ከ437 እስከ 914 የትግራይ ተወላጆች በየቀኑ በረሃብ ይሞታሉ (ጃን ኒሰን)
የአውሮፓ ህብረት ቱርክ ሰው አልባ አውሮፕላኖች ለኢትዮጵያ መሸጧን
አላወገዘም ምክንያቱም ቱርክ ለዩክሬን የሰው አልባ አውሮፕላኖች መሸጧ
ለውይይት እንዳይቀርብ" (ጃን ኒሰን እንዳጋለጠው)
**13 ጥቅምት 2015**
ዓቢዩ ዓዲ ላይ በሰው አልባ አውሮፕላን ጥቃት ህጻናትን ጨምሮ በርካታ ሰዎች
ተገደሉ
**14 ጥቅምት 2015**
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት ከባድ የጦር መሳሪያ ህዝብ በሚበዛባቸው
የኢሮብ ከተሞችና መንደሮች ላይ ጥቃት ሰነዘሩ
ዓድዋ፣ ማይቅነጣል፣ ወርቃምባና አካባቢው በሰላማዊ ሰዎች ላይ ያነጣጠረ የአየር
ድብደባ
መቐለ ላይ የሰው አልባ አውሮፕላን ጥቃት ደረሰ
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት አኹሱምን ይዘው ወደ ዓድዋ ገሰገሱ
**15 ጥቅምት 2015**
የኤሪትርያ ሰራዊት ከዓዲግራት ወደ መቐለና ከዓዲግራት ወደ ዓድዋ
የሚወስደውን አውራ ጎዳና ተቆጣጥሮ በመንገዱ ላይ እየገሰገሰ ነው.
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት ደብረ ገነትንና ለጋሚቲን ይዘው ወደ ማይ
ቅነጣል ገሰገሱ
በደቡብ አፍሪካ የሰላም ድርድር ተጀመረ
**16 ጥቅምት 2015**
የትግራይ ሰራዊት በገንደብታ(ዓድዋ) ከ40 በላይ የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት
ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችን አወደመ
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ዓድዋ በሚገኘው አልመዳ
ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አቅራቢያ ወድመዋል
**17 ጥቅምት 2015**
አሜሪካ ለፕሪቶርያው ድርድር ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረች ነው
ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ፕሬዝዳንት
ሼክ መሀመድ ቢን ዛይድ ጋር ተገናኝተው ጦርነቱ በአስቸኳይ እንዲቆም
ተወያይተዋል
የአውሮፓ ህብረት በሰላሙ ሂደት ውስጥ ያለው ሚና የማይታይ ሆኗል


**18 ጥቅምት 2015**
የትግራይ ሰራዊት ምንም አይነት ስልታዊ መሬት አልለቀቀም
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት በዓድዋ በአብያተ ክርስቲያናትና በመኖሪያ ቤቶች የተጠለሉ ሰላማዊ ዜጎችን ገደለ
"የሰላም ድርድሩ ስኬት በከፊል በኤሪትርያ ላይ በሚደረገው ጫና ላይ የተመሰረተ ነው" ማርክ ሎውኮክ (የተባበሩት መንግስታት)
**21ጥቅምት 2015**
ሓውዜንን ለመቆጣጠር በማለም አርባ ዘጠኝ የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊት ክፍለጦሮች ተሰማሩ
የትግራይ ሃይል ፈላፊል ላይ በኤሪትርያና ኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል
የትግራይ ሃይል ከዓድዋ ወደ ማርያም ሸዊቶ ሲንቀሳቀሱ በነበሩ 5 የኤሪትርያ እግረኛ ክፍለጦሮች፣ 2 የኢትዮጵያ ሰራዊት እግረኛ ክፍለጦሮችና አንድ የኤሪትርያ ሜካናይዝድ ክፍለጦርን አሸንፏል
በሰሜን ምዕራብ ትግራይ በእንዳባጉና፣ በሰለኽለኻ፤ በውቕሮ-ማራይና በሌሎች አካባቢዎች ጦርነቶች ተካሂደዋል
የኤሪትርያ ሰራዊት ከበራሕለ ወደ ውቕሮ ገሰገሱ
የኢትዮጵያ ሰራዊትና ፋኖ ከማይ ጸምሪ ወደ ሽረ የሚወስደውን መንገድ በሙሉ ተቆጣጠሩ
በዛላምበሳ ዙሪያ ከፍተኛ ውጊያ ሲደረግ የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ሰራዊቶች ዓዲግራትን ለመቆጣጠር የትግራይ ሃይል መከላከያዎችን ለመስበር ሞክረዋል
የኤሪትርያ ወታደሮች በድርድሩ ወቅት ሰላማዊ ዜጎችን መግደላቸውን፤ ተሽከርካሪዎችንና የቤት እቃዎችን መዝረፋቸውን ቀጥለዋል
የኤሪትርያና የኢትዮጵያ ወታደሮች በዋጃ፣ ላምባዲና፣ ኮረምና አላማጣ ሰላማዊ ሰዎችን ገድለዋል
**23ጥቅምት 2015**
ከዓድዋ፣ አኹሱም፣ ዓዲግራት፣ ውቕሮ፣ ኮረምና አላማጣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተፈናቃዮች ወደ መቐለ ገቡ
በእንዳጭዋ (እንዳባ ጻሕማ) አቅራቢያ ላይ የአየር ድብደባ ተካሄደ
የኤሪትርያ ሰራዊት መኮንኖች ለኢሳያስ እንዲህ ብለው ነገሩት፡- "ጦርነቱን ማሸነፍ አይቻልም፤ ሰራዊቱም ምንም ሞራል የለውም"
የኤሪትርያ ሰራዊት የኢትዮጵያን ሰራዊት ሲረዳ የነበረው በመጀመሪያ በስለላ፤ ከዚያም በከባድ የጦር መሳሪያ ሽፋን፣ ቀጥሎ በቀጥተኛ ተሳትፎ" (መስፍን ሓጎስ)

## 9.3 የፕሪቶያው የሰላም ስምምነት (24 ጥቅምት 2015)




<u>አንቶንዮ ጉተሬዝ፤ የተ.መ.ድ. ዋና ፀሃፊ 08 መስከረም 2015</u>
“የትግራይ ጦርነት ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁከትና ውድመት አስደንጋጭ ደረጃ ላይ ደርሷል። ማህበራዊ ግንኙነቱ እየተበጣጠሰ ነው፡፡ በትግራይ የሚሰራው የጠላትነት ተግባር አሁን ማብቃት አለበት”

<u>ሰልማን ሩሽዲ</u>
“ከረጅምና ተስፋ ቢስ ጦርነት በኋላ ሰዎች ማንኛውም ዋጋ ከፍለው ለሰላም ይቆማሉ”


African Union

AGREEMENT FOR LASTING PEACE
THROUGH A
PERMANENT CESSATION OF HOSTILITIES
BETWEEN
THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE TIGRAY PEOPLE'S LIBERATION FRONT (TPLF)


AGREEMENT FOR LASTING PEACE THROUGH A PERMANENT CESSATION OF HOSTILITIES
BETWEEN
THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE TIGRAY PEOPLE'S LIBERATION FRONT (TPLF)

PREAMBLE


Article 14 - Effective Date

Article 15 - Amendments to this Agreement

For the Government of the FDRE

For the Tigray People's Liberation Front

1. **ጦርነቱን ለዘለቄታው ማቆም**
    - ሁሉም ዓይነት ግጭቶች የተከለከሉ ናቸው
    - ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የውክልና ጦርነቶች
    - የጥላቻ ንግግር፣ ፕሮፓጋንዳ፣ የአየር ድብደባ፤ ፈንጂዎች
    - ከውጭ የጠላት ኃይል ጋር መተባበር.
2. **የሲቪሎች ጥበቃ**
    - ሲቪሎችን ከሰብአዊ መብት ጥሰት
    - ጾታዊና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት
    - በልጆች ላይ የሚደርስ ጥቃት (የህፃናት ወታደሮችን መጠቀምን)
    - በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት

- በአረጋውያን ላይ የሚፈጸም ጥቃት

**3. የሰብአዊነት ተደራሽነት**

- በተቻለ ፍጥነት ሰብአዊ እርዳታን መፍቀድ
- የተፈናቀሉ ሰዎችንና ስደተኞችን መመለስ ቤተሰቦችን ማገናኘት
- እርዳታን አላግባብ አለጠቀም፣ ለሰብአዊ ዓላማዎች ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ

**4. ትጥቅ ማስፈታት፣ ማሰናበትና እንደገና መቀላቀል**

- ክፍት የመገናኛ ቻናል ስምምነቱን ከተፈራረመ በ24 ሰአት ውስጥ መፈጠር አለበት
- ሁለቱም ወገኖች ኢትዮጵያ "አንድ የመከላከያ ኃይል ብቻ እንዳላት መገንዘብ አለባቸው
- የትግራይ አማፂ ሃይሎች ከተፈራረሙ በ30 ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ትጥቅ ማስፈታት ማሰናበትና እንደገና መቀላቀል አለባቸው.

**5. መተማመንን የሚገነቡ እርምጃዎች**

ህወሓት የተስማማው:-

- የመንግስትን ስልጣን ለማክበር
- በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ካሉ ከማንኛውም የታጠቁ ወይም አፍራሽ ቡድኖች ጋር ከመረዳዳትና ከመደገፍ ወይም ከመተባበር መቆጠብ
- የፌደራል መንግስት ወታደሮችንና የጸጥታ ሃይሎችን ወደ ትግራይ የመላክ ህገ መንግስታዊ ስልጣንን ማክበር
- ወታደራዊ ሃይሎችን አለመመልምል፣ አለማሰልጠን፤ አለማሰማራት ወይም ለግጭት የዝግጅት እርምጃ አለመወሰድ
- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ማክብር፣ በራሱም ሆነ ከውጭ ኃይሎች ጋር ባለው ግንኙነት ይህንን አለመቃረን
- ሕገ መንግሥታዊ ባልሆኑ መንገዶች በመንግሥት ላይ ለውጥ አለማድረግ

መንግስት የተስማማው:-

- በተዋጊዎች ላይ ሁሉንም ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ማቆም
- በተቻለ ፍጥነት ለትግራይ መሰረታዊና አስፈላጊ አገልግሎቶችን ወደነበረበት መመለስ
- ህወሓትን በአሸባሪነት መፈረጅ ማቆም.
- ወደ ትግራይ ያለ ምንም እንቅፋት ሰብአዊ እርዳታን አሳልፍ

6. ዓለም አቀፍ ድንበሮችና የፌዴራል መገልገያዎች

- የፌደራል ሰራዊት በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ድንበሮች ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ ይሰፍራል፤ የሀገሪቱ ደህንነት ከውጭ ወረራና

ከድንበሩ በሁለቱም በኩል ምንም አይነት ቅስቀሳ ወይም ወረራ እንደማይኖር ያረጋግጣል

- የፌደራል ባለስልጣናት በትግራይ የሚገኙ ሁሉንም የአቪዬሽን ቦታዎች፣ አየር ማረፊያዎችና አውራ ጎዳናዎች በሙሉ ውጤታማ ቁጥጥር ያደርጋሉ

**7. የፌደራል ባለስልጣንና የትግራይ ውክልና መመለስ**

- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት በትግራይ ክልል መቀሌ ዋና ከተማን ጨምሮ እንደገና ስልጣን እንዲመሰርት ሊፈቀድለት ይገባል
- የፌደራል ሰራዊትና ሌሎች የሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋማት ፈጣን፣ ሰላማዊና፣ በተቀናጀ መንገድ ወደ ከተማዋ መግባት አለባቸው
- በምትኩ መንግስት የኢትዮጵያን ህገ መንግስት እንዳይጥስ፤ ትግራይ በመንግስት ተቋማት ውስጥ በትክክል እንድትወከል ዋስትና ይሰጣል

**8. የሽግግር እርምጃዎች**

- የህወሓት የሽብር ስያሜ በተወገደ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ነገር ግን ምርጫ ከመደረጉ በፊት አካታች የክልል አስተዳደር መመስረት አለበት
- የአሸባሪው ስያሜ ከተወገደ ከአንድ ሳምንት በኋላ ሁለቱም ወገኖች ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማግኘት የፖለቲካ ውይይት ማድረግ አለባቸው.
- ኢትዮጵያም ተጠያቂና ሃቀኛ ለመሆን ያለመ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለማቋቋምና ለተጎጂዎች ፍትህ ለመስጠት ተስማምታለች
- በተጨማሪም ሁለቱም ወገኖች የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥት በሚያከብር መልኩ "የአከራካሪ አካባቢዎች" ጉዳዮችን ለመፍታት ቃል ገብተዋል

<u>**ክትትል፤ ማረጋገጫና ተገዢነት**</u>

ይህ ሂደት ከኢትዮጵያ መንግስት፣ ከህወሓትና ከመንግስታት የልማት ባለስልጣን (ኢጋድ) የተውጣጡ አንድ አንድ ተወካዮች ያሉት "የጋራ ኮሚቴ" ክትትል እንዲደረግበት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ሁሉም በአፍሪካ ህብረት በ"ከፍተኛ ደረጃ ፓነል" ይመራሉ

## 9.4 “እርግብና ነፍጥ” ከሰላም ስምምነት እስከ ጊዜያዊ መንግስት

የአውሮፓ የውጭ ፕሮግራም ለአፍሪካ (ኢኢፒኤ ሆርን)፣ ትግሃት፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፤ ትግራይ ቲቪ፣ ዲደብሊው ኢንተርናሽናል፣ የክልል መንግስት

**24 ጥቅምት 2015**

- ውጊያው ቀጠለ፤ በማይጨው፤ በዓዲግራትና በእንቲጮ የአየር ድብደባዎች

**25 ጥቅምት 2015**

- የትግራይ መንግስት እንዲህ ይላል፡- የሰላም ስምምነት የትግራይን ህዝብ ጥቅም የሚጎዳ ከሆነ ተግባራዊ አይሆን፡፡ ትግራይ የፈረመው ህገ መንግስቱ የስምምነቱ ማዕከል ነው ብሎ ስላመነ ነው
- በጦርነቱ ወቅት ለተፈፀሙት ወንጀሎች መደበኛ ተጠያቂነት ባለመኖሩ የስምምነቱ አፈፃፀም ተግዳሮቶችን ሊገጥመው ይችላል፡፡ ለወንጀሉ አፈጻጸም አመራር የሰጡት አሁንም በስልጣን ላይ ናቸው
- የሰላም ስምምነቱ ስለ ምእራብ ትግራይ ቀጥተኛ ምልከታ የለውም
- የውጭ ክትትል አጋሮች መኖር ወሳኝ ነው
- ለአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን ሙሉ ፈቃድ መስጠት
- የሰላም ስምምነቱ ኤርትራን በግልጽ አላሰፈረም
- የ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አንድ ወገን መሆኑን በመግለጽ ተቃውመዋል፤ እንዲህ ብለው መግለጫ ስለሰጡ፡- "የኢትዮጵያ የሰላም ሃሳብ መቶ በመቶ ተቀባይነት አግኝቷል"
- የአየር ድብደባ በክልተ አወላዕሎ
- በማይጨው (ደቡብ ትግራይ) በሰላማዊ ሰዎች ላይ ከባድ የመድፍ ጥቃት ደረሰ
- ከባድ ውጊያ ቀጠለ
- የኤሪትርያ ጦር በዛላምበሳ የትግራይ ህይሎችን መከላከያ መስመሮች አጠቃ
- ከባድ ጦርነቶች በዕዳጋ ዓርቢና በነበለት (መካከለኛው ትግራይ)
- ከባድ ጦርነት በደቡብ ትግራይ

**28 ጥቅምት 2015**

- የናይሮቢ ስብሰባ የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ
- በትግራይ የመሰረተ ልማት ውድመት ወደ 20 ቢሊዮን ዶላር አካባቢ ደርሷል

- ጂ.ኤስ.ቲኤ.ስ. ስምምነቱን በደስታ ቢቀበልም  የትግራይ ህዝብ ደህንነት ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው በሚል የህወሓት ትጥቅ ማስፈቱን ተቃወመ

**29 ጥቅምት 2015**

- ኤርትራ የአማራ ክልል መንግስት የአማራን ጥቅም የሚጻረር የሰላም ስምምነቱን ውድቅ እንዲያደርግ ጠይቃለች

**30 ጥቅምት 2015**

- ትግራይ የኤርትራና የአማራ ወታደሮች ትጥቅ ማስፈታት ከመጀመሩ በፊት ትግራይን ለቀው እንዲወጡ አጥብቃ ጠይቃለች
- ትግራይ ከባድ መሳሪያ በቅድሚያ እንዲሰጥ፣ ከዚያም የኢትዮጵያ ሰራዊት የጸጥታና የድንበር ሀላፊነቱን እንደሚወስድ፤ ከዚያም የኤርትራና የአማራ ሃይሎች ትግራይን ለቀው እንዲወጡ ኢትዮጵያ አጥብቃ ትከራከራለች
- የፋኖ ሚሊሻዎች የሰላም ስምምነቱ የአማራን ጥቅም የሚጻረር ነው ሲሉ አውግዘዋል ምክንያቱም በህገ መንግስቱ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ
- የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ የሰላም ስምምነቱ የአማራ የወልቃይትና የራያ ይገባኛል ጥያቄ እውቅና አልሰጠም ብሏል
- የትግራይና የኢትዮጵያ ሰራዊት አባላት ገንባር ላይ ምግብና ሲጋራ ይለዋወጣሉ
- የኤሪትርያ ሰራዊት በዓድዋ አቅራቢያ በዕዳጋ ዓርቢ፣ በነበበትና ላይ ተኩሷል
- በቀርሰበር የኤሪትርያ ሰራዊት የጅምላ ግድያ
- የኤሪትርያ ሰራዊት ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ በተሰነይ በኩል የሚመለሱ በመቶዎች የሚቆጠሩ አውቶቡሶችን ዘግቷል
- የትግራይና የኤሪትርያ ሰራዊቶች ውጊያ በዛላምበሳና በዕዳጋ ዓርቢ ቀጥሏል
- የኤሪትርያ ሰራዊት ዓዲግራትን በመድፍ ሲደበድብ ነዋሪዎች ወደ አካባቢው ተራሮች ይሸሻሉ

**01 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት ከእንዳባጉና-ሽሬ-ዓድዋ-ማይቅነጣል መንገዶችን እየተቆጣጠረ ነው
- የኤሪትርያ ሰራዊት  በዓድዋ ዙሪያ ከትግራይ ሃይሎች ጋር እይተዋጋ ነው

- የኤሪትርያ ሰራዊት  በብዙ የትግራይ አካባቢዎች ከፍተኛ ዘረፋ፣ ግድያና ውድመት እያደረሰ ነው
- የትግራይ ነፃነት ፓርቲ ህወሓት ከትግራይ የፖለቲካ ህይወት እንዲነሳ ጠይቋል፤ ምክንያቱም ህወሓት ስምምነቱን የፈረመው ከሌሎች ፓርቲዎችና ከትግራይ ህዝቦች ጋር ሰፊ ምክክር ሳይደረግ ነው
- የኢትዮጵያ መከላከያ ወታደሮች በጋራ ስምምነት የትግራያ ሃይል በሚቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሙታናቸውን እየቀበሩ ነው
- የዓለም ጤና ድርጅት ከስምምነቱ ከአንድ ሳምንት በኋላ ምንም አይነት የምግብና የህክምና እርዳታ ወደ ትግራይ እንደማይገባ አስታውቋል

**05 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት ከትግራይ የመውጣት ምልክት አላሳየም
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ የአደጋ ስጋት አስተዳደር ኮሚሽን ወደ ትግራይ የሚገቡ ሰብአዊ ኮሪደሮች በሙሉ መከፈታቸውን አስታውቋል. ይሁን እንጂ የእርዳታ ድርጅቶች አሁንም ፈቃድ እየጠበቁ ነው
- የኢትዮጵያ ሰራዊት አባላትና የፌደራል ፖሊስ በሽሬ ሰዎችን በቁጥጥር ስር አውለዋል
- የኢትዮጵያ ሰራዊት የቤት ለቤት ዘረፋ በሽሬና አኹሱም
- የኤሪትርያ ሰራዊት አሁንም በተለይ በሽራሮ እየዘረፈ እየገደለ ነው

**06 ህዳር 2015**

- የአፍሪካ ህብረት በፕሪቶሪያ ስምምነት ለትግራይ መንግስት እውቅና ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ የትግራይ ልኡካን በህወሓት ስም እንዲፈርሙ አድርጓል
- ህወሓት የፈረመው ጦርነቱ የማቆም ስኬት እንዳይሰናከል ለመከላከል ነበር
- የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጉዳይ  በፖለቲካዊ ውይይት ይስተናገዳል
- ኤርትራ የፕሪቶርያን ስምምነት ለማሰናከል በጀመረቺው ዘመቻ ከዴምሂት (ጸረ-ህወሓት የትግራይ ታጣቂ ቡድን) በኤርትራና ከፋኖ ሚሊሻ በአማራ ክልል ጋር በመተባበር ላይ ትገኛለች

- ምንም እንኳን እርዳታ መምጣት ቢጀምርም የሚጣበቀው ግን ገና ብዙ ነው
- የአማራ ባለስልጣናት 3,000 የትግራይ ተወላጆችን ከምእራብ ትግራይ ማጎሪያ ካምፖች ወደማይታወቅ ቦታ አዛወሩ

**07 ህዳር 2015**

- ሳልሳይ ወያነ ትግራይ (ሳወት) እንዳሉት፡_ ስምምነቱ የትግራይን ህዝብ ጥቅም አይወክልም፣ የግጭቱን ዋና መንስኤዎች አይመለከትም፤ እናም ፓርቲው በህዝበ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ የትግራይን ነፃነትና የግዛት አንድነት ለማስፈን፤ ወንጀል ፈጻሚዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ትግሉን ይቀጥላል
- የታላቋ ትግራይ ብሔራዊ ኮንግረስ (ኤን.ሲ.ጂ) ደግሞ እንዲህ ይላል፡- ስምምነቱ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ባይችልም የትግራይ ተወላጆች የስምምነቱን እድሎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲጠቀሙ ያሳስባል
- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል (ኢ.ኢ.ፒ) በሑመራና በሽራሮ የኤሌክትሪክ መስመሮችን ጠገነ
- በሽረ የቀይ መስቀል አለም አቀፍ ኮሚቴ የሙከራ በረራ አደረገ
- ኮንሾይ ማይ ፀምሪ ደርሷል
- የአማራ ፋኖ ሚሊሻዎች ሀይማኖታዊና ባህላዊ ቅርሶችን ለመድፈር፣ ለማጥፋትና፤ ለመዝረፍ ወደ ሽረ፣ አኹሱምና ዓድዋ ተልከዋል

**08 ህዳር 2015**

- የትግራይ መንግስት በፕሪቶሪያ የጦርነት ማቆም ስምምነትና በናይሮቢ የአተገባብር ስልቶች ላይ በየደረጃው ላሉ የሲቪል አስተዳደርና የህወሓት አመራሮች ገለጻ አድርጓል
- የኤሪትርያም ሆነ የፋኖ ሃይሎች ትግራይን ለቀው እንደሚወጡ የሚጠቁም ምንም ፍንጭ የለም
- በዚህ ሳምንት ሶስት የጭነት መኪናዎች ከደረሱ በኋላ በትግራይ መንግስት ቁጥጥር ስር ባሉ የትግራይ አካባቢዎች ምንም ተጨማሪ እርዳታ አልደረሰም

**09 ህዳር 2015**

- “የፕሪቶሪያ ስምምነት በአቢይ መንግስት ረሃብን በመጠቀም የትግራይ አመራሮች እጅ እንዲሰጡ ለማስገደድ ነው” (አሌክስ ደ ዋል- ደብሊው ኤፍ ኤፍ)

- በትግራይ ዋና ከተማ የደረሱት ሁለት የቀይ መስቀል አለም አቀፍ ኮሚቴ የጭነት መኪናዎች ብቻ ናቸው
- የኤሪትርያ ሃይል ሰላማዊ ዜጎችን መግደሉን ቀጥሏል፣ ዘረፉና ንብረት ማውደሙም ሳይቀር

**12 ህዳር 2015**

- ኤርትራ ከስምምነቱ በኋላ ተጨማሪ ወታደሮችን ወደ ትግራይ አሰማርታለች

**13 ህዳር 2015**

- ዓዲግራት ከ142, 000 በላይ ተፈናቃዮችን እያስተናገደች ነው፡፡ ተፈናቃዮቹ ከጉሎመኸዳ፣ ዛላምበሳ፣ ኤሮብና ጋንታ-አፈሹም የጎረፉ ናቸው፡፡ሌሎች ተፈናቃዮች ከመካከለኛውና ከሰሜን ምእራብ የትግራይ ዞኖች እየመጡ ነው
- የኤሪትርያ ሰራዊት ከዓዲግራት በስተሰሜን 7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል

**14 ህዳር 2015**

- የትግራይ ተዋጊዎች ትጥቅ የማስፈታት ፕሮቶኮሎችና የመልቀቅ ጉዳይ ገለጻ ተደርጓል
- የትግራይ መሪዎች ስምምነቱ አንድ ወገን እንደሆነ ስለሚሰማቸው እያወላወሉ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ፌደራል ወደ ትግራይ የሚመጣውን የእርዳታን ማጓተት
- ትግራይ አዲስ አበባ ከአስመራና ከአማራ ጋር እንዲራራቁ ይፈልጋል

**15 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት በተለያዩ የምስራቅ ትግራይ አካባቢዎች መግደል፣ መዝረፍና ማጥፋት ቀጥለዋል

**19 ህዳር 2015**

- የኃይል ማከፋፈያዎች እዚህና እዚያ እየተጠገኑ ነው፡- ሽረ፣ አኹሱምና ዓድዋ

**20 ህዳር 2015**

- ወደ ሶማሊያና ኢትዮጵያ የሚመላለሱት የኤርትራ ባለስልጣናት የኤርትራ ወታደሮች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆዩ ለማድረግ ያለመ ክልላዊ “መከላከያ ጥምረት” ለመፍጠር መሞከራቸውን ሊያመለክት ይችላል
- የኤሪትርያ መከላከያ ሃይል የትግራይ ወጣቶችን ለግዳጅ ሥራና ለጾታዊ ባርነት ወደ ኤርትራ ጠልፎ እየወሰደ ነው

- ለትግራይ የሚደረገው እርዳታ አሁንም ፍላጎቱን ለማሟላት በቂ አይደለም፡- 5 ሚሊዮን ሰዎች የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል
- ባለሥልጣናቱ በትግራይ አገልግሎት ወደነበረበት ለመመለስ የጊዜ ሰሌዳ የለም ይላሉ

**21 ህዳር 2015**

- የፌደራል መንግስት በጦርነቱ ማቆም ስምምነት መሰረት ግዴታውን ለመወጣት ቀርፋፋ ሆኗል
- የባይደን አስተዳደር የኢትዮጵያ መንግስት ወደ ትግራይ ቴሌኮሙኒኬሽን እንዲመለስ ጠይቋል
- በሑመራ፣ በሽረ፣ በአኹሱምና በዓድዋ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ጥገና
- የትግራይ ሰራዊት ከኤሪትርያ ሃይሎች ጋር የሚደረገው ውጊያ ቀጥሏል
- በሁለት ሳምንታት ውስጥ በማይ አባይ ከ600 በላይ ሰዎች፣ በአዲያቦ 1,300፣ እና በአስገደ ጽምብላ 1,000 ተገድለዋል፡፡ በዓዲ ዳዕሮና አካባቢው 2,500 ቤቶች በኤሪትርያ ሃይሎች ተቃጥለዋል

**22 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች መቐለ፤ ዓድዋ፣ አኹሱምና ሽረ.እንዳይደርሱ ከልክሏል
- የኤሪትርያ ሰራዊት ከአስገደ ጽምብላ 1,080 እንስሳትን ዘረፈ

**23 ህዳር 2015**

- የትግራይ ፕሬዝዳንት ለሃይማኖትና ለሲቪል ማህበረሰብ መሪዎች ገለጻ አድርገዋል
- የትግራይ ሃይል ከማይቅነጣል፣ ዛላምበሳ፣ ነበለት፣ ጨርጨር፣ ኩኩፍቶ፣ ሑጉምቢርዳ፣ በሪተኽላይና አበርገሌ ግንባር የመከላከል መስመሮችን ለቋል
- የኤርትራ ወታደሮች በትግራይ ሰላማዊ ዜጎችን መግደላቸውንና ከፍተኛ ዘረፋቸውን ቀጥለዋል

**26 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት በማእከላዊ ትግራይ እገላ ወደ 60 የሚጠጉ ንፁሀን ገደለ

**27 ህዳር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት 80-90 የጭነት መኪናዎች ከኤርትራ ሽራሮ ወደ አኹሱምና ዓድዋ ተንቀሳቅሰዋል
- የኤሪትርያ ሰራዊትና ፋኖ በማዕከላዊ ትግራይ ዞን መግደል፣ አፈና፣ መዝረፍና ማቃጠል ቀጥለዋል

**28 ህዳር 2015**

- የኃይልና የስልክ አገልግሎት ወደ መቐለ ቢመለስም አጥጋቢ አይደለም.
- በምእራብ ትግራይ ለመመልመል የሚሞከሩ የአማራ ሃይሎች አሉ

**29 ህዳር 2015**

- በትግራይ የሚገኙ ሰዎች ከስምምነት በኋላም በህክምና አቅርቦት እጥረት ሳቢያ እየሞቱ ነው
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ የአደጋ ስጋት አስተዳደር ኮሚሽን የኢትዮጵያ መንግስትና አጋር ድርጅቶች በትግራይ ከሚያስፈልገው ምግብ 95% አቅርበዋል ብሏል። የትግራይ የአደጋ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል ግን 76 በመቶ መድረሱን ዘግቧል

**30 ህዳር 2015**

- በነበለት የኤሪትርያ ሰራዊት በግድያ ዘመቻ ላይ
- የኢትዮጵያ ወታደሮች ምላሽ ኃላፊነት የጎደለው ነው:- “የኤሪትርያ ሰራዊት ከአቅማችን በላይ ነው፤ ማምለጥ እንድትችሉ የኤሪትርያ ሰራዊት ሲምጣ እናስጠነቅቃችሁአለን"

**06 ታሕሳስ 2015**

- በመሬት ላይ ያለው እውነታ ከበባው መቀጠሉ ነው

**07 ታሕሳስ 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊትና የአማራ ወታደሮች በማይ ቅነጣል፣ ሓሓይሌ፣ እምባስነይቲ፣ አሕፈሮም፣ ኢንቲጮ፣ እገላ፣ ዓድዋ፣ አሕሳአ፣ ራማና ዓዲ አርባዕተ ከ550 በላይ ንፁህን ዜጎችን ገድለው ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ሴቶችን ደፈሩ

**10 ታሕሳስ 2015**

- ከአማራ፣ ደቡብ፣ ቤኒሻንጉልና ጋምቤላ የተውጣጡ የክልል ታጣቂ ሃይሎች

የትግራይ ሃይሎች ለቀው በወጡባቸው አካባቢዎች ሁሉ ተተክተው ይገባሉ

- በሑመራ፣ አዲ ጎሹ፣ ማይካድራና ዓዲረመጽ መካከል ያሉ ሁሉም ከተሞች ባለፉት ሁለት ሳምንታት ወድመዋል
- የአማራ ሃይሎች ህዝቡ እንዳይመለስ ቤቶችን እያወደሙ ነው
- ከምእራብ ትግራይ የተፈናቀሉ ሰዎች በጸለምቲ፣ አስገደ፣ አኹሱምና ዓድዋ ካምፖች እየታደኑ እየተገደሉ ነው
- ከጎንደር ወደ ትግራይ የሚጓጓዘው እርዳታ ከመድረሱ በፊት ይሸጣል
- በማይቅነጣልና በነበለት መካከል የኢትዮጵያ መከላከያ መንገዶችን የኤሪትርያ ሰራዊት ደግሞ ከመንገድ ውጪ ያሉትን ቦታዎች ይቆጣጠራሉ
- የባንክ አገልግሎቶችንና በይነመረብን ወደነበረበት የመመለስ ምልክቶች የሉም
- ከ100,000 በላይ አዲስ የተፈናቀሉ ሰዎች ከኤሪትርያ ድንበር አካባቢ ወደ አዲግራት ደረሱ
- በትግራይ እንደ ጦር መሳሪያ ረሃብ ቀጥሏል
- አሳማኝ የሴራ ንድፈ ሃሳቦች፡- 1. የፌደራል መንግስት በውስጥ በኩል ምእራብ ትግራይ በአማራ ስር እንዲቆይ ይፈልጋል ምክንያቱም ትግራይ ለዘላለም ትከበባለች፤ 2. የትግራይ ባለስልጣናትን ለማዳከም እኩል ያልሆነ የእርዳታ ስርጭት ህዝባቸውን መሰረታዊ ፍላጎት እየነፈጉ ነው.

**11 ታህሳስ 2015**

- የትግራይ ክልል የድንገተኛ አደጋ ማዕከል እንደገለጸው ከተቸገሩት ውስጥ ወደ 58% ያህሉ እስካሁን መድረስ ያልተቻለ ሲሆን ከሚያስፈልገው ምግብ ውስጥ 63 በመቶው በአካባቢው በአካል ይገኛል
- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግስት የአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን የስልጣን ጊዜ እንዲቋረጥ በመጠየቁ ቁጣን ቀስቅሷል

**13 ታህሳስ 2015**

- በሽረ እንደገና የተከፈቱ ባንኮች ምንም ገንዘብ ማውጣት አይፈቅዱም፤ ነገር ግን ገንዘብ ማስቀመጥና የባህር ማዶ የገንዘብ ዝውውሮች ብቻ ይፈቅዳሉ
- የኤሪትርያ ሰራዊት በትግራይ የእርዳታ አቅርቦትን ማገዱን የቀጠለ ሲሆን አሁንም ግፍ እየፈፀመ ነው.

**14 ታህሳስ 2015**

- የኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ የሰላም ስምምነቱን አጥብቀው ውድቅ በማድረግ ከአማራ ሚሊሻዎች ጋር በመተባበር አዲስ ጦርነት ለመጀመር ቃል ገብተዋል.
- ለትግራይ ተወላጆች ህልውና ወሳኝ የሆኑ አገልግሎቶችና ሰብአዊ እርዳታዎች እስካሁን እድሳት አልተደረገላቸውም በኢትዮጵያ ባለስልጣናት ፈቃድ መስጠትም ገና ነው
- በትግራይ የሚገኙ ከ250,000 በላይ የክልልና የፌደራል የመንግስት ሰራተኞች ደሞዝ ለመክፈል የፌደራል መንግስት እስካሁን በጀት አልመደበም.

**17 ታህሳስ 2015**

- የኢትዮጵያ ፓርላማ አፈ-ጉባዔ ከቡድናቸው ጋር በመሆን የጦርነት ማቆም ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ መቐለ ተጉዘዋል.

**18 ታህሳስ 2015**

- ኢሮብ፣ ጋንታ አፈሹም፣ ጉሎ መኸዳ፣ ዛላምበሳ፣ ዓዴት፣ ዓድዋ፣ አሕፈሮም፣ አሕሳአ፣ ጭላ፣ ዕዳጋ ዓርቢ፣ እገላ፣ እምባሰየንቲ፣ ኢንዳፈላሲ፣ ኢንቲጮ፣ ራማ፣ አስገደና ዛና ሊደረስባቸው እንደማይችል ተዘግቧል

**19 ታህሳስ 2015**

- የትግራይ ባለስልጣናት የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ መንግስት የሰላሙ ውል መከበሩን እንዲያረጋግጥ፤ አሁንም በትግራይ የሚገኙ የውጭ የፌደራል ያልሆኑ ሃይሎችን እንዲያስወግድ ጠይቀዋል.

**20 ታህሳስ 2015**

- በትግራይ የሚገኙ የባንክ ኔትወርኮችን፣ የመገናኛ ዘዴዎችና የኤሌክትሪክ መስመሮችን ከሚጠግኑት ቴክኒሻኖች መካከል አንዳንዶቹ የኤርትራ የስለላ ሰልጣኞች ናቸው ተብለው ተጠርጥረዋል.

**26 ታህሳስ 2015**

- ህወሓት ከባድ መሳሪያዎችን ለኢትዮጵያ መከላከያ አስረከበ
- የትግራይ ደህንነት መጠበቅ የኢትዮጵያ መከላከያና የህወሓት የጋራ ሃላፊነት ይሆናል

- ህወሓት ትግራይን ለመጠበቅ የተመረጡና የሰለጠኑ ሃይሎችን ያሰማራል.

**27 ታህሳስ 2015**

- በሽረ የሚገኙት የኤሪትርያ ጦር አባላትና ፋኖ ሚሊሺያዎች ከባንክ ብር ይዘው የሚመለሱ፤ ከአውሮፕላን የሚወርዱ ሰዎችን አፍነው ገንዘባቸውን ይዘርፋሉ
- የኢትዮጵያ መንግስት በትግራይ ወደ ተከፈቱ ባንኮች ከውጭ የሚላከውን ገንዘብ መበዝበዝ ይፈልጋል

**01 ጥር 2015**

- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከመቐለ ወደ መቐለ በሚጓዙ መንገደኞች ላይ እገዳ ጥሏል.

**02 ጥር 2015**

- በትግራይ ማእከላዊ ዞን የኤሪትርያ ሰራዊት አባላት የንግድ ስራዎችን አቋቁመው እየሰሩ ነው፡- ትራንስፖርትና ንግድ በማይቅነጣል
- የኤርትራ መታወቂያ በአንዳንድ የሰሜን ትግራይ አካባቢዎች ተሰራጭቷል
- የኤሪትርያ ሰራዊት በሺዎች የሚቆጠሩ የቤት እንስሳትን ከእንጉያ፣ ክእገላና ከዝባን ጒላ ዘርፏል

**05 ጥር 2015**

- የአማራ ልዩ ሃይል ከሽረ ለቆ ወጣ
- የኤርትራ ወታደሮች አሁንም በትግራይ በሽረና በአክሱም ይገኛሉ.
- **ዘገባው ወጣ፡-** የትግራይ ጦርነት 18,000 ሄክታር መሬትና 81% የፍራፍሬ ማቆያ፤ 70% የአትክልት እርሻዎች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ አድርጓል፤ ከ1.9 ሚሊዮን የእርሻ በሬዎች ውስጥ ከ40% በላይ የሚሆኑት ተዘርፈዋል ወይም ተጨፍጭፈዋል፣ ከ1,990 የእርሻ ትራክተሮች ውስጥ ከ90% በላይ የሚሆኑት ተዘርፈዋል፤ ከ198ቱ የገጠር የእንስሳት ህክምና ክሊኒኮች 176ቱ ተዘርፈዋል ወይም ወድመዋል

**08 ጥር 2015**

- የኤሪትራይ ሃይል በዓድዋ ዙሪያ 50 የትግራይ ተወላጆችን አፍኖ የወሰደ ሲሆን የት እንዳሉ አይታወቅም

- በትግራይ በተፈጠረው ግጭት የተጎዱ ኢንዱስትሪዎችን የመልሶ ግንባታ ፍላጎት የሚያጠና የባለሙያ ቡድን ወደ ትግራይ ሄደ

**10 ጥር 2015**

- ተቋርጦ የነበረው መስቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ማምረት ጀምሯል

**12 ጥር 2015**

- የኤሪትርያና የኢትዮጵያ መከላከያዎች አባላት አስከሬን ከአክሱም አየር ማረፊያ እየቆፈሩ ወደማይታወቁ ቦታዎች ያዛውራሉ
- ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ እንዲህ አለ፡-"ከምዕራብ ትግራይ የተፈናቀሉ ከ1 ሚሊዮን በላይ የትግራይ ተወላጆች ወደ አገራቸው ከተመለሱ ምዕራብ ትግራይን እናጣለን፤ ስለዚህ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ አንፈቅድም"

**15 ጥር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት አሁንም በሽረና በአድዋ አለ
- ከትግራይ ተዋጊዎች ከባድ የጦር መሳሪያ ለኢትዮጵያ ሰራዊት ሙሉውን ለማስረከብ የኤሪትርያ ሃይል ከትግራይ የሚወጣበትን ጊዜ ይጠብቃል
- ከፕሪቶሪያ ስምምነት ጀምሮ የአማራ ወታደሮች 211 ሴቶችን ደፈሩ፣ 2116 ሰዎችን ገድለዋል፣ 298 አቁስለዋል፣ 680 ሰዎችን በትግራይ ሰሜን ምዕራብ ዞን አግተዋል.

**16 ጥር 2015**

- ተፈናቃዮችን ወደ ቤት ለመመለስ ምንም ጠቃሚ እርምጃ አልተወሰደም.

**17 ጥር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት ለታህታይ አድያቦ ሰብአዊ እርዳታን አግዷል.
- የኤሪትርያ ሰራዊት አሁንም በአክሱም፣ ሽራኔና አድዋ ውስጠ ይገኛል.

**18 ጥር 2015**

- በትግራይ ጦርነት የሰው ሞት ግምት ተሰጠ፡- 518,000 (ዝቅተኛ ግምት 311,000 ከፍተኛ ግምት 808,000)-- 10% በጅምላ ጭፍጨፋ፣ በቦምብና በሌሎች የግድያ ዓይነቶች፤ 30% በጤና አጠባበቅ ስርዓቱ አጠቃላይ ውድቀት ምክንያት፤ እንዲሁም 60% በረሃብ ምክንያት፡፡ የጆሴፍ ቦሬል 800,000 ግምት ለእውነት የቀረበ ነበር ማለት ነው (ጃን ኒሰን)

**22 ጥር 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት አሁንም በትግራይ ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም ለቋል እየተባለ ሪፖርት ተደርጓል

- በአፍሪካ አህጉር ላይ አዲስ የውክልና የቀዝቃዛ ጦርነት ግጭት እየተጠመቀ ነው ተባለ፡-1. አብይ አህመድ የኤሪትርያንና የአማራን አቅም ለማደከም ከሱዳን ጋር አዲስ ጥምረት ሳይፈጥር አልቀረም 2. ኢሳያስ ከሩሲያ ጋር ጥምረት እየፈጠረ ነው.

- የኤሪትርያና የአማራ ሃይሎች አሁንም በመላው ምዕራባዊ ዞን፤ በሰሜን ምዕራብ ዞን ዓዲ አውዓላና ሽራሮ ወስጥ ይገኛሉ.

- የኤሪትርያ ሃይሎች በትግራይ ማእከላዊ ዞን በገርሁ ስርናይ፣ አዲ ጭጎኖ፣ ዕዳጋ ረቡዕና በትግራይ ምስራቃዊ ዞን በጉሎ መኸዳና ኢሮብ ውስጥ ይገኛሉ

- የመንገድ ትራንስፖርት በቅርቡ ወደ መቐለ፣ አክሱምና ሽረ ይጀምራል.

- ድንበር ተሻጋሪ ንግድም በትግራይ ተጀምሯል

**23 ጥር 2015**

- የአማራ ወታደሮች የሰሜን ምእራብ ትግራይ ዓዲ ጎሹን፣ ከተማ ንጉስን፤ እምባጋላን እነደያዙ ናቸው፤ እንዲሁም እምባ ማድረ፤ ማይ ጸምሪ፤ ጻዕዳ ቀርኒ፤ ዓዲ ወሰናይ፤ ማይ ዳጉሻ፤ ማይ ትኽሊት፤ ሰራቆ፤ ሰቆጣ ስላሴ፤ ማይ ሎሚን፤ ሚቻራ፤ ባበኮ፤ ባር ገዛ፤ፊየል ዉሃ፤ የአማራ ወታደሮች አላማጣና ኮረምን እንደያዙ ናቸው

**25 ጥር 2015**

- ከአዲስ አበባ ወደ ትግራይ የተጓጓዙ ከእህል ጋር የተያያዙ ሸቀጦችን የጫኑ ከ300 በላይ መኪኖች በአማራ ባለስልጣናትና በሰሜን ወሎ ፋኖ ተገተው ቆመዋል። በአንድ የጭነት መኪና 20,000 ብር እንዲከፍሉም እየተገደዱ ነው ተብሏል፤300ዎቹ የጭነት መኪናዎች ከአራት ቀናት የመንገድ መዘጋት በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለሱ ታዘዋል

- ትግራይ አሁንም ከኢንተርኔትና ከዲጂታል አገልግሎቶች ዝግ ነች፤ ኔትዎርክ ማግኘት የቻሉ ሰዎች ከዝቅተኛ ፍጥነት ጋር እየታገሉ ነው

**26 ጥር 2015**

- ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ላይ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች

ኮሚሽን በጀት እንዳይመደብለት ለማድረግ ያቀረበችው ሃሳብ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ ተደርጓል

**30 ጥር 2015**

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በትግራይ በሚገኙ ቅርንጫፎቹ ሙሉ የባንክ አገልግሎትን ወደነበረበት ተመልሷል

**03 የካቲት 2015**

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን (ኢኦቲሲ) ለአምስት የትግራይ ሊቀ ጳጳሳት ደብዳቤ ልኳል። ነገር ግን የትግራይ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አቋሜ አልተለወጠም ብላለች

**10 የካቲት 2015**

- የኤሪትርያ ሰራዊት የፍተሻ ኬላዎችን በመቆጣጠር መንገዶችን በመዝጋት ላይ ናቸው.
- የኤሪትርያ ሰራዊት ነዋሪዎችን በማፈናቀል፣ ምሽጎችን በመቆፈርና ፈንጂዎችን በመቅበር ላይ ነው
- የኤሪትርያ ሰራዊት አሁንም በጉሎመኸዳ (ምስራቃዊ ዞን) ውስጥ ይገኛል
- የኤሪትርያ ሰራዊት በሰብአዊ ሰራተኞች ላይ ተኮሰ.
- የትግራይ ነፃነት ፓርቲ ሳልሳይ ወያኔ ትግራይና የታላቋ ትግራይ ብሄራዊ ኮንግረስ በቅርቡ ይፋ በሆነው የሽግግር መንግስት ማቋቋሚያ ኮሚቴ ውስጥ ውክልና እንዲደረግ ጠይቀዋል.

**13 የካቲት2015**

- አለማቀፍ የትግራይ ምሁራን ማህበር የትግራይ የሽግግር አስተዳደር በማቋቋም ሂደት ውስጥ ሰፋ ያለ አካታችነት እንዲኖር ጠይቋል

**22 የካቲት 2015**

- በትግራይ የሚገኙ ሶስት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለ32 ሀገራት ተወካዮች ደብዳቤ ልከው ለትግራይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ አቅርበዋል

**23 የካቲት 2015**

- የሽግግር መንግስት ምስረታ በውስጥ ልዩነትና በፌዴራል መንግስት አዝጋሚ ምላሽ ምክንያት ተጓቷል

**04 መጋቢት2015**

- ኤርትራ የአማራ ወታደሮችን በማሰልጠን አዲስ አበባ ውስጥ በድብቅ አሰማርታለች ተብሏል

**05 መጋቢት 2015**

- የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ደብረፂዮን ገብረሚካኤል የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት ሆነው እንዲቀጥሉ አይፈልጉም፤ ጦርነቱን በመጀመራቸው ተጠያቂ ስላደረጉ

- በመቐለ ጎዳናዎች ላይ የተገኙ አብዛኞቹ ሰዎች ደብረፂዮንን እንደሚደግፉ ገልጸዋል

- 5 ቢሊየን ብር ወደ ትግራይ ባንኮች ከተላከ በኋላ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ነጋዴዎችና ባለጸጎች ገንዘባቸውን በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ሙጥጥ አድርገው አውጥተዋል

**06 መጋቢት 2015**

- የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል.

**11 መጋቢት2015**

- አቢይ አህመድ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አቶ ጌታቸው ረዳ የሽግግር የክልል አስተዳደር ፕሬዝዳንት እንዲሆኑ ሾሙ

**13 መጋቢት 2015**

- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሸባሪ ድርጅትን ስያሜ ከትግራይ ህዝቦች ነፃ አውጪ ግንባር አስወገደ

**14 መጋቢት2015**

- የኢትዮጵያ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ትግራይ ውስጥ አካታች የሆነ የሽግግር መንግስት ለማቋቋም የወጣውን ደንብ ያጸደቀ ሲሆን አብይ አህመድ ጌታቸው ረዳ የክልሉ የሽግግር መንግስት ፕሬዝዳንት ሆነው ተሹመዋል፡፡

# ምዕራፍ ፲

# የድህረ-ፕሪቶሪያ የሃይል አሰላለፍ ለውጥ

## 10.1 የፕሪቶሪያ ስምምነት ተቃውሞ

የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ተስፋ አሰንቋል ቁጣንም ጋብዟል፡፡ ተስፋው የጦርነቱ መአት ለወረደባቸው ሲሆን ቁጣው ደግሞ ሽብሩን ለመቀጠል ቆርጠው ለተነሱ የፖለቲካ ሃይሎች ነበር፡፡ ለትግራይ ህዝብ የፕሪቶሪያ ስምምነት የመጣው በመለኮታዊ ጣልቃገብነት፤ በትግራይ መሪዎች ጥበብና በዩ.ኤስ.ኤ. ወቅታዊ እርምጃ ነው፤ የመጨረሻው የትግራይ ወረራ የምጽአት ቀን የሚመስል ሁኔታን እየፈጠረ የመጣበት ጨለማ ሰአት ነበር የፕሪቶሪያው ዋዜማ፡፡ ጦርነቱን እንደ ቦክስ ግጥሚያ ቆጥረው በድብድቡ ሲደሰቱ በመቋረጡ የተከፉ የአእምሮ ህመምተኛ ፖለቲከኞችም ነበሩ፤ ከሁለቱም ወገን ለሚረግፈው የሰው ህይወት ደንታ ያልነበራቸው! የጦርነቱ መቆም ያበሳጫቸው እነዚህ ብቻ አልነበሩም፡፡ ጦርነቱን እንደ ጢስ ቦምብ በመከለያነት በመጠቀም በመሬት ዝርፊያ፤ በሙስና፤ በጥቁር ገበያ ንግድ፤ ሸቀጦችን በማስወደድ፤ በኮንትሮባንድ፤ ስደተኞችን በመዝረፍ፤ መሳሪያ በመሸጥ፤ የህዝብን ሃብት በመዝረፍ፤ በዝምድና፤ በአገር ልጅነትና በጉቦ ቅጥር በመፈጸም ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሁሉ በስምምነቱ ቀን ምድሩ የጨለመ ሆኖ ተሰማቸው፡፡ ጨልሞ ከነበረም የክርስቶስ ስቅለት ቀን እንደሆነው ህዝብን ከዘላለም ሞት ለማዳን ነው፡፡

በጦርነቱ ዝግጅትና በጦርነቱ ወቅት ለሹመትና ለሃላፊነት የበቁት የሞራል እሴቶችን ሽረው ለሆዳቸው በማደር በህዝብ ላይ የሚካሄድን ጦርነት የደገፉና ያራመዱት እንጂ ለቦታው በሚመጥነው የሙያ ዘርፍ የላቁ ስለሆኑ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ “ሜሪቶክራሲን” ገድሎ አርቆ የቀበረው ኢህአዴግ ቢሆንም የባሰ እስከ አጥንቱ የፈረሰው ግን ጦርነቱን ተጠግቶ ነው፡፡ ለሰላምና ለልማት የማይመጥኑ ሹመኞች ሆኑ ተቀጣሪዎች ከጦርነት በኋላ ለሾማቸው ሆነ ለቀጠራቸው ሸክም እንደሚሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ተቃዋሚዎቻቸውን ለመጠራረግ ጦርነትን ብቸኛ ዘዴ ያደረጉ የመንግስታት መሪዎች በእልቂት ብዛት ጉዳያቸው ሞልቶላቸው ሰላም ሲመጣ የገነቡትን ”የጦርነት ቢሮክራሲ” በአይናቸው ማየት ይጸየፋሉ፤ አንድ በአንድ እየለቀሙም ያስወግዳሉ፡፡ እኩያ ልሁን የሚልና ገበናን የሚያውቅ

በስልጣን ላይ እድሜ አይኖረውም፡፡ ለዚህም ነው በካቢኔው፤ በጦሩ፤ በሚድያው፤ በሙሁራን አምባው፤ በፓርላማው፤ በተቃዋሚው ጎራ አገርን የተጣቡ የጦርነት ጥገኛ "ነፍሳት" አንድ በአንድ መርገፍ የጀመሩት፤ ፕረቶሪያ ሳኒቶሪያ ሆናባቸው!

የኤርትራ ሃይሎችና የአማራ ሚሊሻዎች የፖለቲካ ህልውናቸው በጦርነቱ ቀጣይነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በቃላቸው ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡ በርግጥ የአማራ ሃይሎች ስለ ፕሪቶሪያ ስምምነት ምን ማለት እንዳለባቸው ለማወቅ የኤሪትርያን መግለጫ መጠበቅ ነበረባቸው፤ እንደ ስምንተኛው ሺ ልጅ ከአባታቸው ቀድመው እንዳይናገሩ፡፡ ጥቅምት 29/ 2015 ኤርትራ "የአማራ ክልል መንግስት የአማራን ጥቅም የሚጻረር የሰላም ስምምነቱን ውድቅ እንዲያደርግ" ስትል ጠየቀች፤ የሚጠበቀው ትእዛዝ አክብሮትን ተላብሶ በጥያቄ መልክ መጣ፡፡ በቀጣዩ ቀን ጥቅምት 30/ 2015 የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ "የሰላም ስምምነቱ የአማራ የወልቃይትና የራያ ይገባኛል ጥያቄ እውቅና አልሰጠም" ብሎ ተቃውሞውን አሳወቀ፡፡ በዛው ቀን የፋኖ ሚሊሻዎች "የሰላም ስምምነቱ የአማራን ጥቅም የሚጻረር ነው፤ ምክንያቱም በህገ መንግስቱ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ" ሲሉ አወገዙ፡፡

ህገ መንግስቱ የአማራ ሃይሎች ከምእራብና ከደቡብ ትግራይ ለቀው እንዲወጡ ይጠብቅባቸዋል፡፡ ህዳር 06/ 2015 ኤርትራ የፕሪቶርያን ስምምነት ለማሰናከል በጀመረቺው ዘመቻ ከዴምሂት (ጸረ-ህወሓት የትግራይ ታጣቂ ቡድን) በኤርትራና ከፋኖ ሚሊሻ በአማራ ክልል ጋር በመተባበር ላይ ትገኛለች የሚል ዜና ተሰማ፡፡ ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ ታህሳስ14/ 2015 የኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ የሰላም ስምምነቱን አጥብቀው ውድቅ በማድረግ ከአማራ ሚሊሻዎች ጋር በመተባበር አዲስ ጦርነት ለመጀመር ቃል እንደገቡ ተዘገበ፡፡ ጥር 12/ 2015 የወልቃይቱ "ዎርሎርድ" ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ የፕሪቶሪያን ስምምነት በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባር ለማሰናከል ቁርጠኝነቱን ገለጸ፤ እንዲህም አለ፦ "የተፈናቀሉ ከሚሊዮን በላይ የትግራይ ተወላጆች ወደ ቦታቸው ከተመለሱ ምእራብ ትግራይን እናጣለን፤ ስለዚህ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ አንፈቅድም"፡፡ ከፕሪቶሪያ ውል በኋላ በነበሩት አራት ወራት የኤሪትርያ ወታደሮች የትግራይን ሰፊ አካባቢ ተቆጣጥረው 40 ያህል የግድያ፤ የዝርፊያ፤ የሴቶችን መድፈረና የጠለፋ ወንጀሎች ተዘግቦባቸዋል፡፡

በፌደራል መንግስት መዋቅር ውስጥ የተሰገሰጉት የፕሪቶሪያ ተቃዋሚዎች አፋቸው ሳይናገር ተቃውሟቸውን ሲገልጹ የነበሩት የፕሪቶሪያው ስምምነት አተገባበርን በማጓተት ነበር፤ የማይጮህ ግን ህዝብን ከሞርታር በላይ የሚፈጅና ሞራልን የሚያወድም ደርጊት! ይህ ድምጽ አልባ የተቃውሞ እርምጃ የትግራይ ህዝብ ተስፋ ቆርጦ ስምምነቱን በገዛ እጁ እንዲያፈርሰው የሚገፋፉ ነው፡፡ በዚህ ፈታኝ የሆነ የተቃውሞ ስልት የትግራይ ህዝብ ከሰላማዊ ሰልፍ ያለፈ ምን ውጤት የሚያስገኝ እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል በቅጡ የተረዳ የለም፤ ጦርነት መቀጠሉ ግን አማራጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ታዲያ የትእግስቱ ገደብ እስከምን ድረስ ይሆን?

## 10.2 ፕሪቶሪያ ያስከተለው የጎራ ምስቅልቅል

ሊይ ሰይሞር እንደሚያስገነዝበን ወገን መቀያየር የማንኛውም የእርስ በርስ ጦርነት ባህርይ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ለውጦች የሚያከትሉት ውጤትም ሰፋና ጠለቅ ያለ ነው፡- ጦርነቱ የሚወስደውን ጊዜና መች እንደሚቆም፤ የወታደራዊ ዘመቻዎች ስኬት፤ የሲቪሎች ጉዳት መጠን፤ የወደፊት መልሶ ግንባታ ተስፋ፡፡ በፕሪቶሪያ ስምምነት በኢትዮጵያ-አማራ-ኤርትራ በኩል የሃይል አሰላለፍ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ ለውጡ የተባባሰው በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ህወሓት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአሸባሪዎች ዝርዝር መሰረዟን ተከትሎ ነው፡፡ በትግራይ ጦርነት የገዢ ፓርቲው ቁልፍ አጋር ሆነው የቆዩት ኢዜማና ናማ መጋቢት 16/2015 የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ውሳኔ በመቃወም የጋራ መግለጫ አወጡ፡-

"ህወሓት አሁንም ለአገሪቱ ስጋት ናት፡፡ የመንግስት ውሳኔ በጣም ፈጥኗል፤ ህወሓት አሁንም ትጥቋን ጨርሶ አልፈታችም፡፡ የኢትዮጵያ ሰራዊት ትግራይን ሙሉ በሙሉ አልተቆጣጠረም፤ ጦርነቱን የጀመሩት የህወሓት አመራሮች በድርጊታቸው አልተጠየቁም፤ የትግራይ የሽግግር መንግስትንም በብቸኝነት የምትመራው ህወሓት ናት፤ ህወሓት በህግ መወገድ አለባት፤ ውሳኔው ህወሓት ተመልሳ ብሄራዊ ስጋት እንድትሆን እድል ይሰጣል"

የአማራው 'ተቃዋሚ" ፓርቲ ናማ የተቃውሞ መግለጫ በማውጣት ብቻ አልተወሰነም፡፡ በፓርላማ ተወካዩ በከርስትያን ታደለ አማካይነት በፓርላማው የጥያቄ መልስ ፕሮግራም ላይ የፕሪቶርያ ስምምነትን በመፈረም የከዱት ሆኖ ከተሰማው ከጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አህመድ ጋር ሲፋጠጥ ውሏል፡፡ የፕሪቶሪያ

ስምምነት አፈጻጸም አንዱ ገጽታ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ መከላከያ ሰራዊት በስተቀር ሌላ የታጠቀ ሃይል እንዳይኖር የሚለውን የስምምነት አንቀጽ ለማስፈጸም መንግስት ፋኖን ጨምሮ የክልል ልዩ ሃይሎችን ትጥቅ ለማስፈታት ሲንቀሳቀስ በአማራ ክልል ውጥረት መፈጠሩን ተከትሎ ነበር ክርስቲያን ታደለ የሚከተለውን ፓርላማ ውስጥ የተናገሩት፡-

*“በአሁኑ ጊዜ ያሉት ተጨባጭ እውነታዎች ለዜጎች ደህንነትና ለአገሪቱ ሉዓላዊነት ቁልፍ ስጋት እርስዎ እየመሩት ያለው መንግስት ነው፡፡ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ኢትዮጵያ መቼም እንደማትጠፋ ቃል ገብተዋል፣ በተግባር ግን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በመንግስትዎ እየፈረሱ ነው፡፡ ስራ ለመልቀቅና የመፍትሄው አካል ለመሆን አላሰቡም? በሰብአዊነት ላይ ለተፈፀሙት ወንጀሎች፣ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ተጠያቂ ለመደረግ ዝግጁ ነዎት?”*

በፕሪቶርያው ስምምነት መሰረት ህወሓትን ከሽብር መዝገብ ማስወጣትና መደበኛ ያልሆነው የፋኖ ሃይልን ትጥቅ ማስፈታት ለአማራ የፖለቲካ ልሂቃን በሁለት በኩል ስለት ያለው ሰይፍ እንደተመዘዘባቸው ቆጥረውታል፡፡ የሰይፉ ጫፍ ሶስተኛው ስለት ደግሞ ፕሪቶሪያ የአቢይ አህመድን ብሎም የኦሮሞን ስልጣን የሚያጠናክር ሆኖ የአማራ ልሂቃንን ጣፋጭ ህልም ወደ ቅዠት በመቀየሩ ነው፡፡ የፕሪቶሪያው ስምምነት የመፍትሄ ውሳኔዎች ሁሉ በህገ መንግስቱ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ስለሚደነግግ የአማራ የፖለቲካ ልሂቃን ህገ መንግስቱ የማይቀየር መሆኑ ሲሰማቸው የተፈጠረባቸው ተስፋ የማጣት ስሜት ቀላል አይደለም፡፡ ለዚህም በግንባር ቀደምትነት የሚወነጅሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩን ነው፡፡ አቢይ አህመድ ስልጣናቸው የቆመምበትን ምሶሶ ለማን ብለው እንደሚንዱ መልስ የሚሻ ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኢንሳይት አቤል ተስፋየ መጋቢት 29/2015፡-

*“ብዙ አማሮች በመጀመሪያው ላይ የአቢይን መንግስት ደግፈው ነበር፡፡ ይህም አቢይ ህገ መንግስቱን የማሻሻል ወይም ጨርሶ የመቀየር ሃሳብ አለው በሚል ነበር”*

ከፕሪቶሪያ ስምምነት አምስት ወራት በኋላ ሚያዝያ 7/ 2015 የኢትዮጵያ መከላከያ ኤታ ማጆር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የክልሎች ልዩ ሃይሎች በሚመለከት የመጨረሻ ውሳኔ የሚመስል መግለጫ ሰጡ፡-

| |
|---|
| *“ከዚች ቀን ጅምሮ በክልል ልዩ ሃይል ስም የሚታወቅ መዋቅር አይኖርም፤ ህገ ወጥ ነው”* |

የአማራ ልሂቃን በአቢይ አህመድ ላይና ሽሪኮቹ ናቸው በመባል በሚወገዙት የአማራ ክልል ብልጽግና አመራሮች ላይ ብርቱ የሚድያ ዘመቻቸውን ቀጥለዋል፡፡ የአቢይ መንግስትና የአማራ ልሂቃን ትስስር የገነባው ግዙፍ ህንጻ መናዱ ማረጋገጫ የሆነው በዲያስፖራ የህንጻው አርኪቴክቶች ቁንጮ የነበረው ታማኝ በየነ በሚድያ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ አቢይ አህመድ ላይ ውግዘቱን በአደባባይ ሲያሰማ መታየቱ ነበር፡፡ ከአምስት አመታት በፊት የአማራው ዳያስፖራ "ጎድ ፋዘር" ታማኝ በየነ ብርቱ ስሜት ውስጥ ተነክሮ፤ አቢይ አህመድ ፖለቲከኛ መሆኑን ዘንግቶ ነሃሴ 25/2010 ላይ የተናገረውን እናስታውስ፡-

"ክቡርነትዎ! ዶር. አቢይ አህመድ! በብዙ የአለም ሃገራት መሪዎች የምርጫ ሳጥን ይዘርፋሉ፡፡ ያለ ምርጫ ሳጥን የህዝብን ልብ የሚሰርቅ እንደ ዶር. አቢይ የመሰለ ሰው አላየሁም፡፡ ሊገድሏቸው ሞከሩ፡፡ ቢሞቱም እንኳ በኢትዮጵያ ትልቁን ሃውልት አቁመን ስማቸው ለዘላለም እንዲዘከር እናደርጋለን" ጨረቃ ድረስ የተሰማ ጭብጨባ!



አቢይ አህመድ ነጋሽ እንጂ አንጋሽ አለመሆኑ በጣም ዘግይተው ሲገባቸው መፋረስ መጣና ሚያዝያ 4/2015 ታማኝ በየነ ሰማይ ሰቅሎት የቆየውን የአቢይ አህመድን ስም መሬት ላይ አውርዶ ጣለው፤ እንዲህ በማለት፡-

"አቢይ አህመድ የሚታመን አይደለም፤ በአማራ ያለው ትግል መቀጠል አለበት"

መሳይ መኮንን የጸረ-ትግራዩ ትብብር የፕሮፓጋንዳ "ጉሩ" የነበረ ነው፤ "አሳውን ለመያዝ ባህሩን ማንጠፍ፤ 95 ሚልዮን በ5 ሚልዮን ላይ እንዲነሳ" በመቀስቀስ የሚታወቀው የናዚው ቁራጭ! ኦሮማራን እንደ የኢትዮጵያ መድህን ሲያወድስ ከርሞ አሁን ደርሶ የአማራና የኦሮሞ ብልጽግና ግንባር የኦሮሞ ሎሌነት ሆነበት፡-

"አሁን መደረግ ያለበት የአማራ ክልል ባለስልጣናትን ባደባባይ ማውገዝና ከህዝቡ ጎን እንዲሆኑ በነሱ ላይ ጫና መፍጠር ነው፡፡ አይናቸውን አፍጥጠው አንገታቸው ዙሪያ ክራባታ አስረው በቴሌቪዥን መስኮት ሲቀርቡ ለህዝቡ ጥሩ ነገር የያዙ ይመስላሉ፡፡ ከዚህ የባሰ የሚደብር ነገር የለም፤ ለባርነትም ገደብ አለው"



በአቢይ አህመድ ካምፕ የተዋናዮች ጥምረት ውስጥ ምድር አንቀጥቀጥ የሆነ ለውጥ ተፈጥሯል፡፡ የትግራይን ጦርነት ፍኖት ካርታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጠሁ እኔ ነኝ የሚሉት የእንግሊዝ አገር ዜጋው አንዳርጋቸው ጽጌ ኢትዮጵያና ኢርትራ በትግራይ ላይ የፈጠሩትን ግንባር ያመቻቹ ቁልፍ አገናኝ ነበሩ፡፡ የካቲት 23/2015 አንዳርጋቸው ጽጌ በአባይ ሚዲያ ላይ ተመልካችን ያስደነገጠ ቃለ መጠይቅ አደረጉ፡፡ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የተካሄደውን 127ኛው የአድዋ የድል ቀን አከባበር እንዳይቀላቀሉ በመደረጉ ቅሬታቸውን አሰሙ፡፡ ፕሪቶሪያ የአንዳርጋቸው የፖለቲካ ጸሃይ እንድትጠልቅ አድርጓል፡፡ ለዚህ ውርደት የዳረጋቸው በፕሪቶሪያ ስምምነት ላይ የወሰዱት ለአቢይ የማይመች አቋም ነበር፡-

2

*“ህወሓትና ብልጽግና የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ጥምረት ፈጥረው የሰላም ስምምነቱን የተቃወሙ አማራንና ኤሪትርያን ለመውጋት እየተዘጋጁ ነው”*

የአማራ ፋኖና ልዩ ሃይል በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ትጥቅ አንፈታም በማለታቸው በመላ አማራ ክልል ውስጥ ከባድ ህዝባዊ አመጽ ተቀጣጠለ፡፡ ቀጥሎም ብዙ ወራትን ፈጅቶ እስካሁን እየቀጠለ የሚገኘው የመከላከያ ሰራዊትና የፋኖ ሚሊሺያ ውጊያ በከተሞችም በገጠሩም በአስከፊ ሁኔታ ተስፋፍቷል፡፡ በማንኛውም ሰአት በየትኛውም ስፍራ የደፈጣ ጥቃት ስለሚፈጸም የዚህ እልቂትና ውድመት ማብቂያው መቼ እንደሆነ ለመተምበይ ያድግታል፡፡

የአማራ ልሂቃን በአቢይ አህመድና በኦህዴድ-መር መንግስት ላይ ያነሳሱት ፈታኝ የሆነ ግዙፍ ሃይል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ነው፡፡ በታሪክ ቤተ ክርስቲያኗ የአማራ ልሂቃን የፖለቲካ የበላይነት ማስፈጸሚያ ናት በሚል ትተቻለች፡፡ ወደ ህወሓት ያደላሉ እያሉ በሚነቅፏቸው የትግራይ ትውልድ ያላቸው ፓትሪያሪክ የምትመራው ቤተ ክርስትያን የአማራ ትውልድ ባላቸውና የውጭ አገር ዜጎች ናቸው በሚባሉት ረዳቶቻቸው እጅ ገብታለች፡፡ በትግራዩ ጦርነት የሰላም እጇን ከመዘርጋትና በክልሉ ያሉትን ምእመናን ለመታደግ ሃይማኖታዊ ግዴታዋን ከመወጣት ይልቅ ፓትሪያሪኩን በማግለል የሲኖዶሱ ሊቃነ ጳጳሳት ጦርነቱን በሞራል፤ በገንዘብና ህዝብን በማነሳሳት ሲያበረታቱ ቆይተዋል፡፡

በአማራ መደበኛ ያልሆኑትን ሃይሎች ትጥቅ ለማስፈታት ሲታሰብ በክልሉ ውስጥ ከቁጥጥር ያመለጠ ሰፊ ሽፋን ያለው ጦርነት በመለኮሱና የአማራ ህዝብ እያለቀ በመሆኑ ቤተክርስቲያኒቱ በትግራይ ጦርነት የተለጎመው አፏ ተፈታ፡፡ “ምእመናን እኩል ናቸው፤ ነገር ግን ከፊሎች ምእመናን ከቀሩት የበለጠ እኩል ናቸው” ከሚለው አባባል ጋር የሚቀራረብ አስተሳሰብ ይዛ በአቢይ አህመድ ላይ ተነሳች፡፡ ፖለቲካውን ከሃይማኖት ጋር እያስታከኩ በሊቃነ ጳጳሳቱ ሲነገር የነበረው የዘር ስሜትን የሚነካና አመጽን የሚቀሰቅስ ንግግር የኦሮሞንና የትግራይን ምእመናን የባሰውኑ ሆድ አስባሰና መለያየትን አስመረጣቸው እንጂ ለሰላም የሚበጃቸው ነገር አልሆነም፡፡ ከሃይማኖት መስመር አልፈው “እንደ ዳዊት ጎልያድን ግንባሩን በሉት” የሚሉ አዲስ አይነት ሊቃነ ጳጳሳትም ተፈጥረዋል፡፡

በዚህ ዘረኝነት በነገሰበት የቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደር የተከፉ የኦሮሞ ሊቃነ ጳጳሳት ከሲኖዶሱ እውቅና ውጪ ጳጳሳትን ሲሾሙ ነገሮች ድብልቅልቃቸው

ውጣ፡፡ እርምጃው ሲኖዶሱን ያስቆጣ ሲሆን የተላከከው ደግሞ በአቢይ አህመድና በኦሮሚያ ክልል አመራር ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን አከራሪ የሆኑትን አባሎቿን አስተባብራ የአቢይ አህመድን መንግስት በአንድ እግሩ አቆመቺው፡፡ የካቲት 2/2015 አል አፍሪካ ዶት ኮም በትግራይ ጦርነት የፌዴራል መንግስት አጋር ከነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የተፈጠረው ግጭት ከባድነት እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

"በመንግስትና በቅዱስ ሲኖዶስ መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ መምጣቱን በሚያረጋግጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን መከፋፈል እንደ እድል በመጠቀም መንግስትን በመሳሪያ ሃይል ሊነቀንቅ የሚፈልግ ቡድን እንዳለ መረጃ ደርሶኛል እያለ ነው መንግስት፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ ግን ይህንን ውንጀላ አልቀበልም በማለት ከልከላውን ሽሮ አገር አቀፍ ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚያካሂድ ዝቷል"

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ሲኖዶስና በአቢይ አህመድ መካከል የነበረው ጠንካራ ጸረ-ትግራይ ህብረት እየፈረሰ ከመጥፎ ወደ ከፋ ሁኔታ የተሸጋገረ መሆኑ ማረጋገጫ የሆነው በሚገርም ሁኔታ የአሜሪካ ዜግነት እያላቸው የሲኖዶሱ ዋና ጸሃፊ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩት ጦረኛው ሊቀ-ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ በወጡበት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመለሱ መከልከላቸውና ብጫ ካርዳቸውንም መቀማታቸው ነው፡፡ በጦርነቱ የጫጉላ አመታት አቡነ ጵጥሮስ በሚዘገንን የአድርባይነት ስሜት ተነሳስተው አቢይ አህመድም ቢሆን ሊታዘቧቸው በሚችሉበት ሁኔታ እንዲህ አይነት ቃላት ተናግረው ነበር፡- "እንደ ዶር. አቢይ አህመድ ቅን ልብ ያለው ሰው አላየሁም"፡፡

የወልቃይት ጉዳይ የትግራይ ጦርነት የመጨረሻው ምሽግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከህገ መንግስቱና ከፕሪቶሪያ ስምምነት ውጪ ምእራብ ትግራይ ወደ አማራ አስተዳደር ተካሎ ወልቃይት-ሁመራ-ጸገዴ ዞን በሚል ተሰይሞ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ የጸጥታ ሃላፊ ሆኖ ተመድቧል፡፡ የአማራው ፋኖ ከፌደራል መንግስት ጋር የሞት ሽረት ውጊያ በገጠመበት ሁኔታ ላይ እያለ ፌደራል መንግስት የምእራብ ትግራይን ጉዳይ በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት መፍታት አልቻለም፡፡ ያልቻለው በጉዳዩ ላይ ሌላ ስውር አጀንዳ በመያዙ እንጂ ከአቅሙ በላይ ስለሆነ አይደለም፡፡ ከዚህም የተነሳ ፌደራል መንግስቱ ከህወሓት ጋር ፈጥሮት የነበረው መለሳለስ ሊሻከር የሚችለበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ከፕሪቶሪያው ስምምነትና ከህገ መንግስታዊው አሰራር ውጪ "የምእራብ ትግራይ ጉዳይ በሪፈረንደም ለመፍታት ከትግራይ ጋር ተስማምተናል፤ ዋናዎቹ

ተፈናቃዮችም ተመልሰዋል" የሚል መግለጫ በማውጣቱ ነገሮች ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዲሄዱ የሚያደርግ ሆኗል፡፡ ከፕሪቶሪያ ስምምነት ወዲህ በፌደራል መንግስት ላይ ከረር ያለ ቃል ከመሰንዘር ተቆጥቦ የቆየው የትግራይ የሽግግር አስተዳደር አባላቱ በየፌደራል መንግስቱ የግብዣ ጥሪ ሁሉ እየተገኙ ለመመሳሰልና ጉዳያቸውን በጸባይ ለማስፈጸም ሲጥሩ ቢቆዩም እንደ ፍርሃት እንጂ እንደ በጎ ፈቃድ የተወሰደላቸው አይመስልም፡፡

በዚሁ ላይ የህወሓት የውስጥ ውዝግብ ታክሎበት ፌደራል መንግስት "ቅንድባቸውን ነቀልናቸው" ካላቸው የትግራይ ፖለቲከኞች ላይ ያሻውን ማድረግ እንደሚችል ተሰምቶታል፡፡ ከዚህም የተነሳ ይህ ኤሪትርያና የአማራ ሃይሎችን ያበሳጨው የፌደራል መንግስታና የህወሓት አዲስ "ሽርክና" እየተሸረሸረ መሆኑን ያሳያል፡፡ የፕሪቶሪያ ስምምነቱ ትግበራ ህዝብን ተስፋ ባስቆረጠና በህውሓት ላይ ባስነሳ ሁኔታ ሲጓተት የትግራይ ሽግግር መንግስት ትእግስት እያለቀ መሆኑ የሚጠቁም የግብረመልስ መግለጫ አወጣ፡፡ ይህ በፌደራልና በትግራይ ሽግግር መንግስት መካከል የተፈጠረው ፍጥጫ የተከሰተው የሽግግሩን መንግስት የምትመራው ህወሓት ከኤሪትርያና ከአማራ ጋር ሰላም ለመፍጠር ጥረት እያደረገች ነው እየተባለ በሚወራበት ሰሞን ነው፡፡ ይህ ዜና ከሁለቱም (አማራና ኤሪትርያ) ጋር ለተጣላው ለአብይ አህመድና ለኦህዴድ አደገኛ የሃይል ሽግሽኝ ይፈጥራል፡፡ አቢይ አህመድም ስለ ጉዳዩ ቅሬታውን ለትግራይ መሪዎች ገልጿል፡፡

ሊፈጠር በሚችለው የትግራይ፤ የአማራና የኤሪትርያ አዲስ ጥምረት አቢይ አህመድና ኦህዴድ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ሊወድቁ እንደሚችሉ ግልጽ ነው፡፡ ምናልባትም ኢትዮጵያ ለሁለት ተገምሳ የሴማዊው ሰሜን አጋማሽና የኩሻዊው ደቡብ አጋማሽ የተባሉ ሁለት ነጻ አገሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ እንደ ደቡብና ሰሜን ሱዳን! ኦህዴድ የተቆጣጠረው ፌደራል መንግስት ህውሓትን ብሎም ትግራይን ለመቅጣትና ለማምበርከክ የወልቃይቷን ካርድ እየተጠቀመ ይመስላል፡፡ የምእራብ ትግራይና የተፈናቃዮች መመለስ የትግራይ ፖለቲካ አንኳር ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በፕሪቶሪያ ስምምነት ማግስት እርዳታ ጭኖ ትግራይ የገባው ኦህዴድ፤ የገዳ የባህል ልብስ አስለብሶ የትግራይን የሽግግር መንግስት አባላት ፎቶ ያስነሳው የኦሮሞ የኦህዴድ ፖለቲካ ይህን ያደረገው ትግራይ ላይ ከተፈጸመው ወንጀል እጆቹን ለመታጠብና ከአማራ ፋኖ ጋር ባለው ግብግብ የትግራይን ድጋፍ ለማግኘት በማሰብ ነው የሚል ግምት አለ፡፡ በፌደራል መንግስት በኩል

የትግራዩን ጦርነት በመራው በአህዴድና በትግራይ ህወሓት-መር መንግስት መካከል ተፈጠሮ የነበረውን ጥምረት የሚሸረሽር በቀድሞ የአህዴድ መስራች አመራሮች የሚስጥር ስብሰባ መጠናቀቂያ ላይ አቋም መግለጫ ሆኖ ወጣ፡፡ ይህ መግለጫ "ህወሓት የአህዴድ ግንባር ቀደም ጠላት ናት" የሚል ሲሆን አስገራሚና ያልተጠበቀ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ሌላ መላምት የሚወስድ ነው፡፡

ህወሓት ለተነሳባት የህዝብ ቁጣ ማብረጃ እንዲሆን በአንድ በኩል የስብሓት ነጋ ህወሓትን እንደ መልአክ የሚስለው ቃለ መጠይቅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ህወሓት ከኦሮሞ በኩልም አደጋ እንደተጋረጠባት በማስመሰል በስጋት ስሜት የትግራይ ህዝብ መከራውን ችሎ ዳግም ለህወሓት መከታ እንዲሆን የሚጠነጠን የሴራ ፖለቲካ ነውን? ያሰኛል፡፡ በሌላ በኩልም አህዴዶች ከህግደፍና ከአማራ ሃይሎች ጋር ጨርሰው እንዳይቆራረጡ ከትግራይ ጋር የፈጠሩትን ህብረት "የአብራሃም በግ" እያደረጉት ሊሆን ይችላል፡፡ በትግራይ ጦርነት ማግስት የኢትዮጵያ የሃይሎች መሰባሰብና መበታተን ውስብሰብና በቀናት ውስጥም የሚቀያየር በመሆኑ የፖለቲካ ተንታኞች ፈተና ሆኗል፤ ትናንት የተደረገው ትንተና ዛሬ ዋጋ ቢስ እየሆነ!

የወልቃይቱ ኮሎኔል ደመቀ የጂኦፖለቲካ ሳይንቲስቶችን እንኳ ሳይቀር ሊፈትን የሚችለው የወልቃይት ፖለቲካ ላይ ተቀምጦ ሰለ አዲስ የሃይል አሰላለፍ መግለጫ እየሰጠ ይገኛል፡፡ ኮሎኔል ደመቀ ወልቃይትን የተቆጣጠረው በአማራ ፋኖ ድጋፍ መሆኑን ዘንግቶ ከፌደራል መንግስት ጎን በመቆም ስለ አሁኑ የፋኖ ትግል ፋይዳቢስነት እየተናገረ ነው፡፡ ኮሎኔሉ የሃይል ሚዛኑን አይቶ፤ የፌደራል መንግስት በወልቃይት ላይ የሚያሳየው ለትግራይ የማይመች አቋምም ተመችቶት፤ ከአቅሙ በላይ በሆነ የፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ ዘሎ እየገባ ነው፡፡ ይቺ ቁማር ከኤሪትርያ መንግስትም ጋር የምታነካካው ስትሆን ካለበት አለም አቀፍ የዘር ማጽዳት ክስ ጋር ተደምሮ የፖለቲካ ህይወት ፍጻሜው የመጨረሻው መጀመሪያ ሊሆንብት ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 10.3 የህግደፍ ሽብልቅ ፖለቲካ

ሽብልቅ ፖለቲካ ማለት የጠላትን ጥምረት በተለያዩ ከፋፋይ ዘዴዎች መበታተን መቻል ነው፡፡ የኤሪትርያ መሪዎች አለም የተቀበለውን የፕሪቶሪያን ስምምነት "አልቀበልም፤ ተግባራዊነቱን አደናቅፋለሁ" እያሉ በግትርነት መቀጠሉ እንደማያዋጣ ተገንዝበዋል፡፡ በህወሓትና በአቢይ መንግስት መካከል የተፈጠረው

መቀራረብም አስደንግጧቸዋል፡፡ ኢሳያስና ባልደረቦቹ የቀራቸው አማራጭ ይህን የህወሓትና አቢይ መቀራረብ ንፋስ እንዲገባበት መጣር ነው፡፡ ይህም በሁለቱ መካከል መጠራጥር እንዲሰፍን በማድረግ ነው፡፡ በደሃይ መንእሰያት ሚድያ ሚያዝያ 25/2015 የተነበበውን የህግደፍ ጽሁፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

"በኢትዮጵያ የተከሰተው ቀውስ ያበቃው በፕሪቶሪያ ስምምነት በተደረገው የፖለቲካ ውሳኔ ሲሆን አስፈላጊው የትግበራ ስራ በመሬት ላይ እየተሰራ ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ስልታዊ-ታክቲካዊ እርምጃ ላይ እረፍት አጥቶ እየሰራ ነው፡፡ የወያኔ (ህወሓት) መሪዎች ግን ስምምነቱን ተጠቅመው በአማራና በኦሮሞ ህዝቦች መካከል በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል በኤርትራና በኢትዮጵያ መንግስታት መካከል መለያየት ለመፍጠር ትግራይ-ኦሮሞ የሚል ታክቲካዊ የሆነ ህብረት መስርተዋል፡፡ የኤርትራ መንግስትና የኢትዮጵያ መንግስት የአሜሪካን አጀንዳ ለማክሸፍና የወያኔ (ህወሓት) መሪዎችን ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ሁሉንም ጊዜያዊ መሰናክሎች ማሸነፍን መርጠዋል። በወያኔ መሪዎች ጊዜያዊ ተጣጣፊነት የተነሳ ለድርድር ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች አንድ በአንድ እየሰረዙ ነው። በዋሽንግተን ኢንጂነር የተደረገው የዘር ማጥፋት ክስም ቀስ በቀስ እየደበዘዘ ነው"

ህግደፍ በሌላ በኩል ደግሞ አቢይ አህመድን ከኢትዮጵያውያንና ከአማራ ህዝብ ጋር፤ ህወሓትን ከፌደራል ባለ ስልጣናት ጋር ለማነካከስ ይሞክራል፡፡ ሚያዝያ 29/2015 በአሰና የተነበበው አስተያየት ይህን ይመስላል፡-

"አቢይ አህመድ ለግል ጥቅሙና በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል የአሜሪካን ጥቅም አንድ በአንድ ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል። በአራት ኪሎ ለመቆየት የተጠየቀውን ሁሉ ለማድረግ በፍጹም አያቅማማም። ለኢትዮጵያ ትንሽ ስጋት ወይም ጭንቀት የለውም። የአማራን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ረግጧል፡፡ ትጥቅ ማስፈታትን ከመተግበር ይልቅ ያልተገደበ መሰረታዊ አገልግሎቶችን (ለትግራይ) እየሰጠ ነው። ህወሓት በአማራና በፌደራል መንግስት መካከል እንዲሁም በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ውጥረት ለመፍጠር የሚዲያ ጨዋታ እየተጫወተ ነው። ለጨዋታው ትኩረት መስጠት ያልቻሉት አንዳንድ የፌደራል ባለስልጣናት ከወያኔ ጋር ተጣምረው ይሽኮረመማሉ"

ህግደፍ መጀመሪያ ላይ አብይና ህወሓት በመቀራረባቸው በየተራ ሲወርፋቸው ቆየ፤ አብይንም ለብቻው ከህወሓት ክህደት እንዲጠነቀቅ ሲመክረው ነበር፡፡ ከአስመራ ሲለቀቁ የነበሩት በታኝ ቃላት ሰሚ በማጣታቸው የትግራይ የጊዜያዊ መንግስት ልኡካን አዲስ አበባንና ኦሮሚያን ጎበኙ፡፡ በዚህ ቅናት ያደረበት ህግደፍ በርካታ ባለስልጣናቱን ወደ አዲስ አበባ ልኮ የትግራይ መንግስት አባላት

የደረሱበትን ሁሉ ጎበኙ፡- የትግራይ ባለስልጣናት እንዳደረጉት የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ለብሰው ፎቶ ተነሱ፤ አዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ የጸጥታ፤ ወታደራዊና የስለላ ተቋማትን ጎበኙ፤ የትግራይ ባለስልጣናት ከቆዩበት ሆቴልም ሳይቀር ተስተናገዱ! በጄኔራል አብራሃ ካሳ የሚመራው በርካታ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የያዘው የኤርትራ ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ መንግስት እንደተጋበዘ ተዘግቧል።



ይህ በትግራይ ጥርጣሬን ያጫረ ጉብኝት ኤሪትርያ በትግራዩ ጦርነት ኢትዮጵያን በመርዳቷ ምስጋና ሲቸራት ጭንቀቱን አባባሰው፡፡ ሳጂድ ናዲም ስለ አወዛጋቢው ጉብኝት አስተያየት ሲሰጥ፡- “የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራውያንን የሚያቆላምጠው የተገለሉ ሆነው ከተሰማቸው ተቃዋሚዎቼን ይረዱብኛል በሚል ስጋት ነው” ይላል፡፡ በጉብኝቱ ማብቂያ ላይ የቡድኑ መሪ አብራሃ ካሳ በተበላ የማረጋጋት ዘዴ እንዲህ ብለዋል፡- “የፕሪቶሪያ ስምምነት በሁሉም ገፅታዎች ተግባራዊ ከሆነና ህጉ ተግባራዊ ከሆነ የኤርትራ ህዝብና መንግስት በኤርትራና በኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ፍላጎት አለው”፡፡ በዚህ መግለጫ ጀርባ ኤርትራ ከፕሪቶሪያ ስምምነት የምትፈልገው “በሁሉም ገጽታዎች” ስምምነቱ መተግበሩ ሳይሆን የህወሓትን ትጥቅ ማስፈታት ብቻ ነው።

አቢይ አህመድ ኤሪትርያ በኢትዮጵይያ ጉዳይ ውስጥ እጅ መስደዷን ማስቀጠል አልፈለጉም፡፡ ለዚህም መለሳለስ እንደማያዋጣ የተገነዘቡ ይመስላል፡፡ ሚያዝያ 24/2015 አቢይ አህመድ በአደባባይ ይህን ተናገሩ፤ የአገር ስም ባይጠቅሱም ኤሪትርያን የሚመለከት ለመሆኑ ቃላቱ ራሳቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ንግግር ከጦርነቱ በፊት ቢሆንስ?

“እነዚያን ሃይሎች በተለይም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ የፖለቲካ ችግር በተፈጠረ ቁጥር ጣልቃ መግባት የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ያልሆኑ ሃይሎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማሳሰብ እፈልጋለሁ። ኢትዮጵያን በማበላሸት የሚገኝ የፖለቲካ ትርፍ እንደሌለ ማወቅ አለባቸው። ጉዳያችንን ለእኛ መተው አለባቸው። ያልተቋጨ ብዙ ሥራ አላቸው፡፡ በራሳቸው መሬት ውስጥ የራሳቸውን ሥራ መሥራት አለባቸው”

## 10.4 ‘ያጣ ለማኝ ተሳድቦ ይሄዳል’

ኢሳያስ አፈወርቂ አቢይ አህመድን እንደዚያ አቆላምጦ ይዞት የነበረው ህወሓትን ለማጥፋት እንዲተባበረው ብቻ አልነበረም፤ በዋናነት ኢትዮጵያን በስጦታ ወረቀት ጥቅልሎ እንዲያስረክበው እንጂ፡፡ ህግደፍን በሚመለከት አቢይ አህመድ እንደ ብልጥ ከሌላ ሰው ስህተት ሳይሆን እንደሞኝ ከራሱ ጥፋት የተማረ ይመስላል፡፡ አቢይ አህመድ የነበረው ብኾታ ኢሳያስ አፈወርቂ ወደቦችን በመሶብ ተሸከሞ “ኢትዮጵያየ ፍዮሪ፤ ምሳይ ንበሪ” እያለ ወዳጁን ጥየቃ አዲስ አበባ እንደሚመላለስ ነበር፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የፕሪቶሪያ ስምምነትን ተከትሎ የተከሰተው የአቢይ አህመድና የህወሓት መቀራረብ ህግደፍን አስደንግጦት ስለነበር የአቢይን ወዳጅነት መልሶ ለማግኘት ትዝብት ላይ የሚጥሉ ደርጊቶችን ፈጽሟል፤ ህግደፍ፡፡



ሆኖም ህግደፍ ኢትዮጵያን ሲቋምጥ “አተርፍ ባይ አጉዳይ” ሆኖ ቀይ ባህሩን ሊያጣ እንደሆነ ገባው፡፡ የፖለቲካ ባህሉ ሆኖ ስልታዊ የሆነ ዲፕሎማቲክ ቋንቋን እጅግ አዋራጅ በሆኑ ጸያፍ ቃላት ተክቶ መግለጫ መስጠት የሚያዘወትረው ህግደፍ ለአቅመ ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ለአቅመ አዳምም ያልደረሰ ልጅ ግጥም አስጠንቶ አብይ አህመድን ሲያሰድብ ዋለ፡፡ "አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ አዘዘብህ እንደ ገና ዳቦ እሳት ለቀቀብህ" እንደተባለው የሚኒሊክ ዘመን ታሪክ አብይ አህመድ በህወሓት ላይ አስጸያፊ የሆነ የስድብ ናዳ ሲያወርድና የትግራይን ህዝብ ሰድቦ ለሰዳቢ ሲሰጠው “ነግ በኔ” ማለት በነበረበት እድሜ ላይ ነበር፡፡

## 10.5 ውጥረትና ሹምሽር በብልጽግና ካምፕ

የትግራይ ጦርነት ሲጀመርና በሂደት ላይ እያለም በፌደራል መንግስት መዋቅር ውስጥ ነፋስ እንኳ የሚሾልክበት ክፍተት አልነበረም፡፡ የሁሉም የህብረት ዝማሬ “ጁንታ ይጥፋ! ጁንታ እየጠፋ ነው! ጁንታ ጠፋ!” ነበር፡፡ አድሏዊ መሆን ከማይጠበቅባቸው የሪፓብሊኳ ፕሬዚደንት ጀምሮ ማህበራዊ ጉዳይ የሚመለከታቸው የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ሁሉ ትግራይ ውስጥ የነበረውን እልቂት፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንደ ስራቸው ስኬት ቆጥረው የሚኩራሩበት ሆኖ ነበር፡፡ የፕሪቶሪያ ስምምነት ተፈርሞ ከሱ ጋር በተገናዘበ ምክንያት አማራ ክልል ውስጥ ቀውስ ሲፈጠር እንደ ሸምበቆ አጥር ችምችም ክርክም ብሎ የነበረው የጎራው አንድነት ተናጋ፡፡

ቀደም ብለው የተሾኑት ቱባ ባለስልጣናት (ገዱ አንዳርጋቸው- የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር/ የሃገር ደህንነት አማካሪ፤ ንጉሱ ጥላሁን- የኮሚዩኒካሽን ሃላፊ)፤ ቀጥሎ መአዛ አሸናፊ (ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት)፤ ዮሃንስ ቧያለው (ከፍተኛ የብልጽግና ባለስልጣን)፤ ብርቱካን ሚደቅሳ (ምርጫ ቦርድ ስራ አስፈጻሚ)፤ ዳግማዊት ሞገስ (ትራንስፖርት ሚኒስትር) ተሸኝተዋል፡፡ የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት ዶር. ይልቃል ከፋለም ከአማራ ክልሉ ውጊያ ጋር ተያይዞ ከሃላፊነት ተነስተዋል፡፡ ይህ ሹም ሽር በስፋት እንደሚቀጥል ይታመናል፡፡ ፕሬዚደንቷ አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ በአማራ ክልል ጦርነት በመበሳጨታቸው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በጎሪጥ እየተያዩ የተነቃነቀ ጥርስ ሆነዋል፡፡ የባሰው ግን የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንን ከሃፊነት መወገድ ነው፡፡ የፌደራል መንግስቱ አስኳል የነበሩ ባለስልጣናት ስልጣን መልቀቅ የአቢይ አህመድ የመጨረሻው መጀመሪያ ወይስ ለረዥም የስልጣን ቆይታ የሚደረግ የቤት ጽዳትና የማስተካከል ስራ?



# ምዕራፍ ፲፩

# ኮምፓሱ የጠፋበት የትግራይ ድህረ-ጦርነት ፖለቲካ

## 11.1 የፕሪቶሪያ ስምምነት ተቃውሞና ድጋፍ በትግራይ

በትግራይ ላይ የወረደው መአት ከሰው የማሰብ አቅም በላይ ስለሆነ በርካታ ሰዎች “ፕሪቶርያ ከጦርነቱ በፊት አይቻልም ነበርን?” እያሉ ይጠይቃሉ፡፡ የሰው ልጆች መሰረታዊ ድክመት መተንበይና የማያዋጣውን መተው የሚያስችል ትእግስትና ጥበብ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ ጦርነትን አሸንፌ ፍላጎቴን አስፈጽማለሁ የሚለው ቁርጠኛ ውሳኔ ብሸነፍስ የምከፍለው ዋጋ ጦርነቱን ባልጀመርኩ የሚያስገኝ ይሆን? ብሎ መጠየቅና ውሳኔን በዚህ ላይ እንዲመሰረት ማድረግ ያልቻሉ መሪዎች ብዙ ህዝብ አስጠፍተው ለራሳቸም ጠፍተዋል፡፡ ሂትለርና ሰይጣናዊ ጓዶቹ መላ አውሮፓን የጀርመን ተገዢ ለማድረግ፤ ምድራችን ያለ አርያን ዘር ሌላ እንዳይኖርባት ለማድረግ፤ አይሁዶችን ከምድረገጽ ለማጥፋት የሚል የእብደት እቅድ ይዘው 50 ሚልዮን ህዝብ አስጨረሱ፡፡

በትግራዩ ጦርነት የሶስት ግዙፍ ሃይሎች የበላይነት ህልም እንቅፋት ነች ተብላ የተገመተችው ትግራይን ከአገርና ከአለም ካርታ ፍቀው ህዝቧንም በስደት እንዲበታተን ለማድረግ የታሰበው ዘመቻ እውን ሊሆን ስላልቻለ ህልሙ ወደ አስፈሪ ቅዠት ተቀይሮ አብሮ እንጦሮጦስ ከመግባት የተወሰደ ብቸኛ አማራጭ ነበር ፕሪቶሪያ፡፡ እንዲህ አይነት ጥፋት አስበ ያሳካ ማነው? ያላሳካውስ ማነው? ለምንና ለምን? ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ የተሳካላቸውን ብቻ እየመረጡ የኛም ሊሳካ ይችላል ብለው አሰቡ፡፡ አውሮፓውያን ስደተኞች በአሜሪካ ቀይ ህንዶችን ማጥፋትና የተረፉትን በየመጠበቂያ ማእከሉ ማጎር የተሳካ ታሪካዊ አረመኔነት ፈጽመዋል፡፡ በአሜሪካም አውሮፓዊ የሆነ ስደተኛ ስልጣኔ አብቧል፡፡

ከመላ ብሪታኒያ አለም በቃኝ እስር ቤቶች የተጓጓዙ ፈርደኞች በአውስትራሊያ ነባር ህዝቦች ላይ ፍጅትን ፈጽመዋል፡፡ በአውስትራሊያዋ ታስማኒያ አንድ ሰው እስኪቀር ድረስ ጭፍጨፋ መፈጽሙ እንደመልካም የልምድ ልውውጥ ሆኖ ለኢትዮጵያ ቀርቧል፡፡ ትግራይን የወረሩት ሶስቱም የጥፋት ሃይሎች አላማቸውን እንደሚያሳኩ እርግጠኛ ሆነው ስለነበር ፕሪቶሪያ ከጦርነቱ በፊት ሊመጣ

አይችልም ነበር፡፡ ከጦርነቱ በፊት የነበረው እብደት የሚመስል የጋለ ስሜት ምክንያታዊነትን ጨርሶ የሻረ ነበር፡፡ በመሰረቱ ፕሪቶሪያ ያሳካው ነገር ቢኖር በትግራይ መንግስት ቁጥጥር ስር ባለው አካባቢ ሁሉ የጥይት ድምጽ የማይሰማ መሆኑ እንጂ ጦርነቱን ያስጀመረው ዋና ግብ መከኗል ማለት አይደለም፡፡

የተወረሩት የትግራይ ግዛቶች ካልተመለሱ፤ ወራሪዎችም ጨርሰው ካልለቀቁ፤ ሚልዮን ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው ካልተመለሱ፤ ከስድስት አራት ሚልዮኑ ህዝብ በረሃብ ከተጠቃ፤ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ካልተመለሱ፤ የታመሙትም ታክመው ካልዳኑ፤ ሰራተኞች ክፍያቸውን ካላገኙና አውራጎዳናዎች ሁሉ ክፍት ሆነው ሰውና ሸቀጥ እንደልብ ካልተዘዋወረ ፕሪቶሪያ ያከናወነው ነገር ቢኖር የዘር ማጥፋቱን አላማ ለማሳካት አለም የሚያየውን የፊት በር ዘግቶ በጓሮ በር መግባትን ማመቻቸቱ ነው፡፡ የድህረ-ፕሪቶሪያ አንድ አመት የተስፋ ቆይታ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር ፕሪቶሪያ ማደንዘዣ እንጂ መፈወሻ እንዳልሆነ ነው፡፡

የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት በትግራይ ምን ስሜትን እንደፈጠረ ለመረዳት ስምምነቱን ሊቀበሉም ላይቀበሉም የሚችሉትን የፖለቲካ ሃይሎች አሰላለፍ መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ ከጦርነቱ በፊት ትግራይ በአገር ቤትም በዳያስፖራውም የሚንቀሳቀሱ ሁለት ግልጽ የሆኑ ግን አቅማቸው ተመጥጣኝ ያልሆኑ የፖለቲካ ካምፖች ነበሯት፡- ግዙፏና ግማሽ ምእተ አመት ትግራይን ያለተቀናቃኝ ያስተዳደረችው ህወሓት በአንድ ወገን፤ ህወሓትን ለመገዳደር ተዋህደው ህወሓትን በአቅም ሊፈትን የሚችል አንድ ፓርቲ እንደመመስረት አምስት ስድስት ህዳጣን ፓርቲዎች ፈጥረው ከዝሆነ ጋር የሚታገሉት ተቃዋሚዎች በሌላ በኩል፡፡ ሁለቱም ካምፖች የእውቀትና የገንዘብ አቅም ካካበተው የትግራይ ዳያስፖራ ድጋፍ ለማግኘት የተለያዩ አደረጃጀቶች ስለፈጠሩ የሸኩቻቸው ጦስ ለትግራይ ህዝብም እየደረሰ ነበር፡፡ አስር ጎራ ለይተው በፍልስፍና ሲነታረኩ ተገቢ ትኩረት ሰጥተው ለትግራይ ህዝብ ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ መደላድል ለማበጀት የሚሆን ጊዜ አልነበራቸውም፡- መነሻው ፖለቲካ፤ መንገዱ ፖለቲካ፤ መድረሻውም ፖለቲካ!

ተጽእኖ ፈጣሪ ሊሆኑ የሚችሉት የትግራይ የፖለቲካ ሃይሎች ፓርቲዎች ውስጥ የነበሩት ብቻ አይደሉም፡፡ እነዚህም ከዚህ በፊት ከህወሓት በጸብም በሰላምም

የተሰናበቱ ግለሰቦች፤ እንዲሁም ተጋሩ የቢዝነስ ሃይሎች በአዲስ አበባ ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች ከጦርነት በፊትም በጦርነቱ ወቅትም የተወሰኑት ከፌደራል መንግስት ጎን ሆነው ህወሓትን በማሳደድ ላይ ሲሳተፉ፤ ከፊሎቹ ከህወሓት ወግነው የተጎዱ፤ የታገሉና የተንገላቱ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ መሃል ሰፋሪ ሆነው የሚረዳላቸው ያጡ ነበሩ፡፡ ለጦርነቱ መጀመር ጥፋቱን ህወሓት ላይ የሚጭኑ የትግራይ ተወላጆች እንዳሉ ሁሉ የጦርነቱ መንስኤ ስሩ የሚመዘዘው ከታሪክ እንጂ የአቢይና የህወሓት ጸብ አይደለም ብለው የሚያምኑም አሉ፡፡ ህወሓትን እንደ ጦርነት ቀስቃሽ የሚከሱትና ህወሓት ስልጣን ይበቃታል የሚሉት የፖለቲካ ሃይሎች ፕሪቶሪያ የህወሓት መድህን እንጂ የትግራይን ህዝብ ችግር የሚፈታ አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ የነሱ ምርጫ የነበረው ከጦርነቱ በፊት የተመረጠው የትግራይ መንግስት ምክርቤት በትግራይ ህዝብ ስም እንዲፈራረም ነበር፡፡ በትግራይ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና አመራሮች በጦርነቱ ከህወሓት ካምፕ ተጠግተው ተሳትፈዋል። ይህ ሲባል ግን ከህወሓት ጋር ተግባብተው እስከ ፕሪቶሪያ ስምምነት ድረስ ዘልቀዋል ማለት አይደለም፡፡

በወረራው ትግራይ ቁጥጥር ስር እንደዋለች ህወሓትና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጋራ የሚያስቡት ምንም ነገር ሳይዙ ነበር ወደ ገጠር ለትጥቅ ትግል የወጡት፡፡ ከዚህም የተነሳ በሁለት አመት ውስጥ በትንሹም በትልቁም ሲነታረኩና በየበኩላቸው መግለጫ ሲያወጡ ለትግሉ ያስፈልግ የነበረውን የአላማ አንድነት ፈተና ላይ ጥሎት ለተቃራኒው ወገን ጠቃሚ የፕሮፓጋንዳ ግብአት ሆኖ ነበር፡፡ "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው!"፡፡ የሁለቱም የፖለቲካ ካምፖች አለመግባባት አንኳር ጉዳይ የነበረው ጦርነቱ እንዴት መመራት እንዳለበት ነበር፡፡ ህወሓት የመራችው የአማራ ክልል ውጊያ ዋና አላማው አዲስ አበባን ለመቆጣጠር ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች "ህወሓት ምእራብ ትግራይን ነጻ እንደማወጣት ወደ አዲስ አበባ የገሰገሰቺው ንብረቶቿን ለማስከበርና ከቻለችም የቀድሞ ስልጣኗን መልሳ ለመንጠቅ ነው" ብለው የራስ ወዳድነትና የክህደት ክስ ያቀርባት ነበር፡፡

በጦርነቱ ዋዜማ የትግራይ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሶስት ረድፍ ተሰልፈው ነበር፡፡ ሰልፉ እስከ ድህረ-ፕሪቶሪያ የዘለቀ ነው፡- ሳልሳይ ወያነ (ሳውት)፤ ባይቶና ዓባይ ትግራይና የትግራይ ነጻነት ፓርቲ (ቲፕ) ወረራውን ተቃውመው ወደ ትጥቅ ትግል የወረዱት ናቸው፡፡ ዓረና ትግራይ ወደ ትግል ለመውረድ ፈቃደኛ

ስላልነበረና ትግራይ ውስጥም መቆየት ስለተሳነው ዋና ሰፈሩን አዲስ አበባ አድርጓል፡፡ በጦርነቱ ላይ ያለው አቋም ወለም ዘለም ያለ በመኖሩ በሁለቱም ወገኖች በኩል ተቀባይነት አልነበረውም፡፡ የትግራይ ብልጽግና ፓርቲ የተሰኘው አፍቃሬ-አቢይ ፓርቲ ትግራይ ውስጥ እንደተቃዋሚ ሳይሆን በጠላትነት የተፈረጀ ስለሆነ ማእከሉን አዲስ አበባ ያደረገ ነው፡፡ በትጥቅ ትግል ዘመን የቀድሞ የህወሓት አመራር የነበሩ ግለሰቦች የሚመሩት የትግራይ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ከህወሓት በተጻራሪ የቆመ ብቻ ሳይሆን የትግራይ ጦርነትንም ሲደግፍ የነበረ ፓርቲ ነው፡፡

ምንም እንኳን የፕሪቶርያ ስምምነት ህወሓትን ነጻ የሚያወጣ መሆኑን ጨርሰው የማይቀበሉ ቢሆንም ለአቢይ አህመድ ካላቸው አጋርነት የተነሳ የትግራይ ብልጽግና ፓርቲና የትግራይ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ለሰላሙ ውል ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ስምምነቱን ታከው በትግራይ የስልጣን ተሳትፎ እንደሚፈልጉ ያሳወቁትም ብዙም ሳይዘገዩ ነበር፡፡ ዓረና ትግራይ ፓርቲም ስምምነቱ በትግራይ ለሚኖረው የአመራር ሚና በሩን ወለል አድርጎ የከፈተለት ሆኖ ተሰምቶታል፡፡ ስምምነቱ በህወሓት እንደተፈረመ ትግራይ ውስጥ ያሉት ሶስቱ ተቃዋሚ ፖርቲዎችና በዳይስፖራ የሚገኙት የ“አገረ ትግራይ” ርእዮት አራማጆች ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ አቀረቡ፡፡ በተቃዋሚ ጎራ ብቻ ሳይሆን የፓርቲ ውግንና የሌላቸው የትግራይ ተወላጆችም የህወሓት ስምምነቱን መፈረም የተቃወሙት ከፍተኛ የትግራይ ህዝብ ፍቅር ያተረፈውን የትግራይ ሰራዊትን ገለልተኛነት የሚንድ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ከስምምነቱ ማግስት ጅምሮ “የህወሓት ታጣቂዎች” ወደሚል የወረደው የትግራይ ሰራዊት ክብር የማንንም የትግራይ ተወላጅ ቅስም የሰበረ ሆኗል፡፡

የፕሪቶሪያው ስምምነት ለትግራይ ህዝብ ለጊዜውም ቢሆን እፎይታ ያስገኘ በመሆኑ በስምምነቱ ላይ የነበረው ተቃውሞ ብዙም አልዘለቀም፡፡ ውሎ ሲያድርም ተቃውሞው ወደ ድጋፍ ተቀይሮ ስለተግባራዊነት የሚደረጉ ክርክሮች ቀጠሉ፡፡ ስምምነቱን በመቃወምና በመደገፍ የነበረው አለመግባባት ስምምነቱን በመተግበር ላይ ወደ ተፈጠረው አደገኛ ልዩነት ተሸጋገረ፡፡ የትግበራው ቁልፍ አጅንዳ የሽግግር ወይም የጊዜያዊ መንግስት ምስረታ ነበር፡፡ በፕሪቶሪያ ስምምነት ከጦርነቱ በፊት የተመረጠው የትግራይ መንግስት ተቀባይነት ስላልነበረው በሽግግር ወይም በጊዜያዊ መንግስት መተካቱ የግድ ሆኗል፡፡

በስምምነቱ መሰረት ይህ መንግስት መቋቋም ያለበት የህወሓት የሽብር ስያሜ በተነሳ በሳምንት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ የሚቋቋመው መንግስትም አካታች መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ህወሓት ከሽብርተኛ ዝርዝር የተሰረዘው የፕሪቶሪያ ስምምነት ከተፈረመ በአምስተኛ ወሩ ነው፡፡ ጌታቸው ረዳ የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት ሆኖ በአቢይ አህመድ የተሾመው ግን ህወሓት ከሽብር ዝርዝር በተሰረዘ ማግስት ነበር፡፡

የሽግግሩ መንግስት አካታች እንዲሆን የሚለው የውሉ አንቀጽ አተረጓጎም ላይ በህወሓትና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት በተገኘው ሰላም የፖለቲካ መረጋጋት እንዳይሰፍን አድርጎ ትግራይን በአንድ እግሯ አቆማት፡፡ ህወሓት የሚኖረን ውክልና በቁመታችን ልክ ይሁን ስትል ተቃዋሚዎቹ ግን እኩል እንወከል ብለው ተከራከሩ፡፡ በተፈጠረው መካረር የተሸመደመደው የትግራይ አስተዳደር የአማራና የኤርትራ ሃይሎች ያለ ምንም እንቅፋት በትግራይ እንዲዘዋወሩ አስችሏቸዋል፡፡ የሰላማዊ ሰዎች ግድያ፤ የሴቶች መደፈርና የንብረት ዝርፊያ በሰፊው ቀጠለ፡፡ በትግራይ አውራ ከተሞች ውስጥ የታጠቁ ዘረፋዎችና ሌሎች አይነት ጥቃቶች ከቁጥጥር ውጭ ሆነዋል። በየደረጃው ያሉ የአካባቢ አስተዳደሮች ከፍተኛ ብልሽት ገጥሟቸዋል፡፡ ሰብአዊ እርዳታን በመዝረፍ የተሰማሩም በርካታ ናቸው፡፡ በትግራይ ከተሞች የሚኖሩ ነጋዴዎች ከትግራይ ውጭ ከሚገኙ ነጋዴዎች ጋር በመተባበር የዋጋ ንረት ፈጥረው ያለ ምንም ርህራሄ ህዝቡን እያስቃዩት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ኢንሳይት መጋቢት 22/ 2015 በትግራይ የድህረ-ፕሪቶሪያ የፖለቲካ ውኸንብር ላይ የጻፈው እንዲህ በሚል ነው፡-

> “በህወሓትና በትግራይ ተቃዋሚዎች መካከል በሽግግር መንግስቱ ምስረታ ላይ ያለው ውጥረት ፈልቶ ወደ መገንፈል እየተቃረበ ነው። ተቃዋሚዎች የፖለቲካ ጡንቻቸው ከሚፈቅደው በላይ በሽግግር መንግስቱ ውስጥ ትልቅ ሚና መጫወት ይሻሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ የትግራይን የፖለቲካ ምህዳር ብዝሃነት በሚያንፀባርቅ የስልጣን መጋራት ማነጽ ወሳኝ ነው። የትግራይ ምሁራንና የንግዱ ማህበረሰብ ለማደራደር ተነሳሽነቱን ካልወሰዱ በስተቀር በህወሓትና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለው ውጥረት የትግራይን የድህረ-ጦርነት ሽግግር ሊያናጋ ይችላል።”

## 11.2 በትግራይ የፖለቲካ ዛር መውረድ

አቶ ልደቱ አያሌው በህወሓት ዘንድ የተፈጠረውን ትርምስ አስመልክተው "ከአጼ ዮሃንስ በኋላ በትግራይ የሆነው ነገር እንዳይደግም እሰጋለሁ" ብለው የተናገሩት ቃል ሳምንት ሳይሞላው የሳልሳይ ወያነ ትግራይ ሊቀመንበር አሉላ ሃይሉ ህወሓትን በሃይል ማውረድ ያስፈልጋል ብሎ የርስበርስ ጦርነትን በይፋ ጋበዘ፡፡ ይህ የሚያስገርም ጥሪ ሊሆን አይገባም፤ እንዲያውም ዘግይቷል፡፡ የትግራይ ስር የሰደደ የፖለቲካ ባህል ዓወት ወዳጅ የተባሉ ገጣሚ ስንኝ እንደቋጠሩለት "የጦርነት አንበሳ፤ የሰላም ውሻ" መሆኑን መቀበል የሚከብዳቸው ብዙ ናቸው፡፡ እውነት ነው ህዝብን ያህል ነገር በዚህ አይነት መደምደሚያ መፈረጅ ተገቢ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ትግራይ እንደ አንድ ሰው ሆና ያሸነፈችበት ጦርነት ባበቃ ቁጥር ወደ እርስ በርስ መነካከስ የምትወርድበት፤ ብዙ የከፈለችበትን ድል የምታባክንበት ምስጢሩ ወቅት ጠብቆ ከሚወርደው የፖለቲካ ዛር ካልገኘ ከቶ ከየት ሊገኝ ይችላል? በርግጥ ይህ የድህረ-ጦርነት ንክሻና የድህረ-ህብረት ፍርሻ የህዝቡ ባህል አይደለም፤ የፖለቲካ ባህል ሆኖ የኖረ የልሂቃን ግርሻ ነው እንጂ፡፡

ትግራይ የሶስት ሺ ዘመናት ያልተቋረጠ መንግስታዊ ስርአት ሰፍኖባት የኖረች ናት፡፡ ከዚህ ታሪክ የሚጠበቀው በህዝብ ዘንድ ባህላዊ እሴት ሆኖ የተቀረጸና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር የዳጎሰ የፖለቲካ እውቀትና ክህሎት ነው፡፡ የሮምና የግሪክ ስልጣኔዎች ወራሾች የሆኑ ህዝቦች አስተማማኝ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ገንብተው፤ በውሳኔ አሰጣጥ የተሟላ የህዝብ ተሳትፎን እውን አድረገውና ከለሙ አገሮች ተርታ ተሰልፈው በሰላም ይኖራሉ፡፡ የነዚህን ያህል አይሁን እንጂ በግብጽም፤ በቻይናም፤ በህንድና ፓኪስታንም የረዥም ዘመን መንግስታዊ ስልጣኔ ያስገኘላቸውን የፖለቲካ ህይወት እየተቋደሱ ናቸው፡፡ ትግራይ ውስጥ ያለው እውነታ ግን ቀደም ብለው ከተጠቀሱትና መደበኛ የታሪክ ሂደት ከሚከተሉት ህዝቦች መስመር ያፈነገጠ ነው፡፡

ትግራይ የህዝብ ሳይሆን የልሂቃን አገር ነው፡- በፖለቲካ እውቀት የተካኑ፤ በሃብት የደረጁ፤ የዘር ሃረግ የሚመዙ ጥቂት ሺዎችና የፖለቲካ እውቀትና ክህሎት እንደ ሰማይ የራቃቸው፤ ረዥም ስር በሰደደ ድህነት የሚማቅቁ ብዙ ሚልዮኖች! ሰሞኑን በ88 አመታቸውም ቢሆን  ከፖለቲካ አልላቀቅ ያሉት

የቀድሞ የህውሓት አመራር አባልና መሪ አሁንም ትግራይን ከአሜሪካ በርቀት እየመሩ መሆናቸውን ያረጋገጡበት ቃለመጠየቅ አድርገዋል፡፡ ለትግራይ ህዝብ ይህ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በመሳፍንቱ ዘመን በትግራይ በየደረጃው የነበሩ ገዢዎች አዲስ አበባ ተቀምጠው ለወራት ወይም ለአመታት ግዛቶቻቸውን የሚያስተዳድሩ ነበሩ፡፡ ደጃዝማች ገብረሰላሴ አዲስ አበባ ከነበረው የአራት ኪሎ ግቢ ፖለቲካ ሽኩቻ ውስጥ እየተሳተፉ አድዋን፤ አክሱምንና ሽረን በወኪል ያስተዳድሩ እንደነበረ በዚህ መጽሃፍ ምእራፍ ሁለት በሰፊው ተገልጿል፡፡ ራስ ስዩምም ቢሆኑ አብዛኛውን የትግራይ የስልጣን ጊዚያቸውን ያሳለፉት አዲስ አበባ ፈረንሳይ ለጋሲዮን በሚገኘው ቪላቸው ውስጥ ሆነው ነው፡፡

ትግራይን ትግራይ ውስጥ ሆነው ማስተዳደር ሲገባቸው፤ መቶ ሺዎችን በጎዳው የ17 አመቱ የትጥቅ ትግል ወቅት በገቡት ቃል መሰረት በእውቀታቸውና በችሎታቸው የላቁትን የህወሓት አባላት ትግራይ ላይ መድበው የህዝቡ የፖለቲካ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወትን እንደማሻሻል ከእውቀት ነጻ በመሆናቸው፤ በስንፍናቸው፤ በሌብነታቸውና በጠጪነታቸው  የሚታወቁትን ፋይዳ ቢሶች ትግራይ ላይ መድበው ምን ያህል ህዝቡን እንደሚንቁትና እንደ መገልገያ እቃ እንደሚቆጠሩት ህያው ማረጋገጫ ሲሰጡ ኖረዋል የህወሓት አመራሮች፡፡ በአስራሰባቱ አመት የትጥቅ ትግል ህዝቡን የፖለቲካ መሰረተ ሃሳብ፤ ስለዴሞክራሲና ህዝባዊ አስተዳደር፤ እንዲሁም ስለ ልማት ጎዳናዎች ምርጫ እንደ ማስተማርና ህዝቡን ለሚታገልለት የራሱ የስልጣን ባለቤትነት እንደ ማብቃት ከነሱ በስተቀር ማንም ሌላ ሰው ሊገባው የማይችል በረቀቁ የማርክሳዊ ጻንሰ-ሃሳቦች ክርክር ላይ ጊዜያቸውን ሲፈጁ እንደነበር የሚያሳዩ በርካታ ቪድዮዎች አሉ፡፡ አባይና መለስ ተከራካሪ ሌላው ሰሚና ተመልካች! ስብሓት ነጋ ከ50 አመታት የህወሓት የትግራይ አመራር በኋላ የትግራይ ህዝብ የፖለቲካ መሃይም መሆኑን በማርዳት ውድቀታቸውን ለአለም ባደባባይ መስክረዋል፡፡ “ሳይንስና መስመር” ብሎ መናገሩ የፖለቲካ እውቅት አይሆንም፡፡

የትግራይ ህዝብና የፖለቲካ አመራሩ የሚተያዩበት አይን የጌታና የሎሌ መሆኑ የሚወገዝበትና ለዘላለሙ የሚወገድበት የማይታለፍ የታሪክ አጋጣሚ የተገኘው በትግራዩ ጦርነትና ቀጥሎ በመጣው የሰላም ጊዜ ነው፡፡ ለስልጣንና ሃብት የተቀቡ ሺዎችና ለአገልግሎት፤ ለሞትና ለመከራ ተመድበው የኖሩት ሚልዮኖች እኩል ሆነውና ተደማምጠው ትግራይን በጋራ እንዲገነቡ ተስፋ የተደረገበት

የጦርነት ማግስት ነበር፡፡ ህዝቡን በባዶ ሆዱ ሲያዋጉት የነበሩት የድሮዎቹ መሳፍንት፤ ህዝብን በሴፍቲ-ኔት አድቅቀው ለክፉ ጊዜ እንደ መጠባበቂያ ያኖሩት የዘመኑ መሳፍንትን "ይበቃል!" የሚባሉበት የአዲስ ዘመን ብርሃን የፈነጠቀ መስሎ ነበር፡፡ "ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ" እንደተባለው የህወሓት አመራሮችን ከልሎና አስጠልሎ ከጉድ ያወጣ የትግራይን ህዝብ ከአዲስ አበባ ጋር ባደሱት ግንኙነት ተማማነው በቀድመ-ጦርነት በህዝቡ ላይ የነበራቸውን አመለካከት መልሰው ለማስፍን ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ "እስኪነክስ ያነክስ" ሆነና በህዝብ መስዋእትነት ህይወታቸው ተጠብቆ ለቤታቸውና ለስልጣናቸው የበቁት አመራሮች በጠባቂና በአጀብ ጋጋታ ከህዝባቸው አይን ተሰውረዋል፡፡ ይህን ያህል የሚጠበቁት ከማን ይሆን? ከጠባቂያቸው? "ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ መመለሻ የለውም" ነውና ከትግራይ ህዝብ ተስፋ የመቁረጥ አደጋ ይጠንቀቁ!

የህወሓቱ አንጋፋ መሪ ስብሓት ነጋ ባደረጉት ቃለ መጠይቅ የፖለቲካ ድርጅታቸው ህወሓት ከአፍሪካ የሚወዳደራት ሌላ ፓርቲ እንደሌለ ተናግረዋል፡ የርእዮቱ ቴዎድሮስ ጸጋየ ይህን አባባል ሲተች ህወሓት ከአፍሪካ አንደኛ ፓርቲ ከሆነች ከየት የፈለቀች ፓርቲ ናት ብሎ በመጠየቅ ይጀምራል፡፡ ቀጥሎ ስሌቱን እንዲህ ይደረድራል፡- "ህወሓት የፈለቀችው ከትግራይ ህዝብ ከሆነ፤ ስብሓት ነጋ ደግሞ የትግራይ ህዝብ (አማራን ጨምሮ) ፖለቲካ አያውቅም ብለው ካሳነሱት፤ ከአፍሪካ አንደኛ የሆነ ፓርቲ ከፖለቲካ መሃይም ህዝብ ሊቀዳ ስለማይችል" የስብሓት ነጋን አባባል ዋጋ በማሳጣት "ህወሓት ከሌላ አገር የተገኘች ለትግራይ ባእድ የሆነች ድርጅት መሆኗ ነው" ብሎ ይደመድማል፡፡ የፖለቲካና ማህበራዊ አቧራ ባነሱ ቁጥር ሃይ ተብለው የማያውቁት ስብሓት ነጋ የህወሓት ሙገሳቸው ከፖለቲካ አዋቂዎች ያላሰቡት ትርጉም እንደሚያመጣባቸው ለማሰብ እንኳ ጊዜ አልሰጡም፡፡ በአድናቂዎች ወይም ለሚድያቸው ዘላቂነት በሚጨነቁ ጋዜጠኞች ለቃለ መጠይቅ ሲጋበዙ ላልታሰበ ጥያቄ ዝግጅት ማድረግ አይጠበቅም፤ ጥያቄዎቹም የታወቁ መልሱም ምን ይሁን ምን ተቀባይነት ያገኛልና፡፡ ስብሓት ነጋ በማያስቀው የሚሳቅላቸው የትግራይ ረእሰ-መሳፍንት ሆነው ስለኖሩ፤ ከሚናገሩትና ከሚሰሩት ነገር ተነቅሶ የሚወጣውን ቅራኔ ጮሆ ለመናገር የሚደፍረው ብዙ ሰው አይደለም፡፡

የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ መጠናቀቅን ተከትሎ በበለጠ ድሉን ለማብሰር ለቃለ መጠይቅ ብቅ ያሉት ስብሓት ነጋ ምናልባት እንደተመኙት አከራካሪ ሆነው ሰንብተዋል፡፡ የትግራይ የፖለቲካ ትኩረትም አቅጣጫውን አስቀይረው በሳቸው አጀንዳ ላይ እንዲጠመድ አድረገውታል፤ ህወሓት ከደረሰባት የህዝብ ትችታና ቁጣ ትንፋሿን መልሳ እስክታገኝ ድረስ፡፡ ይህ አይነቱ የማረሳሳትና የጋለ የትግል ስሜትን የማብረድ ታክቲክ ለትግራይ ህዝብ የዘመናት ማደናበሪያው ሆኖ የኖረ ነው፡፡ የባይቶናው ኪዳኔ አሚኔ ስብሓት ነጋን “የኮሚኒስቱ አውራ” አድርጎ መሰየሙ ትልቅ ግድፈትና ቅንንነት የጎደለው ነው፡፡ በመሰረቱ እኒህ ሰው ኮሚኒስት አልነበሩም፤ የተወሰነ የትግራይ ህብረተሰብ ክፍል በፖለቲካም በኢኮኖሚም የበላይ እንዲሆን ለፍተው የተሳካላቸው የድሮዎቹ የትግራይ መሳፍንት ውርስ እንጂ፡፡ ኮሚኒስት ቢያንስ “አለማቀፋዊነት” መርህ ተከትሎ “አለም የሰርቶ አደሮች ትሆናለች!” ብሎ መፈክር የሚያሰማ እንጂ እይታው ከሰፈሩ የማይርቅ አይነጠባብ አይደለም፡፡ በትግራይ የተወሰነ አካባቢ አግንነው ቀሪውን አኮስሰው የሚሰነዝሯቸው ትችቶችና ዘለፋዎች በፈገግታ ሲታለፉ በግብረ-መልስ ተመሳሳይ ተግባር የሚፈጽሙት ላይ ግን የአካባቢያዊነት ሰሌዳ ይለጠፍባቸዋል፡፡

በትግራይ “አንዳንዶቹ ከሌሎቹ የበለጠ እኩል ናቸው” በሚል ስሜት ያካባቢ ተወላጅ የትውልድ ቦታውን እንኳ ማስተዳደር እንደ ነውር ተቆጥሮ ለመላ ትግራይ የዞንና የወረዳ አስተዳድሪዎች ከየትኞቹ የ“ብር ማንኪያ” ልጆች ሰፈር ይሾም እንደነበር የትግራይ ያፈጠጠ ሃቅ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ የሚፈልገው መልካም አስተዳደር፤ ልማትና ዴሞክራሲን እንጂ ባዶ የርእዮተ አለም ንዝንዝ አይደለም፤ “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው”፡፡ ኪዳኔ አሚኔ የተናገሩት የዘመኑ የትግራይ ወጣት ፖለቲከኞች ያለባቸውን ድክመት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ የድሮዎቹ ወጣቶች ሶሻሊዝምን ሳይውቁት ተነከሩበት፤ የዘንድሮዎቹ ደግሞ ሳያውቁት ካፒታሊስምን እየተነከሩበት ነው፡፡ በነዚህ ፖለቲከኞች አምባ ካፒታሊዝም መልአካዊ ሰሻሊዝም ደግሞ ሰይጣናዊ ነው፡፡ በጎቹ፡- “ባለ ሁለት እግር መጥፎ፤ ባለ አራት እግር ጥሩ!”፡፡ ባይቶና የሚፋጀውን ካፒታሊስምን በሶሻሊዝም ቅመም በረድ ያደረገውን ሶሻል ዴሞክራሲ እንደ ርእዮተ አለም የተቀበለ ድርጅት ነበር፤ አሁን አውልቆ ጥሎት ካልሆነ በስተቀር፡፡

ሶሻሊዝምን "ኮሚዩኒዝም" እያለ የሚያሰየጥንበት ብልሃቱ ምንድነው? በመሰረቱ ኮሚዩኒዝም በምናብ ካልሆነ ያልተኖረበት ሊኖርበትም የማይቻል ከሰው ልጅ መሰረታዊ ባህርይ የራቀ ስርአተ ማህበር ነው፡፡ ኮሚዩኒስት የሚለው ቃል አዋራጅ ወይም "ዴሮጌቶሪ" ነው፡፡ በ1960ዎቹ አሜሪካ ከተቀናቃኟ ሶቭየት ህብረት ጋር በነበራት ሁሉን አቀፍ ግድድር የሶቭየት ህብረትና ቻይና ደጋፊዎች እንዳይሆኑ ብላ የምትጠረጥራቸውን ዜጎቿን የምታሳድድበት የህዝብ ማስፈራሪያ ስያሜ ነበር፤ "ጁንታ" ሲባል የኢትዮጵያ ህዝብ ሲደነብር እንደነበረው፡፡ ስብሓት ነጋንና ህወሓትን "ኮሚዩኒስት" እያሉ በአደባባይ መጥራት ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ቢኖር የህዝብ ፍቅርና አመኔታን ሳይሆን የአሜሪካን መንግስት ድጋፍ ነው፡፡ ይቺ ደሮ ጭራ የምታወጣት ፖለቲካ ባትዘወተርና ባትሰለች ጥሩ ነበር፡፡ ስብሓት ነጋንና ህወሓትን መታገል የሚገባው ለራሳቸው ጥቅምና ህልውና የትግራይን ህዝብ ታጋች በማድረጋቸው ነው፡፡ አይተገበርም እንጂ የሚተገበርማ ቢሆን ኮሚዩኒዝም የኤደን ገነት ማለት ነበር፡፡

የስብሓት ነጋን ቃለ መጠይቅ ተከትሎ ስብሓት ከተናገሩት ውስጥ የተሳሳቱት ይሁን ልክ የሆኑበትን ሁሉ ቅዱስ ቃል ለማድረግ ተሰልፈው ወደ ሶሻል ሚድያ ብቅ ያሉ ሰዎች በርክተው ሰንብተዋል፡፡ በስብሃት ነጋ ቃለመጠይቅ የቴዎድሮስ ጸጋይ ተቃራኒ ሆነው በስሜት እየተንተገተጉ ሲከላከሉ የታዩት ድባቤ ነበሩ፡፡ አፍቃሬ ህወሓት መሆናቸውን የማይደብቁት ድባቤ፤ ይህ አመለካከት ሙሉ መብታቸው ሆኖ፤ ነገር ግን የስብሓት ነጋ ንግግሮች የትግራይን ፖለቲካ አካሄድ ወደባሰ የአንድ ፓርቲ ጊዜ የማይሽረው የበላይነት እንዲያመራ የሚፈቅድ ከሆነ የግል አመለካከታቸው ለትችት እንዲጋለጥ ግድ ይላል፡፡ በኪዳኔ አሚኔ ላይ ያወረዱት የቃላት ውርጅብኝ በስብሃት ነጋ "ኮሚዩኒስትነት" ብቻ ሳይሆን ስብሓት ነጋ "ጓድ ኢሳያስ" ብለው ተናገሩ ብሎ ኪዳኔ አሚኔ በመተቸቱ ነው፡፡

እውን ይህ የኪዳኔ አሚኔ የግል ንዴት ብቻ ነው ወይስ የህዝብንም ቁጣ የሚጋብዝ አነጋገር? በጦርነቱ የበኩር ልጃቸውን ያጡ እኒህ አዛውንት አንጋፋ የህውሓት አመራር ኢሳያስ አፈወርቂን "ጓድ" ብለው የጠሩት "በአፍ ወለምታ" ነው እያሉ ድባቤና የቃለ ምልልሱ አዘጋጅ እየተቀባብሉ እንደ መሃይም የቆጠሩትን ተመልካች ማሳመን ሞክረዋል፡፡ ተመልካቾቻቸውን የበለጠ ለማሳመን ባደረጉት ትግል ወደባሰ የቅራኔ ማጥ ውስጥ ገቡ፡፡ ቀጠሉ ድባቤ፡- "የኢሳት ጋዜጠኞች ስብሓት ነጋን 'አቦይ' እያሉ ይጠሯቸዋል፤ ጠላትህን 'ጓድ'

ብሎ መጥራት ምን ነውር አለው?"፡፡ የግራ መንገዱን ይዞ መጥቶ እንደሚያደናብርህ የእንግሊዝ አገር መኪና በዚህ አባባል ላይ ክርክር መክፈት በጊዜና በጉልበት መጫወት ነው፡፡ እንኳን በውኑ እያለ በሌሊት ቅዠትም ቢሆን ጠላቱን "ጓድ" እያለ የሚያቆላምጥ የሰው ፍጡር ሊኖር አይችለም፡፡ "ሆድ ያባውን ምን ያወጣዋል" ሆኖ ነው እንጂ፡፡

ከስብሓት ነጋ ቃለ መጠይቅ መገንዘብ የሚቻለው ሌላው አቢይ ነገር በትግራይ ላይ የህወሓትን አገዛዝ ዘመን የማይሽረው በማድረግ ስርወ-መንግስትን የማደራጀት ያላሰለሰ ጥረት፤ እንዲሁም የትግራይን ህዝብ ታሪክ ከየካቲት 11 ለማስጀመር ያለው ዳርዳርታ ነው፡፡ ህወሓት የትግራይ "ቄሳር" ሆና እንድትኖር ከተፈለገ የትግራይን ህዝብ ፈሪና አማራጭ የሌለው የህወሓት ጥገኛ ማድረግ ነው፡፡ "ኢሳያስ አፈወርቂና አቢይ አህመድ የሲ.አይ.ኤ. ምልምሎች ናቸው" ማለት ህወሓት ካልመራችው የትግራይ ህዝብ በሁለቱም ላይ ምንም አቅም ሰለማይኖረው ለዳግም ወረራ ሊጋለጥ ይችላል የሚል እንደምታ ያለው ነው፡፡ ሌላው የስብሓት ነጋ የቃለ ምልልሱ ገጽታ አቢይ አህመድ የትግራይን ፖለቲካ በበላይነት ለመቆጣጣር ሲል የመስረጽ ("ኢንገልፍ ኤንድ ኢንፍልትሬት") ፖሊሲ እየተከተለ እንደሆነ የሚያስገነዝብ ነበር፡፡ ይህ አባባል በትግራይ ዴሞክራሲ ላይ የተወለወለ አደገኛ መሳሪያ ነው፡፡ ህወሓትን ለማረም ይሁን ከስልጣን ለማስነሳት በሰላማዊ መንገድ የሚታገለውን ሁሉ "የአቢይ ስርጸት" እየተባለ የቱ የአቢይ ህወሓትን የማዳከም ሴራ የቱ ደግሞ በቅንነት ለዴሞክራሲ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል እንደሆነ ሳይለይ በደፈናው እርምጃ ለመውሰድ!

ስብሃት ነጋ ያነሱት የፖለቲካ አቧራ ይህ ብቻ አልነበረም፤ ህወሓትን አዳነ ብለው ያሞጋገሱት የሁለቱ ወራት ስብሰባ ከሁለት አመቱ "መኸተ" ማሰበለጣቸው ነበር፡፡ ስለ ሁለቱ አመታት የትግራይ ጦርነት "የሚያቁት ጥቂት ነገር ብቻ እንደሆነ" ከገለጹ በኋላ ጦርነቱ "በአለም ታይቶ አይታወቅም" በላቸው ጥቂት መረጃ ላይ ተደግፈው ተራራ የሚያክል ድምዳሜ ሰጥተዋል፡፡ ከሁለት ወሩ የህወሓት ስብሰባ አንሶ የታያቸው ታላቁ ህዝባዊ "መኸተ" የስብሓት ነጋ ጉዳይ የህወሓት ህልውና እንጂ የህዝብ ትግል እንዳልሆነ ግልጽ አድረገዋል፡፡

የድህረ-ፕሪቶሪያዋ ትግራይ መጀመሪያ ምስቀልቀሏ የወጣው ስምምነቱን በመፈረሟ በህወሓት ላይ በተነሳው የተቃዋሚዎች ውርጅብኝ ነበር፡፡ ህዝቡ

ያለቁትን ልጆቹን በለቅሶ እያስታወሰ፤ ከሰራዊት ያልተመለሱትን እየናፈቀ፤ የፈረሰውን ቤቱን ታቅፎ ደጅ እየዋለና እያደረ፤ ምግብና ህክምና እንደ ሰማይ ርቆት የሞቱን ቀን እየጠበቀ፤ ከቀየው በሚልዮን ተፈናቅሎ በሸራ ቤትና በኮንክሪት ምሶሶ ስር እያደረ፤ የሱፋቸውና የሽሚዛቸው ጥራትና የአጃቢዎቻቸው ቁጥር መሳሳት የሚያስጨንቃቸው፤ የዊስኪው አይን ቀለም የሚደብራቸው፤ የቪ ስምንት ወንበር የሚደላቸውና ከነሱ ህይወት ያገኙ፤ የነሱን ህይወት የሚመኙ ሁሉ ከህዝቡ ርቀው ማዶ ለማዶ ሰፍረዋል፡፡ ህዝቡ ከልሂቃን ሰፈር የሚሆነውን ለማወቅ የሚችልበት አቅም የለውም፤ ልሂቃኑም ከህዝቡ ሰፈር የሚሆነውን ለማወቅ ጉጉት የላቸውም፡፡ ህዝቡን "ሲፈልጉት ይገኛል፤ ሲጠሩትም ይሰማል" ብለው ከልባቸው ስለሚያምኑ፡፡

ህዝቡ የፖለቲካ ልሂቃኑ በምን እንደሚጨቃጨቁ፤ ለምን እንደሚጭቃጨቁ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ የሚያውቀውና የሚፈራው ነገር ቢኖር "እርስ በርስ ሲራኮቱ ያስበሉናል" የሚለው ስጋቱን ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው ከመአት ለተረፈችው ህይወቱና ጎስቋላ ኑሮው የተጨነቀው ህዝብ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር የሚመኘበት ቅንጦት ላይ ስላልሆነ የተካረሩትን መሪዎች እንዲህ ብሎ የሚመክረው፡- "ተስማምታችሁ ማስተዳደሩን ተዉትና ተስማምታችሁ ግዙን!"፡፡ የሽግግር መንግስቱ (አስተዳደር መባል አለበት የሚሉ አሉ) ተመስርቶ፤ ፕሬዚደንት ተሹሞለት ርክክብ የተደረገ እለት በተረካካቢዎቹ ፕሬዚዳንቶች የተነገሩት እንደ አበባ የፈኩ ቃላትን ያሸተተ ይድናል ማለት ይቻል ነበር፡፡

አስረካቢው የትግራይ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ዶር. ደብረጽዮን ገብረሚካኤል "የትግራይን ግዛታዊ አንድነት ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባራችን ነው፤ የሽግግር መንግስቱንም አቅማችንን ሁሉ አንድ አድርገን ሙሉ ድጋፍ ልንሰጠው ይገባል" ብለው ቃል ገቡ፡፡ የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንትም "የትግራይ የግዛት አንድነት ይመለሳል፤ ተፈናቃዮቹም ወዲያውኑ ቤታቸው መመለስ አለባቸው" በማለት አጽንኦት ሰጡ፡፡ ሁለቱም ፕሬዚዳንቶች የወቅቱ የትግራይ ቁንጮ መሪዎች ናቸው፡- መሬት ላይ ልዩነት ባይኖራቸውም አንዱ የፓርቲ አንዱ የመንግስት ዋና አስፈጻሚዎች ናቸው፡፡ እነሱ የገቡት ቃል መሬት ላይ ጠብ ማለት የለበትም፤ ሆኖም ቃል ገቢዎች ቃለ አባይ ከሆኑ አንድ አመት ሆናቸው፡- ግዛቶችና ተፈናቃዮች አልተመሱ፤ ደብረጽዮንም ጌታቸውን ከልባቸው አልደገፉ!

ከፕሪቶሪያ ፊርማና ከሽግግር መንግስት ምስረታው አተካራ እንደወጡ ጊዜ ሳይጠፉ ወደ የማእከላዊ ኮሚቴ ግምገማ ግቡ! ለስድሳ ቀናት ለሶስት አራት ተከፍለው ሲወነጃጀሉና ሲዘነጣጠሉ ከ1977ቱ የከፋ ነው የተባለው ረሃብ የትግራይን ሰባ ከመቶ ህዝብ አጠቃ፤ ስብሰባው ግን ቀጠለ፡፡ ስልጣን ማደላደል እንጂ ቅድሚያ የሚሰጠው የህዝብ የርሃብ እልቂት ባለመሆኑ የፌደራል መንግስት የፕሮፓጋንዳ ግብአት እስኪሆኑ ድረስ ቸልታው ቅጥ አጣ፡፡ የሽግግሩ መንግስት ፕሬዚዳንት ከስብሰባ የተወሰነ ጊዜ ሸርፈው ሚድያ ላይ በመውጣት ርሃብ አደገኛ ደረጃ እንደደረሰና የፌደራል መንግስትም እርምጃ እንዲወስድ የጠየቁ ማግስት የፌደራል መንግስት ኮሚዩኒኬሽን ሃላፊ ለገሰ ቱሉ በትግራይ አመራሮች ላይ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ትችት አቀረቡ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ መንግስት ለሁለተኛ ጊዜ በህወሓት ላይ የተቀዳጀው የፕሮፓጋንዳ ድል ነው፤ የመጀመሪያው በትግራይ የተፈጸመውና ተዳፍኖ የቀረው የእርዳታ ስርቆት ነው፡- “ህዝብን ቀጣይነት ወዳለው የልማት ስራ ከማስገባት ይልቅ በግምገማ ስም ለወራት ተሰባስቦ የሚቀመጥ አመራር በምን ሞራል ነው ስለ ትግራይ ህዝብ ስቃይ መናገር የሚቻለው?”

## 11.3 የህውሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ውዝግቦች ውጤቶች

ከአውዳሚና ሚልዮን ህዝብ ያለቀበት ጦርነት በማንሰራራት ላይ ያለውን የትግራይ ህዝብ ችላ ብለው “አዳራሹ-ቤቴ” ያሉት የህወሓት አመራሮች በረዥሙ ስብሰባቸው የታዩት ክስተቶች፤ የተነገሩት ቃላት፤ የመቧደኑ ውስብስብነት፤ የሚሰጡት ጉጅሌያዊ አስተያየቶች፤ ምህረት የለሽ ትችቶችና ዘለፋዎች ነገ ተነገ ወዲያ አብረው ትግራይን ሊገነቡ የሚያስችላቸው ህብረትና የአላማ ጽናት ሊኖራቸው ይችል ይሆን ብሎ መጠየቅን ተገቢ ያደርገዋል፡፡ ስብሰባው ለይስሙላ ዝግ ስብሰባ ነው ቢባልም በስብሰባዎቹ የተደረገውና የተነገረው ሁሉ ሳይውል ሳይድር አገር ያወቀው ጸሃይ የሞቀው ይሆናል፡፡ አመራሮቹ የየራሳቸው ኔትዎርክና ሚድያም አላቸው እየተባለ ይወራል፡፡

ምስጢሮችንም እያሾለኩ የሚያቀብሉት ለነዚህ የግላቸው ወይንም የደጋፊዎቻቸው ሚድያዎች ነው የሚለው ውሃ የሚቋጥር መረጃ ነው፡፡ በትግርኛ ቋንቋ የሚሰሩትን ሚድያዎች አስተውሎ ለተከታተለ ከፕሮግራሞች ወይም ከቃለ መጠይቆች ወይም ከትንተናዎች ይዘት ሚድያዎቹ የአንዱ ወይም የሌላው ቡድን

አጋርነት እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡- ”ዘመነ መሳፍት በሶሻል ሚድያ”፡፡ መሪዎቹ የፈጠሩት ኔትዎርክ የኢኮኖሚ ጥቅም ለመጋራት እንጂ መቸም በርእዮተ አለም ላይ የተመሰረተ መቧደን ሊሆን አይችልም፡፡ ይህን ያህል የሚያራኩት የርእዮተ አለም ልዩነት በአንድ ፓርቲ ውስጥ የሚጠበቅ ባይሆነም ልማትን ለማረጋገጥ ይህ ይሻላል ያኛው መንገድ ይበልጣል መባባል ገንቢ እንጂ አፍራሽ አይሆንም፡፡ የጥቅም ኔትዎክ ግን በስልጣን መልቀቅና ሽግሽግ ፍትሃዊ ያልሆነ ሚና የሚጫወት የግለሰቦች ድምጽ አልባ መሳሪያ ነው፡፡ እነዚህ ኔትዎኮች በሶሻል ሚድያ ብቅ እያሉ ህዝቡን ግራ የሚያጋባ ውዥምብር ሲለቁበት ቆይተዋል፡፡ በነዚህ ኔትዎርኮች የነጋዴዎችና ሌሎች የውጭ እጆች ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡ ከስብሰባ መልስ ከነዚህ እጀ-ረዥም ገለሰቦች ጋር በሌላ ስፍራ ሌላ ጉባኤ! የነዚህ መደበኛ ያልሆኑ ጉባኤዎች ውሳኔዎችና ምክረ ሃሳቦች በማግስቱ ወደ መደበኛ ስብሰባዎች አጀንዳ ውስጥ ስለሚሰገሰጉ ስብሰባው መላቅጡ የጠፋ የባቢሎን ግንብ አምሳያ ሆኖ ይገኛል፡፡

ስብሰባው አንዳንዴ የስምንተኛው ሺ ንትርክ ይመስል ነበር፡- ወጣቶች አዛውንትን የሚጠሉበት፡፡ “ይበቃቸዋል ያረጁት ይሂዱ!” ከሚሉት የፖለቲካ ጥበብ ያልነካቸው አስተያየቶች ጀምሮ ጉጅሌዎችን ባላቸው የባለዲግሪዎች ብዛት ተገምግመው እንዲያልፉ ወይም እንዲራገፉ ሃሳብ እስከሚቀርብበት ድረስ ይሄድ ነበር፡፡ “የእከሌን ጉድ  ዘከዘከው፤ አሳት ለቀቀበት፤ ሰበረው፤ ዘረገፈው” የሚሉ ያራዳ ልጆች እንደነበሩም ይነገራል፡፡ የሽግግሩ መንግስት ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ ከህወሓቱ ስብሰባ ውጪ ህዝብን ሰብስበው ያነጋገሩባቸው አንድም ሁለትም አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ “አሸነፍናቸው፤ በተንናቸው፤ ስልክ እየደወሉ መጣንባችሁ ይላሉ፤ ማንን ታግለው ማንን እንዳሸነፉ አይታወቅም” ይላሉ ጌታቸው ረዳ የስብሰባውን ቅጥ ማጣት ፍንጭ ሲሰጡ፡፡

ግብግቡ በቡድኖች መካከልና የውስጦ-ቡድንም ሽኩቻ ስለነበረበት ሁሉም በሁሉም ላይ የሚተኩስ ይመሰል ነበር፡፡ ሆኖም ድፍርሱ እየጠለለ ሲመጣ ጉልህ የሆኑ አምባዎች ተለዩ፤ ግንባር ቀደሙ ኢላማ ጌታቸው ረዳና ከሱ ጎን የተሰለፉት አጋሮቹ ሲሆኑ “የሽግግር መንግስቱ በኛ እጅ መሆን አለበት” ባዮቹ የሚያቀርቧቸው የህዝብን ስሜት የሚነካኩ ሂሶች አእምሮን የሚያስጨንቁ ነበሩ፡- ለምሳሌ ያህል የጌታቸው ረዳ አቋም በምእራብ ትግራይ፤ ከአቢይ አህመድ ጋር ስላለው የቅርበት መጠን፤ ጮክ ተብሎ የማይነገር ነገር ግን ውስጥ

ለውስጥ የሚግም የአካባቢ ጉዳይ፡፡ ይህን አደገኛ አዝማሚያ ጌታቸው ረዳ "ቮቲንግ ፓተርን" የሚል ስያሜ ሰጥቶታል፡፡ የየት አካባቢ ሰዎች ናቸው ለማን ድምጽ እየሰጡ ያሉት? የሚለውን ጥያቄ ሻሽ አልብሶ መናገርን አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ከባቢያዊነት እንዳለ ምልክት አለ የሚለው ጌታቸው ረዳ "መካድ አይቻልም" በማለት አረጋግጧል፡፡ "ከከባቢያዊነት ነጻ የሆነ ግምገማ የለም" ብሎም ሃሳቡን አጠናክሮታል፡፡ "በኦንላየን ከውጭ ሆነው የሚቀሰቅሱ ትልልቅ የሚባሉ ሰዎች አሉ" ያለው ጌታቸው ረዳ "እርጅናቸውን እንዳያስታምሙ ለዚህና ለዛ ድጋፍ ቆመዋል ይባላል" ተብሎ በየደጃ ደጁ የሚወራውን ነገር እውነትነት ህይወት ዘርቶበታል፡፡

ነገሩ በጌታቸው ላይ መክረሩ ግልጽ የሆነው ከዚህ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ቀደም ብሎ የህወሓት ካድሬዎች ሌሊት ከያሉበት "ስንቃችሁን ይዛችሁ እንድትደርሱ" ተብለው በመቶዎች ወደ ዋና ከተማዋ የተመሙበት ተግባር ጌታቸው ረዳ በሱ ላይ የታቀደ የህወሓት መፈንቅለ ሽግግር መንግስት ነበር ብሎ መተርጎሙ ነበር፡፡ የሽግግሩ መንግስት ፕሬዚዳንት እንዲሆን የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ በሙሉ በሚባል ድምጽ መርጦ እንዲያጸድቅለት ለአቢይ አህመድ ልኮ የነበረው ዶር. ደብረጽዮንን ነበር፡፡ አቢይ አህመድ ደብረጽዮንን በጦርነት ጅማሪነት ወንጅሎ ሹመቱን አላጸድቅም በማለቱ በደብረጽዮንና በደጋፊዎቹ ዘንድ ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ ተፈጠሮ ነበር፡፡ ይህ ቅሬታ ከዛ ወዲህ ቀን በቀን እየጋለ እንጂ እየከሰመ አልሄደም፡፡ ህወሓት ሌላ ሰው መርጦ እንዲልክ በአቢይ አህመድ በታዘዘው መሰረት ሌላ ሰው ለመምረጥ የደብረጽዮን ያህል የሚያስማማ ሰው ጠፋ፡፡ ከደብረጽዮን በታች የነበረው የህውሓት አለም በኔትዎርክና በጎጅሌ የታነጸ መሆኑ የተጋለጠው በአቢይ አህመድ እምቢታ አጋላጭነት ነበር፡፡

ለሽግግር መንግስቱ እጩ ፕሬዚዳንት ዳግም ለመምረጥ የህወሓት ማእከልዊ ኮሚቴ ሲሰበሰብ ቢያንስ ሁለት እኩል አቅም ያላቸው ቡድኖች እንዳሉ መሰወር የማይቻል ሆነ፡፡ አንዱ ቡድን ጌታቸው ረዳን በእጩነት ሲያቀርብ ሌላኛው ደግሞ ታዋቂ ያልነበረውን ዶር. ፍስሃን አቀረበ፡፡ እዚህ ላይ ትግራይን ያክል ታላቅ ህዝብ የሚኖርበት ጥንታዊ ክልል ለመምራት የቀረበ ጥቆማ ነው ብሎ ለማመን የሚቸግር ነበር፡፡ እኩል ሊሆኑ ሲሉ በአንዲት ድምጽ ብቻ የተለዩት እጩዎች ህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ለውስጥ የሚፈሰው የድርጅቷን አጥንት ሊያሟማ የሚችለው አሲድ ምን እንደሆነ በግልጽ የታየበት ነበር፡-

በማእከላዊው ኮሚቴ የግምገማ ስብሰባዎች ጌታቸው ረዳን ወጥረው ከያዙት አካላት አንዱ የፓርቲዋ የቁጥጥር ኮሚሽን የሚባለው ነበር፡፡ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር በየሶሻልሚድያው እየቀረቡ ጌታቸው የተናገረውን እያነሱ ሲተቹ፡- “ጉዳዩን ወደ ጉባኤ እንውሰደው የሚለውን የኮሚሽኑን አቋም በጽኑ እየተቃወሙ ነው” ይላሉ፡፡ ጌታቸው ረዳ በበኩላቸው የማይጨውን ህዝባዊ ስብሰባ አጋጣሚ በመጠቀም በኮሚሽኑ ላይ የመልስ ምት ሰንዝረዋል፡፡ “ኮሚሽኑ የስራ ጊዜው አብቅቷል፤ ማንንም መጠየቅ የሚችልበት ህጋዊ ቁመና የለውም” በማለት፡፡ ጌታቸው ረዳ የሽግግሩን መንግስት ካቢኔ በሚመለከት የሚቀርብባቸውን ሂስ ሲያጣጥሉ “እኔ ጌታቸው ረዳ ስለሆንኩባችሁ ነው እንጂ ካቢኔውን እኔ አልሰየምኩትም፤ ደብረጺዮን ፕሬዚዳንት ቢሆን ኖሮም ያው ነበር” በማለት የትችቶቹን መሰረተቢስነትና ስውር ከባቢያዊነት በዘዴ ጸሃይ ላይ አስጥተዋቸዋል፡፡ ፊታቸውና አካላዊ ቋንቋቸው የሚያሳጣ ቢሆንም ጌታቸው ረዳ ነገሮችን ቀለል አድርገው “የምንቀጣውን ቀጣጥተን፤ እንቀጥላለን፤ ማእከላዊው ኮሚቴውም ይቅርታ ይጠይቃል” በማለት በማይሚገተው ተሰብሳቢ ፊት ትልቁን ጉዳይ ወደ መሬት አውርደው ጣሉት፡፡

የማእከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ ቀጠለ፡፡ ከግምገማ በኋላ በፓርቲው ሊቀመንበር በዶር. ደብረጽዮን ላይ ድምጽ ተሰጠ፡፡ ሊቀመንበሩ ከልጣናቸው ተሻሩ፡፡ ድምጽ አሰጣጡ ቀጠለ፤ አለም ገብረዋህድ ከድርጅቱ ጽሃፊነት ወረዱ፡፡ ቀጥሎ ተሰብሳቢው ድምጽ ሊሰጥ መላእከት እንኳ ወደማይደፍሩት አምባ ዘው አለ፡፡ ወይዘሮ ፈትለወርቅ (ሞንጆሪኖን) ከፓርቲው ም/ሊቀመንበርነት ለማንሳት ሲሞከር ለሽምግልና ወይም ለታዛቢነት ስብሰባው ላይ የታደሙት የትግራይ ሰራዊት ጀኔራሎች አንዱ ጣልቃ ገብቶ ስብሰባውን እንዳንደፋረሰው ተዘግቧል፡- “ድርጅቱን ልታፈርሱት ነወይ?” የሚል ጫጫታ ነገሰ፤ ስብሰባውም ፈረሰ፡፡ የስብሰባው “ፓወር ሃውስ” አዳራሹ ውስጥ እንዳልሆነ ፍንትው ብሎ ታየ፡፡ ድርጅቱ የሚፈርስ ከሆነ መፍረስ የነበረበት ደብረጺዮን ገበረሚካኤል ከሊቀመንበርነት ሲወገዱ ነበር፡፡ ብዙ ችግሮች ቢኖሩባቸውም በሳቸው ላይ ያለው የብዙሃኑ አመለካከት ለክፉ የሚሰጥ አይደለም፡፡

በዚህ አጋጣሚ ነበር የአምሳ አመቱ ጎልማሳ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ጨቅላነት የወረደው፡፡ “ድምጽ አሰጣጡ ከተቋረጠ የኛም ድምጽ ይቀልበስ” የሚል አቤቱታ ከዶር. ደብረጺዮን ሲቀርብ “ይህ የማይሆን ከሆነ ስብሰባ አልጠራም” በሚል ዛቻ

ታጅቦ ነበር፡፡ የፓርቲን ፖለቲካ በሽምግልና የሚባል የግጭት አፈታት ሜኑ ለመጀምሪያ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም በትግራይ የቀረበው፡፡ ይህ ሽምግልና የየራሱ በሆኑ ረዣዥም ክሮች የታሰረ ሆኖ ለበለጠ ንትርክ የሚያጋልጥ፤ ሁሉም የየራሱና የየኔትዎርኩ አጀንዳ ይዞ ለመግፋት የሚጥርበት ነበር፡፡ ታላላቅ የህዝብ ጉዳዮችን ዘግቶ ሲካሄድ የቆየው የህወሓት ስብሰባ "የፓርቲውን ሊቀመንበርነትና ጸሃፊነትን አንድ ላይ ለኔ አስረክቡኝ አለ" የተባለው እውነትነቱ ያልተረጋገጠው የጌታቸው ረዳ ጥያቄ ስብሰባው ውስጥ ሰፍኖ የሰነበትውን የእኔና ለኔነት መንፈስ ያንጸባረቀ ነው፡፡ በሽምግልና "አንተ ይህን ያዝ አንቺ ይህ ይበቃሻል" መባባል ፓርቲ ማለት የህዝብ አላማ መሆኑ ቀርቶ ግለሰቦች ለግል ጥቅም የሚገዳደሩበት ኩባንያ ወደ መሆን ወርዷል ማለት ነው፡፡

ይህ የተራዘመ ስብሰባ የህወሓትን ትክክለኛ ተፈጥሮ ያንጸባረቀ ብቻ ሳይሆን የትግራይ የፖለቲካ ባህል ለህዝብ ጉዳይ ቅድሚያ የማይሰጥ የራስ ወዳድነት እሴት የሰረጸበት እንደሆነ ያረጋገጠ ነበር፡፡ በቃላት ይፋ ሆኖ ባይነገርም የህዝብን ቅሬታ በሚመለከት የህወሓት ስብሰባ ያዘለው ስሜት እንዲህ መግለጽ ይቻላል፡- "ከስብሰባው የሚበልጥ ምንም የህዝብ ጉዳይ ስለሌለ በስብሰባ የውስጥ ጉዳያችንን እንስክንጨርስ ድረስ የተራብከውም እንደተራብክ፤ የተፈናቀልከውም እንደተፈናቀልክ መቆየት ግዴታህ ነው፤ ካኮረፍክም የይስሙላ ይቅርታ ጠይቀንህ እንደልማድህ ትመለሳለህ"፡፡ በዚህ መሃል ተደርጎ የማያውቅ ታሪካዊ ነገር ተፈጸመ፤ አለምንም አስደመመ፡፡ ይህ ከብራሰልስ/ቤልጂም የተሰማው ዜና ነበር፡ በህወሓት ሃላፊነት የጎደለው የተራዘመ ስብሰባና በትግሉና በትግሉ መጠናቀቅ ማግስት ሲፈጸም በነበረው የህወሓት አመራሮች የስነ ምግባር ጉድለት ትእግስታቸውን የጨረሱ የትግራይ ዳያስፖራ አባላት በአውሮፓ ህብረት ዋና ጽ/ቤት ፊት ለፊት በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል፡፡

ያሰሟቸው መፈክሮችና ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው፡- "ወንጀለኞች ወደ ፍርድ መቅረብ እንጂ ስልጣን አይገባቸውም፤ እርዳታ የሰረቁ ወደ ፍርድ ይቅረቡ፤ ዳያስፖራው ለትግሉ ድጋፍ ያዋጣውን ገንዘብ ለግላቸው ያዋሉ አመራሮች በፍጥነት ወደ ፍርድ ይቅረቡ፤ የሰራዊት ምግብና ብረታ ብረት የሰረቁ ለፍርድ ይቅረቡ፤ የውስጥና የውጪ ወንጀለኛ ልዩነት የላቸውም"፡፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠር ትሳታፊ የነበራቸው የፕሪቶሪያ ስምምነት እንዲተገበር የሚጠይቁ፤ የተፈናቀሉት ወደ ቀያቸው እንዲመለሱና "በሰላም ውስጥም ሆነን

እያለቅን ነው” የሚሉ መፈክሮች የሚያሰሙ ሰላማዊ ሰልፈኞች ሽረንና መቐለ ከተሞችን አጥለቅልቀዋል፡፡ ይህ እየሆነ የህወሓት ስብሰባ በማናለብኝነት እየተካሄደ ነበር፡፡ የስብሰባው አጀንዳ ረሃብና መፈናቀል ቢሆን ኖሮ ህዝብን የሚያስደስት እንጂ የሚያስከፋ ባልሆነ ነበር፡፡ የሽግግር መንግስቱ ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ ህዝብ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ያጋለጠው እውነታ ህዝብ በህወሓት ላይ የነበረውን የመጨረሻዋ የተስፋ እንጥፍጣፊ የተነነችበት ነበር፡- “ስብሰባው ላይ ስለተፈናቃዮችና ስለርሃብ አላነሳንም ልንገራችሁ እንግዲህ!”፡



ለልደታቸውና ለውሻቸው ትኩረት ሰጡ፤ ህዝብ ተራበ፤ ደርግ ገለበጣቸው



የኢሰፓን ፓርቲ ሲመሰርቱ ህዝቡ በረሃብ አለቀ፤ ህወሓት ገለበጣቸው



ህወሓት "ስብሰባው ወሳኝ ነው" አለ፤ ረሃቡስ? ለሱ "ይቅርታ እንጠይቃለን"

ጌታቸው ረዳን አላስቆም አላስቀምጥ ያሉትን የህወሓት የውስጥ ተቀናቃኞች በህዝብ ፊት ለማጋለጥ ያደረገው ነው ሊባል ቢችልም እውነቱን ማውጣቱ ግን ህዝብን ከ”ህወሓት-መሃይምነት” ለማላቀቅ ወሳኝ ግብአት ሆኗል፡፡ ይህ በህግ

የሚያስጠይቅ ወንጀል ነው! እንዲህ አይነት የንቀትና የማናለብኝነት ተግባር በኢትዮጵያ ታሪክ ሁለት መንግስታት የተገረሰሱበት ምክንያት ሆኖ አልፏል፤ ገርሳሹ የተገርሳሹን ጥፋት ሲደግም በተራው የተገረሰሰበት የኢትዮጵያ አሳዛኝ የፖለቲካ ታሪክ! አጼ ሃይለስላሴ የሰማንያኛው አመት ልደት በአላቸውን ሲያጣጥሙ ከአንድ አመት በላይ ሆናቸው፡፡ በዚህ ወቅት በወሎና በትግራይ ድርቅ ያስከተለው ረሃብ ህዝብ እየፈጀ ነበር፡፡ ለንጉሱ ጭንቀት ሆኖባቸው የነበረው ሚጢጢዋ ውሻቸው የትኛውን ምርጥ ምግብ እንደምትመገብ ነበረ፡፡ ያኔ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የነበሩትና ህወሓትን የመሰረቱት ወጣቶች "ዳቦ ለተራበ" ብለው ከፖሊስ ጋር ግብግብ ገጥመዋል፡፡ ያኔ ለምን? አሁን ለምን?

ወታደራዊው መንግስት የሺዎች አመታት ዘውዳዊ ስርአትን ገርስሶ ለስልጣን የበቃው በታክሲዎች አመጽ፤ በመምህራን ሰልፍ ሳይሆን የዮናታን ዲምቢልቢን የወሎ ረሃብ ሰቆቃ ለህዝብ በቴሌቪዥን ካሰራጨ በኋላ ያስከተለውን የህዝብ ቁጣን ተጠቅሞ ነው፡፡ ወታደራዊው መንግስት የውትድርና ፖለቲካውን አውልቆ ጥሎ የተረጋጋ የሲቪል ሶሻሊስት አምባገነንት ምኞቱን ለማሳካት የወጠነው "የሰራተኛ ፓርቲ" ምስረታ ጉባኤ ማካሄዱን ተያያዘው፡፡ ይህ በንዲህ እያለ የአዲስ አበባ ህዝብ ሳይቀር የረሃብን አለንጋ የቀመሰበት ታላቅ ድርቅና ርሃብ በኢትዮጵያ ላይ ወርዶ ነበር፡- "በርታ ዘመዴ፤ ተወዷል ጤፍና ስንዴ፤ ሩዝህን ልመድ በዘዴ"፡፡ ሁለት ሚልዮን ህዝብ ፈጀ የተባለው የ1977 ዓ.ም ድርቅና ረሃብ በሚመለከት ደርግ በአጼ ሃይለስላሴ ላይ የሰራው ፊልም በሱም ላይ ተሰራበት፡፡ ህዝብ በረሃብ እያለቀ ለፓርቲ ምስረታ ቅድሚያ የሚሰጥ ጨካኝ መንግስት ተባለ! ደርግ በረሃብ እልቂት ፖለቲካ ምክንያት የተነቃነቀ ጥርስ ሆኖ ቆየና በህወሓት "ጉጠት" ተነቀለ፡፡

በትጥቅ ትግል ላይ እያለች ህወሓት የ1977 ዓ.ም ድርቅና ረሃብ በትግራይ ህዝብ ላይ ያስከተለው መከራ ምን እንደነበር ሌላ ነጋሪ አያስፈልጋትም፡፡ በንድፈ-ሃሳብ ለድሃው የቆምኩኝ ነኝ እያለ በተግባር ግን ርህራሄ የሚባል ነገር የማይዳስሰው ሶሻሊዝም ደርግ በከተማ ኢሰፓን ሲመሰርት ህወሓት ደግሞ በድርቅ ማእበል ውስጥ ተነክራ ማሌሊትን ስታዋልድ ነበር፡፡ ህወሓት በሰሞነኛው የፓርቲ ጥገና ወይም ብወዛ ስብሰባ የተረጋገጠው ነገር ቢኖር ፖለቲካን ከህዝብ ጉዳይ ማስቀደም ለድርጅቱ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ነው፡

የህወሓት የቁጥጥር ኮሚሽን ሰብሳቢ ይህን የረሃብና ስብሰባ ጉዳይ በቁጭትና በሃዘኔታ ስሜት እንደማየት ቴክኒካዊ ከሆነ አቅጣጫ ተመልክተው ሲተነትኑ "የረሃቡና የተፈናቃዩ ጉዳይ የሚመለከተው የሽግግሩን መንግስት እንጂ ፓርቲውን አይደለም፡፡ ጌታቸው ረዳ እንደመንግስት መሪ ጉዳዩን ስብሰባ ላይ ካላነሳው ማን እንዲያነሳው ይጠበቃል?" ይላል የቁጥጥር ኮሚሽኑ አለቃ፡፡ ይቀጥልና "ለስብሰባው የመነሻ ጽሁፎችን ያቀረቡት ጌታቸው ረዳና የፓርቲው ጽ/ቤት ሃላፊ አለም ገብረዋህድ ነበሩ፤ በዚህ መድረክ ላይ የድርቅና የተፈናቃይ ጉዳይ አለም ገብረዋህድ አለማቅረቡ የስራ ድርሻው ባለመሆኑ ነው" የሚል የጎመዘዘ ፍልስፍና ቢጤ ሲናገሩ ጌታቸው ረዳን የሚያስወቅሱበት ጥሩ አጋጣሚ ማግኘታቸውን አዩ እንጂ የጉዳዩን አደገኛነት ልብ ሊሉት አልፈለጉም፡፡

ዋናው ነገር ተቀናቃኝን ማሸነፍ ነበር፡፡ "ዘ ኤንድ ጃስቲፋይስ ዘ ሚንስ" አለ ኒኮሎ ማኪያቬሊ፡፡ "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" እንደ ማለት ነው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ትንሽ ቀደም ብሎ ጌታቸው ረዳ ከተናገረው የተጠቀሰው የሽግግሩ መንግስት የህወሓት መሆኑን በአጽንኦት ያስገነዘበበት ቃሉ ነው፡፡ ስለዚህ የድርቁንና የተፈናቃዮች ጉዳይ በህወሓት ስብሰባ ላይ ያልተነሳበት አስገራሚና አሳዛኝ ክስተት "ፓርቲ ሳይሆን መንግስት ማቅረብ ነበረበት" ብሎ መከራከር ጉንጭ አልፋ ነው፤ ፓርቲና መንግስት በቅጡ ባልተለዩበት ትግራይ!

ዶር. ድብረጽዮን በቅርቡ በነበራቸው ቃለ መጠይቅ አላቸው ሲባል የነበረው የህዝብ ተቆርቋሪነትን የሻሩ መልሶች ሲሰጡ ተስተውለዋል፡፡ የትግራይ ግዛቶች፤ የጦር አካል ጉዳተኞች፤ የተፈናቃዮች፤ ወዘተ ጉዳዮች ላይ ሲጠየቁ "የሽግግሩን መንግስት ለሚመለከት ጥያቄ መልስ አልሰጥም" ማለታቸው በአንክሮ የሚታወስ ነው፡፡ በፊት የተሰጠው ድምጽ ትዝብት በሚያተርፍ አስገራሚ ሁኔታ ተሸሮ፤ የዶር. ደብረጺዮን የህወሓት ሊቀመንበርነት ተረጋገጠ፤ ጌታቸው ረዳ የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር ሆነው፤ የህወሓት ስብሰባ ከተጥናቀቀ በኋላ ግን ደብረጺዮን ገብረሚካኤል የፕሪቶሪያ ስምምነት የሚመለከታቸው ሆኖ ተገኘና "ስምምነቱ ተግባራዊ ይሁን" የሚሉ ደብዳቤዎችን በተኑ፡፡ አሁን ደርሶ ጉዳዩ የሽግግር መንግስት ሳይሆን የፓርቲ ጉዳይ የሆነበት ተአምር የተፈጠረው እንዴት ነው? ሁሉም ነገር ወደ ስልጣን ግንባር! ህዝብ በጦርነቱ አእምሮው ተጎድቷል፤ ይባስ ብሎ ከጦርነቱ በኋላ ህወሓት በያዘችው ህዝቡን የሚያስከፋ አካሄድ እያየ ድርጅቷን ሊያምንና ሊከተል የሚችልበት በቂ ምክንያት እያጣ ነው፡፡

ህወሓት እንደዝሆን ግዝፈትና ጉልበት እንጂ ስልት የሚቸግራት የፖለቲካ ድርጅት ናት፡፡ ጠላቶቿ ከህወሓት ጋር ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ይልቅ እንደ አዳኝ ነብር ስስ ብልቷን እየመረጡ ማዳከምን መርጠዋል፡፡ ጠላቶቿ ከህዝብ ጋር የፈጠረችውን ክፍተት ለማስፋት ስልታዊ ዘመቻ አጧጡፈዋል፡፡ የኢትዮጵያ ፓርላማ ህወሓትን ከሽብርተኛ ዝርዝር ባስወገደ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርጫ ቦርድ "ህወሓት የሚባል የፖለቲካ ድርጅት በመዝገቡ ውስጥ እንደሌለ" አስታወቀ፡፡ ይህ መግለጫ ህወሓት ረዥሙን ስብሰባዋን ጨረስኩ ብላ መግለጫ ባወጣች ማግስትም በአጽንኦት ተደግሟል፡፡ ምርጫ ቦርድ ህወሓትን የያዘበት ወጥመድ የማያላውስ ነው፤ ህወሓት ግን ይህን በቅጡ የተረዳች አትመስለም፡፡ ህወሓት እንደ አዲስ ፓርቲ እንድትመዘገብ የቀረበላትን የምርጫ ቦርድ ጥሪ "እንደ ህጻን እዲስ ነን ብለን አንመዘገብም" በማለት የድርጅቷ ሊቀመንበር የፓርቲያቸውን አንጋፋነት ማስረገጥ ሞክረዋል፡፡

አቢይ አህመድ በዚች የድክመት ቀዳዳ ገብተው ህወሓትን በውለታ መዳፋቸው ውስጥ ከተዋል፤ "ህወሓት እውቅናዋ ይመለስላት" ብለው በማዘዝ፡፡ ህወሓት ብልጽግና ፓርቲን እንደትቀላቀል ብትጠየቅ አሻፈረኝ የምትልበት አቅም ይኖራት ይሆን? "ከዚህ ሁሉ ውድመት፤ ተመልሶ መጣ የቅድመ ጦርነት"፡፡ ህወሓት በአይነቱ አዲስ የሆነ ፈተና በመጣባት ቁጥር "በስቴንስል የቀረጸችውን" "የመስመር" ጽናቷን፤ እድሜዋን፤ ህዝባዊነቷን፤ መስዋእትነቷን፤ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያበረከተችውን እየዘረዘረች መግለጫ እየደጋገመች ማውጣቷ የተለመደ ሆኗል፡፡ "ፈጣን ነው ባቡሩ፤ ቆራጥ ያልሆናችሁ እንዳትሳፈሩ" የሚል ለለውጥ ተቀባይነት ምክር የሚለግስ ዘፈን ነበር፤ በደርግ ጊዜ! ይህ መንግስት እስካለ ድረስ ምርጫ ቦርድ ህግን በእጁ ጨብጦ የወሰነ ሲሆን በተቃራኒው በህወሓት እጅ ያለው ህግ ሳይሆን የአንጋፋነት የኩራትና የአልበገር ባይነት ስሜት ነው፡፡

በከፍተኛ የህዝብ መስዋእትነትና የአገር ውድመት ከሞት የተረፈቺው ህወሓት እንደሰጎን ራሷን ከመቅበር ይልቅ ያፈጠጡ ሃቆችን ተቀብላ በጎርፉ ወደ ላይ ሳይሆን ወደታች መዋኘት ለህልውናዋ አዋጪ ምርጫ ነው፡፡ የፕሪቶሪያ ውል ፈራሚው ፌደራል መንግስት ህወሓትን ራሷ በመረጠቻቸው ካርዶች እያጫወታት ነው፡፡ "ስምምነቱን ማስፈጸም የፌድራል መንግስቱ ሃላፊነት ነው" እያሉ ትራሳቸውን ከፍ አድርገው ተኝተው የቆዩት የህወሓት አመራሮች በገዛ እጃቸው ስምምነቱን ማጓተት ለሚፈልገው የፌደራል መንግስት ለጸረ-ህወሓት

ፕሮፓጋንዳው ግብአት ሲያቀብሉት ቆይተዋል፡፡ አቢይ አህመድ የህወሓትን በስብሰባ መጠመድ እንደ እድል ተጠቅሞ "ህወሓት ከትግበራ ወደ ስብሰባ አድልቶ አንድ እጅ ብቻ ሆኛለሁ" በማለት ስምምነቱን ላለመተግበሩ ሰበብ አድርጎ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ ቢያማርር ተጠያቂው ማነው? ህወሓት ወይስ አቢይ አህመድ?

ህወሓት በስድሳ ቀናት ስብሰባዋ ስድሳ ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ሊከናወን የሚችለውን "ሹም ሽር'" አካሂዳ ስትጨርስ የተራዘመና ሁሉን አቀፍ መግለጫ አወጣች፡፡ በነዚህ ሳምንታት ስብሰባዎች ህወሓትን የቀናት ነገር ቢኖር የሊቀመንበሯን ስልጣን ማጽናት፤ የሽግግሩ መንግስት ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳን እሴት በማይጨምርለት የታዛዥነት ቦታ ላይ መመደብ፤ ለጽህፈት ቤቱ ሃላፊነት ወልደማርያምን በገብረማሪያም መተካት ነበር፡፡ ምስል-አልባ መሆናቸውና በስለላ ጥበባቸውም ስማቸው አሜሪካ ድረስ የናኘውን ጌታቸው አሰፋን ከስራ አስፈጽሚ አስወግዶ ተራ አባል ማድረጉም ሌላው የስብሰባው "ስኬት" ነበረ፡፡ በአካሄዱ ሳይስማሙ ቀርተው ከስብሰባው ራስቸውን እንዳገለሉ ከተነገረላቸው ከእኒህ የቀድሞ የኢትዮጵያ የደህንነት መ/ቤት ሃላፊ ሌላ ምክንያቱ ባልተገለጸ ከህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ራሳቸውን ያገለሉ የፌደራል መንግስት ሹመኛም አሉ፡፡ በህወሓት መግለጫ መሰረት የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ "ተስፋን በሚሰንቅ ሁኔታ ተፈጽሟል"፡፡ ተስፋ የሚሰንቀው ማን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንም በስብሰባው የታየው መካረር፤ የውጭ ጣልቃ ገብነትና የውስጥ መቧደን ለድርጅቷ የዘላቂነት ተስፋን የሚያሰንቅ ሳይሆን ፈተናን የሚጋርጥ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ችግርን በግልጽ አውጥቶ እንደመጋፈጥና በአጥፊዎች ላይ የማያዳግም እርምጃዎችን ወስዶ ህዝባዊ አላማን እንደማስፈጸም ህዝብን በእጅጉ የጎዱ እኩይ ተግባራት መፈጸማቸው በግምገማዎች ከተጋለጠ በኋላ የህግ የበላይነትን በሂስና ግለሂስ ትክቶ "በመቻቻል" መቀጠል የተመረጠው ሁሉም ከሳሽ ሁሉም ተከሳሽ በመሆኑ ቀጪውና ተቀጪው ልዩነት ስላለነበራቸው ይመስላል፡፡ ነዳጅ ደብቀው የመከላከል ውጊያዎችን አደጋ ላይ ጣሉ፤ የሚልዮኖች ወርቅና ብር ወደ ውጭ አሸሹ ተብለው ስማቸው ማህበራዊ ሚድያውን አጨናንቆ የከረመው የፈትለውርቅ ገብረ እግዚአብሄር ስም ከድርጅቱ ምክትልነት በእጅጉ የተሻለ የጽ/ቤት ሃላፊነት ቦታ ከተሰጣቸው ውንጀላው መሰረተ ቢስ ነበር ወይም

ግለሰቧ አይነኬ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ያስደርሳል፡፡ ባለፈው አመት ሱዳን የሚታተም አንድ የኦንላይን መጽሄት ተጥቅሶ የተናፈሰ ዜና በወቅቱ "የጠላቶች በታኝ ሴራ ነው" በሚል ችላ ተብሎ ነበር፡፡ ይህ በህወሓት ከፍተኛ አመራር ውስጥ ለነበረው የስልጣን ሽኩቻ ፍንጭ የሰጠ ሪፖርት እንዲህ ይላል፡- ፈትለወርቅ ደብረጽዮንን "ራስህ በራስህ ከስልጣንህ ካልወረድክ 'ህዝብ' በኮላታህ ይዞ ያወርዳሃል"፡፡ ባለፈው ስብሰባ ደብረጽዮን በድምጽ ከህወሓት መሪነቱ ሲነሳ ተቃውሞ አልነበረም፡፡ ስብሰባው የፈረሰው በተመሳሳይ ሁኔታ በፈትለውርቅ ገብረ እግዚአብሄር ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወሰድ ሲል ነበር፡፡

የህወሓት መግለጫ ይቀጥልና "ረዥም ጊዜ ለመፍጀቱ ይቅርታ እንጠይቃለን እንጂ ስብሰባውማ መደረጉ የግድ ነበር" ይላል፡፡ ሊቀመንበርና ጸሃፊን ለመቀየር ወይም ለማጽናት ስብሰባ ከረሃብና ከተፈናቃዮችን ጉዳይ በልጦ ቅድሚያ የሚሰጥበት የትኛው ማህበራዊ ህግ ወይም መርህ ነው፤ እብሪት ካልሆነ በስተቀር? "ከዛሬ ጅምሮ የህዝባችንን ችግር ለማቃለል እንሰራለን" ይላል ሌላው የመግለጫው ይዘት፡፡ የዚህ መግለጫ እንደምታ ለትግራይ ህዝብ ችግር የመፍትሄ ቁልፉ የተገኘው ከዚህ ስብሰባ እንደሆነ ነው፡፡ በተቃራኒው በስብሰባው ሂደት የነበረው ቱማታ የመፍትሄ ቁልፍ ጨርሶ የመጥፋቱን እድል ከፍ ያደርጋል እንጂ የአርኪሜዴስ "ዩሬካ!"ን አያስገኝም፡፡ ይህ መግለጫ አልፎ አልፎ ከሚወረውራቸው አከራካሪ ሃይለ ቃላት ውጪ ሙሉ በሙሉ የህወሓት ስኬቶችን በማሞገስ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ከህወሓት በስተቀር ሌላ የፖለቲካ "አምላክ" እንዳያመልክ ተደርጎ የተሳለው መግለጫ ህዝቡ የኦሊጋርኪ እንጂ የአሳታፊ ዴሞክራሲን ጭላንጭል እንዳያይ አድርጓል፡፡ ትግራይ የሚገባት የብዝሃ ፓርቲ ስርአትን በአንዲት ቃል እንኳ የማያነሳው መግለጫ በጽኑ የሚጠበቅበትን የዳግመ-ህንጸት ስትራተጂ ላይ እንኳ ትንፍሽ አላለም፡፡

ለትግራይ ህዝብ የወደፊት እድሉ መቃናት ቁልፍ ጉዳዮች የሆኑት አሳታፊ ዴሞክራሲ፤ የመልሶ ግንባታና የዘላቂ ልማት ስትራተጂዎች አካታች የሆነ የፖለቲካ ስርአት የሚያስፈልጋቸው እንጂ ትግራይ የህወሓት የፖለቲካ ርስት መሆንን የሚያስተናግዱ አይደሉም፡፡ ገንቢ ትችትን ከስም ማጠልሸት ለይቶ ማየት የሚሳናት ህወሓት እርምትን የምትሸከምበት ጠንከር ያለ ጫንቃ አላዳበረችም፡፡ በመግለጫው ወደ ህወሓት አመራሮችና አባላት ያቀናው መልእክት "የህወሓት ስም ማጠልሸትን ጠንክረው እንዲታገሉ" የሚያሳስብ ነው፤

ለትግራይ ዳያስፖራ በመግለጫው የተላለፈ "ከግራ ቀኝ የሚመጣውን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ" እንዲመክቱላት አደራ ያለችበት ቃልም አለ፡፡ ህወሓት ለፈጸመቻቸው ጥፋቶች ከተጠያቂነት ለማምለጥ አቶ መለስ ዜናዊን ጠቅሳ "ትግል ሲኖር ስህተትም ጥፋትም ይኖራል፤ መላእክት አይደለንም" የሚሉ በሃይማኖት እንጂ በፖለቲካ ቦታ የሌላቸው የንስሃ ቃላት ደርደራለች፡፡

"የውጪም የውስጥም ጠላት አንድ ነው" ያሉትን የብራሰልስ ተጋሩ ስልፈኞች መፈክር ወስደን የህወሓት መግለጫ ለዳያስፖራ ተጋሩ ያቀረበችውን ጥብቅ ማሳሰቢያ እንይ፡፡ "በትግራይ ህዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙት አለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ማድረግ የዳያስፖራው ግንባር ቀደም የትግል አላማ ነው" በሚል መግለጫው በአጽንኦት ያስቀመጠው ጉዳይ "የውስጥ ገዳዮችስ የትኛው ዳያስፖራ ለፍርድ ያቅርባቸው?" ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ የህዝብ እርዳታ መስረቅና ረሃብንና የተፈናቃዮች ስቆቃን ችላ ማለት መግደል ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? የደቡብና የምእራብ ትግራይ ተፈናቃዮች በህወሓት ራስ ወዳድነትና እግር መጎተት የተነሳ ተስፋቸው ስለተሟጠጠ፤ ቢሰለፉም፤ መፈክር ይዘው ቢጮሁም ሰሚ በማጣታቸው "በየመጠለያ ድንኳን ሆነን በረሃብ ከምናልቅ እየተዋጋን ወደ ቀያችን ለመግባት በምናደርገው ሙከራ ብንሞት ይሻለናል" የሚል ህወሓትን ሊያሳፍርና ሊያሸማቅቅ የሚገባው ሃሳብ ያቀርባሉ፡፡

ለትግራይ ህዝብ ህወሓት "ነጭ ዝሆን" ሆናበታለች፤ የሷን ህልውና ለመጠበቅ የሚከፍለው ዋጋ እጅግ ከባድ ሆኗል፡፡ ትልቁ ችግር ህወሓት የሚከፈልላትን ዋጋ እንደ መብት መቁጠሯ ነው፦ "እኛ መኖርና መክበር መብታችን ነው፤ ህዝቡ ደግሞ ለኛ ሲል መሞትና መደህየት ግዴታው ነው"፡፡ ህወሓት በህዝብ ከፍተኛ ጉዳት ከመጥፋት ብትተርፍም ከጦርነቱ በፊት ከነበረው ክብሯና ተፈሪነቷ ወርዳ በፌደራል መንግስት የምህረት መዳፍ ውስጥ ወድቃለች፡፡ ህግ የግለሰብ መሪዎች ስሜት በሆነበት አገር የፕሪቶሪያ ስምምነት ፊርማ ለህወሓት የድርጊት ነጻነት ያስገኘላት ዋስትናዋ አይደለም፡፡ የህወሓት አመራሮችም ሆኑ የትግራይ ሰራዊት አዛዦች በፌደራል መንግስት በጎ ፈቃድ በሰላም የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ ዳግም አቅም መፈታተንም ከባድ ዋጋን ያስከፍላል፡፡

የሰራዊቱ አባላት ሆኑ የትግራይ ህዝብ በህወሓት የድህረ-ጦርነት ድርጊቶች ስለተከፉ፤ በጦርነቱ ጊዜም ቢሆን ወደ ጦርነት መግባቱ የሚያስቆጭባቸው

አስከፊ ድርጊቶች ሲፈጸሙ በመቆየታቸው ዳግም “መኸተ” የሚኖርበት እድል ያለ አይመስልም፡፡ በፕሪቶሪያ ስምምነት መሰረት የትግራይ ሰራዊት የሚበተን በመሆኑ ህወሓት ወታደራዊ ክንድ የሌላት እንደማንኛውም ሲቪል የፖለቲካ ድርጅት ትሆናለች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የትግራይን ህዝብ አጀንዳ በፌደራል መንግስት ላይ የምትጭንበት አቅም የላትም፤ አይኖራትም፡፡ አቅም የላትም ብቻ ሳይሆን ፍላጎትም የላትም፤ ለምን ቢባል በራሷ ላይ የፌደራል መንግስት ቅሬታን መቀሰቀስ ስለማትፈልግ፡፡ እዚህ ላይ ነው በህዝብ ላይ ለተፈጽመው ወንጀል ተጠያቂነት፤ የትግራይ ግዛት አንድነትና የተፈናቃዮች መመለስ የሚሉት ፌደራል መንግስትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማስፈጸም አቀበት የሆነባት፡፡ ህወሓት የገባችበት አጣብቂኝ “የህዝብን ጥቅም ገብሬ ራሴን ላድን? ወይስ የራሴን ደህንነት ገብሬ ህዝብን ላድን?” ፌደራል መንግስት ህወሓትን ቅርቃር ውስጥ አስገብቶ በራሷ ጊዜ እንደምትከስም ተስፋ በማደረግ ትግራይ ውስጥ ያሻውን አስተዳደር ሊያሰፍንበት በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት የትግራይ ብልጽግናንና የትግራይ ልዩ ልዩ ዞኖችችን እንወክላለን የሚሉ አዳዲስ ፖለቲካ ፓርቲዎችን አሰልፎ በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡

ህወሓት ከፌደራል መንግስት ጋር ያላት የሃይል ሚዛን ወደራሷ እንዲያዘነብልና አቅሟን አፈርጥማም ጉዳዮቿን መፈጸምና ማስፈጸም እንድትችል፤ ለህልውናዋም ቢሆን ዋስትና ለማግኘት ስትል ወደ ኢሪትርያ አቅጣጫ ማማተሯ አልቀረም፡፡ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ መጠናቀቅን ተከትሎ የወጣው የህወሓት መግለጫ የኤሪትርያ ህዝብ ከትግራይ ጋር ሰላም እንዲፈጥር የሚማጸን ነው፡- “ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ”፡፡ ህዝቡም ባይሆን የኤሪትርያ የፖለቲካ ልሂቃን የህወሓትን ተማጽኖ የሚመለከቱት እንደ ጥንካሬ ሳይሆን እንደ ድክመት ምልክት ነው፡፡ ለኤሪትርያ ከህወሓት የ‘እንታረቅ” ተማጽኖ የቀረበው ከአምስት ጊዜ በላይ ነው፡፡ በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪካ ላላቸው የበላይነት ምኞት እንቅፋት ሆናባቸው የኖረችው ህወሓትን ለማጥፋት የዘመቱት ኤሪትርያውያን በፕሪቶሪያ ስምምነት “እቅዳችን እንዲከሽፍ ተደረገ” ብለው ከተቆጩ በኋላ በመጠባበቅ ላይ ያሉት የፊቱንና “በሚገባ ሳንጠቅምበት ቀረን” ብለው የተቆጩበት ህወሓትንና ትግራይን የማጥፋት እድል መልሶ ለማግኘት ነው፡፡

ህወሓት በትግራይ ህዝብ ስም በዳይዋን ኤሪትርያን እርቅ እንዲደረግ በተዳጋጋሚ ስትለምን ኢሪትርያ ጆሮ ዳባ ብላ ቆይታለች፡፡ ይህ የኢሪትርያን

ንቀት ከማንጸባረቅ አልፎ የህወሓትን ውስጣዊ አላማ የመጠራጠር ስሜትም ይኖርበታል፡፡ ጥር 22/2016 በተለቀቀው የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ መግለጫ የኤሪትርያ ዳያስፖራ የኤሪትርያ ሰራዊት ከትግራይ ለቆ እንዲወጣ ትግል እንዲያደርጉ ጠይቋል፡፡ የኤሪትርያ ዳያስፖራ ቁጥራቸው ብዙ ነው የማይባል ለትግራይ የሚያዝኑና እርዳታም የሚለግሱ እንዳሉ አይካድም፡፡ አብዛኛው ውጭ ኗሪ ኤሪትርያዊ ግን የህግደፍ ደጋፊ እንጂ ተቃዋሚ አይደለም፡፡ ተማጽኖው የህዝብን ክብር ከመግሰሱ ባሻገር የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለም፡፡ ይህ በንዲህ እያለ ከሶስት ቀን በኋላ ጥር 25/2016 የኤሪትርያ ሰራዊት በትግራይ ሰሜናዊ ክፍል ውስጥ በህዝብ ላይ ግፍ እየፈጸመ መሆኑን አሶሴትድ ፕሬስ ዘግቧል፡፡ እርቅ ቢኖርም ያለክፍያ አይመጣም፤ ህወሓት ያንሁሉ በህዝብ ላይ የደረሰው ግፍ ምን ውስጥ ወሽቃ ነው ከህግደፍ ጋር ጠረጴዛ ዙሪያ የምትቀመጠው? ህግደፍን ወንጀለኛ እያሉ በእርቅ መተቃቀፍ የሚታሰብ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለፌደራል መንግስቱ እንደተደረገለት ለህግደፍም የዘር ማጥፋቱን ክስ የቱርክና የአርመንን ታሪክ እየጠቀሱ ለመቶ አመት ትውልድ ማስተላለፍ ነው?!

ህወሓት የገባችበት ሌላው አጣብቂኝ፡- ኤሪትርያ ትግራይን የምትፈልጋት ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የምትረዳት ከሆነ፤ ኢትዮጵያም ትግራይን የምትፈልጋት ኤሪትርያን ለመቆጣጣር የምትተባበር ከሆነ ነው፡፡ ከዚህ አጣብቂኝ መውጣት የሚቻለው ትግራይ በረዥም ይሁን በአጭር ጊዜ እይታ የሚያዋጣት የትኛው ነው ለሚለው ጥያቄ የማያወላውል መልስ ስትሰጥ ነው፡፡ ትግራይ ኤሪትሪያንና ኢትዮጵያን እያጣቀሰች በሰላምና በልማት መኖር አትችልም፡፡ ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ባላዎች ላይ አይወጣም፤ ውጤቱ መሃል ለመሃል መተርተር ነው፡፡ ትግራይ ወደ ኤሪትርያ ብትወግን የኢትዮጵያን የባሰ ጠላትነት አፍርታ ከኤሪትርያም እንደ እኩያ ተቀባይነት ሳታገኝ “ሁለት ያጣ ጎመን” ትሆናለች፡፡ ቀድሞውም ቢሆን የትግራይን ጦርነት የጋበዘው አውዳሚ ስህተት የትግራይ መሪዎች ኢትዮጵያን እንደበሶ ጨብጠው የኤሪትርያ ተቆርቋሪና መከታ በመሆናቸው ነበር፡፡ ለትግራይ ኤሪትርያ ማለት በአካልም በመንፈስም ባእድ የሆነችባት የአኹሱም ታሪክ ትዝታና ናፍቆት ብቻ ናት፤ ኢትዮጵያ ደግሞ የእንጀራ እናት መራራ እውነታ፡፡ ምርጫው ሻርኮች የሚርመሰመሱበት ጥልቅ ባህር ወይም እሳት የሚንቀለቀልበት ገሃነም፡፡ ሶስተኛው ምርጫ ነጻ መንግስት ምስረታ ሲሆን ጥቅጥቅ ወዳለ ደን ውስጥ ገብቶ ድራሽ እንደመጥፋት ነው፡፡

## 11.4 የትግራይ የድህረ-ጦርነት ማህበራዊ እውነታዎች

ጦርነት ሆነ ድህረ-ጦርነት የሚያስደስቱና የሚያኮሩ በአንጻሩ ደግሞ የሚያሳፍሩና የሚያስከፉ ማህበራዊ ክስተቶች የሚታዩበት ነው፡፡ የትግራይ ጦርነት የቆመ ሳይሆን በኤሌክትሮኒክስ ቋንቋ “ሚዩት” የተደረገ ነው፤ ጆሮን ከሚበጥስ የመሳሪያ ኳኳታ ሞት ሰሚ ወዳጣበት አስፈሪ ጸጥታ፡፡ ምሽግ ለምሽግ እየተያዩ ከመታኮስ  መስመር ወዳልለየ ሰላማዊ ትርምስ፡፡  የግዙፉ የትግራይ ጦርነት ተኩስ ቆሟል፡፡ ይህ የተኩስ ማቆም ስምምነት በትግራይ ምን መልክ ይዟል? ውጊያ እንዳቆመበት ሌላው አለም ትግራይ በአንድ እግሯ ቆማለች?  እንኳንና ግዙፍና በአይነቱ ልዩ የነበረው የትግራይ ጦርነት ይቅርና የሰፈር ጥሎችም ቢሆኑ ለማረጋጋትና ወደ ነበረው ለመመለስ እጅግ ፈታኝ ነው፡፡ የመሪዎቹ አስተዋይነትና ሩቅ አሳቢነት በቂ ባይሆንም በትግራይ ህዝብ ትእግስትና ሰላም ወዳድነት በሌሎች አካባቢዎች የግጭት ማግስቶች የታየው አይነት ሰርአት አልበኝነት አልተከሰተም፡፡ ይህ የህዝብ ታላቅነት ለአለም መልካም ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ ትግራይ ውስጥ ያለው ሰላም እጅግ አስደናቂ ነው፡፡

ሆኖም የትግራይ ህዝብ እያረረ የሚስቅ የባህር ማሽላ መሆኑ በአንክሮ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡- “ጽጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል”፡፡ ህዝቡ ስሜቱን በይፋ አይናገርም፡፡ እንዲናገር የሚያበረታታ የፖለቲካ ባህል የለም፤ ይህ አይነቱ የፖለቲካ ባህል እንዲዳብር የሚፈልግ የፖለቲካ አካልም የለም፡፡ የፖለቲካ መሃይምነት በሰፈነበት ሁኔታ ህዝብን መምራት ለአቅመ ቢስ መሪዎች የተመቸ ነው፡፡ በአመራሩ የተፈለገው አይነት ያበጠ ማስተንፈሻ ንግግር በየስብሰባው ምናልባትም በተመረጡ ግለሰቦች ይደሰኮራል፤ ስብሰባው ሲጠናቀቅ ይረሳል፡፡ የራስ አስተዳደር ከአሃዳዊ አስተዳደር ተመራጭ ሆኖ ከፍተኛ መስዋእትነት ያስከተለ ትግል የተካሄደበት ክኋሮው የበቀሉትን “የራሴ” የሚላቸው መሪዎች በነጻነት እንዲቆጣጠርና መስመር እንዲያስይዝ ነበር፡፡

ከሌላ ህበረተሰብ የፈለቀ የአካባቢውን ወግና ስርአት የማያውቅ አመራር ምንም ደግነትና የህዝብ ፍቅር ቢኖረው በአግባቡ ማስተዳደር ያስቸግረዋል በሚል አስተሳሰብ የተቀረጸ እንጂ የራስ አስተዳደር ማለት ከሰው አገር ጅብ የኔው የኳሮ ጅብ ቢበላኝ እመርጣለሁ ማለት አይደለም፡፡ ትችትን የሞት ያህል የሚፈሩና ከተተቹም የሚበቀሉ አመራሮች ባለበት ሁኔታ የራስ አስተዳደር ትርጉም አልባ

የፖለቲካ ተረት ተረት ነው፡፡ ከማእከላዊ መንግስት ቁጥጥር ርቆ በጀቱንና ሌላው ገቢውን በፍትሃዊነት እንዲጠቀምና እንዲያከፋፍል የሚጠበቅበት የራስ አስተዳደር እንደ ቄሱ ተረት ባርኮ እንዲያከፋፍል ሃላፊነት የተሰጠው ካህን “ይቺ ለድንግል፤ ይቺ ለቅስናየ፤ ይቺ ለመንኩስናየ…” እያለ የዳቦ ቁራሾችን ሁሉ ወደ አኩፋዳው የሚከት ከሆነ ልዩነቱ አሃዳዊነት በአገር አቀፍና አሃዳዊነት በክልል ደረጃ መሆኑ ነው፡፡

አራት ኪሎ ላይ የሚሰየሙት የኢትዮጵያ መሪዎች የትግራይን ህዝብ አያያዝ ስልት አሳምረው ያውቃሉ፡፡ ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ወደ ትግራይ የሚልኩት አስተዳደር ትግራይ-በቀል የሆነውን ነው፡፡ የትግራይን ህዝብ አንበርክኮ ለመግዛት ከራሱ ሰዎች የተሻለ እንደማይገኝ ከተረዱ ዘመናት አልፈዋል፡- በጋብቻ የታሰሩት ራስ ስዩምና ወራሻቸው፤ ቃለ ክርስቶስና ሙሉጌታ፤ ወዘተ፡፡ ይባስ ብሎ በህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ሰር የተደራጁ ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ ተጋሩ በትግራይ ህዝብ ላይ መቅሰፍትን አውርደዋል፡፡ የአማራ ሃይሎች ወልቃይትንና ራያን ጨምድደው ይዘው ፌደራል መንግስት አይን ስር በማናለብኝነት ዘላቂ ሊሆኑ የሚችሉ ስነህዝባዊ፤ ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ሃይማኖታዊ እርምጃዎች በሚወስዱበት፤ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር በግፋዊ ዘር ማጽዳት ወደ አገር ውስጥና ወደ ሱዳን የተሰደደው ህዝብ ባልተመለሰበት፤ እዛው በተገኙት ሺዎች ተጋሩም ላይ ግድያና እስራት በሚፈጽምበት ሁኔታ የፕሪቶሪያን ስምምነት ተግባራዊ እየሆነ ነው ብሎ ማሰብ ስላቅ ከመሆን አያልፍም፡፡

በሰሜን በኩልም የትግራይ (የኢትዮጲያ) ግዛቶች በኤሪትርያ ጦር እጅ ውስጥ ሆነው ህዝቡ ቁም ስቅል የሚያይበት የሃገር ክህደት ወንጀል በሚፈጽምበት አገር የፕሪቶሪያ ስምምነት ተግባራዊነትን እያወደሱ መተቃቀፍ፤ መደጋገስ፤ መሸላለምና መሸኛኘት የስምምነቱ አንድ አመት አሳዛኝ ክስተቶች ነበሩ፡፡ በፕሪቶሪያው ስምምነት ማግስት በፌደራል መንግስት ወገን ፈራሚዎች የተጣደፉት የትግራይን ሃይሎች ትጥቅ ወደ ማስፈታት እንጂ ተዘግቶ የከረመው የትግራይ ህዝብ ችግር ለመፍታት አልነበረም፡፡ በጥይት ለመፍጀት ሄደውበት የነበሩት መስዋእትነት ሳይከፍሉ በራሱ ጊዜ በችጋር ቢያልቅላቸው የሚመኙ እስኪመስል ድረስ ሂደቱን እያጓተቱ ነው፡፡ ከሁለት መቶ ሺ በላይ የትግራይ ሰራዊት አባላት በመላ ትግራይ ገጠሮች እንደፈሰሱ ናቸው፡፡ አመቱን ሙሉ ባልተሟላ ሰላም፤ በቂ ባልሆነ አቅርቦትናና በአስጨናቂ የጦርነት ማገርሸት ስጋት

ውስጥ ሆነው የሚጠብቁት የሰራዊቱ አባላት ትእግስታቸው በታሪክ የሚመዝገብ ነው፡፡ ወይ ቤታቸው አይመለሱ፤ ወይ ሌላ አይነት ሰራዊት አይሆኑ፤ ወይ ማቋቋሚያ ተሰጥቶ ወደ ሲቪላዊ የስራ አለም አልተሰማሩ፤ ወይ ጦርነት አልቀጠሉ፤ የገቡበት አጣብቂኝ ከባድ ነው፡፡

የትግራይ ሰራዊት ፈቷል ተብሎ የተነገረው ከባድ የጦር መሳሪያን ነው፡፡ ቀሪውን የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ለመፍታት የተወረሩ የትግራይ ግዛቶች መለቀቅ አለባቸው የሚል ቅድመ ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም በፌደራሉ የፍላጎት ማነስ ምክንያትም የክንውኑን ጊዜ መተንበይ አልተቻለም፡፡ ያለ ምንም እንቅፋት ሰብአዊ እርዳታ ፍሰት እንዲቀጥል የተወሰነው ውሳኔ “እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው” የሚመስል ያልተጻፈ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን ቆይቷል፡፡ በመሰረተ ልማት ጥገና፤ በወሳኝ የአገልግሎት ዘርፎችም ለረዥም ጊዜ ህዝብን ባሰቃየና ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ እግር ሲጎተት ቆይቷል፡፡ ፈረሱን ወደ ውሃ መውሰድ ተቻለ እንጂ እንዲጠጣ የማስገደድ አቅም አልተገኘም፡፡ የሰራተኛ ደሞዝና የጡረተኞች አበል ላለመክፈል የተኬደበት መንገድ የተወላገደና ሰብአዊነት የጎደለው ነው፡፡ ከአራት ኪሎ የሚመነጨው የፕሪቶሪያው ስምምነት ፈተና ከባድ ሊሆን የቻለው ስምምነቱን ለመፈጸም ዳተኛ ከሆኑት ወገኖች ጥንካሬ የመነጨ ሳይሆን የውሉ ተጠቃሚ የሆነው የትግራይ ወገን ድክመት ነው፡፡

አንድ ሚልዮን ይሆናል ተብሎ የተነገረው የሲቪሎች ሞት ቀሪው ዘመድ አዝማድ በጦርነቱና በዝጉ ጊዜ የቻለውንና የተፈቀደለትን ያህል ሙታንን ቀብሮ እርሙን ያወጣበት ስለሆነ የሚልዮኖች ዋይታና ጸጉር መንጨት ለሚድያ አልበቃም፡፡ የጦርነቱን ክብደት አይቶ ከመገመት በስተቀር ወላጅና ዘመድ አዝማድ ስለተሰዉ የትግራይ ሰራዊት አባላት በርግጠኛነት የሚያውቁት ነገር አልነበረም፤ ታላቁ መርዶ እስኪጀመር ድረስ፡፡ በዚህ የህዝብ ትራጀዲ በሞት የሚነግዱ የሰይጣን ውላጆችች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች ያላቸውን የግለሰብ ሞት መረጃ ለቤተሰብ በውድ ዋጋ የሚሸጡ አረሞችና አረመኔዎች ናቸው፡፡ በአንድ አነስተኛ ሰፈር ውስጥ አስርና አስራ አምስት መርዶ ተሰምቶ በዛም ሳያበቃ እስከቅርቡ ጊዜ ድረስ እየተንጠባጠበ በሚነገረው መርዶ ምክንያት መረጋጋት ያልቻለውን ህዝብ በምን ሁኔታ ህዝቡን በአጭር ጊዜ ውስጥ በመልሶ-ግንባታ በሙሉ ልብ ማሳተፍ እንደሚቻል ማወቅ ያስቸግራል፡፡

የፕሪቶሪያው ስምምነት የአንደኛ አመቱን ያልበሰለ ዳቦ እስኪቆርስ ድረስ የትግራይ ፖሊቲከኞች ከአዳራሾች አልወጡም፡፡ ሁኔታቸው ትግራይ በአለም ዙሪይ አግኝታ የነበረውን ትኩረት፤ አድናቆትና ከበሬታ ክፉኛ አሳጥቷታል፡፡ ሰብአዊ እርዳታ በመዘጋቱ ህዝብ በርሃብ አለቀ ተብሎ ዝጉን ለማስከፈት ያለቀው ወጣት ቤቱ ይቁጠረው፡፡ በስርቆት እርዳታው ሲዘጋስ ማን ያስከፈተው? በየ"ህዝባዊ" ስብሰባው መዝጊያ ላይ እንደማጣፈጫ የሚጨመረው "ለመልሶ-ግንባታ ሁላችንም እንረባረብ" የሚለው ቋንቋ የለበጣ እየመሰለ መጥቷል፡፡ ከመልሶ-ግንባታ ቀድመው የሚመጡ በርካታ የሰብአዊና የህዝብ ደህንነት እንቅስቃሴዎች ሳይነኩ አንድን ዘሎ ስለ ሶስት ማሰብና የመድረክ አደራ ማብዛት የህዝብን አፍ ከመዝጋት ያለፈ ፋይዳ የለውም፡፡ መልሶ-ግንባታ ግብታዊና የስሜት ስራ አይደለም፡፡ ሁሉም አቀፍ ምክክርና የተገቢ ፖሊሲዎች ቀረጻ የሚፈልግ ነው፡፡ ትግራይ አሁን ያሏት የልማት ፖሊሲዎች ከሃያ አመት በፊት የተቀረጹ የሰላም ጊዜ ፖሊሲዎች ናቸው፡፡አፈጻጸማቸውም በፌደራል ደረጃ ክትትል የሚደረግበት ናቸው፡፡ እነሱም ቢሆኑ አሁን የሉም፡፡

ትግራይ መልሶ ግንባታዋን መቼ እንደምትጀምር የሚያመለክት ፍንጭ የለም፤ ከባለስልጣኖች የይሉኝታ ንግግር በስተቀር፡፡ መልሶ-ግንባታው መጀመሩ ሳይታወቅ የሚጀመር ይመስላል፡፡ የፌደራል መንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶች፤ የትግራይ ክልል መንግስት፤ አለም አቀፍ ለጋሾች በየፊናቸው ያልተቀናጀና ወጥ የሆነ የመልሶ-ግንባታ ፖሊሲ የማይመራው እንደየ ፍላጎታቸው፤ እንደየ ብሄራዊ ጥቅማቸው፤ እንደየ ግል ስሜታቸው፤ እንደየ ኢኮኖሚ ፍልስፍናቸው ሊያራምዱት እንደሆነ አዝማሚያው ይታያል፡፡ መልሶ-ግንባታና ልማትን የሚመለከት ጉዳይ በየስብሰባው መድረኮች የመሪዎች የንግግር ማጣፈጫ ከመሆኑ የዘለለ የተሰራው ነገር ቢኖር የፖሊሲ ጥናት ተቋማትን ማራባት ነው፡፡

ከጦርነቱ በፊት ፌደራል መንግስት በህጋዊት በሚያውቀው የክልሉ መንግስት አዋጅ ተመስርቶ የነበረው የፖሊሲ ጥናት ተቋም ሳይከስም ግማሽ የግል ግማሽ የመንግስት የሆነ ሌላ የፖሊሲ ጥናት ተቋም ተመስርቷል፡፡ ለትግራይ ክልል ሁለት የግልና የመንግስት የፖሊሲ ጥናት ተቋማትን ማደራጀት "አስር ብትር" ከመያዝ የተለይ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ይህ ከፈረሱ ጋሪው የማስቀደም ጉዳይ መልሶ-ግንባታውን አካታች በሆነ የፖሊሲ ቀረጻና በተቀናጀ ትግበራ ለመምራት ፍላጎት እያሳየ ላልሆነው የክልሉ ሽግግር መንግስት ምን እንደሚፈይድለት

የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ የፖሊሲ ጥናት ተቋሞቹ ለመልሶ ግንባታ ስትራተጂ ቅድሚያ ሰጥተው ስራ ይጀምራሉ ሲባል የመጀመሪያ ስራቸው የሆነው በቦርዱ ሊቀመንበር በኩል ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት መመስረታቸው ነው፡፡ የህዝብን ስሜት ሳይዳስሱና ሳያማክሩ በማናለብኝነት በምእራብ ትግራይ ወንጀልን በምርምር ሲያግዝ ከነበረው ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት መቀጠል ህዝብን መናቅና ህግን  መጣስ ነው፡፡ የክልል ምክር ቤት በሌለበት ቡድኖች ህዝብን ሳያማክሩ ዘላቂ ውጤት ያላቸው ተግባራትን መፈጸም ከጀመሩ ቆይተዋል፡፡

ድህረ-ፐሪቶሪያ ትግራይን ጠንቅቆ ለተገነዘበ ታዛቢ የወጣት ወንዶችና ሴቶች ሁኔታ አይነቱ ብዙ ነው፡፡ ለማንም ጎብኚ ከሁሉም ነገር ቀድሞ ግልጽ ሆኖ የሚታየው ከሽረ እስከ አኹሱም፤ ከዓድዋ እስከ ዓዲግራት፤ ከዓብዪ ዓዲ እስከ መቐለ የጥይት ድምጽ የማይሰማበት እረጭ ያለ መሆኑ ነው፡፡ ከነዚህና ወደነዚህ ከሚወስዱትና የሚመልሱት መንገዶችም ላይ ዝርፊያ ሆነ ከልከላ አይታይም፤ የሰው ሳርዲን ጣሳዎች ከሆኑት ሚኒባሶች በስተቀር፡፡ ያለፈውን ሚልዮን ህዝብ የፈጀ አውዳሚ ጦርነትን እያሰቡ ትግራይ ውስጥ ከከተማ ወደ ከተማ መጓዝ በሚታየው ሰላማዊ ሁኔታ በጭንቀት መወጠር አይቀርም፡፡ በክፉ ጊዜ የህዝቡ ጀግንነትና መከራ ቻይነት፤ በሰላም ጊዜ ደግነቱና መቻቻሉ ዋናው ምክንያት ቢሆንም እንዲህ ሆኖ ለተጠበቀው ሰላም የትግራይ ሰራዊት በየገጠሩ መሰግሰግ ያለው አስተዋጻኦም ወሳኝ ነው፡፡ በድህረ-ጦርነት ትግራይ ቢያንስ አስር አይነት የወጣቶች ሁኔታ መታዘብ ይቻላል፡-

1ኛ. የሁለት አመቱ ትግል ያልዳሰሳቸው (በገንዘብና በወገን ሃይል ያልዘመቱ ወይም ተደብቀው ያሳለፉ)፤ እነዚህ ወጣቶች የሰፈነው ሰላም በማን ደምና የንብረት ጥፋት እንደተገኘ ማሰብ የማይፈልጉ፤ ጥጋባቸውን መቻል ያቃታቸው፤ በየቢራ ቤቱና በየመንገዱ የዳበረ ደረታቸውን ገልብጠውና ጸጉራቸውን ግራር አስመስለው የሚንጎማለሉ፤ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የሚያወሩና የሚገለፍጡ፤ ከፍተኛ ወጪ እያወጡ በሙዚቃ ባንድ ጩኸት ታጅበው በዛ በደም የጨቀየና በድርቅ የነደደ መሬት ላይ በሃሴት የሚዘሉ ወጣት ነጋዴዎች የነጋዴዎች ወይም የባለስልጣናት ልጆች ወይም ዘመዶች ወይም ከውጭ በሚላክ ገንዘብ ኑሯቸውን የመሰረቱ፡፡ 2ኛ. መንግስታዊ ባልሆኑ የእርዳታ ድርጅቶች ሲሰሩ በሚያገኙት ከፍተኛ ክፍያና አበል ከህብረተሰቡ የተለየ ህይወት ሲኖሩ፤ ብርቅ ድንቅ የሆኑ መኪኖችን እያሽከረከሩና ውድ በሆኑ ሬስቶራንቶች እየበሉ

እየጠጡ፤ ሁልጊዜ ወከሾፕ ሰርክ በኮንፈረንስ ብር እያባከኑ፤ የእርዳታው አሰጣጥ አብቅቶ ስራቸውን እንዳያጡ ከመስጋት በስተቀር በዙርያቸው ስላለው አስከፊ ህይወት ምን ዘላቂ መፍትሄ መስጠት እንደሚገባ ከማሰብ ነጻ የሆኑ፡፡

3ኛ. በጦርነቱ ሃብታቸውንና ቤተሰባቸውን አጥተው ኑሮን እንዴት እንደሚኖሩት ቀኑን እንዴት እንደሚገፉት ግራ የገባቸው፡፡ 4ኛ. መላ ትግራይን አልብሶ የሚገኘውና ስራ-አልባ ሆኖ በሌላ ስራ የተጠመዱትን የፌደራል መንግስትንና የራሱ መሪዎችን ትኩረትና ውሳኔ እየጠበቀ፤ የወደፊቱ ህይወቱ ቀና ይሆናል ብሎ ተአምር የሚጠብቅ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የትግራይ መከላከያ ሰራዊት ወጣት አባል፡፡ 5ኛ. በሁሉም ነገር ተስፋ ቆርጠው ወደ ዘመድም ይሁን እንዲሁ ያለ ምንም ተቀባይ "ከትግራይ የማይሻል ሲኦል የለም" ብለው ወደ አዲስ አበባ የሚፈልሱት በሺዎች የሚቆጠሩ የመልሶ ግንባታና የልማት ሃይል ሊሆኑ ይችሉ የነበሩ ወጣቶች፤ እዚህ ላይ በአንክሮ ማሰብ የሚያስፈልገው ጉዳይ አመራሮች በሚፈጥሩት የማያባራ የፖለቲካ ውጥረት የወጣቱ እጣ ፈንታ የሆነው ተዋጊነት እንጂ አልሚነት አይደለም፤ ከዚህ የከፋ ምን ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ይኖራል?

6ኛ. ትግራይ ውስጥ አሁን አሁን የተሻለ ነገር ይመጣል እያሉ ከራስ ወዳድ መሪዎቻቸው የደበዘዘ ተስፋ የሚጠብቁ፤ የጀበና ቡና ቤቶችን አጨናንቀው የሚውሉ ተስፈኞች፡፡ 7ኛ. ከነጋዴዎችና ከባለስልጣናት ጋር እየተሞዳሞዱ፤ ወይም ተላላኪ እየሆኑ በድለላም ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እየተሻሙ የሚኖሩ የህዝብ ነቀዞች፡፡ 8ኛ. በየተፈናቃዮች መጠለያዎች የቤተሰባቸውንና የራሳቸውን ስቃይ እያዩ ቀን የሚገፉ መጨረሻው የማይታይ መከራ ያደነዘዛቸው መቶ ሺዎች፡፡ 9ኛ. በህይወት ለመኖር ብቻ ሴትነታቸውን አሳለፈው የሰጡ ገንዘብ ላለው ወፈ ሰማይ ሲሳይ የሆኑ ወጣት ሴቶች፡፡ 10ኛ. የጤና አገልግሎት ባልነበረበት ተደፍረው አርግዘው የወለዱና የአረመኔ ደፋሪዎቻቸውን ልጆች የሚያሳድጉ፤ ትግል ላለመሄድ ሲሉ አርግዘው ቀሪ የህይወት እድላቸውን ያበላሹ በትግሉ የወታደራዊ አዛዦች ወጣት ሴት "ረዳቶች" የነበሩ ያሉም፤ በተፈናቃይ ካምፖች ውስጥ በሰፈነው ቁጥጥር አልባ ወሊድ ልጅ አሳዳጊ ሆነው ከንቱ የቀሩ ወጣት ሴቶች፡፡

የገጠሩን አብዝቶ የከፋ ሁኔታ የተሟላ ስእል ማግኘት የሚያዳግት ቢሆንም በከተሞች ያለው ትእይንት ግን ሃዘኔታን የሚያጭር ነው፡፡ መንገድ ላይ ወጥቶ

ለአፍታ ቆሞ የተመለከተ ሰው በጀርባዋ ያላዘለች ወይም በእጇ ልጅ ያልያዘች ሴት የምትታየው አልፎ አልፎ ነው፡፡ ናትና ፎረም የሚባል ሚድያ "የተፈጥሮ ግዴታ" ብሎ ችግሩን አቅልሎ ለመረዳት የሞከረው ልቅ የሆነ እርግዝናና ወሊድ የሚበላ በሌለበት፤ የጤና ክትትል በሌለበት፤ በጦርነት ምክንያት ሞትና መፈናቀል በበረከተበት ለራስ ሆነ ለሚወለዱት ሃላፊነት የማይሰማው የተፈጥሮ ግዴታ አለን? የስነ-ድህነት መማሪያ መጻህፍት በሙሉ የድህነት መንሳኤና ውጤት ልቅ የሆነ ወሊድ መሆኑን በመግቢያቸው ላይ ያሰፈሩት ዋነኛ የዘላቂ ልማት ጸር ነው፡፡ ትግራይ ስርኣት ባጣ የስነ-ህዝብ ልማድ መሻገር አትችልም፤ ገዢዎቿ በተጣሉ ቁጥር የምትገብረው ወጣት ልትፈለፍል ብቻ እንጂ፡፡

11ኛ. አብዛኛዎቹ የትግራይ የከተማ ኗሪ ወጣቶች የሚጋሩት ነገር ቢኖር የቲክ ቶክ ምርኮኞች መሆናቸው ነው፡፡ ቲክ ቶክ ላይ ተደፍተው ሲውሉ የሚማሩት ቁም ነገር የሌለ ብቻ ሳይሆን ወጣቶቹ የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ችግር ለማዳመጥና የመፍትሄው አካል ለመሆን ጊዜ የማይሰጣቸው መሆኑ ነው፡፡ የሚያገኙት ውስን ገንዘብም ቢሆን ለጤና የሚበጅ ነገር ገዝቶ ከመጠቀም "ዳታ" ለመግዛትና የዋይ ፋይ መስመር ለመከራየት ያውሉታል፡፡ ብራቸውንና ጊዜያቸውን አፍሰሰው የሚያገኙት ሌላው ፍሬቢስ ነገር ቀኑንና ሌሊቱን በሙሉ በፌስ ቡክ ሲሰዳደቡ የራሳቸውንም የህዝቡንም ሰላማዊ ህይወት የሚያደፈርሱ መሆናቸው ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ያለበት ስቃይ ያነሰ ይመስል የህዝብ ስሜት ያልተላበሱ ለህብረተሰቡ "ባእድ" የሆኑ ወጣቶች ሌላ ትርምስ ይፈጥሩበታል፡፡

**"ደራሲው በሰማይ ቤት"**

አርቲስት አለማየሁ ታደሰ ገና የትያትር ጥበባት ተማሪ እያለ የተወነበት "ደራሲው በሰማይ ቤት" የሚል ርእስ ያለው ድራማ በድህረ ምረቃ አዳራሽ ውስጥ ሲታይ የመግቢያ ትእይንቱ የዚች አለም ህዝቦች ደስታንም ሃዘንም ሲቀላቅሉ በኑሯቸው እንደማይናበቡ የሚመሰክር ነው፡፡ መድረኩ በቀኝ በኩል "ጉሮ ወሸባየ! የኛ ሙሽራ!" እያሉ እልልታና ሆታቸውን ያቀልጣሉ፤ በመድረኩ በግራ በኩል ደግሞ "ዋይ ዋይ ተለያየን!" እያሉ ፊታቸውን እየነጩ ሙሾ የሚያወርዱ ሰዎች እጅብ ብለው ይዘላሉ፡፡ የሚያለቅሱትና የሚዘፍኑት ተራ በተራ ስላልነበረ ለታዳሚው ድብለቅልቅ አለበት፡፡ ድራማ ማለት እንዲህ ነው፤ ምንባቢው ሳይሆን እውነታዊው አለም የሚወክል! ይህን ድራማ ያየና የተዝናና

ሰው በትግራይ ያየውን ተመሳሳይ እውነታ ሊያስቀው ወይም ዘና ሊያደርገው አይችልም፡፡ የ2016 የመጀምሪያ ሩብ አመት በትግራይ ታሪክ ታይቶ የማያውቅ የሺዎች መስዋእትነት መርዶ ለሳምንት ጊዜ ያህል ሲነገር ምድሪቱ ማቅ ለብሳ ነበር፡፡ በትግራይ ከተሞችም ሆነ የገጠር መንደሮች ወንዱም ሴቱም ነጠላ ለብሶ ለቅሶ ለመድረስ ወዲያና ወዲህ ይሯሯጣል፡፡ ትርምስ ነግሷል! ሟቹ ብዙ' ለቅሶ ቤቱ ብዙ፤ ለቅሶ ደራሹም ብዙ፡፡ ይህን ታሪክ ቆሞ መታዘብ የቻለ ሰው ምንም ቆዳው ቢወፍር ልቡ መነካቱ አይቀርም፡፡

የሃዘኑና የቁጭቱ ስሜት ለስንት ቀን ወይም ለስንት ወራት ወይም ለስንት አመታት ይዘልቃል? የሚለው ጥያቄ መልሱ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን የሚልዮኖች ትራጀዲ፤ እሱን እግር በእግር ተከትሎ የመጣው የድርቅና ርሃብ መቅሰፍት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አእምሮ ሰቅዞ መያዝ ሲገባው የሟች ዘመድና ወዳጅ እንባው ከፊቱ ሳይደርቅ ክልሉን ያዳረሰ በቀንም በሌሊትም የሰርግ፤ የዘፈን፤ የከበሮ፤ የእልልታ፤ የዳንኪራ ድምጽ ጸጥታውን አደፈረሰው፡፡ የትግራይ ሽግግር መንግስት ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ በሸረ ህዝባዊ ስብሰባ ይህ ጉዳይ በጥያቄ መልክ ተነስቶላቸው ነበር፡፡ እንዲህ አይነት ጉዳይ ሲነሳ አንዳንድ የሰፈር ፈላስፎች ወይም የአካባቢ አስተዳደሮች "ቢሰርግ መብቱ ነው፤ በገዛ ገንዘቡ" የሚል የሰው ልጅ ማህበራዊ መልካም እሴቶች ያልዳሰሰው መልስ ይሰጣሉ፡፡ ጌታቸው ረዳ ግን ተገቢ ነው ወይም ተገቢ አይደለም የሚለው ከሳቸው የሚጠበቅ መልስ ሳይነኩ ያን ሰሞን ስለሰሙት አስገራሚ ዜና ተናገሩ፤ ለማሳቅ ወይስ ለማስለቀስ? ጌታቸው ረዳ የሰሙት ነገር እንዲህ ነው፡- "ሰርገኛና ለቀብር የወጣ ህዝብ ድልድይ ላይ ተፋጠጡ!" የአለማየሁ ታደሰ "ደራሲው በሰማይ ቤት" በከፋ መልኩ መሬት ላይ ተከሰተ፡፡ እዚህ ላይ እንቆቅልሽ ሊሆን የሚችለው፡- ይህ መድፍ እያጓራ ባለበት ተደማምጦ ለድል የሚበቃው ህዝብ በሰላም ጊዜ በማህበራዊ ህይወቱ የማይደማመጥበት ምስጢሩ ምንድነው? አንድ ብሄር ማለት ምን ማለት ነው?

**"የጋሪ-ፈረስ"**

የድሮው የወያነ አመጽ የከሸፈው የእንግሊዝ አየር ሃይልና የንጉሱ ሰራዊት ከአመጻኞቹ የላቀ የውጊያ አቅም ስለነበረው ብቻ አይደለም፤፤ የተወሰኑ የትግራይ አካባቢዎች ገዢዎች ወያነዎቹን ተጻረው በመነሳታቸው ጭምር እንጂ፡፡ የወያነ

አመጽ የበደል ምሬት የቀሰቀሰው ግብታዊ መነሳሳት እንጂ በርእዮተ አለም የሚመራ በእዝ ሰንሰለት የተደራጀ የፖለቲካ አካል የሚመራው አልነበረም፡፡ ግብታዊ የሆነ እንቅስቃሴ ምንም ለጭቁኑ የቆመ ህዝባዊ አላማ ቢኖረውም ልክ እንደ ወያነ አመጽ ከሽፎ የሚያተርፈው ነገር ቢኖር በህዝብ ላይ የሚወሰድ የበቀል እርምጃ ነው፡፡ በርእዮተ አለምና በፓርቲ የተመራውም ቢሆን በንድፈ-ሃሳብ ሳይሆን በተግባር ለደሃው የቆመና በሓቅ አሳታፊ ዴሞክራሲን የሚያራምድ ለመሆኑ ዋስትና የለም፡፡ ይህ በህወሓት የትግል ሂደትና በኋላው የአገርና የክልል አመራር በግልጽ የታየ ነው፡፡ ካፒታሊዝም ለምን ይወደዳል ቢባል ግለሰብን ከቡድን አገዛዝ ነጻ አውጥቶ የወሳኝነት አቅም ስለሚያቀዳጀው ነው፡፡ ይህን የሚጠሉ እነማናቸው? ይህን የሚጠሉ ህዝቡ ውሳኔን የሚጠብቅ እንጂ ውሳኔን የሚያፈልቅ እንዳይሆን አድርገው በርእዮት አለም ሰንሰለት ተብትበው ያሰሩትና በሱ ስም፤ በሱ ህይወት፤ በሱ ገንዘብና  በሱ ጉልበት ስልጣን ላይ የመሸጉ አስመሳይ ዴሞክራቶች ናቸው፡፡ የህወሓት መስራቾች “ቀዳማይ ወያነ” የሚሉት በአላማም በአመራሮቹም፤ በከሸፈበት ምክንያትም “ሁለተኛ ወያነ” ከተባለው የህወሓት-መር ትግል ጋር ብዙም የሚገናኝ አይደለም፤ ትግራይ ውስጥ የተፈጸመ ከመሆኑ በስተቀር፡፡

አጥር መዞሩን ትተን ቀጥታ ወደ ሃቁ ከገባን ወያነን በማከሸፍና ኋላም በመቐለ ወረራና ህዝብ ማንገላታት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የአድዋን ጦር የመሩ ገዥ ነበሩ፡፡ ህወሓትን እንደ ግል ንብረታቸው የሚቆጥሩት የአድዋ ሰዎች ያልተባበሩትን እንዲያውም ያጠፉትን ወያነን እንደ ቀዳማይ የእንቅስቃሴያቸው ውጥን መቁጠራቸው የታሪክ ቅሚያና የሞራል ግድፈትም ነው፡፡ በህውሓት የትግል መጀመሪያ ሰሞን የህወሓት አመራር ኢላማ ሆነው የነበሩት የ”መጀመሪያው” ወያነ ታጋዮች ልጆችና የልጅ ልጆች ነበሩ፡- “ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ”፡፡  የህወሓት መስራቾች በዘመኑ የነበረውን ወጣት ሁሉ የማረከው የሶሻሊዝም ርእዮተ አለምን አክርረው በመያዝ “መስመር እዩ ሓይልና” በሚል የግለሰብን ስሜት የማያዳምጥ፤ አባላትን እንደ መንጋ መሪዎችን እንደ እረኛ የሚመድብ ለአምባገነኖች አመቺ የሆነ ርእዮት አለም! ሾሳሊዝም ለኢትዮጵያ ግስጋሴ ገንቢ ሚና ሊኖረው ይችል የነበረውን ወሳኝ ትውልድ የበላ ቢሆንም ለህወሓት ግን የስኬቷ ቁልፍ ሆኖላታል፡- “እልም አለ ባቡሩ፤ ወጣት ይዞ በሙሉ!”፡፡

ህወሓት በጸረ-ጭቆና ስም የከፋ ጭቆና የምታደርግበትን ሶሻሊዝም ለአገዛዝ አመቺነቱን በማየት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጋለችው መጣች እንጂ ለህዝብ ነጻነት ስትል እያበረደችው አልነበረም፡፡ ”መስመር እዩ ሓይልና” የትግራይ ህዝብን በአዚም የሚይዝበት የተለያዩ ዘዴዎች አሉት፡፡ በመሰረቱ የሶሻሊዝም ረእዮተ አለም ህዝብን የሚበላው እንደ ዘንዶ በውበቱ ነው፡፡ የዘንዶ አይን ከማማሩ የተነሳ እሱን አተኩረው እያዩ የሚዋጡት ሌሎች እንሰሳት ብቻ አይደሉም፤ ስውም ጭምር ነው፡፡ የሶሻሊዝም ጭፍን ተከታዮችን እንደ ግመል ቅፍለት መቶዎች ሆነው የሚጎተቱት በአንዲት ገመድ ነው፡- በአብዮታዊ መዝሙርና በትግል ትዝታ፡፡ ህወሓት ወጣቶችን ለትግል የምታሰልፍበት፤ በታማኝነት የምታቆይበትና ለዘለቄታም ምርኮኛዋ አድርጋ የምታኖርበት ስሜትን የሚቀሰቅሱ፤ ለመስዋእትነት የሚገፋፉ ዘፈኖችና መዝሙሮችን የሚያዘጋጁ የባህል ቡድኖች ነበሯት፤ አሁንም አሏት፡፡ ልዩነቱ በትግሉ ወቅት የነበረው ቅስቀሳና ባዶ ኪስ ሲሆን የአሁኑ ደግሞ ቅስቀሳና ሙሉ ኪስ መሆኑ ነው፡፡ ሁለቱም የሚያመሳስላቸው ራሳቸው የማይገቡበት እሳት ላይ ወጣቱን በስሜት አሳውረው እቶን ውስጥ መጨመራቸው ነው፡፡

የህውሓት አመራሮች ሆኑ የትግራይ ልሂቃን የትግራይን ወጣት ምን ያህል እንደ ሸክላ አፈር ጭቃ በፈለጉት ቅርጽ ማድቦልቦል እንደሚችሉ የሚናገሩት በይፋ ነው፡፡ በኢንሳ-ነበር ኮሎኔል ብንያምና በብራኸዋ ጋዜጠኛ መድህን መከከል በተካሄደው ቃለ-ምልልስ፤ ለድህረ-ጦርነት ትግራይ በማይመጥን ሁኔታ አበባ መስለው፤ በትግራይ ውስጥ ጥርስ የሚያስገልጥ ነገር ያለ ይመስል፤ ሲቃ እስኪይዛቸው ድረስ በሳቅ እየተንከተከቱ ሲያወሩ የነበሩት እንዴት አብረው “ለትግል” በርሃ እንደወረዱ ወጣቱን እንዴት እንደመለመሉ ነበር፡፡ የመለመሉት ወጣት በየጥሻው መቅረቱ ትዝ እንኳ የሚላቸው ቢሆን መሳቅ አይደለም አንዲት ቃል መተንፈስም አይገባቸውም ነበር፡፡ የወጣት ምልመላውን ያስመሰሉት የሪል እስቴት ባለቤቶች ገበያ ወርደው የቀን ሰራተኛ እንደሚመለምሉተት አይነት፡፡

በዚህ መንገድ የተመለመሉት ወጣቶች የሞቱት አያዩም፤ የተረፉት ግን ህወሓት እንደመገልገያ ተጠቅማ እንደጣለቻቸው የሚመስክሩት በራሳቸው ልሳን ነው፡፡ የትግራይ ሰራዊት የጦር አካል ጉዳተኞች ሶትት ጊዜ በላይ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል፡፡ በሚደረግላቸው የአያያዝ ጉድለት ምሬታቸውን ለተደፈነ ጆሮ አሰምተዋል፡፡ በሚዘገንን ሁኔታ የሚያስለቅስ ጋዝም ተተኩሶባቸውል፡፡ መሪዎቹ

“የፈለግነውን ሰርታቹኋል ከእንግዲህ የኛ ሸክም አትሁኑ” የሚሏቸው ይመስላሉ፤ ለስብሰባ ፍጆታ ግን “ጀግኖቻችን“ እየተባሉ በምጸት ይሞካሻሉ፡፡ የጦር ጉዳተኞቹ ግን እንዲህ ብለው መፈክር አሰሙ በቅርቡ ባካሄዱት ሰላማዊ ሰልፍ፡- “ጀግና የሚያፍርበት፤ ሌባ የሚኮራበት!” የድህረ-ጦርነት ትግራይ እውነታ! አመራሮቹ የሚጨነቁት የጦር ጉዳተኞቹ ምሳ ከበሉ በኋላ እራታቸው ምን ይሁን እያሉ ሳይሆን፤ የሽግግሩ መንግስት የስራ ጊዜ ካበቃ በኋላ እንዴት አድርገን ምርጫ እናሸንፍና ህዝቡን አንበርክከን መግዛት እንቀጥል ነው፡፡ ህዝቡ ራሱ ለአገዛዝ የተመቸ ነው፡፡ የአስራ ሰባት አመታቱ ትግል ካበቃ በኋላ ከጦርነቱ በፊት በነበሩት 30 የህወሓት አመራር አመታት ለልማት ቅስቀሳ ተብሎ በጅት የወጣለት የትግራይ ሚድያ ዋና ስራው ሆኖ የቆይው ድንዛዜን የሚፈጥር የማያባራ የትግል ዘፈን፤ ማብቂያ የሌለው ከአመራሮች ጋር የሚደረግ የትግል ታሪክ ቃለ መጠይቅ ነበር፡፡ ህዝቡን በአንድ እግር አቁመው መጠባበቂያ ማድረጊያቸው ነበር አመራሮቹ፤ ተሳካላቸው! “እምበር ተጋዳላይ!”



የትግል ዘፈንና እስክስታ የትግራይ ፖለቲከኞችን አይመለከትም፡፡ የትግል ዘፈን እነሱ ህብረተሰቡ ላይ አፍዝ አደንግዝ የሚያደርጉበት እንጂ እነሱ ላይ የሚሰራ አይደለም፡፡ በትግሉ ዘፈንና ሆታ ተመስጠው አይናቸው እንባ ቋጥሮ ወደ እሳት የሚሮጡት ማቅ ሆነ ጨርቅ የሌላቸው የዛ ምስኪን ገበሬ ልጆች ናቸው፡፡ “ታጋይ ሳይንሱን ታጥቆ” እያሉ መትረየስ ተሸክመው ሲዘሉ ሳይንስ ያሉት ምን እንደሆነ የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ መሪዎቹ በትግል ዘፈንና ሆታ ውስጥ

ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው በፕሮቶኮል እስክስታ ሲወርዱ ፎቶ ወይም ቪድዮ ተነስቶ ለህዝብ የሚሰራጭና "የኛዎቹ ናቸው" እየተባለ የህዝብን ልብ የሚሰልብ መሆኑን አሳምረው ያውቃሉ፡፡ በህዝብ ላይ የሚፈጽሙትን የአስተዳደር በደልና ሙስናን የትግራይ ህዝብ በሚያፈቅረው ላጺስ ደብዛውን ያጠፋሉ፡፡ ልሂቁ አዲስ አበባ ውስጥም ሆነ በዳያስፖራው የትግል ዘፈንና ዳንኬራ ተራው ህዝብ ላይ እንደሚሰራው ወርውሮ ጦርነት እቶን ውስጥ የሚከት ሳይሆን የሰርግ ድግስ፤ የወጣቶች ፓርቲና የ"ቤቢ ሻወር" ማጣፈጫ ነው፡፡ ትግራይ ዙርያውን ተዘግቶ ህዝብ በረሃብ በሚያቅበት፤ ህጻናት እንደቅጠል በሚርግፉበት ጊዜ ወርቅን እንደጨርቅ የለበሱ አዲስ አበባ ኗሪ ተጋሩ ወይዛዘርት ለ"ቤቢ ሻወር" እሽሩሩ ክላሽኔ" እያሉ ሌሊቱን በዳንኬራ ያሳልፋሉ፡- "አብድፍያም ዓልል! ዓልል! ዓልል!"

በትግራይ ጦርነት ማግስት የሚታየው ድባብ ከውትሮው የተለየ ነው፡፡ ትግራይ ከተሞች ውስጥ በፊት በየሄዱበት በየደረሱበት አብዝቶ ሲሰማ የነበረው የትግል ዘፈን አሁን አይሰማም፤ የትግል ዘፈን ያልሆነውንም ቢሆን የሚሰማው ሰርግ ላይ ነው እንጂ በያንዳንዱ ቤት ደጃፍ ላይ ሲሰማ የኖረው ድለቃ ደብዛው ጠፍቷል፡፡ እርግጥ ነው ህዝብ አመለካከቱ ተቀይሯል፤ ፖለቲከኞቹ ለራሳቸው ህልውና፤ ሃብት ማግበስበስና ስልጣን ሲሉ ጨምቀው እንደጠጡት ገብቶታል፡፡ ነገር ግን አሁንም የባሰ አቅመ ቢስ ነው፤ ከነሱ እጅ የሚወጣበት የኢኮኖሚ ጉልበት፤ የፖለቲካ እውቀት የለውም፡፡ ህዝብ ያደረበትን የቁጭት ስሜት እየገለጸ ያለው በየትኛውም የትግራይ ከተማ አማርኛ ዘፈኖችን በማዘፈን ይመስላል፡፡ ይህ ክስተት እስኪለመድ ድረስ ለታዛቢው ግራ ሊሆንበት ይችላል፡፡ ህዝብ ከመሪዎቹ ጋር እልክ መጋባት ሲጀምር መሪዎቹ የትኛውን ሽምቀቆ እንደሚያጠብቁበት አሳምረው ያውቃሉ፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላም፤ አሁን ያለውም እየሆነ አሁንም ስለ የካቲት 11 ትዝታ! ቴለቪዥን ጣቢያዎቹ አሁንም፡- "ለካቲት አዴና!"

**ህወሓት፡- "የሰው-ሰው፤ ጎርደንዲኖስ"**

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት (ኢ.ዲ.ዩ.) በኢትዮጵያ የመሳፍነንት ቅሪቶች የተመሰረተ በትጥቅ የተደገፈ ጸረ-ደርግ ትግል ነበር፡፡ የከተማ ትግሉ በመላ ኢትዮጵያ የተዘረጋ ቢኖርም ትጥቅ ትግሉ ግን በትግራይ አዲያቦ አካባቢ የተወሰነ ነበር፡፡ ኢ.ዲ.ዩ. የመሳፍንቱን ስርአት ዲሞክራሲን ቀብቶ ለመመለስ የሚታገል ሲሆን የመደብ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው ብሎ የሚያምን ነበር፡፡ ለዚህም ነበር

የመደብ ልዩነትን “ለማጥፋት” የሚታገሉት የህወሓት አባላት ኢዲዩ ላይ ሲያሾፉ የነበሩት፡፡ እዚህ ላይ እውነቱን ተናግረው ከመሸባቸው ያደሩት ኢ.ዲ.ዩ.ዎች እንጂ ህወሓቶች አልነበሩም፡፡ “ጉድና ጅራት ከኋላ ነው” እንደሚባለው ከትግል መጠናቀቅ በኋላ በትግራይ ህብረተሰብ ውስጥ ህወሓቶች የፈጠሩት የመደብ ልዩነት የኢ.ዲ.ዩ.ዎችን ምኞት የሚያስንቅ ሆነ፡፡ የቀልዱ ይዘት ይህን ይመስላል፡- የኢ.ዲ.ዩ. ሰራዊት አዛዥ ለሰራዊቱ አባላት የፖለቲካ ትምህርት እየሰጠ ነው፡፡ የዛሬው ትምህርት “ስለ መደቦች” ነው፡፡ “መደቦች በሶስት ይከፈላሉ ብሎ ቀጠለ፤ እነሱም፡- የሰው ሰው፤ ሰው፤ ጎርደንዲኖስ፡፡ የሰው ሰው ማለት እንደ ልኡል ጌታየ፤ ሰው ማለት እንደኔ፤ ጎርደንዲኖስ ማለት ደግሞ እንደናንተ እርባና የሌላችሁ!” ብሎ ትምህርቱን ደመደም፡፡ ህወሓት በሆዷ ኢ.ዲ.ዩን የሰው ሰውና ጎርደንዲኖስን እያሰበች፤ በአፏ በሶሻሊዝም የሰው ልጅ እኩልነትን ለሰራዊቷ ታስተምራለች፡፡

በህወሓት ጋብቻ አይታሰብም፤ የጾታ ግንኙነት መፈጸም ያስረሸን ነበር፡፡ መሪዎች የጦርነቱ ማለቅና የስልጣን ተስፋ ጭላጭል ማየት ሲጀምሩ የእከሌ እህት ወንድም፤ አጎት አክስት እየተባባሉ መጋባት ጀመሩ፡፡ ቀሪው “ጎርደንዲኖስ” ወንድነቱን ወይም ሴትነቷን ይዘው የበይ ተመልካች ሆኑ፡፡ የተጋቡትንና የተዋለዱትን መሪዎቻቸውን የነጻነት ብርሃን ለማሳየት የመሰዋት ግዴታ ነበረባቸውና በባል በሚስትና በልጅ ፍቅር መዘናጋት ከቶ አልተፈቀደላቸውም፡፡ በጎቹ ሄደው ግድግዳ ላይ የተጻፈውን ተመለከቱ “አንሶላ ባለው አልጋ ላይ መተኛት አይቻልም”፤ ከዛም ስኲለርን ይቅርታ ጠየቁ! በኋላኛው ዘመን መሪዎቹ የረገሙትንና በመፈክር ያዋረዱትን ካፒታሊዝም እስከ ስኮናቸው ለበሱት፤ ከበርቴዎችም ሆኑ፤ ባለ ፎቅ፤ ባለ ፋብሪካ፤ ባለ ገልባጭ፤ ባለ ፕራዶ ባለ ቪ ስምንት፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸው ያበቃ “ጎርደንዲኖሶች” በየዳንሻውና በየአውራጎዳናው ተበትነው ቀሩ፡፡ በተወረወረባት ፈንጂ ሁለት አይኗን ያጣቻው ሴት ታጋይ በትውልድ ሰፈሯ የድህነት ህይወት ትገፋለች፡፡ የሰፈሩ ሰው “አንቺ እውር” እያለ ይጠራታል፡፡ እንዲህ አትበሉኝ ስትል የሚመለስላት መልስ የበለጠ የሚያሳርራት ነበር፡- “በገዛ እጅሽ ነው የታወርሺው፤ ወደ ትግል ለምን ወጣሽ?”

በቅርቡ በከፊል የተጠናቀቀው የትግራይ ጦርነት እንደ በፊቱ የዩኒቨርሲቲ ለግላጋ ወጣቶች የመሩት አልነበረም፡፡ ትግራይ ለሰላሳ አመታት ከድሮው መስፍናዊ ስርአት በባሰ የኑሮ ልዩነቱ ሰማይና ምድር የሆነባት ነበረች፡፡ እንዲህ ባለ ልዩነት

ነበር በ2013 ወደ ትግል ሜዳ የተወጣው፡- ምኞት የለመዱ የህወሓትና ወታደራዊ አመራሮች፤ “በህይወት ሲመለሱ” የስራ ዋስትና እንዳያጡ ፈርተው ሜዳ የወረዱ የሲቪል ሰርቪሱ ባልደረቦች፤ “የስንዴ ሚሊሺያ” ብለው የሚያንኳስሷቸው በሰብአዊ እርዳታ ኑሯቸውን የሚገፉቱ፤ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሌሎች በርካታ ቅምጥሎች፡፡ ጥያቄው እነዚህ ሁሉ ያገኙትን ስራስር፤ ቂጣና ዶኬ እኩል ይበሉ ነበር? ለታጋዮች ምግብ መግዣ እየተባለ ከዳያስፖራው በተለያየ መንገድ ሲገባ የነበረው ገንዘብ የት ገባ የሚለው ጉዳይ እርስ በርስ መከታከቻ ዱላ ሆኖ ከርሟል፡፡ የሚታወቀው ነገር ግን የሰራዊት አዛዦች ፍየል እየጠበሱ ሲበሉ ሌላው ታጋይ ያንን እያሸተተ በውሃ እንኳ የማይወርድ ደርቅ ቂጣ ሲበላ እንደከረመ በምሬት ይነገራል፡- “ሕደግ ውረድ”!

## “የቤት እቃህን ብላ”

ድመት አይጥ ትይዝና ሁለት አይናን ታጠፋለች፡፡ ድመቲቱ አይጧን ለቀቅ ስታደርጋት አይጧ ሮጣ ለማምለጥ ትሞክራለች፤ ድመት መልሳ ትይዛታለች፡፡ ያልራባት ድመት መጫወቻዋ ይኸው ነው፡፡ ፌደራል መንግስት እርዳታ እንዳይገባ ከልክሎ የትግራይ ህዝብ በረሃብ ሲያልቅ ነበር፡፡ በአንድ ጀሮ እርዳታው ይለቀቅ ሲባል በሌላ ጀሮ ደግሞ “ገታ አድርጉ” የሚባልበት የጭካኔ ድርጊት ባለበት እያለ የወገን ጠላትም ህዝቡን የመበደል ድርሻውን እየተወጣ ነበር፡፡ የእርዳታ ማከፋፈሉ ተግባር ለአካባቢ የአስተዳደር ሃላፊዎችና ቡድኖች ተሰጥቶ እንደለመዱት በህዝቡ ላይ በደላቸውን የሚፈጽሙበት እድል አገኙ፡፡ እነዚህ እርዳታውን በፍትሃዊነት እንዲያከፋፍሉ አደራ የተሰጣቸው ሃላፊዎችና ግለሰቦች የሚዘርፉት እርዳታ እንዳለ ሆኖ ሲያከፋፍሉ የሚጠቀሙበት የችግረኛ መመዘኛ ግራ የሚያጋባ ነበር፡፡ ቦብ ማርሊ የተባለው ዝነኛ አቀንቃኝ “ጌታየ ሆይ ከወዳጆቼ ጠብቀኝ፤ ጠላቶቼንስ አሳምሬ አውቃቸዋለሁ” ብሎ ያዜመው ይህን የትግራዩን ጉደኛ ክስተት የሚገልጽ ነው፡፡

የትግራይ ህዝብ ቪላ ይኑረው ደሳሳ የሳር ጎጆ፤ ሙሉ የቤት እቃ ይኑረው ጥቂት ቅራቅምቦ፤ ሁሉም ተርቧል፡፡ ሃብት የነበራቸው ሰዎች ተርበው ሰው እንዳያያቸው ለልመና በሌሊት እየወጡ መንገድ ዳር ተቀምጠው ቤተከርስትያን የሚሄድ የሚመለሰውን ለኩርማን እንጀራ የአስር ጻድቃንና መላእክት ስም ይጠራሉ፡፡ በመከራ ጊዜ የሰው ልጅ ሊያዝናናው የሚችል ቀልድ ቢኖረው በራሱ

ላይ መቀለድ ነው፡፡ ልመና “ልማት” የሚል ስም የወጣለት መሆኑ ሲሰማ መቸም ፈገግ የሚል አይጠፋም፡፡ ወዶ አይስቁ! እርዳታ የሚያከፋፍሉት ሰዎች ቤት ለቤት ይዞራሉ፤ ወደ ውስጥ እየገቡም ያያሉ፡፡ ፍሪጅና ቴለቪዠን ካዩ ባለቤቶቹ ለእርዳታ አይበቁም፤ እቃቸውን ሸጠው ምግብ እንዲገዙ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲህ እያደረጉ የተረጂውን ቁጥር በማቀናነስ በህዝብ ቁጥር የመጣውን እርዳታ ያንንም ያንንም ከልክለው ለራሳቸው ይወስዳሉ ለሚፈልጉትም ይሰጣሉ፡፡

### *“የገበያ ግርግር ለቀጣፊ ያመቻል”*

ጥር 25/2016 የባይቶና ፓርቲ መሪ “ባለስልጣናት ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ በከተሞች የመሬት ወረራ ላይ ተሰማርተዋል፤ መአድናትንም በህገወጥ መንገድ በማውጣት ላይ ይገኛሉ” የሚል ክስ አቅርቧል፡፡ መቶና ሁለት መቶ ሺ እየተከፈለ የተወረረው መሬት ህገወጥ ካርታ እያሰሩለት እንደሆነም ተገልጿል፡፡ አብይ አህመድ መቐለን “በሻሻ” አድርጓት ቢሆን የትግራይ አመራሮችና ነጋዴዎች ደግሞ በተራቸው ከተማዋን “ካራካስ” እያደረጓት ነው፡፡ ካራካስ የቬንዙዌላ ርእሰ ከተማ ስትሆን በሰፈነባት ህገውጥነት ከአለም አንደኛ ናት፡፡ በቅርቡ በተለቀቀ ሪፖርት በመቐለ 5000 ሰው መሬት ወሯል፡፡ ሊዝም እየተካሄደ ነው፤ ጊዜያዊ መንግስት ሆኖ ይህን ማከናወን ይችል እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ሌላው ህዝብ መሬት ማግኘት አልቻለም፡፡

በ“መኸተ” አመታት ነዳጅ፤ ብረታ ብረት፤ የእርዳታ እህል እየዘረፉ፤ ከተቀባዩ ጋር እኩል የሚካፈሉት ገንዘብ ከውጭ እያስገቡ፤ አራጣ እያበደሩ፤ ንብረት በዝቅተኛ ዋጋ ከተቸገሩ ሰዎች እየገዙ፤ ወደ ኤሪትርያም በከፍተኛ ትርፍ ንግድ እያጧጧፉ፤ መጠጥና ሌሎች ነገሮች በስውር እያስገቡ የከበሩ ሰዎች ያገኙትን ህገወጥ (ቆሻሻ) ገንዘብ ለማጠብ (መኒ ላውንደሪንግ) መሬትን በተጋነነ የሊዝ ጨረታ እየገዙ ነው፡፡ “በዚህ አይነት አካሄድ መላ ትግራይ በአምስት ሰው እጅ ልትወድቅ ትችላለች” አለ የሽግግሩ መንግስት ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ፡፡ ችግሩ ከአቅሙ በላይ ሆኖ የተሰማው ይመስላል፡፡ ህዝባዊ ዝቅጠት!

> “ጦርነት ማጭበርበር ነው፤ ትርፉ በዶላር ኪሳራው ግን በሰው ህይወት የሆነ አብዛኛዎቹ ዋጋ የከፈሉበት ጥቂቶች ብቻ የሚጠቀሙበት፤ በጦርነት ጥቂት ሰዎች ብቻ ከፍተኛ ሃብት ያካብታሉ” ሜጀር ጄኔራል ስሜድሊ በትለር

# የደራሲው ቁዘማ፦ "የሁለት ተጋሩ ወግ"

የሁለት ተጋሩ ወግ፤
ስለ ልቅሶ ስለ ሰርግ፡፡

አሉ ሁለት አይነት ተጋሩ፤
ሰለጉዳያቸው በጋራ ማይመክሩ፡፡

በጦርነት አይለያዩ፤
በሰላሙ አይተያዩ፡፡

አንዱ በረሃብ ቸነፈር ሲሞት፤
ሌላው ይመርጣል ሻኛ ከዳቢት፤
ዊስኪ ሲጠጣ ያነጋል ሌሊት፡፡

አንዱ የመኖር ባለ መብት፤
ሌላው ተፈጥሯል ለመስዋእት፡፡

አንዱ በችጋር ደቆ፤
ሌላው በወርቅና ጨርቅ ደምቆ፡፡

አንዱ ከዚህ ወረዳ ነው የበላይ፤
ሌላው ከዛ ሰፈር ነው ተበዳይ፡፡

አንዱ ለህይወቱ በጋርዶች ታጅቦ፤
ሌላው በህግ አገር በሃንጎች ተከቦ፡፡

አንዱ ባራጣ ብር መሬት ሲያግበሰብስ፤
ሌላው በሸራ ቤት ዝናብ ሲበሰብስ፡፡

አንዱ በቪኤይት ፕራዶ፤
ሌላው በእግሩ ነው በባዶ፤
ትግራዋይ ነኝ ይላል ሁሉም በተለምዶ፡፡



ያለፉትን ጊዜያት ፊት ለፊት አምጥቶ፤ ከፉን ቢሆን በጎ ትዝታን ተክቶ፤
አፍ እንኳ ባይኖረው ይናገራል ፎቶ!



## "ህዝቡን እንደዋዛ፤ አደረጉት ፈዛዛ ደንዛዛ"

በልጆችህ ለቅሶ አይንህ እየጠፋ፤
ሞትህ ያልጎዳቸው ያገር ቱሪናፋ
"በጦር ሜዳ አይገኝ ከቀለቡ አይጠፋ"፡፡

ሳይገድሉ ጎፈሬ የድል ጋማ ለብሰው፤
በዩቱብ በቲክቶክ ኮርተው ተኮፍሰው፤
ገድል ሲዘክሩ ያንተን ታሪክ ወርሰው፤
ስምህ ለራሳቸው ዝናህ ለልጃቸው፡፡

ከትግሉ በኋላ ከዛ መስዋእትነት፤
አንተን ገሸሽ አርገው ሲነከሩ በሀብት፤
እንደ ዳዋ አስመቱህ አይጡ በበላበት፡፡
በድነህ በቁምህ እያለህ የለህም፤
እንኳን ፩ሚሊዮን አንድም አይደለህም፡፡

ለአንዱ ሞት ጉዳት መቶ ማስታወሻ፤
ለሺዎቹ እልቂት አንድ ሃውልት ማስረሻ
በሞትም አድልዎ በሞትም ልዩነት፤
ሰማእት በጌትነት ሰማእት በሎሌነት፡፡

የመሳፍንትን ዛር ስታቋድስ ኖረህ፤
ሚስትና ልጆችህ ከወና ቤት ጥለህ፤
ዛሬም እንደ ትናንት ለጌቶቹ አድረህ፤
ኑሮን ለእድል ትተህ ታሸረግዳለህ፡፡

ትግል ዴሞክራሲ ትግል ለአርነት፤
አንዴ በመደብ ስም አንዴ ብሄርነት፤
የገዢዎችህ ለውጥ አይነት የባርነት፡፡

ግማሽ ምእተ አመት ሞትና መከራ፤
ዴሞክራሲ ፋና ከሩቅ የሚያበራ፤
ሲሄዱበት ሲርቅ ሲይዙት አይሰራ፡፡

ልብስህ ተቦጫጭቆ አቧራው ስፍሮብህ፤
እህል የግዜር ውሃ ህልም እንደሆነብህ፡፡
እነሱ ግን አምረው ለብሰው ተኳኩለው፤
የስልጣን ውርርድ ካንተ አስቀድመው፤
መፈክር ደርድረው ባንዴራ አውለብለበው፤
በስምህ አማትበው በስምህ ዘምረው፡፡

የራስህ ወገኖች ካላዘኑልህ፤
ጠላትህ ነው ከቶ የሚደርሰልህ?
ምን ቸገረው ብታልቅ ቢጠፋ ድራሽህ፤
ሁለት ያጣህ ጎመን ቢፈራርስ ቤትህ፡፡

ትናንት እንደ ድሮ ካራት ኪሎ ጋራ፤
ህዝብን በእጅ ይዞ ቀጠለ አተካራ፡፡
ዛሬ መተቃቀፍ መፋቀር መላመድ፤
ነገ ደግሞ በመድፍ በታንክ መወጋገድ፡፡

ለያዘህ አባዜ መፍትሄ ስራዩ፤
ከወዴት ይገኛል ይሆን ከበላዩ?
እሱማ ትቶሃል አርቆ ጥሎሃል፤
ለራስ አልሆን ብለህ ጠልቶሃል ረስቶሃል፡፡
በርስ በርስ ሽኩቻ ክፋት ምቀኝነት፤
ስድብ መዘላለፍ ስርቆት መቀማማት፤
አፍቅሮ ንዋዩ ሱስም ሴሰኝነት፡፡
እንዴት አይረሳህም እንዴትስ አይርቅም፤
ለራሱ ያልሆነ ለፈጣሪ አይበጅም፡፡

የትግራይ ህዝብ ለምን ለምን ሞተ!
ለጋ ወጣት ለምን ለምን ሞተ!
**ዴሞክራሲ በቅሎ በስሎ ካላሸተ!**



## ዋቢ ጽሁፎች

Annys, S., Vanden Bempt, T., Negash, E., De Sloover, L., and Nyssen, J., 2021. Tigray: Atlas of the humanitarian situation.

Hagos G/Yohannes 2003 Political History of Tigray: Rivalry for Power (1910-1935)

Munro-Hay, S. 1991 Axum: An African Civilizations of Late Antiquity. Edinburgh: Edinburgh University Press.

Plaut M. and S. Vaughan 2023 Understanding Ethiopia's Tigray War

Prunier, Gérard 2010 "The 1943 Woyane Revolt: A Modern Reassessment". The Journal of the Middle East and Africa. **1** (2): 187–195.

Seymour Lee J.M 2014 Why Factions Switch Sides in Civil Wars: Rivalry, Patronage, and Realignment in Sudan. International Security. Vol. 39, No. 2, pp. 92-131.

Teshome Sirany Badechy and Esubalew Tadele 2022 Economics of Sesame and Its Use Dynamics in Ethiopia.The Scientific World Journal (3):1-13.

Ullendorff, E. 1973. The Ethiopians. London: Oxford University Press. pp. 31, 35–37.



"ጦርነት እርስ በርሳቸው የማይተዋወቁ ሰዎች እርስ በርስ ለሚተዋወቁ ግን እርስ በርስ ለማይጨፋጨፉ ሰዎች ጥቅም ሲሉ የሚጨፋጨፉበት ነው"

ፖል ቫለሪ (ፈረንሳዊ ገጣሚ)

ዮሃንስ አበራ
ፒኤችዲ፤ ተባባሪ ፕሮፌሰር




"ሁሌ ጥቁር መልበስ አያምርብንም፤ ይበቃል ጥቁር መልበስ! ለምንድነው ለመሞት ብቻ ወደፊት የምንለው? አሁን ወጣቶች አይሂዱ፤ አሁን ሽማግሌዎች ይሂዱ፤ ድንጋይ ያንሱና ሳር ይበጥሱ፤ እናታቸው ላይ ይዘው—በሽምግልና ይሻላል፤ አፈሙዙ ይበቃል!"


ዲሽታ ጊና (ኢትዮጵያዊ የሰላም ታጋይ

CamScanner